# አሮናዊ የክህነት ሥልጣን

## መመሪያ 1

# አሮናዊ የክህነት ሥልጣን
መመሪያ 1

በኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሶልት ሌክ ሲቲ ታተመ

© 2001 by Intellectual Reserve, Inc
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
በዩ. ኤስ ኤ ታተመ
እንግሊዘኛው የጸደቀበት፥ 5/94
ትርጉሙ የጸደቀበት፥ 5/94
የ *Aaronic Priesthood 1* ትርጉም

# ማውጫ


| የትምህርቱ ቁጥር እና አርዕስት | | ገጽ |
|---|---|---|
| | ለአማካሪው | v |
| 1 | የክህነት ስልጣን | 1 |
| 2 | የዲያቆን ጥሪ | 4 |
| 3 | ቅዱስ ቁርባንን ማገልገል | 7 |
| 4 | የጾም በኩራትን መሰብሰብ | 10 |
| 5 | በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን | 14 |
| 6 | መንፈስ ቅዱስ | 17 |
| 7 | “ታላቅ የልብ ለውጥ” | 21 |
| 8 | “አባትህን አክብር” | 24 |
| 9 | እናቶችን እና መለኮታዊ ሚናቸውን ማክበር | 27 |
| 10 | የቤተሰብ አንድነት | 30 |
| 11 | “እኔ እንደወደድኳችሁ፣ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ” | 34 |
| 12 | ህያው ነቢይን መከተል | 38 |
| 13 | እያንዳንዱ አባል ሚሲዮናዊ ነው | 40 |
| 14 | ሌሎችን ማገልገል | 43 |
| 15 | በክህነት ስልጣን ውስጥ አንድነት እና ወንድማማችነት | 47 |
| 16 | ፍጹም ፍቅር | 50 |
| 17 | የግል ማኅደር | 54 |
| 18 | የጥበብ ቃል | 59 |
| 19 | ፈተናዎችን መቋቋም | 63 |
| 20 | የነፃ ምርጫ ትክክለኛ ጥቀም | 66 |
| 21 | ንጹህ አስተሳሰብ፣ ግልጽ ቋንቋ | 70 |
| 22 | ቃል ኪዳኖች ድርጊቶቻችንን ይመራሉ | 73 |
| 23 | ለአመራር መጸለይ | 76 |
| 24 | ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ ንስኃ | 79 |
| 25 | ምህረት | 83 |
| 26 | በሰንበት ቀን መልካምን አድርግ | 87 |
| 27 | አክብሮት | 92 |
| 28 | ሴቶችን ማክበር | 96 |
| 29 | ዘለዓለማዊ ቤተሰብ | 99 |
| 30 | የደህንነት እቅድ | 102 |
| 31 | በፃም እና በጸሎት ተጉ | 106 |
| 32 | አስራት | 109 |
| 33 | የቅዱስ መጽሐፍ ጥናት | 112 |

| | | |
|---|---|---|
| 34 | ታዛዥነት | 116 |
| 35 | ቅዱስ ቁርባን | 120 |
| 36 | ምስክርነት | 124 |
| 37 | የአሮን ክህነት | 128 |
| 38 | የአሮናዊ ክህነት ያዥ ጥሪን ማጉላት | 131 |
| 39 | ሚሲዮናዊ ስራ በአርአያነት | 133 |
| 40 | የጌታ ቤት | 137 |
| 41 | የፈቃደ ሥጋ ንጽህና | 142 |
| 42 | ታማኝነት | 145 |
| 43 | ቅዱሳን መጻሕፍትን መመርመሪያ መሳሪያዎች | 149 |
| 44 | የተሻለ የቤት አስተማሪ መሆን | 155 |
| 45 | የተቀደሰ የመዋለድ ኃይል | 159 |
| 46 | ውሳኔ ማድረግ | 163 |
| 47 | መለየት እና መስዋዕትነት | 167 |
| 48 | የማጥመቅ ኃይል | 170 |
| 49 | ጊዜን በብልሃት መጠቀም | 173 |
| 50 | ለቡድኑ አማካሪ፥<br>ከአጠቃላይ ጉባኤ ንግግሮች ላይ ትምህርቶችን ማቀናበር | 177 |
| | ሥዕሎች | |

# ለአማካሪው

እነዚህ ትምህርቶች የታቀዱት ወጣት ወንዶች ስለ ወንጌል እንዲማሩ እና አሮናዊ የክህነት ሥልጣን ስብሰባዎች አስደሳች እና ትርጉም ያላቸው እንዲሆኑላቸው ለመርዳት ነው፡፡ ይህን መመሪያ እያንዳንዱን የቄሶችን፣ የአስተማሪዎች፣ እና የዲያቆኖች ቡድን፣ ወይም የሶስቱንም ክፍል ቡድኖች በሙሉ ለማስተማር መጠቀም ትችላለህ፡፡ እያንዳንዱን ትምህርት በጸሎት በማዘጋጀት ወጣቶችን በአሮናዊ የክህነት ስልጣን ውስጥ ጥሪያቸውን እንዴት ማጉላት እና በእውነት የእግዚአብሔር ልጆች መሆን እንዴት እንደሚችሉ እንዲማሩ መርዳት ትችላለህ (ት እና ቃ 84፥26–42 እና ዮሐንስ 1፥12–13 ተመልከት)፡፡

ይህ መመሪያ በዓመት ውስጥ አስተምረህ መጨረስ ከምትችለው በላይ—ሃምሳ ትምህርቶችን ይይዛል፡፡ የምታስተምራቸውን የወጣት ወንዶች ፍላጎት የሚያሟሉ ትምህርቶችን በጸሎት ምረጥ፡፡ አንዳንድ ትምህርቶች ለቄሶች ተስማሚ ሊሆኑ ይችላሉ፣ እንዲሁም ሌሎች ለዲያቆኖች እና ለአስተማሪዎች ተስማሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**ለተሳካ ትምህርት ቁልፎች**

በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉትን ትምህርቶች ጠቃሚ ለማድረግ፣ የሚከተሉትን ለተሳካ ትምክህርት ቁልፎች ተጠቀም፣

1. *በሐዋርያቶቻችን ላይ ትኩረት አድርግ፡፡* ወጣት ወንዶች የክርስቶስ ደቀመዛሙርት እንዲሆኑ እያስተማርክ ነው፡፡ የክህነት ሥልጣንን ተግባርን ወይም መርህን ብቻ ለእነሱ ማስተማር በቂ አይደለም፣ እርሱን ከማመን እና ከመውደድ ባሻገር የእርሱ ደቀመዛሙርት እንደመሆናቸው መጠን ይህ ጌታ እንዲፈጽሙ የሚፈልገው ነገር መሆኑን ማወቅ አለባቸው፡፡
2. *መንፈስን ፈልግ፡፡* እነዚህን ትምህርቶች በምታዘጋጅበት እና በምታቀርብበት ጊዜ የሰማይ አባትን እርዳታ ጠይቅ፡፡ "የእምነት ጸሎት መንፈስ ይሰጥሀል፣ እናም መንፈስን ካልተቀበልክ ማስተማር አትችልም" በማለት ጌታ ቃል ገብቷል (ት እና ቃ 42፥14)፡፡ ስለ ክርስቶስ በምትመሰክርበት፣ ተከታይነትን በምታስተምርበት እና እንደ እርሱ ደቀመዝሙርነትህ ከእራስህ ልምድ ስታስተምር እና ስትመሰክር መንፈስህ ይጠነክራል፡፡
3. *የቡድን ፕሬዚዳንትን አሳትፍ፡፡* የአሮናዊ የክህነት ሥልጣን ቡድን ፕሬዚዳንት የቡድኑን አባላት ምድብ ሥራዎቻቸውን ያስተምራል (ት እና ቃ 107፥85–87 ተመልከት)፡፡ የቡድን ፕሬዚዳንት፣ ከአንተ እርዳታ ጋር፣ የትኛው ትምህርት መሰጠት እና በምን ቀደም ተከተል መሰጠት እንዳለበት በመወሰን መርዳት አለበት፡፡ የቡድን ጸሐፊው የትምህርቶችን መደጋገም ለማስወገድ በጊዜ ሠንጠረዥ ላይ መመዝገብ አለበት፡፡
4. *ወጣት ወንዶችን ውደዳቸው፡፡* ለምታስተምረው ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ ንጹህ ፍቅር አጎልብት፡፡ በምታደርገው ነገር ሁሉ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ፍቅርን አሳይ፡፡ የእያንዳንዱን የቡድን አባል፣ ፍላጎቱን እና ችግሮቹን እወቅ፡፡
5. *ዝግጁ ሁን፡፡* አንድን ትምህርት ከማቅረብህ በፊት ቢያንስ ሁለት ወይም ሶስት ሳምንት አስቀድመህ አንብብ፡፡ እነዚህን ትምህርቶች ለማዘጋጀት ከምታቀርብበት ከአንድ ቀን በፊት ማለትም እስከ ቀዳሚ ከዘገየህ ትምህርትህ ጥራቱን ይቀንሳል። በእያንዳንዱ ትምህርት መጀመሪያ "ዝግጅት"ን በጥሩ ሁኔታ አስተውል፡፡

   አመች በሆነበት ወቀት፣ *ለወጣቶች ጥንካሬ* ትምህርቶችህን ለማሳደግ በራሪ ወረቀትን ተጠቀም፡፡ ወጣት ወንዶች በበራሪው ወረቀት ላይ ከተጻፉት ደንቦች ጋር እንዲተዋወቁ እርዳቸው፡፡ ዘወትር እንዲያነቡት እና በውስጡ የተዘረዘሩትን ደንቦች እንዲጠብቁ ወጣት ወንዶችን አበረታታቸው፡፡

   ትምህርቱን በምታዘጋጅበት ጊዜ እንድትረዳቸው እና በጥሩ ሁኔታ ለማቀረብ እንድትችል ታሪኮችን በውስጡ ስታገኝ ደጋግመህ አንብብላቸው፡፡

**ተጨማሪ አስተያየቶች**

የሚከተሉት አስተያየቶች እያንዳንዱን ትምህርት ማራኪ እና ጠቃሚ ለማድረግ ይረዳሉ፡፡

1. *ቅዱሳን መጻሕፍትን ተጠቀም፡፡* ወጣት ወንዶች ቅዱሳን መጻሕፍቶቻቸውን በየሳምንቱ ለክህነት ስብሰባ ይዘው እንዲመጡ አበረታታቸው፡፡ በእያንዳንዱ ትምህርት ክፍል ጊዜ እንዲጠቀሙበት ምልክት ማድረጊያውን እርሳስ አቀርብላቸው፡፡
2. *የቡድን ውይይትን አበረታታ፡፡* ወጣት ወንዶች ነፃ ሆነው መልስ እንዲሰጡ እና ጥያቄ እንዲጠይቁ ጋብዛቸው፡፡ ወደፊትም ተሳትፎውን እንዲገፋበት የእያንዳንዱን ወጣት ወንድ አስተያየት ተገንዘብ፡፡

3. *ትምህርቶቹን ከአንተ አኳኋን ጋር አቀናጅ፡፡* ወጣት ወንዶችን የሚያስደስት የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን ተጠቀም፡፡ ትምህርቶችን ለወጣት ወንዶች ተስማሚ ለማድረግ ይረዳህ ዘንድ በወጣት ወንዶች ህይወት ውስጥ ወይንም በሚተዋወቋቸው ሰዎች ህይወት ውስጥ ክስተቶችን እና ልምዶችን ተመልከት፡፡ አንዳንዴ የባህልህን ሁኔታዎች ለማሟላት ታሪኮችን እና ምሳሌዎችን መጠቀም ትችላለህ፡፡

   አንዳንድ ትምህርቶች በአንድ ትምህርት ክፍለ-ጊዜ ውስጥ ለማስተማር ከሚገባው በላይ ብዙ ነገሮች እንደሚይዙ ታያለህ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ወጣት ወንዶች በጣም የሚፈልጓቸን ነገሮች ምረጥ ወይም ትምህርቱን ለማቅረብ ከአንድ ክፍለ-ጊዜ በላይ ተጠቀም፡፡

4. *በመመሪያው ውስጥ የተጠቃለሉትን ሥዕሎች ተጠቀም፡፡* በዚህ መመሪያ ሽፋን ላይ ያሉትን ሥዕሎች በጥሩ ሁኔታ ጠብቅ፡፡ አትቀደዳቸው፡፡ ከተገቢ ትምህርቶች ጋር ተጠቀማቸው፡፡ የጸሎት ቤት ቤተ-መጻሕፍት የቅዱሳን መጻሕፍት ታሪኮችን ለማሳደግ የምትጠቀምባቸውን ሥዕሎች ሊይዝ ይችላል፡፡ በጸሎት ቤት ቤተ-መጻሕፍት የሚገኙ የመመሪያው ሥዕሎች በተራ ቁጥራቸው ተዘርዝረዋል፡፡ ለእርዳታ የጸሎት ቤቱን የቤተ-መጻሕፍት ሠራተኞችህን አነጋገር፡፡

5. *ጠመኔ እና ጥቁር ሰሌዳን ተጠቀም፡፡* ከእያንዳንዱ ትምህርት ክፍለ-ጊዜ በፊት ትምህርትህን ለማጠናከር ጥቁር ሰሌዳን በተሻለ እንዴት መጠቀም እንደምትችል አጥና፡፡ ጥቁር ሰሌዳን ስትጠቀም ከረጅም ንግግሮች ውስጥ ቁልፍ ቃላቶችን ብቻ ጻፍ፡፡

6. *መልመጃዎችን ስጥ እናም ተከታተላቸው፡፡* እያንዳንዱን ትምህርት በተወሰነ መልመጃ አጠቃልል፡፡ ወጣት ወንዶችን ተከታተላቸው እናም መልመጃውን እንዲሰሩ አበረታታቸው። መልመጃውን በመስራት ስኬታማነታቸውን እንዲያስተዋውቁ ጋብዛቸው፡፡

7. *በአቅራቢያህ የሚገኙትን የቤተክርስቲያን መጽሔቶች ተጠቀም፡፡* ኒው ኤራ፣ ኢንዛይን፣ አለም አቀፍ መጽሔቶች በዚህ መመሪያ ውስጥ የተወሰኑ ትምህርቶችን ለማጠናከር ብዙ ታዋቂ ታሪኮችን እና አንቀጾችን ይይዛሉ፡፡ የታህሳስ እና የግንቦት እትሞች፣ በጠቅላላ ጉባኤ ላይ በቤተክርስቲያኑ የበላይ ባለሥልጣናት የተሰጡትን ንግግሮች ስለሚይዙ በተለይ ጠቃሚዎች ናቸው፡፡

8. *የሚታደሉ ጽሑፎችን ተጠቀም፡፡* ወጣት ወንዶች እንዲማሩ እና የወንጌል መሠረተ ሐሳቦችን ለማስታወስ እንዲረዳቸው በአንዳንድ ትምህርቶች መጨረሻ ላይ በእጅ የሚታደሉ ጽሑፎች ተመልክተዋል፡፡ ተገቢ በሆነ ጊዜ ከእያንዳንዱ ትምህርት ጋር ለመጠቀም የጽሑፎቹን ቅጂ አዘጋጅላቸው።

---

**የአመራር ጉብኝት ለጀማሪ ክፍል**

የዲያቆናች ቡድን አመራር ሌሎች ወጣት ወንዶች የክህነት ስልጣንን እንዲቀበሉ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት፡፡ እነዚህ ወጣት ልጆች ለሚከታተሉት የጀማሪ ክፍል አጠር ያሉ ትምህርቶችን እንዲያቀርቡ አመራሩን አበረታታ፡፡ እነዚህ ትምህርቶች ሶስት ዋና ዓላማዎችን ሊይዙ ይገባል፡

1. ለዲያቆን ቡድን አመራር ወጣት ወንዶች ልጆችን የማስተማር ልምድን መስጠት፡፡
2. የክህነት ስልጣንን ለመቀበል በዝግጅት ላይ ያሉትን ወጣት ወንዶች የአሮናዊ የክህነት ስልጣን ሥፍራዎችን እና በረከቶችን እንዲያውቁ መርዳት። የቡድኑ አመራር በአገልግሎት እና መልካም ምሳሌ በመሆን አስፈላጊነት ላይ እና በዚህ አማካኝነት የሚመጣውን ደስታ እና እርካታ አበክሮ መግለጽ አለበት፡፡
3. ወጣት ወንዶች በቡድን ውስጥ ተቀባይነት እንዳላቸው እንዲያውቁ መርዳት፡፡

አመራሩ ትምህርቶቹን ከመስጠቱ በፊት ትምህርቶቹን ለማዘጋጀት አንተ እና የዲያቆናች ቡድን አመራር ጀማሪዎችን መምህር ማነጋገር አለባችሁ፡፡ የጀማሪዎች ክፍል ጉብኝት ከጀማሪዎች ክፍል ፕሬዚዳንት ጋር የተቀናጀ መሆን አለበት፡፡ አመራሩ ከዚህ በታች ከተጠቀሱት ከሁለቱ ጋር የሚመሳሰል ትምህርት ሊሰጥ ይችላል፡፡

*"ዲያቆን ሌሎችን ያገለግላል"*

የዲያቆን ቡድን አመራር ዲያቆናች የክህነት ስልጣን ተግባራቸውን በማከናወን እና በዚህ አገልግሎት አማካኝነት የሚመጣውን ደስታ እና እርካታ በማካፈል ሌሎችን እንዴት እንደሚያገለግሉ የሚያስረዳውን የሃያ ደቂቃ ትምህርት ማዘጋጀት ይችላሉ፡፡ የቡድን አመራር ቅዱስ ቁርባንን ማስተላለፍ እና የጾም በኩራትን ማሰባሰብ የዋርድ አባላትን ህይወት እንዴት እንደሚባርክ ማስረዳት አለበት፣ እናም ደግሞ በተወሰኑት የአገልግሎት ፕሮጀክቶች ላይ ሪፖርት ማቅረብ ይችላሉ።

*"ምሳሌ ሁን"*

የዲያቆን ቡድን አመራሮች ኢየሱስ ክርስቶስን የሚወክለውን የክህነት ስልጣን ያዥ እንደመሆናቸው መጠን መልካም ምሳሌ የመሆንን አስፈላጊነት የሚጠቀስ የሃያ ደቂቃ ትምህርት መስጠት አለባቸው፡፡ በተለይ ቅዱስ ቁርባንን በሚያስተላልፉበት እና የጾም በኩራትን በሚያሰባስቡበት ጊዜ በአለባበስ እና በአነጋገር መልካም ምሳሌን የማስቀመጥ አስፈላጊነትን መግለፅ አለባቸው፡፡

# የክህነት ስልጣን

# 1

| | |
|---|---|
| **አላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ወንድ በእግዚአብሔር ስም ለማገልገል እንዲችል የተሰጠውን ታላቅ ኃይል እና እድል ይረዳል። |
| **ዝግጅት** | 1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፤<br>ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቅዱሳን መጻሕፍት።<br>ለ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ ወረቀት እና እርሳስ።<br>ሐ. ጥቀሶችን ምልክት ማድረጊያ እርሳስ።<br>መ. የአስፒሪን እንክብል ጠርሙስ ወይንም መያዣ።<br>2. ከታች የተጠቀሰውን በፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል የተዘጋጀውን የክህነት ስልጣን ትርጉም ፖስተር ማዘጋጀት ትችላለህ። |

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**የክህነት ኃይል እና ስልጣን**

ጥቁር ሰሌዳ እና የጽሑፍ ተሳትፎ

የሚከተለውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ፡፡ *የክህነት ስልጣን* . . .

ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ ወረቀት እና እርሳስ ስጥ። ስለ ክህነት ስልጣን አጠር ያለ ገለጻ በወረቀታቸው ላይ እንዲጽፉ ወጣት ወንዶችን አዘዛቸው። ሁሉም ካጠናቀቁ በኋላ ወረቀቶቹን ሰብስብ እናም የቡድኑ ፕሬዚዳንት እያንዳንዱን ከፍ ባለ ድምፅ እንዲያነብ አድርግ። ከዚያም በኋላ የክህነት ስልጣን ማለት በእግዚአብሔር ስም የማገልገል ኃይል ነው ብለው የሚያመለክቱትን አባባሎች አጠቃላቸው።

በቡድን ውስጥ ይህን ኃይል ያለውን እያንዳንዱን ሰው እንዲቆም ጠይቅ። የሰማይ አባት ለእያንዳንዳቸው ኃይሉን ማካፈሉን እንዲገነዘቡት ወጣት ወንዶችን እርዳቸው።

ጥቅስ እና ፖስተር

በፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል የተነገረውን የሚከተለውን ጽሑፍ አንብብ፡ “የክህነት ስልጣን በምድር ላይ በማናቸውም ነገሮች የሰዎችን ደህንነት በተመለከተ ለሰው የተሰጠ የእግዚአብሔር ኃይል እና ስልጣን ነው። ጌታ በሰዎች አማካኝነት ነፍሳትን ለማዳን የሚሰራበት መንገድ ነው። ያለዚህ የክህነት ስልጣን ሰዎች ይጠፋሉ” (“The Example of Abraham,” *Ensign*, ሰኔ 1975,ገፅ 3)።

ውይይት

• መወከል ማለት ምን ማለት ነው? (የአንዱን ስልጣን ለሌላ መስጠት ማለት ነው።)

ከላይ ከተጠቀሰው ጥያቄ ጋር እንደገና አጣቅስ።

• ለአገልጋዮች የክህነት ስልጣንን ሲሰጣቸው ጌታ የሚወክልላቸው ሁለት ነገሮች ምንድናቸው? (ለእርሱ የማገልገልን ኃይል እና ስልጣን ናቸው።)

ታሪክ እና ውይይት

የሚከተለውን ታሪክ ተናገር፤ ስህተቱን እንዲለዩ ለማድረግ ወጣት ወንዶች እንዲሰሙት አድርግ።

ሮናልድ ጆንስ በከተማችን ከሚገኙት ከዋርዱ ጳጳሳት አንዱ ነው። በተጨማሪም አጐቴ ነው፣ በህይወት ያለ ብቸኛ የአባቴ ወንድም። እርሱ እና አባቴ በጣም ይቀራረባሉ። ባለፈው እሁድ አጐት ሮን በመኪና አደጋ በፅኑ ቆስሎ ነበር። የቤተክርስቲያን ሥራዎቹን ለማከናወን እንደማይችል ያውቃል፤ ነገር ግን አባቴ፤ የዋርዳችን ቄስ፤ ሁሉንም ነገር እንደሚያከናውን አበሰረለት። እሁድ ጠዋት፣ አባቴ በአጎቴ ዋርድ ተገኝቶ ስብሰባው በጊዜ እንዲጀምር ጠራ።

• በዚህ ታሪክ ውስጥ ያለው ስህተት ምንድን ነው?

አንድ ሰው ሰውየው በእራሱ እንደ ጳጳስ ሆኖ ለማገልገል መወሰን የለበትም ብለው እስኪገልጽ ድረስ ወጣት ወንዶች ምላሽ እንዲሰጡ አድርጋቸው። የጳጳሱ ወንድም ምንም እንኳ የክህነት ስልጣን ቢኖረውም ቁልፎች እንዳልተሰጡት
እና እንዲሁም በወንድሙ ዋርድ የጳጳሱን ሥራ እንዲያከናውን እንዳልተሾመ አስረዳ። እነዚህ ቁልፎች ሊኖሩት ይገባዋል እናም ይህን ስልጣን ለማግኘት ሊሾም ይገባዋል።

• ጳጳስ በማይኖርበት ጊዜ ኃላፊነትን መውሰድ የሚችለው ማነው? (የእርሱ አንደኛ አማካሪ ነው።)

ቅዱስ መጽሐፍ፤ ጥቅስ፤ እና ውይይት

• ይህን ኃይል እና ስልጣን አንድ ሰው እንዴት ይቀበላል?

አንድ ወጣት ዕብራውያን 5፡4 እንዲያነብ እና ሌሎች ከመጽሐፍ ቅዱሳቸው እንዲከታተሉት አድርግ። አንድ ሰው ከእግዚአብሔር መጠራት እንዳለበት እና እጅን በመጫን መሾም እንደአለበት በበለጠ አስረዳ። ወጣት ወንዶች ይህን ጥቅስ ምልክት እንዲያደርጉበት ንገራቸው።

በኦርሰን ፕራት የተሰጠውን የሚከተለውን ንግግር ወጣቱ እንዲያነብ አድርግ፣

“የእግዚአብሔር የክህነት ስልጣን ታላቅ ኃይል፣ የጻኑ እና የከበሩ የዓለም ነዋሪዎችን በሙሉ የሚገዛ ህጋዊ ስልጣን ነው። በውስጡ ዓለማትን በሙሉ የመፍጠር ኃይል አለው. . . .። ሚኒራሎችን፣ አትክልቶችን እና እንስሳትን በብዛታቸው [ብዙ] በተለያየ መልኩ የፈጠረ ኃይል ነው” (Orson Pratt, *Masterful Discourses and Writings of Orson Pratt*, compiled በ N. B. Lundwall [ሶልት ሌክ ሲቲ Bookcraft’ 1962], ገጽ 316)።

• ኦርሶን ፕራት የክህነት ስልጣንን እና ኃይል እንዴት ገለጸው? (እግዚአብሔር ሁሉም ነገሮች የሚፈጥርበት እና የሚገዛበት ኃይል አለው።)

ጥቁር ሰሌዳ፣ ቅዱስ መጽሐፍ፣ እና ውይይት

ወጣት ወንዶች የጻፉትን ገለጻ የሚቀይሩበትን ወይም በገለጻው ላይ የሚጨምሩበትን መንገዶች እንዲወያዩ አድርግ።

ይህን በመጻፍ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ዓረፍተ ነገሩን አሟላ፣ *እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ለሰው የተሰጠ ኃይል እና ስልጣን። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር የሚፈጥርበት እና የሚገዛበት ኃይል።*

ወጣት ወንዶች በክህነት ስልጣን እና በክህነት ኃይል መካከል ያለውን ልዩነት እንዲወያዩበት አድርግ። እጅን በመጫን ስልጣኑን መቀበል እንደሚችሉ ነገር ግን ኃይሉ ከጽድቅ አኗኗር እንደሚመጣ አንዲረዱ እርዳቸው።

አንድ ወጣት ትምህርት እና ቃል ኪዳን 121፡36 እንዲያነብ እና ሌሎች እንዲከተሉት አድርግ።

• የክህነት ስልጣንን ኃይል እንዴት እናገኛለን? (በጽድቅ አኗኗር።)

ጥቀስ እና ውይይት

አንድ ወጣት ስለ እነዚህ ሁለቱ ቃሎችን የጻጳስ ኤች ቡርኬ ፒተርሰንን ገለጻ እንዲያነብ አድርግ፣

“በክህነት ስልጣን እና በክህነት ኃይል መካከል ልዩነት አለ. . . .። ሁላችንም የክህነት ስልጣንን የያዝን ለጌታ የማገልገል ስልጣን አለን፣ ነገር ግን የስልጣናችን ውጤታማነት—ወይም በዚያ ስልጣን አማካኝነት የሚመጣው ኃይል፣ የሚያስደስታችሁ ከሆነ—እሱም በአኗኗራችን የተወሰነ ነው፣ ጽድቅ በሆነው አኗኗራችን ላይ የተወሰነ ነው” (በ Conference report, ሚያዝያ 1976, ገፅ 50; or *Ensign,* ግንቦት 1976, ገፅ 33)።

• ለጌታ የማገልገልን ስልጣን እንዴት ነው የምንቀበለው? (እጅን በመጫን፣ በመሾም።)

---

**የክህነት ስልጣንን ማክበር—የተቀደሰ ልዩ መብት ነው**

በቁሳዊ የተደገፈ ትምህርት

የአስፒሪንን እንክብል የኮትህ ኮሌታ ላይ ወይም የሸሚዝህ ኪስ ላይ ለጥፍ። ወጣቶች አንተ የምታደርገውን ነገር በምንም ዓይነት አይጠራጠሩም። በየአራት ሰዓቱ አስፒሪን እንድትወስድ ዶክተርህ አዞሀል፣ ነገር ግን ጣዕሙን ስላልወደድክ በምትኩ ልትለብሰው እንደወሰንክ ንገራቸው። ምናልባት አንድ ሰው ካልዋጥከው በስተቀር ምንም ሊፈይድልህ አይችልም ብሎ ሊናገር ይችላል። ይህም ከአንድ ነገር ጥቅም ልታገኝ የምትችለው በተገቢው ስትጠቀምበት ነው እናም ብዙዎቹ ካህናት የክህነት ስልጣን ኃይልን እና በረከትን ለዚህ ምክንያት እንደማይቀበሉ እና እንደማይጠቀሙበት ለማስረዳት እድል ይሰጥሃል። ውጤቱን ሊያውቁት ይችላሉ ነገር ግን በረከቱን ለመቀበል መኖር የሚገባቸውን አኗኗር ለመኖር ፈቃደኞች አይደሉም እናም ኃይሉንም አይጠቀሙም።

ወጣቶች ትዕዛዙን በበለጠ ሲታዘዙ የበለጠ ኃይል እንደሚኖራቸው እና የማገልገል ፍላጎታቸው ታላቅ እንደሚሆን እንዲያውቁ እርዳቸው። በጥሩ ሁኔታ ሲያገለግሉ የክህነት ስልጣንን የመያዝን እና የማክበርን ታላቅ መብታቸውን ይረዳሉ።

ጥቀስ እና ውይይት

ቄስ ጀምስ ኢ ታልሚጅ፣ የአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን አባል የነበሩት፣ በክህነት ስልጣን ስለ መሾማቸው እና ለማክበር በሞከሩም ጊዜ የነበረውን ስሜት የጻፉትን አስረዳ። የቡድን አባላት የቄስ ታልሚጅን አባባል ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡት አድርግ።

“ከተሾምኩኝ በኋላ ወዲያውኑ ልገልጸው የማልችለው ስሜት ተሰማኝ። በመጠኑም ቢሆን የእኔ፣ የትንሹ ልጅ፣ በክህነት ስልጣን መጠራት በእግዚአብሔር ዘንድ ለመታመን ትንሽ የማይታመን ይመስል ነበር. . . .። የጌታ ነኝ፣ እናም ከእኔ በምፈልገው ሁሉ ይረዳኛል በሚለው የጠነከረ አስተሳሰብ ተመሰጥኩኝ።

“የሹመቱ ውጤት እንደ ዲያቆንነቴ ወደ ልጅነት ህይወቴ ጉዳዮች በሙሉ ተጋባ። በፊት እንዴት እንደነበርኩ አንዳንዴ ስለምረሳ እፈራለሁኝ፣ ነገር ግን ሁልጊዜ ስለማስታውሰው ዘወትር አመሰግናለሁኝ፣ እናም ትውስታው ዘወትር የተሻልኩ እንድሆን ረድቶኛል። በትምህርት ቤት ሜዳ ጨዋታ ምናልባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም በጨዋታ ውስጥ ለማግኘት ስሞክር፣ ከእኔ ጋር ከሚጫወቱት ጋር አለመግባባት ላይ ስደርስ፣ የማስታውሰው፣— ‘እኔ ዲያቆን ነኝ፣ እናም ዲያቆን ይህን ማድረጉ ተገቢ አይደለም።’ የሚል ትልህ በሆነ ድምፅ ይሰማኝ ነበር። በፈተና ቀን የሌሎች ልጆችን ሥራ መኮረጅ ቀላል መስሎ ሲታየኝ . . . በአዕምሮዬ እንዲህ አላለሁ፣ ‘ይህንን ማድረግ ከእነርሱ ይልቅ ለእኔ በጣም መጥፎ ይሆናል፣ ምክንያቱም እኔ ዲያቆን ነኝ።’

“የሹመቴ ታላቅ ክብር ስሜት ሁሉንም አገልግሎት ጥሩ አድርጎልኛል።”

• ቄስ ታልሚጅ በክህነት ስልጣን ውስጥ ዲያቆን ስለ መሆን እንዴት ተሰማቸው? (እርሱም የጌታ እንደሆነ እና ጌታም እንደሚረዳው ተሰማው፣ በፈተና ወቀተም ዲያቆን እንዴት መሆን እንደሚገባው ለእራሱ አስታውሷል።)

ወጣት ወንዶች በክህነት ስልጣን በተሾሙበት ጊዜ ያገኙትን ስሜት እንዲወያዩ አድርግ። በቄስ ታምለጅ ከተገለጹት ልምዶች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ማናቸውን ያገኙትን ልምዶች እንዲያካፍሉ አድርግ።

የቄስ ታምሌጅን አስተያየቶች ሌላው የቡድን አባል አንብቦ እንዲጨርሰው አድርግ።

“ዲያቆን በነበርኩኝ ጊዜ በአእምሮዬ የተጎናጸፍኩትን አድናቆት በፍጹም አልረሳም። ካህን እንደመሆኔ መጠን ለጌታ ልዩ አገልግሎት የመጠሬት ስሜት በዓመታት ሁሉ የብርታት ምንጭ ሆኖልኛል። ከዚያም በቤተክርስቲያን ውስጥ ለታላቅ አገልግሎት ከተሾምኩኝ በኋላ፣ በእያንዳንዱ አጋጣሚ፣ ተመሳሳይ የሆነ መተማመን መጥቶልኛል፣—ከሰማይ በሚመጣ ኃይል በተዋበ እውነት ውስጥ ነኝ፣ እናም ስልጣኑን እንዳከብር ጌታ ይጠብቀብኛል። ከዚያም በኋላ አስተማሪ፣ ቄስ፣ ሊቀ ካህን እናም በመጨረሻ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋሪያ በመሆን ተሾምኩኝ፣ እናም በተሾምኩበት በእያንዳንዱ ሹመት አዲስ እና ነፍስን የሚያስደስት ስሜት ዲያቆን እንድሆን በተጠራሁኝ ጊዜ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳወቅኩት በጌታ አገልግሎት ውስጥ መሆኔን ነው” (*Incidents from the lives of Our Church Leaders* [deacons instruction manual, 1914], pp. 135–36)።

• ቄስ ታልሚጅ እንዳደረጉት የእራስህን ጥሪ አጥብቀህ ከያዝከው፣ በቤት ውስጥ እንዴት ነው የምታገለግለው? በቤተክርስቲያንስ? በትምህርት ቤትስ?

ለቄስ ታልሚጅ እንደነበረው የክህነት ስልጣን ያዦች ለቡድን አባላት የጥንካሬ ምንጭ መሆን ለሚችሉበት ለጌታ ልዩ አገልግሎት የተጠሩ መሆናቸውን እንዲያውቁ ግለጽላቸው።

ጥቅስ እና ውይይት

ብቁ የክህነት ስልጣን ያዦች ለመሆን በጽድቀ አኗኗር መኖር አለብን። ፕሬዚዳንት ሃሮልድ ቢ. ሊ የሚከተለውን መግለጫ ሰጥተዋል፣

“የህያው አምላክ ክህነት ስልጣን ያዥ ስለሆንኩ የሰማይ አባታችን ወኪል ነኝ እናም እርሱ በእኔ ውስጥ የሚሰራበት የክህነት ስልጣን አለኝ፣ ማድረግ የሚገባኝን ነገር ከማከናወን አልቆጠብም በሌላ መንገድ ከእግዚአብሔር የክህነት ስልጣን ጋር ቀረቤታ ስላለኝ—ብለን ማለት አለብን።’

“ያም የክህነት ስልጣን ያዦች ለእራሳቸው ማለት የሚገባቸው ነው፣ ‘የክህነት ስልጣን ያዦች ሆነን እንደሌሎች ሰዎች መሆን የለብንም። የተለየን መሆን አለብን፣ ምክንያቱም የክህነት ስልጣን ማለት በእግዚአብሔር መንግሥት ንጉሳዊ ቤተሰብ ውስጥ አባል መሆን ማለት ነው’” (በ Conference Report, ጥቅምት 1973, ገጽ 115; or *Ensign*, ጥር1974, ገጽ 97)።

• እኛ እንደ ክህነት ስልጣን ያዥነታችን ከሌሎች ሰዎች እንዴት መለየት እንችላለን?

ይህን ጥያቄ ወጣት ወንዶች በመወያየት ላይ እንዳሉ፣ መልሳቸውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ።

---

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት

የቡድኑ አባላት የእግዚአብሔር እውነተኛ የክህነት ስልጣን እንዳላቸው ምስክርነትህን ስጥ። በእለት ኑሯቸው ውስጥ ይህን የክህነት ስልጣን ከአከበሩ፣ በተገቢው ከተጠቀሙ፣ እናም ከእነርሱ ከሚጠበቀው በላይ ከሰሩ ከጌታ ብዙ ታላቅ በረከቶችን እንደሚቀበሉ መስክር።

አሮናዊ የክህነት ስልጣንን መቀበል የክህነት ስልጣን ኃይላቸውን ለመጠቀም ብቁ ሆኖ የመኖርን ያህል አስቸጋሪ እንዳልሆነ ለወጣት ወንዶች ግለጽላቸው። ይህ የማያቋርጥ ጥረት እና ሥራን ይጠይቃል።

ሙከራ

የክህነት ስልጣን መሪዎቹ የሚሰጡትን ሁሉንም የማገልገል እድል እንዲቀበል እያንዳንዱን ወጣት ወንድ አበረታታ። በተጨማሪም፣ ከቀጣዩ የቡድን ስብሰባ በፊት እያንዳንዱ ሰው ለክህነት ስልጣኑ የሰማይ አባትን እንዲያመሰግን አበረታታ።

# 2 የዲያቆን ጥሪ

| | |
|---|---|
| **አላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ወንድ በአሮናዊ የክህነት ስልጣን ውስጥ የዲያቆንን ተግባር ይረዳል እናም እንደ አሮናዊ የክህነት ስልጣን ያዥ ጥሪውን ለማጉላት ይፈልጋል። |
| **ዝግጅት** | 1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፥<br>ሀ. መደበኛ ቅዱሳን መጻሕፍት ለእያንዳንዱ ወጣት።<br>ለ. ጥቀሶችን ማስመሪያ እርሳስ።<br>2. የእያንዳንዱን ተጫዋች አቀጣጫ እና እንቅስቃሴ በማሳየት የእግር ኳስ ጨዋታን ንድፍ አዘጋጅ። |

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

**የዲያቆን ተግባሮች**

ሁኔታ እና ውይይት

የሚከተሉትን ሁኔታዎች አቀርብ፥

በምሽት አንድ ፖሊስ በመገድ ላይ እየሄደ ነው። አንድ ሰው የአንድ ጌጣጌጥ መጋዘንን መስኮት ትልቅ መስታዋት ሲያደቀ ከፍተኛ ድምጽ ይሰማል እናም ይመለከታል። ሰውየው አንድን ትልቅ ዶንያ ውድ በሆኑ ቀለበቶች፣ ሰዓቶች እና ዕንቁዎች መሙላት ይጀምራል።

• በዚህ ሁኔታ ውስጥ ፖሊሱ ምን እንዲያደርግ ተጠብቃላችሁ? (ሰውየውን በቁጥጥር ስር እንዲያውለው።) ለምን? (ምክንያቱም ህግን እና ሥርዓትን ለማስከበር መርዳት የፖሊሱ ተግባር ነው።)

• *ተግባርን* እንዴት ተገልጻለህ? (አንድ ሰው ያለው ኃላፊነት፣ ግዴታ፣ ወይም አንድ ሰው ሊፈጽመው የሚገባ ነገር ነው።)

ፖሊሱ የህግ ሠራተኛ እንደመሆኑ መጠን የሚፈጽመው የተወሰኑ ተግባሮች እንዳሉት ሁሉ ዲያቆንም የክህነት ስልጣን ያዥ እንደመሆኑ መጠን የተወሰኑ ግዴታዎች እና ኃላፊነቶች አሉት።

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

አንድ ወጣት ወንድ ትምህርት እና ቃልኪዳን 107፥13–14 እንዲያነብ አድርግ። ይህን ጥቀስ የቡድኑ አባላት እንዲያሰምሩበት ተናገር።

• ሁለቱ የአሮናዊ የክህነት ስልጣን ታላላቅ አላማዎች ምንድን ናቸው? (የቤተክርስቲያኑን “ውጫዊ ሥርዓቶችን” ማከናወን እና ወጣት ወንዶች የመልከጼዴቀ የክህነት ስልጣንን እንዲቀበሉ ማዘጋጀት ናቸው።)

• “ውጫዊ” ሥርዓት ምንድን ነው? (ውጫዊ ሥርዓት የሚያመለክተው ጊዜያዊ ወይም ቁሳዊ ሥርዓቶችን እነሱም ቅዱስ ቁርባንን መባረክ እና ማስተላለፍን እንዲሁም ማጥመቅን ነው።)

ይህ ትምህርት የዲያቆኖችን ኃላፊነቶች የአሮናዊ የክህነት ስልጣን ዓላማዎችን እንዴት እንደሚያሟሉ እንደሚያብራራ አስረዳ። የዲያቆን ተግባሮች ጊዜያዊ ቢሆኑም እንኳን፣ እነዚህ ጊዜያዊ ተግባሮች ወጣት ወንዶች የመልከጼዴቀ የክህነት ስልጣን መንፈሳዊ ሥርዓቶችን፣ እነሱም ህሙማንን መባረክ እና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን መስጠትን ለማከናወን እንዲዘጋጁ ይረዳሉ። እያንዳንዱ የአሮናዊ የክህነት ስልጣን ያዥ ቄስ፣ አስተማሪ ወይም ዲያቆንም ቢሆን ጥሪውን ለማጉላት የዲያቆንን ተግባሮች መረዳት አለበት።

ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት

የሚከተሉትን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ፥ *የዲያቆን ተግባሮች*

• የዲያቆን ተግባሮች ምንድን ናቸው?

የወጣት ወንዶችን መልሶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ። መልሶቹ በይበልጥ የሚከተሉትን ማጠቃለል አለባቸው፥

1. የጾም በኩራትን ማሰባሰብ
2. ቅዱስ ቁርባንን ማስተላለፍ
3. እንደ ጳጳሱ መልእክተኛ ማገልገል
4. ለቤተክርስቲያኑ መሰረታዊ እና ቁሳዊ መገልገያዎች እንክብካቤ ማድረግ
5. በጳጳስ እንደተመደበው በአገልገሎት ፕሮጀክቶች ወይም በበጎ አድራጎት ሥራዎች መርዳት

6. ቤተክርስቲያንን መጠበቅ እና እንደቋሚ አገልጋይ መሥራት (ት እና ቃ 84፥111 ተመልከት)

7. በሚሲዮናዊነት እና በማበረታታት ጥረቶች ውስጥ መሳተፍ (ት እና ቃ 20፥58–59 ተመልከት)

8. እንደአስፈላጊነቱ አስተማሪዎችን በተግባራቸው ሁሉ መርዳት (ት እና ቃ 20፥53፣ 57 ተመልከት)

9. በቤተክርስቲያን ስብሰባዎች ንግግር ማድረግ

ዝርዝሮቹን አንብብ እናም የእግዚአብሔርን መንግሥት በመገንባት በእያንዳንዱ አገልግሎት ድርጊት አስፈላጊነት እና ውጤት ላይ ተወያይ።

ጥቅስ

ዲያቆን ሆኖ ሥራውን ማከናወንን እንደ ታላቅ ክብር የተመለከተውን፣ የፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦልን የሚከተለውን አስተያየት አንድ ወጣት እንዲያነብ አድርግ፣

"አስታውሳለሁኝ ዲያቆን እያለሁኝ. . . . ዲያቆን መሆን ታላቅ ክብር እንደሆነ አስብ ነበር። አባቴ ስለአለኝ ኃላፊነቶች ዘወትር ጥሩ አመለካከት ነበረው እናም የጾም በኩራትን እንድሰበስብ በፈረስ የሚጎተት ጋሪ ሁል ጊዜ እንድወስድ ይፈቅድልኛል። የእኔ ኃላፊነት የምኖርበትን ከተማ ያጠቃልላል፣ ነገር ግን ወደ ቤት ለመሄድ ረዘም ያለ ጉዞን ይጠይቃል፣ እናም ጆንያ ሙሉ ዱቄት ወይም ጠርሙስ ሙሉ ፍራፍሬ ወይም አትክልት ወይም ዳቦ ሲጠራቀም ከባድ ይሆን ነበር። ስለዚህም በፈረስ የሚጎተተው ጋሪ የተመቻቸ እና ጥሩ የሚያገለግል ነበረ። ባለፉት ቀናት በገንዘብ ቀይረነው ነበር ግን በእኔ ጊዜ በሸቀጥ ነበር። በሸቀጣ ሸቀጥ ፋንታ ገንዘብ የሚሰጥበት ጊዜ ቢቀየርም እንኳን ለሰማይ አባት ይህን ማድረግ ታላቅ ክብር ነበር፣ አሁንም ቢሆን ይህን አገልግሎት ማከናወን ታላቅ ክብር ነው" (በ Conference Report ሚያዚያ 1975, ገፅ 117; or *Ensign*, ግንቦት 1975, ገፅ 79)።

የማሰላሰያ ጥያቄዎች

ወጣት ወንዶች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከፍ ባለ ድምፅ ሳይመልሱ እንዲያስቡ ጠይቃቸው።

- የክህነት ስልጣን ተግባሮቻችሁን እና ኃላፊነቶቻችሁን ማሟላት ክብር እንደሆነ ትገምታላችሁን?
- ቅዱስ ቁርባንን በምታስተላልፉበት ጊዜ በተገቢ ሁኔታ በመልበስ፣ ቀድስናን የተላበሳችሁ በአክብሮት የተሞላችሁ መሆናችሁን ታረጋግጣላችሁን?
- የጾም በኩራትን መሰብሰብ አስደሳች ሥራ የሚያደርገው ግንዛቤ ምንድን ነው?

---

### ኃላፊነትን በመቀበል በጋራ መሥራት

ንድፍ እና ውይይት

የቡድን አባላት በሙሉ እንዲያዩት የእግር ኳስ ንድፍን ከፍ አድርገህ አሳይ። ለጥቂት ጊዜ እንዲያጠኑት ፍቀድላቸው።

- ይህ ከፍ አድርጌ የያዝኩት ንድፍ ምንድን ነው? (የእግር ኳስ ጨዋታ ንድፍ።)
- ለምን ይጠቀማል? (ለዚህ ጨዋታ የእያንዳንዱ ተጨዋች ሥራ ምን እንደሆነ ለመግለፅ።)
- ከተጨዋቾቹ መሀል አንዱ ተግባሩን ባይወጣ ምን ሊከሰት ይችላል? (ጨዋታው ከሞላ ጐደል የተሳካ ሊሆን አይችልም፣ ጨዋታው ውጤታማ እንዲሆን እያንዳንዱ ተጨዋች ማከናወን የሚገባው አስፈላጊ ሥራ አለው።)

ሁሉም ቡድኖች ስኬታማ ለመሆን የተስተካከለ አደረጃጀት እንደሚያስፈልጋቸው አስረዳ። የእግር ኳስ ቡድንም ሆነ የካህናት ቡድን፣ እያንዳንዱ አባል የተወሰኑ ተግባሮች እና ኃላፊነቶች አሉት። ጥቂቶቹ የዲያቆን ተግባሮች ከሌሎች የክህነት ቢሮዎች ጋር የመስራት የጋራ ጥራትን ይጠይቃሉ።

- በዋርድ የሚገኘው ዲያቆን ቅዱስ ቁርባንን ባያስተላልፍ ምን ይከሰታል? (ሀላፊነታቸውን ለመወጣት ያዳግታቸዋል፣ ስለዚህ፣ የዲያቆኑን ኃላፊነቶች ለማከናወን ሌሎች የክህነት ስልጣን ያዣች ሊጠሩ ይችላሉ።)

ጥቅስ እና ውይይት

ቄስ ዴቪድ ቢ. ሃይት የአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት ቡድን ዲያቆን እንደመሆኑ መጠን ስለእሱ ኃላፊነቶች የተናገረውን ወጣቱ እንዲያነብ አድርግ።

"ዲያቆን ሆኖ መሾምን በግልፅ አስታውሳለሁኝ። አዲስ ዓለም ተከፈተልኝ። አሁን ጥሩ ኑሮ በመኖር ላይ እገኛለሁኝ። ሰዎች 'የክህነት ስልጣን አለህ' ሲሉ እሰማለሁ፣ ሙሉ በሙሉ ለመረዳት ቀላል አልነበረም። ነገር ግን በትሁት አስተማሪዎች አማካኝነት፣ እንደ ዲያቆንነታችን የተቀደሱ ነገሮችን ለመሥራት በረከት እና ስልጣን እንደተሰጠን መረዳት ጀመርን።

"እንደ ቡድን ባላስልጣን ለአባላቶቻችን በሙሉ ተጠያቂዎች ነን እናም ሁላችሁም በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደሚኖሩ እንከታተል ነበር። አብሮ በመኖር ደስተኞች ነበርን። ለአረጋዊያን እና ለመበለቶች እንጨት ፈልጠናል፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ የከሰል በርሚል ሞልተናል፣ የፀሎት ቤትን ዘወትር ቀዳሚ ከሰዓት አጽድተናል፣ ደረጃዎቹን ጠርገናል፣ የጠጠር ግቢውን አስተካክለናል፣ የቅዱስን ቁርባን ጨርቆች እና . . . አልባሳት ንጹህ እና የጸዱ መሆናቸውን አይተናል እና በተንሿ የስብሰባ አዳራሻችን አኳሃን እውነተኛ ኩራትን አግኝተናል" (በ Conference Report, ሚያዝያ 1981, ገፅ 58; or *Ensign*, ግንቦት 1981, ገፅ 42)።

- ቄስ ሃይት እንዳደረገው ወጣት ወንዶች የራሳቸውን ጥሪ ለማጉላት ዛሬ ዓይነት ምን ተግባሮችን ማከናወን አለባቸው? (የቅዱስ ቁርባን ማቀረቢያዎችን ማጽዳት፣ ከቅዱስ ቁርባን ስብሰባ በፊት ወይም በኋላ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ አሮጌ የታተሙ ፅሑፎችን ወይም ወረቀቶችን ማንሳት፣ በቤተክርስቲያን መሬት አካባቢ ያለውን ቁሻሻ ማንሳት፣ የቤተክርስቲያኑን ክልሎች ከአረም መጠበቅ፣ የአገልግሎት ፕሮጀክቶችን ማከናወን፣ እና ሌሎችን መርዳት፡፡)

ጥቀስ

ጳጳስ ኤች ቡርክ ፒተርሰን የጳጳሳት የበላይ አመራር የክህነት ስልጣን ተግባሮችን የማከናወንን አስፈላጊነት አጥብቆ የተናገረውን ግለጽ፡፡ የሚከተለውን ጥቀስ አንብብ፣

“እንደ ወጣት ወንዶች እና እንደ ቄሶች የያዝነው የክህነት ስልጣን ለዳኝ የእኛ ኃላፊነት ቢኖረው ኖሮ እንደሚያደርገው ተግባሮቻችንን የማከናወን ስልጣን ነው” (በ Conference Report, ጥቅምት 1974, ገፅ 99; or *Ensign*, ህዳር 1974, ገፅ 70)፡፡

ስለዚህ አባባል ያለህን ስሜት ግለፅ፣ እናም ወጣት ወንዶች እራሳቸውን እንዲገልጹ አበረታታቸው፡፡ ቡድኑ በዋርድ ውስጥ የአገልግሎት ፕሮጀክት እንዲመሠርት ለመርዳት ኤጲስ ቆጶሱን የተወሰኑ ሐሳቦችን መጠየቅ ትችላለህ፡፡

---

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት

የአሮናዊ የክህነት ስልጣን ያዥ እንደመሆናችን መጠን ጥሪያችንን ስናጉላ እና ከእኛ የሚጠበቁትን ተግባሮች እና ኃላፊነቶች ስናከናወን ለውጥን እናያለን፡፡ ከለዳኝ ጭምር፣ ሌሎችን እያገለገልን በማወቅ መሆናችንን መልካም ስሜት ይኖረናል። አሮናዊ የክህነት ሥልጣንን መያዝ ቀላል ነገር አይደለም፡፡ አሮናዊ የክህነት ስልጣንን ከያዘ ሰው ብዙ ይጠበቃል፡፡

ሙከራ

የቡድን አባላት የክህነት ስልጣን ተግባራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ለዳኝን እያገለገሉ እንደሆነ እንዲያስታውሱ እና ተግባራቸውን ጌታ እንዲያሳዩ በሚፈልገው ክብር እና ቀድስና በተቻላቸው መጠን እንዲያከናውኑ አበረታታቸው፡፡ ወጣት ወንዶች የክህነት ስልጣን ተግባራቸውን በብቃት በሚወጡበት ጊዜ፣ ክርስቶሳዊ አገልግሎትን እያከናወኑ እንደሆነ አብራራ፡፡ ከክህነት ስልጣን ጋር በተጣመረው ሁኔታ ታላቅ በረከት እንደተሰየሙ አስታውሳቸው፡፡ ቢሆንም፣ እነዚህ በረከቶች የሚገኙት ግዴታቸውን እና ኃላፊነቶቻቸውን በማከናወን ጥሪያቸውን ሲያጉሉ ብቻ ነው፡፡

# ቅዱስ ቁርባንን ማገልገል

# 3

**አላማው**

እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ቅዱስ ቁርባንን ሲያገለግል በበለጠ የተቀደሰ እና መፈሳዊ ይሆናል እናም የቁርባንን ቅዱስ የሆነ ገጽታውንም በበለጠ ይረዳል።

---

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሣሪያዎች፥
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጻሕፍት።
   ለ. ሥዕል 1፣ የመጨረሻው እራት (62174)፤ እና ሥዕል 2፣ የጥምቀት ገንዳ (62031)።
   ሐ. ጥቅሶችን ምልክት ማድረጊያ እርሳስ።
   መ. ሁለት የቅዱስ ቁርባን ማቀረቢያዎች፣ አንድ ለዳቦ፣ አንድ ለውሃ።
2. ቅዱስ ቁርባንን በቅድስና የማገልገልን አስፈላጊነት ከወጣት ወንዶች ጋር እንዲወያይ ጳጳሱን ወይም አማካሪውን ጋብዝ።

---

**ለትምሕርቱ ዕደገት**
**የቀረበ ሐሳብ**

**የቅዱስ ቁርባን አስፈላጊነት**

ሥዕል እና ውይይት

የጥምቀት ገንዳውን ሥዕል አሳይ እናም በትምህርቱ ክፍለ-ጊዜ መጀመሪያ ለዳቦው እና ለውሃው ለሁለቱም የቅዱስ ስቁርባን ማቀረቢያዎች በጠረጴዛው ላይ አስቀምጥ።

• ቅዱስ ቁርባን እና ጥምቀት በጋራ ምን አላቸው? (ስንጠመቅ ቃል ኪዳን እንገባለን። በእያንዳንዱ ጊዜ ቅዱስ ቁርባንን ስንወስድ ያንን ቃል ኪዳን እናድሳለን።)

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

ወጣት ወንዶች በተጠመቁበት ጊዜ የገቡትን ቃል ኪዳን እንዲያስታውሱ ለመርዳት፣ የቡድኑ አባል ሞዛያ 18፥10 እንዲያነብ እና ሌሎችም ከቅዱሳን መጻሕፍቶቻቸው እንዲከታተሉ አድርግ።

• በጥምቀት ላይ የምንገባው ቃል ኪዳን ምንድን ነው? (ጌታን ለማገልገል እና ትዕዛዛቱን ለመጠበቅ።)

• ጌታ በተዘዋዋሪ ቃል የገባልን ምንድን ነው? (መንፈሱን ከእኛ ጋር ሊኖር ይችላል።)

ቅዱስ ቁርባንን በምንወስድበት በእያንዳንዱ ሰዓት መንፈሱ ከእኛ ጋር ይሆን ዘንድ ልናስታውሰው እና ትዕዛዛቱን ልናከብር ለጌታ ቃል ኪዳን እንደምንገባ ለወጣት ወንዶች አስታውስ።

ቅዱስ መጽሐፍ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ውይይት

ሞሮናይ 4፥3 እና 5፥2ን አንድ ወጣት እንዲያነብ አድርግ። ወጣት ወንዶቹ እነዚህን ምንባቦች በቅዱሳን መጻሕፍቶቻቸው ውስጥ ምልክት እንዲያደርጉባቸው አድርግ።

• ቅዱስ ቁርባንን በምንካፈልበተ ጊዜ ቃል ኪዳናችንን ማደስ የሚገባን እንዴት ነው?

በጥቁር ሰሌዳ ላይ ዘርዝር፦ *ጥምቀት—ቃል ኪዳን እንገባለን*

*ቅዱስ ቁርባን—ቃል ኪዳናችንን እናድሳለን*

---

**የቅዱስ ቁርባን ትርጉም**

በቁሳዊ የተደገፈ ትምሕርት

የቅዱስ ቁርባን ማቀረቢዎችን ጥቀስ።

• እነዚህ ማቀረቢያዎች ለምን ያገለግላሉ?

የወጣት ወንዶችን መልስ ተቀበል። ቅዱስ ቁርባንን ማስተላለፍ ያለንን የክህነት ስልጣን ሥራችንን ለማሟላት እንደሚጠቀም አሳስብ። ማቀረቢያዎቹ ቅዱስ ቁርባንን ለማስተለለፍ ቢያገለግሉም እንኳ በእራሳቸው ምንም የተለየ ትርጉም እንደሌላቸው በውውይቱ ውስጥ ግለጽ።

• እነዚህ ማቀረቢያዎች ትርጉም እንዲኖራቸው ምንን መያዝ አለባቸው? (ዳቦ እና ውሃ።)

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

አንድ ሰው 1ኛ ቆሮንጦስ 11፥23–25 እንዲያነብ እና ሌሎች በመከታተል ጥቅሱን ምልክት እንዲያደርጉበት አድርግ።

• ዳቦው የሚወክለው ምንን ነው?

ዳቦው የሚወክለው ለእኛ መስዋዕት ያደረገልንን የአዳኛችንን ሥጋ እንደሆነ ወጣት ወንዶች መረዳታቸውን እርግጠኛ ሁን።

ውይይት

• ውሃው የሚወክለው ምንን ነው?

ውሃው የአዳኙን ደም እንደሚወክል በውይይቱ ውስጥ አስረዳ። ሉቃስ እንደገለጸው ይህን ታላቅ ስቃይ በበለጠ ተወያይ ወይም ግለጽ። (ሉቃስ 22፥39–46 ተመልከት)። ኢየሱስ ለእኛ ኃጢያት እንደተሰቃየ አስረዳ።

ኢየሱስ በጌቴሰማኒ ስለ እኛ በመሰቃየቱ ይቀርታን ለማግኘት እንዳስቻለን ግለጽ። ከስህተቶቻችን ንስኃ እንድንገባ እና እንድንታረም መንገዱን አዘጋጅቶልናል።

ስቅለትን እና ትንሳኤን በአጭሩ ተወያይ። ድንቅ ክስተት እንደተፈጠረም ግለጽ። የሞተው ኢየሱስ ህያው ነበር። መንፈሱ ከሰውነቱ ጋር ተዋህዷል። አንድ ቢመስልም እንኳን፣ የተለየ ነበር። ሰውነቱ ተለውጧል። ኢየሱስ ዳግም አይሞትም፣ ነገር ግን ለዘለዓለም ይኖራል። ይህም በዚህ ምድር ላይ ሁሉም ከሞት ሊነሱ የቻሉበት የመጀመሪያው ጊዜ ነበር። የኢየሱስ ትንሳኤ በምንድር ላይ ለኖሩ ወይም በምድር ላይ ለሚኖሩ ሁሉ ከሞቱ በኋላ ዳግም መኖር እንዲችሉ አድርጓል። ኢየሱስ ይህን በጣም ውድ ስጦታ እና እድል ሰጠን።

ቅዱስ ቁርባን በመጀመሪያ በተከናወነበት ጊዜ ቅዱስ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም ቅዱስ እንደሆነ ጥቀስ።

በህይወትህ ውስጥ የቅዱስ ቁርባንን አስፈላጊነት መስክር።

---

**ኢየሱስ ቅዱስ ቁርባንን አሳለፈ**

ሥዕል እና ውይይት

የመጨረሻ እራትን ሥዕል አሳይ።

ከዚህ ስብሰባ አስቀድሞ አዳኛችን ታላቅ ስቃዩን እና መስዋእትነቱ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ መሆኑን በማወቅ፣ በሶስት አመታት የአገልግሎት ዘመኑ ከእርሱ ጋር ያገለገሉትን በዙሪያው እንደሰበሰበ ግለጽ። እነዚህን የመጨረሻ ጊዜያት ከእነርሱ ጋር ለመካፈል ፈልጓል።

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

ወጣቱ ሉቃስ 22፥19–20 እንዲያነብ እና ሌሎች በመከታተል ጥቀሶችን ምልክት እንዲያደርጉባቸው አድርግ።

አዳኛችን በዚህ ስብሰባ ላይ ምን ሠራ? (ቅዱስ ቁርባንን አስተዋወቀ።)

ለወጣት ወንዶች ይህ ሥዕል ቅዱስ ቁርባን የተላለፈበትን የመጀመሪያውን ጊዜ እንደሚያሳይ ግለጽላቸው። ኢየሱስ እራሱ ቅዱስ ቁርባኑን እንዳዘጋጀ፣ እንደባረከ እና እንዳሳለፈ አብራራ።

አዳኛችን የክህነት ስልጣንን ለያዙት በእርሱ ፈንታ እነዚህን የተቀደሱ የዳቦ እና የውሃ ምሳሌዎችን የማዘጋጀት፣ የመባረክ እና ማሳለፍ እድል ሰጥቶአቸዋል።

ጥቀስ

ስለዚህ ኃላፊነት የቤተክርስቲያኑ መሪ ጳጳስ ጆን ኤች ቫንደንበርግ ያለውን የቡድን አባል እንዲያነብ አድርግ።

“ይህን ኃላፊነት ያላችሁ ወጣት ወንዶች፣ አዳኛችን እንዳከናወነው ተመሳሳይ ሥራ የምታከናውኑ መሆናችሁን በአዕምሮአችሁ በማሰብ ቅዱስ ቁርባንን ታገለግላላችሁ፣ ታዘጋጃላችሁ፣ እናም ታሳልፋላችሁን? እናንተ ዲያቆኖች ይህ አስተሳሰብ በቅዱስ ቁርባን ጊዜ በቀድስና መቆየት እና በንጽህና እና በክብር ቅዱስ ቁርባንን እንድታሳልፉ ይረዳችኋልን?” (*Improvement Era*, ህዳር 1967, ገጽ 15)።

• አዳኛችን ያከናወነውን ሥርዓት እያከናወናችሁ መሆኑን ማወቅ ምን ዓይነት ስሜትን ይፈጥርባችኋል?

ወጣት ወንዶች ይህን በመወያየት ላይ እንዳሉ ቅዱስ ቁርባንን በማስተላለፍ ያላቸውን ጌታን የማገልገል ታላቅ፣ የተቀደሰ እድል እና ክብር እንደገና አስረዳ።

---

**ቅዱስ ቁርባንን ይበልጥ በተከበረ ሁኔታ ማሳለፍ**

ከተቻለ የዚህን ትምህርት ክፍል ጳጳሱ ወይም ከአማካሪዎቹ አንዱ እንዲመሩት አድርግ። ይህን ክፍል በሚቀጥለው ሰንበት ጳጳሱ እንደተለየ ትምህርት እንዲያስተምር ማድረግ ትችላለህ።

ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት

• ቅዱስ ቁርባንን የተሻለ ቅዱስ ልምድ ለማድረግ ምን ማድረግ ትችላለህ?

እያንዳንዱ ወጣት ቅዱስ ቁርባንን በተገቢው በማሳለፍ ሰዎች የክርስቶስን ስቃይ እንዲያስታውሱ እና ከሰማይ አባታቸው ጋር ቃል ኪዳናቸውን እንዲያድሱ መርዳት እንደሚችል እንዲገነዘብ እርዳ። ለሚካፈሉት ሁሉ የቅዱስ ቁርባን ስብሰባን የበለጠ መንፈሳዊ እና ትርጉም ያለው የሚያደርጉትን የወጣቶቹን ሐሳብ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ዘርዝር።

ሊሰነዘሩ የሚችሉት ሐሳቦች የሚያጠቃልሉት—

1. ስለ አዳኛችን እና ስለ እርሱ መስዋዕትነት ማሰብ።
2. የቅዱስ ቁርባን ጸሎቶችን በጥሞና ማዳመጥ።
3. ስለ ቅዱስ ቁርባን ትርጉም በጥልቀ ማሰብ። የቅዱስ ቁርባንን መዝሙር ቃላቶች ማሰብ። የቅዱስ ቁርባንን ጸሎት ማዳመጥ። ቅዱሳን መጻሕፍትን መከለስ።
4. እራስህን በክብር እና በቀድስና መምራት።

# 4 የጾም በኩራትን መሰብሰብ

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት የድሆችን ፍላጎት በሚገነዘብበት ጊዜ የጾም በኩራትን በፈቃደኝነት ሲሰበስብ እና ሸክማቸውን ለማቃለል ሲረዳ ጌታን ያገለግላል፡፡ |
| **ዝግጅት** | 1. አስፈላጊ መሣሪያዎች፡ ጥቀሶችን ማስመሪያ እርሳስ፡፡<br>2. የዮሐንስን ታሪክ ማጥናት።<br>3. በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ ከሚገኘው የተዘጋጀ ጽሁፍ ለእያንዳንዱ ወጣት "የጾም በኩራትን ለመሰብሰብ መሠረታዊ መመሪያዎች" የሚል ቅጂን አዘጋጅተህ ስጣቸው፡፡<br>4. በሉቃስ 10፡30–37 የሚገኘውን መልካም ሰማሪያዊውን ታሪክ አንድ ወጣት በእራሱ ቃላቶች ለመናገር ተዘጋጅቶ እንዲመጣ አንዱን ወጣት ጠይቀ፡፡ |

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**የችግረኞችን ሁኔታ መረዳት**

ውይይት

- ያለ ምግብ ለረጅም ጊዜ የቆየህበት ወቀት ምን ያህል ጊዜ ነው? ምን ነበር የተሰማህ?
- ዘወትር ረሀብተኛ የሆነ ሰው በቂ ምግብን ከሚያገኝ ሰው በምን አኳኋን ይለያል ብለህ ታስባለህ?

ታሪክ እና ውይይት

ረሀብን የመሳሰሉ ችግሮች በየስፍራው እንደሚከሰቱ ግለጽ፡፡ ዮሐንስ ስለሚባለው ወጣት እና ስለቤተሰቡ የሚከተለውን ታሪክ ስትናገር ወጣት ወንዶች እንዲሰሙት አድርግ (ወይም ተገቢ የሆነውን የግል ታሪክ መተካት ትችላለህ)፡፡

ዮሐንስ የዲያቆን ቡድኑ ታታሪ አባል ነበር፡፡ በእያንዳንዱ ወር ብዙም ባለማሰብ የጾም በኩራትን አሰባስቧል፣ ማንም ሰው ሊያከናውነው ስለ ማይፈልግ ዲያቆኖች የጾም በኩራትን ማሰባሰብ እንደነበረባቸው ዘወትር እምነቱ ነበር፡፡

የዮሐንስ አባት በመኪና አደጋ በፅኑ ቆስሎ ስለ ነበር ለሁለት ወር ከሁለት ሳምንት መስራት አይችልም ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት፣ የዮሐንስ ወላጆች ምግባቸውን ለመግዛት እና በየወሩ ለሚፈለግባቸው ግልጋሎቶች ሂሳብ ለመክፈል በቂ ገንዘብ አልነበራቸውም፡፡

ዮሐንስ እናቱ እና አባቱ እንደተጨነቁ ያውቅ ነበር፡፡ ችግራቸውን ለመደበቅ ለእነርሱ አስቸጋሪ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ፣ ዮሐንስ እና ሌሎች ልጆችም ተጨንቀዋል፡፡

- ይህ በአባቶቻችሁ ላይ ቢደርስ ምን ይሰማችኋል?

የዮሐንስ ቤተሰብ የገንዘብ እጦት ችግሮች እንዳሏቸው በማወቀ፣ ጳጳሱ እና የሴቶች መረዳጃ ማህበር ፕሬዚዳንት የዮሐንስን ወላጆች ለመጎብኘት መጡ፡፡ እነርሱ ተመልሰው ከሄዱ በኋላ፣ ዮሐንስ በእናት እና አባቱ አመለካከት ላይ ታላቀ ለውጥን አየ፡፡ የተዝናኑ እና የተደሰቱ መሰሉ፡፡ ልጆቹም ይህንኑ የአስተሳሰብ ለውጥ በማየት በጣም መጨነቀን አቆሙ፡፡ የቤተሰቡ አኗኗር ወዲያውኑ የተስተካከለ ሆነ፡፡

የዮሐንስ አባት የእጅ ጥበብ ሙያ የነበረው ነው። ማገገም እንደጀመረ ተነስቶ በአካባቢው መዟዟር ሲጀምር የእቃ ሣጥኑን ይዞ ወደ ስብሰባ አዳራሽ በመግባት የተፈለገውን አነስተኛ ጥገናዎች እና ማሻሻያዎችን አደረገ፡፡ ብርታቱን ካገኘ በኋላ፣ ወደ መደበኛ ሥራው ለመመለስ በቂ አቀም እስኪያገኝ ድረስ ለረጅም ጊዜ ይሠራ ነበር፡፡

አባቱ ሥራን መሥራት ባልቻለበት ጊዜ፣ ዮሐንስ ከጳጳሱ መጋዘን ምግብ እና ልብስ ሲመጣ ተመለከተ፡፡ የቤት ኪራይን እና ጋዝ፣ ኤሌክትሪክ እና የጤና ግልጋሎቶችን እንዲከፍሉ ለመርዳት ገንዘብ ተሰጣቸው፡፡

- ጳጳሱ የዮሐንስ ቤተሰብን ለመንከባከብ ገንዘብ ከየት አገኘ? (ከጾም በኩራት፡፡)
- ዮሐንስ ለጾም በኩራት ገንዘባቸውን ለሰጡት ለእነዚያ የዋርድ አባላት ምን ይሰማዋል ብለህ ታስባለህ?
- የዮሐንስ ቤተሰቦች የጾም በኩራትን ለማሰባሰብ ቡድኑ ባደረገው ጥረት ምን ይሰማቸዋል ብለህ ታስባለህ?

**የጾም በኩራትን ማሰባሰብ**

የአማካሪው አቀራረብ

የእርሱ ደቀመዛሙርት የሆኑት ችግረኞችን እንዲንከባቡ እና የራባቸውን እንዲመግቡ ለኖኝ እንዳስተማረ አስረዳ። የክህነት ስልጣን ስላለን፣ እንደ ለዳኛችን ተከታዮች መሥራት እና እርሱ እዚህ ቢሆን የሚያደርጋቸውን ነገሮች ማድረግ አለብን።

የክህነት ስልጣን ያዥ እንደመሆናችን መጠን ያለብን አንዱ ኃላፊነት በችግር ውስጥ ያሉትን ለመርዳት የጾም በኩራትን ማሰባሰብ ነው። የጾም በኩራትን የማሰባሰብ ግዴታችንን በመወጣት፣ ለጌታ ደቀመዛሙርቱ መሆናችንን እና ባልንጀሮቻችንን እንደምንወድ እናሳያለን።

የቀዱስ መጽሐፍ ታሪክ

ችግረኞችን ስለ መርዳት ለኖኝ ያለውን እንዲሰሙ ወጣት ወንዶችን ጠይቀ። ስለ መልካሙ ሰማሪያዊ ታሪክ የተመደበው ወጣት በራሱ ቃላት እንዲናገር አድርግ።

• መልካሙ ሰማርያዊ ለቀሰለው ለአይሁድ ሰው ምን አደረገ?

• በዚህ ምሳሌ ክርስቶስ ምን ያስተምረናል?

• የጾም በኩራትን ማሰባሰብ ችግረኞችን ለመርዳት እንዴት ይረዳናል?

• የጾም በኩራትን ለማሰባሰብ ኃላፊነቱ ሲሰጠን እንዴት ማድረግ አለብን?

ታሪክ

ከብዙ ዓመታት በፊት የጾም በኩራትን ስለ አሰባሰበው ወጣት የሚከተለውን ታሪክ ተናገር። ስለዚህ ጥሪ እርሱ እና ቤተሰቡ እንዴት እንደተሰማቸው ምሳሌ ያገኙ እንደሆን ለማየት ወጣት ወንዶች እንዲሰሙት አድርግ።

አንድ ጋሪ ሙሉ የጾም በኩራት

"በዲያቆንነት ከተሾምኩ ከአሥር ደቂቃ በኋላ በቤተክርስቲያን ሥራ ላይ ተመድቤ ነበር።

" 'በሚቀጥለው ቀዳሚ የጾም በኩራትን ለመሰብሰብ ከፍሬድ ኤድዋርድ ጋር ትሄዳለህ። ጠዋት በአራት ሰዓት ፍሬድን ወንድም ፒርሰን ዘንድ አግኘው። ወደ ሥራህ ካዘነበልክ እና ብዙ ካልተጫወትክ፣ እስከ ምሣ ሰዓት ትጨርሳለህ።'

"— በደስታ ወደ ቤት ሮጥኩኝ እናም ስለ ሥራው ለእናቴ ነገርኳት . . ."

• ሥራውን በተቀበለ ጊዜ የወጣቱ አመለካከት እንዴት ነበር?

"በሰኞ እና ቀዳሚ መካከል ረጅም ጊዜ መሰለ። በከፊሎቹ ጊዚያት በመሆን ስጠባበቀ እናም በከፊሎቹ ጊዚያት በመፍራት ስጠብቀ ነበር። ለጾም በኩራት ስጠይቀ እየለመነ ነው ብለው ለባላት እንደማያስቡ ተስፋ አደርግ ነበር።

"የጾም በኩራት (እና አሥራት) ዘወትር *በዓይነት* ይሰጡ ነበር። ያም ማለት የቤተክርስቲያን አባላት ያመረቱትን ወይም ያዘጋጁትን ዕንቁላሎች፣ ቀቤ፣ ዱቄት፣ ዳቦ፣ አትክልት፣ ወይም ማንኛውንም ይሰጣሉ. . . .

"የወንድም ፒርሰን ቤት ሦስት ረድፍ ርቀ ቢገኝም እና እስከ አራት ሰዓት እዚያ መድረስ ባይኖርብኝም፣ እናቴ በአንድ ሰዓት ቀሰቀሰችኝ። በተለምዶ መጀመሪያ እንደተነሳሁ ገላዬን እታጠብ ነበር፣ ሆኖም ግን በዚያን ቀን ለረፋዱ አስተላለፍኩኝ። ከዚያም በኋላ ጫማዬን እንድጠርግ አዘዘችኝ፣ ነገር ግን እንዳደርጋቸው አልፈቀደችልኝም ወይም አዲስ ቱታዬን እስክሄድ ድረስ እንድለብስ አልፈቀደችልኝም። ማድረቂያ ከተጨመረበት ነጭ ሸሚዜ፣ ከደረቀ ቱታዬ እና ከጥብቀ የሰንበት ጫማዬ ጋር ለመሄድ የተዘጋጀሁኝ መሰለኝ። ነገር ግን አልሆነም። ክራባትን እንዳስር አደረገችኝ!

" ' . . . ትሁት መሆንህን እርግጠኛ ሁን። በኩራትን በምትጠይቀበት ጊዜ "እባክህን" በል እናም በሚሰጡህ ጊዜ "አመሰግናለሁ" በል . . . እህት ስኩልዝ እቤት ካለች፣ ልትረዳት የምትችለው ነገር እንዳለ ጠይቃት . . .' "

• "ስለ ጾም በኩራት የወጣቱ እናት ምን ይሰማታል ብለህ ታስባለህ?

"መጀመሪያ የሄድንበት ቤት ከወንድም ፒርሰን አንድ ብሎክ ቀጥሎ ወዳለው ወደ ወንድም ዮሐንስ አንደርሰን ቤት ነበር— እህት አንደርሰን ስናንኳኳ መጣች።

" 'ከፍሬድ መስፈሪያውን በመቀበል ላይ እንዳለች "'ደህና፣ ደህና፣ አዲስ ዲያቆን አለን፣ የለንምን? አለች፣ 'ቤተሰብህ እንዴት ነው፣ ክሪስ? እናም ያንተስ እንዴት ነው፣ ፍሬድ?'

"መልስ ከመስጣችን በፊት፣ ወደ ቤት ገባች፣ እናም መስፈሪያ ሙሉ ዱቄት ይዛ ተመለሰች።

"ፍሬድ የማስታወሻ ደብተር እና እርሳስ አውጥቶ 'እህት አንደርሰን፣ ሁለት ዶንያ ዱቄት' ብሎ ጻፈ፣

"አሁን በኤድ ፒተርሰን በር ደጃፍ ላይ ነበርን። በማንኳኳቴ እና ለጥያቄዬ መልስ እህት ፒተርሰን የጓጉለን የልብስ ዶንያ ሰጠችኝ።

" 'ይኸውና ደርዘን ሙሉ እንቁላል. . . .'

“በሚቀጥለው የስም ዝርዝራችን ላይ ጆን ጃኮብሰንስ ነበሩ። አዲስ ሙሽሮች ናቸው. . . .

“ ‘ይህ አሁን የጋገርኩት ዳቦ ነው፣’ አለች፡፡ በዶንያው ውስጥ የዳቦው ሙቀት ይሰማኛል።

“በመቀጠልም በዝርዝራችን ላይ ያለው ጆርጅ ፒተርሰን እና ከዚያም ጆርጀን አልሰን ነበሩ፡፡ ሁለቱም ጥቂት ዱቄት ሰጡን፡፡

“የመጨረሻው ቦታችን የእህት ሴና ስኩዝ ቤት ነበር . . . ‘ልጆች ግቡ፡፡ በእርግጥ ለእናንተ አንድ ነገር አለኝ፣ ነገር ግን ከማምጣቴ በፊት ትንሽ ልትረዱኝ ትችላላችሁ?’

“ ‘በእርግጥ፣ ይመስለኛል፡፡ ምንድነው እሱ?’

“ ‘ከለማዳ ጠቦቶቼ መሀከል አንደኛው ከጉሮኖው አምልጧል እናም ብቻዬን ልመልሰው አልቻልኩኝም፡፡ አሁን ፍሬድ በቀራጭ መሬቱ ሰሚን ምስራቅ መዓዘን ላይ ከቆምክ እና ክሪስ አንተ በሌላ በኩል ከቆምክ በመከከላችን አስፈራርተን ወደ ጉሮኖው ልንመልሰው እንችላለን፡፡

“ፍሬድ እና እኔ እጃችንን ማወራጨት መጮህ ጀመርን፡፡ እህት ስኩልዝ ሽርጧን ማወራጫት እና ‘ሹ! ሹ!’ እያለች መጮኽ ጀመረች!’

“ጠቦቱ መጫወት እንደፈለግን አድርጎ ያሰበ ይመስላል፡፡ በትንሿ መሬት ውስጥ ወዲያ ወዲህ ይሮጣል። አንዴ ለጥቂት ጊዜ ጭራውን እቁሞ በአየር ላይ ይዘላል፡፡ ያን ጠቦት በመዓዘን ላይ ከበን እና ገፍተን ወደ ጉሮኖው ለመመለስ ግማሽ ሰዓት ወሰደብን፡፡

“ ‘ኦ አመሰግናለሁኝ፣ ልጆች . . .’

“ ‘ኦ፣ ትንሽ ጠብቁ፡፡ አንድ ነገር ረሳሁኝ፡፡’ ወደ ሽርጧ ኪስ ገባች እና ሁለቴ የተጣጠፈ፣ በላስቲክ የተጠቀለለ ፖስታ አወጣች፡፡ ‘አሥር ሳንቲም የጾም በኩራት ከሴና ሱኩልዝ።’ የሚል ከውጭ ተጽፏል፡፡’

“ ‘ወደ ወንድም ፒተርሰን ቤት ተመልሰን እየኼድን ሳለ ‘እርሷ ሁልጊዜ ለእኛ አንድ ነገር አላት፣’ አለ ፍሬድ፡፡

“ወንድም ፒተርሰን መዝገባችንን አየ፡፡ ‘እስቲ እንይ ስምንት ፓውንድ ዱቄት፣ አንድ ደርዘን እንቁላል፣ ትኩስ ዳቦ እና ሰላሳ አምስት ሣንቲም በገንዘብ. . . .ይህንን በመሰብሰባችሁ አንድ ችግረኛ ሰው እንደሚደሰትባችሁ እርግጠኛ ነኝ’ ” (Chris Jensen, “A Wagonful of Fast Offerings,” *Ensign*, ሐምሌ 1978, ከገጽ 34–36)፡፡

ውይይት

• ስለ ጾም በኩራት በጐ አመለካከት እንደነበረው ለማሳየት ክሪስ ምን አደረገ? የጾም በኩራትን ስለ መሰብሰብ መልካም አመለካከት እንዲኖረን ምን ምን ነገሮችን ማድረግ እንችላለን?

የሚታደል ጽሑፍ

ለወጣት ወንዶች የመመሪያዎቹን ቅጂ ስጣቸው እና ከእነርሱ ጋር ከልሳቸው እናም መመሪያዎቹን ተወያይባቸው፡፡

የጾም በኩራትን የመሰብሰቢያ መሠረታዊ መመሪያዎች

1. አስደሳች አመለካከት ይኑርህ፡፡ ከጳጳሱ ይህን ሥራ ስታሚላ፣ እንደ ጌታ ወኪል እያገለገልክ ነው፡፡
2. በጳጳስህ እንደ ታዘዝከው፣ አለባበስህ ያማረ ይሁን።
3. በሩን ለምትከፍትልህ ግለሰብ፣ “እንደምን አደርሽ፣ እህት ጆንስ?” በማለት ሰላምታን አቅርብ።
4. ክብርን በተሞላ እና በሚያስደስት ሁኔታ እራስህን አስተዋውቅ፡፡
5. ለምሳሌ፣ “ጳጳስ (ወይም የቀርንጫፍ ፕሬዚዳንት) የጾም በኩራታችሁን እንድቀበል ልኮኛል፡፡” በማለት ዓላማህን ግለጽ።
6. የጾም በኩራትን ፖስታ ለአባል ስጥ፣ እርሱ ወይም እርሷ የጾም በኩራቱን በፖስታው ውስጥ ያስቀምጣል ወይም ታስቀምጣለች፣ መጠኑን በስጦታው ደረሰኝ ላይ ይመዘግባል ወይም ትመዘግባለች፣ ደረሰኙን በፖስታው ውስጥ ያስቀምጣል ወይም ታስቀምጣለች፣ የደረሰኙን ቅጂ ያስቀምጣል ወይም ታስቀምጣለች፣ እናም ፖስታውን ለአንተ ይመልሳል ወይም ተመልሳለች፡፡
7. በጳጳሱ ለተወከለው ሰው ፖስታውን መልስ፡፡

ጠቃሚ የሆኑትን ሌላ ማናቸውንም መመሪያዎች ከወጣት ወንዶች ጋር ተወያይ፡፡

በጨዋታ መልክ የሚቀርብ

አንድን አሮናዊ የክህነት ስልጣን ያዥ ወጣት የጾም በኩራትን በማሰባሰብ ሚናን እንዲወስድ ጠይቀው፡፡ ሌላኛው ሰው የተላከውን ሰው ይወክላል፡፡ በሚከተሉት ሁኔታዎች በሩን ለሚከፍተው ሰው በተገቢው ሁኔታ ለማነጋገር ትክክለኛውን ሁኔታ እንዲገልጹ ጠይቃቸው፣

1. ከጐልማሳ ይልቅ ልጅ በርን በሚከፍትበት ጊዜ (የልጁ እናት ወይም አባት እንዲቀርቡ ጠይቅ።)
2. አባሉ መጥሮ ስሜት ካለው ወይንም የተበሳጨ ከሆነ። (ትሑት ሁን)
3. አዲስ አባላት ምን ያህል አስተዋፅኦ ማድረግ እንደሚገባቸው ማወቅ ይፈልጋሉ። (አነስተኛው መመሪያ የሁለት ምግብ ዋጋ ነው፣ ነገር ግን ለጋሶች እንድንሆን በቤተክርስቲያን እንመከራለን።)

ግንኙነታቸው የፆም በኩራትን ከሚሰበስብ ከቤተክርስቲያን የቤት ለቤት አስተማሪ ወይንም ወጣት ወንድ ጋር ብቻ የሆኑ አንዳንድ ቤተሰብ በዋርዱ ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህም ቤተሰቦች የጾም በኩራትን በሚያሰባስበው ወጣት አመለካከት ጠቀላላ ቤተክርስቲያኗን ሊፈርዱ ይችላሉ። ወጣት ወንዶች የጾም በኩራትን በማሰባሰብ ከእነዚህ ቤተሰቦች የሰማይ አባታቸውን የማገልገል እድል ይሰጧቸዋል።

የአሮናዊ የክህነት ስልጣን ያዦች የታዘዙ የጌታ ወኪሎች ናቸው። ወጣት ወንዶች ሥራቸውን በማሟላት፣ ጌታ ለድሆች እና ለችግረኞች ያለውን እቅድ እንዲያሟላ ይረዳሉ። ታማኝ የአሮናዊ ክህነት ስልጣን ያዦች በዋርድ ውስጥ ለሚገኘው እያንዳንዱ ቤተሰብ በጌታ ሥራ ውስጥ የመሳተፍ እድል በመስጠት ከጳጳሱ ጋር አብሮ የሚሠሩ ይሆናሉ።

---

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት እና ሙከራ

ወጣት ወንዶች የጾም በኩራትን በማሰባሰብ የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ድሆችን እና ችግረኞችን እንዲንከባከቡ እየረዱ መሆናቸውን መስክር። ወጣት ወንዶች ይህን ኃላፊነት አጥብቀው እንዲይዙት እና በሚችሉት አቅም በክብር እንዲያሟሉት አበረታታቸው።

---

# የጾም በኩራትን የማሰባሰቢያ መሠረታዊ መመሪያዎች

1. አስደሳች አመለካከት ይኑርህ። ይህን ጳጳስ የሰጠህን ሥራ ስታሟላ እንደ ጌታ ወኪል እያገለገልክ ነው።
2. በጳጳስህ እንደታዘዘው፣ አለባበስህ ያማረ ይሁን።
3. በሩን ለምትከፍትልህ ግለሰብ "እንደምን አደርሽ እህት ጆንስ?" በማለት ሰላምታን አቅርብ።
4. ክብርን በተሞላ እና በሚያስደስት ሁኔታ እራስህን አስተዋውቅ።
5. ለምሳሌ "ጳጳስ (ወይም የቅርንጫፍ ፕሬዚዳንት) የጾም በኩራታችሁን እንድቀበል ልኮኛል።" በማለት አላማህን ግለፅ
6. የጾም በኩራትን ፖስታ ለአባል ስጥ፤ እርሱ ወይም እርሷ የጾም በኩራቱን በፖስታው ውስጥ ያስቀምጣል ወይም ታስቀምጣለች መጠኑንም በስጦታው ደረሰኝ ላይ ይመዘግባል ወይም ትመዘግባለች፣ ደረሰኙን በፖስታው ውስጥ ያስቀምጣል ወይም ታስቀምጣለች የደረሰኙን ኮፒ ያስቀምጣል ወይም ታስቀምጣለች፣ እናም ፖስታውን ለአንተ ይመልሳል ወይም ትመልሳለች።
7. በጳጳሱ ለተወከለው ሰው ፖስታውን መልስ።

# በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን

# 5

**ዓላማው**

እያንዳንዱ ወጣት በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ለአሮናዊ የክህነት ስልጣን ያዥ ጠቃሚ እንደሆን እና በህይወቱም ጠቃሚ ውጤት እንዳለው በበለጠ በሙላት ይረዳል፡፡

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሣሪያዎች፥
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት ቅዱሳን መጻሕፍት፡፡
   ለ. ለእያንዳንዱ ወጣት የመዝሙር መጽሀፍ፡፡
2. (በአማራጭነት፡፡) "አዳኜ እንዳለ አውቃለሁ" የሚለውን መዝሙር የያዘውን ካሴት አዘጋጅ (*መዝሙር* ቁ 136)፡፡
3. ከቀዳማዊ ሳሙኤል 17 አንድ ወጣት የዳዊትን እና የጎሊያድን ታሪክ እንዲያዛምድ መድብ፡፡

**ለትምሕርቱ ዕደገት የቀረበ ሐሳብ**

**ቀዳሚ የወንጌል መሠረታዊ መርህ፥ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማመን**

ታሪክ

የሚከተለውን ታሪክ አንብብ፥

ኤለን እንደ ድንገት ተነስታ አንድ ነገር ስህተት እንደነበር ተረዳች። ቤቱ ፀጥ ብሎ ነበር፡፡ በፀጥታው መሀል አዳመጠች እናም አደጋው ምን ሊሆን እንደሚችል ለማወቅ ሞከረች፡፡ በደቂቃ ውስጥ አደጋው ምን እንደሆነ አወቀች። እናም የእኩለ ሌሊት ፀጥታውን በመሰባበር ጩኸቷን አቀለጠች። "ጭስ! እናቴ! ሮብ! ትሬሲ! ጭስ እየሸተተኝ ነው!" ወደ መኝታው ክፍል አመራች እናም የመዝጊያ መክፈቻውን ለመያዝ እጇን ዘረጋች። ስትነካው የጋለ ነበር። በበሩ ጣሪያ ስር ወፍራም ጭስ በቀስታ ያልፋል። እያሰቃየ በማስጨነቅ ወደ አፍንጫ ቀዳዳዋ እና ሳንባዋ ገባ። በሌላኛው አቀጣጫ ባለው በተዘጋው በር በኩል ወላፈን ይቀጣጠላል። ተጠመደች።

በክፍሉ ራቅ ባለው ጉን ወደ ትንሿ መስኮት በዳሰሳ ተጓዘች፡፡ አሁን ክርቀት የእሳት አደጋ መኪና እና የድምጽ ጩኸት ተሰማለች፡፡ "ቶሎ በል . . . ኦ፥ እባክህ ፍጠን፥" በትንሹ አለቀሰች፡፡ ቤተሰቦቿን . . . እናቷን፥ ትንሿን ትሬሲን እና ሮብን ማሰብ ስትጀምር ለጊዜው ስለ እራሷ ህይወት ፍራቻ ለቀቃት፡፡ አባታቸው ላይ አደጋ ከደረሰ በኋላ ለኤለን ታላቅ ወንድም እና አባት የሆነው ተወዳጁ ሮብ ነበር፡፡ እነርሱስ ለማምለጥ በጊዜ ተነሱ ወይንስ በእሳት እና ፍም ግድግዳ ጀርባ በጣም ተጣበቁ?

በመስኮት ቀዳዳ የሚገባው የለሰለሰና የቀዘቀዘው ምሽት አየር ፊቷን ያቀዘቀዘው ዘንድ ወደ ለስላሳውና፥ ልትከፍተው ወደምትችልበት መስኮት ቀረበች። ከታች በፍርሃት አንጋጠው የሚያዩትን ሰዎች ድምጽ ትሰማለች፡፡ ኤለን የቻለችውን ያህል በትንሿ መስኮት ላይ ተደገፈች፡፡ "እርዱኝ! እርዱኝ፥ እባካችሁ!"

"ተመልከት! እዚያ ከፍታ ላይ ያለው መስኮት ውስጥ አንዲት ልጃገረድ አለች!" በማለት አንዲት ሴት ጮኸች፡፡ የሚጮኸው የእሳት አደጋ መኪና ወደ መሄጃው ተጠጋ፡፡ ኤለን፥ . . . "ሄይ አንቺ! . . . እዛ ላይ! መረብ ለቀናል፡፡ ወደ እርሱ ዝለይ፡፡ ቀጥ ብለሽ ዝለይ። ጣሪያው በጥቂት ጊዜ ውስጥ ሊደረመስ ነው!" የሚልን የአንድ ሰው ድምፅ ሰማች። ኤለን በጠባቡ መንገድ ውስጥ ቀዘዘች፡፡ "ዝለይ!" የሰውዬው ድምፅ በድጋሚ በፍጥነት ተጣራ፡፡

ለእሳት መከላከያው ሠራተኛ ጉረቤቷ እንዲህ ብሎ ሲጮህ ሰማች፥ "ልጅቷ እውር ናት! ወዴት እንደምትዘል አታውቅም፡፡" በድንገት ኤለን የሮብን ድምፅ ሰማች፡፡

"ኤለን . . . እኔ ሮብ ነኝ፡፡ ከመስኮትሽ ዝቀ ብዬ ነው ያለሁት፡፡ ዝለይ ኤለን፡፡ እዚህ ነኝ፡፡ እይዝሻለሁ፡፡ ዝለይ!"

ኤለን በጥልቁ ተነፈሰች እናም ቋጠሮዋን በጠባቡ መንገድ ላይ ለቀቀችው፡፡ ከትንሿ መስኮት ጣሪያ እንደተወረወረች "ሮብ እየመጣሁ" ነኝ በማለት በሹክሹክታ ተናገረች።

ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት

• ይህ ታሪክ ስለምን እንደሆነ የሚገልጽ አንድ ቃል ምንድን ነው? (እምነት፡፡)

*እምነት* የሚለውን ቃል በጥቁር ሰሌዳው አናት ላይ በግራ በኩል ላይ ጻፍ፡፡

• ኤለንን በተመለከተ፥ በእሳት መከላከያው ሠራተኛ እና በሮብ መካከል ያሉት ልዩነቶች ምንድን ነበሩ? (ወንድሟን ታውቅ ነበር እናም በእርሱ እምነት ነበራት፡፡)

**መድገም**

ወጣት ወንዶች አራተኛውን የእምነት አንቀጽ እንዲደግሙት አድርግ፡

“የመጀመሪያዎቹ የወንጌል መርሆች እና ሥርዓቶች፣ አንደኛ፣ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማመን፤ ሁለተኛ፣ ንስሐ፤ ሶስተኛ፣ ለኃጢያት ሥርየት ውኃ ውስጥ በመጥለቅ መጠመቅ፤ አራተኛ፣ እጅን በመጫን መንፈስ ቅዱስን መቀበል ናቸው” (የእምነት አንቀጾች 1፥4)።

በጥቁር ሰሌዳው ላይ *እምነት* ከሚለው ቃል በመቀጠል በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለውን ጨምርበት።

• በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ለምን በጣም አስፈላጊ ሆነ? (ከኃጢአታችን ንስሐ መግባት የምንችለው እና ክርስቶስን መምሰል የምንችለው በእምነት አማካኝነት ብቻ በመሆኑ።)

ሁላችንም ኃጢአትን እንደሰራን፣ ነገር ግን እንድንነጻ ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ እንደተሰቃየ ግለጽ። በመታዘዝ እና ንስኃ በመግባት በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት በማሳየት ብቻ ከኃጢያታችን ይቅርታን ማግኘት እና ወደ ሰማይ አባታችን ዘንድ መመለስ እንችላለን።

**የቅዱስ መጽሐፍ ታሪክ እና ውይይት**

አንድ ወጣት የዳዊትን እና የጎሊያድን ታሪክ በእራሱ ቃል እንዲናገር አድርግ (ሳሙኤል ቀዳማዊ 17 ተመልከት)።

ወጣት ወንዶች ሳሙኤል ቀዳማዊ 17፥26 እንዲያነብ አድርግ።

• ጎሊያድ እስራኤልን ሲገዳደር ዳዊት ለምን ተደነቀ? (በዳዊት እምነት ምክንያት የእስራኤል ጦር የህያው አምላክ ጦር ነበር።)

ወጣት ወንዶች ሳሙኤል ቀዳማዊ 17፥28–29 እንዲያነቡ አድርግ።

• ጎሊያድን ለመዋጋት በጎቹን ትቶ ሲሄድ ታላቁ ወንድሙ ኤሊያብ በተቆጣው ጊዜ የዳዊት መልስ ምንድን ነበር? (“ምክንያት የለምን?”)

ወጣት ወንዶች ቀዳማዊ ሳሙኤል 17፥36–37፣ 40፥46–49 እንዲያነቡ አድርግ።

የጎሊያድን መገዳደር በመቀበል በጌታ ታላቅ እምነት ስላሳየው ዳዊት ያለህን ስሚት ግለጽ። ዳዊት ወጣት ቢሆንም እንኳን ጎሊያድን ተዋግቶ ድልን ተቀዳጅቷል።

• በህይወታችን ውስጥ እንደጎሊያድ የሚከሰተብን የትኛው ችግር አለን?

የጓደኛ ግፊትን እንደመቋቋም፣ አስቸጋሪ የትምህርት ቤት ትምህርትን በስኬታማነት ማጠናቀቅ፣ የአንዳንድ ቅዱሳን መጻሕፍት ጥቀሶችን ትርጉም ማንበብ እና መረዳት፣ አዲስ ስፖርትን እንደመማር፣ አዲስ ጥበብን እና ሙያን እንደመማር፣ ትልቅ መጽሐፍን እንደማጠናቀቅ፣ እና የክህነት ስልጣን ኃላፊነታችንን ቀላል አድርጎ ለለመቀበል ስለ መሳሰሉት ፈታኝ ሁኔታዎች ለወጣት ወንዶች አስታውሳቸው።

እያንዳንዳችን በህይወታችን ውስጥ እንቅፋት እንደሚገድጥመን ግለጽ። ዳዊት የነበረው ጽናት እና እምነት ካለን፣ ውጤቱ ተመሳሳይ ይሆናል።

**ጥቅስ**

እምነትን በተመለከተ ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል የተናገሩትን አንብብ፡

“የዛተባችሁን ጎሊያድን ታገኛላችሁ። የእናንተ ጎሊያድ የከተማ በጥባጭ ወይም ለመስረቅ ወይም ለማጥፋት የሚፈታተን ወይም ለመዝረፍ ሙከራ የሚያደርግ ወይም የመሳደብ እና የመማል ፍላጎት ያለው ቢሆንም፤ የእናንተ ጎሊያድ ግብረገብነትን በማጣት ጥፋትን መፈጸም ወይም በማመንዘር ፈተና ውስጥ መውደቅ እና ኃጢያትን መፈጸም፣ ወይም ሥራን የማስወገድ ግዴታ፣ ማንኛውም ነገር ሊሰየፍ ይችላል። ነገር ግን አስታውሱ፣ ድልን ለመቀዳጀት፣ አንድ ሰው ዳዊት የተከተለውን መንገድ መከተል አለበት፣

“‘ዳዊት በመንገዱ ሁሉ እራሱን በብልሃት መራ፤ ጌታም ከእሱ ጋር ነበር’ (ቀዳማዊ ሳሙኤል 18፥14)” (በ Conference Report, ጥቅምት 1974, ገጽ 116; or *Ensign*, ህዳር 1974, ገጽ 82)።

**ውይይት**

• በህይወታችን ውስጥ ያለውን ጎሊያድን ለመቋቋም ምን ማድረግ እንችላለን?

ወጣት ወንዶች ሐሳባቸውን እንዲወያዩ ጊዜ ስጣቸው። የሚከተሉትን ሐሳቦች ትኩረት ስጥባቸው፣ ከቤተሰብ፣ ከጓደኞች፣ እና ከቤተክርስቲያን መሪዎች እርዳታን መሻት፣ ችግርን በሚገባ ማጥናት እና ለውሳኔ ጽናት መጸለይ፤ ጌታ እንዲመራን እና እንዲገልጥልን ቅዱሳን መጻሕፍትን ማጥናት፤ መጸለይ እና መጾም።

---

## ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ የሚያምኑትን ይባርካቸዋል

**ታሪክ እና ውይይት**

በጳጳስ ኤች ቡርክ ፒተርሰን የጻጻሳት መሪ የተነገረውን የሚከተለውን ታሪክ በኢየሱስ ክርስቶስ የማመን ኃይል እውነተኛ ምሳሌ እንደሆነ ግለጽ፣

“ከጥቂት ዓመታት በፊት በዩ. ኤስ የዋርድ ጳጳስ ነበርኩኝ። የኋለኛው ቀን ቅዱሳን መሆን የሚገባቸው መልካም ምሳሌ የነበሩ የወጣቶች ቡድን በዋርዳችን ውስጥ ነበረን። በወጣትነት ዕድሜ ውስጥ የምትገኘውን አንዲት የቤተክርስቲያን አባል ያልሆነችን ልጃገረድ ያገኛታል። ይህች ወጣት ልጃገረድ ደንቆሮ ነበረች፣ ነገር ግን በዓይኗ የከንፈርን እንቅስቃሴ በማየት ማንበብን ተምራለች፣ እናም ከፊትለፊቷ ቆማችሁ ብታናግሯት፣ ከንፈራችሁን በማንበብ የምትሉትን ነገር መናገር ትችላለች። እናም ደግሞ የልብ ህመም ነበረባት። ከሌሎች

ልጃገረዶች ጋር በማንኛውም የአትሌቲክስ ውድድር መሳተፍ አትችልም ነበር፡፡ የሞርሞን ወንዶች እና ልጃገረዶች ለእርሷ ጎደኞች፣ አዛኝ፣ እና ሁኔታዎቿን የተረዱ ነበሩ፡፡ እንክብካቤያቸውን ወደደችው፡፡ ምሳሌያቸውን ወደደችው፡፡ ወዲያውም ሚሲዮናዊያን የሚሰጡትን ትምህርት ለመስማት ተጋበዘች፡፡ ትምህርቱም እንዳበቃ ስትማር የቀየችውን አመነች እናም ተጠመቅ ዘንድ ቤተሰቦቿ እንዲፈቅዱላት ጠየቀች፡፡ እነርሱም ደግሞ ትምህርቱን ሰሙት፣ ነገር ግን እርሷ እንደተቀበለችው እውነታውን አልተቀበሉትም፡፡ ሆኖም ግን፣ እንድትጠመቅ ለእርስዋ ፈቃድ ሰጧት።

“አንድ ቀን ቀዳሚ ከሰዓት ይህች ዲዳ ወጣት ልጃገረድ ወደ ውሃው ስትገባ በመጠመቂያው ገንዳ ዙሪያ ተሰባሰብን፡፡ ከጥምቀቱ በኋላ የቤተክርስቲያኑ አባል ትሆን ዘንድ ማረጋገጫ ሊሰጣት ነበር፡፡ ቄሶቹ በክቡ ዙሪያ መቆም አፈልግ እንደሆን ጠየቁኝ፡፡ እንደተጠየቅሁኝም አደረግሁ። ከንፈሩን ማየት ስለማትችል ከቄሱ የሚሰጡትን የማረጋገጫ ቃላት እና በረከት መስማት እንደማትችል አውቃለሁኝ፣ ስለዚህ ቄሱ የቤተክርስቲያኑ አባልነትን ሲያረጋግጥላት ቡራኬውን በጥሞና ሰማሁኝ፡፡ በመጨረሻም እርሱ የተናገረውን ነገር ልነግራት ፈለግሁኝ፡፡

“ቡራኬው በቄሱ ተሰጠ፡፡ ይቻላሉ ብዬ የማላምናቸውን ነገሮች ስለተናገረ በሰማሁ ጊዜ ጆሮዬን አላመንኩኝም፡፡ እርሱ የሰጠውን ቡራኬ ጌታ እንደሚሰጥ ሙሉ እምነት ነበረኝ፡፡

“ከማረጋገጫው እና ከቡራኬው በኋላ ወደ ቢሮዬ እንድትመጣ ወጣቷን ሴት ጋበዝኳት፡፡ አሁን ቄሱ የሰጣትን በረከት ልነግራት ስዘጋጅ ከፊት ለፊቴ ተቀመጠች፡፡ እንዲህ አልኩኝ፣ ዶናንሲ፣ ቄሱ ስለሰጠሽ ቡራኬ ልነግርሽ እፈልጋለሁኝ፡፡’ ወደ እኔ ተመለከተች እና እንዲህ አለች፣ ‘ጳጳስ ፒተርሰን፣ ቡራኬውን ሰምቻለሁኝ፡፡’ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ናንሲ ፉለር መስማት ቻለች፡፡ ደንቆሮ ሆና አልቀረችም ነበር፡፡ ልቧም ደግሞ ስለተፈወሰ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የመረብ ኳስ፣ ሶፍት ኳስ፣ እና ቴኒስ መጫወት ትችላለች” (በ Conference Report, Korea Area Conference 1975, ገጽ 25)፡፡

- ናንሲ ፉለርን ያዳናት ኃይል ምንድን ነው? (ከእምነቷ እና ከቄሱ እምነት ጋር የክህነት ስልጣን ኃይል ነው፡)
- በኢየሱስ ክርስቶስ እምነታችንን እንዴት ማጠናከር እንችላለን?

የወጣት ወንዶችን መልስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ፡፡

---

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት

በእያንዳንዱ ወጣት ህይወት ውስጥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ያለውን ኃይል በግል በመመስከር ትምህርቱን መፈጸም ትችላለህ፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ የህይወትን ፈተናዎች አልፈን ወደ ሰማይ አባታችን መመለስ እንደምንችል መስክር፡፡

የቴፕ ቀጂ

“አዳኜ እንዲኖር አውቃለሁኝ” የሚለውን የመዝሙር ቀጂ በሚያዳምጡበት ጊዜ ወጣት ወንዶች ስለ አዳኛችን እንዲያስቡ ጠይቀ፡፡ የመዝሙር መጽሐፍትን ልታከፋፍላቸው እና ከቃሉ ጋር አብረው እንዲሄዱ ማድረግ ትችላለህ ወይንም ይህን መዝሙር መዘመር ወይም ቃሉን መደጋገመ ይችላሉ፡፡ መዝሙሩን በሙሉ እንዲያጠኑት አበረታታቸው፡፡

# መንፈስ ቅዱስ

# 6

**ዓላማው** እያንዳንዱ ወጣት የመንፈስ ቅዱስን የቀርብ ጓደኝነትን ያዳብራል እናም ከግፊቱም መጠቀምን ይማራል፡፡

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፡
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጻሕፍት።
   ለ. ሁለት እርሳሶች እና ሁለት ወረቀቶች፡፡
   ሐ. አንድ አምፑል፡፡
2. እያንዳንዳቸውን የሚከተሉትን ጥቅሶች በተለያየ ወረቀት ላይ ጻፋቸው፡፡ እጠፋቸው እና ሁሉንም በዕቃ መያዣ ውስጥ ጨምራቸው፡፡ የእያንዳንዱን ጥቅስ ማጣቀሻ ተከታዩን አባባል ለትጨምር፡፡ እነዚህ ጥቅሶች ለአንተ እንደአማካሪ ይጠቀሙኃል፤ እያንዳንዱን ጥቅስ በምትወያይበት ጊዜ በትምህርቱ ውስጥ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፋቸው፡፡

1ኔፊ 10፥17፡፡ (መንፈስ ቅዱስ ራእዮች የሚታዩበት ኃይል ነው፡፡)
1 ኔፊ 10፥19 (እርሱ ሚስጥራትን ይገልፃል።)
1ኔፊ 10፥22 (እርሱ ስለ እውነት ይመሰክር ዘንድ ስልጣንን ይሰጣል፡፡)
2ኛ ኔፊ 31፥12 (ከተጠመቅን በኋላ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን እንቀበላለን፡፡)
2ኛ ኔፊ 32፥5 (ማድረግ የሚገቡንን ነገሮች ሁሉ ያሳየናል፡፡)
2ኛ ኔፊ 32፥8 (እርሱ እንድንጸልይ ያስተምረናል፡፡)
አልማ 5፥46፡፡ (እርሱ ስለ እውነት ይመሰክራል፡፡)
ሂለመን 5፥45–47፡፡ (እርሱ የሰላምን ስሜት ይሰጣል፡፡)
ሞሮናይ 8፥26፡፡ (እርሱ አጽናኝ ነው፡፡)
ሞሮናይ 10፥5፡፡ (እርሱ የሁሉንም ነገሮች እውነታ ያስተምራል፡፡)
ሞሮናይ 10፥8፡፡ (እርሱ የመንፈስ ስጦታዎችን ይሰጣል፡፡)

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች**

የቅዱስ መጽሐፍ ፍለጋ

ወጣት ወንዶችን በሁለት ቡድን ክፈላቸው እና ለእያንዳንዱ ቡድን እርሳስ እና ወረቀት ስጥ፡፡ ማጣቀሻውን የያዙት ወረቀቶች በሙሉ ለቡድኑ እኩል እስኪከፋፈሉ ድረስ እያንዳንዱ ቡድን ተራ በተራ የተጠቀለለውን ወረቀት ከዕቃ መያዣው ውስጥ እንዲያወጣ አድርግ፡፡ ምልክት ሲሰጥ፣ እያንዳንዱ ቡድን ማጣቀሻውን ማየት እንዲጀምር አድርግ፡፡ ወጣት ወንዶቹ ጥቅሶቹን ሲያመለክቱ እና ሲያነቡ ጥቅሶቹ ስለ ማን እንደሚናገሩ መወሰን እና ይህ ሰው የሚያደርገውን የሚገልጹ ጥቂት ቁልፍ ቃላቶችን መጻፍ አለባቸው፡፡ ሁለቱም ቡድኖች ሲጨርሱ ትምህርቱን ቀጥል፡፡

- እነዚህ ጥቅሶች ስለ ማን ይናገራሉ? (ስለ መንፈስ ቅዱስ፡፡)

ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት

ከጥቁር ሰሌዳው አናት ላይ *መንፈስ ቅዱስ* የሚለውን ቃል ጻፍ። የእያንዳንዱን ጥቅስ ማብራሪያ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ጻፍ እናም መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ እያንዳንዱ ጥቅስ ምን እንደሚል ሁለቱም ቡድኖች እንዲገልጹ አድርግ። እያንዳንዱን አባባል ከሚያመለክተው ማጣቀሻ ጋር ጻፍ።

**የመንፈስ ቅዱስ ጓደኝነትን ማግኘት**

ታሪክ

የሚከተለውን ታሪክ አንብብ፡

በወርሃዊ ፆም እና ምስክርነት ስብሰባ ውስጥ፣ አንድሪው ታናሽ ወንድሙ ብሬን፣ የቤተክርስቲያን አባልነቱ ሲረጋገጥለት አይቶ ነበር። የማረጋገጫው የጸሎት ቃላት፣ “መንፈስ ቅዱስን ተቀበል” የሚሉት በተለይም ለብሬን አስደንቀውታል። ቢሆንም አባልነቱ ከተረጋገጠለት በኋላ በፊት ከነበረው ምንም ልዩ ስሜት ስላልተሰማው በእውነት መንፈስ ቅዱስን መቀበሉን አንዳላሰበ ለአንድሪው አወያየው።

ጥቀስ እና ውይይት

• እናንተ አንድሪውን ብትሆኑ ኖሮ መንፈስ ቅዱስ መቀበልን ለወንድማችሁ እንዴት ትገልጹ ነበር?

ይህን ጥያቄ ወጣት ወንዶች እንዲወያዩበት አድርግ። ከዚያም በፕሬዚዳንት ማሪዮን ጂ ሮምኒ የተጠቀሰውን ጥቀስ አንብብ፣

“የቤተክርስቲያኗ አባላት የሆንን እያንዳንዳችን እጆች በራሳችን ላይ ተጭነዋል፣ እናም ሥርዓቱ እንደሚሰጠው መጠን፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተሰጥቶናል። ነገር ግን፣ እንማስታውሰው፣ ማረጋገጫው በተደረገልኝ ወቀት፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ እኔ እንዲመጣ አልታዘዘም፤ እኔም ‘መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል’ ተዘጋጀሁኝ። መንፈስ ቅዱስን ብቀበል እና መመሪያውንም ብከተል፣ በእነዚህ አስፈሪ ጊዜያት ውስጥ ከተጠበቁት እና እንክብካቤ ከተደረገላቸው መካከል እሆናለሁ” (በ Conference Report, መስከረም 1961, ገጽ 60)።

የቤተክርስቲያኗ አባል ለመሆን ማረጋገጫ ሲሰጠን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንቀበላለን፣ ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስን ጓደኝነት እንደማናገኝ አብራራ።

• በመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እና በመንፈስ ቅዱስ ጓደኝነት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

በቁሳዊ የተደገፈ ትምህርት

• የመንፈስ ቅዱስን ጓደኝነት እንዴት ማግኘት እንችላለን?

ለአንድ ወጣት የኤሌክትሪክ አምፑል ስጠው እና እንዲያበራ ጠይቀው።

• የኤሌክትሪክ አምፑል እንዲበራ ለማድረግ ምን ማድረግ አለብን?

ወጣት ወንዶች የኤሌክትሪክ መብራትን በቤታቸው ለመጠቀም በሚያስፈልጉት ነገሮች ላይ እንዲወያዩባቸው አድርግ። የሚከተሉትን ነጥቦች አሳይ፣

1. ኤሌክትሪኩ ከመቀጠሉ በፊት እንደሚሰራ እምነት ይኑርህ።
2. ቤቱ የኤሌክትሪክ ብርሃን እንዲያገኝ የኤሌክትሪክ ሽቦ ያለው እና የተዘጋጀ እንዲሆን አድርግ።
3. በአገልግሎት ላይ የዋለውን የኤሌክትሪክ ፍጆታ ለመክፈል ገንዘብ ይኑርህ።
4. በቤት ውስጥ ያለውን የኤሌክትሪክ ገመድ ከዋናው የኃይል መስመር ጋር አገናኝ።
5. በትክክል የሚሰራን አምፑል ከማቀፊያዎቹ ጋር አገናኝ።
6. አምፑሉን ከሶኬቱ ጋር አገናኝ እናም አምፑሉን የሚያበራውን ማብሪያና ማጥፊያ አብራ።

• በቤት ውስጥ ኤሌክትሪክን በመጠቀም እና የመንፈስ ቅዱስን ጓደኝነት በማግኘት መካከል ያሉት ተመሳሳይነቶች ምንድናቸው?

ወጣት ወንዶች የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለመቀበል በሚያስፈልገው ነገር በመወያየት ላይ እንዳሉ፣ እኛ ያሉብንን ኃላፊነቶች መረዳታቸውን አረጋግጥ—

1. የመንፈስ ቅዱስን ጓደኝነት መሻት።
2. ስለ መንፈስ ቅዱስ በበለጠ መማር።
3. መንፈስ ቅዱስ እንዲመራን ከልብ በጸሎት መጠየቅ።
4. ለዚህ ለተቀደሰ ጓደኝነት በብቃት መኖር።

---

**መንፈስ ቅዱስን መስማት እና ከእርሱ ግልጋሎትን ማግኘት**

የማሰላሰያ ጥያቄዎች

የመንፈስ ቅዱስን ተጽእኖ መገንዘብ አንዳንድ ጊዜ አስቸጋሪ እንደሆነ ለወጣት ወንዶች ለይተህ ግለጽላቸው። የሚከተሉትን የማሰላሰያ ጥያቄዎች ጠይቀ፣ ነገር ግን ወጣት ወንዶች ጮክ ብለው እንዳይመልሱት አድርግ።

• መንፈስ ቅዱስ እንዴት ምሪትን ይሰጣል?
• የመንፈስ ቅዱስን ተፅእኖ እንዴት መገንዘብ እንችላለን?
• በመንፈስ ቅዱስ እየተመራን መሆናችንን እንዴት ማወቅ እንችላለን?
• ትክክለኛ ውሳኔ ማድረጋችንን፣ እንዴት እናውቃለን?
• የተሳሳተ ውሳኔ ብንፈጽም፣ እንዴት እናውቃለን?

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

መንፈስ ቅዱስ ሊመራን የሚችልበት ብዙ የተለያዩ መንገዶች እንዳሉት አስረዳ። ለመጽሐፈ ሞርሞን ትርጓሜ የነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ ጸሐፊ የነበረው ኦሊቨር ካውድሪ፣ የሚረዱት ጥቂት መመሪያዎች ተሰጥተው ነበር።

አንድ ወጣት ትምህርት እና ቃል ኪዳን 9፥7–9 እንዲያነብ እና ሌሎቹ ቅዱሳን መጸሐፍቶቻቸው ውስጥ እነኚህን ጥቅሶች ምልክት እንዲያደርጉባቸው ጠይቅ።

• ለአንድ ችግር ከጌታ መልስን በምንፈልግበት ጊዜ፣ ይህ ጥቅስ ምን ማድረግ እንዳለብን ይነግረናል? (በአዕምሮአችን ውስጥ ጥያቄውን ማጥናት እና ውሳኔ መፈጸም። ከዚያም ውሳኔአችን ትክክለኛ መሆኑን በጸሎት መጠየቅ።)

• ትክክለኛ ውሳኔ መፈጸማችንን እንዴት እናውቃለን? (ትክክለኛ ውሳኔ ከፈጸምን በውስጣችን የመቃጠል ስሜት ይሰማናል። የተሳሳተ ውሳኔን ካደረግን የአዕምሮ መረበሽ ይኖረናል።)

ጥቅስ

በቄስ ማሪዮን ጂ ሮምኒ የተሰጠው የሚከተለው ንግግር በመንፈስ እንዴት እንደምንመራ በሰፊው እንደሚገልጽ ለወጣት ወንዶች ይንገራቸው፣

“አሁን ወንድሞቼ እና እህቶቼ፣ መንፈስን መሻት አለብን። እውነተኛ መሪ እንደሆነም መገንዘብ አለብን። ጌታ መንፈስ እንዳለን. . . . የምናውቅበትን ብዙ ሙከራዎች ሰጥቶናል።

“አሁን፣ እኔ የምነግራችሁ የመንፈስ ቅዱስን አመራር ለመከተል መማር የምትችሉ ከሆነ በህይወታችሁ ውስጥ እያንዳንዱን ውሳኔ በትክክል መፈጸም ትችላላችሁ። ለመንፈስ ግፊት ራሳችሁን በመስጠት ሥርዓትን የምትይዙ ከሆነ ይህን ማድረግ ትችላላችሁ። ችግራችሁን አጥኑ እናም በጸሎት ውሳኔን ፈጽሙ። ከዚያም ያንን ውሳኔ ውሰዱ እናም በቀላል፣ ሁኔታ በታመነ ልመና እንዲህ በሉት ‘አባት ሆይ፣ ትክክለኛ ውሳኔን ለመፈጸም አፈልጋለሁኝ። ትክክለኛ ነገርን ለማድረግ አፈልጋለሁኝ። መፈፀምም ያለብኝ ይህን ነው፣ ይህም ትክክለኛ መንገድ መሆኑን አሳውቀኝ።’ ውሳኔአችሁ እውነት ከሆነ ይህን በማድረግ በውስጣችሁ መቃጠል ይሰማችኋል። ይህን መቃጠል ካላገኛችሁ፣ ውሳኔአችሁን ቀይሩ እናም አዲስ ውሳኔን አቀርቡለት። በመንፈስ መረመድን ከተማራችሁ ስህተትን አትፈጽሙም። ይህን የመቃጠል ስሜት የማግኘት ምስክርነት ምን እንደሆነ አውቃለሁኝ። በመንፈስ የመመራት ሌሎች መገለጦችም እንዳሉም ደግሞ አውቃለሁኝ” (በ Conference Report, መስከረም 1961, ከገጽ 60–61)።

ሁሉም የጽድቅ ውሳኔዎች በሰማይ አባታችን እርዳታ መፈጸም እንዳለባቸው ወጣት ወንዶችን አስታውሳቸው። አዳኛችንም እንኳ የአባቱን ፈቃድ ያልሆነውን ማንኛውንም ነገር አላደረገም ወይም አላለም። (ዮሐንስ 5፥30 ተመልከቱ)።

---

**ማጠቃለያ**

የአማካሪው አቀራረብ

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የቤተክርስቲያን አባልነታቸው ለተረጋገጠላቸው የተሰጠ ታላቅ በረከት እንደሆነ አሳስብ። ለጓደኝነቱ በብቃት ከኖርን፣ በምድር ላይ ተልኮአችንን በተሳካ ሁኔታ እንድንፈጽም ይረዳናል። እኛን በመምራት፣ በመንከባከብ፣ በማጽናናት እና ወደ ክርስቶስ እንመጣ ዘንድ በመርዳት ይህን ይፈጽማል።

ታሪክ

የአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት መማክርት ቄስ ብሩስ አር መኮንኪን መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደረዳቸው የሚገልጸውን የሚከተለውን ታሪክ አንብብ ወይም ተናገር፣

“ከልጅነት ትዝታዎቼ አንዱ በፖም የአትክልት ሥፍራ ውስጥ ፈረስ መጋለቤ ነበር። ፈረሱ ለማዳ እና ጥሩ ሽምጥ ጋላቢ ነበር እናም በኮርቻው ውስጥ ሆኜ ምቾት ይሰማኝ ነበር።

“ነገር ግን አንድ ቀን አንድ ነገር ፈረሴን አስደነገጠው፣ እና በተክል ቦታው ውስጥ ደንብሮ ሮጠ። በጣም ከሚወራጩት እግሮቼ የተነሳ ከኮርቻው ተወረወርኩኝ፣ እናም አንድ እግሬ ተንሸራትቶ እርካቡ ውስጥ ገባ። ከብት ጠባቂ ኮርቻውን ለማሠር በሚጠቀምበት የተበጠሰ የቆዳ ገመድ ላይ በሚያስፈራ ሁኔታ ተንጠልጥዬ ነበር። ክብደቴ የቆዳውን ገመድ መቁረጥ ነበረበት፣ ነገር ግን ለጥቂት ጊዜ ያዘኝ። ሌላኛው ፍርጥጫ ወይም ሁለቱ የፈረስ እርምጃ ቀጭኑን የቆዳ ገመድ ከእጆቼ በመበጠስ ወይም በመንጠቅ እና እግሮቼን በእርካቡ ውስጥ በመጣል ለመቁሰል ወይም ለሞት እንድጎተት አድርጎ ይተወኝ ነበር።

“በድንገት ፈረሱ ቆመ፣ እናም አንድ ሰው ልጓሙን አጥብቆ እየያዘ መሆኑን እና የሚንቀጠቀጠውን እንስሳ ለማቀም እየጣረ መሆኑን አወቀኩኝ። ወዲያውኑ በፍጥነት ወደ አባቴ እቅፍ ገባሁኝ።

“ምን ተከሰተ? ደንብሮ ገደል ሊከተኝ በሚሞክረው ፈረስ ምክንያት ገደል ከመግባቴ በፊት እንዲያድነኝ አባቴን በጥቂት ሰኮንድ ልዩነት ውስጥ ምን አመጣው?

“ወደ ተክል ቦታው ሩጥ!’ ብሎ መንፈስ በሹክሹክታ ሲነግረው፣ አባቴ በቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ ጋዜጣ ያነብ ነበር።

“ለጥቂት ጊዜም ባለማመንታት፣ ለምን እና በምን ምክንያት እንደሆነ ሳያውቅ፣ አባቴ ሮጠ። ለምን እዚያ እንደመጣ ሳያውቅ እራሱን በተክል ሥፍራው ውስጥ አገኘ፣ የሚሮጠውንም ፈረስ በማየት *ይህን ፈረስ ማቆም አለብኝ* ብሎ አሰበ።

“እንደዚያው አደረገ እናም እኔን አገኘኝ። በዚህ ሁኔታ ነበር ከብርቱ ቁስል ወይም ሊከሰት ከሚችለው ሞት የዳንኩት” (“Hearken to the Spirit,” friend መስከረም 1972, ገጽ 10)።

ውይይት

• ቄስ መኮንኪን መንፈስ ቅዱስ እንዴት ረዳው? (መንፈስ ቅዱስ አባቱ የት መሄድ እንዳለበት እና እንዴት እንደሚያድነው በመንገር።)

ለወጣት ወንዶች በመንፈስ የተመራህባቸውን ጊዜያት ንገራቸው እናም እነርሱም በአንፃሩ ያንኑ እንዲያደርጉ ፍቀድላቸው፡፡

ብዙ ሰዎች እነዚህን የመሳሰሉትን ልምዶች ያላቸው መስሎ የማይታያቸው መሆኑን አብራራ፣ ነገር ግን በአመዛኙ ሲገለጥላቸው እና በመንፈስ ቀዱስ በሚመሩበት ጊዜ መረዳትን አልተማሩም።

ምስክርነት እና ሙከራ

ከመንፈስ ቀዱስ መገለጥን ለመቀበል እና ግፊትን ለመስማት እና ለመከተል ብቁ የመሆንን አስፈላጊነት መስክር፡፡

በየዕለት ኑሮአቸው የመንፈስ ቀዱስን ግፊቶች እንዲሰሙ እና ምላሽ እንዲሰጡበት ወጣት ወንዶችን አበረታታ

# “ታላቅ የልብ ለውጥ” 7

**ዓላማው** እያንዳንዱ ወጣት በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት አማካኝነት፣ እራሱን ለመቆጣጠር እና ለማሻሻል ኃይል ማግኘት እንደሚችል ይረዳል።

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፥
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. ብዙ ገመዶች ወይም ረጃጅም ሲባጐዎች።
   ሐ. ለእያንዳንዱ ወጣት እርሳስ እና ወረቀት።
   መ. የሚገኝ ከሆነ፣ *ለወጣቶች ብርታት የሚለውን* ቅጂ ለእያንዳንዱ ወጣት።
2. ለወጣቶች ብርታት *የተሰጡትን ደንቦች ከልሳቸው።*

**ለትምህርት ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

## ድክመታችንን ስንቋቋም ጌታ ያጠናክረናል

**ምሳሌያዊ መግለጫ**

በቡድኑ ፊት እንዲቆም አንድ ጥሩ አቀራረብ እና ቀና አመለካከት ያለውን ወጣት ጋብዝ። አንዳንድ መጥፎ ባህሪዎችን የጀመረውን ወጣት እንደሚወክል ግለጽ። መዘግየትን፣ ማታለልን፣ ስንፍናን እና በተቀደሱ ነገሮች ላይ መሳለቅን፣ መዋሸትን፣ የመሳሰሉትን ባህሪዎች ስትዘረዝር በአንገት፣ በትከሻው እና በሰውነቱ ላይ ገመድ ወይም ሲባጐ ጠምጥም። የመጥፎ ባህሪዎችን ውጤት ለመወከል ገመዱን በብዙ ቦታ ላይ ቋጥር። ብዙ ገመዶችን በወጣቱ ላይ ከጠመጠምክ በኋላ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያይ፣

- መጥፎ በህሪዎች በህይወታችን ውስጥ ምን ተፅዕኖ አላቸው?
- እነዚህን ባህሪዎች እንዴት ማቀም እንችላለን?

በጌታ እርዳታ እራስን መቆጣጠርን በማጎልበት መጥፎ በህሪዎችን ማሸነፍ እንደምንችል ወጣት ወንዶች እንዲረዱት እርዳቸው።

**ጥቅስ**

ራስን መቆጣጠርን የማጎልበትን አስፈላጊነት ለመረዳት የሚከተሉት ሁለት ጥቅሶች ሊረዱን እንደሚችሉ ለወጣት ወንዶች ንገራቸው፣

“ራስን መግዛት . . . ማለት አመች ሆኖ ቢገኝም ባይገኝም መከናወን የሚገባውን ነገር ማከናወን ማለት ነው። ራስን መግዛት ብዙውን ጊዜ የሚነሳሳው በእምነታችን፣ በውስጣዊ ተስፋችን፣ እና በፍላጐታችን ነው”(Robert L. Simpson, “Your 1975 Game Plan,” [ዓመታዊ ንግግር] *Speeches of the Year*, 1975 [Provo: Brigham Young University Press, 1976], ገፅ 321)።

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል ደራሲው ያልታወቀውን ጽሁፍ እንደሚከተለው ይጠቀሱታል፣

“ ‘የሰው ስኬታማነት የሚለካው እራሱን በመግዛቱ ነው፤ የውድቀቱም ጥልቀት የሚለካው እራሱን በመጣሉ ነው. . . .። *በራሱ ላይ የበላይነትን መሰረት መመስረት የማይችል በሌሎች ላይ የበላይነት አይኖረውም። እራሱን የሚቆጣጠር ሰው ንጉስ ይሆናል’* ” (*The Miracle of Forgiveness* [ሶልት ሌክ ከተማ: Bookcraft, 1969], ገጽ 176)።

## ምርጫዎች ውጤት አላቸው

**ታሪክ እና ውይይት**

የሚከተለውን ታሪክ አንብብ ወይም ተናገር። ከእራሳቸው ህይወት ጋር የሚያነጻጽሩበትን መንገዶች ወጣት ወንዶች እንዲያስቡ ጠይቅ።

“አንድ የወጣት ወንዶች ቡድን በአንድ ወቀት ከከተማቸው በላይ ከሚገኙት ተራራዎች ሥር የአሮጌ ከባድ መኪና የተረሳ አካል አገኙ። ከቀርብ ሆነው ሲመረምሩት አራቱ ጎማዎቹ በሙሉ እና መሪው በጥሩ ሁኔታ እንደሚገኝ አወቁ። በጽኑ ፍላጐት ወደ ሳሩ መስከ ትንሽ ዘንበል አድርገው ገፉት እና መርከብ ላይ ጫኑት። አሮጌው መርከብ ወደ መስኩ መጨረሻ ተሻገረ እና ወደ አጥሩ ማቆሚያ ደረሰ።

“ወደ ጐን ከተኛበት ከተከታታይ ሙከራ በኋላ፣ ከወንዶቹ አንዱ ወደ ከተማው የሚያመራው መንገድ ላይ ለማውጣት ሙከራ የማድረግን ሐሳብ ሰጠ። ከቡድኑ ውስጥ ሁለቱ ጥሩ አይደለም ብለው ወሰኑ እናም ሄዱ፣

ነገር ግን ሌሎች ስድስቱ ወደ ውስጥ ገቡ እናም የወላለቀውን ተሽከርካሪው በቀርቡ ወደ አለው መንገድ አስጠጉ። ያንንም በመግፋት፣ ከወላለቀው ክፍሉ እራሳቸውን ከማራቃቸው በፊት ጥቂት ፈጥነው ለመሄድ ቻሉ። ወዲያውም መንገዱ ቁልቁል ወደ ሆነበት ሥፍራ ደረሱ፣ እናም ድጋሚ መግፋት አልነበረባቸውም። ማንም ሰው እንደዚያ ዓይነቱን ኃላፊነት የሚወስድ ያበደ መሆን አለበት ብሎ በማጋነን ተሽከርካሪው ፍጥነቱን ሲጨምር ከወንዶቹ መካከል አንዱ ዘሎ ወረደ።

"የተቀሩት ተሳፋሪዎች አፌዙበት እናም ሳቁበት በዚህ በማያሳስብ ጨዋታ ውስጥ ማን ማን ሰው ሊፈራ ይችላል . . .፣ ሁሉም ሳይሆኑ ከእነርሱ አንደኛው አፌዘ። ይኸው ልጅ ከእርሱ በታች በኩል የሚያልፈውን የእግረኛ መንገድ ሲመለከት በጣም ግራ እየተጋባ ሄደ። መጨረሻም፣ ምንም ቃል ሳይናገር፣ ወደ ኋላው ዘለለ። በተደጋጋሚ በመንከባለል፣ በመጥፎም ሁኔታ በመቁሰል በመጨረሻም ቆመ፣ ነገር ግን ከዚሁ መጥፎ ሁኔታ ተመልሶ እናም ደህና በመሆኑ ተደሰተ።

"የመኪናው ፍጥነት በጨመረ ቁጥር፣ የተቀሩት አራት ወንዶች በጣም ግራ እየተጋቡ ሄዱ። ምክንያቱም ምንም ፍሬን አልነበረውም፣ ፍጥነቱን ለመቆጣጠር አስቸጋሪ እየሆነ ሄደ። አንድ ልጅ ከኋላ ዘለለና ከመንደርደሩ ለማረጋጋት ሞከረ፣ ነገር ግን ወደ ፊት ሲወድቅ ክንዱ ተሰበረ። ሌላኛውም እንዲሁ ለመዝለል ሞከረ፣ ነገር ግን በጉማው ሥር ወድቆ በብርቱ ቆሰለ።

"ወዲያውም ለመንዳት እስኪያዳግት ድረስ መኪናው ፍጥነቱን ጨመረ። በዚያ ሁኔታ ላይ ሁለት ልጆች ብቻ ተስፋ በማጣት ተንጠልጥለው መልካሙን ሁሉ ይጠባበቁ ነበር። የአሮጌው መኪና አካል መንገዱን ለቆ ከትልቅ ዛፍ ጋር በተጋጨ ጊዜ በድንገት ቆመ። አንደኛው ልጅም ሞተ ሌላኛውም ልጅ ዕድሚውን በሙሉ አካለ ጉደሎ ሆነ" (*Teachers Study Course Series* A [*Aaronic Priesthood manual*, 1976], ከገጽ 29–30)።

- ልጆቹ ድርጊቶቻቸውን መቆጣጠር ያቆሙት በምን ደረጃ ላይ ነበር?
- ሁኔታው ሙሉ በሙሉ ከቁጥጥር ውጭ የሆነው በምን ደረጃ ላይ ነበር?
- አስከፊ ውጤት ያለውን ነገር የሚሰሩ ሰዎች ሌሎችም እንዲተባበሩአቸው የሚያሳምኑት ለምንድን ነው?
- የትኛው ነው የበለጠ ብርታት የሚጠይቀው፣ በአደገኛ ሥራ መሳተፍ ነው ወይስ ከቡድኑ ጋር አለመተባበር?
- ይህ ታሪክ በህይወታችን ውስጥ ከሚገጥሙን ምርጫዎች እና ውጤቶች ጋር እንዴት ይነጻጸራል?

ልጆቹ በመጀመሪያ ላይ ወደ ተጣለው ተሽከርካሪ በመጡ ጊዜ ሁኔታዎችን በሙሉ ተቆጣጥረውት እንደነበር አመልክት። መኪናው እንዲፈጥን ባደረጉበት ጊዜ በጥንቃቄ ለማቆም የነበራቸው አቅም ያነሰ ነበር። በስተመጨረሻም፣ በመኪናው ውስጥ የቀሩት በሙሉ በመጥፎ አጋጣሚያቸው የተነሳ ሊቆጣጠሩት አልቻሉም።

ሰይጣን እንደ እርሱ መከረኛ እንድንሆን እንደሚፈልግ ሁሉ በተደጋጋሚ የጥፋት ጎዳና ላይ ያሉ ሰዎች ሌሎችን ወደ እነርሱ ለመቀላቀል ይፈልጋሉ። በተሳሳተ ሥራቸው ከእነሱ ጋር ከመሆን ይልቅ ግፊታቸውን ለመቋቋም በጣም ከፍተኛ ብርታትን ይጠይቃል።

ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት

*አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ሐሳባዊ* እና *መንፈሳዊ* የሚሉትን ቃላት በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ። እነዚህ ቃላት በወጣት ወንዶች ህይወት ውስጥ እንዴት እንደሚተገበሩ ተወያይ። ወጣት ወንዶች በበለጠ እራስን ለመግዛት ለማኖር የሚፈልጓቸውን ጥቂት ግቦች እንዲጠቁሱ ጠይቅ። ሀሳባቸውን እንዲጀምሩ የተወሰኑ ምሳሌዎችን ልትሰጣቸው ትችላለህ። የወጣት ወንዶች አስተዋጽኦን በተገቢው ክፍል ሥር በጥቁር ሰሌዳው ላይ ጻፍ። የተሟላው ጥቁር ሰሌዳህ ይህን ሊመስል ይችላል፣

| **አካላዊ** | **ስሜታዊ** |
|---|---|
| በጊዜ ወደ መኝታ ሂድ<br>ማልደህ ተነስ<br>ሥራን እና የአካል እንቅስቃሴን አድርግ<br>የጥበብ ቃልን ጠብቅ | አመልህን በመቆጣጠር<br>ለሌሎች ደግ ሁን |
| **መንፈሳዊ** | **አዕምሮአዊ** |
| ትዕዛዛትን አክብር<br>ዘወትር ቅዱሳን መጽሐፍትን አንብብ<br>ከልብ ፁም<br>የቤተክርስቲያን ስብሰባዎችን ተከታተል<br>ዘወትር ሳታቋርጥ ከልብ ጸልይ<br>ሙሉ አሥራትን ክፈል | የቤት ሥራን በጊዜ ሥራ<br>ጥሩ መጽሐፍትን አንብብ<br>ንጹህ አስተሳሰብን ብቻ አስብ |

ወጣት ወንዶች በህይወታቸው ዘመን በእነዚህ ሁሉ ሊካባቢዎች የሚፈጽሟቸው ምርጫዎች እንዳሉ ግለፅ፣ የሚያጉለብቱት እራስን መግዛት ትክክለኛውን ውሳኔዎች እንዲፈጽሙ ይረዳቸዋል።

- እራሳችንን ሥርዓት የምናስይዝባቸው አንዳንድ መንገዶች ምንድን ናቸው?

ለወጣት ወንዶች ባህሪያችንን ማቀሙ ብቻ በቂ እንዳልሆነ ግለፅላቸው፣ ንስኃ መግባት እንዳለብንም አስረዳ። ለኃጢአታችን ንስኃ ለመግባት እና መጥፎ ልማድን ለማቆም የጌታ እርዳታ እንደሚያስፈልገን በሚገባ ግለፅ። የሚከተለውን የፕሬዚዳንት እዝራ ታፍት ቤንሰንን ንግግር አካፍል፥

"በእውነት ኃጢያትን ለማስወገድ ከፈለግን፥ የደህንነታችን ምንጭ ወደሆነው [ኢየሱስ ክርስቶስ]. . . . መጀመሪያ መመልከት አለብን።

"ንጉስ ቢኒያም አመርቂ ንግግሩን በዛርሄምላ ምድር ውስጥ ባጠናቀቀ ጊዜ፣ ሰዎቹ እንዲህ አሉ፣ 'የኃያሉ ጌታ መንፈስ ኃያል . . . በእኛ ውስጥ፥ ወይም በልባችን ውስጥ ለውጥን አስቀምጧል፥ . . . ተጨማሪ መጥፎ ሥራን ለመስራት ሳይሆን በተከታታይ ደጉን ለመሥራት ባህሪ ይኖረናል።' (ሞዛያ 5፥2።)

"በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ እና በእኛ ላይ ባለው መንፈስ ሥራ አማካኝነት ይህን ታላቅ ለውጥ በምናይበት ጊዜ አዲስ ሰው እንደሆንን ይሰማናል . . . ወደ ጥንት መንገዶቻችን የመመለስ ባህሪ አይኖረንም" ("A Mighty Change of Heart," *Ensign*, ጥቅምት 1989, ከገጽ 2–5)።

---

**ማጠቃለያ**

ተሳትፎ እና ሙከራ

ለእያንዳንዱ ወጣት እርሳስ እና ወረቀት አድል። እያንዳንዱ ወጣት ራሱን መግዛት የሚፈልግባቸውን ሦስት የረጅም ጊዜ አላማዎችን እንዲዘረዝራቸው አበረታታ። እነዚህ አላማዎች የሥራ ፍላጐቶችን (ለምሳሌ መልካም አስተማሪ ወይም አናፂ መሆንን) እናም አንተ ከተወያየህባቸው አራት አካባቢዎች ያሉትን አላማዎች ሊያጠቃልል ይችላል፣ ለምሳሌ፣ ወጣቱ ኮሌጅ መግባትን፣ የሙያ ትምህርት ማግኘትን፣ ሚሲዮን ሆኖ ማገልገልን፣ በቤተመቅደስ ውስጥ ማግባትን ወይም የተሻለ ጸባይን ማጐልበትን በመመኘት ላይ ትኩረት ሊያደርግ ይችላል። እነዚህን ግቦች ለመምታት እንዲያግዘው እያንዳንዱ ወጣት እራሱን ለመርዳት በየቀኑ ማድረግ የሚችለውን አንድ ወይም ሁለት የተወሰኑ ነገሮችን እንዲዘረዝር ጠይቀ። ለዚያም ለተወሰነው ግብ የዘረዘራቸውን የተወሰኑ ነገሮች እንደሰራ ለማረጋገጥ ምሽቱ ላይ ማስታወሻዎችን እንዲይዝ ጠይቀው። ለምሳሌ ወጣቱ እንደ ረጅም ጊዜ ትልም የቤተመቅደስ ጋብቻን ወይም በመንፈሳዊነት መሻሻልን መርጦ ከሆነ፣ እንደ የሁለት ቀን ግቦቹ "ለአንድ ሰው አንድን መልካም ነገር መፈፀም" እና "ለአሥር ደቂቃ ቅዱሳን መጽሐፍትን ማንበብ" የሚሉትን መዘርዝር ይችላል። በየቀኑ እነዚህን ግቦች ማሟላቱን ማረጋገጥ አለበት።

*ለወጣቶች ብርታት* በሚለው ውስጥ የታቀዱትን ደንቦች እንዲከልሱ ወጣት ወንዶችን አበረታታቸው። በየቀኑ እነዚህን ደንቦች እንዲከተሉ ወጣት ወንዶችን አለማምዳቸው።

# 8

# “አባትህን አክብር”

**ዓላማው**

እንደ በላይ ባለሥልጣንነቱ መጠን እያንዳንዱ ወጣት በቤት ውስጥ ለአባቱ ፍቀርን፣ አክብሮትን እና ድጋፍን አባት ያሳያል፡፡

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት፡፡
   ለ. ጥቅሶችን ማስመሪያ እርሳስ፡፡
   ሐ. አንድ በጣም ያማረ የፍራፍሬ ዘለላ።
2. ከሚከተለው የፕሬዚዳንት ሁፍ ቢ ብራውን ንግግር ጋር አንድ ማስታወቂያ አዘጋጅ፡፡

   “አባታዊነት ከአምላካዊነት ቀጥሎ ያለ ነው፣ እናም ስለዚህ መልካም አባት ለመሆን የህይወት ጊዜን ይወስዳል” (“Each Must Live With Himself,” *Improvement Era*, ታህሳስ 1963, ገጽ 1095)፡፡
3. ትምህርቱን ከመስጠትህ አንድ ሳምንት ቀደም ብለህ፣ የእያንዳንዱን ወጣት አባት (ወይንም አባት በቤት ውስጥ ከሌለ እናት) አነጋግር፡፡ ልጃቸው አባቱን ወይም እናቱን ለማክበር እና ለመርዳት የሚያደርገውን ወይም የፈጸመውን የተወሰኑ ነገሮች በመግለጽ ስለ ልጃቸው አጭር የስተያየት ደብዳቤ እንዲጽፉ እያንዳንዱን አባት ወይም እናት ጠይቀ፡፡ ወጣቱ እናት ወይም አባት ከሌለው፣ በህይወቱ ውስጥ የዚህ ወጣት ድርጊት አንድን ሰው እንዴት እንዳስከበረ ዘመድን ወይም አሳዳጊን ጠይቀ፡፡

**ለትምሕርት ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**አባት ፓትሪያርክ ነው**

በድራማ መልክ የሚቀርቡ

ወጣት ወንዶች በሚከተሉት ሁኔታዎች ሚና ወስደው እንዲጫወቱ አድርግ፡፡ በየራሳቸው ድርሻዎች እንዲወያዩ ለእያንዳንዱ ቡድን ጥቂት ደቂቃዎችን ፍቀድ፡፡

ድርጊት 1፣ ምንም መሪ የሌለበት እና እያንዳንዱ አባል የቤተሰብ ተሳትፎን በተመለከተ ለእራሱ ሐሳብ የሚከራከርበትን የቤተሰብ መማክርት ያሉበትን ሦስት ወይንም አራት ወጣት ወንዶች ሚናን እንዲጫወቱ ምረጥ። እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል በሌሎች ሐሳብ አይስማማም እናም የእራሱን ሐሳብ ብቻ ይፈልጋል፡፡

ከሚና መጫወቱም በኋላ፣ የሚከተለውን ጥያቄ ጠይቀ፣

- ውሳኔን ለማድረግ ያልቻሉት ለምንድን ነው?

ድርጊት 2፣ አባት የሚመራበትን፣ የእያንዳንዱ አባል ሐሳብ የሚወሰድበትን፣ እና ከውሳኔ ለመድረስ ሁሉም የሚሳተፉበትን፣ ምሳሌአዊ የቤተሰብ ሸንጐ እንዲያሳዩ ሦስት ወይም አራት ወጣት ወንዶችን ምረጥ፡፡

ከሚና መጫወቱም በኋላ፣ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይ፣

- ይህ ቤተሰብ ውሳኔን እንዲፈጽም ያስቻለው ምንድን ነው?

ማስታወቂያ

በፕሬዚዳንት ሁፍ ቢብራውን የተሰጠውን የንግግር ማስታወቂያ አሳይ [ዝግጅትን ተመልከተ]፡፡ መልካም አባት በመሆን በአብዛኛው ስኬታማነቱ የሚወሰነው ከቤተሰቡ በሚያገኘው ፍቀር እና ድጋፍ መሆኑን ግለጽ፡፡

ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት

*ፓትሪያሪክ* የሚለውን ቃል በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ፣ እናም ቃሉ ለእነሱ ምን ማለት እንደሆነ እንዲያብራሩ ወጣት ወንዶችን ጠይቀ፡፡ ወጣት ወንዶች ለመልሶቻቸው የስቴክ ፓትሪያሪክን ሊጠቀሱ ይችላሉ። በብሉይ ኪዳን ዘመን ፓትሪያሪክ ቤተሰብን እንዲመራ እና እንዲቆጣጠር በጌታ የተመረጠ መሆኑን አስረዳ፡፡ አዳም፣ ኖህ፣ አብረሃም፣ ይስሃቀ፣ እና ያዕቀብ፣ ሁሉም በፓትሪያሪክነት እንደሚታወቁ መግለጽ ትችላለህ፡፡

ፓትሪያርክ የቤተሰብ መሪ እንደመሆኑ መጠን፣ ለቤተሰብ ራዕይን የመቀበል መብት እና ኃላፊነት አለው፡፡

ጥቅስ

የአባትን ጠቀሚ ሚና በበለጠ እንዲረዱት ወጣት ወንዶችን ለመርዳት የሚከተለውን ጥቅስ አንብብ፡፡

“በእውነተኛነት፣ እያንዳንዱ ቤተሰብ በእራሱ ግዛት ነው፡፡ አባት ያንን ግዛት ይመራል። በመጀመሪያ በምድር ላይ ብቸኛው መንግሥት ቤተሰብ ነበር እናም ከአዳም ወደ ዘሮቹ ተላልፏል፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ በሚገባ ከተደራጀ፣ አባት የዘለዓለማዊ ቤተሰብ ክፍል ፓትሪያሪክ ነው፡፡ ሰማይ፣ ለእኛ፣ በቀላሉ ቀጣዩ ተስማሚ ቤት ይሆንልናል፡፡ እንደ በላይ የክህነት ሹም፣ አባት ሊተካ የማይችለውን ሚና ይሞላል” (A. Theodore Tuttle, በ Conference Report, ጥቅምት 1973,ገጽ 86; or *Ensign*, ጥር 1974, ገፅ 66.)

### የጽድቅ ሥራችን አባቶቻችንን ያስከብራል

**ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት**

አንድ ወጣት ዘጸአት 20፥12ን እንዲያነብ አድርግ።

- አባትህን ማክበር ማለት ምን ማለት ነው?

አንድን አባት ማክበር ማለት ክብርን ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መኖር መሆኑን ከወጣት ወንዶች ማጠቃለያ ሐሳብ ውሰድ። ፓትሪያርክ ዘሮቹን በሙሉ ስለሚመራ እና ስለሚቆጣጠር፣ አባቶቻችንን፣ አያቶቻችንን እና ሁሉንም ቀድመ አያቶቻችንን ማክበር አለብን። አባቶቻችንን በምናከብርበት ጊዜ የሰማይ አባታችንንም እያከበርን ነው።

**ቅዱስ መጽሐፍ እና በቁሳዊ የተደገፈ ትምህርት**

አንድ ወጣት ማቴዎስ 7፥17–20 እንዲያነብ አድርግ። ወጣት ወንዶች በእነኚህ ጥቅሶች ከፍ አድርገህ ላይ በመጽሐፍ ቅዱሶቻቸው ውስጥ ምልክትን እንዲያደርጉባቸው ንገራቸው። ፍራፍሬውን ከፍ አድርገህ ያዝ እናም በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያይ።

- ይህን መልካም ፍሬ ስላፈራው ዛፍ ምን ማለት እንችላለን?
- ዛፉ እንክብካቤ አልተደረገለትም ወይንም በሽተኛ ነው ባላችሁ ታስባላችሁን? ለምን ወይንም ለምን አታስቡም?
- ፍሬው የተገኘበትን የዛፍ ዓይነት እንዴት ያመለክታል?
- ያንተ ማንነት በወላጆችህ እና በቤተሰቦችህ ላይ እንዴት ይንፀባረቃል።
- ከመልካም ቤት መምጣትህን ለሌሎች እንዴት ማሳየት ትችላለህ?

በድርጊቶቻችን ወላጆቻችንን እና ቤተሰቦቻችንን እንደምናከብር ወይም እንዳማናከብር አስረዳ። የጽድቅ ሥራ ቤተሰቦቻችንን ያስከብራል።

**ታሪክ**

ፕሬዚዳንት ደቪድ ኦ ማኬ በአንድ ወቀት አንድ ወጣት በአባቱ ላይ ያለውን ታላቀ እምነት፣ ፍቅሩን እና አድናቆቱን ያሳየበትን መንገድ እንዲህ በማለት ተናግረዋል።

“የእንግሊዝ የእፅዋት ተመራማሪዎች ቡድን በስዊስ አልፕስ በብዛት የማይገኙትን አበቦች በማሰባሰብ የእረፍት ጊዜያቸውን አሳለፉ። አንድ ቀን ጠዋት ብዙ ጫማዎች ከፍ ብሎ፣ ጥልቀት ካለው ገደል አፋፍ ሥር፣ በትንሽ አረንጓዴ ስምጥ ሸለቀ ውስጥ ያደገውን ልዩ አበባ አዩ። ቀጥሎም በመውጫቸው አንድ ትንሽ ልጅ ከቡድናቸው ጋር ተቀላቀለና ሂደቱን በአድናቆት ተመለከተ። ከቡድኑም አንዱ ወደ ልጁ በመዞር፣ ‘አንተ ወጣት፣ ከእነዚያ አበባዎች ነቀለህ እንድታመጣልን ገመድ በወገብህ ላይ አሰረን ከገደሉ ላይ ወደ ታች ብንለቀህ፣ እና ተክሉ ሳይጐዳ ጐትተን ብናወጣህ፣ አምስት ፓውንድ እንሰጥሀለን’ አለው።

“በገመድ ገደሉ ላይ እናንጠለጥልሃለን ሲሉት ለተወሰነ ጊዜ ልጁ በፍርሃት ካሰበ በኋላ ወዲያውኑ በድንጋጤ ሮጠ፣ ነገር ግን በጥቂት ጊዜ ውስጥ፣ የጐበጠ ሽበታም፣ እጆቹ በጉልበት ሥራ ያበጡ እና የደራረቁ ሽማግሌ ይዞ ተመለሰ። የእፅዋት ተመራማሪዎቹ ጋር ከደረሰ በኋላ ልጁ ወደ ጠያቂው ሰው ተመለሰ እና፣ ‘ጌታዬ፣ ይህ አባቴ ነው። አባቴ ገመዱን እንዲይዝ ከፈቀዳችሁለት ወደ ሸለቆው እወርዳለሁ!’” አለ። (*Melchizedek Priesthood Lessons*, 1965, ገጽ 86)።

**ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት**

በጥቁር ሰሌዳው ላይ፣ *ለባቶቻችንን እንዴት እንደምናከብር የሚለውን ጻፍ*።

- ወጣት ወንዶች አባቶቻቸውን በምን መንገዶች ማክበር ይችላሉ?

“አባቶቻችንን እንዴት እንደምናከብር” ከሚለው ሥር የወጣት ወንዶችን አስተያየቶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ። አስተያየቶቻቸው ለእርዳታ እና ለምክር ወደ እርሱ መሄድን፣ ምክርሩን መከተልን፣ በአክብሮት ስለ እርሱ እና ለእርሱ መናገር፣ ለእርሱ መጸለይን፣ ችግሮች እና አስቸጋሪ ጥያቄዎች በሚነሱበት ጊዜ ለበረከት መጠየቅን፣ ጓደኛው መሆንን፣ ነገሮችን ለእርሱ መሥራትን፣ እና የጽድቅ አኗኗር መኖርን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ።

በእነዚህ ሐሳቦች ላይ ተወያይ። ለአባቶቻቸው አክብሮትን እንዴት እንዳሳዩ እንዲናገሩ ወጣት ወንዶችን አበረታታ።

---

### የሰማይ አባትህን አክብር

**ጥቅስ**

በጳጳስ ሮበርት ዲ ሄልስ የተሰጠውን የሚከተለውን ንግግር አንብብ።

“በወጣትነቴ፣ በዩ ኤስ አየር ኃይል ውስጥ በተዋጊ ጀት አብራሪነት የማገልገል እድል አግኝቼ ነበር። በብርጌዳችን ውስጥ እያንዳንዱ ክፍል ጥረቱን የሚያነሳሳ መመሪያ ነበረው። የክፍላችን መመሪያ—በአውሮፕላናችን ከጐኑ ላይ የተጻፈው—‘በክብር ተመለስ።’ የሚል ነበር። ተልዕኮአችንን በስኬታማነት ለማጠናቀቀ ጥረታችንን በሙሉ ከአከልን በኋላ ብቻ ወደ ቤታችን በክብር ለመመለስ ይህ መመሪያ የመነሳሳታችን የዘወተር ማስታወሻ ነበር።

“የኸው ተመሳሳይ መመሪያ፣ ‘በክብር ተመለስ’ የሚለው፣ በዘለዓለማዊ አቀድ አድገታችን ውስጥ ለእያንዳንዳችን ሊሰራ ይችላል። ከሰማይ አባታችን ጋር በመኖራችን እና ወደ ምድራዊ ህይወት በመምጣት ወደ ሰማያዊ ቤት ዳግም በክብር ለመመለስ ውሳኔ ሊኖረን ያስፈልጋል።”

• ወደ ሰማዩ አባታችን በክብር እንዴት መመለስ እንችላለን?

“ጥፋቶችን ለማስወገድ ልክ የአውሮፕላን አብራሪዎቹ የተወሰኑ ሕጎችን ማክበር እንዳለባቸው ሁሉ፣ እኛም በዚህ ምድራዊ ህይወት ውስጥ— በዚህ የዝግጅት ጊዜ—ወደ ዘለዓለማዊው ህይወት ግባችንን ለመድረስ ማወቅ እና ማክበር የሚገቡን ህጎች፣ ሥርዓቶች እና፣ ቃል ኪዳኖች አሉን”። (በ Conference Report, ሚያዚያ 1990, ከገጽ 51–52; ወይም *Ensign*, ግንቦት 1990, ገጽ 39)።

---

**ማጠቃለያ**

ደብዳቤዎች

ለወጣት ወንዶቹ ደብዳቤዎቹን አከፋፍል። አባቶቻቸው ደብዳቤዎቹን እንደጻፉላቸው ግለጽላቸው እናም ወጣት ወንዶች ደብዳቤአቸውን ለየግላቸው እንዲያነቡ አበረታታቸው። ወጣት ወንዶች በሳምንቱ ጊዜ ውስጥ ለአባቶቻቸው ደብዳቤን በመጻፍ ወይም እነርሱን በማናገር ፍቅራቸውን እና አድናቆታቸውን እንደሚገልጹ ንገራቸው። ወጣት ወንዶች በቤታቸው ውስጥ ጥሩ ምሳሌ ለመሆን እንዲተጉ እና ዘወትር አባቶቻቸውን እንዲያከብሩ አበረታታቸው። ሊዘጋጁለት የሚገባው የወደፊት አባትነት ለእያንዳንዱ ወጣት የተቀደሰ በረከት መሆኑን መረዳት አለባቸው።

# እናቶችን እና መለኮታዊ ሚናቸውን ማክበር

# 9

**ዓላማው**

እያንዳንዱ ወጣት ከእናቱ ጋር ያለውን ግንኙነት ያጠናክራል እናም ያከብራታል።

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፥
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. ጥቀሶችን ምልክት ለማድረጊያ እርሳሶች።
   ሐ. ለእያንዳንዱ ወጣት እርሳስ፣ ወረቀት፣ እና ፖስታ።
2. ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፋቸው፥
   ሀ. ወደዚህ ህይወት ተመጣ ዘንድ የእርሷን ህይወት በአደጋ ውስጥ የጨመረችው ማነች?
   ለ. ከተወለድህ በኋላ ታላቅ ፍቅርን ያሳየህ ማን ነው?
   ሐ. ለእኛ ታላቅ መስዋዕትነትን ለከፈሉት ታላቅ ምስጋናችንን እንዴት ማሳየት እንችላለን?
3. ልጃቸው የእናት እና ልጅ መቀራረብን ለማጠናከር የሚያደርገውን ቢያንስ አንድ ነገር እንዲናገሩ በቡድኑ ውስጥ የሚገኙትን የእያንዳንዱን ወጣት እናት በማግኘት ጠይቅ። የሁሉንም እናቶች መልስ በፖስተሩ ላይ ጻፍ። ማንኛውም ከወጣት ወንዶቹ መካከል እናት የሌለው ካለ፣ ወጣቱ በቤቱ ውስጥ የሚረዳበትን አንድ መንገድ እንዲናገሩ ዘመዱን ወይም አሳዳጊውን ጠይቅ።

**ለትምሕርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**እናቶች በእግዚአብሔር እቅድ አስፈላጊዎች ናቸው**

ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት

የወጣት ወንዶችን ትኩረት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ወደ ተጻፉት ጥያቄዎች መልስ (“ዝግጅትን” ተመልከት)። ሶስቱንም ጥያቄዎች ከፍ ባለ ድምጽ አንብቡ።

• የመጀመሪያዎቹን ሁለት ጥያቄዎች የሚመልሰው አንድ ቃል ምንድን ነው? (እናት።)

በትምህርቱ ጊዜ እያንዳንዱ ሰው ስለ እነርሱ እንዲያስብ ጥያቄዎቹን በጥቁር ሰሌዳ ላይ እንደምትተዋቸው ለወጣት ወንዶቹ ንገራቸው።

ሁላችንም እናቶቻችንን ብንወዳቸው እና ብናደንቃቸውም እንኳን፣ ብዙ ጊዜ የሚገባውን ያህል ሥፍራ አንሰጣቸውም። እስክንርቃቸው ወይንም ከቤት ርቀን እስክንሄድ ድረስ እናቶቻችን ምን ያህል እንደሚጠቀሙን አንዳንዴ አንገነዘብም።

ታሪክ

በአንድ ዋርድ ለሚገኙ ወጣት ወንዶች በሙሉ ሽርሽር መሄዳቸው አስደሳች ልምድ ሆኖላቸው ነበር። ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀናት ከቤት ርቀው በመሄዳቸው ደስተኞች እንደነበሩ ይናገሩ ነበር። ይሁን እንጂ፣ ሽርሽሩ ወደ ማብቂያው እንደተቃረበ፣ ወደ ቤት ለመሄድ መጓጓት ጀመሩ። በመጨረሻው ስብሰባቸው በተሰባሰቡበት ጊዜ፣ በሽርሽሩ ላዩ በነበሩበት ሳምንት ስለ እናታቸው ያሰቡትን አንዳንድ ሐሳቦች እንዲያካፍሉ አማካሪው ወጣት ወንዶችን ጠየቃቸው።

በሽርሽሩ የመጨረሻ ምሽት በወጣት ወንዶች የተሰጠውን የሚከተሉትን አስተያየቶች እንዲያቀርቡ ወጣት ወንዶችን ጠይቅ።

1. “እናቴ ለልደቷ ቀን የተቀበለችውን ገንዘብ እንዴት እንደተጠቀመችበት ታውቃላችሁ? የአዲስ ቀሚስ መግዣዋ ነበር፣ ነገር ግን በምትኩ፣ ወደ ካምፑ መምጣት እንድችል ለእኔ አዲስ የመኝታ ፍራሽ ለመግዛት አዋለችው። ዘወትር ወደዚያው የመኝታ ፍራሽ ውስጥ በምገባበት ጊዜ እናቴ ያደረገችልኝን መስዋዕትነት አስታውሳለሁኝ። እርሷ ሁሌም መስዋዕትነት ትከፍልልኛለች።”
2. “ሁላችንም በቤት ውስጥ ምግብ የመሥራት ተራችንን መቀበል አለብን። በፊት ሁሌም አሰልቺ ሥራ እንደሆነ አስብ ነበር። በካምፑ ውስጥ ምግብ የማዘጋጀቱ ተራዬ በደረሰ ጊዜ፣ እናቴ በድንገት ናፈቀችኝ። እቤት ሆኜ ምግብን በማዘጋጅበት ጊዜ ለንግግር ጊዜ እንዲኖረን ዘወትር ትረዳኝ እንደነበር አስታወስኩኝ። የየቀን ሥራዎችን እና ችግሮችን ለእርሷ ማካፈሉን በእውነቱ ናፈቀሁኝ። ለመናገር በምትፈልግበት ጊዜ የሚያዳምጥህ ሰው ዘወትር እንዳለህ ማወቁ አስደሳች ነው።”
3. “ብዛት ያላቸው ፍልፈሎች ወደ ፊት እና ወደ ኋላ በመሮጥ አካባቢውን ሲቧጥጡ፣ በአንድ ትልቅ አለት ላይ በመቀመጥ ተመለከትኩኝ። ይህም የልጅነት ጊዜዬን አስታወሰኝ። ነፍሳትን ወይም የዱር አራዊቶችን

ለመያዝ ዘወትር አሞክር ነበር፡፡ መሆን እንዳለባቸው፣ እነርሱን ለመያዝ እና በሳጥን ውስጥ ለማስቀመጥ በመሞከር እንዳንጎዳቸው እና እንዳናስፈራራቸው፣ በነጻነት እንዲኖሩ እንድንፈቅድላቸው እናቴ አስተምራኛለች፡፡ እንስሳትን ትወዳለች እናም የሰማይ አባት ፍጡራን እንደሆኑ እና ሁሉንም ህይወት በአክብሮት መያዝ እንዳለብን ዘወትር ትነግረናለች፡፡”

4. “እናቴ እንዴት እንደማበስል ስለነገረችኝ ምናልባትም በእውነት እናንተ ደስተኞች ናችሁ፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ ባለፈው ምሽት ሁላችንም በጣም ርቦን ሳለ እና የማብሰል ተራው የእኔ በነበረበት ወቀት ትናደዱ ነበር፡፡ ሚሲዮናዊ ሆኜ ለአገልግሎት በምሄድበት ጊዜ ስለማብሰል ጥቂት ነገሮችን በማወቄ ደስተኛ እንደምሆን ተነግሮኛለች። ለዚህም መቀየት የለብኝም—አሁን ደስተኛ ነኝ፡፡”

5. “ባለፈው እሁድ በጾም እና ጸሎት ስብሰባ ላይ እህቴ ህጻን ልጇ ተባርኮላት ነበር፡፡ ምስክርነቷን በሰጠች ጊዜ፣ የእራሷን ልጅ እስክትወልድ ድረስ እናታችንን ፈጽሞ በእውነት ለመስግና እንዳማታውቅ ተናገረች፡፡ አሁን የእናት ጊዜዋ፣ ገንዘቧ፣ ጥረቷ እና ሐሳቢ ለልጆቿ እንደሆነ ተገነዘባለች፡፡ እንደዚያ ህጻን ልጅ ሳለሁ በዚያ መልኩ እንዴት እንደጀመርኩኝ እና ለዚህ ደረጃ እኔን ለማብቃት እናቴ ምን ያህል መሥራት እንዳነበረባት አሰብኩኝ፡፡ እህቴ ህጻን ልጇን ስትንከባከብ ማየቱ በእውነቱ እናቴን እንዳመሰግናት ረድቶኛል፡፡”

ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት

(ከወጣት ወንዶቹ መካከል እናት የሌላቸው ወጣቶች ቢኖሩ መልካም ፍርድን እና አመለካከትን ተጠቀም፡፡) እናታቸው ለእነርሱ እና ለቤተሰቦቻቸው ያበረከቱትን አስተዋፅኦ ዝርዝር ለማዘጋጀት ትረዳቸው ዘንድ ወጣት ወንዶችን ጠይቀ፡፡ ወጣት ወንዶቹ በሁለት ወይም ሦስት ደቂቃዎች ውስጥ ሊያስቧቸው የሚችሉትን አያሌ ነገሮች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ፡፡ ሁሉንም ነገር በተሟላ ሁኔታ ለመዘርዘር ጊዜ ሊያጥርህ ይችላል፣ ነገር ግን ሁላችንም ተገቢውን ሥፍራ የማንሰጣቸውን፣ እናቶች በየቀኑ ምን ያህል የፍቅር እና የአገልግሎት ተግባራትን እንደሚያከናውኑ የሚያሳዩአቸውን በቂ ነገሮችን አካትት። ወጣት ወንዶቹ እንዲጀምሩ ለማድረግ፣ በጠዋት እየነቁ መሆናቸውን እንዲያስቡ ማድረግ ትችላለህ፣ ከዚያም የእናቶቻቸውን አስተዋፅኦ በመቀበል፣ በአንድ ለየት ባለ ቀን እንዲያልፉ አድርጋቸው።

ለእናቶቻችን ፍቀርን እና ምስጋናን፣ እንዲሁም ታማኝነታችንን እና አክብሮታችንን መስጠት አለብን የሚለውን ከዝርዝሩ ውስጥ አጠቃል፡፡

ጥቅስ

በፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬ የተሰጠውን የሚከተለውን መግለጫ አንብብ እና ተወያይ፣

“እናትነት እግዚአብሔር የሰጠውን የመፍጠር እና መስዋዕትነት የመክፈል ምግባርን የሚገልፅ በአለም ሁሉ በበለጠ ምሳሌ የሚሆን ነገር ነው—። ከዘላለማዊ ህግ ጋር የምትቀናጀው፣ እናት፣ በፍጥረት ሂደት ውስጥ የመጀመሪያ ማዕረግን የሚይዘውን ህያው የሆነን ነፍስ ወደ ዓለም ታመጣለች፡፡” (*Gospel Ideals* [ሶልት ሌክ ከተማ: Improvement Era, 1953], ገጽ 456.)

ቅዱስ መጽሐፍ

ዮሐንስ 15፥13 አንብብ፡፡ ወጣት ወንዶች ይህን ጥቅስ ከሥሩ እንዲያሰምሩበት አድርግ፡፡

ህይወታቸውን ለእኛ ለመሰዋት ፈቃደኛ ሆነው በመዝመት ከጦር ሜዳ የሚመለሱትን ወታደሮች እንደምናከብር አመልክት፣ የምትወልድ እያንዳንዷ እናት ለዚያ ልጅ ህይወቷን የመሰዋት ፈቃደኛነቷን ታሳያለች። እኛ ዘወትር ለእናቶቻችን ተገቢውን ክብር እና ምስጋና አናሳይም፡፡ እኛ በምንወለድበት ጊዜ በወሊድ ህመም እና አደጋ ውስጥ ማለፍ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን እኛን ለማሳደግ እናቶች በህይወታቸው ሁሉ ጊዜያቸውን እና ችሎታቸውን ይሰዋሉ፡፡

---

**ከእናታችን ጋር ያለንን ግንኙነት ማጠናከር እንችለለን**

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

የወጣት ወንዶችን ትኩረት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ባለው በመጨረሻው ጥያቄ ላይ አኑር። በዚህን ጊዜ መልስ እንዲሰጡ አትጠይቀ፡፡ ክርስቶስ ምሳሌ እንዳኖረልን አመልክት። በመስቀል ላይ በነበረበት ወቀት፣ ከመጨረሻ ሐሳቦቹ ውስጥ አንዱ የእናቱ ደህንነት ነበር፡፡

ዮሐንስ 19፥25–27 አንድ ወጣት እንዲያነብ አድርግ፡፡

ኢየሱስ በስቃዩ ላይ ቢሆንም እንኳ፣ ስለ እናቱ በመጨነቀ ዮሐንስ እንዲንከባከባት ጠይቋል፡፡

• ለእናትህ ማሰብህን እና አድናቆትህን ለማሳየት ምን ማድረግ ትችላለህ?

ማስታወቂያ

እያንዳንዱ ወጣት ቢያንስ አንድ ሐሳብ እንዲሰጥ አበረታታ፡፡ እናቶችን ሊያስደስቱ ከሚችሉ ነገሮች አንዱ ከልጆቻቸው ጋር የቀርብ የሆነ የፍቀር ግንኙነትን ማግኘት እንደሆነ ግለጽ፡፡ ያዘጋጀኸውን ማስታወቂያ ለወጣት ወንዶች አሳይ፡፡ ለእናቶቻቸው ቃለ መጠይቀ እንዳደረጉላቸው እና እነዚህ እናቶች ከልጆቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ሊያጐለብቱ የሚችሉባቸው የተወሰኑ ነገሮች ናቸው ብለው የሚያስቧቸው እንደሆኑ ንገራቸው፡፡ በቀረበው ሐሳብ ላይ ተወያይ፡፡

ጥቅስ

ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ፣ ስለ እናቶች ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፣ “በአድናቆት እና በፍቀር ደብዳቤአችሁ ብታናግሯት፣ የደስታ እምባዋን ታፈሳለች” (“The True Mother,” *Instructor*, ግንቦት፣ 1960, ገጽ 142)፡፡

| | |
|---|---|
| ተሳትፎ | ለእያንዳንዱ ወጣት እርሳስ፣ ወረቀት እና ፖስታን አከፋፍል። እያንዳንዱ ወጣት ለእናቱ የፍቅር እና የምስጋና ማስታወሻን እንዲጽፍ ጠይቅ። እያንዳንዱ ወጣት ለእናቱ ታላቅ ክበሬታን ለማሳየት እና ከእርሷ ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር የተወሰኑ ውሳኔዎችን ሊጨምር ይችላል። |

---

**ማጠቃለያ**

እናቶቻችን የምስጋና እና ጥቂት የአድናቆት ቃላት ትርጉም የሚሰጡአቸውን ያህል፣ እነርሱን ልናመሰግናቸው ከምንችልባቸው መንገዶች አንዱ የክህነት ሥልጣናችንን በማክበር እና በሚፈልጉት መጠን ታማኝ እንድንሆን፣ እምነት ያለን ሰዎች በመሆን ማደግ እንደሆነ ለወጣት ወንዶች ግለጽ።

| | |
|---|---|
| ሙከራ | እያንዳንዱ ወጣት ለእናቱ እንደ ዘላቂ ቀርስ እንደሆነ አብራራ። በአኗኗሩ ሁኔታ እናቱን ሊያከብር እና ላያከብር ይችላል። የጽድቅ ህይወትን በመኖር እናቱን እንዲያከብር እያንዳንዱን ወጣት አበረታታ። |

# 10 የቤተሰብ አንድነት

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት በምድራዊ ቤተሰቡ ውስጥ አስፈላጊ ሥፍራ እንዳለው ይረዳል። |
| **ዝግጅት** | 1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣<br>ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።<br>ለ. ሥዕል 3፣ ለወላጆች መልካም ምሽት የሚሉ ልጆች፤ ሥዕል 4፣ የቤተሰብ ጸሎት፤ ሥዕል5 ማርያም፣ ዮሴፍ እና ኢየሱስ (62495)።<br>ሐ. የማንቀርቀሪያ ውሃ እና መጠጫ ብርጭቆ።<br>2. ብዙ የመቀላለፊያ ቀዳዳ ያለውን እንጨት የመሰለውን እንቀቀልሽ አዘጋጅ። ቀላል የልጆች እንቀቀልሽን ተጠቀም፣ ወይም አንድ የአራስህን አዘጋጅ። |

**ለትምሕርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**በሰማያዊ አባታችን ዕቅድ ውስጥ ቤተሰብ አስፈላጊ ሥፍራን ይይዛል**

ሥዕሎች እና ውይይት

ትምህርቱ ስለ ምን እንደሆነ ሳትናገር፣ የቤተሰቦችን ሥዕል አሳይ።

• እነዚህ እያንዳንዳቸው ሥዕሎች በጋራ ምን አላቸው? (ሁሉም ምስሎች ቤተሰብን ይወክላሉ።)

የቤተሰቦችን ሥዕል ጥቀስ ወደ ዮሴፍ፣ ማርያም እና የኢየሱስ ሥዕል ጠቁም።

• ኢየሱስ ወደ ቤተሰብ ለምን ተላከ?

• ቤተሰቡ እንዴት ረዳው?

ቅዱስ መጽሐፍ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ውይይት

ሌሎች ከቅዱሳን መጻሕፍቶቻቸው በመከታተል ላይ እያሉ አንድ ወጣት ከሉቃስ 2፡52 እንዲያነብ አድርግ።

• ኢየሱስ ክርስቶስ ያደገባቸውን አካባቢዎች በዚህ ጥቀስ ውስጥ የሚወክሉ ቃላቶች የትኞቹ ናቸው? ቀጥሎ እንደተመለከተው ጥቁር ሰጼዳን አዘጋጅ (ጥበብ፣ ቁመና፣ በእግዚአብሔር እና በሰው ዘንድ ሞገስ።)

ቀጥሎ እንደተመለከተው ጥቁር ሰሌዳን አዘጋጅ፣

| | |
|---|---|
| ጥበብ | በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ |
| ቁመና | በሰው ዘንድ ሞገስ |

ልክ አዳኛችን ወደ ቤተሰቡ እንደተላከው ሁሉ፣ እኛም እነኚህን በመሳሰሉት አካባቢዎች እንድናድግ፣ እንድንጎለብት፣ እና እንድንሻሻል ይረዱን ዘንድ ወደ ቤተሰብ የተላክን መሆናችንን አስረዳ።

• ጥበብ ሲባል ምን ማለት ነው? (ትክክለኛ የሆኑ ውሳኔዎችን ከመፈጸም ልምድ የሚመጣ መልካም ፍርድ ነው።)

• ቤተሰቦቻችሁ በጥበብ ታድጉ ዘንድ እንዴት ይረዷችኋል?

"ጥበብ" በሚለው ስር የወጣት ወንዶችን መልሶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ።

በጥበብ እንድታድግ የረዳህን ከቤተሰብህ ያገኘኸውን አጠር ያለ የግል ልምድህን ማካፈል ትችላለህ።

**ጥቅስ**

የበላይ አመራር ፕሬዚዳንት ኤን ኤልደን ታነር ኃላፊነት ያለው እና ደጋፊ ሰው ለመሆን የሚከተለውን እንዴት እንደተማረ የሚገልጸውን ሐሳብ አብራራ፣

“በማንኛውም መንገድ ድጋፍ ስለ መሆን በምናገርበት ጊዜ፣ ልጅ ሳለሁ ስለ ደጋፊነት ከፍተኛ አድናቆትን እና ታላቅ ማስተዋልን የሰጠኝን ልምድ አገኝቻለሁ። አባቴ ለቤክርስቲያን ሥራ ርቀ ይሄድ ነበር እናም ለወንድሜ እና ለእኔ እንዲህ አለ፣ ‘እኔ ስሄድ ይህን እና ይህን ብትሰሩልኝ እመኛለሁ።’ ብዙውን ጊዜ የሚጓዘው ከሰዓት በኋላ ነው ብለን እናስብ ነበር። የምንኖረውም በእርሻ ሥፍራ ነበር፣ እናም በከብቶች ጋጥ ውስጥ የተወሰኑ ጥጆችን በማየታችን በቀድሚያ ለመጋለብ እና ከዚያም ልንሰራ አሰብን።

“አባታችን ይመጣል ብለን ካሰብንበት ጊዜ ቀደም ብሎ መጣ፣ እናም ወደ እርሱ ጠርቶኝ እንዲህ አለኝ፣ ‘የእኔ ልጅ፣ እመካብሃለሁ ብዬ አስብ ነበር’—። ይህንንም እንዳሰብኩ፣ ‘ቁስ ኤልደን ታነር እመካብሃለሁ ብዬ አስብ ነበር፣’ በፍጹ እንዳይል *ለማንም* ደግሜ ይህን ምክንያት አልሰጥም ብዬ ወሰንኩኝ፣ እናም በዚያ ምሽት ወደ መኝታዬ ስሄድ ለጌታ እንደጸለይኩት፣ ‘ባንተ የምደገፍ ይመስለኝ ነበር’ ብሎ ለማለት ምንም ምክንያት አባቴ እንዳይኖረው ጠንቃቃ እንደምሆን ለመወሰን ቃል ገባሁኝ” (በ Conference Report, Paris France Area Conference 1976፣ ገጽ 25)።

**ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት**

• ቁመና ማለት ምን ማለት ነው? (የአካል ጥንካሬ እና እድገት። በጉርብትና መኃል የተከበረ ሰው ማለትም ሊሆን ይችላል።)

• በቁመና እንድታድጉ እና በአካል እንድትጠነክሩ ቤተሰቦቻችሁ እንዴት ይረዷችኋል? (መጠለያን በማቅረብ፣ ህክምናን በመከታተል፣ በምግብ፣ እናም ሙያዎችን እና ችሎታዎችን እንድታጐለብቱ በማበረታታት።)

ወጣት ወንዶች መልስ በሚሰጡበት ጊዜ፣ መልሳቸውን በጥቁር ሰሌዳው ላይ “ቁመና” ከሚለው ሥር ጻፍ።

• “በእግዚብሔር ሞገስ” ማደግ ማለት ምን ማለት ይመስልሃል? (እግዚአብሔር ድርጊታችንን ሲደግፈው እናም በእኛ ሲደሰት።)

• በእግዚአብሔር ሞገስ ታድጉ ዘንድ ቤተሰቦቻችሁ ሊረዷችሁ የሚችሉባቸው አንዳንድ መንገዶች ምንድን ናቸው? (የወንጌል መሠረቶችን እንዴት እንደምንኖር በማስተማር፣ መደበኛ የቤተሰብ የቤት ምሽትን እና የቤተሰብ ጸሎትን በማድረግ፣ ቀዱሳን መጻሕፍትን በማጥናት እና ከእኛ ጋር ቤተክርስቲያንን በመካፈል፣ እንዲሁም ለቤተክርስቲያን ንግግር እንድናዘጋጅ በመርዳት።)

የወጣት ወንዶችን መልስ በጥቁር ሰሌዳው ላይ “በእግዚአብሔር ሞገስ” ከሚለው ሥር ፃፍ።

አንድ የቤተሰብ አባል ለጌታ ቀርብ እንዲሆኑ በረዳቸው ጊዜ የነበራቸውን ልምድ እንዲያካፍሉ ወጣት ወንዶችን ጠይቅ። የራስህን ልምድ ማካፈል ትችላለህ።

• በሰው ዘንድ ሞገስን በማግኘት መጠናከር ማለት ምን ማለት ነው? (ከሌሎች ጋር መተባበርን መማር ነው።)

• ከሌሎች ጋር እንድትተባበሩ ሊረዷችሁ የሚችሉትን ምን ምን ፀባዮችን ቤተሰቦቻችሁ ሊያስተምሩችሁ ይችላሉ?

የወጣት ወንዶችን መልሶች በጥቁር ሰሌዳው ላይ “በሰው ዘንድ ሞገስ” በሚለው ሥር ዘርዝር። አንዳንድ መልሶች ማካፈልን፣ መተዛዘንን፣ መከባበርን፣ መተባበርን፣ መተማመንን፣ ፍቅርን፣ ኃላፊነትን ተቀባይነትን እና ታጋሽነትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ።

---

### ቤተሰቦቻችን ተጽዕኖ ያሳድሩብናል፣ እናም እኛ በቤተሰቦቻችን ላይ ተጽዕኖ እናሳድራለን

**በቁሳዊ ነገሮች ላይ የተደገፈ ትምህርት**

የማንቆርቆሪያ ውኃን እና የመጠጫ ብርጭቆን በጠረጴዛ ላይ አኑር። ማንቆርቆሪያው ቤተሰባችንን እና ብርጭቆው እኛን እንደሚወክል አስረዳ። ውኃው ቤተሰቦቻችን የሚሰጡንን እርዳታ ይወክላል። ቤተሰቦቻችን እኛን በአካል፣ በአዕምሮ እና በምንፈልጋቸው መንፈሳዊ ነገሮች በመሙላት ሊረዱን ይችላሉ።

ብርጭቆውን ገልብጠህ አስቀምጠው።

• እኛ ተገልብጦ የተቀመጠውን የመጠጫ ብርጭቆ ለመሙላት ብንሞክር ምን ይከሰታል?

• አንዳንዴ የተገለበጠውን የመጠጫ ብርጭቆ እንዴት እንመስላለን? (ቤተሰቦቻችን የሚሰጡንን እርዳታ ሳንቀበል።)

የመጠጫውን ብርጭቆ በትክክል አፉን ወደ ላይ መልሱት እና በውኃ ሙሉት። ቤተሰቦቻችን የሚሰጡንን እርዳታ በምንቀበልበት ጊዜ፣ ብርጭቆን በውኃ መሙላት እንደሆነ አስረዳ።

• ቤተሰብህ እንዴት ይረዳሃል?

በጥቁር ሰሌዳ ላይ ያለውን ሰንጠረዥ አመልክት።

• ቤተሰብህ ሊረዳህ የሚችልባቸው ሌሎች መንገዶች አሉን?

ወጣት ወንዶቹ ከመለሱ በኋላ፣ የብርጭቆን ውኃ ወደ ማንቆሮቆሪያው ጨምር።

• ቤተሰብህን እንዴት ትረዳለህ?

በጥቁር ሰሌዳው ላይ በቀኝ በኩል መልሶቹን ዘርዝር፡፡

እያንዳንዱ ወጣት አንድ ሰው ብቻ እንደሆነ፣ ነገር ግን በብዙዎች ላይ ተጽዕኖን የማድረግ ኃይል እንዳለው አስረዳ፡፡ ቤተሰቦቻችን በቀርበት የምንገናኛቸው ናቸው፡፡ ማንኛውንም ሰው ከምንወደው በላይ ቤተሰቦቻችንን ብንወድም እንኳ፣ አንዳንዴ አነስተኛ ፍቅርን እና አክብሮተን እናሳያቸዋለን፡፡ የየዕለት አኳኋናችን ይሰማቸዋል እናም በድርጊቶቻችን ተጽዕኖ ያድርባቸዋል። አኳኋናችን የእነርሱን አኳኋን ሊያንጸባርቅ ይችላል እናም አኳኋናቸውም ዘወትር የእኛን ያንጸባርቃል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ በሌሎች ላይ ተጽዕኖን እንዴት እንደምናሳድር ያለማቋረጥ ማወቅ አለብን፣ እናም ዘወትር በጐ የደስታ ነጸብራቅ እንዲኖረን መሞከር አለብን፡፡

ታሪክ

ቤተሰቦቻችን ላይ እንዴት ለመልካም ነገር ተጽዕኖ ልናደርግባቸው እንደምንችል የሚከተለው ታሪክ ያሳየናል፡፡

“መልከ መልካሙን የአሥራ ሰባት አመት ልጅ ጆንን በቤታችን ማግኘታችን በጣም እድለኞች ነን፡፡ ሁሌም አብረውት ሊኖሩ የሚገባ ግሩም ልጅ ነበር፣ ነገር ግን ከዓመት በፊት ከተለመደው በይበልጥ ተወዳጅ መሆኑን መንገንዘብ ጀምረናል፡፡ እርሱ ሰላም ፈጣሪያችን መሆን ጀምሯል፡፡ በቤት ውስጥ ችግር በተፈጠረበት ጊዜ ሁሉ፣ የእርሱ ፀጥተኛ፣ የረጋ፣ አቀራረብ ለቤተሰብ ወዲያው ሰላምን ያመጣል፡፡ አንድ ሰው በሚናደድበት ቀን ወይም በሚቀየምበት ቀን፣ ጆን ወደ ጥግ ይዞት በመሄድ ሲናገረው እና ያዘነው ልቡ እስኪረጋጋ ድረስ ሲያበረታታው እናያለን፡፡ እነርሱን እንደሚወዳቸው እና በመናገር የተለዩ እንደነበሩ በማሰብ የጻፈላቸውን ማስታወሻ ብዙውን ጊዜ የቤተሰቡ አባላት ነግረውኛል፡፡

“በስተመጨረሻም፣ ወደ እርሱ ሄድኩኝ እና በቤተሰብ ውስጥ የነበረውን ተጽዕኖውን እንደተገነዘብን እና እንደወደድንለት ነገርኩት እናም ለሁላችን ላሳየው አስደናቂ ዝንባሌ ምን ምክንያት እንዳለው ጠየቅሁት፡፡ መልሱን በፍጹም አልረሳም፡፡ እንዲህ አለ፣ ‘ቅዱሳን መጽሐፍትን በየቀኑ አነባለሁ እናም እነርሱም ህይወቴን ለውጠውታል፡፡’ በእርግጥም ህይወቱን ለውጠውታል እናም፣ ይህንንም በማድረጉ፣ የመላው የቤተሰባችንን ህይወት እና መንፈስ ለውጧል፡፡”

ጥቁር ሰሌዳ

• ጆን ቤተሰቡን በምን መንገዶች ረዳ? የወጣት ወንዶችን መልስ በጥቁር ሰሌዳው ላይ “በሰው ዘንድ ሞገስ” በሚለው ሥር ዘርዝር፡፡

---

### እያንዳንዱ የአሮናዊ የክህነት ሥልጣን ያዥ በቤተሰቡ ውስጥ አስፈላጊ ሚና አለው

እንቆቅልሽ እና ውይይት

ለሁለት ወይንም ሦስት ወጣት ወንዶች በከፊል ያልተሟላን እንቆቅልሽ ስጣቸው፣ እናም እንዲገጣጥሙት ጠይቃቸው፡፡ ጠፍቶ የጐደለውን ክፍል በሚጠይቁህ ጊዜ፣ አሟላላቸው። ከጨረሱ በኋላ፣ እንቆቅልሹ ከመቀጠሉም በፊት እንቆቅልሾቹን የያዙትን ቁራጮች በሙሉ ሰብስባቸው።

• የጐደለው የእንቆቅልሽ ክፍል ለሌሎች እንቆቅልሾች ለምን አስፈለገ?

• ማንኛውም የእንቆቅልሽ ክፍል ቢጐድል የሚፈጥረው ልዩነት አለን? (እንቆቅልሹን ለማሟላት ሁሉም ቁራጮች ጠቃሚ ናቸው፡፡)

• እንቆቅልሹ እና የጠፋው የእንቆቅልሽ ክፍል ከቤተሰቦች ጋር በምን ይዛመዳል?

• በቤተሰባችን ውስጥ ብዙ አባላት ቢኖሩም እንኳ፣ አንድ አባል በማይኖርበት ጊዜ ለምን ሙሉነት አይሰማንም?

እያንዳንዱ ሰው በቤተሰቡ ውስጥ ልዩ ቦታ እና የሚያበረክተው የተለየ አስተዋፅዖ እንዳለው ቡድኑ እንዲረዳ እርዳ፡፡

የትኛውም ግለሰብ ሆነ የቤተሰብ አባል ሊኖረው በቶይችልበት ጊዜ እያንዳንዱ ልጅ በልቧ እና በቤተሰቡ ውስጥ የተለየ ሥፍራ እንዳለው አንዲት እናት በአንድ ወቅት እንዳሳሰበች ግለጽ። ያም ልጅ በሄደ ጊዜ፣ ልጁ እስኪመለስ ድረስ ባዶነት ወይም እንደማትጠቀም ሆና እንደተሰማት ተናገረች። በምድራዊ ቤተሰቦቻችንም እንዲሁም በሰማያዊው ቤተሰባችን ውስጥ ይህ ዓይነቱ ለእያንዳንዳችን ምክንያት አለው። ዘወትር ለእኛ የተለየ ቦታ ይኖረናል፣ በምንሄድበት ጊዜ እንናፈቃለን፣ እናም እስክንመለስ ድረስ ባዶነት ይኖራል፡፡ የሰማይ አባታችን ከእይታው በምንሰወርበት ጊዜ ይናፍቀናል እናም ልክ የምድራዊ ወላጆቻችን እንደሚሰማቸው ሁሉ እያንዳንዳችን ወደ ሰማያዊ ቤተሰቡ እንድንመለስ ይፈልጋል፡፡ ወደ እርሱ ዘንድ ለመመለስ የሚያስፈልጉንን መስፈርቶች ለማሟላት እንዲረዳን በምድር ላይ በቤተሰብ ባርኮናል፡፡

ታሪክ

የሚከተለው ታሪክ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ቤተሰቦቹ ምን እንደሚሰማቸው ይገልጸል፡፡

“ከዕረፍት ጊዜያችን ወደ ቤት ሰንመለስ፣ መኪናችን በሻንጣ እና በሰው ተጨናንቃ ነበር፡፡ የሴት አያቴ እና የወንድ አያቴ በዚያን ዓመት ከእኛ ጋር ነበሩ፣ ስለዚህ በመኪናው ውስጥ ስምንት ነበርን፡፡ ነዳጅ ለመሙላት በቆምን ጊዜ ልጆች እግራቸውን ለማፍታታት እና በአካባቢው ለመሮጥ ከመኪናው ወረዱ፡፡ ስቲቭ ወደ መኪናው ለመግባት በተመለሰ ጊዜ፣ ባዶ እግሩ በዘይት እና በግሪስ ተጨማልቀ አየሁት፣ እናም ጫማውን እና የእግር ሹራቡን ሰጠሁት እግሩን ታጥቦ ጫማውን እንዲያደርግ እና ከዚያ ወደ መኪናው ተመልሶ ወደሚፈልገው ሥፍራ እንዲቀመጥ ነገርኩት፡፡

“በመሃሉም፣ ለመኪናው ነዳጅ ሞላን እና ከምሳችን በኋላ ለመጠጣት ሎሚናት ወደ ገዛንበት ፈጣን የምግቦች መደብር ተጓዝን፡፡ ከዚያም ወደ ቤት ጉዞአችንን ጀመርን፡፡

“በግማሽ ሰዓት ውስጥ፣ የምሳ ሰዓትም እንደደረሰ፣ ሳንድዊቾችን ማከፋፈል ጀመርኩ፡፡ ከመኪናው በስተጀርባ አካባቢ ‘ስቲቭ ምን፣ ዓይነት ሳንድዊች ነው የምትፈልገው?’ ብዬ ተጣራሁ፡፡

“ብዙ ጫጫታ ስለነበረ መልሱን መስማት አልቻልኩም፣ ስለዚህ ትንሽ ጮክ ብዬ ጥያቄዬን ደገምኩኝ፡፡ ምንም መልስ አልተመለሰም፡፡ ከዚያም ‘ስቲቭ እዚህ የለም፡፡ መኪና ውስጥ የለም፡፡ ከነዳጅ ማደያው ጋር ነው የቀረው’ በማለት ልጆች መጮህ ጀመሩ፡፡

“እውነት ነበር፡፡ ስቲቭ ከእኛ ጋር አልነበረም፡፡ ሰውነቱ የቀዘቀዘ ልጅ ወደ እኔ የሚመጣ መስሎ ተሰማኝ እናም የታመምኩ እስኪመስል ድረስ መላ ሰውነቴ በስጋት ደረቀ፡፡ የእኔ ትንሹ ስቲቭ በመፍራት እና ለምን እንደጣልነው በማሰብ ብቻውን ከነዳጅ ማደያው ዘንድ ቀርቷል፡፡

“ነጻ መንገዱን ወዲያው ልናቋርጥ አልቻልንም፣ ስለዚህ ባለቤቴ አዙሮ ወደ አካባቢው እስኪመለስ ድረስ፣ ከጠፋው ህጻን ልጃችን፣ ርቀን መሄዱን ቀጠልን፡፡ ትክክለኛ አቀጣጫውን ይዘን በመጓዝ ወደ ነዳጅ ማደያው ቶሎ ለመመለስ ፍጥነታችንን መቆጣጠር አልቻልንም፡፡

“እነዚያ አርባ አምስት ደቂቃዎች አርባ አምስት ስዓታት መሰሉ። ሁሉም ዓይነት ሐሳብ በየመልኩ በአዕምሮዬ ውስጥ ተመላለሰ። በዳገት የሚጓዝ ፓትሮል ይዞት እኛ ላይ ለመድረስ እየሞከረ ያለ ቢሆንስ! እኛ በዚህን ጊዜ ወደ ቤት እየተመለስን ነው፡፡ በፍጹም አያገኙንም፡፡ ሌላ ሰው ይዞት ቢሆንስ! አምርሮ ያለቀስ እና በጣም ይፈራ ይሆን? እያንዳንዳችን ሌሎችን ለማጽናናት እየሞክር ነበር፡፡ ወንድሞቹ እና እህቶቹ ለእርሱ ፈርተው ይጮሁ ነበር፡፡ አያታችን በመቀመጫው ጫፍ ላይ ነበረች፡፡ የተቻለውን ያህል ተጠንቅቆ አባቴ በፍጥነት እየነዳ ነበር፡፡ አያቴ ደግሞ ይወተውተው ነበር፡፡ በዚሁም ወዲያው እዚያ እንደምንደርስ እና ሁሉም ደህና እንደሚሆን ይነግረኝ ነበር፡፡

“ማደያው ጋር በደረስን ጊዜ፣ ስቲቭ በአንድ ደግ ሰው እጅ በጥብቅ ተይዞ ያን ያህል ሰዓት ይጠብቅ ከነበረ ሰው ጋር ቆመዋል። በሙሉ ቆመዋል፡፡ ሰውዬው ቤተሰቦቹ ወዲያው ተመልሰው እንደሚመጡለት እየነገረው እና እያጽናናው ነበር፡፡ ስቲቭ አያለቅስም ነበር፣ ነገር ግን የተናደደ እና የፈራ ይመስል ነበር፡፡ ማቆሚያው ላይ ደረስን እናም በሩን ገፍትሬ ከፈትኩኝ፡፡ ሮጦ እና ዘሎ በክንዴ ውስጥ ገባ። ሁላችንም ማልቀስ በጀመርን ጊዜ፣ የተቀላቀለው እንባችን ህመማችንን እና ፍርሃታችንን የጠረገልን መሰለ፡፡ በመኪናው ውስጥ በእያንዳንዱ ጉንጭ ላይ የደስታ እምባ ይታይ ነበር፡፡ ይህም ዳግም መገናኘታችን ሁላችንም የማንረሳው አንድ ነገር ነበር፡፡ ሁላችንም እንደ አንድ ቤተሰብ ተመልሰን መገናኘት ማለት፣ የማይገለጽ ደስታ ነበር፡፡ ከእኛ አንዳችን በጠፋን ጊዜ፣ እያንዳንዱ ሃሳብ፣ የልብ ትርታ፣ ጸሎት ለእሱ ነበር፤ እርሱ ከተገኘ በኋላ ብቻ ነው እንደገና አንድ የነበርነው፡፡”

---

**ማጠቃለያ**

| | |
|---|---|
| ምስክርነት | ስለቤተሰብ እና ስለ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል አስፈላጊነት ለወጣት ወንዶቹ ምስክርነትን ስጥ፡፡ ስለ እራስህ ቤተሰብ ስሜትህን መግለጽ ትችላለህ፡፡ |
| ሙከራ | እያንዳንዱ ወጣት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ አንዱን ጠቃሚ ሐሳብ እንዲወስድ እና በሚቀጥለው ሳምንት ውስጥ በዚያ በተወሰነ የህይወት ክፍል ውስጥ ለመሻሻል እንዲጥር አበራታታ፡፡ |

# 11

# “እኔ እንደወደድኳችሁ፤ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ”

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ሌሎችን በደግነት እና በአክብሮት ያስተናግዳል፡፡ |
| **ዝግጅት** | 1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣<br>ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት፡፡<br>ለ. ጥቀሶችን ምልክት ለማድረጊያ እርሳስ፡፡<br>2. በክፍል ውስጥ ላለው ለእያንዳንዱ ሰው የዮሐንስ ወንጌል 13፡34–35 ቀጂ አዘጋጅ፡፡<br>3. *ለወጣቶች ጥንካሬ* በሚለው መጽሐፍ በገጽ 9 ላይ ስለ *ወዳጅነት የተሰጠውን*ምክር ክልስ፡፡ |

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**ሌሎችን በደግነት ማስተናገድ አለብን**

ታሪክ

የሚከተለውን ታሪክ ለወጣት ወንዶች አካፍል፣

“አንዲ ማንም የሚወደው ደስ የሚል፣ አስደናቂ ህጻን ልጅ ነበር። ነገር ግን ችኩል ነበር ምክንያቱም አንዲ ድሬክን በዚህ መልኩ ነበር አንድ ሰው ያስተናገደው፡፡ ጥሩ ተጫዋች ነው እናም በእያንዳንዱ የዓይኑ ጭፍን ‘አመሰግናለሁ፣ አመሰግናለሁ፣ አመሰግናለሁ’ የሚሉ በሚመስሉ ትላልቅ ዓይኖቹ ፈገግታን ያጅባል፡፡ ማንኛችንም . . . እፍረታችንን ለመወጣት በምንፈልግበት ጊዜ አንዲ የሚያበረታታን ልጅ ነበር፣ እስከ አሁን ድረስ ይህንን ልዩ ክፍያ ለቡድናችን አንድነት ለመክፈል ደስተኛ ነው. . . .።

“ . . .ከአባላቱ ጋር መቀላቀል ለሁላችንም መብታችን እንደሆነ አስተያየታችን ግልጽ ነው ነገር ግን አንዲ በእኛ ፈቃድ እዚያ ነበር ሁላችንም አንዲን እስከዚያን ቀን. . . . እስከዛች ሰዓታም ቢሆን እንወደዋለን፡፡

“ ‘እርሱ የተለየ ነው! አንፈልገውም፣ አይደል?’ ማንኛችን ነበር ያልነው? . . . ማን እንዳለው ለማስታወስ በታማኝነት መናገር አልችልም፣ እነዚያን ጨካኝ የሥራፈት ውሸት ከመሃከላችን ማን እንዳለው ለማስታወስ በታማኝነት መናገር አቭችልም፣ ምንም ችግር የለውም ምክንያቱም አስለቀሶን ለጥልቀ ስሜት አጋልጦናል . . .

“ይህኛው የሳምንቱ መጨረሻ ቡድኑ አብሮ የተደሰተበትን ያለፈውን ብዙ ሳምንት ይመስል ነበር፡፡ አርብ ከትምህርት በኋላ፣ በአንዳችን ቤት እንሰበሰባለን—ይህ ጊዜ የኔ ነው— በቀርበት በሚገኘው ደን ውስጥ ነው የምንሰበሰበው፡፡ እናቶቻችን፣ ለዚህ ሽርሽር ዝግጅቱን በበለጠ ያደረጉልን ከተለመደው ሥራችን በኋላ ዘወትር ተጨማሪ ጅንያዎችን ለአንዲ ያስይዙት ነበር።

“ . . . የእኔ ግብዣ እስከሆነ ድረስ አንዲ እንዳልተጋበዘ መናገር ያለብኝ እኔ እንደሆንኩ ሌሎች ነገሩኝ— ሌሎቹ ከሚያስቡልኝ በላይ የሚያስብልኝ አንዲ ነው ብዬ ሳስብ ነበር ምክንያቱም በሚያየኝ ጊዜ ልክ ታዛዥነቱን በዓይኑ ለመግለጽ እንደሚሞክር ወንድ ውሻ ነው የሚሆነው፡፡ ያ አስደስቶኛል፡፡

“በአሮጌው ካናቴራው ላይ የተለያየ መልክ እንዲንጸባረቅ የምሽቱ ብርሃን በጥቁር ቀጭን የዛፎች ቀዳዳ ያልፍ ስለነበር አንዲ ወደ እኛ ሲመጣ ማየት ቻልኩ፡፡ ባረጀች፣ በዛገች፣ የአትክልት ጉማም ከቸርኬው ጋር በሽቦ ከታሰረባት፣ የሴቶች ሞዴል ብስክሌቱ ላይ ተቀምጦ ነበር። በህይወቱ ሁሉ ጎረምሳ የመሰለው እና ከቡድኑ ጋር የመጀመሪያ ጊዜ መዝናናትን እና ቀልድን የሚፈልገው ይህ ህጻን ልጅ ከዚህ በፊት ከአየሁት የበለጠ ደስተኛ መስሏል፡፡

“ካምፑን እያጸዳሁ ሳለሁ እጁን አወዛወዘልኝ። ሰላምታውንም ችላ አልኩት፡፡ ንግግሩን ሳያቋርጥ ከብስኬሌቱ ወርዶ በሶምሶማ ወደ እኔ መጣ። በድንኳኑ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ የተሸሸጉት ልጆች ፀጥ ብለዋል ነገር ግን እንደሚያዳምጡ የሰማኛል፡፡

“ለምን ኮስተር አይልም? ፊት እንዳልሰጠሁት መመልከት አይቻለውምን? አሁን ማጉረምረሙ እኔ ጋ እንደማይደርሰው አይመለከተምን? ከዚያም በድንገት ተመለከተ፣ ንጹህ ገጽታው ከሁሉም በበለጠ ሁኔታ በቀላሉ የሚጐዳ እንዲመስል አድርጎታል። የሚያሳየው ፀባይ በሙሉ እንዲህ ይላል፣ ‘በጣም መጥፎ ይሆናል፣ አይደለምን? እንያዘው።’ ያለምንም ጥርጥር ንዴትን መጋፈጥ የለመደው፣ ለጡጫው ምንም ድጋፍ አላደረገም።

“በማይታመን ሁኔታ እራሴን እንዲህ ስል ሰማሁት፣ ‘አንዲ አንፈልግህም፡፡’ በብሩህ የማስታውሰው ከአይኖቹ ውስጥ ሁለት ትላልቅ የእንባ ዘለላዎች በፍጥነት ያመነጨው እና እዛው የቀመው ነው—በረታሁኝ

ምክንያቱም በአዕምሮዬ ውስጥ ሚሊዮን የዕብደት አስፈሪ ድርጊት ሲመላለስ አይቻለሁኝ፡፡ በዚህ መልኩ— ለዘለዓለም ድርቅ ብሎ—ወደ እኔ ተመለከተ፤ ምንድን ነበር? ጥላቻ አልነበረም፡፡ መንቀጥቀጥ፣ አላምንም ወይም– ለእኔ አዝኖ ነበር?

“በመጨረሻም፣ ቀላል መንቀጥቀጥ ከንፈሩን አንቀጠቀጠው፣ እናም ያለምንም ተቃውሞ ዞረ. . . .

“እናም ስምምነት ነበር፡፡ ምንም ምርጫ አልተደረገም፣ ምንም ቃል አልተነገረም፣ ነገር ግን ሁላችንም አውቀናል፡፡ አንድን ነገር በአስፈሪ ሁኔታ፣ በጭካኔ እንደሠራን አውቀናል፡፡ እራሱን በመሳሪያ ለመከላከል ምንም መንገድ በሌለው— በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን ሰው ገድለናል፡፡” (Ben F. Burton, ከ *Today’s Education*, the Journal of the National Education Association, ጥር 1967; በፈቃድ የተወሰደ)፡፡

ውይይት

• አንዲ እንዴት ተሰምቶታል ብላችሁ ታስባላችሁ? (ሐዘን፣ ዋጋ ቢስነት፣ ብቸኛኝነት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ አቀመቢስነት፡፡)

• ሌሎች ወንዶችስ ምን የተሰማቸው ይመስላችኋል? (ጥፋተኝነት፣ ኀፍረት፣ ገብጋባነት፣ ራስ ወዳድነት፣ ሐዘን፡፡)

• ይህ ተቀባይነትን ማጣት አንዲን እንዴት ይጐዳዋል?

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

• አዳኛችን በምድር ላይ በነበረበት ወቀት ሌሎችን እንዴት መንከባከብ እንዳለብን አሳይቶናል፡፡ ሌሎች ሰዎችን—ጓደኛን፣ ጠላትን ወይም እንግዳን—እንዴት እንደምንይዝ ጥርጣሬ በገባን ጊዜ ምን መመሪያን መከተል እንችላለን?

መልሱን ለማግኘት፣ ወጣት ወንዶች የዮሐንስ ወንጌል 13፡34–35 ገልጠው በጸጥታ እንዲያነቡት ጠይቀ፡፡

• ኢየሱስ ምን እንድናደርግ ነገረን?

በእውነት አዳኛችንን የምንወድ ከሆነ እርስ በእርሳችን እንደምንወዋደድ ግለጽ፡፡ እያንዳንዱን ሰው በደግነት በማስተናገድ ይህንን ፍቅር ልናሳይ እንችላለን፡፡ ሌሎችን ሳንወድ ግን ኢየሱስን እንወዳለን ብንል እውነተኛ ደቀመዛሙርቶቹ አይደለንም፡፡

• ሌሎቹ ልጆች ለአንዲ ደግ ቢሆኑ ኖሮ ታሪኩ እንዴት ያበቃ ነበር?

• የአንዲን በመሰለ ሁኔታ ውስጥ ገብተህ ታውቃለህ? እናም አንድ ሰው በጥሩ ሁኔታ አስተናግዶህ ያውቃልን? ምን እንዲሰማህ ነበር ያደረገህ?

ምናልባት በክፌል የተለየ ሆኖ እና ከጓደኞቹ በጥሩ ሁኔታ ሳይግባባ ቀርቶ በክፌል ተሳትፎን የቀነሰ ሰው ካለ ሁኔታውን ለመወያየት ይህ ጥሩ ጊዜ ሊሆን ይችላል፡፡ የኢየሱስን ትምህርት ለመከተል እና ተሳትፏቸውን የቀነሱትን ወጣት ወንዶች እንዲያበረታቱ እራሳቸውን አሳልፎ እንዲሰጡ ወጣት ወንዶችን ጠይቀ፡፡

---

**ደግ የሆኑ ወጣት ወንዶች የሌሎችን ክብር እና ፍቅር ያገኛሉ**

የማሰላሰያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጸጥታ እንዲመልሱ ለወጣት ወንዶቹ ንገራቸው፡፡ ወጣት ወንዶች ከእራሳቸው ጋር ታማኝ መሆን እንዳለባቸው አበክረህ ግለጽ፡፡

• በምትሰራው ነገር ላይ አንድ ሰው ሐሳብ ቢሰጥ እንዴት ይሰማሃል?

• ብቃት እንዲሰማህ የሚያደርግህ ምንድን ነው?

• ሌሎች ከልባቸው እንዲያደንቁህ ትፈልጋለህን?

• ብቃት እንዳለው ሰው አድርገው ሌሎች እንዲያስቡህ ትፈልጋለህን?

ውይይት

• አንድ ወጣት የሚፈልገውን ፍቅር እና አክብሮት እንዴት ማግኘት ይችላል? (ባለመለወጥ ለሌሎች ደግ የሆኑ ሰዎች የሌሎችን ፍቅር እና አክብሮት ያገኛሉ— እናም ስለራሳቸው ጥሩ ይሰማቸዋል፡፡)

ምሳሌያዊ ጥናቶች እና ውይይት

የሚከተለውን ምሳሌያዊ ጥናት አቀርብ፡

ምሳሌያዊ ጥናት 1

ቲም—ጀፍ፣ ቻድ፣ ማት እና ዴቭ የሚባሉ የእራሱ የሆኑ የጓደኞች ቡድን ነበረ፡፡ ዘወትር በትምህርት ቤት እና በቤተክርስቲያን ነገሮችን አብረው ይሰራሉ፡፡ በእርግጥ አልፎ አልፎ አለመግባባት ይከሰታል ነገር ግን ወዲያው ይፈታል እናም ልጆች እንደገና ጓደኛሞች ይሆናሉ፡፡ ይህም ቢል ወደ ዋርዱ እስከ ተቀየረበት ጊዜ ድረስ ቀየ፡፡ ቲም እዚያ በነበረበት የመጀመሪያ እሁድ ቢልን አየው እናም እንዴት ነህ አለው፡፡ ነገር ግን የተቀሩት ልጆች የቢል ጓደኛ ለመሆን አልፈለጉም፡፡ የቡድናቸው አካል እንዲሆን አልፈለጉትም ነበር፡፡ ቀስ በቀስ፣ ከቲም ጋር ቢል በበለጠ ጓደኛ ሆነ፡፡ ቲም የተቀሩት ልጆች ከእሱ ጋር እስከዚህም እንደሆኑ ተገነዘበ፡፡ ምክንያቱም ቢል ጥሩ እንዲሰማው እየሞከረ በመሆኑ እንደነበር ተገነዘበ፡፡

• እናንተ ቲምን ወይም ቢልን ብትሆኑ ምን ይሰማችሁ ነበር?

• አዳኛችን ምን እንድታደርጉ ይፈልጋል? ለምን?

ምሳሌያዊ ጥናት 2

ሮብ የሚችለውን ያህል ተጫወተ ነገር ግን ቡድኑ አሁንም ተሸንፈዋል—በብዙም ባይሆን ግን ተሸነፉ። ከግጥሚያው በኋላ የሮብ ቡድን ልጆች እርስ በእርሳቸው በመነጋገር ላይ ሳሉ፣ ከእነርሱ አንዱ “ፖል በቡድናችን ውስጥ ባይኖር ኖሮ እናሸንፍ ነበር። ፖል በጣም ቀርፋፋ ነው በራሱ እግር ይደናቀፋል” ’ ሲል ሮብ ሰማው። ፖል አስተያየቱን የሰማ እንደሆን ለማየት ሮብ በዓይኑ ቃኘ። በቅርብ ሆኖ የጨዋታ መሳሪያዎችን እየሰበሰበ ነበር፣ እናም ፖል ተቸቱን ይስማ አይስማ ሮብ በእርግጥ አያውቀም።

- ፖል አስተያየቱን ቢሰማ ኖሮ መልሱ ምን ይሆን ነበር? እንዴት ይሰማዋል?
- እነዚህ ስሜት ጎጂ ነገሮች እንዴት ሊወገዱ ይችላሉ?
- አንድ ጥሩ ያልሆነ ድርጊት እንዴት ወደ ሌላ ነገር ሊመራ ይችላል?

**ውይይት**

ወጣት ወንዶች በቤት፣ በትምህርት ቤት ወይም በቤተክርስቲያን ሌሎችን በበለጠ በደግነት የሚያስተናግዱባቸውን አያሌ መንገዶች ሐሳብ እንዲያቀርቡ ጠይቅ። አንድ ሰው በአስፈሪ ወይም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለአንተ ሩህሩህ በመሆን አንተን ለመርዳት ደግ የሆነበትን የእራስህን ተመሳሳይ ታሪክ መናገር ትችላለህ።

ከፈለጉ ተመሳሳይ ልምድን እንዲያካፍሉ ወጣት ወንዶችን ጋብዝ።

አስፈላጊዎች ነን ብለን እራሳችንን ብናስብም እርስ በእርስ ከመዋደድ እና የአዳኛችንን ምሳሌ ከመከተል ውጪ የፍላጎታችንን በፍጹም ማድረግ እንደሌለብን አስረዳ። ሌሎችን ዘወትር በደግነት እና በአክብሮት ማስተናገድ አለብን።

**ታሪክ እና ውይይት**

የእግዚአብሔር ነቢይ አብሮት ለሚጓዘው ጓደኛው ያሳየውን የሚከተለውን የደግነት ታሪክ አካፍል፣

“በጉዟችን መጀመሪያ ላይ፣ በፕሬዚዳንት ኪምቦል እና በእህት ኪምቦል ምክንያት ከእነርሱ ጋር ከሚሄዱት ሌሎች ሰዎች ጋር ተጓዝኩኝ። እኔና ሚስቴ በሶልት ሌክ ከተማ በተሳፈርን ጊዜ፣ ከፕሬዚዳንት ኪምቦል በስተጀርባ ሆነን ተቀመጥን። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም አውሮፕላኑ ተነሳ እናም የመቀመጫው የቀበቶ ምልክት ተቀየረ፣ ፕሬዚዳንት ኪምቦልም ወደ እኛ በመዞር ‘ተመቸቷችኋልን?’ አለን። እዚያ የነበርኩት እርሱን እና ከእርሱ ጋር ያሉትን ሌሎች መንገደኞችን ለመርዳት ነበር፣ ነገር ግን ለእኛ እንደሚያስብ አሳየን። ይህ ታላቅ፣ ደግ፣ ጓደኛ የሆነ ሰው በጉዞው ሁሉ በአካባቢው ስለሚገኙት ሰዎች ደህንነት ይጨነቅ ነበር። በሩህሩህነቱ እና በደግነቱ ምክንያት ከእርሱ ጋር ባደረግነው ጉዞ ደስ ብሎናል” (James O. Mason, “Traveling with a Missionary Prophet,” *New Era*, ጥቅምት 1977, ገጽ 6)።

- ይህ ለሌሎች ደግ መሆን ሊማሩት የሚቻል ልማድ ሊሆን ይችላል? እንዴት?

---

### ለሌሎች ደግ መሆን ለአዳኛችን ያለንን ፍቅር ያሳያል

**ጥቀስ እና ውይይት**

የሚከተለውን ሁኔታ አስረዳ፣

ለወጣቶች ጉባኤ፣ “የአገልግሎት ዋጋ” የሚባለውን ወርክሾፕ ለማቀድ እና ለመስጠት እንዲሳተፉ ብዙ ወጣት ወንዶቹ ተጠየቁ። “ትናንሽ ነገሮች” በሚል መልእክት ላይ የተመረኮዘ ነበር። መልዕክቱን ለሌሎች በእውነት ማቅረብ እንዳለባቸው ወሰኑ፣ ስለዚህ ከጉባኤ በፊት ለብዙ ወራት፣ ትናንሽ ነገሮችን—ለቤተሰቦቻቸው፣ ለጐረቤቶቻቸው፣ ለጓደኞቻቸው፣ ለጳጳሳቸው እና ለሌሎች በማከናወን አገልግሎትን ለመስጠት ሞከሩ። ከወጣት ወንዶች አንዱ ለኮሚቴው የሚከተለውን ምስክርነት ሰጠ።

“ ‘አባት ሆይ፣ መልካም ቀን እንዲኖረኝ እርዳኝ።’ እያልኩ በእያንዳንዱ ቀን እጸልይ ነበር። አንድ ቀን ያ የራስ ወዳድነት ጸሎት እንደሆነ ወሰንኩኝ። ለሰማይ አባት አንድ ነገር ማድረግ እንደምፈልግ ተሰምቶኝ ደስ አለኝ እናም ‘መልካም ቀን እንዲኖረኝ እርዳኝ’ ከማለት ይልቅ ‘ዛሬ መልካም ቀን እንዲኖረኝ እንዴት ልረዳህ እችላለሁ? ዛሬ ምን ላደርግልህ እችላለሁ? ዛሬ እንዴት ላስደስትህ እችላለሁ?’ ብዬ የሰማይ አባትን ጠየቅኩኝ።

“ከዚያም በኋላ በግልጽና በጥሩ ሁኔታ ቃላቶች ወደ አዕምሮዬ መጡ። ‘ዛሬ ልታስደስተኝ ከፈለክ ወደ ውጪ ውጣ እና አንተን የሚፈልገውን ሰው ፈልግ እና አንድ ነገር አድርግለት። ዛሬ ልታስደስተኝ የምትፈልግ ከሆነ ትዕዛዛቴን ጠብቅ።’

“የሰማይ አባትን ማስደሰት ማለት በቀላሉ ያን ማድረግ ብቻ ነው— ልጆቹን ማገልገል እና ትዕዛዛቱን መጠበቅ ማለት ነው።”

- ሌሎችን በደግነት እና በአክብሮት ማስተናገድ ለሰማይ አባታችን ፍቅርን እንዴት ያሳያል።

**ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት**

ወጣት ወንዶች ትምህርት እና ቃል ኪዳን 42፥38 እንዲከፍቱ አድርግ። ይህን ጥቀስ በትምህርት እና ቃል ኪዳን መጽሐፍ ውስጥ ምልክት እንዲያደርጉበት ወጣት ወንዶችን ጠይቅ።

ለእያንዳንዱ ወጣት የዮሐንስ ወንጌል 13፥34–35 ግልባጭ ስጥ።

- እነዚህን ጥቀሶች ማስታወስ ከሌሎች ሰዎች ጋር ላለን ግንኙነት እንዴት ሊረዳን ይችላል?

**ማጠቃለያ**

ሙከራ

በእነዚህ ሁለት ጥቀሶች አማካኝነት የደግነትን ሥራ እንዲያስቡ እና ዕድል በመጣ ጊዜ ሁሉ ደግ እንዲሆኑ ወጣት ወንዶችን ጠይቅ። በቤት ከቤተሰባቸው አባል ወይም በአሁኑ ጊዜ እጅግን በማያውቁቸው ወይም በጣም በማይወዱዋቸው ሰዎች መልካም አጋጣሚ እንደሚመጣ አስታውሳቸው።

*ለወጣቶች ጥንካሬ* በገጽ 9 ላይ ስለጓደኝነት የተሰጠውን ምክር ከልስ። ይህን ምክር እንዲተገብሩት እና በሚቀጥለው ሳምንት ውስጥ ለሌሎች ሰዎች ደግ የሚሆኑበትን መንገዶች እንዲፈልጉ ወጣት ወንዶችን አበረታታ። በሚቀጥለው የቡድን ስብሰባ መጀመሪያ ላይ ስለ ሥራቸው ዘገባ እንዲያቀርቡ ወጣት ወንዶችን አድርግ።

# 12 ህያው ነቢይን መከተል

**ዓላማው**

በእግዚአብሔር የተሾመውን ነቢይ አመራር ለማወቅ እና ለመከተል እያንዳንዱ ወጣት ይወስናል፡፡

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት፡፡
   ለ. የህያው ነቢይ ፎቶ።
   ሐ. የመዝጊያ ቁልፍ ወይም የመቀርቀሪያ ቁልፍ (አማራጭ ያለው)፡፡
2. በቅርብ ጊዜ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በህያው ነቢይ የተደረገውን ንግግር የያዘ ግልባጭ አግኝ፡፡ በተለይ ለክፍል አባላት ትርጉም ሊሰጥ የሚችለውን በህያው ነቢይ የተሰጡትን የተወሰኑ ዝርዝር ትዕዛዛትን ለማካፈል አጥና ወይም ተዘጋጅ፡፡
3. አንድ ወጣት አሞፅ 3፣7 እንዲያነብ እና ጥቅሱ ለእሱ ምን ማለት እንደሆነ በአጭሩ አስተያየት እንዲሰጥ መድብ፡፡

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**መግቢያ**

*አማራጭ ያለው በቁሳዊ የተደገፈ ትምህርት*

ወጣት ወንዶች ትክክለኛ ባልሆነ ቁልፍ ወይም መቀርቀሪያ ቁልፉን ለመክፈት እንዲሞክሩ አድርግ፡፡ ከዚያም ለምን ማንም ሰው ሊከፍተው እንዳልቻለ ጠይቅ፡፡ ምናልባት ወጣት ወንዶቹ ትክክለኛ ቁልፍ ወይም መቀርቀሪያ እስከሌላቸው ድረስ መክፈት እንደማይችሉ ሊናገሩ ይችላሉ፡፡ የተገለጡት የነቢይ መመሪያዎች ልክ እንደ ቁልፉ ወይም መቀርቀሪያ እንደሆኑ አስረዳ፡፡ እነርሱም የጌታን ፈቃድ ይገልጡልናል ወይም ይከፍቱልናል፡፡ ነቢይ ወደ ደህንነት እና ዘለዓለማዊ ህይወት የሚወስደውን መንገድ እንድንማር ይረዳናል፡፡

*ጥቅሶች*

እንደ ጌታ አገልጋይ፣ ነቢዩ "እውነቱን ለማወጅ እና ለቅዱሳን እና ለዓለም ምክርን እና ትዕዛዛትን ለመስጠት ከጌታ ብርሃንን እና ራዕይን . . . ይቀበላል" (Joseph Fielding Smith, በ Conference Report, ሚያዝያ 1972, ከገጽ 12–13; or *Ensign*, ሐምሌ 1972, ገጽ 27)፡፡

ቄስ ዴቪድ ቢ ሃይት ከአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት መማክርት አንድ ነቢይ የሚመራበትን መንገድ እንደሚከተለው አብሮ ገልጾአል፣ "ድምጹ አዲስ ፕሮግራሞችን፣ አዲስ እውነታዎችን፣ አዲስ መፍትሔዎችን . . . ለመግለጽ የእግዚአብሔር ድምጽ ይሆናል። በተቃውሞ ጩኸት ውስጥ ቢሆን ለመናገር ደፋር መሆን አለበት. . . . የሰለስቲያል ሹመቱን፣ ለአገልግሎት የመጥራት ስልጣኑን፣ ለመሾም፣ ዘለዓለማዊ ቁልፍን የሚስተካከሉ ቁልፎችን ለማስተላለፍ ለመለኮታዊ ምርጫው እርግጠኛ መሆን አለበት" ("Come, Listen to a Prophet's Voice," በ *Speeches of the Year*, 1976 [Provo: Brigham Young University Press, 1977], ገጽ 291)፡፡

**ጌታ በነቢያቱ አማካኝነት እውነቱን ይገልጻል**

*የመጽሐፍ ቅዱስ ዘገባ እና ውይይት*

ወጣት ወንዶች አሞፅ 3፣7 እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ የተመደበውን ወጣት አሞፅ 3፣7 እንዲያነብ እና በጥቅሱ ላይ የራሱን አስተያየት እንዲሰጥ ጋብዝ።

ትምህርት እና ቃል ኪዳን 1፣38ን አንብብ እና ተወያይ፡፡

- ከጌታ ድምፅ ጋር የሚመሳሰለው የማን ድምፅ ነው? (የነቢይ፣ የስቴክ ፕሬዚዳንት፣ የጳጳስ፡፡)

ጌታ ዘወትር በነቢያቶች አማካኝነት እንደሚናገር እና ወደፊትም መናገሩን እንደሚቀጥል እነዚህ እና ሌሎች ቅዱሳን መጽሐፍት እንደሚናገሩ አስረዳ፡፡ በ1829 ጌታ ለዮሴፍ ስሚዝ "ይህ ትውልድ ቃሌን በአንተ አማካኝነት ያገኛል" ብሎ ነግሮታል (ት እና ቃ 5፣10)፡፡ በ1830 ቤተክርስቲያኗ በተቋቋመችበት ወቅት ዮሴፍ ስሚዝ "ባለራዕይ፣—ነቢይ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ፣ በእግዚብሔር ፈቃድ አማካኝነት የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ትሆናለህ ተብሎ ተነገረለት ሌላኛውን ራዕይም ተቀበለ" (ት እና ቃ 21፣1)፡፡ ይህን ምንባብ ከአመሠራረቱ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ቤተክርስቲያኗን የመሩትን የሁሉንም ነቢያት ኃላፊነት ይገልጻል፡፡ በተሾሙ መሪዎቹ የተገለጡ ቃላት የእርሱ ቃላት እንደሆኑ ጌታ በበለጠ ገልጿል፣

"እናም በመንፈስ ቅዱስ . . . በመመራት የሚናገሩት ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሆናል፣ የጌታ ሐሳብ ይሆናል፣ የጌታም ቃል ይሆናል፣ የጌታም ድምጽ ይሆናል፣ እናም የእግዚብሔር የመዳን ኃይል ይሆናል" (ት እና ቃ 68፣4)፡፡

ጥቀስ እና ውይይት

እኛን ስለሚወደን እና ወደ እርሱ ዘንድ እንድንመለስ ስለሚፈልግ ጌታ ነቢያቱን እንደሚልክ አስረዳ። ነቢይ ክርስቶስን እንዴት እንደምንከተል እና ወደ እርሱ ዘንድም እንደምንመለስ ያስተምረናል። የበላይ አመራሩ ፕሬዚዳንት ኤን ኤልደን ታነር እንዲህ ሲሉ መስክሯል፣ “ከዚህ ቤተክርስቲያን አራት መሪዎች ጋር ሆኜ ጌታ በእነሱ አማካኝነት እንዴት እንደሚራ ለማየት ታላቅ እድል አግኝቻለሁኝ። በእውነተኛ እና በጽድቅ መንገድ ሲመሩን እና እራሳችንን . . . ለዘለዓለማዊ ህይወት እንድንዘጋጅ በሚረዱን ጊዜ ሰው ሲያይ የእግዚአብሔር ነቢያት መሆናቸውን አይጠራጠርም” (በ Conference Report, ጥቅምት 1980, ገጽ 5; or *Ensign*, ህዳር 1980, ገጽ 6)።

- የጌታ ፈቃድ በሾማቸው መሪዎች አማካኝነት እንደሚገልጽ በግል ማወቅ ለእያንዳንዳችን ለምን አስፈለገ?

---

**ህያው የሆነውን ነቢይ በምንከተልበት ጊዜ እንባረካለን**

የሥዕል ትምህርት አቀራረብ

የህያው ነቢይን ፎቶ አሳይ። የህያው ነቢይ የተገለጠ ምክርን እንድንከተል በተለይ የታዘዝን መሆናችንን ግለጽ።

በዚህን ጊዜ ለቤተክርስቲያኑ አባላት ህያው ነቢይ ትዕዛዛትን ከጌታ እንደሚቀበል አስረዳ። እያንዳንዱ ትውልድ በተለያየ ሁኔታ ስለሚኖር ጌታ በእያንዳንዱ ትውልድ ውስጥ ቤተክርስቲያኑን በነቢያት አማካኝነት ይመራል።

ጥቀስ

“በዚህ የጊዜ ሙላት ዘመን፣ በሌሎች ዘመናት ፈጽሞ ያልተገለጹ እና የእያንዳንዱን ዘመን አስፈላጊ ነገሮች የሚገልፁ ነገሮች ሁሉ አለን . . .።

“አዎን፣ በህያው ነቢይ፣ በባለራዕይ እና በትንቢት ገላጭ እናምናለን. . . .። ባለፉት ጊዜያት በተሰጡት ራዕዮች ላይ ብቻ ጥገኛ የምንሆን አይደለንም ነገር ግን እግዚአብሔር ሐሳቡን እና ፈቃዱን የሚገልጥለት እና እየገለጠለት ያለውን የእግዚአብሔር ወኪል አለን” (Harold B. Lee, *Stand Ye in Holy Places* [ሶቭት ሌክ ከተማ : Deseret Book Company, 1975], ከገጽ 161, 164)።

የህያው ነቢይ ግልጽ አመራር የቤተክርስቲያን አባላት መከራ እንዲቋቋሙ፣ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ፣ ጌታን ከመታዘዝ የሚመጡትን በረከቶች ሊሰበስቡ ዘንድ እንደሚረዳ አስረዳ።

የጥቁር ሰሌዳ ተግባር

*የነቢዩን ትዕዛዝ* ብለህ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከላይ በግራ በኩል ጻፍ እናም *የተስፋ ቃሎቹን* እና *በረከቶቹን* በማለት ከላይ በቀኝ በኩል ጻፍ።

የነቢዩን መልዕክት በመጠቀም፣ መልዕክቱን በማካፈል እና የተወሰኑ ትዕዛዛትን እና የተወሰኑ የተስፋ ቃሎችን እና በረከቶችን በማካፈል የነቢዩን ጉዳይ እንዲያደንቁ ወጣት ወንዶችን እርዳ። የነቢዩን ምክር በሚሰሙበት ጊዜ ወጣት ወንዶች ነገሩን በዝርዝር እንዲያቀርቡ አድርግ።

የነቢዩን ምክር ለመቀበል ወዲያውኑ ምክንያት እንደማናገኝ ግለጽ። ለምሳሌ ከ 150 ዓመት በፊት ጌታ በነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ አማካኝነት ተምባሆ፣ ቡና እና ሻይ ለሰውነት ጉጂዎች እንደሆኑ ገልጿል። በዚያን ጊዜ፣ ሰዎች እነዚያ ነገሮች ጉጂዎች እንዳልሆኑ ያስቡ ነበር፣ እናም በዚህ ራዕይ ተገርመው ነበር። ከብዙ ዓመታት በፊት ነቢዩ የገለጸውን እውነታ ሳይንቲስቶች ያረጋገጡት በቅርቡ ነበር። ነቢዩን የተከተሉ እና የጥበብ ቃልን ያከበሩ ብዙ ቅዱሳን ስለታዛዥነታቸው በመንፈስ እና በአካል በረከትን አግኝተዋል። እንደዚሁም፣ የነቢዩን ምክር ከታዘዝን እንባረካለን።

---

**ማጠቃለያ**

ጥቀስ እና ውይይት

ወጣቶችን በመምራት እና በማስተማር አብዛኛውን ህይወቷን ያሳለፈችው፣ እህት ኤሌይን ኤ ካኖን፣ ስለ ሕያው ነቢይ ይህን ምስክርነት ሰጥታለች፣ “አሁን፣ እሱ ሲናገረን . . . ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱ የሚናገረን ነው የሚመስለው . . .ከዚህ ቀደም ለልጆቹ ‘እናንተን እንዲያገለገሉ የሾምኩአቸውን . . . የእነዚህን ቃላት የምትሰሙ ከሆናችሁ ብሩካን ናችሁ’ ብሎ በተናገረበት ወቀት ክርስቶስ ይህን በጣም ግለጽ አድርጓል (3ኔፊ 12፥1) . . . መንገዳችሁ ንጹህ መሆን አለበት ምርጫችሁ ለእናንተ መታወቅ አለበት . . . የግል ሐሳብ ይለያያል። ዘለዓለማዊ መርሆች በፍጹም አይሰሩም። ነቢይ በሚናገርበት ጊዜ . . . ክርክር ያበቃል” (“If We Want to Go Up, We Have to Go On,” *New Era*, ጥር–የካቲት 1979, ከገጽ 40–41)።

- ነቢይ በሚናገርበት ጊዜ ክርክር አይኖርም ስትል እህት ካኖን ምን ማለቷ ነው?
- ይህ ለምን ያስፈልገናል?

ምስክርነት እና ሙከራ

ህያው ነቢይ የማግኘትን በረከት መስክር። እያንዳንዱ ወጣት በትምህርቱ ውስጥ ንግግር ከተደረገበት የነቢዩ መልዕክት አንዱን ትዕዛዝ እንዲመርጥ እና በየቀኑ በበለጠ እንዲያከብር አበረታታ። በተጨማሪም ክፍሉ የነቢዩን የወደፊት ምክር በበለጠ በጥንቃቄ እንዲሰሙ እና የየዕለት ውሳኔዎቻቸውን ለመፈጸም እንዲጠቀምበት አጠናክር።

# 13 እያንዳንዱ አባል ሚሲዮናዊ ነው

**ዓላማው** እያንዳንዱ አባል ሚሲዮናዊ እንደሆነ እያንዳንዱ ወጣት ይረዳል፡፡

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት፡፡
   ለ. ጥቅሶችን ለማስመሪያ እርሳሶች።
2. በትምህርት ላይ እንዲነበብ የሚከተሉትን ጥቅሶች የያዙትን ብጣሽ ወረቀቶች አዘጋጅ፣ ማቴዎስ 24፥14፤ ማቴዎስ 28፥19–20፤ ማርቆስ 16፥15፤ ትምህርት እና ቃል ኪዳን 90፥11፤ እና ትምህርት እና ቃል ኪዳን 133፥37፡፡
3. (አማራጭ) "አንድ ሰው ይጠብቃችኋል" የሚለውን የሚገልጽ ተለጣፊ የቃላት መስመር እና በእጅ የተዘጋጀ ጽሑፍ ለእያንዳንዱ ወጣት አዘጋጅ።
4. ስለ ሚካኤል ታሪክ እንዲናገር ወጣቱን ቀደም ብለህ አዘጋጅ (ትምህርቱን ተመልከት)፡፡

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

## የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ ወንጌልን መስማት አለባቸው

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፣ ሰሌዳ እና ውይይት

በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይህን ጻፍ፣ *ወንጌልን የሚቀበለው ማን ነው?* ይህን ጥያቄ ቅዱሳን መጽሐፍት እንደሚመልሱት አስረዳ፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ማጣቀሻን የያዘውን ወረቀት እንዲመለከቱት ለአምስት ወጣት ወንዶች ስጥ፡፡ ጥቅሳቸውን ጮክ ብለው እንዲያነቡ እና ከዚያም ወንጌልን ማን መማር እንዳለበት እንዲናገሩ ጠይቃቸው፡፡ መልሶቹ ከታች በቀንፍ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ መልሳቸውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ፡፡ እነዚህን ምንባቦች ከፊል ምልክት እንዲያደርጉባቸው ወጣት ወንዶችን አበረታታ።

ወንጌልን የሚቀበለው ማን ነው?

| | |
|---|---|
| ማቴዎስ 24፥14 | (ዓለም በሙሉ) |
| ማቴዎስ 28፥19–20 | (አህዛብ በሙሉ፡፡) |
| ማርቆስ 16፥15 | (እያንዳንዱ ፍጡር፡፡) |
| ትምህርት እና ቃል ኪዳን 90፥11 | (እያንዳንዱ ሰው በቋንቋው፡፡) |
| ትምህርት እና ቃል ኪዳን 133፥37 | (እያንዳንዱ አህዛብ፣ ዘር፣ እና ማንኛውም ቋንቋ ተናጋሪ እና ህዝብ፡፡) |

ወጣቱ ትምህርት እና ቃልኪዳን 18፥10 እንዲያነብ ጠይቅ፡፡

• እያንዳንዱ ሰው ወንጌልን የመስማት ዕድል ማግኘቱ ለምን አስፈለገ?

ጥቅስ

"እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር አምሳል እንደሆነ እና የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንዲሁም እያንዳንዱ ሴት የእሱ ሴት ልጅ እንደሆነች እንገነዘባለን። የተም ይሁኑ፣ ልጆቹ ናቸው ይወዳቸዋል እናም ደህንነታቸውን ይመኛል፡፡ በእርግጥ የዚህች ቤተክርስቲያን አባል እንደመሆናችን መጠን ብቻችንን አንሆንም፡፡ እንባረካለን በማለት የዘለዓለማዊ ህይወት እውቀትን በራስ ወዳድነት በመያዝ ለእኛ የሚሰጠንን የሰማይ አባታችንን ጠቃሚ ግልጋሎት መቀበል አንችልም፡፡ ህይወታችንን የሚገነባው በምንቀበለው ነገር ሳይሆን በምንሰጠው ነው" (George Albert Smith, በ Conference Report, ሚያዝያ 1935, ገጽ 46)፡፡

## እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን አባል ወንጌልን የማካፈል ኃላፊነት አለው

ዝርዝር ቃላቶች እና ውይይት

የቃላት ዝርዝርን አሳይ ወይም *"አንድ ሰው ይጠብቃችኋል"* የሚለውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ፡፡ ይህ ሐረግ ለእነሱ ምን ማለት እንደሆነ ወጣት ወዶችን ጠይቅ፡፡

ታሪክ እና ውይይት

እህት ፔትራ ጀ ደ ሄርናንዴዝ የሞንተሬ፣ ሜክሲኮ የሚሲዮናዊያን መልዕክት ህይወቷን እንዴት እንደለወጠው እንዲህ ስትል ትናገራለች፣

“ከአስራ ዘጠኝ ዓመት በፊት ባለቤቴ በመኪና አደጋ ሞተ። ከዚያ በኋላ ነበር ከቤተሰቤ ጋር እግዚአብሔር እንዲረዳኝ የመፈለግ ፍላጎት የተሰማኝ። ወጣት ልጄ አሥራ አንድ ወር ሆኗታል።

“አንድ ምሽት ተስፋዬን በቀረጥኩበት ጊዜ፣ . . . ለሌላ ሰው የምናገር ይመስል ለጌታ ጸለይኩኝ። ህይወቴን የምመራበትን መንገድ ያሳየኝ ዘንድ ጠየቅኩኝ። እሱ እንደሚኖር፣ ነገርግን የት እንዳለ እንደማላውቀ ነገርኩት። እንዴት እንደማገኘው እና የት እንደምፈልገው እንዲያሳየኝ ጠየኩት። እውነቱን ለማግኘት በእምነት እና በፍላጐት ጸለይኩኝ ያንን ጸሎት በፍጹም አልረሳም. . . .።

“የጸሎቴ መልስ አልዘገየም ነበር። አንድ ቀን ጠዋት ሁለት ወጣት ሚሲዮናዊያን በሬን አንኳኩ እናም ከሞርሞን ቤተክርስቲያን እንደሆኑ እና መልካም መልዕክት እንዳመጡልኝ ነገሩኝ። ስለሞርሞኖች ሰምቻለሁኝ ነገር ግን ፍላጐት የሌለኝ መስዬ አልታየሁም። ግቡ አልኳቸው እናም የመጀመሪያውን ትምህርት ጀመሩ። የመጀመሪያውን ትምህርት እንደተቀበልኩኝ የሚናገሯቸው ነገሮች እውነት እንደሆኑ ተሰማኝ. . . .። ከቤተሰቦቼ. . . . ጋር መጠመቀ እንደምፈልግ ነገርኳቸው...።

“ወንጌልን ከተቀበልንበት ቀን ጀመሮ ህይወታችን ሙሉ በሙሉ ተለወጠ። አሁን እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንደሚሰማን እርግጠኛ ነኝ . . . በወንጌል እና ከአሥራ አምስት ዓመት በፊት በሬን ባንኳኩት ሁለት ሚሲዮናዊያን ምክንያት በእርግጠኝነት የተደራጀን ቤተሰብ ነን እላለሁኝ።

“በሬን ስላንኳኩልኝ እና ወንጌልን ለእነሱ ለማምጣት ልጆቼ ሚሲዮናዊ ሆነው በራቸውን ያንኳኩትን ሰዎች በማወቁ ዘወትር በእነሱ እደሰታለሁኝ” (Leoa R. Hartshorn, comp., *Inspirational Missionary Stories* [ሶልት ሌክ ከተማ: Deseret Book Co., 1977], ከገጽ 123, 125)።

• ወንጌልን እንድታካፍል ማን እየጠበቀህ ይሆን? (ጐረቤት፣ አስተማሪ፣ ዘመድ ጓደኛ።)

ወንጌልን ለእነሱ በማስተዋወቅ እያንዳንዳችን የሌሎችን ህይወት መቀየር እና ወደ ክርስቶስ ይመጡ ዘንድ መርዳት እንደምንችል ወጣት ወንዶች እንደገነዘቡ እርዳቸው። በዓለም ውስጥ ብዙ ሰዎች ወንጌልን ይፈልጉታል ነገር ግን የት እንደሚያገኙት አያውቁም። እኛ ካልረዳናቸው የወንጌልን መልዕክት ፈጽሞ መስማት አይችሉም።

ጥቅስ

“አንድ ሰው ምናልባት እንዲህ ብሎ ሊጠይቀ ይችላል፣ እያንዳንዱ ወጣት፣ እያንዳንዱ አባት እና እናት፣ እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን አባል ሚሲዮናዊ ሆኖ ማገልገል አለበት? ‘እንደገና ጌታ መልስ ሰጥቷል፣ አዎን፣ እያንዳንዱ ወንድ፣ ሴት እና ልጅ— እያንዳንዱ ወጣት እና እያንዳንዱ ትንሽ ልጅ እንዲሁም ልጃገረድ—ሚሲዮናዊ ሆኖ ማገልገል አለባቸው። ይህ ወደ ውጭ ሄደው ማገልገል ወይም እንዲያውም እንደ ሙሉ ጊዜ ሚሲዮናዊ በሥርዓቱ መጠራት እና መሾም አለባቸው ማለት አይደለም። ነገር ግን የተሰጠንን የወንጌል እውነታዎችን የመመስከር ኃላፊነት እያንዳንዳችን አለብን ማለት ነው። ሁላችንም ዘመዶች፣ ጐረቤቶች፣ ጓደኞች እና የሥራ በልደረቦች አሉን እናም በምሳሌነት እና በግብረገብ የወንጌልን እውነታ ለእነሱ የማስተላለፉ ኃላፊነት የእኛ ነው” (Spencer W. Kimball, “It Be cometh Every Man,” *Ensign*, ጥቅምት 1977, ገጽ 3)።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እና ውይይት

ወጣቱ ትምህርት እና ቃል ኪዳን 50፥13–14 ሲያነብ ሌሎቹ ቅዱሳን መጽሐፍቶቻቸው ላይ ምልክት ያድርጉ።

• እያንዳንዳችን ምን እንድንሠራ ነበር የተሾምነው? (ወንጌልን እንደንሰብክ።)

ሌላ ወጣት ትምህርት እና ቃል ኪዳንን 88፥81 እንዲያነብ አድርግ። ወጣት ወንዶች ይህን ጥቅስ ምልክት እንዲያደርጉበት ንገራቸው።

• “ጐረቤትህን አስጠንቅቀ” ማለት ምን ማለት ነው?

---

**ወንጌልን ለማካፈል ብዙ መንገዶች አሉ**

ውይይት

• “ለጐረቤቶችህ” ወንጌልን የምታስተዋውቅበት አንዳንድ መንገዶች ምንድናቸው? (መልካም ምስሌን በማኖር፣ በጓደኝነት፣ ለቤተክርስቲያን ሥራዎች እና ለተለየ የቤት ምሽት በመጋበዝ፣ የቤተክርስቲያን መጽሔት ለእነርሱ በማስተዋወቀ፣ ስለ ቤተክርስቲያን ማወቀ የሚፈልጉ እንደሆን በመጠየቀ።)

እነሱ ወይም ቤተሰቦቻቸው ወንጌልን በማካፈል ቀደም ብሎ ያገኙትን የእራሳቸውን ልምድ እንዲናገሩ ለወጣት ወንዶች እድል ስጥ።

ታሪክ

ሚካኤል የሚባለው ወጣት ስለ መለወጡ የጻፈውን ወጣት ወንዶች እንዲያዳምጡ ጠይቀ። የተመደበው ወጣት የሚከተለውን ታሪክ እንዲናገር አድርግ።

“የሁለተኛ ዓመት የባይሎጂ ትምህርት የሚወሰድበት ሌላኛው መለስተኛ፣ የትምህርት ቤቱ ሴሚስተር በሀውስተን ቴክሳስ ተጀምሮ ነበር። ወረኞች በሆኑ የልጃገረዶች ቡድን ተከብቤ ነበር እኖራለሁ ብዬ አላሰብኩም።

“ዶና ተናጋሪ፣ ዘወትር ደስተኛ እንደምትመስል እና ፊቷ እንደሚያበራ ተገነዘብኩኝ፡፡ በዚያን ምሽት ዓመታዊ መጽሐፉን አገላበጥኩኝ እናም ፎቶግራፏን አይቼ ስሟም ዶና እንደሚባል አወቅኩኝ፡፡

“አንድ ቀን ዶና ደብዳቤ እያነበበች ሳለ በትከሻዋ በኩል ሆኜ ስመለከት *ሞርሞን* የሚል ቃል አየሁ. . . . ሞርሞንን በፍጹም አይቼ አላውቅም፣ እናም ለዶና ብነግራት ጥሩ ይሆናል ብዬ አሰብኩኝ፡፡

“ዶና ንግግሯን ከመጀመሯ በፊት እንደምንም ብዬ ሞርሞን የሚለውን ቃል ጠቀስኩ። ማንም ሰው ስለ ኃይማኖት ሲደነቅ አይቼ አላውቅም፡፡

“በእርግጥ ያለችውን አንድም ቃል አላመንኩም፣ ለማወቅ ግን ጓጉቼ ነበር። ብዙ በራሪ ወረቀቶችን መጽሔቶችን እና መጽሐፈ ሞርሞንን አመጣችልኝ—በዚያን እሁድ ከእሷ ጋር ወደ ቤተክርስቲያን ለመሄድ ቃል ገባሁኝ፡፡

“በኋላም አንድ ቀን ከሰዓት ሥራ ላይ እያለሁ ከሚሲዮናዊያን የስልክ ጥሪ ደረሰኝ፡፡ ችላ ልላቸው አሰብኩኝ፡፡ በሳምንቱ መጨረሻም ሌላ ጥሪ ደረሰኝ፡፡ ሌላ ምክንያት ፈጠርኩኝ፡፡ ሳምንታት አለፉ፣ ነገር ግን ሚሲዮናዊያኑ ተስፋ አልቆረጡም፡፡ በመጨረሻም ቤተሰቦቼ እንደማይፈቅዱላቸው ለዶና ነገርኳት፡፡

“በድፍረት ወደ ሥራ ሄዳ ውይይቱን የምጀምርበትን ቤት አገኘች፡፡ ለወላጆቼ ነገርኳቸው። አልተቃወሙኝም. . . .።

“ከአራት ወራት የክትትል ትምህርት በኋላ ከጌታ መልሴን አገኘሁኝ፡፡ ብቸኛ እና እውነተኛ ቤተክርስቲያን እንዳገኘሁኝ አውቅ ነበር፡፡

“ወላጆቼ ተገረሙ ነገር ግን የማያደርገውን ነገር ለማወቅ የበሰልኩ መሆኔን ነገሩኝ . . .

“አርብ፣ ግንቦት 28፣ 1976፣ ተጠመቅኩኝ እናም ማረጋገጫ ተሰጠኝ. . . . በህይወቴ በጣም ታላቅ ቀን ነበር፡፡

“ዶና የኋለኛው ቀን ቅዱስ እንድሆን ያንን ታላቅ ሚና ተጫወተች ነገር ግን ስለ እርሷ ያልነገርኳችሁ አንድ ነገር አለ፡፡ ከሙሉ ሚሲዮናዊ ሥራዋ፣ ከጠነከረው ምስክርነቷ እና ለቤተክርስቲያኑ ካላት ፍቅር ጋር አባል ትሆን ዘንድ የቤተሰቧን ፈቃድ በመጠባበቅ ላይ ያለች አባል ያልሆነች ልጅ ነች” (Mike Corbin, “Every Nonmember a Missionary,” *New Era*, ጥቅምት 1977, ገጽ 41)፡፡

ውይይት

• አባል ያልሆነችው ለጐረቤቷ ወንጌልን ለማስተማር ያን ያህል የምትደሰት ከሆነች እኛስ እንዴት ነው የአባልነት በረከት ሥራ ያለን?

• ዶና ወንጌልን ለማካፈል ምን ዘዴዎች ተጠቀመች? (አርአያነቷ ጥንካሬዋ፣ የቤተክርስቲያኑ በራሪ ወረቀት፣ መጽሐፈ ሞርሞን፣ የሙሉ ጊዜ ሚሲዮናዊያን፡፡)

ስለ ተመለሰው የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ያለንን መልዕክት ለመስማት እያንዳንዱ ሰው መብቱ እንዳለው ይግለጹ፡፡ አንድ ሰው ይጠብቃችኋል፡፡ ፍቅራችሁን እና ምስክርነታችሁን ካላካፈላችሁ አንድ ሰው የወንጌልን ደስታ በፍጹም ማወቅ አይችልም፡፡

ጥቅስ

ከፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል የተሰጠውን የሚከተለውን ጥቅስ አንብብ፣

“የሚሲዮናዊ ሥራን በመሥራት፣ ሰዎችን በማስተዋወቅ፣ ሚሲዮናዊያን ውይይትን በሚሰጡበት ወቅት በማገዝ መንፈሳዊ አደጋ አለ፡፡ አስደናቂ እና አጸፋ መላሽ ነው፡፡ አንዲት ነፍስ እንኳ ለመጠመቅ ንስኃን እና እምነትን እና ፍላጐትን በምታሳይበት ጊዜ ሰዓታት፣ ጥረት፣ መደነቅ፣ ሁሉም ጠቃሚ ናቸው” (“It Becometh Every Man,” ገጽ 7)፡፡

---

**ማጠቃለያ**

መልመጃ እና በእጅ የተዘጋጀ ጽሑፍ

“አንድ ሰው ይጠብቃችኋል” የሚለውን የሚገልጽ በእጅ የተዘጋጀ ጽሑፍ ለእያንዳንዱ ወጣት ስጥ፡፡ አንተ የተወያየህበትን ዘዴ በደንብ በመጠቀም በሚቀጥለው ወር ውስጥ አንድ ሰው እንዲያገኙ ጠይቃቸው፡፡ ከወር በኋላ ለቡድን ፕሬዚዳንት እና ለአንተ ሪፖርት እንዲያደርጉ በማድረግ ሙከራቸውን ተታተል፡፡

# ሌሎችን ማገልገል

# 14

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ሌሎችን በማገልገል ፍቀሩን ያሳያል። |
| **ዝግጅት** | 1. አስፈላጊ መሣሪያዎች፣ ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት። |
| | 2. በሞዛያ 2፡17 ውስጥ የሚገኘውን የንጉስ ቢኒያምን የመልዕክት ፖስተር ያዘጋጁ። |
| | 3. *አድርገው!* የሚለው ሐረግ የተጻፈበትን በእጅ የተዘጋጀ ጽሑፍ ለእያንዳንዱ ወጣት አዘጋጅ። |
| | 4. *ለወጣቶች ጥንካሬ* በሚለው ገጽ በ19 ላይ ስለአገልግሎት የተሰጠውን ምክር ለወጣቶች ጥንካሬ ይክልሱ። |
| የአስተማሪው ማስታወሻ | ለወጣት ወንዶች የአገልግሎት ፕሮጀክትን ለማቀድ ያበረታታ ዘንድ ይህን ትምህርት እንደምትሰጥ አስብ። ለክፍል አባላቱ ፕሮጀክት ለመምረጥ የሚያነቃቁቸውን ስብሰባ ማቀድ ትችላለህ። |

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ** — **እውነተኛ አገልግሎት ሸክም ሳይሆን ዕድል ነው።**

ታሪክ — የሚከተለውን ታሪክ አንብብ፥

“ከጉልበቴ በላይ ከፍ ብሎ የተከሰተው ድንገተኛ ወለምታ በአደጋ ውስጥ እንዳለሁኝ ነገሮኛል። የድርቀሽ መወዛወዣ መዶሻ ጉልበት በሰጠው ኃይል መጥፊያ ዘንግ ተይዤ ከማሽኑ ጋር በኃይል ስጣበቅና ተጐትቼም በአካባቢው ስወረወር ምን እንደተከሰተ ለመገንዘብ ጊዜ አልነበረኝም. . . .

“ሙሉ በሙሉ በማሽኑ ጥንካሬ እና ግፊት በመድከም ከባዱ የሥራ ጫማዬ እስኪቦጨቀ ድረስ ጉልበቴን አጥፎት አቀመቢስ ሆንኩኝ። በእግሬ ወደ አስፈሪው ዘንግ መወርወሬን ማስታወስ አልችልም። በስተመጨረሻው በተንሿ የከብቶች መኖ ላይ ወደቀሁ።

“በአጋጣሚ፣ ጫማዬ ተቀዶ ተፈታ ምንም እንኳ ቁርጭምጭሚቴን ወለምታ ቢሰማውም ከሚሽከረከረው ማሽን ብረት ግን ነፃ ነበርኩኝ።

“በአቀራቢያው ወደሚገኘው የአጥር ምሰሶ እያነከስኩኝ ተጠጋሁ እናም አጥብቁ ያዝኩት። መኪናው መታጠፊያውን ዞሮ መንገዱን ብዙም ሳይጓዝ፣ በጭንቀት እጄን አወዛወዝኩኝ እናም ሹፌሩ ጎረቤቴ አይቶኝ አቀመ።

“ወደ ሆስፒታል አሥር ማይል አድካሚ በሆነው መንገድ ስጓዝ፣ ንቁ ነበርኩኝ. . . .

“የተደረገው ቀዶ ጥገና፣ የተለጠፈልኝ ፕላስተር፣ እና የመንቀሳቀሻ ክራንች የአስፈሪው ክስተት ጥቂቶቹ ልምዶች ነበሩ። ይሁን እንጂ፣ ታላቁ ተዝታ ህመም እና ስቃዩ አይደለም፣ ነገር ግን በአደጋ ጊዜ አገልግሎቱ አመርቂ ለሆነው የኋ.ቀ.ቀ ወጣት ወንዶች ውለታ ነው።

“ቤትን የመገንባት የአናጢነት ሥራዬ ውስጥ ተመልሼ መሥራት እንደማልችል ስገነዘብ፣ እንደ አማካሪ አብሪያቸው የምሰራው የቁሶች ቡድን . . .፣ አንድ ሰው የመምራት ልምድ ያለው ሰው ቢገኝ የቤቱን ሥራ ግንባታ ፕሮጀክት ለማጠናቀቀ ወጣቶች የጋለ ፍላጎት እንዳላቸው ገለጹ . . .።

“እናም፣ ስለዚህ የህንጻ ተቋራጭ ባለሙያ እና፣ የመንፈሳዊ ቡድን ቁስ በሆነው ጳጳስ ሳንቶን ባሬት እርዳታ በመዶሻ እና በመጋዝ ታጥቀው 1200 ካሬ ጫማ የሆነውን ቤት ማሳመሩን ጀመረ።

“‘ጳጳሱ መሰረት እንደጣሉልን በሚስማር እንመታዋለን፣’ አለ ሚካኤል [ከፕሮጀክቱ አመራር አንዱ] ከዚያም በኋላ ቡድኑ ከመሰረት ጀምሮ እስከጣራው ድረስ ቤቱን በሁለት ቀን ብቻ እንዴት እንዳጠናቀቀው በማብራራት እንዲህ ሲል ሚካኤል ገልጿል. . . .

“በግንባታ ላይ ያለው ቤት ባለቤት አቶ ቦብ ፋይንድሊ እና ወይዘሮ ቦብ ፋይንድሊ ደግሞ እርዳታቸውን ለግሰዋል። ‘ቦብ ከተቀረነው ሰዎች ጋር ውስጥ ገብቶ ሲሰራ ሚስቱ ምሳ አመጣችልን። ያም የተራበው ሠራተኛ በሥራው እንዲገፋ ረዳ፣’ አለ ሚካኤል። በእርግጥ ጥቂት መቁሰል እና የተጣጠፉ ምስማሮች ነበሩ ምንም እንኳ ሥራው ከባድ ቢሆንም በቦታው ጥሩ መንፈስ ነበር. . . .።

“እንዲህ በማለት ጳጳስ ባሬት ለሥራው መሳካት አንዱን ምክንያት ተናግረዋል፣ ‘ወጣት ወንዶች እየሰሩ ያሉት አማካሪያቸው የአገልግሎት ፕሮጀክቱን ስላቀደላቸው አይደለም ነገር ግን እራሳቸው በአንድነት አቀደውታል . . . እናም ያ ነው ልዩነቱን ያመጣው።’

“የመጨረሻው ምስማር ቀዳሚ ማምሻውን በጣራው ላይ ከተመታ በኋላ፣ ቤቱን የማቆም ሥራ ተጠናቀቀ ነገር ግን ሥራው እንደተናቀቁ በመግለጽ ሊያስደንቁን ጊዜው ገና ነበር።

“ከሆስፒታል ከወጣሁኝ በኋላ የመጀመሪያ እሁድ ላይ ያልተለመደ በአሥራዎቹ የእድሜ ክልል ያሉ የልጆችን ቡድን በተገናኘሁ ጊዜ ሰላምታ አቀረበልኝ፡፡ የሚያፍረው እና አንዳንድ ቃላት የሚያጥረው የቡድኑ አባል ወጣ በማለት እንዲህ አለ፣ ‘ለአንተ አንድ ነገር አለን . . . ምክንያቱም ልንረዳህ እንፈልጋለንና፡፡’ የግንባታ ሥራቸውን የሚያሳይ፣ ፎቶግራፍ በቤት ውስጥ የተሠራ ከአንኳን ደስ አለህ የሚል ካርድ ጋር ሰጠኝ፡፡ በሥዕሉ አማካኝነት ንድፉን ሳይ ክፍሉ ጸጥ ብሎ ነበር፡፡

“በዚያው በጸጥታ በተሞላ ጊዜ ውስጥ በአገልግሎት ትምህርት ላይ ከመመሪያው ላይ እርግጠኛ ሳልሆን በአንድ በክፍል ውስጥ ደግመን ወደ ተነጋገርንበት አዕምሮዬ ተመለሰ፡፡ በአጋጣሚ በፊት የመነገሪያው ርዕስ የሆነውን ደስታ እያገኘን ነበር፡፡ በዚያን ቀን ትምህርቱ በቃላት አልተገለጸም ነበር፡፡

“በመጨረሻም፣ እንዲህ በማለት ዝምታውን ሰበርኩ፣ ‘አሁን እውነተኛ የአገልግሎትን ደስታ አውቃችኋል— ነገር ግን ከሚቀጥለው ፕሮጀክት የድርቆሽ ክምር እናውጣ!’ ” (Paul Willie, “A Service Project with a Special Meaning,” *New Era*, ግንቦት 1976, ከገጽ 16,18)።

ውይይት

• ከብዙዎቹ ውጥናቸው እና በደንብ ካልተሳኩላቸው የዚህ ዓይነት ፕሮጀክት ውስጥ ይህን የአገልግሎት ፕሮጀክት ልዩ ያደረገው ምንድን ነው?

ይህን መልስ ለመመለስ እንዲረዳ የክፍሉ አባል ትምህርት እና ቃልኪዳን 58፡27 እንዲያነብ ጠይቁ፡፡

• እንደዚህኛው ጥቀስ አባባል በእራሳችን ፈቃድ ምን ማድረግ አለብን?

• ማገልገል አለብን ብሎ በማገልገል እና ልናገለግል እንፈልጋለን ብሎ በማገልገል መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

---

**አገልግሎት የሚያነሳሳ፣ የሚያበረታታ ወይም ሌላውን ሰው የሚረዳ ማንኛውም አድራጐት ነው**

ማስታወቂያ

ከሞዛያ 2፡17 ቃላትን የጻፍክበትን ማስታወቂያ አሳይ፡፡ በምታይበት በሁለቱም ቦታ ላይ *አገልግሎት* የሚለውን ከሥሩ አስምርበት።

አገልግሎትን እንዲገልጹ ወጣት ወዶችን ጠይቁ፡፡ ሐሳባቸውን ተጠቀም እናም የሚከተለውን የሚመስል ገለጻ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉ፣

“አገልግሎት የሚያነሳሳ፣ የሚያበረታታ ወይም ሌላውን ሰው የሚረዳ ማንኛውም አድራጎት ነው፡፡”

ታሪክ

በወጣቱ አገልግሎት ምክንያት በህይወቱ ዘመን በችግር ጊዜ የተነሳሳውን እና ያጠናከረውን ሰው የሚከተለውን ታሪክ ተናገር፡፡

“ከቅዱስ ቁርባን ስብሰባ በኋላ ጳጳሱ ሊያነጋግረኝ ወደ ቢሮው ጠራኝ፡፡ እንዲህ ይሆናል ብዬ አሰብኩኝ፣ *የአስተማሪዎች ቡድን ፕሬዚዳንት እሆናለሁ እወራረዳለሁኝም።* በኩራት እና በደስታ ተሞልቼ ነበር፡፡ *ወይ፣ ዋርዱ በሙሉ እጄን ይጨብጠኝ ይሆን፡፡* እናቴ በጣም ተደሰታለች!

“ከጳጳሱ ባሻገር ትልቅ ወንበር ላይ ቁጭ አልኩኝ፡፡ ዘወትር ፈገግታ የማይለየው፣ ደስተኛ ሰው ነበር፣ ነገር ግን፣ ይህ ንግግር ዋጋ ያለው እንደሚሆን ተሰማኝ፡፡

“ ‘ስቲቭ፣ ለአንተ የምንሰጥህ ሥራ አለን’ አለ፡፡ የልቤ ምት ጨመረ!

“ ‘ይህ ልዩ “የመልካም ጉረቤት” ሥራ ነው፡፡ ስለሃስቲ መክፋርላን አሰብን። እርሱም በጣም ያዘነ ሽማግሌ ነው። አንድ ሰው ጓደኛው እንዲሆነው ይፈልጋል፡፡ የቤተክርስቲያን አባል አይደለም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ፍቅር ለሁሉም ይደርሳል፣ እናም እኛ የቤተክርስቲያኑ አባል እንደመሆናችን መጠን ይህን የማሳየት ኃላፊነት አለብን፡፡ ምናልባት ያንን ፍቅር የማሳየት አጋጣሚ አለን ማለት አለብኝ፡፡’

“ ነፍስ ያጣሁ መምሰል ያለብኝ ይመስለኛል።

“ ‘ሀስቲን ታውቀዋለህ፣ አታውቀውም ስቲቭ? ብሎ ጳጳሱ ጠየቀው፡፡

“ከሁለት ሳምንት በፊት እኔና ጥቂት ጓደኞቼ በማንጓራጎር እና ቀልዶችን በመናገር ያሾፍንበት ትዝ አለኝ፡፡

“ ‘አዎን፣ አውቀዋለሁኝ፣’ ማናደዴን እና ጥፋቴን አምቄ በመያዝ፡፡ ‘ከከተማ ውጭ የሚኖር ያረጀ ባህታዊ ነው አልኩኝ፡፡’

“ ‘ትክክል’ አለ ጳጳሱ፡፡ በሳምንት ውስጥ ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ወጣ ብለህ እንድታየው እፈልጋለሁኝ፡፡’

“ ‘እሺ’ ማለት የምችለው ብቸኛ መልስ ነበር፡፡ ጳጳሱ ከወንበሩ ወደፊት ጐንበስ በማለት ትኩር ብሎ እያየኝ ስለሆነ ስሽማቀቀ አይቶኛል፡፡

“ ‘አሁን ይህ ሥራ የሚበዛብህ ከሆነ ለመናገር አትፍራ፡፡’

“ተከዝኩኝ። ‘ኦ፣ አደርገዋለሁ፣ ጌታዬ’ አልኩኝ።

“ ‘መልካም’ አለ ጳጳሱ በፈገግታ፣ እናም ትንፋሼ ከመመለሱ በፊት፣ ቀጠለ። ለእሳት እንጨት ትፈልጥለታለህ እና ምግብ፣ ብርድ ልብስ—ይረዳኛል ብሎ የሚፈልገውን ሁሉ ትሰጠዋለህ። ጓደኛ ሁን። አባትህ ሥራውን ያውቃል፣ እናም እንደሚረዳህ ነገሮኛል። አንተንም የሰማይ አባትህ ይገፋፋሀል።’

“ ‘አዎን ጌታዬ’፣ አልኩኝ።

“ . . .በዚያ በመጀመሪያ ከሰዓት ከትምህርት ቤት በኋላ ወደ ጐጆው ረጅሙን የእግር ጉዞ ተያይዤ ሳለሁ፣ እያንዳንዱ በእግር መንገድ ዳር ያለው የፈረንጅ ጥድ የሀስቲንን ብቸኝነት ሹክ የሚል መሰለኝ . . .

“ . . .ሀስቲ በአካባቢው በነበረበት ወቀት አብዛኛዎቹ ህጻናት እና የከተማ ሰዎች ጥሩ ያልሆነ አስተያየት የማድረግ ልማድ ነበራቸው ወይም አንድ ‘ብልጠት’ ነበራቸው። ከቀልደኞቹ መካከል እኔን ያስታውሰኝ ይሆን? ከጐጆው በደረስኩ ጊዜ በእርግጥ ፈራሁኝ።

“አንኳኳሁ። መልስ የለም። እንደገና አንኳኳሁ። ውስጥ መኖር እንዳለበት ተረዳሁ። ሌላ ቦታ የት ሊሄድ ይችላል?

“ ‘ሀስቲ፣ እዚያ ነህ?’

“ሲንኮሻኮሽ በመስማት፣ በድፍረት አንገቴን ብቅ አድርጌ ወደ ውስጥ በበሩ ዙሪያ አሾልቄ አየሁ። የሀስቲ ጐጆ ይበርዳል እናም በጣም ይጨልማል። በአልጋ ላይ ሰው ይታየኛል። ተዝለፍልፏል. . . .የተዝለፈለፈ ይመስላል ምክንያቱም ሌላ ነገር ለማድረግ ምንም ምክንያት የለም። አፈር የለበሰው፣ ጥንካሬ የሌለው ተቀምጦበት የነበረው ብርድልብስ ሽንቁር የሆነ ብርድልብስ መሆኑን ተረዳሁኝ . . .

“ ‘ሀስቲ፣ የምረዳህ ነገር አለን?’ አልኩት።

“ስሜን ነገርኩት እናም የኋ.ቀ.ቀ ቤተክርስቲያን ጳጳስ እንዴት እንዳየው እና እንድረዳው እንደላከኝ ነገርኩት። ምንም አልተናገረም. . . .

“ ‘ሀስቲ፣ እሳትህ ጠፍቷል።’ ምንም መልስ የለም። ‘ጥቂት እንጨት ልፍለጥልህ?’ ምንም መልስ የለም።

“ወጣ አልኩኝ፣ ፋስ አገኘሁኝ እና የተከመረ እንጨት ለእሳት መፍለጥ ጀመርኩኝ። በእያንዳንዱ የፋስ ምት አዕምሮዬ ደቀቀ። ምን እየሰራሁ ነኝ እዚህ? ለምን እኔ? ለምን?

“ ‘አታጉረምርም’ አለ በውስጤ ያለው ድምጽ። ‘ሽማግሌው የበረደው እና ብቸኛ ነው፣ እናም ልትረዳው ትችላለህ።’

“ ‘እሳቱን አቀጣጠልኩኝ እና ላነጋግረው ሞከርኩኝ ነገር ግን ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እየሰማኝ አይደለም ብዬ ወሰንኩኝ። አዲስ ብርድልብስ ያስፈልገዋል እናም ጥሩ ወፍራም ንጹህ የሆነውን እንደማመጣለት ነገርኩት እናም በሚቀጥለው ቀን አመጣሁለት። ከዚያ በኋላ በየቀኑ መጣሁኝ። ከሚቀጥሉት ብዙ ሳምንታት በኋላ ቀስ በቀስ መናገር ጀመረ።

“ጥቂት ከተነጋገርን በኋላ አንድ ቀን እንዲህ አለ፣ ‘ልጄ ለምን መጣህ? በአንተ እድሜ ያለ ልጅ እንደ እኔ ዓይነቱን በሽተኛ እና ተፈላጊነት የሌለውን ሽማግሌ ከመጐብኘት ይልቅ ሌላ የሚሰራው ነገር እንደሚኖር እርግጠኛ ነኝ። ነገር ግን በመምጣትህ ደስ ብሎኛል።’ እናም ከዚያ ፈገግ አለ።

“በምስጋና ቀን ሀስቲንን ለእራት ቤታችን ጋበዝኩት። ነገር ግን እርሱ አልመጣም፣ ቤተሰባችን የእራቱን ክፍል ወሰዱለት። እኛን ለማመስገን ሲሞክር በዓይኑ እንባ ይታይ ነበር።

“ጉብኝታችንን በቀጠልን ጊዜ ሀስቲ እረኛ እንደነበር አውቀኩኝ። በአንድ ወቀት ሚስት እና ልጆች ነበሩት ነገር ግን በአደገኛ ተኩሳት ተይዘው ሞቱበት።

“በሐዘኑ ህይወቱን የተሰባበረ አድርጐ በማሰብ ሀስቲ በአገሬቷ እንደ ባይተዋር ተንከራተተ። በፊቱ ጉን ላይ የበሽታው ማየል አንድ ዓይኑን አሳወረው። መጫወት እና ትክክለኛ ቀልድ ጀመረ።

“ግን ለእኔ ሽማግሌው ዳግም አስጠሊታ እና አስፈሪ አልመሰለኝም። እንዲያውም፣ ከትምህርት ቤት መልስ እሱን ለመርዳት እና ታሪኩን ለመስማት ወደ ጎጆው እቻኮላለሁኝ።

“ገና በመጣ ጊዜ እንደገና በድጋሚ እራት ጋበዝነው። በዚህን ጊዜ መጣ በተለየ ሁኔታ ንጹህ እና የሚያምር ሱፍ ለብሶ መጣ። አምሮበት ነበር። ፈገግታው በከንፈሮቹ ተንቀረቀረ። ተፈላጊ ሰው መሆኑን ስለ አሳየነው ሀስቲ ደስተኛ ነበር።

“እራት በልተን ስናበቃ፣ ለሴኮንድ ሽማግሌው ጉንበስ አለ፣ ከዚያም ቀና ብሎ እንዲህ አለ፣ ‘እርግጠኛ ነኝ እናንተ ሰዎች አስደናቂዎች ናችሁ። ለረጅም ጊዜ ህይወቴ ሥርዓት እና ወግ አጥቶ ነበር፣ ነገር ግን ያሳያችሁኝ ፍቅር የተለየ ሰው እያደረገኝ ነው። በጣም አመሰግናለሁኝ።’

“እሱ ያንን እንደተናገረ፣ በደረቴ ውስጥ ትንሽ እሳት ትልቅ ሲሆን ተሰማኝ። ጥሩ ተሰማኝ” (Terry Dale, “Hasty,” *New Era*, ጥር– የካቲት 1981, ከገጽ 10–11)።

**ውይይት**

- ስቲቭ፣ ጳጳሱ፣ እና ቤተሰቦቹ እሱን ባይፈልጉት ኖሮ የሀስቲ ህይወት እንዴት የተለየ ይሆን ነበር?
- በአንዳንድ መንገድ በማገልገል የምታስደስተውን ሰው ታውቃለህ?

**ፖስተር እና ውይይት**

የሞዛያን 2፥17 ፖስተር ወጣቱ እንዲያነብ አድርግ።

- ይህ ጥቅስ ማንን እርዱ ነው የሚለን?
- ለአንድ ሰው ማገልገል ማለት እግዚአብሔርን ማገልገል ለምን ይሆናል?

የሰማይ አባት ልጆቹን በሙሉ እንደሚወዳቸው እና እነርሱን ለመርዳት የምናደርገው ሁሉ እንደሚያስደስተው ወጣት ወንዶች እንዲያውቁ እርዳቸው፡፡

አንዳንዴ አገልግሎታችን የተሳካ እንዲሆን እናስባለን፣ ታላቅ እና አስደሳች አገልግሎት መሆን እንዳለበት አስረዳ፡፡ ይሁን እንጂ ጥቂት የአገልግሎት አድራጎቶችም አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ ጥቂት በአጋጣሚ የምናደርጋቸው ሥራዎች ለእኛ እና ለምናገለግላቸውም ጠቃሚ በረከትን ያስገኙልናል፡፡

- ሌሎችን በየቀኑ እንዴት ማገልገል እንችላለን? የወጣት ወንዶችን ሐሳብ በጥቁር ሰሌዳው ላይ መዘርዘር ትችላለህ፡፡

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ**

ወጣት ወንዶች ማቴዎስ 7፥21 እንዲገልጹ አድርግ እናም ለእራሳቸው ጥቅሱን እንዲያነቡት ጠይቃቸው፡፡

- በዚህ ጥቅስ አባባል፣ ለማገልገል ቁልፉ ምንድነው? (*ማድረግ* የሚለውን ቃል ወጣት ወንዶች ማወቅ አለባቸው፡፡)

**የአማካሪው በእጅ የተዘጋጀ ጽሑፍ እና አቀራረብ**

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል ዘወትር በጠረጴዛው ላይ “አድርግ!” የምትል ትንሽ ከሸክላ የተሰራች ጌጥ እንደሚያስቀምጥ ለወጣት ወንዶች ንገራቸው፡፡

- የጌታ ነቢይ ይህን መፈክር በጠረጴዛው ላይ ለምን ያስቀመጠ ይምስልኃል? *አድርግ!* የሚለውን በእጅ የተዘጋጀ ጽሑፍ አከፋፍል፡፡

---

## ማጠቃለያ

**ሙከራ**

*ለወጣቶች ብርታት* በሚለው በገጽ 19 ላይ ስለ አገልግሎት የተሰጠውን ምክር ከልሱ፡፡ እያንዳንዱ የአሮናዊ ክህነት ስልጣን ያዥ ሌሎችን ሊረዳ የሚችልበት የተወሰኑ መንገዶችን እንዲፈልግ ያበረታቱ፡፡

ሌሎችን በማገልገል ጌታን በሚያገለግሉበት ሌሎችን ብቻ ሳይሆን እንደሚያስደስቱ ነገር ግን እነርሱም የበለጠ እንደሚደሰቱ፣ በኑሮአቸው በበለጠ እንደሚረኩ እናም ብዙውን ችግራቸውን እንደሚረሱ ለወጣት ወንዶች ቃል ግባላቸው፡፡ እያንዳንዱ ወጣት አንድን ሰው በየቀኑ እንዲረዳ ወይም እንዲያበረታታ እናም ሥራውን እና የተሰማውን ስሜት በእራሱ አጀንዳ ላይ እንዲመዘግብ አበረታታቸው፡፡

የክፍል አገልግሎት ፕሮጀክትን እንዲመርጡ ለወጣት ወንዶች ጊዜ ስጣቸው፡፡ ፕሮጀክቱን ምረጥ እናም የጳጳሱን ድጋፍ አግኝ፡፡ የቡድን አመራር ፕሮጀክቱን እንዲያደራጅ እና እንዲያቅድ አድርግ፡፡ ወጣት ወንዶች በተደራጀ መደበኛ በጎ አድራጊ ድርጅት በኩል አገልግሎት መስጠትን ለምሳሌ መጠለያ ቤት የለሽ በሚል ሊያዋቅሩት ይፈልጋሉ፡፡

**ክትትል**

ከሚቀጥለው ሳምንት ትምህርት በፊት፣ ወጣቶች በሳምንቱ ጊዜ ውስጥ ስለ አበረከቱት አገልግሎት እንዲናገሩ ጥቂት ደቂቃዎችን መስጠት ትችላለህ፡፡

# በክህነት ስልጣን ውስጥ አንድነት እና ወንድማማችነት

# 15

**ዓላማው**

እያንዳንዱ ወጣት አሮናዊ የክህነት ስልጣን ያዥ እንደመሆኑ መጠን አንድነትን እና ወንድማማችነትን በማሳደግ ውስጥ ታላቅ ጥንካሬ እንዳለው ይረዳል።

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሣሪያዎች፣ ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።
2. ከሶስት እስከ ስድስት እርምጃዎች ቁመት ያለውን ገመድ እና ብዙ ጅማቶች የሌሉት ቁርጥራጭ ገመድ አግኝ (ለእያንዳንዱ ወጣት አንዳንድ ጅማት ስጥ)።
3. መዝሙረ ዳዊትን 133፥1፣ ትምህርት እና ቃልኪዳን 38፥24፣ እና ትምህርት እና ቃል ኪዳን 51፥9 አጥና።

**ለትምህርት ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**የክህነት ስልጣን ያዥ እያንዳንዳቸው ጥሩ እንዲሰማቸው መረዳት አለባቸው**

ታሪክ እና ውይይት

በምሽጐች መካከል አልፎ በጎኑ የቀሰለውን ጓዱን ከአደገኛ አካባቢ ለማምጣት የበላይ አለቃውን ፈቃድ ስለጠየቀው ወታደር የሚከተለውን ታሪክ ወጣት ወንዶች እንዲሰሙት አድርግ።

" 'መሄድ ትችላለህ' አለ አለቃው፣ 'ነገር ግን ተገቢ አይደለም። ምናልባት ጓደኛህ ተገድሎ ይሆናል እናም የራስህን ህይወት ታጣለህ።' ይሁን እንጂ ሰውዬው ሄደ። እንደምንም ጓደኛው ጋር ደርሶ በትከሻው ላይ ተሸክመው እናም ወደ ምሽጉ አመጣው። ሁለቱም ተንገዳግደው ከምሽጉ ውስጥ ተኙ። አለቃው ሊድን ይችላል የሚባለውን ጓድ ተመለከተ እናም ከዚያ እንዲህ አለ፣ 'ዋጋ የለውም ብየህለሁኝ። ጓደኛህ ሞቷል እናም አንተም ቆስለሃል።'

" 'ቢሆንም ዋጋ አለው፣ ጌታዬ።'

" 'እንዴት "ዋጋ አለው ትላለህ"? ልንገርህ፣ ጓደኛህ ሞቷል።'

" 'አዎን፣ ጌታዬ' አለ ልጁ፣ 'ነገር ግን ዋጋ አለው፣ ምክንያቱም ወደ እርሱ በሄድኩ ጊዜ እንዲህ አለ፣ "እንደምትመጣ አውቃለሁ" ' " (*A Story to Tell*, comp. General Board of the Primary Association and Deseret Sunday School Union Board [ሶልት ሌክ ከተማ: Deseret Book Company, 1945], ገጽ 28)።

- ለወጣቱ ዋጋ አለው ብለህ ለምን ታስባለህ?
- የክህነት ስልጣን ያዦች ይህን የመሰለ ታዛዥነት በምን መንገዶች እርስ በእርሳቸው ሊያሳዩ ይችላሉ?

ታሪክ እና ውይይት

የሚከተለውን ታሪክ ተናገር፣

ቶም እና ቢል ወደ ትልቅ ከተማ የተጓዙት ቀርብ ጊዜ ነበር። ከአዲሱ ዋርዳቸው የአሮናዊ ካህናት ቡድኖች በሐይቅ ዳርቻ የዋና ግብዣ ነበራቸው። ወንድም ጆንሰን ልክ የምግብ ሰዓት ምልክት ሲያሳይ አብዛኞቹ ወጣት ወንዶች ወደ እሳት ይሮጡ ነበር። ለዋርዱ አዲስ የነበሩት ቶም እና ቢል ከዳርቻው በላይ ይዋኛሉ። ከዋናው ቡድን ርቀው ውጪ ነበር ያሉት ምክንያቱም የዋርዱ ወጣት ወንዶች አነርሱን ለማጫወት ሥራ የበዛባቸው ይመስሉ ነበር። ከዚህ በፊት አንዳቸውም ትልቅ ከተማ አልኖሩም፣ እናም እያንዳንዳቸው ከብዙ አንግዶች መሃል የሌሉ መስሎ ተሰማቸው።

"እንውጣ እና እንብላ" አለ ቢል።

"አንተ ቀጥል" አለ ቶም። "በውቅያኖስ ውስጥ ስዋኝ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው እናም አሁን ለማቆም አልችልም በጣም ደስ ብሎኛል።"

"ደህና፣ እኔ ርቦኛል፣ እናም ልበላ እየሄድኩ ነኝ፣" አለ ቢል፣ "ነገር ግን በጊዜ ብትመጣ ይሻልሃል።" ቢል ከውሃው ውስጥ እንደወጣ፣ ያልተለመደ ለቀሶ የሰማ መሰለው። "ምናልባት እንደ ሰው ከሽርሽር ቦታ ከሚነደው እሳት ይሆናል አልያም የባህር ጭላት ነው፡" በማለት ቢል ለእራሱ አሰበ።

ቢል ወደ ቡድኑ በመጣ ጊዜ ወንድም ጆንሰን እራት ሰጠው። ቶም የት አለ? ከአንተ ጋር አይደለም?" ሲል ጠየቀው

"አይደለም" አለ ቢል። "እየዋኘ ሊቆይ ፈልጓል።"

ቶም ወዳለበት አደጋ ወጣት ወንዶችን ለመቀስቀስ ለብዙ ጊዜ ሲያመነታ ቆይቶ ወንድም ጆንሰን ወደ ውኃው ሮጠ፡፡ ከሃምሳ ጫማ ርቀት በላይ ሆኖ በተስፋ መቁረጥ አንድ እጅ ሲወዛወዝ አየ፡፡ ወንድም ጆንሰን ውሃው ውስጥ እንደገባ፣ ከጎኑ አራት ወይም አምስት የነፍስ አድን ዋናተኞች እየዋኙ እንደሆነ አወቀ፡፡ በወጣት ወንዶቹ እርዳታ ወንድም ጆንሰን ቶምን በሰላም ወደ ዳር እና በጉጉት ወደሚጠብቁት ወጣት ወንዶች ሊመልሰው ችሏል፡፡

• ይህ ኃይለኛ አሳዛኝ ክስተት እንዴት ሊወገድ ቻለ? (ከቶም ጋር ጓደኛ በሆነ እና ከእርሱ ጋር በቀረ ሰው፡፡ ቶምን እና ቢልን ጥሩ እንዲሰማቸው በቡድኑ ውስጥ ያሉ ወጣት ወንዶች በበለጠ ይሳተፉ ጀመር፡፡)

• አንድ ሰው ከቡድን የቀረበትን ማንኛውንም አጋጣሚ ታውቃለህ?

• ብቻህን ቀርተህ ታውቃለህ?

• ብቻህን ቀርተህ፣ ምንም ሰው ጓደኛህ ሊሆን ያልፈለገበት መስሎ በታየህ ግዜ ምን ይሰማህል?

ይህ በተወሰነ ምክንያት ብቻቸውን ስለቀሩት ብዙም ተሳትፎ የሌላቸውን ማናቸውንም ወጣት ወንዶች ጉዳይ ለመወያየት መልካም ጊዜ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁሉንም የአሮናዊ ክህነት ስልጣን ያዦችን ጥሩ እንዲሰማቸው የመርዳት ኃላፊነታቸውን እንዲያውቁ ወጣት ወንዶችን እርዳ፡፡

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እና ውይይት**

ወጣቱ 1ኛ ጴጥሮስ 3፥8 እንዲያነብ እናም ሌሎች ወጣት ወንዶች በመጽሐፍ ቅዱሳቸው ውስጥ እንዲከታተሉ አድርግ፡፡

• በሐሣብ አንድ መሆን ማለት ምን ማለት ነው? (የጽድቅ ሥራን በመሥራት አንድ መሆን ማለት ነው፡፡)

• የቢል እና የቶም ቡድን በምን መንገድ ነው በአስተሳሰብ አንድ ያልሆኑት? (ቶምን ወይም ቢልን በቡድኑ ውስጥ ስላላካተቷቸው ነው።)

**የማሰላሰያ ጥያቄዎች**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይቅ እናም ለእያንዳንዱ ጥያቄ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ በጸጥታ ወጣት ወንዶች እንዲመረምሩ አድርግ፣

• አንድ አዕምሮ አለን?

• ለእያንዳንዳችን ርህራሄ አለን?

• ትሁት ነን?

• ፍጹም ንጹህ አስተሳሰብ እናሳያለን?

**ግላዊ ልምድ**

ብቸኝነት የተሰማህበትን የግል ልምድ ለወጣት ወንዶች አካፍል፡፡ ልምዱ እንዴት እና እንዴት እንደተፈታ ለወጣት ወንዶች ንገራቸው፡፡ ከተቻለ፣ ምሳሌው ቡድን ወይም አባል የቡድኑ አባል ረጂ እንድትሆን እንዴት እንደረዳህ ማሳየት አለበት፡፡

---

**ለእያንዳንዱ ፍቅርን እና ወንድማማችነትን ማሳየት**

**በቁሳዊ ነገሮች ላይ የተደገፈ ትምህርት**

ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ ከትልቅ ገመድ የወሰድከውን የገመድ ጅማት ስጥ፡፡ ሁለቱንም ጫፍ በመያዝ ለመበጠስ እንዲሞክሩ እያንዳንዳቸውን ጠይቅ (ሁሉም እንዲሞክሩት ጅማቶቹ በጣም ቀጫጭን መሆን አለባቸው)፡፡ አሁን የበጠሱትን ጅማቶች በክፍሉ ፊት ለፊት በመደዳ እንዲያስቀምጡት ወጣት ወንዶችን ጠይቅ፡፡ የጠንካራ ገመድን ርዝመት አሳይ እናም ሁለት ወጣት ወንዶች የገመዱን ጫፍ እና ጫፍ ይዘው ለመበጠስ ይሞክሩ፡፡ ለጥቂት ጊዜ ከሞከሩት በኋላ እንዲቀመጡ ንገራቸው፡፡

• ገመዱን ሳይሆን ጅማቱን ለመበጠስ ለምን ቻላችሁ? (ገመዱ ብዙ ጅማቶች አሉት እና አንድ ላይ የተገመደም ነው፡፡)

ገመዱን ከቡድኑ ጋር አወዳድር፡፡ በሚደራጁበት ጊዜ ቡድኑ ጠንካራ እንደሚሆን ወጣት ወንዶች እንዲገነዘቡ እርዳቸው፡፡ በአንድ አዕምሮ በማይሆኑበት ጊዜ ልክ እንደ አንድ የገመድ ጅማት ቡድኑ ደካማ ይሆናል፡፡

**የጥቁር ሰሌዳ ሥራ**

• የቡድናችንን ወንድማማችነት እና አንድነት ለማጠናከር ምን ማድረግ እንችላለን?

ወጣት ወንዶች ሐሳባቸውን በሚወያዩበት ጊዜ መልሳቸውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ፡፡ መልሳቸው እንደ የቡድን የአገልግሎት ፕሮጀክት መሥራትን፣
የአትሌትክስ ጨዋታን አብሮ መጫወትን፣ የምስክርነት ስብሰባ ማድረግን፣ የቡድን አባላትን ዳግም ለመቀስቀስ አብሮ መሥራትን፣ አብሮ የክህነት ኃላፊነትን መሥራትን፣ እና የመዝናኛ፣ ወይም መንፈሳዊ ወይም እንደ ቡድን የትምህርት ሥራዎችን አብሮ መሥራትን ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እና ውይይት**

ወጣቱ ትምህርት እና ቃል ኪዳን 38፥24 እንዲያነብ እናም ሌሎች ወጣት ወንዶች በመጽሐፍ ቅዱሳቸው ውስጥ እንዲከታተሉ አድርግ፡፡

• ሁላችንም ወንድማማች የምንሆነው እንዴት ነው? (ሁላችንም የሰማዩ አባታችን ልጆች ነን እናም በክህነት ወንድማማቾች ነን፡፡)

• ወንድማችንን እንደ ራሳችን ማበረታታት ማለት ምን ማለት ነው? (መንከባከብ፣ መርዳት ማለት ነው፡፡)

| | |
|---|---|
| የቅዱስ መጽሐፍ ጥቅስ | ወጣቱ ዮሐንስ 10፥17–18 እንዲያነብ አድርግ። |
| | አዳኛችን እኛን በጣም ከመውደዱ የተነሳ ህይወቱን ለእኛ አሳልፎ እንደሰጠ ለወጣት ወንዶች ንገራቸው። በእርግጥ፣ ለኃጢያታችን በተሰዋ ጊዜ ታላቁ የፍቅር እና የመስዋዕት ሥራውን ፈጽሞዋል። ለፍቀሩ ምስጋናችንን ከምንገልጽባቸው መንገዶች አንዱ ለቡድን አባላቶቻችን ፍቅርን በማሳየት እንደሆነ በደንብ አስረዳ። |

---

### ማጠቃለያ

| | |
|---|---|
| የአማካሪው አቀራረብ | ወጣት ወንዶች በክህነት ስልጣን ጥሪያቸው ጓደኛ በመሆን፣ እርዳታ ሰጪ በመሆን እና እርስ በእርስ በመተሳሰብ ጌታን ማገልገል እንደሚችሉ አስረዳ። የእያንዳንዳችንን መብት እና ግላዊ ስሜትን ማክበር አለብን፣ ነገር ግን የክህነት ስልጣን ያዥ ጓደኛችንም ብቸኛ ወይም ያልተፈለገ መስሎ እንዲሰማው የሚያደርገውን ማንኛውንም ነገር ማድረግ እንደሌለብን ማስታወስ ደግሞ አለብን። |
| | የቶም እና የቢል ታሪክ እንደሚገልጸው እያንዳንዳችን እንፈላለጋለን። ወጣቱ ሰምጦ ነበር ምክንያቱም ብቻውን ስለነበር ከቡድኑ ውስጥ የሚረዳው ማንም ሰው አልነበረም። ይህን በመሰለ ምክንያት ብዙም ተሳትፎ የሌላቸው ወጣት ወንዶች በመንፈስ "ይሰምጣሉ"። አብሮ በመሆን ውስጥ ደህንነት አለ። ሁላችንም ወንድማማቾች ነን እናም በደግነት እያንዳንዳችንን መጠበቅ አለብን። |
| ሙከራ | *ለወጣቶች ጥንካሬ* ከሚለው ገጽ ስለ ጓደኝነት የተሰጠውን ምክር ከልስ። ወጣቶች የቡድን ወንድማማችነትን ለማጠናከር በሳምንት ውስጥ ቢያንስ አንድ ነገር እንዲፈጽሙ አበረታታቸው። ሥራውን በቡድንም ሆነ በግል ማከናወን ይችላሉ። ወጣቶች ሥራውን በግላቸው ከሰሩት የሥራቸውን ፍጻሜ ሪፖርት እንዲያደርጉ በሚቀጥለው ሳምንት ውስጥ በየግል አነጋግራቸው። የቡድን ሥራን ከመረጡ የሥራውን ፍጻሜ ለመወያየት በሚቀጥለው እሁድ የቡድን ትምህርት ክፍለ ጊዜ ጥቂት ደቂቃዎችን ውሰድ። |
| ምስክርነት | ስለካህናት ወንድማማችነት አስፈላጊነት ለወጣቶች ምስክርነትህን አካፍል። ምስክርነታቸውን ለመስጠት የሚፈልጉትን እንዲሁ ይመሰክሩ ዘንድ ፍቀድላቸው። |

# 16 ፍጹም ፍቅር

**ዓላማው** እያንዳንዱ ወጣት ፍጹም ፍቅርን ለማሣደግ እና ለመግለጽ ይጥራል፡፡

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈለጉ የትምህርት መሳሪያዎች፡
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ ቅዱሳን መጽሐፍት፡፡
   ለ. የቃላት መስመር መለጠፊያ ፕላስተር ወይም ሌሎች ቁሳቁሶች፡፡
2. የሚከተሉትን የቃላት መስመር አዘጋጅ፡
   ሀ. “ፍፁም ፍቅር የክርስቶስ ንፁህ ፍቅር ነው፡፡”
   ለ. “ፍጹም ፍቅር ይታገሳል፣ ደግ ነው።”
   ሐ. “ፍጹም ፍቅር አይቀናም፡፡”
   መ. “ፍጹም ፍቅር አይመካም፣ አይታበይም፡፡”
   ሠ. ፍጹም ፍቅር “ብቻዬን ይድላኝ አይልም፡፡”
   ረ. ፍጹም ፍቅር “የራሱን ብቻ አይፈልግም፡፡”
   ሰ. ፍቅር “አያበሳጭም፡፡”
   ሸ. “ፍጹም ፍቅር ክፉን ነገር አያስብም፡፡”
   ቀ. ፍጹም ፍቅር “ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፡፡”

**ለትምህርቱ እድገት የቀረበ ሐሳብ**

**ፍጹም ፍቅር የክርስቶስ ንፁህ ፍቅር ነው**

ውይይት

• ፍጹም ፍቅር የሚለው ቃል ላንተ ምን ማለት ነው?

ይህን ጥያቄ ወጣት ወንዶቹ ይወያዩበት፡፡ **ፍጹም ፍቅር** ማለት **የፍቅር** ሌላ ቃል መሆኑን ትኩረት ስጥበት፡፡

ታሪክ እና ውይይት

ወጣት ወንዶቹ በሚከተለው ታሪክ ውስጥ ፍቅርን ያሳየ ሰው ይኖር እንደሆነ ያስተውሉ ዘንድ እንዲያዳምጡ አድርግ፡

ክሬይንግ የቡድኑ አዲስ አባል ነበር፡፡ እሱም ከተቀሩት የቡድኑ አባላት ጋር ወደ ኃይቅ በሚደረገው የሽርሽር ጉዞ ላይ ለመሳተፍ ስሜቱ በደስታ ተነሳስቶ ነበር፡፡ ከቡድኑ ጋር የመጀመሪያ የሽርሽር ጊዜው መሆኑ ነበር፡፡ ቤተሰቡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ንቁ ተሳታፊ አልነበረም፣ እናም የተቀሩት የቡድኑን አባላት እንደተቀበሏቸው ሁሉ ሌሎቹ ልጆች እሱን አልተቀበሉትም፡፡

ወጣት ወንዶቹ በየትኛው መኪና እንደሚሄዱ በሚወስኑበት ግዜ፣ ክሬይግ የመጨረሻውን ምርጫ ነበር ያገኘው፡፡ ከርሱ አጠገብ ለመቀመጥ ማንም የፈለገ ሰው አልነበረም፡፡ በካምፑ በደረሱ ጊዜ፣ ብቻውን ድንኳኑ ውስጥ ተተቶ ነበር፡፡ ለዋና ጨዋታዎች የእርሱ የቀርብ ጓደኛ ለመሆን የወደደ ማንም አልነበረም፡፡ የሥራ መደቦች በተሰጡ ጊዜ፣ ክሬይግ ከራሱ ድርሻ በላይ ነበር የተሠጠው፡፡

በካምፑ ውስጥ በነበሩት የሣምንቱ ጊዜ ውስጥ ደስተኛ አይመስልም ነበር፡፡ ጊዜውን ለብቻው ነበር የሚያሳልፈው፣ በሽርሽሩ ማብቂያ ወደ ቤት መሄጃ ጊዜ በመሆኑ ደስተኛ ይመስል ነበር፡፡

• ከቡድኑ እንቅስቃሴ ክሬይግ የተገለለው ለምንድን ይመስልሃል?

• በዚህ ታሪክ ውስጥ አፍቃሪ የሆነ ሰው ነበር?

• በአንተ ቡድን ውስጥ ይህ ቢከሰት ኖሮ፣ ለአዲስ አባል ፍጹም ፍቅርን ለማሳየት ምን ልታደርግ ትችል ነበር?

ቅዱሳን መጽሐፍት እና ውይይት

አንድ ወጣት ሞሮናይ 7፥47–48 እንዲያነብ አድርግ።

ፍጹም ፍቅርን ላሳዩ ሰዎች ሽልማታቸው ምንድን ነው?

ሐዋሪያው ጳውሎስ በቆሮንጦስ ለነበሩት የመጀመሪያዎቹ ቅዱሳን፣ ፍጹም ፍቅር እንዳላቸው ድርጊቶቻቸውን ይመረምሩ ዘንድ በመምከር ደብዳቤ ጽፏል፡፡ አንድ ወጣት ወንድ 1ኛ ቆሮንቶስ 13፥1–2 ሲያነብ ሌሎቹ ከመጽሐፍቶቻቸው ላይ እንዲከታተሉ አድርግ፡፡

• ጳውሎስ “እንደሚጮህ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸው ፅናፅል” መሆን ሲል ምን ማለቱ ይመስልሃል? (እውነተኛ ካልሆነ የልብ ፍላጐት፣ ያለታማኝነት ከተናገርን ወይም ካደረግን፣ ቃላቶቹ ወይም ድርጊቶቹ ባዶ እና እንዲያው ድምፅ ብቻ ይሆናሉ፡፡)

• ያለ ትክክለኛ ግንዛቤ የሰጠን እንደሆነ ለምን ይሆን ምናልባት “እንደሚጮህ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸው ጽናጽል” የምንቀጠረው?

• በቁጥር ሁለት መሠረት፣ ፍጹም ፍቅር ማግኘት ከየትኞቹ ኃይለኛ ስጦታዎች መካከል እጅግ አስፈላጊ ይሆናል?

• ሞሮናይ ፍቅርን እንዴት ነበር የገለጸው? (የክርስቶስ ንጹህ መውደድ፤ አስፈላጊ ከሆነ ሞሮናይ 7፥47) እንደገና አንብብ።

የቃላት ዝርዝር እና ውይይት

“ፍጹም ፍቅር የክርስቶስ ንፁህ ፍቅር ነው”፤ የሚለውን የቃላት መስመር ሀ. ለጥፍ፡፡

• ፍጹም ፍቅር ከ“ፍቅር” ይልቅ “የክርስቶስ ንፁህ ፍቅር ነው” የተባለው ለምን ይመስልሃል? (ፍጹም ፍቅር ከመስጠት በላይ፣ እንዲያውም በስሜት ከመስጠት በላይ ነው፡፡ ክርስቶስ በሚያፈቅረው ዓይነት መንገድ ማፍቀር እና ካስፈለገም ሌሎችን ለማገልገል የራስህን ህይወት ለመስጠት ፍቃደኛ መሆን ነው፡፡)

ክርስቶስ የፈወሰው፣ የሰበከው፣ በሽተኛን የባረከው፣ እና ሕይወቱን የሰጠው ተግባሩ ስለሆነ ወይም ሀይሉን የመጠቀም ፍላጐት ኖሮት ሣይሆን፣ ነገር ግን ከፍቅር የተነሳ መሆኑን ግለፅ፡፡ እሱም እንዲህ ብሏል፣ “እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፣ አዲስ ትዕዛዝ እሰጣችኋለሁ፡፡” (ዮሐንስ 13፥34)

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቀስ እና ውይይት

አዳኛችን፣ “አዎን በዘላለም ፍቅር ወድጄኃለሁ” ይላል (ኤርሚያስ 31፥3)፡፡

ሐዋርያው ዮሐንስ ክርስቶስ ለኛ ስላለው ፍቅር ምክንያት ያለብንን ኃላፊነት ይነግረናል፡፡ አንድ ወጣት ወንድ ዮሐ 15፥12 እንዲያነብ አድርግ፡፡

• ይህ ኃላፊነት ምንድን ነው?

---

**ተስማሚ ያልሆኑ ባህሪያትን በማሸነፍ የበለጥን አፍቃሪ እንሆናለን**

ቅዱስ መጽሐፍት የቃላት ዝርዝሮች፣ እና ውይይት

ፍጹም ፍቅር እዴት እንደምናሳይ ክርስቶስ በምሳሌ እንዳሳየን ግለጽ። በህይወታችን ውስጥ ፍጹም ፍቅርን ለማጐልበት ሞክረናል ስለዚህም እሱን የበለጠ ለመምሰል ችለናል፣ ነገር ግን አንዳንዴ እንደዚህ ከማድረግ የሚገቱንን ነገሮች እናደርጋለን፡፡

ፍጹም ፍቅርን ተጨማሪ ባህሪያት ለመማር፣ አንድ ወጣት 1ኛ ቆሮንቶስ 13፥4 እንዲያነብ አድርግ፡፡

“*ፍጹም ፍቅር* ይታገሳል፤ ደግ ነው።” የሚለውን የቃላት መስመር ለ. ለጥፍ፡፡

• “ይታገሳል” ለማለት ሌላው መንገድ ምን ሊሆን ይችላል? (ቻይ ነው፡፡)

• ምንም እንኳን ጥፋተኞች ቢሆኑም መታገስ እና ደግ መሆን ሌሎችን እንዴት ልንወዳቸው ያኛችለናል?

የክርስቶስ ፍቅር እኛ በምንመስለው ወይም በምናደርገው ላይ ያልተመረኮዘ መሆኑን ግለፅ፡፡ የእርሱ ፍቅር ተለዋዋጭ አይደለም፡፡ ጥፋተኞች ብንሆንም እንኳ እርሱ ይወደናል፡፡

“ፍጹም ፍቅር አይቀናም” የሚለውን የቃላት ዝርዝር ሐ. ለጥፍ፡፡

ለወጣት ወንዶቹ የሚከተለውን ሁኔታ ንገራቸው፡፡ ዳዊት፣ ዝነኛው ልጅ፣ የቅርጫት ኳስ ቡድን ባቋቋመ ግዜ፣ ጂም እንዲህ ብሎት ነበር፣ “ያን ያህል ጉበዝ አልነበረም፡፡ አሠልጣኙ ስለሚወደው ብቻ ነው ቡድኑን ያቋቋመው፡፡”

• ጂም ምናልባት ምን እየተሰማው ይሆን? (ቅናት ወይም ምቀኝነት፡፡)

• ምቀኝነትን እንዴት ነው የምናሳየው?

• አሽሙር እና ነቀፌታ አንዳንዴ ምኘቀንነትን ያሳያሉ? ለምን እና እንዴት?

• ጂም የምቀኝነት ስሚቱን ለማሸነፍ ምን ማድረግ ይችላል?

አፍቃሪ የሆነ ሰው አንድ ሌላ ግለሰብ ሊሳካለት ደስተኛ እንደሆነ ግለጽ።

“ፍጹም ፍቅር አይመካም፤ ፍቅር አይታበይም” የሚለውን የቃላት ዝርዝር መ. ለጥፍ፡፡

• መመካት ሲል ምን ማለቱ ነው? (በከንቱ መኩራት፣ መፎከር ወይም ማድረግ፡፡)

የሚከተለውን ሁናቴ አቀርብ፡፡ የውጤት ካርዶች ሲታደሉ፣ ማይክ እንዲህ አለ፣ “እንዲያውም የእኔን መመልከት አያስፈልገኝም! የኔ ነጥቦች ሁሌም በክፍሉ ውስጥ ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡”

• ማይክ በነጥቦቹ የተኩራራው ለምን ይመስላችኋል?

• በከንቱ ማድረግ ወይም መኩራራት አላፍቃሪነቱ ምን ላይ ነው?

• እንድትኩራሩ ብትፈተኑ ምን ማድረግ ትችላላችሁ?

ፍጹም ፍቅርን በበለጠ ለመግለፅ፣ አንድ ወጣት 1ኛ ቆሮንቶስ 13፥5 እንዲያነብ አድርግ። ወጣት ወንዱ ፅሑፉን በሚያነብበት ጊዜ ከጥቀሱ መጀመሪያ “ፍጹም ፍቅር ያላቸው የአሮናዊ ክህነት ያዦች . . .” የሚሉትን ቃላት እንዲያስገባ አድርግ።

ፍጹም ፍቅር “ብቻዬን ይድላኝ አያሰኝም” የሚለውን የቃላት ዝርዝር ሠ. ለጥፍ።

• ነውር ፀባይ ምንድን ነው? (ጥሩ ያልሆነ ወይም የማይገባ ፀባይ ማሳየት።)

• እንደዚህ ባለ መንገድ ጸባይን ማንጸባረቅ ለምንድን ነው ለላፍቃሪ የሚያደርገው?

ፍጹም ፍቅር “የራሱን አይፈልግም” የሚለውን የቃላት ዝርዝር ረ. ለጥፍ።

• “የራሱን አይፈልግም” ለሚለው ሌላ የአባባል መንገድ ምንድን ነው? (ስግብግብ አለመሆን።)

ሙሉ በሙሉ እንደ ኢየሱስ ራስ ወዳድ አለመሆን በየዕለቱ ልንሰራለት የሚገባ ግብ መሆኑን ግለፅ።

ሽማግሌ ማሪዮን ዲ ሀንክስ እንዲህ ብለዋል፡ “እግዚአብሔር እያንዳንዱ ልጁን ይወዳል፣ . . . ነገር ግን እግዚአብሔር የፍቀሩን መሳሪያዎች ይሻል። እሱ ፍቅሩን መሸከም እና በሌሎች ሕይወት ውስጥ ትርጉም ያለው እና ግላዊ ማድረግ . . . የሚችሉትን ይሻል” (“Gifts You Can’t Wrap,” *New Era*, ታህሳስ 1972, ገጽ 18)።

• የሰማዩ አባታችንን ፍቅር ለሌሎች ሰዎች ለማዳረስ ምን ልታደርግ ትችላለህ?

• ይህ እንዴት ራስ ወዳድነትን እንድታሸንፍ ሊረዳህ ይችላል?

ፍጹም ፍቅር “አይበሳጭም” የሚለውን የቃላት ዝርዝር ሰ. ለጥፍ።

• ብስጩ መሆን ምን ማለት ነው? (ቁጡ፣ ተናዳጅ መሆን፣ የራስን ባህሪ አለመግዛት።)

የሚከተለውን ሁናቴ በራስህ አባባል አቅርብ። የቶድ ታናሽ ወንድም የቶድን ብስክሌት በጣም ይወዳታል። አንድ ቀን ብስክሌቷን ሳይጠይቅ ተዋሰ። ቶድ ጉዳዩን ባወቀበት ግዜ፣ ለወንድሙ እንዲያብራራለት ዕድል ሳይሰጠው በቁጣ ጦፈ።

• በቀላሉ ተናዳጅ መሆን እንዴት እኛን እና ሌሎች በጉዳይ የምንገናኛቸውን ሰዎች ሊጐዳ ይችላል?

ፍጹም ፍቅር “ክፉን ነገር አያሳስብም” የሚለውን የቃላት ዝርዝር ሸ. ለጥፍ።

• “ክፉን የሚያሳስቡ” አንዳንድ ምሳሌዎች የትኞቹ ናቸው? (ብልግና፣ ንጹህ አለመሆን፣ አመለቢስ፣ ወይም ጥሩ ያልሆኑ አስተሳሰቦች።)

• ክፉ ማሰብ በፀባይህ ላይ እንዴት ተፅእኖ ያረጋል?

አንድ ወጣት 1ኛ ቆሮንጦስ 13፥6 እንዲያነብ አድርግ። በጥቀሉ መጀመሪያ ላይ ወጣት ወንዱ “ፍቅር ያላቸው የአሮናዊ ክህነት ያዦች . . .” የሚሉትን ቃላት አስገብቶ ፅሑፉን እንዲያነብ አድርግ።

ፍጹም ፍቅር “ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም” የሚለውን የቃላት ዝርዝር ቀ. ለጥፍ።

• በዓመፃ አለመደሰት ምን ማለት ነው?

• አንዳንድ ሰዎች በዓመፃ እንዴት ነው የሚደሰቱት?

• እውነት በህይወታችን ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ታሪክ

አንድ ወጣት ወንድ ለጓደኛው እንዴት ፍጹም ፍቅርን እንዳሳየ የሚተርከውን ታሪክ እንዲያዳምጡ አድርግ።

“በህይወት ተለዋዋጭ ደረጃዎች እና ጦርነቱ ባስከተለው ውጤቶች ምክንያት፣ በታኢ ዋህን ሀገር፣ በኮሪያ እንክብካቤ የጎደላቸው ብዙ ሕፃናት አሉ። አብዛኛዎቹ ለመሠረታዊ ፍላጎቶች ያህል ብቻ በማግኘት የሚኖሩ፣ ወላጆቻቸውም እነሱን ት/ቤት ለመስደድ ያላቸውን ሁሉ የሰጡ ናቸው። ነገር ግን ታኢ ዋህን እድለኛ ነው። የኪም ቤተሰቦች ከአብዛኛዎቹ ቤተሰቦች በእጅጉ የተሻሉ ናቸው።

“አንድ ጠዋት ታኢ ዋህን እናቱን እንዲህ ብሎ ጠየቃት፣ ‘እማ፣ ሌላ ተጨማሪ ምሳ ትሰሪልኛለሽ?’ ወ/ሮ ኪም ልጇ እየወፈረ በማደጉ ሌላ ተጨማሪ ትንሽ ምግብ እንዳስፈለገው እያሰበች ምሳ አዘጋጀችለት። ከዚህ ግዜ በኋላ በየቀኑ ይዞት የሚሄድ ተጨማሪ ምሳ ታዘጋጅለታለች።

“አንድ ቀን ዶክተር ኪም ከቀርብ ጓደኛው በሥራ ቦታ ላይ እንዳለ የስልክ ጥሪ ተደረገለት።

“ ‘ሄሎ፣ ዶክተር ኪም። ሰሞኑን ቤተሰብህ እንዴት ነው?’

“እንዴ . . . በጣም ደህና ናቸው!’ በፈገግታ ዶክተር ኪም መለሰ።

“ሁለቱ ጓደኛሞች ለቶ ሊ በመሀሉ በድንገት፣ ‘በቀርቡ ቤተሰብህ ምንም ችግር እንደሌለበት እርግጠኛ ነህ?’ በማለት እስከ ተናገረበት ግዜ ድረስ እየተቀባበሉ ያወጉ ነበር።

“ትንሽ ዝም ብሎ፣ ዶክተር ኪም በጥያቄ፣ ‘ለምን፣ የምን ችግር?’ በማለት መለሰ፡፡

“ ‘ዶክተር ኪም፣ ታኢ ዋህን ከጥቂት ቀናት በፊት በየሠፈሩ ጋዜጣ እያዘዋወረ ሲሸጥ አይቼዋለሁ፡፡’

“‘ምን? እርግጠኛ ነህ?’

“ ‘እርግጠኛ ነኝ! ስለ ቤተሰብህ ደህንነት ተቀርቋሪ ብቻ ስለነበርኩ እና ካንተ ለማረጋገጥ ስለፈለኩ ነበር፡፡

“ ‘ዶክተር ኪም ያን ቀን ከሰዓት በኋላ በቢሮው ውስጥ ታኢ ዋህን ለምን ይህን ነገር እንደሚያደርግ እናም ለማንም ሳይናገር ባለማለቱ ሲገረም፣ ሲደነቅ ነበር፡፡ ያን ቀን ማታ ከአራት በኋላ፣ ዶክተር ኪም ከልጁ ጋር የሚነጋገርበትን አጋጣሚ በፀጥታ ተጠባበቀ፡፡ በመጨረሻም፣ ‘ታኢ ዋህን፣ ለደቂቃ ካንተ ጋር መነጋገር እችላለሁ?’ አለ፡፡

“እንዴ እንዴታ፣ አባዬ’

“ ‘ልጄ፣ ዛሬ ከአቶ ሊ ስልክ ደርሶኝ ነበር፡፡ ከጥቂት ቀናት በፊት በመሀል ከተማ ጋዜጣ ስትሸጥ እንዳየህ ተናገረ፡፡ እውነት ነው?’

“ታኢ ዋህን ‘አዎን፣ አባዬ፣ ነገር ግን የክፍል ጓደኛዬን ለመርዳት ብዬ ነው፡፡ የሚበላው ምሣ ስላልነበረው ከኔ ትርፍ የሆነውን ምሳ እየሰጠሁት ነው፡፡ ለምንሽጠውም ለእያንዳንዱ ጋዜጣ፣ 40ዋን ይከፍለናል፡፡’

“ ‘ልጄ፣ ለምንድን ነው ይህን የምታደርገው? እኔን መጀመሪያ መጠየቅ ይገባህ ነበር፡፡’

“ ‘ነገር ግን፣ አባዬ፣ ሁልጊዜ ጓደኛዬን በረዳሁት ቁጥር፣ መልካሙን ሳምራዊ እንደሆንኩ ይሰማኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ እንደ እኔ እድለኞች ያልሆኑትን የክፍል ጓደኞቼን መርዳት እፈልጋለሁ፡፡ የማደርገውን ነገር ያን ያህል ትልቅ አይደለም፡፡ በሲምናሪ የመምሪያ መፅሐፌ ላይ ስለሱ አንብቢያለሁ እናም ማድረግ የሚገባኝ ነገር መሆኑ ተሰማኝ፡፡’

“ታኢ ዋህን የአዳኛችንን ትዕዛዝ፣ ‘ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም፣ በፍጹም ኃይልህም በፍጹም አሳብህም ውደድ፣ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ የሚለውን ትርጉም ያውቃል፡፡’ (ሉቃስ 10፡27፡፡)” (“Profiting for Others,” *New Era*, ሰኔ 1979, ገፅ 50)፡፡

- ታኢ ዋህን ለጓደኛው እንዳደረገለት አንተስ አንድ ነገር ልታደርግለት የምትችለውን ሰው ታውቃለህ?

---

**ማጠቃለያ**

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቀስ እና ውይይት**

እምነተ ቢስነትን፣ ራስ ወዳድነትን፣ ግልፍተኝነትን፣ ምቀኝነትን፣ ከንቱነትን፣ ጥሩ ያልሆነ ምግባረን፣ ቁጣን፣ ሐሜትን፣ እና አጭበርባሪነትን ከሕይወታችን ውስጥ ስናስወግድ ደግሞ ፍቀርን ማጉልበት እንደምንችል ግለጽ፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስን ምሳሌ በመከተል፣ የበለጠ አፍቃሪ እንሆናለን፡፡

ሞሮናይ 7፡47–48 እንደገና አንብብ እና ወጣት ወንዶቹ ፍቀርን ለማጉልበት ምን ለማድረግ እንደሚችሉ ለማሰብ እንዲያዳምጡ ጠይቀ፡፡

- ይህ ጥቀስ ምን እንድናደርግ ነው የሚነግረን?
- አፍቃሪ ሕይወትን ለሚኖሩ ሰዎች ምን ተስፋዎች ተሰጥቷቸዋል?

**ሙከራ**

ወጣት ወንዶቹ ከቤተሰባቸው መካከል ወይም ከሚያውቋቸው ሰዎች መካከል ፍጹም ፍቀርን ሊያሳዩት የሚችሉትን አንድ ሰው እንዲመርጡ ሞክር፡፡ የክርስቶስን ንጹህ ፍቀር ለማዳበር እንዲፀልዩ እና የሰማዩ አባትን ዕርዳታ እንዲሹ አበረታታቸው፡፡ በዋርዱ ውስጥ ለአንድ ሰው ወጣት ወንዶቹ ፍቀርን ማሳየት ይችሉ ዘንድ የቡድን እንቅስቃሴ ማቀድ ትችላለህ።

# 17 የግል ማኀደር

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት አንድ የግል መጽሔት የመያዝን አስፈላጊነት መረዳት አለበት፡፡ |

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት ቅዱሳን መፅሐፍት።
   ለ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ ወረቀት እና እርሳስ።
2. ግላዊ ልምዶችን ለመናገር ተዘጋጅተህ እና (የትምሕርቱን መግቢያ ተመልከት)።
3. ለእያንዳንዱ የአሮናዊ ክህነት ያዝ "የግላዊ ማህደር አያያዝ ምሳሌ" የሚለውን በእጅ የተዘጋጀ ጽሑፍ ቅጂ ያዘጋጁ።
4. በሳምንቱ ውስጥ ሁለት ወይም ሶስት ወጣት ወንዶች መጥተው ያዘጋጁትን ልምድ ወይም ስለ እራሳቸው ማህደር አያያዝ እንዲያካፍሉ ጠይቅ፡፡

የአስተማሪው ማስታወሻ — ወጣቶቹ ስለ ማህደር ስለ መያዝ ጥቅም እንዲያደንቁ ከማድረግህ በፊት አስቀድመህ ግልጋሎቱን ልትረዳ ይገባሀል። የዚህን ትምህርት ጠቀሜታ ለማወቅ እና እንዴት እንደምታቀርበው ምሪት እንድታገኝ የመንፈስ እርዳታን ፈልግ። ከዚህ ቀደም እንዲህ አድርገህ የማታውቅ ከሆነ ከእራስህ ማህደር ላይ ለመጻፍ እና ከወጣት ወንዶች ጋር ስለዚህ ልምድ ስሚትን ለመግለጽ በዚህ ሳምንት ተጠቀም።

---

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**እያንዳንዳችን ለራሳችን ማህደር ማዘጋጀት አለብን**

የአማካሪው አቀራረብ — ያለህን መንፈሳዊ ወይም አስደሳች ልምድ ለወጣት ወንዶቹ ንገራቸው፡፡ ልምዱ እንዲያስደስት አድርገህ በሚቻልህ መጠን ንገራቸው፣ እና ከዚያ በኋላ እንዴት እና ለምን በማህደርህ ውስጥ ተጣድፈህ እንደጻፍክ ንገራቸው፡፡ በግዜው ማህደር ከሌለህ፣ እነዚያን ለምን ለማስቀመጥ እንደቻልክ እና እንደፈለገህ ንገራቸው፡፡ ወይም ክፍሉ ሊደሰትበት የሚችለውን የቀድመ አያቶችህን ማህደር አንዱን ክፍል ማንበብ ትችላለህ። አንተ እና ሌሎች እነዚያን አያቶች በሚገባ ያውቁት ዘንድ ይህ በአጋጣሚ ተጽፎ መገኘቱ ምን ያህል እንዳስደሰተህ ግለጽ።

ልምዳቸውን ለማካፈል ተዘጋጅተው የመጡትን ወጣት ወንድ ሰዎች ጋብዝ።

• ስንተቻችሁ ናችሁ የግል ማህደር የያዛችሁ?

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እና ውይይት — አንድ ወጣት ወንድ ልጅ ሙሴ 6፡5–6 እንዲያነብ አድርግ።

• የሰው ዘር ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ መዝገቦችን እንድንይዝ የታዘዝነው ለምን ይመስለሃል?

ወጣት ወንዶች እንዲመልሱ ፍቀድላቸው፣ ከዚያ በኋል ንጉስ ቢኒያም ለወንድ ልጁ የሰጠውን አንድ በጣም አስፈላጊ ምክንያት ንገራቸው፡፡

አንድ ወጣት ወንድ ሰው ሞዛያ 1፡4–5 ያንብብ፡፡

• የንጉስ ቢንያም አደራጐት ትክክለኛ ታሪክ ለመመዝገብ እኛ ከጌታ ጋር ስላለን ኃላፊነት የሰጠው ምክንያት ምን ነበር?

ጥቅስ — ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል እያንዳንዱ ሰው ማህደር መያዝ እንዳለበት እንደሚያበረታታ ግለጽ።

"ወጣት ቤተሰቦቼ የማስታወሻ ደብተር ይኑራችሁ፣ መዝገቡ ሁል ግዜ መቀየት ከቻለ፣ ምናልባት መልዕክቶች ለዘለዓለም ውስጥ ከእሱ ለመጠቀስ ይችላሉ፡፡ ዛሬ ጀምሩ እና በውስጡ የእናንተን አካሄዶች እና አመጣጦች ጻፉ፣ ትልቅ ሐሳቦቻችሁን፣ የእናንተን ከፍተኛ ስኬቶች እና የእናንተን ውድቀቶች፣ እና ድሎቻችሁ፣ ግምቶቻችሁ እና የምስክርነቶቻችሁ፡፡ መልዕክቶች ከዚህ ይጠቀሱ ("The Angels Qouted From It," *New Era*, ጥቅምት 1975, ገጽ 5)፡፡

---

**ታሪክን መመዝገብ አስፈላጊ መመሪያ ነው፡፡**

ታሪክ — "በልጅነቴ እናቴ በእርግጥ ምን እንደምትመስል ለማወቅ እፈልግ እንደነበር ማስታወስ እችላለሁ. . . .። እናቴን በጣም እፈልጋታለሁ፡፡

“በእርግጥ፣ ሜሪ ብላክ ሮላይን የምትባል እናት ነበረችኝ፣ ነገር ግን የዘጠኝ ሳምንት እድሜ ሳለሁ ነበር በሃያ ስድስት አመት እድሚዋ የሞተችው። አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ አባቴ ከሥራ ወደ ቤቱ ሲመለስ እሷን በማዕድ ቤቱ ወለል ላይ ወድቃ አገኛት፣ በልብ ድካም ሞታለች። ስለ እናቴ ጠንቀቀው የሚያውቁ ስለ እርሷ መናገር በጣም ስቃይ እንደሆነ ያውቃሉ ስለዚህ ስለ እርሷ በበለጠ ለማወቅ መሞከር አልፈለግም።

“አስራ ሰባት ዓመት ሲሞላኝ የአባቴ እናት እኔን ለማየት መጣች። እናቴ ስለ ልቧ ሁኔታ ስታገባ ታውቅ እንደነበር ነገረችኝ። ልጅ ከወለደች ምናልባት እንደምትሞት ታውቅ ነበር። ነገር ግን እናቴ፣ ተስፋ ሳትቆርጥ በጥንካሬ አገናዝባ ልጅ እንዲኖራት ወሰነች እኔም ከሷ ወሰንኩ። ያን ባወቅሁ ጊዜ ለእናቴ ያለኝ ፍቅር በጣም ጨመረ፣ እናቴም እንድሁ እንደምትወደኝ አውቃለሁ፣ በጣም ስለምትወደኝም ነው በፍቃደኝነት ሕይወቷን ስለ እኔ ስትል የሰጠች።

“ከዚያ በኋላ እናቴ የጻፈችውን ማስታወሻ አባቴ አመጣልኝ። በአንድ ዓመት አጭር ህይወቷ ውስጥ በየእለቱ ያሰበሰበችው ነበር። የእናቴን የአንድ ዓመት ሕይወት በእጄ አሉኝ። በዚያ ዓመት ፀሆሚ ውስጥ አስተማሪ ነበረች፣ እናም በእራሷ ቃላቶች አማካኝነት በመጨረሻ ትክክለኛ ሰው መሆኗን አወቀሁ ጮኸች፣ ታገለች፣ ሳቀች፣ ስለልቧ ሁኔታ ተማረች እና እኔ. . . . እኔ ይህን እሷነቷን ከእርሷ ጋር ተካፈልኩ!

“የ ማስታወሻ፣ የከበረ የፍቅር ማስታወሻ—ይህ ሁሉ ስለ እሷ አለኝ። ማስታወሻውን” (“For Your Remembrance: A Presentation on Record Keeping” [audiovisual presentation, 1975 MIA ሰኔ Conference)።

**ውይይት**

- መጽሔቱን ለማዘጋጀት በዚህ ታሪክ ውስጥ የተንጸባረቀው አስፈላጊ ምክንያት ምንድን ነው?
- የአንተን ማን ያነብ ይሆን?
- እንዴት ያገለግላቸው ይሆን?

ማኅደሮች ለልጆቻችን እና ለልጅ ልጆቻችን የህይወታችንን ገጠመኝ የምናካፍልበት የተለየ መንገድ መሆኑን ግለጽ።

---

## እያንዳንዱ የአሮናዊ ክህነት ያዥ የግል ማህደር ማዘጋጀት አለበት

**የአማካሪ አቀራረብ**

ሁላችንም የሰራናቸውን እና እየሰራናቸው ያሉትን ነገሮች ለማስፈር የመስህብነት ዝንባሌ የላቸውም ብለን እንደምናስብ ግለጽ። ነገር ግን በወደፊት ዓመታቶች ውስጥ—እኛም ስናረጅ ሆነ፣ ለልጆቻችን፣ ወይም ለልጅ ልጆቻችን—እነዚህ ነገሮች ስሚትን ቀስቀሰው ህይወታችን እና የእኛን ዓለም ሊያዩ ይችሉ ይሆናል። ከእያንዳንዱ አዲስ ትውልድ አዲስ ሀሳቦች፣ አዲስ መንፈሳዊ ልምዶች፣ እና ለእድገት አዲስ እድሎች እና አስተዳደጉች ይመጣሉ።

የግል ማኅደር ማን እንደሆንን፣ ወዴት እየሄድን እንደሆነ፣ እና ምን እያከናወንን እንደሆነ የሚገልጽ ሁል ግዜም የሚያድግ መዝገብ መሆኑን ለወጣት ወንዶቹ አሳስብ። ጌታ የሚፈልገውን ዓይነት ሰው ለመሆን ማኅደሮቻችን አቀዶቻችንን እና የየቀኑን ሙከራዎችን ለመመዝገብ እጅግ በጣም ጥሩ ቦታ ናቸው።

**ምንባቦች፣ ጥቁር ሠሌዳ፣ እና ውይይት**

በርከት ያሉ ወጣት ወንዶችን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ፣ ከዚያም በራሳቸው አገላለጽ የምንባቡን ይዘት እንዲያስረዱ ጠይቅ። በጠመኔ ሠሌዳ ላይ ፍሬ ሀሳቡን በአጭሩ አቅርብ።

1. *ምን አይነት ማኅደር መጠቀም ይገባኛል?* የእለት እንቅስቃሴዎችህን የምትመዘግብበትን ማህደር ምረጥ። ይህም ውድ ያልሆነ፣ የማይለወጥ ያልተበላሸ ወይም ጠንካራ የሆነ የቀን ተቀን ማስታወሻ ይሆናል። ዋነኞቹ መስፈርቶች ጥራት ያለው ወረቀት እና ጠንካራ ቻይ ሽፋን መቦን ናቸው።
2. *በማኅደሬ ውስጥ ስንቴ መፃፍ ይገባኛል?* የግል ባህሪህ፣ ፍላጐቶችህ እና ጊዜህ በማኅደርህ ስንት ጊዜ መፃፍ እንዳለብህ ይወስናሉ። በእያንዳንዱ ጊዜ ያለፉትን ድርጊቶች መዝገቦች መያዝ አያስፈልግም። ካለፉት ድርጊቶች ደማቅ እና ዋናዎቹን መዝግብ፣ እንዲሁም የአሁኖቹን ክንዋኔዎች መዝን ከዚያም ከአሁኖቹ ጋር ቀጥል። ሁል ጊዜ በፃፍክ ቁጥር፣ ማኅደርህ ይበልጥ ትክክለኛ ይሆናል። አንዳንዱ ነገር በየዕለቱ ይፃፋል፣ ሌሎች በሳምንት ሁለቴ ወይም ሦስቴ ይጻፋሉ። ዕቅድ አኑር እናም ስራበት።
3. *ምን መመዝገብ ይገባኛል?* (በፕሬዚዳንት ኪምቦል የተሰጠውን አባባል አንድ ወጣት እንዲያነብ ጠይቅ።)
4. *ማኅደሬን ሳዘጋጅ እንዴት የፈጠራ ችሎታ ያለው መሆን እችላለሁ?* ምናልባት አልፎ አልፎ የልብስ ወይም የምግብ ወይም የንባብህ ወይም ኃይማኖታዊ ስሚትህን እና ችግሮችህን፣ ስለ ትምህርት እና መንግስት አስተያዩቶች ወይም አሁን ስላለህ የገንዘብ ይዞታ በዝርዝር መፃፍ ትችላለህ። የመግቢያህ ንጽሮችን፣ ቀርጾችን፣ ፎቶ ግራፎችን ወይም ግጥሞችን ልትጨምራቸው ትችላለህ።

**ተሳትፎ**

በማህደራቸው ውስጥ አንድ ነገር ለማከል በመጻፍ እድል ለማግኘት እንደሚችሉ ለወጣት ወንዶች ንገር። ከዚህ ቀደም ማኅደር ያላቸው እቤታቸው ሲደርሱ ይህንን ጨምረው መመዝገብ ይችላሉ። ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ አንድ ገጽ ወረቀት እና እርሳስ ስጥ። በአለፉት ቀናቶች ያላቸውን ልምድ እንዲጽፉ ጠይቅ፣ ስለ አደረጉት ማንኛውም ነገር ስሚታቸውን በማከል መሥራታቸውን አረጋግጥ። የተሰማቸውን ሥራ በክፍል ውስጥ ለመጨረስ ግዜ ከሌላቸው፣ በመኖሪያ ቤታቸው ለመጨረስ አበረታታቸው። ማኅደርህ የህይወትህን ስቶቶች እና ታላላቅ ጉዳዮች የምትመዘግብበት ስፍራ መሆኑን አስታውስ።

| | |
|---|---|
| | **ማጠቃለያ** |
| ሙከራ | ወጣት ወንዶችን ማኅደሮቻቸው ውስጥ በየዕለቱ ወይም በየሳምቱ መፃፍ እንዲቀጥሉ ፍላጎታቸውን አነሳሳ። ከዚያ በኋላ ከነሱ ጋር በየወቀት ለብዙ ወራቶች ውስጥ ተከታተላቸው እና ብዙ ግዜ አበረታታቸው። |
| የሚታደል ጽሑፍ | ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ ማጣቀሻው ይሆንለት ዘንድ በማህድሩ ሽፋን ውስጥ ማስቀመጥ የሚፈልገውን የሚከተለውን በእጅ የተዘጋጀ ጽሑፍ ቀጂ ስጥ።<br><br>• ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ ማጣቀሻው ይሆንለት ዘንድ በማህድሩ ሽፋን ውስጥ ማስቀመጥ የሚፈልገውን የሚከተለውን በእጅ የተዘጋጀ ጽሑፍ ቀጂ ስጥ። |

# ማኅደር የማዘጋጃ ምክሮች

1. ጥሩ ዓይነት ብዕር እና ወረቀት ተጠቀም። የተበላሸ ብዕር ወይም እርሳስ በጭራሽ አትጠቀም።
2. የጋዜጣ ቁርጥራጮች የማስታወሻውን ገጾች ወደ ቢጫነት ይለውጣሉ።
3. የተያያዙ የወረቀት ቁርጥራጭ እና የዛጉ እስፒሎች፣ የማስታወሻ ገጾችን በጣም ሊያቆሽሻቸው ይችላል።
4. ከግዜ በኋላ አብዛኛውን የጥቅል ማጣበቂያዎች እና ማስቲሾቶች በቀላሉ ስለሚለቁ ለረጅም ግዜ ለመያዝ አይችሉም።
5. ለማን፣ የት፣ ምን፣ ወዴት፣ መቼ እና ለምን ነገሮችን እንደምትሰራ አብራራ። ያደረካቸውን ውሳኔዎችን እንዴት እነዚህ ውሳኔዎች ላይ እንደደረስክ ግለጽ።
6. ቀኖችን፣ ወሮችን፣ እና ዓመታትን ከየአንዳንዱ መግቢያ ጋር አመልክት። ለመጀመሪያ ግዜ ስትጠቀሰው ወይም ስትጠቀሳት ሙሉ ስምን ጻፍ። ከእኛ ጋር ሁልጊዜ ይሆናሉ ብለን የምናስባቸው የቀርብ ጓደኞቻችን ቤት ለቀው ሊሄድ ይችላሉ እናም ግንኙነታችንን ልናቋርጥ፣ ስለምንችል ስማቸውንና ሁኔታውንም ልንረሳ እንችላለን።
7. ችግሮችን ጥርጣሬዎችን፣ እና ጥላቻዎችን መጥቀስ ደህና ነው፣ ነገር ግን የተለመዱ ቀናቶችን እና የደስታ ግዜያቶችን በጣም መናገር ተገቢ ነው። (ጥቂት ቀደምት ሀሳቦች የተዘጋጁት ከዊሊያም ጂ ሀርትሌ፣ Diary and Journal Ideas," *New Era*, መጋቢት 1977, ከገፅ 40–43)።

**አማራጭ ተሳትፎ**
**ቤተሰብ ምርምር ጋር**
**ቀድመ አያቶችን መፈለግ**

**ዓላማው**

አማካሪዎች የቤተሰብ ጥናት ምን እደሆነ፣ ወጣት ወንዶች ቀድመ አያቶቻቸውን ለመለየት እንዲችሉ እንዴት እንደሚረዳቸው እና በበለጠ ጠቃሚ ለማድረግ ምን ማድረግ እንደሚችሉ ይገልጻሉ።

ይህ እንቅስቃሴ ወጣት ወንዶችን የቤተሰብ ምርምር ወደሚገኝበት ቦታ ይሰወዳቸዋል።

**ዝግጅት**

በዝግጅት ጊዜ፣ እንቅስቃሴዎቹ የት መደረግ እንዳለባቸው ወስን፡፡ በአካባቢው ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ፣ ይህ የቤተሰብ ታሪክ ማዕከል፣ የእስቴክ ማዕከል፣ የአካባቢ የመሰብሰቢያ ቤት፣ ወይም የአባላት መኖሪያ ቤት ሊሆን ይችላል ከተቻለ፣ ብዙ ወጣቶችን በተመመሳሳይ ጊዜ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ከአንድ የበለጠ የቤተሰብ ጥናት የሚደረግበት የሥራ ጣቢያ ምረጥ።

ማስታወሻ፤ ቡድኑ በጣም ትልቀ ከሆነ ምናልባት ወደ አነስተኛ ቡድን መክፈሉ አመቺ ነው፡፡

ለሥራው ሌላ ተጨማሪ አማራጭ የሚሆን አሰራር አዘጋጅ። ጥቂት ወጣት ወንዶች የቤተሰብ ጥናትን ሲጠቀሙ ሌሎች ስለ ቤተሰብ መዝገብ አሰባሰብ መማር ይችላሉ እና ከዚያም በማንኛውም የማሰባሰቢያ ፕሮጀክት መሳተፍ ይችላሉ። ይህ የሚቀነበባረው በዋርድ የቤተሰብ ታሪክ መሪ አስተባባሪ መሆን አለበት፡፡ ሌላው እንቅስቃሴ ስለ ቤተመቀደስ ወይም በቀደም አያቶቻቸው ላይ እንደሚያነጣጥሩ የሚስብ ለወጣት ወንድ ሰዎች የሚረዳ መመሪያን የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡

ከእንቅስቃሴው በፊት ወጣት ወንዶች ከወላጆቻቸው ጋር እንዲሰሩ፣ የዘር ሐረግ ሰንጠረዥን እንዲሞሉ በተቻለ መጠን መድብ።

**በቤተሰብ ታሪክ ሥራ አማካኝነት የእኛን ቀድመ አያቶች መለየት**

የአማካሪው አቀረረብ

በዚህ ህይወት የተቀበልነውን በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ የመታተምን ተመሳሳይ ዕድል ለመስጠት ቀድመ አያቶቻችንን እንደምንፈልግ ለወጣት ወንዶች ንገራቸው፡፡ ብቁዎች ከሆንን እነዚህ የደህንነት ሥርዓቶች ማለትም (ጥምቀት፣ ክህነት ስልጣን ሹመት፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እና ህትመቶች) ወደ ሰለስቲያል መንግስት እንድንገባ ያደርጉናል።

*የቤተሰብ ምርምር* ስለ ቀድመ አያቶችህ መረጃ ለመፈለግ የሚያስችል የኮምፒተር ዘዴ ነው። የቀድመ አያትህን ስም በኮምፒዩተር ውስጥ ስትጽፍ፣ የቤተሰብ ምርምር በፍጥነት የሚመሳሰሉ ስሞችን በሚሊዮን ከሚቆጠሩ የኮምፒዩተር ፋይሎቹ ውስጥ ይመለከታል። በእስክሪኑ ፋይል ላይ ከሥሞችን ማውጫዎች አንስቶ እስከ የትውልድ የጋብቻ እና የሞት ቀናትን እና ቦታን፤ እንዲሁም የወላጆችን፤ ልጆችን እና የጋብቻ ጓደኛን ስሞችን ያሳያል።

በቤተሰብ ምርምር ውስጥ የመረጃ ምንጮች ከቤተሰብ የዘር ሐረጎች፣ ከቤተክርስቲያን መዝገቦች፣ የመንግስት መዝገቦች ይመጣሉ፡፡

የቤተሰብ ምርምር ከብዙ ፋይሎች መረጃ የተሰራ ነው፡፡ ለአንተ በጣም የሚረዳው ፋይል የዘር ሀረግ ፋይል ነው ይህ ፋይል ከ1979 ጀምሮ በቤተክርሲያኑ አባላት እና በዓለም ሁሉ ከሚኖሩት ሌሎች ሁሉ የተሰባሰበውን የቤተሰብ ታሪክ መረጃን ይይዛል።

ማስታወሻ፣ ሙሉ የዘር ሀረግ ሰንጠረዦችን እና የቤተሰብ ቡድን መዝገብ የያዘውን የቤተሰብ ታሪክ መረጃ “የማስታወሻ መጽሐፍን” በመያዝ ለወጣት ወንዶች የቤተሰባቸውን ታሪክ ለተዋጣት አስፈላጊነት ማብራራት ትችላለህ። በመጽሐፉ ውስጥ ያለው መረጃ በጣም ዋጋ እንዳለው ማስረዳት ትችላለህ፣ ነገር ግን በዚህ ህትመት ይዘትና አቀራረብ ለጥቂት ሰዎች ብቻ ይጠቀማል። በመሆኑም ይህ መረጃ በኮምፒዩተር አቀራረብ ሲለወጥ (በኮምፒዩተር ፕሮግራም የቀድመ አያት የግል ፋይል አጠቃቀም)፣ በቀድመ አያት ፋይል ውስጥ ሊጠቃለል ይችላል፣ ይህን ሌሎች ይጠቀሙበታል፡፡

እንዲሁም የቀድመ አያት ፋይል አለመጠናቀቃቸውን አመልክት። እነኚህ ብዙ መረጃዎች አሏቸው፣ ነገር ግን—ወጣት ወንዶች ስለ እራሳቸው ቀድመ አያቶች ሊኖራቸው የሚችለው ጨምሮ ብዙ ሊጨመርባቸው ይችላል፡፡

የቀድመ አያት ፋይል መረጃ፣ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሰዎችን ስም እና አድራሻዎች አካቷል። ምናልባት በዚህ መንገድ ወጣት ወንዶቹ ፈጽሞ ያላገኟቸውን ዘመዶች ሊያገኙ ይችላሉ።

ለበለጠ እርዳታ ወጣት ወንዶቹ የቤተሰብ ምርምር ታላቀነት በማገናዘብ ከኮምፒዩተር ውጭ ስለ ቀድመ እያቶቻቸው መረጃ ለመፈለግ በማይክሮ ፊልም ጥቀሎች እና ከመጽሐፍት ገጾች መመልከት እንዳለባቸው ማስረዳት፡፡ ከዚህ በፊት ይህን ላደረጉ ብዙዎች፣ ይህ ብዙ ሥራ ጠይቋል። አንድ ዓይነት መረጃን በደቂቃዎች ውስጥ ለመመርመር ኮምፒዩተር የተሻለ ይሠራል፡፡

**የኮምፒዩተር ተግባር**

ስለ ቀድመ አያቶቻቸው መረጃ በመፈለግ የቤተሰብ ምርምርን ልምምድ ወጣት ወንዶቹ ማድረግ አለባቸው፡፡ በዘር ሀረጋቸው ሠንጠረዥ ስሞችን እንዲጠሩ እርዳ። በቀድመ አያቶች ፋይል ውስጥ ስለ ቀድመ አያቶቻቸው ምንም ነገር ባይኖር፣ ስለ ቀድመ አያቶቻቸው ለፋይሉ የተዋጣውን ያንን መረጃ በማየት ታላቀ አገለግሎት ማድረግ እንደሚችሉ አስታውሳቸው።

ወጣት ወንዶች የቤተሰብን ምርምር ሲጠቀሙ፣ ያገኙትን መረጃ በጉልህ መፃፍ አለባቸው፡፡ በቀድመ አያቶች ፋይል፣ የዘር ሀረግ ሠንጠረዥ በጉልህ መፃፍ ይችላሉ።

የሆነ ሆኖ ወጣት ወንዶች የቤተሰብ ምርምርን ለመጠቀም እድሉ አላቸው፣ ያከናወኑትንም መከለስ አለባቸው፡፡ ስለ ቀድመ አያቶቻቸው መረጃን እንዲፈልጉ እንዲሁም የቀድመ አያቶች ፋይል እገዛ ማድረግ እንዲቀጥሉ ፍላጐታቸውን አነሳሳ።

---

## ሥራዎችን በጥንቃቄ ተከታተል

**የአገልግሎት እንቅስቃሴ**

ጥቂት የዋርድ አባሎች የታተሙ የቤተሰብ የታሪክ መረጃ አቀራረብ (የማስታወሻ መጽሐፍት) አሏቸው፡፡ የወጣት ወንዶች ዋጋ ያለው አገልግሎት መረጃን በኮምፒዩተር በማስገባት እና የባሎችን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ በመርዳት መፈፀም ይችላሉ፡፡ ወጣት ወንዶቹ ይህን ለማድረግ እንዲያስችላቸው፣ የግል ኮምፒዩተሮች ከግል የቀድመ አያት ፋይል ጋር አብሮ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። የዋርድ የቤተሰብ ታሪክ አማካሪዎች እንዲህ ያለውን የአገልግሎት ሥራ በማደረጃጀቱ ሊረዱህ ይችላሉ፡፡

# የጥበብ ቃል

# 18

**ዓላማው** እያንዳንዱ ወጣት ወንድ በጥበብ ቃሎች ሲኖር በመንፈሳዊ እና በስጋዊ በረከቶች እንዴት መባረክ እንደሚችል ይገነዘባል።

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት ቅዱሳን መፅሐፍት።
   ለ. ቅዱሳን መጽሐፍትን ምልክት ማድረጊያ እርሳሶች።
2. በትምህርቱ የመጨረሻ ክፍል ውስጥ ሁለት ወጣት ወንዶች ታሪክ እንዲያነቡ ወይም እንዲናገሩ ጠይቅ። (በሚገባ እንዲዘጋጁ አበረታታቸው።)
3. በአካባቢህ ከተገኘ፣ "ሱስ የነፃነት ጠር፣" ከቤተሰብ ምሽት የቪዲዮ ማሟያ [*Family Home Evening Video Supplement* 2] 2(53277) ማሳየት ትችላለህ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሀሳብ**

**መግቢያ**

ቅዱሳን መጽሐፍት እና ውይይት

- "የጥበብ ቃል" የሚለው ሐረግ ለአንተ ምን ማለት ነው?
- የጥበብ ቃልን የት እናገኘዋለን? (ትምህርት እና ቃል ኪዳን 89)
- ጌታ የጥበብ ቃል የሰጠን ለምን ይመስልሀል?
- ጌታ እንደ አንድ ልጁ ለአካላዊ ደህንነትህ የሚቸገረው ለምን እንደሆነ ይሰማሀል?
- የጥበብ ቃል እንድናስወግድ የሚነግረን ምንድን ነው?

የወጣት ወንዶችን መልሶች በጠመኔው ሰሌዳ ላይ ፃፍ።

ወጣት ወንዶቹ ትምህርት እና ቃል ኪዳን 89 እንዲገልጡ እና ተጨማሪ መመሪያዎችን እንዲፈልጉ አድርግ።

- የጥበብ ቃልን ለማይታዘዙ ሊደርሱባቸው የሚችሉ ውጤቶች ምንድን ናቸው?

ወጣት ወንዶቹ ሲመልሱ፣ የአስተያየታቸውን ፍሬ ነገር ባጭሩ በጠመኔ ሰሌዳ ላይ በሰንጠረዥ ውስጥ በሚከተለው ተመሳሳይ ሁኔታ አቅርብ።

| **አስወግድ** | **ሊደርስ የሚችል ችግር** | |
|---|---|---|
| አልኮልነት ያላቸው መጠጦች | አደገኛ የሆነ ሱስ | ጤና፣ መኖሪያ ቤት፣ ቤተሰብ፣ ሥራ፣ ገንዘብ ማጣት፣ |
| | ከሱስ ሊመጡ የሚችሉ | ደግነትን ማጣት፣ የአባለዘር በሽታ፣ ያልተፈለገ እርግዝና |
| | ጠጥቶ መንዳት | አደጋዎች፣ ጉዳት ሞት |
| | የምግብ ጉድለት | የልብ በሽታ፣ የጉበት በሽታ፣ ያልተወለዱ ያሉ ህጻናትን መጉዳት፡፡ |
| ትምባሆ | ኒኮቲን ሱሰኝነትን | ነቀርሳ (ካንሠር)፣ ኢንፌዝማ፣ የደም በደንብ አለመዘዋወር፣ የልብ በሽታ፣ የተረገዙ ሕጻናትን መጉዳት |
| ሻይና ቡና | አደገኛ የሆነ ሱስ | የጤንነት ችግር ለልብ በሽታ ያለው አስተዋፅኦ |

ስለ አደገኛ ዕጽ ጉዳት ብዙ ቢባልም፣ አሁንም ብዙዎች ትንባሆ፣ አልኮል፣ ሻይ እና ቡና፣ ሁሉም አደገኛ እፅ እደያዙ አልተረዱም። እነሱን በስፋት በመጠቀም ምክንያት ቡና፣ ሻይ፣ አልኮል፣ እና ትንባሆ ወደ አደገኛ እፅ ሱሰኝነት የሚያመሩ በይበልጥ የተለመዱ ንጥረ ነገሮች ናቸው።

ጥቅሶች እና ውይይት

ምንም እንኳ በትምህርት እና ቃል ኪዳን በክፍል 89 ስለ ማሪዋና፣ ኮኬን ወይም ስለሌሎች አደገኛ እፆች የተባለ ነገር ባይኖርም፣ የቤተክርስቲያን መሪዎች ስለነዚህ አደገኛ እፆች ማስጠንቀቃቸውን ግለፅ።

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪንቦል የሰጡትን የሚከተለውን ምክር ግለፅ፣

"ሰዎች ሁሉንም ዓይነት እፅ ከህይወታቸው ለማስወገድ እንደሚችሉ ተስፋ እናደርጋለን። ብዙዎች በእጾች ላይ እንደማስታገሻ መድኀኒት እና ለእንቅልፍ አጋዥነት ስለሚጠቀሙባቸው ጥገኛ ናቸው፣ ሁልግዜ አስፈላጊነት የሌለው ነው።

"ማሪዋናን እና ሌሎች ገዳይ እፆችን በመጠቀም ብዙ ወጣት ሰዎች በፍጹም እየተበላሹ ወይም እያለቁ ነው። በዚህም እናዝናለን" (በ Conference Report ጥቅምት 1974, ገጽ 6; ወይም *Ensign* ታህሳስ 1974, ገጽ 6)።

የዚህ አይነት እፆችን አደገኛነት በአጭሩ ተወያይ። አደገኛ እፆች ለሱሰኛነት እና አእምሮንና ሰውነትን ለመጉዳት ምክንያቶች እደሆኑ መጥቀስ ትችላለህ።

ግዜ ከፈቀደልህ ሕይወቱ በአደገኛ ንጥረ ነገሮች ተመርዞ የተጐዳን አንድ የምታውቀውን ሰው ታሪክ፣ ስም ሳትጠቀስ መናገር ትችላለህ። አካሎቻችንን ለመጠበቅ እና በአደገኛ ንጥረ ነገር ምክንያት የሚመጣን ሐዘን ለማስወገድ እንዲረዳን ጌታ የጥበብ ቃል እንደሰጠን አጥብቀህ ተናገር።

---

**የጥበብ ቃልን መጠበቅ ታላቅ አካላዊ እና መንፈሳዊ በረከቶችን ያመጣል**

ቅዱስ መጽሐፍት እና ውይይት

ጌታ በጥበብ ቃል ለሚኖሩ እና አካሎቻቸውን በጥሩ ጥንቃቄ ለጠበቁ ልጆቹ ሁሉ ታላቅ በረከቶችን ቃል እንደገባላቸው ግለፅ። ምን በረከቶችን ቃል እንደገባልን ለማወቅ፣ አንድ ወጣት ትምህርት እና ቃል ኪዳን 89፥18–21ን በሚያነብበት ግዜ ሌሎች ቅዱሳን መፃህፍቶቻቸውን እንዲከታተሉ አድርግ። ይህን ጥቅስ ምልክት እንዲያደርጉበት አበረታታቸው።

- ትዕዛዛቶቹን እና የጥበብንም ቃል ለሚጠብቁ ጌታ ቃል የገባላቸው በረከቶች ምንድን ናቸው?

ታሪክ

የጥበብ ቃል በጠበቅን ጊዜ የምንቀበላቸውን በረከቶች አንድ ወጣት እንዴት እንደተማረ የሚነግረንን የሚቀጥለውን ታሪክ አንብብ፣

"በትክክል አስራ ሁለት ዓመት አልሞላኝም ነበር፣ ነገር ግን ከ60 አመት በፊት ከአባቴ ጋር በትክክል እሰራ ነበር። እሱ ሲያጭድ እኔ ደግሞ እህሉን አስር ነበር . . . በየቀኑ፣ አድካሚ ሥራ ነበር።

"ቀዳሚ ቀን ጉህ ሲቀድ ሥራ ጀመርን ከዚያም የዚያኑ ቀን ማታ ወደ ሁለት ሰዓት ተኩል ገደማ ሥራችንን አቆምን። በጣም ደክሞኝ ነበር እንዲያውም እራት ሳልጠብቅ ጋደም ብዬ መተኛትን እፈልግ ነበር።

"አባቴ ወደ እኔ እየተመለከተ በርጋታ እንዲህ አለኝ፣ 'ሊ፣ ዛሬ ያጨድኩበት የእህል መደብ በጣም እርጥብ ነበር፡፡ እስከ ሰኞ ድረስ ከጠበቅን . . .፣ ፍሬዎቹ ይጨማደዳሉ ዛሬ ማታ መሥራት አለብን፡፡ እውጭ (ብሩህ) ጨረቃ አለች፡፡ እኔን ልትረዳኝ የምትችል ይመስልሀል?

"እንባዎቼን በትግል መለስኩ እና በመስማማት እራሴን ነቀነቅሁ።

"አባቴም ጥሩ ነው ትንሽ እራት ሊኖረን ይገባል አለ፣ እኔ አሳማዎችን ልመግብ እና ጥራጥሬውን ማሰር እችላለሁ፡፡

"ዳቦ እና ወተቱን ቶሎ ጨረስን፣ ነገር ግን አሁንም በጣም ደክሞኝ ስለነበር እራሴን ማንሳት አልቻልኩም። አባቴ አሳማዎቹን ሊመግብ ሲወጣ፣ በጠረጴዛው አጠገብ ተቀምጬ አምርሬ አስብ ነበር፣ ፈፅሞ ጠጥቼ ወይም አጭሼ አላውቅም፣ ሁል ጊዜ የጥበብን ቃል አከብራለሁ። ትምህርት እና ቃል ኪዳን እንደሚለው የጥበብ ቃልን ካከበርክ ትሮጣለህ አትደክምም እና ትሄዳለህ አትጐዳም፡፡ እናም አሁን በጣም ደክሞኛል እራሴንም ማንሳት አልችልም። በድካም እንባዬን ለመቀዋጥ ስትገል አፌ ተርገበገበ።

"ምን እንደተከሰተ ለመግለጽ የሚያዳግት ነው፣ ነገር ግን በጣም የሚያምር የሚሽከረከር የነጭ ብርሃን ብልጭታ ወደ ሰውነቴ የገባ መሰለኝ፣ አካላቴን የሆነ መንፈሳዊነት ተሰማው፡፡ አባቴ ተመለሰ እና ወደ እርሻዎቹ ሄድን።

"አባቴ በጣም ፈጣን ሠራተኛ ነበር፣ ምንም እንኳን በሚቻለው ፍጥነት መሥራት ቢችልም ግን በዚያ ምሽት ከኔ ጋር ሊወዳደር አልቻለም፡፡ እስሮች ሳይባክኑ ብዙ ከእኔ ክብደት በላይ የነበሩትን ጣል በማድረግ፣ ከ[ዳር እስከ ዳር] ሮጥሁ፡፡ በአባቴ አይኖች ውስጥ የታየውን አድናቆት በጭራሽ ልረሳው አልችልም፡፡

"ይህ የተከሰተውን ነገር የነገርኩት ከሰላሳ አመት፣ በኋላ ነበር ነገር ግን እስካሁን ያንን ሌሊት ያስታውሰዋል፡፡ ይህን በጭራሽ ልረሳው አልችልም፡፡" (Leo W. Spencer, "To Run and Not Be Weary," *Ensign,* መጋቢት 1974, ገጽ 45)፡፡

ጥቅስ እና ውይይት

አብዛኛውን ጊዜ ለጥበብ ቃል መታዘዝ አካላዊ ጥቅም ብቻ እንዳለው እናስባለን።

- የጥበብ ቃል እንዴት በመንፈስ ሊባርክህ ይችላል?

በቄስ ቦይድ ኬ ፓኬር የተጻፈውን የሚከተለውን አረፍተ ነገር አንብብ፡

“የጥበብ ቃል አመሰራረት ከራዕይ ጋር እንደሆነ . . . ለማወቅ ችያለሁኝ።

“ማናቸውም ጤንነትህን የሚረብሹ ሻይ፣ ቡና፣ የአልኮል መጠጦች፣ ትንባሆ፣ አደንዛዥ እጾችን እንድታስወግድ ከትንሽነትህ ጊዜ ጀምሮ አንተን አስተምረንሃል፡፡

“አንዳችሁን ከነዚህ ነገሮች ጋር ሲነካካ ብናገኝ እና ብናውቀው ያ እኛን በጣም ያስጨንቀናል፡፡

“በተፅእኖ ሥር ያሉ ሰዎች ግልፅ ንግግርን ምንም ለመስማት አይችሉም፣ ታዲያ በጣም ለስላሳ ስሜቶቻቸውን ለሚነካ መንፈሳዊ መነሳሳት እንዴት መመለስ ይችላሉ?

“የጥበብ ቃል እንደ ጤንነት ህግ ጠቃሚ ነው፣ ምናልባት ከስጋዊነት የበለጠ ለመንፈሳዊነት ጠቃሚ ነው፡፡

“የጥበብ ቃሉን ብትጠብቀ እንኳ፣ በአንተ አካል የሚከሰቱ ጥቂት ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፣ ነገር ግን እነዚያ ነገሮች በጥቅሉ የአንተን መንፈሳዊነት ሙሉ በሙሉ ሊያበላሹት አይችሉም” (በ Conference Report, ጥቅምት 1979, ከገጽ 28–29; ወይም *Ensign,* ህዳር 1979, ገጽ 20)፡፡

- የእውቀት “ድብቀ ሀብቶች መኖር” ማለት ምንድን ነው? (ይህ ማለት መንፈስ ቅዱስ ወደ እውቀት፣ እውነት እና ምስክርነት ሲመራን እና ሲገልጥልን እናገኘዋለን ማለት ሊሆን ይችላል።)
- የጥበብ ቃልን ከታዘዝን ምን ሌላ መንፈሳዊ በረከቶችን መቀበል እንችላለን?

---

**የጥበብ ቃልን በመኖር አንድ ጥሩ ምሳሌ ማስቀመጥ እንችላለን**

ታሪክ

የተመደበው ወጣት ወንድ የሚከተለውን ታሪክ እንዲያነብ ወይም እንዲናገር አድርግ፡፡

“በየተራ እየተጠባበቃችሁ አትገቡና አትሞቁም?” ተናጋሪው ታቲሱ ሣቶ በጃፓን ናሪያሚ መንደር ውስጥ እንግሊዝኛ የሚናገር እሱ ብቻ ነበር፡፡ በሱቁ መስኮት ውስጥ የአሚሪካን ወታደሮችን አየ፣ በአየሩ ውስጥ ቀዝቃዚ እንዳለ ትንፋሻቸው ያሳያል፣ እንዲሞቃቸው እግሮቻቸውን በደረቁ መሬት ላይ አሳርፈዋል። ምንም እንኳ ሶስቱ ወታደሮች በመደነቅ ቢመለከቱም፣ የአጭሩን ባለግርማ ሞገስ ጃፓናዊ ሰው ግብዣ ወዲያውኑ ተቀበሉ፡፡

አንዴ ወደ ውስጥ በመግባት፣ አሚሪካኖቹ ባለቤቱን በማመስገን በተንሿ ሂባቺ ውስጥ እጆቻቸውን በአንድነት በሚያስተናግደው ከሰል ላይ እያሹ ሳሉ የእንግዳ ተቀባይነት ምልክት ይሆን ዘንድ ታቴሱ ሳቶ ለየአንዳንዱ እንግዳ እንፋሎት ያለው ምርጥ ሻይ ሰጣቸው፡፡ “እናመሰግናለን፣ ነገር ግን ሻይ አንጠጣም ወይም ሌሎች የሚያነቃቁ ነገሮች አንጠቀምም፣” ሲል አንዱ ወታደር መለሰ፡፡ “አካላቶቻችን በጣም የተቀደሱ የእግዚአብሔር ስጦታዎች መሆናቸውን ቤተክርስቲያናችን አስተምራናለች እናም ለጤንነታችን የተለየ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡”

“ይህ በጣም እንግዳ ትምህርት ነው፣” ሳቶ ሣን አለ። “መጽሐፍ ቅዱስን ሳጠና እንዲህ ያለ እምነት በፍጹም ሰምቼ አላውቅም”፡፡

“የጥበብ ቃል” ተብሎ ስለሚጠራው የእግዚአብሔር ራዕይ ወታደሮቹ ገለጹለት፣ ለዝምተኛው ምሁር ሰው ይህን ተመልሰው በይበልጥ ስለእምነታቸው ለመንገር ጋበዙት፡፡

ቃል እንደገቡት፣ ወታደሮቹ ተመለሱ እናም ከሳቶ ቤተሰብ ጋር የጥናት ክፍሎችን መያዝ ጀመሩ፡፡ ታትሱ ሣቶ ያመጡለትን መጽሐፈ ሞርሞን ከሽፋን እስከ ሽፋን አነበበ። ከዚያም በድጋሚ አነበበ፣ አጠና፣ ፀለየም።

በናሩሚ የበጋ ዝናብ በሚመጣበት ወቅት ታትሱ ሣቶ እና የእሱ ሚስት መጽሀፉ እውነት እንደሆኑ አመኑ። የኋለኛው ቀን ቅዱሳን አገልጋዮች የእነሱን ሻይ ለመጠጣት ካልፈቀዱ እና ስለእምነቶቻቸውም ከነገሯቸው በኋላ ህይወታቸው ተለወጠ።

በሃያ አመታቶች ውስጥ የሳቶ ቤተሰብ ጥምቀት በጃፓን ቅዱሳን ትውልድ ውስጥ የመጀመሪያው ጥምቀት ነበር እናም ለቤተክርስቲያኗ በጃፓን ውስጥ አዲስ ዘመን ጀመረ፡፡ ወንድም ሣቶ ለጃፓን ሚሲዮን አስተርጓሚ እና የትርጉም ሠራተኛ ሆነ፡፡ ብዙ መመሪያዎች እና ትናንሽ መጽሐፍ፣ እንዲሁም የቤተመቅደስ ሥነሥርዓት በጃፓንኛ፣ እና በርከት ያሉ የተወሰኑ ሥራዎች ተርጉሟል፡፡ እሱና ሚስቱ የዘር ሀረግ ሥራዎችን ምርምር ብዙ የጃፓኖችን ስሞች በመመዝገብ የንጉሳዊ ቤተሰቦችንም በማጠቃለል ለቤተመቅደስ ስራዎች በማመቻቸት ሠርተዋል፡፡ በጃፓን ውስጥ ቤተመቅደስ ሲገነባ ወንድም እና እህት ሳቶ ለምርቃቱ እዚያ ነበሩ እናም ወንድም ሳቶም በቤተመቅደስ ውስጥ አጣማሪ ሆነ፡፡ በዚህ በአንድ ሰው ድካም አማካኝነት የሺዎች ጃፓናውያን ሕይወት ተለወጠ (ከ Harrison T. Price, “A Cup of Tea,” የተወሰደ *Improvement Era,* መጋቢት 1962, ከገጽ 160–61, 184, 186)።

ውይይት

የጥበብ ቃሎችን የአገልግሎት ሰዎች በመጠበቃቸው ያስከተለውን ውጤት ተወያይበት፡፡

- ወታደሮቹ ሻያቸውን ጠጥተው ቢሄዱ ኖሮ ይህ ታሪክ እንዴት የተለየ ይሆናል?

ታሪክ

የተመደበው ወጣት የሚከተለውን ታሪክ እንዲናገር ወይም እንዲያነብ አድርግ፡

“በቲህራን የኢራን ዋና ከተማ ውስጥ የተመደበ አንድ ወጣት ሰው . . . የቤተክርስቲያናችን አባል ነበር፡፡ እዚያ በነበረ ግዜ ግዜውን ለተሻለ ጥቀም ለማዋል ወስና የፋሪስ ቋንቋ ተማረ። ይህን ለማድረግ የተሻለ መንገድ አስቦ ከትናንሽ ልጆች ጋር እነሱ የፋርስን ቋንቋ ሲያስተምሩት እሱም እንግሊዝኛ ያስተምራቸዋል . . . በአስተርጓሚ በኩል በጣም ብልህ ወጣት ልጆች አገኘ፤ ወጣት ወንድ ልጅ እና ወጣት ልጃገረድ፤. . . . አገኘ—እንግሊዘኛ የሚያስተምራቸው እነሱም ፋርሲ እንዲያስተምሩት መሆኑን ነገራቸው። በእዚህ እድል በበለጠ ተደሰቱ እና ይህንንም ጀመሩ . . . እርስ በርሳቸው ጋር ለመገናኘት የቻሉት በጣም አጭር ግዜ ብቻ ነበር። እሱ ምንም ዓይነት የማስተማሪያ ቁሳቁሶች አልነበረውም፤ ነገር ግን የነበረው *የአገልጋይ ሰው የወንጌል መመሪያዎች* እና የእሱ መጽሐፈ ሞርሞን ነበሩ፤ ከነሱ ጋር ከነዚህ የእንግሊዝኛ መጽሐፍት ማንበብ ጀመረ፡፡ በትምህርቱ ላይ፤ ስለጥበብ ቃል እና የምናምነውን እና በቤተክርስቲያናችን ውስጥ የምናደርገውን ብዙ ነገሮች አስተምሯቸዋል፡፡ አንድ ቀን መጥቶ ከአጎታቸው ጋር እንዲገናኝ ጋበዙት. . .። ትንሿን ሴት ልጁ በትከሻው ላይ እንዲሁም ወንዱን ልጁ በእጁ ይዞ ወደ አጎትዬው ቤት እየተሳሳቁ እና መንገዱን ሁሉ እየተጫወቱ ሄዱ፡፡ እዚያ ሲደርሱ አጐታቸው እጆቹን ዘርግቶ ተቀበላቸው። በጣም በጣም እንግዳ ተቀባይ ነበር እናም ግዜያቸውን በግሩም ሁኔታ አሳለፉ፡፡ በመጨረሻም ሰውዬው ተነሳ እና ወደ እሱ የመጽሐፍት ሳጥን ሄደ፤ ክዳኑን ከፈተ፤ እናም ወደ ውስጥ ዘለቀ፤ በጣም ጥሩ የብር ዝርግ ሣህን፤ የብር ፍንጃልና ከብር የተሠሩ በጣም ትንንሽ ኩባያዎች ነበሩ፡፡ በሚያምረው የነሐስ ጠረጴዛ ላይ ዝርጉን ሳህን አምጥቶ ከፊታቸው አስቀመጠው፤ እና በጣም በጥንቃቄ ቡሹን ከፍንጃሉ ላይ በማንሳት በጣም ግሩም ቀይ የወይን ጠጅ ወደ ትናንሾቹ የብር ኩባያ ቀዳ፡፡—[ወጣቱ ወንድ] ለራሱ እያሰበ፤ ‘ምን ማድረግ አለብኝ? በዚሁ ነገር አላምንም፤ ነገር ግን ከሁሉም በኋላ ለእኔ በጣም እንግዳ ተቀባይ ሁኗል እናም ይህ የሀገሩ ባህል ነው፡፡ በማናቸውም መንገድ እሱን ለመከላከል አልፈለግም እናም ይህን ማድረግ አለብኝ፤’ አለ። እና በትክክል ይህንኑ አደረገ ዝርጉ የማቀረቢያ ሳህን ሲመጣለት፤ ከጭላጭ የማይበልጠውን ይህን ትንሽ የብር ኩባያ በማንሳት ስለ ሰውዬው ጤንነት በመቀመስ ጠጥቶ ጨረሰ። ወዲያውኑ ጭውውቱ ተጓተተ። በክፍሎቹ ውስጥ ዝምታ ሰፈነ፡፡ እሱም ያልተረጋጋ ሆነ እና ጭውውቱን አቋረጠ፤ ትንሿን ሴት ልጁ በትከሻው ላይ ያዘ እናም ትንሹን ወንድ ልጁ በእጁ ይዞ ወደቤታቸው ሲሄዱ በመንገድ ላይ ትንሿ ልጅ ማልቀስ ጀመረች፡፡ ‘ማሬ ለምን ታለቅሻለሽ?’ አለ? ለምን ጠጣህው? እሱም አለ ምን ጠጣሁ፤ እናም ልጅየው አለ ለምን ያን መጠጥ ወደድክ? እሱም ደህና አለ ይህም ትንሽ ለምልክት የተሞላ ነበር “ደህና አለ ልጁ ያ ምንም ልዩነት የለውም፡፡ አባትዬውም አለ አንተም ይህን ታደርገዋለህ ስለጥበብ ቃሎች ሁሉንም ነገርነው፤ እናም እሱም አለ እነዚህ አሜሪካኖች ስለብዙ ነገር ያወራሉ፤ ነገር ግን በእነርሱ አያምኑም። እኛም በትክክል እንዲደረግ ነገርነው ነገር ግን አንተ አላደረግኸውም፡፡ (ወጣቱ ወንድ ሰው) ወዲያው እንደተከሰተ ደህና አለ የአደረገውን ድርጊት ካስታወሰ ቀኝ እጁን መታጠብ ብቻ የሚቻለው ይሆናል፤ ምክንያቱም ከነዚያ ትናንሽ ልጆች ሕይወታቸው ላይ እሱ ያደረገውን ውድመት ያውቃል፡፡ እነዚያ በጭራሽ ወደኋላ አላመለጡም፡፡ እነዚያ ሐገር ውስጥ ስሜት ላላቸው ሕዝቦች ወንጌልን ለማሰራጨት ምናልባት ዋጋ ያለውን ግንኙነት እድል አጡ፡፡ (“Theodore M. Burton, *Tickling the Tiger,* Brigham Young University Speeches of the Year [Provo, ጥር 17 1961], ከገጽ 7–9)፡፡

ውይይት

- የዚህ የወጣት ወንድ የድርጊቶች ውጤት ምን ነበር?
- ወጣቱ ወንድ ወይኑን ለመጠጣት ባይስማማ ይህ ታሪክ እንዴት ልዩነት ሊኖረው ይችላል?
- በትንሽ ስኒ ውስጥ ያለና በጣም ጥቂት ከሆነ መጠን ያልበለጠ ወይን የወጣቱን ሰውነት ይጐዳዋል ብለህ ታስባለህ?

ጉዳት የሚያስከትል ትንሽ መጠን ያለው ማናቸውም ነገር ለእኛ ተፈጥሮአዊ አካል ጥሩ ያለመሆኑን ወጣት ወንዶቹ እንዲያገናዝቡ እርዳቸው። የአልኮል ሱሰኞች የመጀመሪያዋን መጠጥ ባይወስዱ ኖሮ የአልኮል ሱሰኛ አይሆኑም ነበር።

- ይህ መንፈሱን ይጐዳዋልን?

---

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት

ጌታ ለወጣት ወንዶች የጥበብ ቃልን የሰጠበት ምክንያት ስለሚወደን እና በአካላዊ እና መንፈሳዊ ንጽህና ብቻ የሚመጣውን ደስታ እንድናገኝ ስለፈለገ እንደሆነ ለወጣት ወንዶቹ በአእምሯቸው እንዲያድርባቸው አድርግ። የጥበብ ቃልን ከአከበርን ጌታ በገባው ቃል ኪዳን በአካላዊ እና በመንፈሳዊነት ይባርከናል።

ስለ ጥበብ ቃሎች እና ለክህነት ሥልጣን ተሸካሚዎች በሙሉ ይህንን መታዘዝ እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ ያለህን ምስክርነት ስጥ።

ሙከራ

*ወጣቶችን ለማጠናከር* በገጽ አስራ ሁለት ላይ የአእምሮ እና አካላዊ ጤንነት የተሰጠውን ምክር ከልስ፡፡ ወጣት ወንዶች የጥበብ ቃልን እንዲያጠኑ የተሻለ ግንዛቤም እንዲያተርፉ ፍላጐታቸውን አነሳሳ። በፅኑ የጥበብ ቃል እንደ ጌታ ትዕዛዝነቱ ሕይወታቸውን ሙሉ በትምህርቱ መሠረት ይኖሩበት ዘንድ ተገቢ ስለመሆኑ ጠንካራ እምነት ይኖራቸው ዘንድ በቀጣይነት ስለ ጥበብ ቃል እንዲፀልዩ አድርጋቸው።

# ፈተናዎችን መቋቋም

# 19

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ፈተናዎችን ማስወገድ እንደሚችል መገንዘብ አለበት። |
| **ዝግጅት** | የሚያስፈልጉ የትምህርት መሣሪያዎች<br>1. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ ቅዱሳን መፅሐፍት<br>2. የቅዱስ መጽሐፍት ጥቀሶችን ምልክት ማድረጊያ እርሳሶች።<br>3. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ እርሳስ እና ወረቀት። |

**ለትምህርት ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**ፈተናዎችን ማወቅ እና መቋቋም**

ታሪክ እና ውይይት

አንድ ሰው ለመጓጓዣ ኩባኒያው ለአዲስ ሹፌሮች ቃለ መጠይቅ ያደርግ ነበር፡፡ መንገዱ በጣም አደገኛ እና በተራራው መተላለፊያ ውስጥ ብዙ ገደላማ ደረጃዎች ያስኬዳል፡፡ ቃለ መጠይቅ አቀራቢው እያንዳንዱን ሰው እንዴት በገደሉ ጠርዝ ጥግ በደህንነት ለመንዳት ትችላለህ ሲል ጠየቀ። የመጀመሪያ ሰው፣ “እኔ ከገደሉ አፋፍ በስድስት ኢንች ውስጥ ለመንዳት እችላለሁ” አለ። ሁለተኛውም ሰው፣ “እኔ ከገደሉ አፋፍ ኢንች ውስጥ ማሽከርከር እችላለሁ፡፡” ሶስተኛው ሰው መለሰ፣” በሚቻለኝ ከገደሉ አፋፍ እርቃለሁ” አለ።

• ሥራው ለማን ይሰጣል ብለህ ታስባለህ? (ለሶስተኛው ሰው።)

• የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሰዎች ምናልባት ትልቅ የመንዳት ችሎታዎች ቢኖራቸውም እንኳን፣ ለሶስተኛው ሰው ሥራው ሊሰጠው የቻለበት ለምን ይመስልሃል? (በሚቻለው ከአደጋ በርቀት መቆየት እንዳለበት ስለ ተገነዘበ።)

ይህ ትምሕርት ስለ ፈተና እንደሚያስረዳ እና ሰማያዊ አባታችን በዚህ ምድራዊ ህይወት ፈተናን እንድንለማመድ ስለ በመፍቀዱ መሆኑን አስረዳ።

ቅዱሳን መጽሐፍት፣ እና ጥቁር ሰሌዳ ውይይት

አንድ ወጣት ሰው ያዕቀብ 1፥12–14 እንዲያነብ አድርግ፡፡

• ከዚህ ቅዱስ መጽሐፍት ጥቀስ ምንድን እንማራለን?

የሚከተሉትን ሶስት ነጥቦች በጠመኔ ሰሌዳ ላይ መዝግብ፥

1. ፈተናዎችን በምንታገስ ጊዜ እንባረካለን፡፡

2. እግዚአብሔር አይፈትነንም።

3. ማንኛውም ሰው ይፈተናል።

በጠመኔ ሰሌዳው መኻል ከላይ ወደታች ቀጥ ያለ መሥመር አስምር፡፡ አንደኛውን ወገን ጥሩ፣ እንዲሁም ሌላኛውን መጥፎ ብለህ ሰይም። ሁለት ነጥቦችን አኑር፣ ሁለቱንም በተከፈለው መሥመር በጥሩ ጉን ላይ ይሁኑ—አንዱ ነጥብ ወደ መሥመሩ ይጠጋል፣ እና ሌላኛው ከመስመሩ በፍጹም ይርቃል፡፡

• እነዚህ ሁለት ነጥቦች ሁለት የተለያዩ ግለሰቦችን እንደሚወክሉ ገምቱ፡፡ የትኛው ነው በይበልጥ ጥሩ ሆኖ ሊቀይ የሚችለው? (ከመስመሩ ርቀ ያለው።)

• ለምን? (ከገደሉ አፋፍ እርቀ በመቆየቱ እንደተቀጠረው ብልሁ ሹፌር፣ ከፈተና ርቀ መቆየት፣ ለፈተናው እጃችንን መስጠትን ይበልጥ ይቀንሳል።)

ጥያቄ

በፕሬዚዳንት ጆርጅ አልበርት ስሚዝ ፈተናን ስለ ማስወገድ የተሰጠውን የሚከተለውን መግለጫ ወጣቱ ወንዶች እንዲያነቡ ያድርጉ።

“አያቴ ለቤተሰቡ እንዲህ ይናገር ነበር፣ ‘በጌታ ግዛት እና እና በዳቢሎስ ግዛት መኻከል ግልጽ የሆነ የተከለለ መሥመር አለ። በጌታ ወገን ባለው መስመር ከቆየህ፣ በእሱ ተጽኖ ሥር በመሆን ስህተት ለማድረግ ምንም ፍላጉት ሊኖርህ አይችልም፤ ነገር ግን አንድ ኢንች ወደ ዳቢሎስ መስመር ካቋረጥክ፣ በፈታኙ ኃይል ውስጥ ነህ፣ እናም እሱ ውጤታማ ከሆነ አንተ የማሰብ ችሎታ ወይም ምክንያት በትክክል ሊሆን አይችልም፣ ምክንያቱም የጌታ መንፈስ ሊኖርህ አይችልም።’

"አንዳንድ ግዜ አንድ ነገር ለማድረግ በምፈተንበት ጊዜ 'በየትኛው የመስመር አቀጣጫ ላይ ነኝ?' ስል እራሴን እጠይቃለሁ፣ በሚያስተማምነው ወገን መሆኔን ሳውቅ፣ ከጌታ ጐን ሁል ጊዜ ትክክለኛውን ነገር ለማደረግ እችላለሁ፡፡ ፈተና ሲመጣብህ፣ ስለ ችግርህ በማሰብ ጸልይ፣ እናም የጌታ የመንፈስ ተጽእኖ በብልሀት ለመወሰን ያስችልሃል፡፡ ደህንነት የሚኖረውን በጌታ ወገን ብቻ ስንሆን ነው" (በ Spencer W. Kimball, *The Miracle of Forgiveness* [ሶልት ሌክ ከተማ: Bookcraft 1969], ገጽ 232)፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እና ውይይት

• ጌታ እንድንፈተን የፈቀደው ለምን ይመስልሃል? ፈተና ከሌለብን ነፃ ምርጫዎቻችንን ለመምረጥ አንችልም ነበር።)

ትምህርት እና ቃል ኪዳን 29፡39 አንድ ወጣት ወንድ እንዲያነብ አድርግ።

• ልንቋቋም ካልቻልን ሰይጣን በጣሙን ሊፈትነን ይችላልን?

ወጣት ወንዶች ይህንን ጥያቄ እንዲወያይበት አድርግ።

ልንቋቋመው ከምንችለው ኃይል በላይ እደማንፈተን እንዲሁም መውጫውን ከፈለግን ጌታ ሁል ጊዜ መውጫውን እንደሚያበጅልን የሚያበራራውን 1ኛ ቆሮንቶስ 10፡3 ሰው እንዲያነብ አድርግ። ወጣት ልጆቹ ይህን ጥቀስ ምልክት እንዲያደርጉበት አሳስብ።

ይህ ጥቀስ እራሳችን ለምንፈጥረው ማናቸውም ሁኔታ ጌታ እንድንቋቋም ይረዳናል ማለቱ እንዳልሆነ አስረዳ። ፈተናን ለማስወገድ በእኛ በኩል መስራት አለብን የሚከተለውን ምሳሌ አካፍል፣ እርኩስ ሐሳቦችን ለማሰብ ምክንያት ወደሚሆነው ሲኒማ ቤት እንድትሄድ ጓደኞችህ ይፈልጋሉ እንበል።

• እንደዚህ ወዳለው ሲኒማ ቤት በመሄድ ንፁህ ሐሳቦችህን ጌታ እንዲጠብቅልህ እርዳታውን ትፈልጋለህ?

• ይህንን ሁኔታ ከጓደኞችህ ጋር እንዴት መቆጣጠር ይገባሃል?

---

**ፈተናን ማስወገድ እና ማሸነፍ**

የጠመኔ ሰሌዳ እና ውይይት

• ወጣት ወንዶችን የሚያጋጥማቸው የተለያዩ ዓይነት ፈተናዎች ጥቂቶቹ ምንድን ናቸው?

በጥቁር ሠሌዳው ላይ የወጣት ወንዶችን መልሶች በዝርዝር ፃፍ። ዝርዝሩ የሚከተሉት ጥቂት ሃሳቦችን ሊያጠቃልል ይችላል፣

1. ንጹህ ያልሆኑ ሐሳቦች
2. ታማኝ ያለመሆን ወይም ማታለል
3. መሐላ እና የብልግና ቃላት
4. አደንዛዥ እጾች፣ ሲጃራ፣ ወይም የአልኮል መጠጥ
5. የብልግና ፊልሞች እና ቪዲዮዎች

• ፈተናን እንዴት መቋቋም ትችላለህ?

ጥቀሶች፣ ቀዱሳን መጽሐፍት፣ እና ውይይት

ወጣት ወንዶቹ ፈተናን ስለ መወጣት ሐሳባቸውን እንዲሰጡ አበረታታቸው፡፡ በያንዳንዱ ሐሳብ ተወያይ፣ ፈተናን ስለ መከላከል ወይም ስለ መወጣት የተወሰኑ አስተሳሰቦችን ስጥ፡፡ የሚከተሉትን ጥቂት ሀሳቦች መጠቀም ትችላለህ፣ ነገር ግን በመጀመሪያ ወጣት ወንዶቹ ሐሳባቸውን እንዲሰጡ ማበረታታት ይገባሃል።

1. ንጹህ ያልሆኑ ሀሳቦች፣ ቁስ ቦይድ ኬፓኬር በአቀረቡት ሐሳብ ንጹህ ያልሆኑ ሐሳቦች ወደ አምሮአችን ተስበው በሚገቡበት ጊዜ *መዝሙር ወይም ዜማ በቃላችን ስናጠናና ቃላቶቹንም በዓዕምሮአችን ስንከልስ* እነዚህ ሐሳቦች ሾልከው ይወጣሉ ብለዋል።
2. ታማኝ ያለ መሆን ወይም ማታለል፣ ቁስ ጀምስ ታለማጅ እንደ ዲያቆንነታቸው ታማኝ ያለመሆንን ፈተና እንዴት እንደተቋቋሙ እንደሚከተለው ነግረውናል፣ "ወደ ልጅነቴ ሕይወት ጉዳይ ውስጥ ሁሉ ሥርዓተ ሹመቴን ገብቷል. . . . በትምህርት ቤት ሜዳላይ ስጫወት፣ ምናልባት በቡድኑ ውስጥ አግባብ ያልሆነ ነገር ለቶድረግ በተገፋፋሁ ጊዜ . . .፣ እኔ ዲያቆን ነኝ፣ እናም ዲያቆን በዚህ መንገድ መሥራቱ ትክክል አይደለም፡፡ በፈተና ቀናቶች፣ የሌላን ልጅ ሥራ መኮረጅ ቀላል ቢመስልም . . . በአዕምሮዬ እንዲህ እል ነበር፣ አስታውሳለሁ ከነርሱ ይልቅ የእኔ ያንን ማድረጊ የበለጠ መጥፎ ነው፣ ምክንያቱም ዲያቆን ነኝ" (*Incidents from the Lives of Our Church Leaders* [የዲያቆናት መመሪያ፣ 1914], ገጽ 136).
3. መራገም ወይም ስድነት እርግማን ወይም የብልግና ቃላት በአንድ ጭውውት ሊደረጉ እንደሚችሉ የሚከተለው ምሳሌ እንድንገነዘብ ሊረዳን ይችላል። በአንድ ፒያኖ የሙዚቃ ትዕይንት ላይ ነበርክ እንበል። ሙዚቃኛው ለአሥር ደቂቃዎች አሳምሮ ይጫወት ነበር ከዚያም ወዲያኑ ትክክል ያልሆኑ ኖታዎችን ለብዙ ደቂቃዎች ተጫወተ፣ ከዚያ በኋላ ወደ መጀመሪያው ውብ ዜማው ተመለሰ። ምንም እንኳ አብዛኛዎቹ የሙዚቃ ትርኢቶች ውብ ቢሆኑም፣ የትኛውን ክፍል በይበልጥ ታስታውሳለህ? ንግግራችን ውብና ንጹህ ሊሆን ይችላል። በርግማን አታበላሸው!

4. አደንዛዥ እጾች፣ ሲጃራ፣ እና የአልኮል መጠጥ፣ ጠንንካራ እና ጤነኛ እንድንሆን ይረዳን ዘንድ ጌታ የጥበብ ቃል ሰጥቶናል (ት እና ቃ 89 ተመልከት)። ወጣቱ 1ኛ ቆሮንቶስ 3፥16–17 ጮክ ብለው እንዲያነብ አድርግ። *ሰካላቶቻችንን ቤተመቀደስ መሆናቸውን፣ እና ልናረክሳቸው እንደማይገባ ሰጥብቀህ ተናገር።*
5. ንጽህና የጐደላቸው ፊልሞች፣ የአንድ የፊልም ወይም የቴሌቪዥን ፕሮግራም የሚያጠራጥር ከመሰለህ፣ *ስለ እነዚህ ምቹነት ስሜት ማሰብ ይገባሃል። ወደተያትሩ ለመግባት ምቹነቱን ለጳጳስህ ወይም የካህናት መሪህን ለተገቢነቱ ጠይቀ።* ለአንተ ካልተስማማህ በመሠረቱ መሄድ የለብህም።
6. ኀሊናህን እና መንፈስ ቅዱስ ውሳኔዎችን እንድታደርግ እንዲረዳህ ፍቀድላቸው (ሞሮናይ 7፥16–19 ተመልከት)፡፡
7. ለክፉት መጋለጥን አስወግድ፡፡ ወደ ሃጢአት ምን ያህል እንደተጠጋህ አትመልከት ኔፊ በኃጢያት በጣም በመታየቱ ለደረሰበት ንዝረት ጽልዮ ነበር፡፡ (2 ኔፊ 4፥31 ተመልከት)፡፡
8. ውሳኔ በምታደርግበት ጊዜ፣ እራስህን ጠይቅ፣ “ኢየሱስ ምን አደረገ?”
9. በጫና ውስጥ ውሳኔ እንዳታደርግ ሁኔታው ከመፈጠሩ በፊት ውሳኔዎች አድርግ።
10. ፈተናን ለመቋቋም ለጥንካሬ ጸልይ እና ከጌታ እርዳታ ጋር ያንን አስታውስ፣ ሁሉንም ፈተናዎች መቋቋም ትችላለህ፡፡

**ጥቅሶች**

የሰይጣንን ከፍተኛ ተጽእኖ እንጠነቀቅ ዘንድ ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል እንደመከረን ግለጽ። እንዳሉትም “ሰይጣን ጥቁሩን ነጭ ነው ብሎ ይነግረናል፡፡ ይዋሸናል፣ ስለዚህም፣ በሰይጣን ፊት የድፍረት አቋም ለማድረግ መዘጋጀት አለብን. . . . ለመቋቋም እንድችል የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ያስፈልገናል” (“The Blessings and Responsibilities of Womanhood” *Ensign* መጋቢት 1976 ገጽ 71)፡፡

---

**ማጠቃለያ**

ፈተናን ከመቋቋም ስለሚመጣው መንፈሳዊ እድገት እና ደስታ ምስክርነትህን ስጥ፡፡

ሙከራ

እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ለመስራት በሚፈልገው ሁለት ፈተናዎች ላይ እንዲያስብ አድርግ። ከዚያም፣ እያንዳንዳቸውን እነዚህን የተለዩ ፈተናዎች ሊያሸንፉ የሚችሉባቸውን ምንገዶች እንዲያስብ አድርግ። እነዚህን ሁለት ፈተናዎች ነቀተው እንዲከላከሏቸው በሚመጣው ሳምንት የወጣት ወንዶቹን ፍላጎቶች አነሳሳ፡፡

# 20 የነፃ ምርጫ ትክክለኛ ጥቅም

**ዓላማው** — እያንዳንዱ ወጣት አዳኛችንን ለመከተል እና በመንፈሳዊነት ለማደግ ነፃ ምርጫውን ይጠቀማል፡፡

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለየአንዳንዱ ወጣት ቅዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. የኋ.ቀ.ቀ የመዝሙር መጽሐፍት፡፡
   ሐ. እርሳስ ቅዱሳን መጽሐፍትን ምልክት ማድረጊያ እርሳስ።
2. የአደጋ ምልክት ወይም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይህን ሰንጠረዥ ማዘጋጀት፣

   የአዙሪት—አደጋ
   መዋኘት አይፈቀድም!

3. የሚከተለውን ጥቅስ በሰንጠረዥ ወይም በጠመኔ ሠሌዳ ላይ ጻፍ፤

   "የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ፤ . . . እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን" (እያሱ 24፡15)፡፡
4. በትምህርቱ መጨረሻ "ትክክለኛውን ምረጥ" የሚለውን መዝሙር እንዴት ለመጠቀም እንድምትፈልግ ወስን (*መዝሙር* ቁጥር 239)።
5. በአካባቢህ የሚገኝ ከሆነ፣ ይህን ትምህርት "ምርጫዎቻችንና የሚያስከትሉት ውጤቶች ('The Pump') ከቁጥር ስድስት ክፋል ጋር አሟላ፣ "የቤተሰብ የቤት ምሽት ማሟያ ቪዲዮ [*Family Home Evening Video Supplement*] (53276)።

**ለትምህርቱ ዕድገተት የቀረበ ሐሳብ**

**ምርጫዎችን እንድናደርግ እና የሚያስከትሏቸውንም ውጤቶች እንድንቀምስ የመምረጥ ችሎታችን ይፈቅድልናል**

**በቁሳዊ ነገሮች ላይ የተደገፈ ትምህርት**

የማስጠንቀቂያ ምልክት አሳይ። የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያይባቸው፣

- ይህ ምን አይነት ምልክት ነው?
- እንደዚህ ያለ ምልክት ጥቀሙ ምንድን ነው?
- ነፃነታችንን እንዴት አድርጐ ይወስናል?
- ይህን ችላ ብንለው ምን ሊከሰት ይችላል?
- ምልክቱን ብናከብር ምን ዓይነት ጥቀሞች ወደ እኛ ይመጣሉ?

**ውይይት**

ይህን የመሰለ የማስጠንቀቂያ ምልክት በምናይበት ጊዜ ነፃነታችን የተገታ ሊመስለን እንደሚችል ግለጽ። ነገር ግን አሁንም ብዙ ምርጫዎች አሉን፡፡

- በዚህ ሁኔታ ያሉን ጥቂት ምርጫዎች ምንድን ናቸው? (ሌላ ቦታ ለመዋኘት ወይም በባህሩ ዳርቻ ለመራመድ እና የባህር ዛጐሎችን ለመልቀም ነፃ ነን፡፡ የፀሐይ መጥለቅን ማየት እንችላለን፡፡ ወደ መኖሪያ ቤት ለመሄድ ነፃ ነን፡፡ እንዲሁም ምልክቱን ችላ ብለን በአደገኛው ቦታ ለመዋኘት መብት አለን።)

አንዴ በአዙሪት ከተያዝን እና ከውኃው በታች ከተጐተትን፣ ያሉን በጣም ጥቂት ምርጫዎች እንደሆኑ ግለጽ

- ምን ምርጫዎች አሉን? (ለእርዳታ ልንጣራ እንችላለን፣ ነገር ግን እንሰምጥ ይሆናል።)

"ምንም እንኳ የድርጊት አቀጣጫችንን ለመምረጥ ነፃ ብንሆንም ድርጊቶቻችን የሚያስከትሏቸው ውጤቶችን ለመምረጥ መብት እንደሌለን መረዳት አለብን። ውጤቶቹ፣ መጥፎ ወይም ጥሩ ይሁኑ፣ በምናደርገው ማናቸውም ምርጫዎች ምክንያት ይመጣሉ. . . . ለምሳሌ የጋለን ነበልባል ብንነካ እንቃጠላለን "(*የወንጌል መመሪያዎች* [Gospel Principles] [ሶልት ሌክ ከተማ የኋለኛው ቀን ቅዱስን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ 1978]፣ ከገጽ 20–21)፡፡

**የቅዱስ መጽሐፍት ጥቅስ እና ውይይት**

ነፃ ምርጫ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ወጣት ወንዶች እንዲወያዩበት አድርግ፡፡ ነጻ ምርጫ ማለት ደጉን ወይም ክፉውን የመምረጥ ችሎታ እና ነፃነት መሆኑን እንዲገነዘቡ እርዳቸው።

ወጣት ወንዶች ሂለመን 14፥30–31 እንዲያነቡ፣ እንዲወያዩ ምልክት እንዲያደርጉበት አድርግ።

**ጥቅስ**

ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ እንዳሉት፣

ህይወትን ከመስጠት ባሻገር ያንን ህይወት የመምራቱ መብት እግዚአብሔር ለሰው የሰጠው ታላቅ ስጦታ ነው . . .። ምድር ልትሰጠን ከምትችለው ማናቸውም ሀብት እና ንብረት የበለጠው የመምረጥ ነፃነት ነው” (በ Conference Report, ሚያዚያ 1950, ገጽ 32)።

ዘለዓለማዊ መሻሻላችን የተመሰረተው በነጻ ምርጫችን አጠቃቀም ላይ በመሆኑ እንደ ሰማዩ አባታችን ለመምሰል እናም እሱ ወደሚኖርበት ለመመለስ፣ እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ማመንን እና ትክክለኛ ምርጫዎችንም ማድረግ እንዳለብን መማር አለብን። ወደ ምድር የመጣንበት አንዱ ምክንያት ይ ነው፡፡

**ቅዱሳን መጽሐፍት እና ውይይት**

2ኛ ኔፊ 2፥27 እና አብርሃም 3፥24–26 አንብብ። ወጣት ወንዶች የእነዚህን ጥቅሶች ክፍል ላይ ምልክት ማድረግ ይችላሉ።

- የምንፈተነው እንዴት ነው?
- የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለመቀበል የመረጡ ምን በረከቶች ይጠብቃቸዋል?

---

**የወደፊት ህይወታችን መንፈሳዊ ብቁነት የሚመሰረተው በምርጫዎቻችን ላይ ነው።**

**የቅዱስ መጻፍት ታሪኮች እና ውይይት**

ቅዱሳን መጽሐፍት የታላላቅ ሰዎች ምሳሌን እና ስለ ፈጸሙት አስቸጋሪ ምርጫዎች እደሚያስረዱት ግለጽ። ምንም እንኳ ሙሴ ውልደቱ ከዕብራዊያን ወላጆች ቢሆንም ለፈርኦን የሴት ልጅ እንደ ልጅ በመሆን በምቾት ህይወት ማደጉን አብራራ። ሙሴ ሕይወቱን ሙሉ በቅንጦት መኖር ይችል ነበር፡፡ በሱ ፋንታ ለዕብራዊያን ባሮች መብት ለመቆም መረጠ፡፡

- ሙሴ ይህንን ውሳኔ ያደረገው ለምን ይመስልሃል?
- የሙሴ ውሳኔ ያስከተሏቸው ውጤቶች ምን ነበሩ? (ወደ ምድረ በዳ መሸሽ ግድ ሆነበት፣ ነቢይ እንዲሆን በእግዚብሔር ተመርጦ ነበር፣ ዕብራዊያን ባሮችን ከግብጻዊያን ባርነት ነጻ ማድረግ በእግዚአብሄር እጅ መሳሪያ ለመሆን ችሎ ነበር፣ እስራኤላዊያንን በምድረ በዳ ውስጥ ለብዙ ዓመታት መርቷል በሰለስቲያል መንግሥት ውስጥ ዘለዓለማዊ ድህነትን አትርፏል፡፡)

የሶስቱን አይሁዳዊያን ሰዎች ታሪክ— ሲድራቅ፣ ሚሳቅ፣ አብድናጐም—በባቢሎን በአንዳንድ ጉዳዮች ኃላፊነት እንደነበራቸው ተርክ። ንጉስ ናቡከደነፆር ህዝቦቹ የሚሰግዱለትን የወርቀ ምስል ሰራ። ናቡከነፆር ህዝቡ ሁሉ የሙዚቃ መሳሪያዎቹን ድምፅ በሰሙ ጊዜ ተደፍተው ለቆመው ለወርቁ ምስል እንዲሰግድ አዘዛቸው። ተደፍቶ የማይሰግድ ሰው በሚነድድ እቶን እሳት ውስጥ ይጣላል። ሲድራቅ፣ ሚሳቅ፣ እና አብድናጐን የወርቁ ምስል እግዚአብሔር እንዳልሆነ ያውቁ ነበር። ከአስርቱ ትዕዛዛት አንድ የሆነው ለሐሰተኛ አማልክት አትስገድ የሚለውን እንደሚከላከላቸው ያውቁ ነበር። ስለዚህ፣ ናቡከደነፆር ላቆመው የወርቀ ምስል አንሰግድም አሉ። ሶስቱ ወጣቶችም በጥበቃ ስር እንዲሆኑ ተደረገ። ምርጫ ተሰጣቸው። ለወርቁ ምስል አጐንብሰው እንዲሰግዱ ወይም በሚነደው እቶን እሳት አዲጣሉ። እነዚያ ሶስት ወጣቶች የራሳቸውን ውሳኔ አደረጉ ለንጉሱም እንዲህ አሉት “ንጉሥ ሆይ ባያድነን፣ አማልክህትህ እንደማናመልክ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንደማንሰግድለት እወቀ አሉት” (ዳንኤል 3፥18)። ናቡከደነጾር በጣም ተናደደ። የእቶንም እሳት ይነድድ ከነበረው ይልቅ እጥፍ እንዲያደርጉት አገልጋዮቹን አዘዘ። ሲድራቅንና ሚሳቅንም አብድናጐንም ታስረው ወደሚነደው እቶን እሳት እንዲጣሉ አዘዘ። የእቶኑም እሳት እጅግ ስለሚነድ የጣሉአቸውን ሰዎች የእሳቱ ወላፈን ገደላቸው። ናቡከደነፆር በእሳቱ መካከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች ጉዳት ሳይደርስባቸው በማየቱ ተደነቀ። ናቡከደነጾር በእሳቱ መካከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች ጉዳት ሳይደርስባቸው በማየቱ ተደነቀ። አራተኛውም መልአክ እንደነበር ግልጽ ነው። ፈፅሞ አልተጐዳም ነበር። የራሳቸውም ጠጉር እንዳልተቃጠለች፣ ልብሳቸውም የእሳቱ ሽታ እንዳልደረሰበት አየ። ናቡከነጾር የሲድራቅ፣ የሚሳቅንና የአብድናጐምና አምላክ አመሰገነ። ንጉሱም በወጣቶች አምላክ ላይ የስድብን ነገር የሚናገር ይገደላል ብሎ አዘዘ። ሦስቱም ወጣቶች ከንጉሱ ሹመትን ተቀበሉ። (ዳንኤል 3 ተመልከት።)

- በነዚህ በሶስቱ ወጣት ወንዶች ሥፍራ ብትሆን፣ ለወርቀማው ጣኦት አጐንብሰው መስገድ ለምን አስቸጋሪ ውሳኔ ይሆናል?
- ለጣኦቱ መስገድ ትክክለኛ ውሳኔ ነው የሚል ሐሳብ እንዴት ሊኖራቸው አልቻለም?
- እነዚያ ለመስገድ በመቃወማቸው አንተ ምን አሰብክ?

ኢያሱ የሙሴ ተተኪ እንደነበር ይህን አስረዳ፡፡ እንደ እስራኤል ልጆች መሪ፣ እያሱ ሕዝቦችን በሱ ዙሪያ አሰባሰበ እና ሊያደርጉአቸው የሚችሉአቸውን ምርጫዎች ተናገረ፡፡ ኢያሱ 24፥15 እና ይህ ቁጥር የታተመበትን ቻርት አሳይ።

በሚቀጥለው ሁኔታዎች ውስጥ ያደረጓቸው ምርጫዎች (ወይም ተመሳሳይ የራስህን አንድ ምርጫ) እንዴት በአሁኑ እና በወደፊቱ ህይወታቸው ሊነኳቸው እንደሚችሉ ከወጣት ወንዶቹ ጋር ተወያይ።

1. በትምህርት ቤትን ፈተና ማታለል፡፡

2. የሱቅ ሌብነት፡፡

3. በየቀኑ መጸለይ።

4. አስራትን መክፈል።

የሚከተለውን ምሳሌ አቅርብ

"በቤተክርስቲያን ውስጥ ቄሶች የሆኑ ሁለት ወጣት ወንዶች በአንድ ኩባኒያ ውስጥ ይሰራሉ፡፡ አለቃቸው ወደ ሥራ በሰንበት ቀን እንዲሄዱ ጋበዛቸው፡፡ ሁለቱም መሥራት ይወዳሉ፣ እናም ሁለቱም አቋማቸውን ከአለቃቸው ዘንድ ለማረጋገጥ ይፈልጋሉ፡፡ ሁለቱም በቤተክርስቲያን በሰንበት ቀን ኃላፊነት አለባቸው 'ከአንተ ጋር መሄዱ ያስደስተኛል' አለ አንዱ፣ ሌላኛውም አለ፣ አንድ ቀዳሚ ከአንተ ብሄድ እደሰት ነበር ነገር ግን እሁድ ለመሄድ ጥሩ ስሜት አይኖረኝም" (*የቤተሰብ የቤት ምሽት* መመሪያ፣ [*Family Home Evening Handout*] [1979-80] ገጽ 13)፡፡

• እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ሰው በምርጫው የግል ሕይወቱን? የመንፈሳዊ ህይወቱን? እና ቤተሰቡ ላይ እንዴት ተጽዕኖ ይኖረዋል?

ጥቅስ እና ውይይት

ቄስ ማርክ ኢ. ፒተርሰን እንዳሉት፣

"ይህ ሕይወት የምርጫ ግዜ ነው። ውሳኔዎቻችን በእኛ ህይወት ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ሕይወት ላይ ተፅእኖ አላቸው። ምርጫ አስቸጋሪ ነው፣ ምክንያቱም ማናቸውም ነገር የምርጫ ጉዳይ ነው" ("This Life Is a Time for Choosing," *Improvement Era*, የካቲት 1967, ገጽ 6)።

ምርጫው አስቸጋሪ ሊሆን ስለሚችል የሰማይ አባታችን እርዳታ እንደሰጠን ለወጣት ወንዶች ንገራቸው።

• መልካሙን ለመምረጥ ይረዳን ዘንድ የሰማይ አባታችን ምን ዓይነት ነገሮችን ነው የሰጠን? (ቅዱሳን መጽሐፍት፣ ወላጆች፣ ጸሎት፣ ከመንፈስ ቅዱስ የሚያነሳሳ መንፈስ፡፡)

ውሳኔዎቻችንን ከልብ ካጠናናቸው፣ በመንፈስ ብቁ ሆነን ከኖርን፣ እና ከመረመርን፣ የሰማይ አባታችን ይመራናል፣ እንዲሁም የህይወታችን መንፈሳዊ ብቃት እንደሚሻሻል አስረዳ።

ጥቅስ

ከፕሬዚዳንት እዝራ ታፍት ቢንሰን ጥቀሶች የሚከተሉትን አንብብ፣

"ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ወንድ እና ሴት ከህይወታቸው አብዛኛውን ለፈጣሪ እነርሱ ከሚችሉት የበለጠ ሊሰራላቸው ይችላል። እሱም የደስታቸውን ጥልቀ ሊያደርገው ይችላል፣ ራዕያቸውን ያጎለብታል አዕምሮአቸውን ሊያፈጥን፣ ጡንቻቸውን ያጠነክራል፣ መንፈሳቸውን ያነሳል፣ በረከታቸውንም ያበዛል፣ እድላቸውን የጨምራል፣ ለነፍሳቸው መጽናኛ፣ ጓደኞቻቸውን ያቀርባል፣ እናም ሰላምን ያስገኝላቸዋል፣ ማንኛውም ሕይወቱን ለእግዚአብሔር በማገልገል ውስጥ ከአጣ ዘለዓለማዊ ህይወትን ያገኛል" የዕዝራ ታፍት ቢንሰን ትምሕርት [The Teachings of Ezra Taft Benson] [ሶልት ሌክ ከተማ የመጽሐፍ ጥበብ፣ 1988]፣ ገጽ 36)፡፡

ታሪክ

ከሚከተለው ታሪክ ወጣቱ የኋለኛው ቀን ቅዱስ ማድረግ ስለነበረበት ምርጫዎች ክፍሉ እንዲያስብ አድርግ።

በአስራ እድሜ ውስጥ ያለው ዮሐንስ ጓደኞች እየጋለቡ ደርሰውበት ለግልቢያ ከእነርሱ ጋር እዲሄድ ሲጠየቁት በእሁድ ዕለት ለቁርባን ስብሰብ እየኼደ ነበር። ሞቀታማ በሆነው ቀን እና ከጓደኞቹ ጋር ለመጋለብ ያገኘው እድል ሳበው። ወላጆቹ በስብሰባው ላይ እንደሚገኝ ቢያስቡትም እንኳን ወደ ስብሰባው ለመሄድ አልፈለገም ነበር። ልጆቹ ስብሰባው ከማለቁ በፊት እንደሚመለሱ ቃል ገብተው ነበር። ወላጆቹ በጭራሽ እደሚያውቁ ለማሳመን ሞከረ።

ውይይት

የዮሐንስ ምርጫዎች ምን እንደነበሩ እና እያንዳንዱ የሚያስከትሉት ውጤቶች ምን ሊሆን እንደሚችል ወጣት ወንዶቹ እንዲወያዩበት ፍቀድላቸው።

ጥቂቶቹ ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎች—

• የዮሐንስ ውሳኔ ወደ ግልቢያ እንዲሄድ የጋበዙትን የእሱ ጓደኞች እንዴት ሊጐዳ ይችላል?

• ሰንበትን እንዴት ሊያከብር ይችላል?

• ውሳኔው ከቤተሰቡ ጋር ባለው ግንኙነት ላይ እንዴት ተፅእኖ ሊያደርግ ይችላል?

• ውሳኔው እንዴት መንፈሳዊ እድገቱን ሊጐዳው ይችላል?

• ዮሐንስን ብትሆን ኖሮ ምን ታደርጋለህን? ለምን?

ምርጫዎቻችን በሚያስከትሉት ውጤቶች ስለምናዝን ወይም ስለምንደሰት ሁል ጊዜ የእያንዳንዱን ውሳኔ ማብ እና ትክክለኛውን መምረጥ ይገባናል።

---

**ማጠቃለያ**

ጥቅስ

በቁስ ቦይድ ኬ ፓከር የተሰጠውን የሚከተለውን መግለጫ አንብብ፣

“ወደዚህ ሚች ሕይወት የመጣነው አካልን ለመቀበል እና ለመፈተን፣ መምርጥን ለመማር ነው፡፡

“የሕይወት ምርጫ በዝና እና በውድቀት መሀከል አይደለም፣ ምርጫችንም በሀብት እና በድህነት መሃከል ያለ ምርጫም አይደለም፡፡ ምርጫ በክፋት እና በመልካም መሃል ነው፣ በእርግጥ ያ በጣም የተለየ ነገር ነው፡፡

“በመጨረሻ ይህንን ትምህርት በሚገባ በምንረዳበት፣ ከዚያም ጊዜ ደስታችን ቁሳዊ ነገሮች አይወስንም ምናልባትም ያለ እነርሱ መደሰት እንድምንችል ወይም መልካም ውጤት ልናገኝ እንችላለን . . .

“ሕይወታችን በየቀኑ በሺህ ምርጫዎች የተሰሩ ናቸው። እነዚህ ጥቃቅን ምርጫዎች ከዓመታት በላይ በአንድነት ቢታሰሩ እና በግልጽ ምን ዋጋ እንዳላቸው ያሳያል፡፡

“ቁርጠኛ የህይወት ፈተና፣ እደግመዋለሁ፣ ምርጫው በዝና እና በውድቀት መኻል፣ በሀብት እና በድህነት መሃከል ያማከለ አይደለም፡፡ ታላቁ የህይወት ውሳኔ በመልካምነት እና በክፋት መካከል ነው፡፡” (በ Conference Report, ጥቅምት 1980 ከገጽ 28-29 ወይም Ensign ህዳር 1980 ገጽ 21)።

መጽሐፍ ቅዱስ

በሰንጠረዥ ላይ ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንደገና አንብብ፣ “የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ፣— እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን” (እያሱ 24፡15)

መዝሙር

ክፍሉ ወይም አንድ ሰው “ትክክለኛውን ምረጥ” የሚለውን መዝሙር እዲዘምሩ አድርግ (*መዝሙር* ቁጥር 239)፣ ወይም ከወጣቶቹ አንድ ቃላቶቹን እንደ ግጥም እንዲያነብ አድርግ።

# 21 ንጹህ አስተሳሰብ፤ ግልጽ ቋንቋ

**ዓላማው**

እያንዳንዱ ወጣት ንጹህ አስተሳሰብ ማግኘት እና የሚያንፁ ቋንቋዎችን የመጠቀምን አስፈላጊነት በይበልጥ ይረዳዋል።

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለየአንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት
   ለ. ለእያንዳንዱ ወጣት አንድ አነስተኛ ነጭ ወይንም ቀለሙ ያልደመቀ ቁራጭ የልብስ ጨርቅ።
   ሐ. ከቁሳዊ ትምህርት በኋላ ለማጽጃነት የሚያገለግል እርጥብ ጨርቅ።
   መ. ለእያንዳንዱ ወጣት እርሳስ።
2. በሥዕላዊ መግለጫ የሚከተለውን አዘጋጅ፣ "አዕምሮአችን፣ እንደቀለም ቀቢ እጅ በያዘው ነገር ይቀለማል"
3. በአንድ ትንሽ ጐድጓዳ ሳህን የተፈጨ እንጆሪ፣ ጭማቂ፣ ወይም ነጣ ያለውን ትንሽ ቁራጭ ጨርቅ ሊያቀልመው የሚችል አንድ ተመሳሳይ ነገር አዘጋጅ።
4. ለእያንዳንዱ ወጣት "የመጽሐፍ ቅዱስ መልመጃ" የሚለውን በእጅ የተዘጋጀ ጽሑፍ ቅጂ አዘጋጅ ወይም ወጣት ወንዶች በቡድን እንዲሰሩት አጠር ያለች የማነቃቂያ ጥያቄን በትልቀ ፖስተር ላይ ጻፍላቸው።
5. *ለወጣቶች ጥንካሬ* በገጽ 14 እና 15 ላይ ስለ ቋንቋ የተሰጠውን ምክር ከልስ።

**ለአስተማሪው ማስታወሻ**

ንጹህ አስተሳሰቦች ንጹህ ለሆኑ ተግባሮች አስፈላጊ ናቸው፡፡ የዘመኑ የብዙሃን መገናኛ ምስሎች እና ቋንቋ በወጣት ወንዶች ህይወት ውስጥ የሚኖራቸው ተፅእኖ ከባድ የጥፋት ጠንቅ ሊሆን ይችላል። የአሮናዊ ክህነት ስልጣን መሪዎች ወጣት ወንዶች ንጹህ እና ጽድቀ የሆነ ህይወትን እንዲመርጡ በመምራት ታላቀ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሣብ**

**በምንጠቀመው ቋንቋ እራሳችንን እንገልጻለን**

**ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት**

የሚከተሉትን ንግግሮች በጥቁር ሰሌዳው ላይ ጻፍ፣

"ቋንቋ የአስተሳሰብ ልብስ ነው፣ በምትናገርበት ጊዜ ሁሉ አዕምሮህ በከባድ እንቅስቃሴ ላይ (ባልታወቀ ደራሲ, *Richard Evans' Quote Book*, comp. Richard L. Evans [ሶልት ሌክ ከተማ: Publishers Press, 194)።

• ይህ አነጋገር ምን ማለት ነው? (እኛ ስንናገር፣ ብዙ ግዜ ሌሎች ሰዎች ስለምናስበው እናም ምን ዓይነት ሰዎች እንደሆንን ይነግሩናል፡፡ እኛ ባለማቋረጥ ጥሩ አስተሳሰባችን ለማሰብ እና ንጹህ ንግግሮችን በመጠቀም መምከር አለብን፡፡)

**ተሳትፎ**

ከዚህ በፊት የተዘጋጁትን "የመጽሐፍ ቅዱስ መልመጃ" የሚሉትን ቅጂዎች አሰራጭ እና እርሳስ ለወጣት ወንዶች አዘጋጅ ወይም ያዘጋጀኸውን ትልቁን የማነቃቂያ ጥያቄ ያለውን ፖስተር አሳይ። ይህን ጥያቄ በክፍል ውስጥ አብረህ ባዶ ቦታውን በመሙላት፣ ወጣቶቹን ማሰራት አለብህ ያለበለዚያ እራስህ ሥራ ወይም እያንዳንዱ ወጣት በግል እንዲሰራ ፍቀደለት። ወጣት ወንዶቹን ከያዕቆብ መልዕክት 3፡2–13 በመጠቀም በክፍት ቦታው እንዲሞሉ ጠይቃቸው፡፡ የዚህ መልመጃ ዓላማ ወጣት ወንዶች ምዕራፎቹን እንዲያገናዝቡ ለመርዳት እንጂ፣ ትክክለኛውን ቃል እንዲፈልጉ ለማስገደድ አይደለም፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ መልመጃ

በሚከተሉት ክፍት ቦታዎች ውስጥ ለመሙላት እንዲረዳህ የያዕቆብ መልዕክት 3፡2–13 ተጠቀም።

1. አንድ ሰው የሚናገረውን <u>ቃላቶች</u> መቆጣጠር ከቻለ፣ መላ አካላቱን የመቆጠጣር ችሎታ ይኖረዋል። (ቁጥር 2)
2. የፈረስ አካል በአፉ ውስጥ ባለች ትንሽ <u>ልጓም</u> መቆጣጠር ይቻላል (ቁጥር 3)

3. በባህር ውስጥ ትልቅ መርከብ በኃይለኛ ነፋስ ቢነዳም እንኳን፣ በጣም ትንሽ የመርከብ መሪ በማናቸውም አቀጣጫ ይመራዋል። (ቁጥር 4)

4. የእኛ ምላስ ከፈረስ ልጓም እናም ከመርከብ መሪ ጋር የሚወዳደር ነው ሊነፃጸር ይችላል ምክንያቱም በመላው አካላታችንን ላይ ተጽዕኖን ያደርጋል። (ቁጥሮች 5–6)

5. ሰው ማናቸውንም እንስሳ መግራት ይችላል፣ ነገር ግን እራሱ በጣም ከሚቸገርባቸው ነገሮች አንዱ የራሱን ምላስ መግራት ነው። (7–8 ቁጥሮች)

6. አንዳንድ ሰዎች ምላሳቸውን እግዚአብሔርን ለማመስገን እንዲሁም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን ሰውን ለመርገም ይጠቀማሉ። (ቁጥር 9)

7. በረከት እና እርግማን ሁለቱም ከአንድ አፍ መውጣት አይገባቸውም። (ቁጥር 10)

8. ጣፋጭ እና መራር ውኃ ከአንድ ምንጭ አይገኙም። (ቁጥር 11)

9. ጥበበኛ ከሆንን፣ በመልካም ንግግራችን ውስጥ ልናሳየው እንችላለን። (ቁጥር 13)

በዚህ ምዕራፍ የመልዕክት ይዘት ውስጥ ያለውን ጥቀም ለመወያየት ጥቂት ደቂቃዎችን አሳልፍ። ወጣት ወንዶቹ ጥቀሶችን ምልክት እንዲያደርጉባቸው አስተያየት ስጥ።

የማሰላሰያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን የማሰላሰያ ጥያቄዎች በምትገልጽበት ጊዜ ወጣት ወንዶች በጣም የሚያከብሩትን እና የሚያደንቁትን—ለህይወታቸው ምሳሌ ሊያደርጉ የሚፈልጉትን—የቤተክርስቲያን አባል ምስል በአዕምሮአቸው እንዲቀርጹት አድርጋቸው፣

- ይህ ሰው እንዴት ይናገራል?
- የእርሱ ወይም የእርሷ ንግግር በሌሎች ላይ ምን ዓይነት ተጽእኖ አለው?
- እርሱ ወይም እሷ የቀሸሸ እና የብልግና ቋንቋ ቢጠቀሙ አንተ ስለዚያ ሰው ወይንም ስለዚያች ሴት እንደ ቀድሞው ተመሳሳይ የሆነ ስሜት ይሰማኻልን?

ሰለምናደንቀው ሰው በምናስብበት ጊዜ ምን አይነት ሰው መሆን እንደምንፈልግ አሁን መወሰን እንችላለን እናም ልክ እንደዚያ ሰው እናደርጋለን። ይህንን በማድረግ ፣አይነተኛ አርአያ መሆን እንችላለን።

- ቋንቋህ ስለ አንተ ምን ይገልጻል?
- እንደ እግዚአብሔር ልጅ ለመናገር እና ለማሰብ ተሞክራለህን?

---

**ንፁህ አስተሳሰቦች መልካም አባባልን ይከተላል**

በቁሳዊ የተደገፈ ትምህርት እና ፖስተር

ጉድጓዳ ሳህን ጭማቂ (ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ፈሳሾችን አሳይ)። በጭማቂው ትንሽ ቁራጭ ልብስ እንዲያቀልሙ ወጣት ወንዶችን ጋብዝ፣ እነዚህ ጭማቂዎች ልብሶቻቸውን እንዳይነኩ ጥንቃቄ ያድርጉ። ይህንን ካደረጉ በኋላ ወደ እጆቻቸው እንዲመለከቱ ጠይቃቸው። ምናልባት ጥቂት ጭማቂዎች እጃቸው ላይ ይኖራቸዋል። እጆቻቸውን እንዲያጸዱበት የረጠበ ጨርቅ ስጣቸው።

“አዕምሮአችን እንደ ቀለም ቀቢ እጅ በያዘው ነገር ይቀለማል” የሚለውን ማስታወቂያ አሳይ፣

“ወጣት ወንዶች ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ በመመለስ ላይ እያሉ ስለ አባባሉ እንዲያስቡ ጠይቃቸው፣

- ባትሰርቁም እንኳን መስረቀ ቀላል ነው ብላችሁ ማሰብ ለምን ጉጅ ሊሆን ይችላል?
- ለማንም ሰው ሐሳባችሁን ባትናገሩም እንኳ ስለ አንድ ሰው መልካም አለማሰብ እና ክፋን ማሰብ ጉጅ ሊሆን የሚችለው ለምንድ ነው?

በማስታወቂያው ላይ ያለውን ጥቀስ በድጋሚ አንብብ።

- በዚህ መንገድ ማሰቡ አዕምሮአቹን ሊያቀሽሽ ይችላልን?

ጥቀስ እና ውይይት

የሚከተለውን መግለጫ አንብብ፣

“ጨዋ እና የእግዚአብሔርን የመሰለ ጠባይ—በቀና አስተሳሰብ የሚመጣ የተከታታይ ጥረት ተፈጥሮአዊ ውጤት ነው። (James Allen, *As a Man Thinketh* [New York፡ Thomas Y. Crowell Company, n.d], ከገጽ 7–8)።

አስተሳሰባችንን ለመቆጣጠር ትልቅ ጥረትን እንደሚጠይቀ አበክረህ ተናገር። ነገር ግን እኛ የክርስቶስ እውነተኛ ተከታዮች ለመሆን ከፈለግን አስተሳሰባችንን ንጹህ ለማድረግ ማናቸውንም ጥረት ማድረግ አለብን።

- በንግግራችን እና በአስተሳሰባችን ላይ ተፅዕኖን የሚያደርጉ ጥቂት ነገሮች ምንድን ናቸው? (ጓደኞች፣ ፊልሞች፣ መጽሔቶች፣ ቀልዶች፣ ቀናት፣ ራስ ወዳድነት ናቸው።)

ለጥሩ ወይም ለመጥፎ እንዴት እነዚህ እያንዳንዳቸው በህይወታችን ላይ ተፅዕኖን እንደሚያደርጉ ተወያይበት።

**ሐሳባችንን ለመቆጣጠር መለማመድ ያስፈልገናል**

ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት

• አስተሳሰባችንን መቆጣጠር የምንችልበት ጥቂቶች መንገዶች ምንድን ናቸው?

ወጣት ወንዶች እንዲመልሱ ፍቀድላቸው፡፡ መልሳቸውን የሚከተሉትን ትምህርቶች በማጠቃለል በጠመኔ ሰሌዳ ላይ ይመዝግቡ፥

1. የእኛን ሐሳቦች እና ንግግር ለመግዛት እንዲረዳን በቅንነት ለሰማይ አባታችን ጸልዩ፡፡
2. ስለ አዳኛችሁ አስቡ እንዲሁም አስተሳሰቦቻችን እና ንግግሮቻችን የነጹ እና የሚያስከብሩ እንዲሀሆኑ ህይወታችሁን በእርሱ ምሳሌ ላይ መስርቱ።
3. የምትወዷቸውን መዝሙሮች ውሰዱ እና በመጥፎ አስተሳሰብ በመተካት ተጠቀሙ፡፡
4. በአስተሳሰቦች እና በንግግርህ ላይ ጥሩ ስሜት ያላቸውን ጓደኞችህን መምራት ትችላለህ፡፡
5. እንደ ቴሌቪዥን መስኮት አዕምሮአችንን በአይነ ህሊና እንይ፡፡ እርኩስ መንፈስ ሲገባባቸው የአዕምሮው ጣቢያዎች በመለወጥ የሚያነቃቃ አንድ ነገር አስቡ፡፡
6. ልዩ ትርጉም የሚሰጥህን አንድ የምትወደው ቅዱስ መጽሐፍ ጥቅስ ውሰድ፡፡ ይህንንም አንብብ፡፡ በምታስበው ወጥመድ ወደ አዕምሮአችን እርኩሰት ሲገባ አስተሳሰቡ እስኪተውህ ከቅዱስ መጽሐፍት ደጋግመህ ጥቅሶችን አንብብ፡፡

---

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት እና ስሜትን ማነሳሳት

በ14 እና 15 ገጾች ላይ ስለ ቋንቋ የተሰጠውን ምክር ለወጣቶች ጥንካሬ ላይ ከልስ፡፡ አስተሳሰባችንን እና ንግግራችንን ስለ መቆጣጠር ጥቅም ምስክርነትህን ስጥ፡፡ በወጣቱ ወንዶች ችሎታ ውስጥ በእራስ መተማመንን በአዕምሮአቸው እንዲቆጣጠሩ ግለጽላቸው፡፡ አስተሳሰባቸውን መንገድ ለመቆጣጠር እንዲመርጡ ስሚታቸው ማነሳሳት የተሻለ መሥራት እንዲችሉ እና የሚመጣው ሳምንት ለልምምድ ይጠቀሙበት፡፡

---

# የመጽሐፍ ቅዱስ መልመጃ፡፡

የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በመሙላት ውስጥ አንተን እንዲረዳህ የያዕቀብ መልዕክት ም 3፥2–13 ተጠቀም፡፡

1. አንድ ሰው የሚናገረውን______________ መቆጣጠር ከቻለ፤ መላአካላቱን መቆጣጠር ችሎታ ይኖረዋል። (ቁጥር 2)
2. የፈረስ አካል በአፉ ውስጥ ባለች ትንሽ______________ መቆጣጠር ይቻላል። (ቁጥር 3)
3. በባህር ውስጥ ትልቅ መርከብ በኃይለኛ ንፋስ ቢነዳም እንኳን በጣም ትንሽ______________ በማናቸውም አቀጣጫ ይመራዋል። (ቁጥር 4)
4. የእኛ______________ ከፈረሱ ልጓም እና ከመርበቡ መሪ ሊወዳደር እና ሊነፃፀር ይችላል ምክንያቱም በመላው አካላታችን ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል እና። (ቁጥሮች 5-6)
5. ሰው ማናቸውንም እንስሳ መግራት ይችላል፣ ነገር ግንእራሱ በጣም ከሚቸገርባቸው ነገሮች አንዱ የራሱን ______________ መግራት ነው (7-8 ቁጥሮች)
6. አንድ አንድ ሰዎች ምላሳቸውን እግዚአብሔርን______________ እንዲሁም በእግዚአብሔር ሀምሳል የጽፈጠረውን ሰው______________ ይጠቀማሉ። (ቁጥር 9)
7. መባረክ እና እርግማን ሁለቱም ከአንድ______________ መውጣት አይገባቸውም (ቁጥር 10)
8. ሁለቱም______________ እና ______________ ውኃ ከአንድ ምንጭ አይገኙም፡፡ (ቁጥር 13)
9. ጥበበኛ ከሆንን በመልካም______________ ውስጥ ልናሳየው እንችላለን (ቁጥር 13)

# ቃል ኪዳኖች ድርጊቶቻችንን ይመራሉ

# 22

**ዓላማው** 

እያንዳንዱ ወጣት የገባቸውን ቃል ኪዳኖች ለመጠበቅ ይጥራል እንዲሁም አድራጉቱን በዘለዓለማዊ ህይወት መንገድ ላይ ለመምራት ይጠቀምባቸዋል።

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለየአንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. ጥቀሶችን ምልክት ማድረጊያ እርሳሶች።
2. የሚከተሉትን የቅዱስ መጽሐፍት ጥቀሶች ማጣቀሻን አዘጋጅ፣ 1ኔፊ 11፥21–22፣ 1ኔፊ 12፥16፣ 1ኔፊ 11፥25፣ 1ኔፊ 12፥17፣ 1ኔፊ 11፥36፣ እና 2ኔፊ 31፥18።
3. በጥቁር ሰሌዳው ላይ የሌሂን ህልም ምሣሌ በመሳል ተለማመድ (ትምህርቱን ተመልከት)
4. የሌሂን ህልም ተዘጋጅቶ እንዲያነብ አንድ ጥሩ አንባቢ ወጣት ጠይቅ፣ 1ኔፊ 8፥2፣ 5–13፣ 19–28።
5. በ 1ኔፊ 8 የሚገኘውን የሌሂን ህልም ታሪክ አጥና። እንዲሁም አንዳንድ አዛማጅ ማጣቀሻዎችንም ማንበብ ትችላለህ።
6. ወጣት ወንዶቹ ቃል ኪዳኖችን ከጌታ ጋር እንዲያደርጉ እና እንዲጠበቁ ለማስተማር ይህ ትምህርት መሰረታዊ የቅዱሳን መጻሕፍት ጥቀሶች ማጣቀሻዎችን ያዘጋጃል። በክልልህ የሚገኙትን የቪዲዮ ወይም የኦዲዮ እርዳታዎችን መጠቀም ትችላለህ። *የቤተሰብ የቤት ምሽት የቪዲዮ ማሚያ* (53276) "ጥምቀት—ኢየሱስን ለመከተል ቃል ኪዳን" የሚለውን በጣም ጥሩ ምርጫ ሊሆን ይችላል።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**መግቢያ**

ጥቅስ እና ውይይት

• የሰማይ አባት ሊሰጠን ካሉት ውስጥ ታላቁ ስጦታ ምንድን ነው?

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት አንድ ወጣት ትምህርት እና ቃልኪዳን 14፥7ን እንዲያነብ አድርግ። ይህን ቁጥር ምልክት እንዲያደርጉበት ወጣት ወንዶቹን አሳስቧቸው።


ከክርስቶስ ልደት ከስድስት መቶ ዓመት በፊት፣ ሌሂ እንዴት ዘለዓለማዊ ህይወትን እንደምናገኝ የሚነግረንን ድንቅ ህልም ተመለከተ።

ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት

ከዚህ በፊት የተመደበውን ወጣት 1ኔፊ 8፥2፣ 5–13፣ 19–23ን እንዲያነብ አድርግ። በማንበብ ላይም እያለ፣ የሚከተለውን የጥቁር ሰሌዳ ገለፃ አዳብር። ወጣት ወንዶቹ በጠቃሚ ምንባቦች ላይ ምልክትን እንዲያደርጉ አበረታታቸው።

በሚከተለው ቀደም ተከተል የሌሂን ህልም በጥቁር ሰሌዳው ላይ ሳል።

1. ዛፍ
2. የወንዝ ውኃ
3. የብረት ዘንግ
4. ቀጭኑ እና ጠባቡ መንገድ
5. የጨለማ ጭጋግ
6. ታላቁ እና ሰፊው ሕንፃ
7. ብዙ ሰዎች—ጥቂቶቹ በመንገዱ ላይ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ ከመንገድ ውጭ



የቅዱሳን መጽሐፍት እና ውይይት

እያንዳንዱ የሊሂ ህልም የሚገልጸው ምን እንደሆነ ለማወቅ፣ የሚከተሉትን የቅዱሳን መጻሕፍት ጥቀስ ማጣቀሻዎችን አድል። እያንዳንዱ ወጣት ወንድ የእራሱን ጥቀሱ እንዲመለከት እና የሊሂ ህልም ምንን እንደሚወክል ተዘጋጅቶ እንዲናገር አድርግ።

1. 1 ኔፊ 11፥21–22 (ዛፉ እና ፍሬው የእግዚአብሔርን ፍቅር ወይም ዘለዓለማዊ ህይወትን ይገልፃሉ።)
2. 1ኔፊ 12፥16 (ወንዙ የሲኦልን ጥልቀት ይወክላል።)
3. የ 1ኔፊይ 11፥25 የመጀመሪያ ግማሽ (የብረት ዘንጉ የእግዚብሔር ቃል ነው።)
4. 2 ኔፊ 31፥18 (ቀጭኑ እና ጠባቡ መንገድ የዘለዓለማዊ ህይወት መንገድ ነው።)
5. 1 ኔፊ 12፥17 (የጨለማው ጭጋግ የዲያቢሎስ ፈተናዎች ናቸው።)
6. የ1 ኔፊ 11፥36 የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር (ታላቁ እና ሰፊው ህንፃ የዓለም ኩራት እና ከንቱነት ነው።)

---

**እያንዳንዱ ወጣት የተቀደሱ ቃል ኪዳኖች አድርጓል**

ቅዱስ መፃህፍት፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ውይይት

እንደ ክርስቶስ ደቀመዛሙርትነታችን ከፍተኛ ኃላፊነት እንዲሁም ትልቅ ችሎታ አለን። እንደተወያየነው፣ ሊሂ የሰማይ አባትን መምሰል ስለ መቻላችን ሂደት እና ዘለዓለማዊ ህይወት ማግኛችንን ቀጭኑን መንገድ ተመልክቷል።

ወደ ህይወት ዛፍ የሚመራውን መንገድ እንዴት እንደምንከተል ለማንበብ፣ አንድን ወጣት ወንድ 2 ኔፊ 31፥17–18ን እንዲያነብ አድርግ።

• አንድ ሰው እንዴት በቀጭኑ እና በጠባቡ መንገድ ይገባል? (በንስኃ እና በመጠመቅ።)

በምንጠመቅበት ጊዜ፣ ከሰማይ አባታችን ጋር ቃል ኪዳን እንደምንገባ ግለጽ። አንዳንድ ነገሮችን የምንሰራ ከሆነ የዛፉ ፍሬ ተካፋዮች እንደምንሆን እና የዘለዓለም ህይወትን እንደምንቀበል ቃል ኪዳን ገብተልናል።

በዘላለማዊ የህይወት መንገድ ላይ እንድንቀይ የገባናቸውን ቃል ኪዳኖች ወጣት ወንዶቹ እንዲማሩ ለመርዳት ሞሮናይ 4፥3 እና ሞዛያ 18፥18–10 እንዲያነቡ አድርግ።

• በተጠመቅን ጊዜ ለመፈጸም የገባነው ቃል ምንድነው? የሚከተሉትን ነጥቦች በጥቁር ሰሌዳው ላይ ዘርዝር፣ (1) የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በላያችን ላይ ለመውሰድ (2) ዘወትር ኢየሱስ ክርስቶስን ለማስታወስ፣ (3) ትዕዛዛቶቹን ለመጠበቅ (4) የሌሎችን ሸክም ለመሸከም፣ (5) ከሌሎች ጋር ለማዘን፣ (6) ማጽናናትን መስጠት፣ (7) የእግዚአብሔር ምስክሮች በመሆን ለመቆም።

እንዴት ሊፈፅሟቸው እንዲሚችሉ ወጣት ወንዶቹን በመርዳት የእነዚህን ቃል ኪዳኖች ትርጉም ተወያዩባቸው። በገባናቸው በእነዚህ ቃል ኪዳኖች ሁሉ ክርስቶስን እና ትምህርቱን የህይወታችን ማዕከል ማድረግ እንደሚገባ ትኩረት ስጥ።

• እነዚህን ቃል ኪዳኖች ከጠበቅን፣ የሰማይ አባት ሊሰጠን የገባልን ቃል ኪዳን ምንድን ነው? (መንፈሱን—መንፈስ ቅዱስን።)

• የዘላለምን ህይወትን ለማግኘት መንፈስ ቅዱስ እንዴት ይረዳናል? (በቀጥተኛው እና በጠባቡ መንገድ እንድቆይ መንፈስ ቅዱስ ይመራናል እናም ይረዳናል።)

---

**ተጨማሪ ቃል ኪዳኖች ለዘላለማዊ ህይወት አስፈላጊዎች ናቸው**

ውይይት

በዕድሜ እየገፉን በሄድን ቁጥር ዘለዓለማዊ ህይወትን ለመቀበል አስፈላጊ የሆኑን ተጨማሪ ቃል ኪዳኖች ለማድረግ ዕድል እንደተሰጠን አብራራ።

• እነዚህ ሌሎች ቃል ኪዳኖች ምንድን ናቸው? (የክህነት ስልጣንን መቀበል፣ የቤተ-መቅደስ ስጦታዎቻችንን መቀበል፣ እና በቤተመቀደስ ጋብቻን መፈጸም።)

ከእግዚአብሔር ጋር ያደረግነው እያንዳንዱ ቃል ወይም ቃል ኪዳን በቀጭኑ እና በጠባቡ መንገድ እንድንቀይ ይረዳናል በዚህም የሰማይ አባትን ለመምሰል እና ዘለዓለማዊ ህይወት ለማግኘት እንችላለን።

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

ጌታ ስለ ቃል ኪዳኖች ምን እንዳለ ለማወቅ፣ አንድ ወጣት ትምህርት እና ቃልኪዳን 82፥10ን እንዲያነብ አድርግ።

• *አጣመረ* የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?

• ጌታ የእራሱን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ የማይጣመርበት ጊዜ መቼ ነው?

• ጌታ ቃል የተገባልንን በረከቶች ይሰጠን ዘንድ ሊጣመር የወሰነው ለምን ያህል ጊዜ ነው?

• የዘላለማዊ ህይወት በረከቶችን ለመቀበል ምን ማድረግ አለብን? (የጌታን ትዕዛዛቶች መጠበቅ።)

---

**ማጠቃለያ**

ጥቅስ

ወጣት ወንዶቹ መዝሙር 89፥34ን እንዲያነቡ ድርጋቸው። የእኛን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ ተመሳሳይ ኃላፊነት እንዳለብን አብክረህ አስረዳ። ፍጹማን ባንሆንም እንኳን፣ ምንጊዜም ለጌታ የገባነውን ቃል ኪዳን በታማኝነት ለመጠበቅ መጣር እንዳለብን አስረዳ።

ሙከራ

ወጣት ወንዶች ለቃል ኪዳኖቻቸው በተቻላቸው መጠን እውነተኞች ለመሆን በሏቸው ችሎታዎች ላይ በራስ መተማመንን ግለጽላቸው። ከታላቅ ሙከራቸው ውስጥ እንዱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆናቸውን እና እንደ እርሱ የመሆን ኃይል ያላቸው መሆኑን ዘወትር ማስታወስ እንደሆነ ግለጽ።

በጥምቀት ጊዜ የገቧቸውን ቃል ኪዳኖች በበለጠ እንዲገነዘቡ ይረዳቸው ዘንድ የሰማይ አባትን እንዲጠይቁ እና በክህነት በሚቀዩበት ጊዜ ወደ ፊት ያሉትን ቃል ኪዳኖች ለማሟላት ብቁ ሆነው እንዲኖሩ ለመወሰን እና በቤተመቀደስ ስጦታቸውን እንዲቀበሉ ወጣት ወንዶችን አበረታታ።

# 23 ለአመራር መጸለይ

**ዓላማው**

እያንዳንዱ ወጣት ወንድ የሰማይ አባቱን ምሪት እንዴት እንደሚሻ እና እንደሚያውቅ ይማራል።

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለየአንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. ጥቀሶችን ማስመሪያ እርሳሶች።
2. ቢያንስ ከዚህ ትምህርት አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ፣ በቡንዲ እና በማት መካከል የተደረገውን የሚና ጨዋታ ሁለት ወይንም ሶስት ጊዜ እንዲያነቡት እና በትምህርቱም ወቀት ለማቀረብ እንዲዘጋጁ ሁለት ወጣት ወንዶችን ጠይቀ።
3. "የመጀመሪያው ራዕይ፣" *On Moments from Church History* (53145), በአቀራቢያህ የሚገኝ ከሆነ የቪዲዮ ካስት ይኑርህ። የማይገኝ ከሆነም፣ Joseph Smith —History 1፣5–20 ክልስ።

**ለትምህርት እድገት የቀረበ ሐሳብ**

**ጌታ መመሪያን እንዴት እንደምንቀበል ነግሮናል**

*ውይይት*

• በእናንተ እድሜ ውስጥ ያሉ ወጣት ወንዶች ሊያደርጓቸው የሚችሏቸው አንዳንድ አስቸጋሪ ውሳኔዎች ምንድናቸው?

• በመደበኛ ቀን ሥራዎች ውስጥ ማድረግ የሚገባችሁ አንዳንድ ውሳኔዎች ምንድናቸው?

ሀሳባቸውን ይሰጡበት ዘንድ ሁሉንም ወጣት ወንዶች አበረታታ።

*ቅዱሳን መጽሐፍት፣ የጥቁር ሰሌዳ፣ እና ውይይት*

ወጣት ወንዶች በቅዱሳን መጸሐፍቶቻቸው ውስጥ የሚከተሉትን ጥቀሶች እንዲጠቁሙ አድርግ። የተለያዩ ወጣት ወንዶችን በመጥራት ከፍ ባለ ድምፅ እያንዳንዱን ጥቀስ እንዲያነቡ አድርግ፡፡ እያንዳንዱ ጥቀስ በሚነበብበት ጊዜ፣ ሌሎች ወጣት ወንዶች እንዲያዳምጡ እና ጥቀሱ ምን እንደሚል ለመናገር እንዲዘጋጁ ጠይቃቸው። በእያንዳንዱ ጥቀስ በስተቀኝ በኩል ቁልፍ የሆኑ ቃላትን ወይም ዓረፍተ ነገሮችን ፃፍ። ወጣት ወንዶቹ ለእነርሱ አስፈላጊ በሆኑት ዓረፍተ ነገሮች ላይ ማስመር ይችላሉ።

1. ትምህርት እና ቃል ኪዳን 112፣10—ለጸሎቶቻችሁ መልስን ለማግኘት "ትሁት ሁኑ"።
2. 1ኛ ኔፊ 17፣45— "ዝግ ባለ ድምፅ . . . እርሱ ተናግሯል፣ ነገር ግን እናንተ ስሜት አልነበራችሁም [እናም] ቃሉ ሊሰማችሁ አልቻለም።"
3. ዮሐንስ ራዕይ 3፣20—"እነሆ በደጅ ቆሚ አንኳኳለሁ።"
4. ሞሮናይ 10፣3–5—"በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካይነት።"
5. ትምሕርት እና ቃል ኪዳን 9፣7–9 "በአዕምሮአችሁ ውስጥ አጥኑት፣ ከዚያም እውነት እንደሆነ እኔን ልትጠይቁ ይገባል።"

• ትክክለኛ ውሳኔን በመወሰን ለመመራት እንዴት እንደምንጸልይ እንድናውቅ እነዚህ ጥቀሶች የሚረዱን እንዴት ነው?

የሰማይ አባት እንደሚወደን እና መመሪያውን ከተከተልን ህይወታችን የበለጠ የደስታ እና ውጤታማ እንደሚሆን እንደሚያውቀ ግለፅ። ወደ ሰማዩ አባት ከጸለይን፣ ውሳኔዎቻችን ትክክል ስለ መሆናቸው እንደናውቀ ይረዳናል። በመንፈስህ ቅዱስ አማካኝነት በዚህ ዕውቀት ይባርከናል።

**የጸሎታችንን መልሶች ማዳመጥና ማገናዘብን መማር አለብን**

*የቪዲዮ ካሴት*

በአካባቢዎ የሚገኝ ከሆነ፣ *On Moments from Church History*, ከሚለው ላይ "የመጀመሪያው ራዕይ" የሚለውን የቪዲዮ ካሴት አሳይ። ቪዲዮው የማይገኝ ከሆነ፣ በራስህ አባባል የዮሴፍ ስሚዝን የመጀመሪያ ራዕይ ታሪክ ተናገር። እግዚአብሔር ጸሎትን እንደሚሰማ እና እንደሚመልስ ለወጣት ወንዶቹ ግለጽላቸው። በሰማይ መልዕክተኞች መጐብኘትን ሊያገኙ ይችላሉ፣ ነገር ግን የመንፈስ ድምፅ በጥንቃቄ የሚያዳምጡ ከሆነ፣ ጸሎቶቻቸው መቼ እንደተመለሱ ያውቃሉ።

ውይይት

• ከተዘረዘሩት ዝርዝሮች ውስጥ የዮሴፍስሚዝን ልምድ የሚገልፀው ጥቅስ የትኛው ነው? (ት እና ቃ 112፥10።)

ይህን ማጣቀሻ በጥቁር ሰሌዳው ላይ አስምርበት።

ጥቅስ

• እግዚአብሔር ጸሎትህን እንደመለሰልህ እንዴት ማወቅ ትችላለህ?

ጳጳስ ኤች ቡርክ ፒተርሰን ለጸሎት መልስን ስለ መሻት ይህን ጠቃሚ ምክር እንደሰጡ ለወጣት ወንዶች ንገራቸው፥

"ማዳመጥ የጸሎት አስፈላፍጊው ክፍል ነው። መልሶች ከጌታ የሚመጡት በፀጥታ—ሁል ጊዜ በፀጥታ ነው። በርግጥ፣ ጥቂቶች መልሱን በጉልህ በጆሮአቸው ይሰሙታል። በጥንቃቄ ማዳመጥ አለብን አለዚያ በፍጹም አንገነዘባቸውም። ከጌታ የሚመጡ መልሶች አብዛኞቹ በልባችን እንደሞቃት ማጽናኛ አገላለጽ ሊሰሙን፣ ወይም እንደ ሀሳብ በአዕምሯችን ሊመጡ ይችላሉ። የሚመጡት ለተዘጋጁት እና ለትዕግስተኞች ሰዎች ነው" (በ Conference Report, ጥቅምት 1973, ገጽ 13; or *Ensign*, ታህሳስ 1974, ገጽ 19)።

የሚና ጨዋታ

አስቀድመው የተመደቡት ወጣት ወንዶች የሚከተለውን ድራማ እንዲያቀቡ አድርግ። እርስ በርሳቸው በስልክ እየተነጋገሩ ነው።

አንዲ፣ (በፍጥነት በማውራት) ማት፣ ቡድናችን ለሚቀጥለው ወር ያቀደውን ያንን የመዝናኛ ጉዞ ታውቃለህ? ደህና፣ አባቴ የሒሳብ ውጤትህን ከፍ ካደረክ ትሔዳለህ ብሎኛል! የሚያስደስት አይደለምን? በመጀመሪያ አይቻልም ብሎ ነበር። አሁን ለጉዞው መወሰድ የሚያስፈልጉንን ነገሮች መሰብሰብ ጀምሬአለሁ ምን ሊኖረኝ እንደሚገባኝ ንገረኝ።

ማት፣ መልካም፣ የሚያስፈልግህ—

አንዲ፣ በማቋረጥ እናም በርግጥ ነገ በትልቁ የሒሳብ ፈተና ጥሩ ደረጃ ማግኘት አለብኝ፣ ዛሬ አንተ በሰሌዳ ላይ የሰራኸውን ጥያቄ እንዴት እንደምሰራም አላወቀሁም። እንዴት እንደሰራኸው ልትነግረኝ ትችላለህ?

ማት፣ ኦ! አዎ! ማድረግ ያለብህ . . .

አንዲ፣ በማቋረጥ ሄይ! ከትምህርት በኋላ የነበረውን የኳስ ጨዋት አይተሃል? ደስ የሚል አይደለም? እኔ ያገባሁት ግብ በዛ ቀን አሸናፊ አደረገን። እስከ ዛሬ ከተጫወትኩት ሁሉ የተሻለው ነበር የተጫወትኩት፣ አይመስልህምን? ሆኖም፣ ጥሩ ተከላካይ መሆን ብችል እመኛለሁ። ሌሎቹ ቡድኖች እንዳያልፉኝ እና ግብ እንዳያገቡ ለማስቀም ማድረግ ያለብኝ ምንድነው ብለህ ታስባለህ? ስህተት የሆነን እየሰራሁ ነውን?

ማት፣— ጥሩ ለመከላከል እንድትችል ብታደርግ ኖሮ ብዮ እኔ የማስበው —

አንዲ፣ በማቋረጥ ልሄድ ይገባኛል። እማማ ከእራት በፊት ክፍሌን እንዳጸዳ ተፈልጋለች። ስለ እርዳታህ አመሰግናለሁ። ነገ እንገናኛለን። ቻው። (ስልኩ ይዘጋል)

ማት፣ (የተጨነቀና ያዘነ መሰለ) ደህና ሁን፣ አንዲ።

ውይይት

• በአንዲና በማት መሃከል ባለው ግንኙነት ዋና ችግር የነበረው ምንድነው?

• በዚያ ንግግር እና በጸሎታችሁ መካከል ተመሳሳይነት ታገኛላችሁን?

በልባችን እና በአዕምሮአችን ካዳመጥን መንፈስ ቅዱስ የጌታን መልስ ለመስማት እንደሚረዳን አስረዳ። በጸሎት ጊዜ እና ከጸሎት በኋላ መስማትን ማወቅ አለብን። ሁሉም መልሶች ወዲያው አይመጡም፣ ነገር ግን በድንገት ይመጣሉ። አንዳንዴ ጸሎት ከተደረገ ከረጅም ጊዜ በኋላ መልስ ይመጣል። አንዳንድ መልሶች በተወሰነ ምክንያት ህይወታችንን በሚነኩ ሰዎች አማካይነት ይመጣሉ። ከሰማይ አባታችን መልስን ለመቀበል እራሳችንን ብቁ ማድረግ ማስታወስ አለብን።

• አንዳንድ ግዜ የሰማይ አባትን ድምፅ እንደማንሰማ ወይም አድናቆትን እንደማንሰጥ በዝርዝሩ ላይ የሚገልጸው ጥቅስ የትኛው ነው? (1ኔፊ 17፥45።)

ከሰሌዳው ላይ ማጣቀሻዎቹን አስምርባቸው።

ታሪክ

ጌታ ሁልጊዜም ልባዊ ጸሎትን እንደሚሰማ እና እንደሚመልስ ለወጣት ወንዶች ያረጋግጥላቸው። ለማዳመጥ መማር አለብን። ይህን ጉዳይ ለመግለጽ የሚከተለውን የተለወጠውን ዳንሻዊ ልምድ ተናገር፥

ዳንሻዊ የሆነ አርነ ያቀብሰን፣ ቤተክርስቲያንን ይከታተል ነበር። መጽሐፈ ሞርሞንን ለመረዳት ባስቸገረው ጊዜ ያደረገውን እንዲህ በማለት ገልጿል፥

"ቅዱሳን መጽሐፍትን በምናነብበት ጊዜ ለማስተዋሉ ለእግዚአብሔር መጸለይ እና መጠየቅ እንዳለብን ሚሲዮናዊያን እንደመከሩን አስታውሳለሁኝ። ይህንንም ከአደረኩኝ በኋላ መጽሐፈ ሞርሞንን አንብቤ ተረዳሁኝ። ሞሮኒ 10፥3–5 በተለይ መልካም አድናቀትን አሳድሮብኛል።

"መልካም ህይወትን ያኖርኩ ስለማይመስለኝ ስለ መጽሐፈ ሞርሞን እውነተኛነት እግዚአብሔር ጸሎቴን አይመልስልኝም ብዬ ፈርቼ ነበር። ሆኖም ግን፣ አንድ ቀዳሚ ማታ ተንበርክኬ ጌታ ጸሎቴን ከመለሰልኝ በዘመኔ ሁሉ እንደማገለግለው ቃል ገባሁለት። በጸጥታ 'መጽሐፈ ሞርሞን እውነት ነው። የእኔ ቃል ነው። ዮሴፍ

ስሚዝ እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢይ ነው። ቤተክርስቲያኔ በሐዋሪያት እና በነቢያት ላይ የተመሰረተች ናት’ የሚሉትን ቃላት ተቀበልኩኝ። ያገኘሁት ደስታ በቃላት ብቻ ሊገለጥ አይችልም።

“ተጠመቅሁኝ እናም ከጥቂት ወራት በኋላ ውድ ባለቤቴን እና ሁለት ታላላቅ ወንዶች ልጆቼን አጠመቅኩኝ። አሁን የስምንት ደስተኛ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን ቤተሰብ አባላት ነን” (Arne Jacobsen, “Three Well-Behaved Young Men,” *Ensign*, ሐምሌ 1974, ገጽ 40)።

- ይህ ታሪክ የሚያሳየው ከዝርዝራችን ላይ የትኛውን ጥቅስ ነው? (ራዕይ 3፥20 እና ሞሮኒ 10፥3–5።)

ይመራን ዘንድ በምንጸልይበት ወቀት ወይም “በበሩ ላይ ቆመን ስናኳኳ” ለጸጥተኛ፣ አነስተኛ ድምጽ ትኩረት የምንሰጥ ከሆነ ጌታ ጸሎታችንን ይሰማናል እናም መልስ ይሰጠናል የሚለውን በደንብ አስረዳ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ

አንድ ወጣት በዚህ ወቀት በህይወቱ የሚወስናቸው ውሳኔዎች ጠቃሚ እንደሆኑ ግለፅ። ከልብ ከፈለግነው እና ምላሹንም መገንዘብን ከተማርን እግዚአብሔር ይረዳናል።

ውሳኔዎችን በምንወስንበት ጊዜ ለምንከተለው የተለየ መመሪያ ትምህርትና ቃል ኪዳን 9፥7–9 ያንብቡ።

ጥቅስ

ፕሬዚዳንት ማርዮን ጂ ሮምኒ ችግራቸውን ለመወጣት የሚከተለውን መመሪያ ከትምህርት እና ቃል ኪዳን እንዴት እንደተጠቀሙ ግለፅ፥

“በችግር ስጠመድ በጸሎት የትኛው ጥሩ እንደሆነ ውሳኔ ላይ ለመድረስ በአዕምሮዬ አማራጭ መፍትሄዎችን አመዛዝናለሁ እናም የትኞቹ የተሻሉ ናቸው ወደሚለው ማጠቃለያ እደርሳለሁኝ። ከዛ ችግሬን ለጌታ በጸሎት አቀርባለሁ፣ በእኔ ፍርድ፣ ትክክለኛ የሆነውን ትክክለኛ ምርጫ ለማድረግ እንደምፈልግ እነግረዋለሁ። ከዚያም ለኦልቨር ካውድሪ ጌታ ቃል እንደገባው ትክክለኛ ውሳኔን እንዳደረኩ በውስጤ መቃጠልን እንዲሰጠኝ እጠይቀዋለሁ። መረዳት እና ሰላም ወደ አዕምሮዬ በሚመጣበት ግዜ፣ ጌታ እሺ እያለኝ እንደሆነ አውቃለሁ። “በአዕምሮ ውስጥ የማይጸና ሐሳብ” ካለኝ እግዚአብሔር አይሆንም እያለኝ እንደሆነ አውቃለሁ፣ እናም አንድ ተመሳሳይ መንገድን በመከተል እንደገና እሞክራለሁ።

“በመጨረሻ፣ እደግመዋለሁ፥ በሚሰማኝ መንገድ ጌታ ጸሎቴን መቼ እና እንዴት እንደሚመልስልኝ አውቃለሁ” (ከ “Q and A” *New Era*, ጥቅምት 1975, ገጽ 35)።

ውይይት

“በአዕምሮ የማይፀና ሀሳብ” እና “በሰውነት ውስጥ መቃጠል” ሁሉ ለጸሎት ጥያቄ” መልስ እንደሚሆን አትኩሮት ስጥበት። ጌታ ከነዚህ መንገዶች በአንዱ በአብዛኛውን ጊዜ ከልብ የሆኑትን ጥያቄዎች እንደሚመለስ እንደሚያስተውሉ ወጣት ወንዶችን እርዳቸው።

---

**ማጠቃለያ**

ምስክርነቶች

ለጸሎታቸው መልስ ስለማግኘታቸው ያላቸውን ልምዶች እንዲያካፍሉ ለወጣት ወንዶቹ ይፍቀዱላቸው።

በክፍልህ ውስጥ ወጣቶቹን ሊያነቃቁ የሚችሉ የጸሎት ልምዶች ካሉህ ካፍል።

ሙከራ

እንደ ሰማይ አባት ለመሆን በሚጥሩበት ጊዜ በህይወታቸው ውስጥ ለአመራር እንዲጸልዩ ወጣት ወንዶችን አበረታታቸው።

# ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ ንስኃ

# 24

**ዓላማው** — እያንዳንዱ ወጣት ወንድ በዕለት ሕይወቱ ውስጥ ንስኃን መመሪያው ያደርጋል።

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች
   ሀ. ለየአንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቀዱሳን መጽሐፍት
   ለ. ጥቀሶችን ማሰመሪያ እርሳሶች።
2. የሚከተሉትን በተለጣፊ ቁራጭ ወረቀት ላይ ጻፍ፡፡
   ሀ. የእኛን ኃጢአት መገንዘብ
   ለ. በኃጢአታችን ማዘን
   ሐ. በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአት ክፍያ ማመን
   መ. ኃጢአታችንን መናዘዝ
   ሠ. ኃጢአታችንን መተው
   ረ. ለኃጢአታችን ካሣን መክፈል
   ሰ. ትዕዛዛቱን መጠበቅ እና እስከ መጨረሻው መጽናት
3. (የአልማን መለወጥ) አልማ 36፥6–26 ከልስ፡፡
4. በአካባቢህ ውስጥ ከተገኘ "የንሥሐን ስጦታ"፣ በቤተሰብ የቤት ምሽት የቪዲዮ ማሟያን [*Family Home Evening Video Supplement*] (53276) አግኝ፡፡
5. *ለወጣቶች ጥንካሬ* ከሚለው ውስጥ በገጽ 17 እና 18 ስለ ንሥሐ የተሰጠውን ምክር ከልስ፡፡

**ለትምህርት ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**መግቢያ**

በቤተሰብ የቤት ምሽት በቪዲዮ ማሟያ [*Family Home Evening Video Supplement*] የሚገኘውን "የንስኃ ስጦታ" ትምህርት፣ በአካባቢህ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ አሳይ፡፡

ውይይት — "በጥቁር ሰሌዳ ላይ "ንስኃ ማለት—" በማለት ፃፍ

ንስኃን ለማስረዳት ሊረዱ ስለሚችሉት ቃላቶች ወይም ሀረጐች እንዲያስቡ ወጣት ወንዶችን ጠይቀ፡፡ መልሶቻቸውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ፡፡ መልሶቹ ሂደትን፣ ትዕዛዛትን፣ የልብ መለወጥን፣ የአንድን ሰው ሕይወት ማሻሻልን፣ እና ለኃጢአታችን የሀዘን ስሜቶችን ያጠቃልላሉ፡፡

---

**ንስኃ ሂደት ነው**

ቀዱሳን መጽሐፍቶች፣ ተለጣፊ የቃላት ዝርዝሮች፣ እና ውይይት፡፡

ንስኃ ወደ ሰማዩ አባታችን ለመቀረብ የሚያበቃን ሂደት መሆኑን ለይተህ አመልክት፡፡ አልማ በንስኃ ሂደት ውስጥ እንዴት እንዳለፈ እንደሚያነቡ ለወጣት ወንዶች ንገራቸው፡፡

አንድ ወጣት አልማ 36፥6–16ን እንዲያነብ ጠይቀ፡፡

- አልማ ስለፈፀማቸው ኃጢአቶች ምን ተሰማው?
- እኛ ስለ ኃጢአታችን እንዴት ሊሰማን ይገባል?

ንስኃ መግባት ከመቻላችን በፊት ኃጢአት መስራታችንን ማወቀ እና ኃጢዓታችንን መለየት የሚገባን መሆኑን ለወጣት ወንዶች ንገራቸው። ከዚያም የእግዚብሔርን ትዕዛዛቶች ባለማክበራችን ማዘን አለብን፡፡ የመጀመሪያዎቹን ሁለት የቃላት መሥመሮችን አመልክት።

- በየዕለት አኗኗራችን ውስጥ የምንሰራቸው ስህተቶች ምን ዓይነት ሊሆኑ ይችላሉ?

ንስኃ የምንገባቸው ዋና ዋና መተላለፎች መግደል፣ ማመንዘር ወይም ስርቀት የመሳሰሉት ብቻ እንዳልሆኑ ወጣት ወንዶቹ እንዲገነዘቡት እርዳቸው። አንዳንድ ግዜያቶች በየዕለቱ በየዕለቱ ለፈፀምነው ጥቃቀን ነገሮች ንሥኃ መግባት ያስፈልገናል። እነሱም እንደ እምነት ማጉደል ያሉ ድርጊቶች፣ መልካም ጸባይ ማጣት፣

ለወላጆቻችን አክብሮትን ለለማሳየት፣ ሀሚት፣ ወይንም የመንፈስ ቀዱስን አጋርነት እንድንደሰት እና የሰማዩ አባትን እንድንመስል የተሰጠንን የቤት ሥራ እንዳንከተል በተያግዱን ደካማ ባህሪያት ውስጥ መውደቅ ናቸው።

አንድ ወጣት አልማ 36፥17–19 እንዲያነብ ጠይቅ። “በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአት ክፍያ እምነት ይኑርህ” የሚለውን የቃላት ዝርዝር ለጥፍ።

• አልማን ኃጢአቶቹን ከማስታወስ ስቃይ ያዳነው አስተሳሰብ ምንድነው?

• ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአት ክፍያ ስታስብ እንዴት ይሰማሃል?

ጥቀሶች

ፕሬዚዳንት እዝራ ታፍት ቤንሰን እንዳስረዱት በእውነት ንስኃ ለመግባት ከፈለግን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነትን ማሳየት አለብን፣

“ንስኃ ማለት ዝም ብሎ ፀባይን ከማሻሻል የበለጠ ነው። በዓለም ውስጥ ብዙ ወንዶች እና ሴቶች ጉጂ ልምዶችን እና የስጋን ድክመት በመቋቋም ታላቅ ኃይልን እና የግል ሥነ-ሥርዓትን አሳይተዋል። ግን በዚሁ በተመሳሳይ ወቀት ለጌታ ምንም ሐሳብ የላቸውም፣ እንደውም አንዳንድ ጊዜም በግልፅ ያገሉታል። እንደዚህ ያሉ የፀባይ ለውጦች፣ በመልካም አቀጣጫ ውስጥ ቢሆኑም እንኳ እውነተኛ ንስኃን አይፈጥሩም።

“በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ልባዊ እና ትርጉም ያለውን ንስኃ ልገነባበት የሚገባ መሰረተ ነው። በእውነት ኃጢአትን ከእኛ ለማራቅ ከፈለግን፣ የደህንነታችን ፋና ወጊ ወደሆነው መመልከት አለብን” (“A Mighty Change of Heart,” *Ensign*, ጥቅምት 1989, ገጽ 2)።

አልማ የኃጢአተኛነቱን ለጌታ እንደተናዘዘ ግለፅ። “ኃጢአታችንን መናዘዝ” የሚለውን ተለጣፊ የቃላት ዝርዝር ለጥፍ።

• ኃጢአቶቻችንን ለማን መናዘዝ ይገባናል?

ወጣት ወንዶቹ ሐሳባቸውን ከገለፁ በኋላ፣ ለበደልነው መናዘዝ እንዳለብን ግለፅ። ለጌታም መናዘዝ አለብን፡፡ በተጨማሪም፣ የተላለፍነው ከፍተኛ ኃጢአት ከሆነ ወደ ጳጳስ መሄድን ይጠይቅ ይሆናል፡፡ ጳጳሱ እዚያ ያለው ለመርዳት እንጂ ወጣት ወንዶችን ለመውቀስ እንዳለሆነ ለወጣት ልጆች ንገራቸው። ጳጳሳት እንዲህ ያለውን መረጃ ሁል ጊዜ በሚስጥርነት ይጠብቃሉ።

• ምን አይነቶቹን ኃጢአቶቻችንን ጳጳሳችን እንናዘዛለን?

ቄስ ማርዮን ጂ ሮምኒ እንዳስረዱት፣ የአንድ ሰው መተላለፉ እንዳለ ከሆነ ማለትም ንስኃ ያልገባለት ከሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ አባልነቱን ወይንም ህብረቱን አደጋ ላይ ስለሚጥለው፣ ሙሉ እና ውጤታማ *ኑዛዜ*. . . . ለጳጳሱ መናዘዝን ይጠይቃል (በ Conference Report, ጥቅምት 1995, ገጽ 125, ልዩ ጽሁፍ የተጨመረ)።

እንደዚህ ያሉት ኃጢአቶች የዝሙት እና ማናቸውንም የንፅህና ሕግን እና ደንብን መተላለፎችን ያጠቃልላል፡፡

አንድ ወጣት አልማ 36፥20–23 እንዲያነብ ጠይቅ፡፡

• ኃጢአቶቹን ከተናዘዘ በኋላ አልማ እንዴት ተሰማው?

• የጌታን ይቀርታን ካገኘ በኋላ ወደ ኃጢአቱ ቢመለስ ኖሮ አልማ ምን ይሰማው ነበር ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ንስኃ ፈጣን ወይም ቀላል ሂደት እንዳልሆነ ወጣት ወንዶች መረዳታቸውን አረጋግጥ። እንደ አልማ ሁሉ፣ ንስኃ ስንገባ ህመም እና ስቃይ ይሰማናል። የጌታን ይቀርታ ከመቀበላችን በፊት ምናልባት በረጅም የንስኃ ሂደት ውስጥ እንድንሄድ እንጠይቅ ይሆናል፡፡

“ኃጢአታችንን መተው” የሚለውን የቃላት መስመር ከፍ አድርገህ ያዝ። ኃጢአታችንን መተው ማለት ምን ማለት እንደሆነ ወጣት ወንዶችን ጠይቅ። ለኃጢአቱን በእውነት ንስኃ የገባ ሰው መድገም እንደሌለበት ወጣት ወንዶች እንዲገነዘቡት እርዳቸው፡፡

“ለኃጢአታችን መካስ” የሚለውን የቃላት መስመር ከፍ አድርገህ ያዝ።

*ካሣ* የሚለው ቃል ለተደረገው ስህተት ትክክለኛውን መስራት እንደሆነ አስረዳ፡፡

• አንድ ወጣት ወንድ አልማ 36፥24–26 እንዲያነብ አድርግ።

• አልማ ለኃጢአቱ ካሣን እንዴት አደረገ? (ሰዎችን ለመርዳት በመሞከር እርሱ የተሰማውን ደስታ እንዲሰማቸው ወንጌልን ሰበከላቸው፡፡)

በሚቀጥሉት ጥቀሶች ላይ እንደተገለጸው ሙሉ በሙሉ ሊፈጸሙ አይችሉም የማይባሉ ጥቂት ጥፋቶች እንዳሉ ቡድኑን አስታውስ፣

“የልጆች በራሪ መጫወቻዎች በባለ ነጭ ክንፍ ወፎቻቸው ቢጐተቱም— ቃላትን ስታበር እንዲያ ማድረግ አትችልም። በቃላት ያልተገለፁ ሀሳቦች እንዳንዴም ቢሞቱም አንዴ ከተነገሩ ግን እግዚአብሔር እራሱ ሊገድላቸው አይችልም።” (ዊል ካርለተን)

መሐላ፣ ሀሜት፣ ውሸት፣ እና የሀሰት ምስክርነት በዚህ ክፍል ውስጥ እደሚጠቃለሉ ግለጽ። ነገር ግን አብዛኛዎቹ ጥፋቶች ይጠገናሉ፡፡

ጥቅስ

ከብዙ ዓመታት በፊት የአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት መማክርት ሁለተኛ ረዳት የነበሩ ቄስ ዊሊያም ጀ ክሬችሎው፣ የሚከተለውን ብለዋል፥

“የእስካውትን ሽልማት ለመቀበል ዝግጁ የሆኑ ሶስት ልጆች የመንገድ መብራትን ሲጥሱ ተስተዋሉ። እናም በመያዛቸው አዝነው ነበር። በኋላ ግን ሽልማታቸውን ከመቀበላቸው በፊት፣ ድርጊታቸውን በማወቀ ስካውት እንዳልሆኑ ተገነዘቡ፤ እናም በእውነተኛ የፀፀት ስሜት ሌሎች ተመሳሳይ መተላለፎችን ለመናገር ወደ ኩባንያው ሄዱ እናም መብራቱን ስለ መጣሳቸው ካሣን ከፈሉ” (“Spelling Repentance with Seven Big R’s,” *Instructor*, መጋቢት 1966, ገጽ 93)፡፡

ተረቶች

የሚሲዮናዊነትን ጥሪ ስለተቀበለው ወጣት አንድ ሌላ ምሳሌ ተነግሯዋል። ያንን ሚሲዮን ለማገልገል እራሱን በማዘጋጀት ሳለ፣ ያለፉትን አነስተኛ ጥፋቶች ሁሉ ለመጥረግ እና ለማጽዳት ወሰነ፡፡ ከዓመታት በፊት የተከሰተውን በፈተና ላይ ያደረገውን ማታለል ወደ ኋላ ባሰበበተ ወቀት እንደ አስፈላጊነቱ ካሣን ለመክፈል ፈለገ። ለዚያች አስተማሪ ደብዳቤን በመጻፍ ኃጢአቱን በመናዘዝ እርሷን ይቅርታ ጠየቀ፡፡ ከንፁህ ህሊና ጋር ጌታን ለማገልገል ወደ ፊት ለመሄድ እንደሚችል ሊሰማው ችሏል፡፡

“ትዕዛዛቱን ጠብቀ እናም እስከ መጨረሻው ጽና” የሚለውን የፈጨረሻው ተለጣፊ የቃላት መስመር ከፍ አድርገህ ያዝ።

በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ካለን ኃጢአታችንን ለማሸነፍ እና በህይወታችን ሁሉ የጌታን ድጋፍ እና ምሪት ለማግኘት እንደምንችል ግለፅ።

የቅዱስ መጽሐፍ ጥቅስ እና ውይይት

አንድ ወጣት አልማ 36፥27–28ን እንዲያነብ ጠይቀ፡፡

• አልማ ተስፋውን እና እምነቱን በማን አኖረ?

• የአልማ እምነት በህይወቱ ሁሉ መከራን ለመቋቋም እንዴት ረዳው?

ይህ እርምጃ ምናልባት ከባዱ እንደሆነ ግለፅ። ወደ ጥንት ልማዶቻችን እንዳንመለስ ዘውትር ልንጠብቀው የሚገባን ታማኝነታችንን ማረጋገጥ ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ይቅር ባይነት ለማግኘት ተጨማሪ ማይል መጓዝ አለብን፣ ይህም ከኃጢአታችን መራቀ ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ሥፍራ በምንችለው ሁሉ ጥሩ በመስራት ነው። ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬ እንዳሉት “ደስተኝነት ጽድቀ ነው” (በ William J. Critchlow Jr. የተጠቀሰ . . . *Instructor* መጋቢት 1966, ገጽ 93)።

ታላቁ ነቢይ ሊሂ፣ “ጽድቀ ከሌለ ደስታ የለም” ብሏል (2ኔፊ 2፥13)፡፡

---

**ንስኃ እራስህን ይቀር ማለትን ያጠቃልላል**

የቅዱስ መጽሐፍ ጥቅስ እና ውይይት

• ንስኃ እንዳንገባ እኛን የሚያግድበተ የሰይጣን ታላቁ መሳሪያ ምን ይመስልሃል?

የተለያዩ መልሶችን ታገኝ ይሆናል፡፡ ሁሉም መልሶች ተቀባይ ሊሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን ለዚህ ውይይት ዓላማ፣ “ተስፋ መቁረጥን” ተመልከተ፡፡

የጥፋተኝነት ስሜት የጤንነት ምልክት ሊሆን እንደሚችል ግለፅ፤ ኃጢአት እንዳደረግን እና ንስኃ መግባት እንደሚያስፈልገን ያኞታውሰናል፡፡ ነገር ግን ከልባችን ንስኃ ከገባን በኋላ በደለኛነት ከተሰማን ተስፋ እንድንቆርጥ ያደርገናል እንደገናም ለፈተና ይዳርገናል፡፡

ትምህርት እና ቃል ኪዳን 58፥42 አንብብ እና ተወያይ፡፡

ወጣት ወንዶቹ ንስኃ ከገቡ በኋላ የሚሰማቸው የበደለኝነት ስሜት የሚቀጥል ከሆነ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እራሳቸውን መጠየቀ እንዳለባቸው ግለጽ፥

1. ሁሉንም የንስኃ ደረጃዎች ተከትያለሁን?

2. የሰማይ አባት ይቀር እንዲለኝ ጠይቄዋለሁን?

3. ጌታ እርሱን በማመኔ ሸክሚን እንዲወስድልኝ አድርጌአለሁን?

4. ትዕዛዛቱን ለመጠበቀ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁን?

---

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት

የሰማይ አባት እያንዳንዳችንን እንደሚያውቀ እና እንደሚወድ ምስክርነትህን ስጥ፡፡ የምናደርገውን ያውቃል፣ እናም በልባችን ውስጥ ያለውን ያውቃል፡፡ ኃጢአታችን ለእርሱ ታላቀ ኃዘንን ለእኛ ደግሞ መበሳጨትን ያመጣብናል፡፡ ምንም ያህል መጥፎ ነን ብለን ብናስብም ንስኃ ለመግባት እና ዳግም ለመጀመር መዘግየት የለብንም። ማናችንም አንዳንድ ነገርን ማሻሻል የሌለብን ፍጹሞች አይደለንም፡፡ ጌታ “ወደ እኔ ኑ፣” በማለት ሲናገር ለሁሉም ነበር።

ሙከራ

ለወጣቶች ጥንካሬ ከሚለው በገጽ 17 እና 18 ስለ ንስኃ ምክር ከልስ፡፡ ወጣት ወንዶች የእለት ሐይወታቸውን ዝርዝር እንዲወስዱ አበርታቸው፡፡ ለምሳሌ፣ ለማሻሻል ወይም ንስኃ ለመግባት የሚፈልጉት ምንድን ነው? ለመለማመድ እንዲጀምሩ፣ የሚቀጥለውን ጥያቄ በዝምታ እራሳቸውን እንዲጠይቁ ጠይቃቸው፣

"የመንፈስ ቅዱስ ጓደኝነትን ሙሉ በሙሉ እንድደሰትበት ምን ማድረግ እችላለሁ?"

የሚመጡላቸውን መልሶች ምንም አስተያየት ሳይሰጡ እንዲያሰላስሉት አድርግ፡፡

# ምህረት

# 25

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ምህረትን ሲያደርግ እና ሲፈልግ በአካባቢው ካሉት ሰዎች ጋር በታላቅ ስምምነት ይኖራል። |

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለየአንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. ሥዕል 1፣ የመጨረሻው እራት።
   ሐ. ጥቅሶችን ለማስመሪያ እርሳሶች።
   መ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ እርሳስ።
2. "እኔ ይቀር ባይ ሰው ነኝን" የሚለውን የሚታደል ጽሑፍ ቅጂ ለእያዳንዱ የክፍል አባል አዘጋጅ።
3. ምህረት ስለሌለው አገልጋይ ታሪክ ለመናገር ተዘጋጅቶ እንዲመጣ አንድን ወጣት ወንድ መድብ (የማቴዎስ ወንጌል 18፥23–35 ተመልከት)።
4. ወደ ግብጽ ስለተሸጠው ዮሴፍ ታሪክ አንብብ (ኦሪት ዘፍጥረት 37፣ 39–46 ተመልከት)። የማቴዎስ ወንጌል 18፥23–35 እና የሉቃስ ወንጌል 23፥33–34 አጥና።

**ለትምህርቱ እድገት የቀረበ ሐሳብ**

**ቅዱሳን መጽሐፍት የይቅርታን ምሳሌዎች ይሰጡናል።**

ተሳትፎ

"አንድ ወጣት ከሥር የተጠቀሱትን ፍንጮች እንዲያነብ በማድረግ "እኔ ማን ነኝ" የሚለውን ተሳትፎ ምራ። አንድ ሰው እየተገለጸ ያለውን ግለሰብ ማንነት ያወቀ መስሎ ከተሰማው፣ ወዲያውኑ እጁን ማንሳት አለበት። ሆኖም ግን፣ ዝርዝሩ እስከሚያልቅ ድረስ ወይም ሁሉም ወጣት ወንዶች እጆቻቸውን እስከሚያወጡ ድረስ አንባቢው መቀጠል አለበት።

እኔ ማነኝ?

1. በውሸት ተከስሼ ወደ እስር ቤት ተላኩኝ (ኦሪት ዘፍጥረት 39፥11–20 ተመልከት)።
2. በኋላ ከእስር ነፃ ወጥቼ በሰው ሀገር ውስጥ ከፍተኛ የአመራር ማዕረግ ተሰጠኝ (ኦሪት ዘፍጥረት 41፥37–43 ተመልከት)።
3. ለብዙ ዓመታት ከቤተሰቤ ተለይቼ ነበር (ኦሪት ዘፍጥረት 37፥28፤ 39፥1–2፤ 20፤ 41፥1፥14፤ 46–48 ተመልከት)።
4. የጠጅ አሳላፊውን፣ የእንጀራ አበጋዙን፣ እና የመሪውን ሕልሞች ፈታሁ (ኦሪት ዘፍጥረት 40–41 ተመልከት)።
5. በረሀብ የተነሳ ቤተሰቦቼ የትውልድ ሀገራቸውን ለቀው እኔ ወደምኖርበት ተዘዋወሩ። ስለዚህ፣ ልረዳቸው ቻልኩኝ (ኦሪት ዘፍጥረት 45–46 ተመልከት)።
6. ልጅ በነበርኩበት ጊዜ አባቴ አንድ የተዋበ ኮት ሰጠኝ (ኦሪት ዘፍጥረት 37፥3 ተመልከት)።
7. ምንም እንኳን ወንድሞቼ ለባርያ ነጋዴዎች ቢሸጡኝም፣ እኔ ምህረት አደረኩላቸው፣ በግብጽ የሚያስደስት ሕብረት ነበረን እናም ለብዙ ዓመታት በደስታ ኖርን (ኦሪት ዘፍጥረት 45–46 ተመልከት)።

• እኔ ማን ነኝ? (ወደ ግብፅ የተሸጠው፣ የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍ)

ውይይት

ወጣቶቹ ሙሉውን ታሪክ እንዲያዛምዱ እርዳቸው።

• ይህ ታሪክ የሚገልፀው መሠረተ ሀሳብ ምንድን ነው? (ምሕረት።)

• የሚያስደስት ሕብረትን ሊያስገኝ የቻለው ምንድን ነው? (ዮሴፍ ለበፊቱ ጥፋት ምህረት ለማድረግ ፈቃደኛ ነበር።)

የቅዱስ መጽሐፍ ጥቅስ እና ውይይት

የሉቃስ ወንጌል 23፥33–34 አንብብ እና ይህንን ታላቅ የምህረት ታሪክ ከወጣት ወንዶቹ ጋር ተወያይ።

**ምሕረትን አድራጊ መሆንን መማር አለብን።**

የማሰላሰያ ጥያቄዎች

*ምሕረት* የሚለውን ቃል በጥቁር ሰሌዳው ጫፍ ላይ ጻፍ፡፡

ወጣት ወንዶቹ ስለሚከተሉት ጥያቄዎች እንዲያስቡ አድርግ፡፡ መልሶቻቸውን ከሌሎች ወጣት ወንዶች ጋር መካፈል የለባቸውም፡፡

- በሌላ ሰው ላይ ስለፈጸምከው ስህተት ምሕረት እንዲደረግልህ ፈልገህ ታውቃለህን?
- ምህረት ሳይደረግልህ በፊት የተሰማህ ምንድን ነው?
- ምህረት ከተደረገልህ በኋላ የተሰማህ ምንድን ነው?

የቅዱስ መጽሐፍ ታሪክ

የተመደበው ወጣት ይቅር ባይ ስላልሆነው ባሪያ ምሳሌ እንዲናገር ጠይቀው (የማቴዎስ ወንጌል 18፥23–35 ተመልከት)፡፡

- ኢየሱስ በዚህ ምሳሌ ሊያስተምረን የሞከረው ምን ይመስልሃል?

ቅዱስ መጽሐፍ፣ ጥቅስ፣ እና ውይይት

አንድ ወጣት የማቴዎስ ወንጌል 18፥35 እንዲያነብ አድርግ፡፡

በዘመናችን የገንዘብ መጠን፣ የመጀመሪያው የአስር ሺህ መክሊቶች ዕዳ ከዘጠኝ ሚሊዮን ዶላር በላይ ሲሆን፣ የሁለተኛው የመቶ ዲናር ዕዳ ወደ አስራ አምስት ዶላር እንደሚሆን ግለጽ (James E. Talmage, *Jesus The Christ* (ኢየሱስ ክርስቶስ) ይመልከቱ ሶስተኛውን እትም ተመልከት። [Salt Lake City: (ሶልት ሌክ ሲቲ) The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints, 1916], ገጽ 394, 396–97)፡፡

- ለዳኛችን በዚህ ምሳሌ ላይ ለራሳችን ሕይወት ያስተማረውን መልዕክት ምንድነው?

የቅዱስ መጽሐፍ ፍለጋ

የሚከተሉትን ጥቅሶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ፣ እና የማቴዎስ ወንጌል 6፥14–15 እና ትምህርት እና ቃል ኪዳን 64፥9–10 ለማመልከት ማን የመጀመሪያ ሊሆን እንደሚችል ለማወቅ ወጣት ወንዶቹን አበረታታ፡፡ አንድ ወጣት እያንዳንዱን እንዲያነብ አድርግ፡፡ ወጣት ወንዶቹ ምናልባት የእነዚህን ቁጥሮች ክፍል ምልክት ሊያደርጉባቸው ይፈልጉ ይሆናል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢአታችን እንደተሰቃየ እና እንደሞተ ለወጣት ወንዶቹ ግለጽ፡፡ ከልባችን ንስኃ ስንገባ፣ ምህረት ያደርግልናል፡፡ ለሌሎች ሰዎች ኃጢአት ለመሰቃየት አልተጠየቅንም፣ ግን “ሁሉንም ሰዎች” ይቅር ለማለት ታዘናል፡፡ ኢየሱስ ምህረት እንዳደረገልን፣ እኛም ለሌሎቹ ምህረት በማድረግ፣ የበለጠ እንደ እርሱ መሆንን እንማራለን፡፡

አጭር ፈተና

ለእያንዳንዱ ወጣት “እኔ ምህረት አድራጊ ሰው ነኝን?” የሚለውን ጽሑፍ ቅጂ እና እርሳስ ስጥ እና ይህም ምህረትም ስለማድረግ አጭር ፈተና እንደሆነ ግለጽ። ሁሉም ጥያቄዎች በታማኝነት በቀላሉ አዎን ወይም አይደለም ተብለው መመለስ አለባቸው፡፡ ይህም የግል ተሳትፎ እንደሆነ እና፣ መልሶቻቸውን ለክፍሉ ማካፈል እንደሌለባቸውም ክፍሉን አስታውስ፡፡

“እኔ ምህረት አድራጊ ሰው ነኝን?”

1. “ደህና፣ ምህረትን አደርጋለሁ፣ ነገር ግን በፍጹም ልረሳው አልችልም” ብለህ ታውቃለህን?
2. በማትወደው ሰው ላይ መጥፎ አጋጣሚ ሲከሰት በውስጥህ ተደስተህ ታውቃለህን?
3. አንድ ሰው ላደረገብህ ነገር አንተም በምላሹ ያንኑ ልትፈፅምበት ተመኝተህ ታውቃለን?
4. የምታርቀው ወይም የማታነጋግረው ሰው አለን?
5. በአንድ ሰው ስትናደድ፣ ንዴትህን ለማቃለል ለትንሽ ቀናት ታኮርፋለህን?
6. በደል አድርሶብኛል ብለህ ስላሰብከው ሰው ለሌሎች መጥፎነቱን ተናግረህ ታውቃለህን?
7. ከቅርብ ቤተሰብህ ውስጥ ላደረገብህ ወይም ላደረገችብህ ነገር የተቀየምከው ሰው አለን?
8. ከወንድሞችህ ወይም ከእህቶችህ ጋር ስትጨቃጨቅ፣ ከዚህ በፊት ያደረጉብህን ነገሮች ታነሳለህን?

ወጣት ወንዶቹ ከጥያቄዎቹ አዎን ብለው መመለስ ስለነበሩባቸው መልሶች እንዲያስቡባቸው አድርግ፣ ምህረት ማድረግ ቀላል እንዳልሆነ፣ ከታላቅ ፈተናዎቻችን አንዱ እና ለሌሎቹ ያለን እውነተኛ ፍቅር መፈተኛ እንደሆነ ግለጽ፡፡

ታሪክ እና ውይይት

ወጣት ወንዶቹ ለምህረት ቁልፍ የሆነውን የሚከተለውን ታሪክ እንዲያዳምጡ አድርግ፡፡

“ማርቆስ ንቁ፣ ጩኸት የሚያበዛ ልጅ ነበር፡፡ አንዳንዴ በቤቱ አካባቢ ያሉ ነገሮች በጣም ፀጥ ያሉ መስሎ ይሰማዋል፣ ስለዚህ አንድን ነገር ለመጀመር ይሞክራል፡፡ አንድ ቀን ማታ ከእህቱ ከሱዛን ጋር መነጋገር ፈለገ፡፡ ማርቆስን በትምህርት ቤት አንድ ዓመት ተቀድመው ነበር፣ እናም አብዛኛውን ጊዜ ብዙ የቤት ስራ ነበረባት፡፡

“ስራ ከሌላት፣ ከማርቀስ ጋር ተነጋገር እና ትስቅ ነበር፣ ነገር ግን በዚህ ምሽት በጣም ስራ በዝቶባት ነበር። በእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት የቤት ስራ ስለነበራት ብዙ ጭንቀት ይሰማት ነበር። ስራዋን ለማርቀስ ነግራ ብቻዋን ትቷት እንዲሄድ ለማድረግ ሞከረች፣ ነገር ግን የሚያናግረው ሌላ ማንም ሰው ስላልነበረ፣ ማርቀስ በመናገር እና በመሳቅ እርሷን መጨቀጨቁን ቀጠለ። የውጭ ሀገር ቋንቋ እንዲመስል እያንዳንዱን ቃል ወደ ኋላ በማዞር መነጋገርን ይለማመድ ነበር። በዚህ ጨዋታ በመኩራራት ከሚወዱት መዝሙሮች አንዱን መልሶ ወደ ኋላ በመዘመር ችሎታውን ለሱዛን ለማሳየት ፈለገ።

“በመጨረሻ፣ ሱዛን በእንባ ታጠበች እናም ‘ሊገባህ አይችልምን? ማጥናት አለብኝ። ማጥናት አለብኝ። አሁን ለመናገርም ሆነ፣ ያንተን ንግግር ለማዳመጥ ጊዜ የለኝም እንዴት እንደሆነ ልነግርህ ሞክሬ ነበር። ለብቻዬ ልትተወኝ አትችልምን?’ በማለት በማርቀስ ላይ ጮኸችበት፣ መጽሐፏን በንዴት ቀለለች እና ወደ ክፍሏ ሮጠች፣ በሩን ወደ ኋላዋ ደረገመችው።

“መጨረሻ ላይ በፍጥነት ከክፍሏ ወጣት እናም እራሷን በእርሱ ቦታ አድርጋ ባለማየቷ ማርቀስን ይቅርታ ጠየቀችው። ‘የቤት ስራዬን ስጨርስ፣ ያንን መዝሙር ስትዘምር መስማት እፈልጋለሁ። አሁን ለትንሽ ጊዜ ተለማመድ፣ እና በኋላ ለኔ ትዘምርልኛለህ፣’ አለችው።

“ማርቀስም በቀላሉ እንዲህ አለ፣ ‘እሺ። ስለ ረበሽኩሽ አዝናለሁ። ምን ያህል መስራት እንዳለብሽ አላወቀሁም ነበር። ለማንኛውም አንዳንድ የምደውልላቸው ልጆች አሉኝ። ሄጄ እርሱን ላድርግ” (*Love Makes Our House a Home* [Family Home Evening manual, 1974], ከገጽ 141–42)።

- ማርቀስ እና ሱዛን እርስ በእርስ የተናደዱት ለምንድን ነው?
- እርስ በርስ ይቅር ለመባባል የቻሉት እንዴት ነው? (እያንዳንዳቸው የሌላውን ሁኔታ ለማወቅ ሞከሩ።)

ታሪክ እና ውይይት

“የመጨረሻውን እራት” ሥዕል አሳይ፣ እና የሚከተለውን የሊዮናርዶ ዳቪንቺን ታሪክ አካፍል፣

“ሊዮናርዶ ዳቭቪንቺ ምንም እንኳን (1452 ተወልዶ) ከብዙ ዓመት በፊት የኖረ ቢሆንም፣ ጥበብ ለተሞላበት ሥዕሉ በአለም ሁሉ ታዋቂ ሆኖ ቀርቷል። “በሁሉም ዘመናት በተሳሉት ሥዕሎች ታሪክ በይዘቱ በጣም ፍጹም’ ተብሎ የተደነቀው ‘የመጨረሻ እራት’ ከታዋቂ ስራዎቹ አንዱ ነው።

“በአንድ ታሪክ መሠረት፣ ሊዮናርዶ ዳቪንሲ ‘የመጨረሻውን እራት’ በተስልበት ወቅት በአንዱ ጓደኛው በጣም ተበሳጭቶ ነበር። ወደ ሥዕሉ ሲመለስ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ እና በሐዋሪያቱ ፊቶች ላይ የሚሞላውን ባሕሪይ መስራት አልቻለም።

“በመጨረሻ የበደለውን ሰውዬ ፈልጐ ይቅርታ ጠየቀው። ስራውን መቀጠል የቻለው የሱ የፈጠራ ሰዎች ሊያንጸባርቁት ከሚገባቸው ከዚያ ከሚያውቀው መንፈስ ጋር ህይወቱን ባስማማ ጊዜ ነበር” (Arthur S. Anderson, “They Taught Forgiveness,” *Instructor*, ሰኔ 1959, ገጽ 190)።

የሊዮናርዶ ዳቪንሲን ታሪክ በአጭሩ ከተወያየህ በኋላ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይቅ፣

- ይህ ታሪክ የሰማይ አባታችንን መንፈስ እንድንደሰትበት ስለሚያደርገን ችሎታ የነገረን ምንድን ነው?
- የምህረት መንፈስ በቤተሰባችን ውስጥ ሊረዳን የሚችለው እንዴት ነው?

---

**ማጠቃለያ**

ሙከራ

ወጣት ወንዶቹ ወረቀቶቻቸውን እንዲመልሱ እና በሚቀጥለው ሳምንት ውስጥ ለአንድ ጓደኛቸው ወይም ለአንድ የቤተሰብ አባል ይቅርታ ለማድረግ እና ፍቅራቸው እንዲጨምር የሚረዳቸውን አንድ ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ የሆኑበትን ነገር እንዲጽፉ ጠይቅ። ወጣት ወንዶቹ በሁሉም ሕብረታቸው፣ በተለይ ከራሳቸው የቤተሰብ አባላት ጋር የምህረትን መንፈስ እንዲያሳድጉ አበረታታቸው። ይህንን ጥሩ የወንጌል መሠረተ ሀሳብን በተመለከተ ምስክርነትህን ግለጽ።

# ምህረት አድራጊ ሰው ነኝን?

1. “ደህና፣ ምህረት አደርጋለሁ፣ ነገር ግን በፍጹም ልረሳው አልችልም” በማለት ትናገራለህን?
2. በማትወደው ሰው ላይ መጥፎ አጋጣሚ ሲከሰት በውስጥህ ትደሰታለህን?
3. አንድ ሰው ላደረገብህ ነገር አንተም በምላሹ ያንን ልትፈጽምበት ትመኛለህን?
4. ያራቅኸው ወይም የማታነጋግረው ሰው አለን?
5. በአንድ ሰው ስትናደድ፣ ንዴትህን ለማቃለል ለትንሽ ቀን ታኮርፋለህን?
6. በደል አድርሶብኛል ብለህ ስላሰብከው ሰው ለሌሎች መጥፎነቱን ትናገራለህን?
7. ከቅርብ ቤተሰብህ ውስጥ ላደረገብህ ወይም ላደረገችብህ ነገር የተቀየምከው ሰው አለን?
8. ከወንድሞችህ ወይም ከእህቶችህ ጋር ስትጨቃጨቅ፣ ከዚህ በፊት ያደረጉብህን ነገሮች ታነሳለህን?

# በሰንበት ቀን መልካምን አድርግ

# 26

**ዓላማው**

እያንዳንዱ ወጣት ወንድ የሰንበትን ቀን መሰረተ ሐሳብ ያውቃል እናም በደንብ ከማክበር የሚመጣውን በረከት መቀበል ይፈልጋል።

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች
   ሀ. ለየአንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቅዱሳን መጻሕፍት።
   ለ. አንድ መሐረብ ወይም የተቋጠረ ትንሽ ገመድ።
   ሐ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ እርሳስ።
2. “ተገቢ የሰንበት ተሳትፎዎች” የሚለውን የሚታደል ጽሑፍ ቀጂ ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ አዘጋጅ።
3. *ለወጣቶች ጥንካሬ* ከሚለው ከገጽ 16 እና 17 ላይ ስለ እሁድ ጠባይ የተሰጠውን ምክር ከልስ።

**ለትምህርቱ እድገት የቀረበ ሐሳብ**

**“በሰንበት መልካምን ማድረግ ተፈቅዷል”**

ተሳትፎ

ወጣቶቹ በአዳኛችን ጊዜ እየኖሩ እንደሆነ አድርገው እንዲገምቱ አድርግ፣ እና በታሪክ በዚያን ጊዜ በሕጉ መሠረት የሰንበትን ቀን በቀድስና የሚጠብቀው ማን እንደሆነ ሊያዩ እንደሆነ ግለጽ።

እያንዳንዱ ወጣት ወንድ በመሐረቡ ወይም በገመዱ ላይ ያለውን ቋጠሮ ለመፍታት እንዲሞክሩ ፍቀድ። አንድ ወጣት ቋጠሮዎቹን በሁለቱም እጆቹ የሚፈታ ከሆነ፣ ሰንበትን በቀድስና እንዳልጠበቀ ንገረው፣ ነገር ግን ለምን እንደሆነ አትግለጽ። በአንዱ እጁ ብቻ ከፈታው፣ የሰንበትን ቀን በቀድስና እንደጠበቀ ንገረው። ወጣት ወንዶቹ ሁሉም ቋጠሮውን ለመፍታት እስኪሞክሩ ድረስ የሰንበትን ቀን በቀድስና መጠበቃቸውን እና አለመጠበቃቸውን እንዴት እንደምታውቅ ላለመናገርህ እርግጠኛ ሁን።

እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ተራው ከደረሰው በኋላ፣ አዳኝ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ስለሰንበት ቀን ምን መሰራት እና አለመሰራት እዳለበት ሰዎች የፈጠሯቸው ሕጐች እና ትእዛዞች እንደነበሩ ግለጽ። በአንድ እጅ ሊፈታ የሚችለው ቋጠሮ በደንብ ያልተቋጠረ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ቋጠሮውን ለመፍታት ሁለት እጆችን መጠቀም ሰንበትን እደማፍረስ ይቆጠራል። አጥንቶቻቸው የተሰበረ ወይም መጋጠሚያቸው የወለቀባቸው ግለሰቦች አደጋዎቹን ከመታከማቸው በፊት ሰንበት እስከሚያልፍ መጠበቅ ነበረባቸው። ሕንፃ ቢፈርስ እና ከፍርስራሹ ስር የተቀበሩ ሰዎች ቢኖሩ፣ በህይወት ካሉ ቆፍሮ እነርሱን ማውጣት ሕጋዊ ነበር፣ ከሞቱ ግን ሰንበት እስከሚያልፍ ድረስ ባሉበት መተው ነበረባቸው (James E. Talmage, *Jesus the Christ*, 3ኛውን ህትመት ተመልከት [ሶልት ሌክ ከተማ: The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints, 1916], ከገጽ 215-16; Cunningham Geikie, *The Life and Words of Christ* [London: Longmans, Green, and Company, የሚለውንም ተመልከት። 1903], ከገጽ 406–17)።

የቅዱስ መጽሐፍ ታሪክ

በአንድ የሰንበት ቀን ኢየሱስ ወደ ምኩራብ ገብቶ በጉባኤው ውስጥ አንድ ቀኝ እጁ የሰለለችን ሰው እንዳየ ግለጽ። በሕዝቡ መሀል የፈረሳዊያን ቡድን፣ አሁን የተወያየንባቸውን ሕጐች የፈጠሩት ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ሕጉን በማፍረሱ እንዲያዝ ይሞክሩ ነበር። እርሱን የሚይዙበትን መንገድ በመፈለግ፣ በጥንቃቄ ተከታተሉት። “በሰንበት መፈወስ ተፈቅዶአልን?” ብለው አዳኙን ጠየቁት።

- አዳኛችን ምን ያለ ይመስላችኋል?

ወጣቶቹ እንዲመልሱ አድርግ፣ ከዚያም ታሪኩን ቀጥል።

አዳኙም እንዲህ ሲል በጥያቄ መለሰ፥ “ከእናንተ አንድ በግ ያለው፣ በሰንበት፣ በጉድጓድ ቢወድቅበት ይዞ የማያወጣው ሰው ማን ነው? እንግዲህ ሰው ከበግ ይልቅ እንደምን አይበልጥም? . . .

“ስለዚህ በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዶአል” (Talmage, *Jesus the Christ*, ገጽ 214–15; ማቴዎስ 12:10–13; ማርቆስ 3:1–6; እና ሉቃስ 6:6–8 የሚለውን ተመልከት)።

የቅዱስ መጽሀፍ ጥቀስ እና ውይይት

እኛም ብዙ ጊዜ፣ እንደ ፈሪሳዊያን፣ የሰንበትን ቀን መጠበቅ ልክ ልንሰራቸው የማንችላቸው ነገሮች ስብስብ አድርገን እናያለን። ልክ አዳኛችን ለፈሪሳዊያን በሰንበት ቀን መልካምን እንዲያደርጉ እንደነገረ፣ ሰንበትን በተመለከተ ጌታ ለዘመናችን ነቢያትም ተናግሯል።

አንድ ወጣት ትምህርት እና ቃልኪዳን 59፡9–10 እነዲያነብ አድርግ።

• እራሳችንን “ከአለም አንፅተን” የምንጠብቀው እንዴት ነው?

ጥቅስ

በቂስ ብሩስ አር መኮንኪ የተነገረውን የሚከተለውን ገለፃ አካፍል፡

“ይህ ቀን . . . *ሰንበት* ይባላል፡ *ሰንበትን* በዕብራዊያን *የእረፍት ቀን* የሚለው ትርጉም አለው፡፡ *እረፍት*፣ ቢያስፈልግም፣ እንኳ በእውነተኛው መንገድ ሰንበትን የመጠበቅ እድል ነው። የበለጠ አስፈላጊው ነገር ሰንበት ለጌታ *የተቀደሰ ቀን*መሆኑ ነው— የአምልኮ ቀን፣ ሰዎች ሙሉ ነፍሳቸውን ወደ ጌታ የሚያዞሩበት፣ ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳናቸውን የሚያድሱበት፣ እናም ነፍሳቸውን በመንፈስ የሚመግቡበት ቀን ነው. . . .

“እናም ሰንበትን የማክበር ጉዳይ በዚህ ጊዜ ቅዱሳንን ከዓለማዊያን እና ከኃጢአተኞች ከሚለዩ ታላቅ ፈተናዎች አንዱ በመሆን ጸንቷል።

“እሁድ የጌታ ቀን በመሆን፣ ሰዎች የጌታን ስራ ብቻ የሚሰሩበት ቀን ነው፡፡ ጊዚያዊነት ያላቸው አላስፈላጊ ሥራዎች መሰራት የለባቸውም፣ መዝናናት አይኖርም፣ አላስፈላጊ ጉዞ አይኖርም፣ ለመደሰት በመኪና መሄድ አይኖርም፣ እናም የመሳሰሉት፡፡ ሰንበት መንፈሳዊ አምልኮ የተረጋገጠበት ቀን ነው” [የሞርሞን ትምህርት], ሁለተኛው እትም [ሶቨት ሌክ ከተማ : Bookcraft, 1966], ከገጽ 658–59)።

---

**ሰንበትን በቅድስና በመጠበቃችን የተባረክን ነን**

ታሪክ

“ልጅ በነበርኩበት ጊዜ ገንዘብ በማይገኝበት እና ሥራ በሚበዛበት በዩታ ትንሽ የእርሻ ቦታ እንኖር ነበር፡፡ በነዛ በጥንት የዕድገት ዓመታት በጋዎቹ ለእኔ በጣም አስቸጋሪ እና ማለቂያ በሌለው በማያስደስት ሥራ የተሞሉ ይመስሉ ነበር . . .

“የመፍትሔው መድኃኒት፣ ከበጋ ሥራዎች ሁሉ መሐል አስደሳች የነበረው የሰንበት ቀን ነበር። ሁላችንም እሁድ የጌታ ቀን እንደሆነ እናውቅ ነበር፡፡ አረም፣ በእርሻ መሬት ላይ የተሰጣው ድርቆሽ፣ እና ያልተሰበሰቡ እህሎች በሙሉ እስከ ሰኞ መቀመጥ ነበረባቸው፡፡

“በሰንበት መስራትን ማቆም ሁል ጊዜ ዶማን እንደመስቀል እና ወደ በቀሎ እርሻ መሬት እንዳለመመለስ ቀላል አይደለም፡፡ የተወሳሰቡ ነገሮች ነበሩ፡፡ የገንዘብ ደህንነት ማስተማመኛን ለመሰብሰብ በጋ ብቸኛው ትክክለኛ እድል ነበር፡፡ አንድ ገበሬ በዚያች በአጭር የበጋ ወራት ካልከበረ፣ ረዥሙ ክረምት የዘመመ እና አስቸጋሪ ይሆንበታል፡፡ የውኃ እጥረት በነበረበት በዩታ፣ አልፎ አልፎ በዝናብ መልክ የሚመጣው ውኃ፣ በክረምት እና በፀደይ ወራት መጠራቀም የነበረበት እና በሞቃታማው እና በበጋው ሳምንታት ውስጥ በጥንቃቄ የሚታደለው ውኃ— በይበልጥ ብዙ ጊዜ ለዚህ መልካም ብልጽግና ቁልፍ ባይሆንም እህሉ አጥጋቢ መሆን *ነበረበት*፡፡

“እያንዳንዱ እርሻ በመስኖ ግድብ የተመሰረተ ነበር፡፡ ህይወትን ከሚሰጠው ውኃው ጋር፣ ግድቡ፣ በገበሬው እና በችግሩ መሐከል ያለው ብቸኛው ነገር ነበር፡፡ መስኖ አስፈላጊ ነበር፣ አንዳንዴም ሰንበትን ለማክበር እና ላለማክበር መወላወልን ይፈጥራል፡፡ አንዳንድ ዓመት የገበሬዎቹ ተራ ሰኞ ላይ ይሆናል፣ አንዳንዴ ማክሰኞ፣ አንዳንዴ በሌላ የሳምንቱ ቀናት ላይ ይሆናል፡፡ አንዳንዴ ተራው እሁድ ቀን ላይ ይሆናል፡፡ ገበሬው ምርጫ አልነበረውም፡፡

“እንደ ማንኛውም ሰው፣ የአባቴ ተራ ለጥቂት አመታት ሰኞ ሆነ፡፡ እነዛን ዓመታት በደንብ አስታውሳቸዋለሁ ምክንያቱም ሁል ጊዜ ሰንበትን በቅድስና ለመጠበቅ በአባቴ ውሳኔ እገረም ነበር፡፡ ለእርሻውን በእሁድ ቀን መስኖ ስላወጣለት ጌታ ይወቀስዋል ብዬ አላስብም፡፡ የአባቴን ልብ ያውቃል፣ እናም እርሱ እና ሌሎቹ ገበሬዎች የሰሩበትን ሁኔታዎች ያውቃል፡፡ ሆኖም ግን፣ አባቴ ያንንም የሰንበት ስራ ቢሆን ለመተው ፈለገ፡፡ ለገበሬዎች ያንን ውኃ የማጠጣት የጊዜ ሰሌዳ ጌታ እንዳስተካከለው አመነ፣ በእርሱ ሰንበት ምንም ተራ እንደማይኖር፡፡ አባቴ የጌታን ቅዱስ ቀን ያለመጣስ ውሳኔውን በቃሉ ሲናገር በፍጹም ሰምቼው አላውቅም ነገር ግን ሕይወቱ ይህን ያንጸባርቅ ነበር፡፡

“የአባቴ ተራ በእሁድ ቀን ሲሆን፣ በሰንበት መስኖ መገደብን ለማስቀረት የቻለውን ሁሉ አደረገ፡፡ እርብ እና ቀዳሚ ማንኛውንም መስመሩን ጥሶ ከገበሬቹ የመስመር ክልል የሚፈስ ውኃ መኖሩን ይከታተላል፡፡ ከእያንዳንዱ ግድብ የሚገኘውን ውኃ ያጠራቅማል፣ እናም እሁድ እርሻው መስኖ ያገኛል፡፡ በጌታ ቀን ለመስራት ተገዶ የሚያውቅበትን ቀን አላስታውስም፡፡ ይህም ማለት በሌላ ቀን ስራ ይበዛበታል ማለት ነው፣ ነገር ግን አባቴ በሰንበት የሚያሳርፈው ከሆነ መስዋእትነትን ለመክፈል ፍቃደኛ ነበር፡፡

“ሁሉም ነገር ሁልጊዜ የሰመረለት ይመስላል፡፡ ለዓመታት እንደተመለከትኩት፣ መንፈሳዊነቱ እና ቁራጥነቱ ጌታ ትዕዛዛቱን ለማክበር የሚለፉትን እንደሚባርክ ለኔ ምስክርነት ሆነ፡፡

“ከዚያም እምነቱን በልዩ ሁኔታ የሚፈትን አንድ ዓመት መጣ፡፡ በዚያን ዓመት የሚያቃጥለው የበጋ ሙቀት፣ ድርቅን በማስከተል፣ ቀደም ብሎ የመጣ ይመስል ነበር። ፀሐዩ ሁሉንም ነገር ጠበሰው፣ ቀናቶቹ ቀስ ብለው ነበር የሚያልፉት፣ –የግቢ መስክ፣ የአትክልት ቦታን፣ እና እርሻው በሚያቃጥለው ፀሐይ የተነሳ ጠወለገ፡፡ ከዓመት ሁሉ የሰንበት ቀን ውኃ ተረኛ ልንሆን ሆነ! እርሻው ውኃ ያስፈልገዋል፣ እርብ እና ቀዳሚ ከመስኖ ግድብ የሚፈስ ውኃ አልነበረም፣ በዚህም ምክንያት፣ እርሻው በእርግጥ ደረቀ ነበረ፡፡

“እናም በአንድ የእሁድ ማለዳ፣ እናቴ በታላቅ ጭንቀት አባቴን አነጋገረችው። ዮሴፍ ቢያንስ በግቢ መስክ ላይ እና በአትክልት ቦታ ውኃ ከግድቡ መልቀቅ አለብህ። እየተቃጠሉ ነው፣’ አለችው።

“እናም ተቃጥለዋል። ሁሉም ነገር ውኃ በማጣት እየተቃጠለ ነበር። ምንም አማራጭ አልነበረም። እርሻው ውኃ ማግኘት ነበረበት፣ እና አባቴም መስኖውን የመገደብ ተራውን ቢያሳልፍ፣ እስከሚቀጥለው እሁድ ውኃ አይኖርም ነበር። እርሻው እስከሚቀጥለው ሳምንት በፍጹም አይደርስም ነበር።

“እናም፣ ለእሁድ ስብሰባው ከመልበሱ በፊት፣ አባቴ አካፋውን በትከሻው ላይ ተሸክሞ፣ ከቤት ወጣ። የዛንለት ጠዋት ዳገቱን መውጣት ለእርሱ በጣም የሚያበሳጭ ነበር። ይህን ሁሉ ዓመት የዚያን ዕለት ቀን ስራ ለማስቀረት ለፋ፣ እናም አሁን ተያዘ። ጌታ እንደማይወቀሰው እርግጠኞች ነበርን፣ አሁንም፣ አባቴ ሌላ ዘዴን ማግኘት በጣም ፈለገ።

“ከመስኖው ቦይ ደረሰ እና የሸራውን መገደቢያ በቦታው አስቀመጠ፣ ነገር ግን ሌላ ነገር ከመስራቱ በፊት፣ አሁንም ቦዩ ላይ እንዳጐነበሰ፣ ቆም ብሎ አሰላሰለ። ምን ማድረግ ይችል ነበር? ሰንበትን ለመጠበቅ የጌታን ትዕዛዝ አሰላሰለ። እንዲሁ በከንፈሩ ብቻ ሳይሆን በህይወቱ በእውነት ያንን ያምን ነበርን?

“በሐሳብ ተመስጦ እንዳለ፣ ሊረሳው የማይችለው፣ ኃይል ያለው መልእክት በውስጡ ተሰማው፣ ‘መገደቢያህን ወዲያ በል። አካፋህን እና መሣሪያዎችህን አንሳ። እኔ በጥንቃቄ ሁሉንም ነገሮች አደርግልኃለሁ። ከቀኑ ቀደም ብሎ ላይሆን ይችላል፣ ነገር ግን እኔ ጥንቃቄን አደርግልሃለሁ። በጋውን በተመለከተ ለኔ ተወው። እኔ አዘጋጅልሀለሁ።’

“አባቴ ቀጥ ብሎ ተነሳ። ማንም በዙሪያው አልነበረም። ወደ ሰማይ ተመለከተ። ሰማዩ ንጹህ እና ብሩህ ነበር፣ ደመናም አይታይም። የታፈነን እና የተጨናነቀን ቀን ሊያስከትል ደረቅ ንፋስ ይነፍስ ነበር።

“በሚያቃጥለው የፀሐይ ሐሩር እና በደረቀው እና በአቧራማው ደረቅ መሬት፣ አባቴ የሸራውን ግድብ በማንሳት፣ ቦዩንም ትቶ፣ ወደ ቤት ተመለሰ። ለእርሱ ተነግሮታል። ያንን ያውቃል። እንዴት ጥንቃቄ እንደሚደረግለት አያውቅም፣ ነገር ግን ቃል እንደተገባለት ያውቃል። እርሻውን በሕይወቱ ሙሉ ላመነው ኃይል በመተው ለበሰ እና ወደ ሰንበት ስብሰባው ሄደ።

“ከስብሰባቸው ወደ ቤት ሲመለሱ፣ ሰማዩ አሁንም ንጹህ ነበር፣ አየሩ ይሞቃል፣ እርሻው ከሚያቃጥለው ፀሐይ በታች ደርቋል። ምንም የዕረፍት ምልክት በማይታይበት ሁኔታ፣ እናቴ፣ አሁንም ስለ አትክልቱ ቦታ በጣም ተጨንቃ፣ የዚያን ዕለት ጠዋት ያገጠመውን ላልገለጸላት፣ ለአባቴ እንዲህ ስትል ተናገረች። ‘በትክክል የሚዘንብ አይመስልም፣ ስለ አትክልቱ ቦታ ምን ልታደርግ ነው?’

“በሁኔታው በማዘን በዚያን ቀን አባቴ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ መስኖው ግድብ ወጣ፣ በማመንታት መገደቢያውን በቦዩ ውስጥ አስቀመጠ፣ ከዛን ግን ቆም በማለት፣ በራሱ አጠራጣሪ እምነት ተደነቀ። ‘እምነትህ የት አለ? እራሱን ጠየቀ . . .

“በአዲስ ውሳኔ ተሞልቶ፣ መገደቢያውን ከጉድጓዱ ላይ ጎትቶ ተራራውን ወረደ፣ ዳግም በፍጹም በሰንበት ወደ ቦዩ ላለመሔድ ወሰነ።

“ከዳገቱ ወደታች ሲወርድ፣ ዓይኑን ወደ ሰማይ አነሳ እና ዳመና ሲሰበሰብ አየ። በሰዓት ውስጥ ዝናቡ እንደወራጅ ውኃ መጣ። ደረቁ መሬት በሚያስፈልገው እርጥበት ራሰ፣ የግቢ መስክም፣ የአትክልት ቦታ፣ እና እርሻዎቹ ለመለሙ።

“ያ ዝናብ ተአምር ነበር፣ ነገር ግን ጅማሬው ብቻ ነበር። በጋ ገና መጀመሩ ነበር። የሚያቃጥሉት የሐምሌ እና የነሐሴ ወራቶች ወደፊት ተቀምጠዋል። አባቴ ግን ጭንቀት አልነበረበትም፣ ሕግን በሰጠው እና ለመታዘዙ መንገድን በሚያዘጋጀው ቃል ተገብቶለታል።

“በሚቀጥለው ሳምንት አንድ ጐረቤቱ እሁድ ውኃ የማጠጣት ተራውን ለቀዳሚ እንዲለውጠው አባቴን ጠየቀው። አባቴ ተደሰተ። ቀዳሚ በዚያ በአጭር ጊዜ ውስጥ የግቢውን መስክ እና የአትክልት ቦታውን ለማጠጣት ቻለ። አሁንም፣ ቀዳሚ በእነዚያ ጥቂት ሰዓታት የበቀሎ፣ የገብስ፣ እና የድርቆሹን ሰፊ የእርሻ መሬት በመስኖ ለመገደብ አመቺ መንገድ አልነበረም። ጌታ ግን በሌላ መንገድ ባረከው። በበጋ ውስጥ በየወቀቱ፣ ልክ ዝናብ በጣም ባስፈለገበት ወቀት፣ ዳመና ተከማቶ፣ ዝናብም መጣ፣ እህሎቹም ውኃን አገኙ።

“አባቴም ጌታ እንደሚጠብቀው ስላረጋገጠ በበጋ አንዴም ግድቡን አላጸዳም ወይም ለማሽላው ዘር መስመር አላወጣም። ያሉት ገበሬዎች በሙሉ በዚያ በመስኖ ግድብ ላይ ጥገኛ የሆኑበት ይህ፣ ደረቁ ዩታ ነበር፣ ነገር ግን በዚህ በጋ በአባቴ እርሻ ላይ ያለው ግድብ በጥቀም ላይ ውሎ አጨውቀም ነበር። አባቴ በፊት በጋውን በሙሉ እርሻውን በመስኖ ሳይገድብ በፍጹም አሳልፎ አያውቀም፣ የዚህኛው በጋ ግን የተለየ ነበር። ይህ በጋ የጌታ በጋ ነበር፣ እናም ያዘጋጀውም እርሱ ነበር።

“በጋ ሲያልቅ አባቴ ሦስት ጭነት የድርቆሽ እህሎች፣ የተትረፈረፈን የገብስ ምርት፣ እናም የበቀሎ እሸት ለምለም እህል ሰበሰበ። የሰማይ መስኮቶች በእውነቱ ተከፈቱ፣ በርግጥም ጌታ አዘጋጀ” (Alma J. Yates, “The Unforgettable Summer,” *Ensign*, ነሐሴ 1982, ከገጽ 57–58)።

ውይይት

- በዚህ ታሪክ ገበሬው ሰንበትን በቅድስና በመጠበቅ ያደረገው ትግል ጥረት ምን ነበር?
- ጌታ ይህንን ሰው የባረከው እንዴት ነው?

• ሰንበትን በቀድስና መጠበቅ ያስፈለገው ለምንድን ነው?

ሰንበትን በቀድስና ስለ መጠበቃችን የምንቀበላቸው በረከቶች በሙሉ ይህ ገበሬ እንደተቀበላቸው ዓይነት አስገራሚ ላይሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን ትዕዛዛቱን ለመጠበቅ እምነት ካለን አስፈላጊ እና ትርጉም ያላቸው ሊሆኑልን ይችላሉ።

---

**ሰንበትን በቀድስና መጠበቅ**

ጥቀስ እና ውይይት

አንዳንድ ጊዜ በሰንበት ተገቢ የሆኑት ተግባሮች ምን ምን እንደሆኑ እርግጠኞች እንዳይደለን ግለጽ። ሰንበትን ከመጠበቅ ጋር የሚሄደውን ተግባር ለማወቅ መልካሙ መንገድ ትክክለኛውን ለመወሰን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ መጠቀም ነው። በተጨማሪም የመሪዎቻችንን ምክር መከተል አለብን።

የቁስ ሩዘል ኤም ኔልሰንን የሚከተለውን ጥቀስ አንብብ፣

“በሌሎች የተጠረዙትን የአድርግ እና አታድርግ ዝርዝሮችን በቸልተኝነት ከመከተል በላይ የሆነን ነገር ታደርጉ ዘንድ አለምናችኋለሁ። የራሳችሁን አመራር አፍልቁ፣ እናም በእነርሱ ኑሩ። ከዘመናት በፊት፣ ‘ሰንበታቴንም ቀድሱ፣ እኔም እግዚአብሔር አምላካችሁ እደሆንኩ ታውቁ ዘንድ በእኔና በእናንተ መካከል ምልክት ይሆናሉ ያለውን የጌታን መመሪያ ተከተሉ።’ . . .

“በሰንበት ቀን ጥሩ ባሕሪን በተመለከተ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ቀዱሳን መጽሐፍትን ስታጠኑ እናም ለእግዚአብሔር ያላችሁን ክብር ለመስጠት የምትመርጡትን ምልክት ስትወስኑ በቀላሉ ምላሽ ያገኛሉ” (“Standards of the Lord’s Standard-bearers,” *Ensign*, ነሐሴ 1991, ገጽ 10).

---

**ማጠቃለያ**

አጭር ፈተና

በገጽ 16 እና 17 *ለወጣቶች ጥንካሬ* ከሚለው የተሰጠውን ስለ ሰንበት ባሕሪ ምክርን ከልስ። “ተገቢ የእሁድ ስራዎች” የሚለውን ጽሑፍ ቀጂ እና አንድ እርሳስ ለእያንዳንዱ ወጣት ስጥ፣ እናም የፈተናውን የመጨረሻ ስነ-ስርዓቱን ግለጽ። ወረቀቱን እንዲጨርሱ በቂ ጊዜን ስጣቸው፣ እናም አርመው። እያንዳንዱ መልስ አዎን እንደሆነ ማሳሰብህን እርግጠኛ ሁን። እነዚህ የዘረዘርናቸው ተግባሮች በሙሉ ለሰንበት ተገቢ መሆን ይችላሉ። እነዚህን ተግባሮች ተወያይ እናም የክፍሉ አባላት ለወደፊት እንዲያዩት ወረቀቱን እንዲይዙት አድርግ፡ ሰዎች በእርሱ ጊዜ የነበራቸውን ሕጐች አዳኝ እንዳላጸደቃቸው አስታውሳቸው ምክንያቱም ሁል ጊዜ ሰዎችን መልካምን ከመስራት ያግዷቸው ስለነበር ነው። ይህ ዝርዝር አንዳንድ አስተያየቶችን ብቻ እንደያዘ እና እያንዳንዱ ወጣት ሰንበትን በቀድስና ለመጠበቅ መጣር እንዳለበት፣ መንፈስ ቀዱስም ከእርሱ ጋር መሆን እንደሚችል ደጋግመህ አሳስብ። ይህንን ካደረገ፣ በእውነቱ ይባረካል።

ሙከራ

ወጣት ወንዶቹ ለሚቀጥሉት አራት ወይም አምስት ሳምንታት በእያንዳንዱ የሰንበት ቀን ስር በማህደራቸው ውስጥ ስሚታቸውን እንዲመዘግቡ አድርግ። ለዚያ ቀን ተግባሮቻቸውን መመርመር እና ስለዚያ ተግባሮች ስሚታቸውን መጻፍ አለባቸው። በዚህ ታማኝ የስራ ጥረት ወጣቶቹ ከቤተሰቦቻቸው እና ከጌታ ጋር የቀርብ ግንኙነትን እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል።

# ተገቢ የሰንበት ተሳትፎዎች

መመሪያዎች፣ በእሁድ ቀን መስራት ተገቢ ነው ብላችሁ ካሰባችሁ በተሳትፎው በግራ በኩል ባለው ባዶ ቦታ ላይ "አዎን" የሚለውን መልስ ጻፉ፡፡ በእሁድ ቀን መሰራት የለበትም ብላችሁ ካሰባችሁ "አይደለም" የሚለውን ጻፉ፡፡

_____ 1. ቅዱሳን መጽሐፍትን፣ የጉባኤ መግለጫዎችን፣ እና የቤተክርስቲያን ጽሑፎችን ማንበብ፡፡

_____ 2. የነቢያት ሕይወቶችን እና ትምህርቶችን ማጥናት፡፡

_____ 3. የቤተክርስቲያን ትምህርቶችን እና ሌላ የቤተክርስቲያን ስራዎችን ማዘጋጀት፡፡

_____ 4. በማስታወሻ ታሪክ መዝገብ ላይ መጻፍ፡፡

_____ 5. መጸለይ እና ማሰላሰል፡፡

_____ 6. ለጓደኞች እና ለዘመዶች መጻፍ ወይም መጐብኘት፡፡

_____ 7. ለሚሲዮናዊያን (ለጓደኞች፣ ለቤተሰብ አባላት፣ ለዋርድ አባላት) መጻፍ፡፡

_____ 8. መንፈስን በሚያነቃቃ ሙዚቃ መደሰት፡፡

_____ 9. በቤተሰብ የወንጌል ትምህርት መካፈል፡፡

_____ 10. የቤተሰብ የምክር ስብሰባዎችን ማድረግ፡፡

_____ 11. ከአንድ ልጅ ጋር ማንበብ፡፡

_____ 12. የቤተሰብ ታሪክ ጥናትን ማድረግ፣ የዘር ግንድ ሰንጠረዦችን መሙላትን እና በቤተሰብ ወይም በግል ታሪኮች ውስጥ መጻፍን ያጠቃልላል፡፡

_____ 13. የቤተክርስቲያን መዝሙሮችን መዘመር፡፡

_____ 14. መንፈስን የሚያነቃቁ ስነ ጽሑፎችን ማንበብ፡፡

_____ 15. ለባህላዊ ኪነ ጥበባት አድናቆትን ማዳበር፡፡

_____ 16. የቤተሰብ የቤት ምሽት ጥናትን እና ተግባሮችን ማቀድ፡፡

_____ 17. ሌሎች የቤተሰብ ተግባሮችን ማቀድ፡፡

_____ 18. አባል ያልሆኑትን ጓደኛ ማድረግ፡፡

_____ 19. ከጐረቤቶች ጋር ሕብረት ማድረግ

_____ 20. የታመመን፣ ያረጀን፣ እና ብቸኛን ሰው መጐብኘት፡፡ (ከ *Our Family*, [በራሪ ወረቀት, 1980], የተወሰደ ገጽ 2.)

# 27 አክብሮት

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ለተቀደሱ ነገሮች የበለጠ አክብሮት ይኖረዋል፡፡ |

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች
   ሀ. (በአማራጭነት) ሥዕል 6፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ሥዕል 7፣ ፀሎት ቤት፤ ሥዕል 8፣ ተወዳጅ ቤተሰብ፤ ሥዕል 9፣ ቅዱሳን መጽሐፍት፤ እና ሥዕል 10፣ 11፣ እና 12 ቤተመቅደሶች፡፡
   ለ. ለእያንዳንዱ ወጣት እርሳስ፡፡
2. የሚከተሉት የተጻፉባቸውን አስር ትለጣፊ የቃላት መስመሮች አዘጋጅ፣
   (1) አክብሮት በፀሎታችን ወቀት
   (2) አክብሮት በስብሰባ ቤቶች እና በቤተመቅደሶች
   (3) አክብሮት በቅዱስ ቁርባን ስብሰባ እና በክፍል ውስጥ
   (4) አክብሮት በቤታችን ውስጥ
   (5) አክብሮት በንግግራችን
   (6) አክብሮት ለቤተሰባችን እና ለጓደኞቻችን
   (7) አክብሮት ለመሪዎቻችን
   (8) አክብሮት ለሰውነታችን
   (9) አክብሮት ለተፈጥሮ
3. “በዚህ ትምህርት መጨረሻ የሚታደል ጽሑፍን በመጠቀም የእኔ አክብሮት ቁጥር ካርድ” የሚለውን ቀጂ ለእያንዳንዱ ወጣት አዘጋጅ፡፡

---

**ለትምህርቱ እድገት የቀረበ ሀሳብ**

**አክብሮት ለተቀደሱ ነገሮች የሚኖረን ክብር ነው**

ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት

*አክብሮት* . . .ነው የሚለውን ጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ

• ይህን ዓረፍተ ነገር እንዴት መጨረስ ትችላለህ?

ወጣት ወንዶቹ ሀሳባቸውን ካካፈሉ በኋላ፣ *አክብሮት ለተቀደሱ ነገሮች የሚኖር ክብር ነው* በማለት ዓረፍተ ነገሩን በጥቁር ሰሌዳው ላይ እንዲያነቡ በማድረግ ባዶ ቦታውን አሟላ።

አክብሮት ለአንድ የተቀደሰ ነገር የሚኖረን የጠለቀ የፍቀር ስሜት ወይንም አመለካከት እንደሆነ አሳስብ።

• አክብሮት የሚሰማን ለምን ወይም ለማን ነው? የወጣት ወንዶችን መልሶች በዚስ ሳትሰጥ አዳምጥ፡፡

አማራጭ ሥዕላዊ መግለጫ

በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በአንዳንድ አካባቢዎች አክብሮታዊ አመለካከት ስለሚገባቸው ነገሮች ግንዛቤ እንዲያገኙ እንዲረዳቸው የተቀደሱ ነገሮችን ሥዕል ለወጣት ወንዶች አሳይ። ሥዕሎቹን በአንድ ላይ ወይም እያንዳንዱን በውይይት ግዜ ልታሳይ ትችላለህ፡፡

ጥቅስ

በፕሬዚዳንት ጆሴፍ ፊልዲንግ ስሚዝ የተሰጠውን የሚከተለውን አባባል አንብብ፣

አክብሮት የተቀደሰ መመሪያ ነው፡፡ ይህም የወንጌል መመሪያ ነው፡፡ አክብሮትን ለሰማይ አባታችን ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ እናሳያለን፡፡ በእሱ ፊት ፊዘኞች መሆን አንችልም፡፡ በዚህ ስብሰባ ውስጥ እርሱ ቢገኝ ሁላችንም በፀጥታ ገብተን ቦታ ቦታችንን እንደምንይዝ እርግጠኛ ነኝ። አምልኮ ቦታ ስንገባ እርሱ በዚያ መኖሩን ስለምን አናስብም?” (ጆሴፍ ፊልዲንግ ስሚዝ, *Seek Ye Earnestly* [*በትጋት ፈልግ* ] [ሶልት ሌክ ከተማ: Deseret Book Company, 1970], ገጽ 117)።

ውይይት

• ዛሬ ወደ ክፍል ስትመጣ እየሱስ ክርስቶስ እዚህ እንደሚኖር ጠብቀህ ቢሆን ምን የተለየን ነገር ታደርግ ነበር?

• ለእርሱና ለቤቱ ክብር እና አክብሮትን ለማሳየት ባንችል የሰማዩ አባታችን ምን ይሰማዋል ብለህ ታስባለህ?

### በፀባያችን እና በድርጊታችን አክብሮትን ማሳየት እንችላለን

ጥቁር ሰሌዳ፣ የቃላት ዝርዝሮች፣ እና ውይይት፣

*አክብሮትን ማሳየት አለብን*፣ የሚለውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ፡፡

ለወጣት ወንዶች ዘጠኙን የቃላት ዝርዝሮች አከፋፍል፡፡ ከቃላት መስመሮቹ የበለጠ አባላት ካሉህ ክፍሉን በቡድን ክፈል፡፡

በእነርሱ የቃላት ዝርዝሮች ላይ በተገለጸው አካባቢ ውስጥ እንዴት አክብሮትን ማሳየት እንደሚችሉ ለወጣት ወንዶች አንድ ወይም ሁለት ደቂቃ እንዲያስቡበት ስጣቸው፡፡ ወጣት ወንዶቹ ሀሳቦቻቸውን እንዲናገሩ አድርግ። በትምህርቱ ላይ ያላቸውን ተጨማሪ ሀሳቦች ለሌሎች ወጣት ወንዶች እንዲያካፍሉ ፍቀድላቸው። እያንዳንዱን አርዕስት ክፍሉ በዝርዝር እንዲውያዩበት ጊዜውን በጥንቃቄ ተጠቀም። ያለህን ማንኛውንም ሐሳብ ተጠቀም፣ ወይንም የሚከተለውን መልዕክት እንዳስፈላጊነቱ ተጠቀም።

የመጀመሪያውን የቃላት ዝርዝር የያዘውን ወጣት ጥራ።

ጥቅስ

(1) *አክብሮት በፀሎታችን ወቀት* (አልማ 46፥13 ተመልከት)

"በእነዚህ የጥድፊያ ቀናቶች ውስጥ፣ ብዙዎቻችን አምብዛም ለጸሎት በቂ ጊዜ የለንም፡፡ እና ብዙዎቻችን በጭራሽ አንጸልይም፡፡ ነገር ግን ስንጸልይ—በችኮላ ልናደርገው ይገባልን? ጸሎትን መስማት የሚችለው በጌታ ቦታ እራሳችሁን አድርጉ። ጸሎቱን ሳይገልጽ በፍጥነት የሚጸልየው ሰው ጥቂት እና ፈጣን የተዘበራረቁ ቃላት ትኩረት ትሰጣላችሁን? እናንተ [ወላጆች ብትሆኑ] እና ልጆች በፍጥነት እናንተ ዘንድ ቢመጡ እና ትንፋሽ እያጣራው በችኮላ እናንተን ለርዳታ ቢጠይቋችሁ እና ከዚያም ወደ ሌላ ፍላጐታቸው ቢሮጡ ትደሰታላችሁ?" (Mark E. Petersen, *Your Faith and You* [ሶልት ሌክ ከተማ: Bookcraft , 1953], ከገጽ 14-15)።

ሁለተኛውን የቃላት ዝርዝር የያዘውን ወጣት ጥራ፡፡

(2) *አክብሮት ፀሎት ቤቶች እና በቤተመቀደሶች* (ትምህርት እና ቃልኪዳን 109፥21 ተመልከት)

የአማካሪው አቀራረብ

የስብሰባ ቤቶች እና ቤተመቅደሶች ለጌታ የተሰጡ መሆናቸውን ግለጽ፡፡ በውስጣቸው ካለን የእሱ መንፈስ ከእኛ ጋር እንዲሆን እንጸልያለን፡፡ ተናጋሪዎችን በማዳመጥ፣ መዝሙሮችን በመዘመር፣ እና በጸሎቱ መዝጊያ "አሜን" በማለት አክብሮትን እናሳያለን፡፡ በሰዓት መገኘት፣ በፀጥታ ሥፍራዎቻችንን መያዝ፣ እና በማንኛቸውም መንገድ እስከ ጸሎቱ ፍጻሜ መቀየት አክብሮትን ማሳየትን ነው።

ነቢዩ ዮሴፍ እስሚዝ እንዳለው አንድ "ስብሰባ ከመጠናቀቁ በፊት አቋርጦ የሚሄድ ሰው ስብሰባውን እንደመዘለፍ ነው . . . በማብቂያው ካልሆነ በስብሰባ ወቀት ወጥቶ የሚሄድ ሰው አይኑር" (History of the Church 5፥388–39)።

በቤተክርስቲያን ሕንጻ ውስጥ ክፍሎችን፣ ዕቃዎችን መጽሐፎችን በጥንቃቄ እና በክብር መያዝ እንዳለባቸው አስረዳ፡፡ ያለ ጥንቃቄ መያዝ ወይም በመዝሙር መጽሐፍቶች፣ በግድግዳዎች ወይም በዕቃዎች ላይ መጻፍ የአክብሮት ጉድለት ነው፡፡

ሶስተኛውን የቃላት ዝርዝር የያዘችውን ወጣት ጥራ።

(3) *አክብሮት በቅዱስ ቁርባን ስብሰባ እና በክፍል* ዕብራዊያን 12፥28 ተመልከት)።

ከልባዊ ፍልጐት ጋር ለማዳመጥ እና ለመማር በተገቢው ለብሶ መምጣት የአክብሮት ፀባይን እንደሚያሳይ አስረዳ። አለባበሳችን በምናደርገው ነገር ላይ ተጽዕኖን ያሳድራል። በፅዳት እና በጥሩ ሁኔታ ስንላበስ መልካሙን እንሰራለን። አንድ ሰው በሚናገርበት ጊዜ ሌሎችን ማስጨነቅ እና በትምህርት ክፍል-ጊዜ መረበሽ አስጸያፊ ነው። ይህንን ስናደርግ የጌታ መንፈስ አይኖረንም። ቅዱስ ቁርባንን በምናገለግልበት ጊዜ የአክብሮት ምሳሌነትን ማስቀመጥ አለብን። ከቅዱስ ቁርባን አገልግሎት በኋላ በፀጥታ ተመልሰን ከቤተሰቦቻችን ጋር መቀመጥ አለብን፡፡

አራተኛውን ተለጣፊ የቃላት ዝርዝር የያዘን ወጣት ጥራ።

(4) አክብሮት *በመኖሪያ ቤቶቻችን* (በተጨማሪም መዝሙር 89፥7 ተመልከት)

መኖሪያ ቤቶች "በምድር ላይ ያሉ መንግሥተ ሰማያት" መሆን እንዳለባቸው አስረዳ፡፡ ንጽህና እና መታዘዝ ለመኖሪያ ቤታችን ፍቅር እና አክብሮትን ያሳያሉ፡፡ ለመጠለያ እና ለምግብ ምስጋናን ማሳየት አክብሮት ነው፡፡ የሌሎች የቤተሰብ አባላትን የግል ኑሮ እና ንብረትን ማክበር አስፈላጊ ነው፡፡

አምስተኛውን ተለጣፊ የቃላት ዝርዝር የያዘውን ወጣት ጥራ።

(5) *አክብሮት በንግግራችን* (በተጨማሪም ትምህርት እና ቃል ኪዳን 107፥4 ተመልከት)፡፡

የሁከት ድምጾች እና አልባሌ ንግግሮች የሚያስደስቱም ሆነ አክብሮት ያላቸው እንዳልሆኑ ግለፅ። ትክክለኛ ቃላቶችን መምረጥ፣ ተራ እና አፀያፊ አነጋገርን ማስወገድ፣ እና በረጋ አነጋገር ከአክብሮታዊ የድምጽ ቃና ጋር ለአድማጮች መናገር አክብሮትን ያሳያል፡፡

ታሪክ

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል በሶልት ሌክ ከተማ ሆስፒታል የጉሮሮ ቀዶ ጥገና ህክምና ከተደረላቸው በኋላ የሚከተለው አጋጣሚ ደርሶባቸዋል። ከቀዶ ጥገናው በኋላ በተሽከርካሪ ጠረጴዛ ላይ ተኝተው ወደ ክፍላቸው በመመለስ ላይ ነበሩ።

"ስፔንሰር ጠረጴዛቸው በአሳንሰሩ አጠገብ እንደቆመ በሆነ ነገር የተናደደ የሆስፒታሉ ሰራተኛ፣ የጌታን ስም ሲያረክሰው ሲሰሙ፣ የማደንዘዣ መድሀኒት ገና አልለቀቃቸውም ነበር። እራሳቸውን በግማሽ ቢስቱም፣ እንዲህ በማለት በሲቃ ድምፅ ተማፀኑ፥ 'አባክህን እንደዚያ አትበል። እርሱም በዚህ ዓለም ላይ ካለው ነገር ሁሉ አብልጬ እወደዋለሁ። እባክህ።' ዝምታ ሰፈነ። ከዚያም ሰራተኛው እንዲህ ሲል በቀስታ ድምፅ ተናገረ፥ 'እንደዚያ ማለት አይገባኝም ነበር። አዝናለሁ።'" (Edward L. Kimball and Andrew E. Kimball, Jr., *Spencer W. Kimball* [ሶልት ሌክ ከተማ: Bookcraft, 1977], ገፅ 264)።

ስድስተኛውን ተለጣፊ የቃላት መስመር የያዘውን ወጣት ጥራ።

(6) *አክብሮት ለቤተሰቦቻችን እና ለጓደኞቻችን* (በተጨማሪም ኦሪት ዘፀአት 20፥12 ተመልከት)

አንዳንድ ሰዎች ለቤተሰብ አባላቶቻቸው አስከፊ እና መናኛ ነገሮችን በመናገር ቀልደኛ እና ጨዋ የሆኑ እደሚመስላቸው አስረዳ፡፡ ሁሉም ሰዎች በሰማዩ አባታችን አምሳል መፈጠራቸውን ለወጣት ወንዶች አስታውስ፡፡ የእርሱ ልጆች በመሆናቸው ፍቀር እና አክብሮት ይገባቸዋል፡፡ እራሳችንን ሥነሥርዓት ከጐደላቸው አባባሎች መቀጠብ፣ ወደ አእምሮቻችን የሚመጡትን እንዲህ የመሳሰሉትን ነገር መግታት ተገቢውን አመለካከት ያሳያል። አስተሳሰቦቻችንን ለመገምገም ቀም ማለት "ለመናገርም ሆነ ዝም ለማለትም" ጊዜ እንዳለው እንድንገነዘብ ይረዳናል (መክብብ 3፥7)።

ሰባተኛውን ተለጣፊ የቃላት ዝርዝር የያዘውን ወጣት ወንድ ጥራ፡፡

(7) *አክብሮት ለመሪዎቻችን* (ት እና ቃል ኪዳን 84፥35–38 ተመልከት)

የሰማዩ አባታችን ባለስልጣናትን እና የቤተክርስቲያን መሪዎችን እንዲያስተምሩን ይመርጣቸዋል። እነዚህ መሪዎች በእግዚአብሔር የተመረጡ ስለልሆኑ፣ አክብሮትን ልናሳያቸው ይገባል።

ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት

የቤተክርስቲያን የአመራር ሰንሰለቶችን በጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲመዘግቡ ወጣት ወንዶችን ጥራ። ይህ ጳጳስን፣ እስቴክ ፕሬዚዳንትን፣ ነብይን፣ ሀዋሪያትን፣

ሰባዎቹን፣ እና የቡድን ፕሬዚዳንትን ያጠቃልላል፡፡

ስምንተኛውን ተለጣፊ የቃላት ዝርዝር የያዘውን ወጣት ጥራ

(8) *አክብሮት ለሰውነቶቻችን* (1ኛ ቆሮንቶስ 3፥16–17 ተመልከት)

ሁላችንም በጣም ተፈላጊ መሆናችንን አስረዳ። እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን እናም እኛ እዚህ ያለነው ለተለያዩ እና ጠቃሚ ለሆኑ አላማዎች ነው። አካላችን አስፈላጊ፣ አስደናቂ ፍጥረት ነው፣ እና ከአክብሮት ጋር ልንንከባከበው ይገባል። ከአክብሮት ጋር ለመንከባከብ ጠንቃቃ መሆን አለብን፣ የተቀደሰ ነውና። የምናነበው፣ የምናየው፣ እና ምግብ የምንሰማው እንደምንመገበው ሁሉ ሰውነታችንን በንጽህና ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው።

ዘጠነኛውን ተለጣፊ የቃላትን ዝርዝር የያዘውን ወጣት ጥራ

(9) *አክብሮት ለተፈጥሮን*

የቅዱሳን መጽሐፍ ጥቀስ እና ውይይት

ትምሕርት እና ቃል ኪዳን 59፥18–20ን ሌሎች ካቅዱሳን መፅሐፍቶቻቸው ውስጥ እየተከታተሉት እንዳለ አንድ ሰው እንዲያነበው ጥራ።

- የሰማዩ አባታችን ለምን አላማ አትክልቶችን፣ ዛፎችን፣ እና እንሥሣትን ፈጠረ?

ለእነዚህ ፍጥረቶች የአክብሮት ሁኔታ ካለን በሚወድሙበት እና በሚበላሹበት ጊዜ ስለ እነርሱ እንደምናዝን አስረዳ። ስሞችን በድንጋይ ወይም በእንጨት ላይ የሚጽፉ እንደነዚህ አይነት ሰዎች ውበትን እና የሌሎችን ደስታ ያጠፋሉ።

---

**ማጠቃለያ**

ተሳትፎ

ለየአንዳንዱ ወጣት ወንድ የነጥብ መያዣ ካርድ እና አንድ እርሳስ ስጥ። እያንዳንዱን አረፍተ ነገር ማንበብ እንዳለበት እና በተገቢው መስመር ላይ ውጤቱን ማስቀመጥ እንዳለበት አስረዳ። ይህ የግለሰብ ግምገማ ሊሆን ይችላል። እያንዳንዱን ዐረፍተ ነገር እንዴት እንደሚያስበው ሳሆን እንዴት እደሚያከናውነው መናገር አለበት። እያንዳንዱ ወጣት የእራሱን ውጤት እንዲደምር እና ለእራሱ ውጤትን እንዲሰጥ አድርግ።

ሙከራ

እያንዳንዱን ወጣት በዝንባሌው እና በሥራው አክብሮትን ለማጐልበት የሚረዳውን በአንድ ወይም ከአንድ በበለጠ ቦታ ላይ በሚቀጥለው ሳምንት እንዲሰራ አበረታታ። እያንዳንዱ ወጣት ለእራሱ አነስተኛ ውጤት የሰጠባቸውን አካባቢዎች ከፍ ያለ ቅድሚያን በመስጠት መሻሻልንም ያገኝ ዘንድ ሀሳብህን አቅርብ።

# የእኔ የአክብሮት ነጥብ ካርድ

በመቆጣጠሪያ ዝርዝርህ ላይ እንደሚከተለው ነጥብን ስጥ፥

| | | |
|---|---|---|
| በጭራሽ 0 ነጥብ | አልፎ አልፎ 1 ነጥብ | አንዳንድ ጊዜ 2 ነጥቦች |
| ብዙ ግዜ 3 ነጥቦች | አብዛኛውን ጊዜ 4 ነጥቦች | ሁልጊዜ 5 ነጥቦች |

______ 1. በጊዜ ወደ ሰብሰባዎች እመጣለሁ።

______ 2. እኔ ተናጋሪዎችን እና አስተማሪዎችን በአክብሮት አዳምጣለሁ።

______ 3. በተገቢው ሁኔታ እለብሳለሁ።

______ 4. የክህነት ሥልጣን ኃላፊነቶቼን ከአክብሮት ጋር አሟላለሁ።

______ 5. እኔ በቤተክርስቲያን ውስጥ በፀጥታ እራመዳለሁ።

______ 6. የክህነት መሪዎቼን አልቃወምም፥ ነገር ግን በማክበር እታዘዛቸዋለሁ።

______ 7. ለፀሎት ቤቶች አክብሮት አለኝ፤ በጭራሽ በማናቸውም መንገድ ውስጥ አላጎድፋቸውም እናም ንጽሕናቸውን በመጠበቅ እረዳለሁ።

______ 8. እንስሳትን እና እፅዋትን ሁሉ በአክብሮት እይዛለሁ።

______ 9. እኔ ፀጥተኛ እና በቅዱስ ቁርባን ጊዜ ስለ አዳኜ የማስብ ነኝ።

______ 10. ጥሩ ምሳሌን እኖራለሁኝ።

______ 11. ቤተሰቦቼን እታዘዛለሁ እናም አከብራቸዋለሁ።

______ 12. ለቤተሰቤ እና በመኖሪያ ቤቴ ውስጥ አክብሮትን አሳያለሁ።

______ 13. የመዝጊያ ጸሎት እስከሚደረግ ድረስ በቤተክርስቲያን ስብሰባዎች ውስጥ በመቀመጥ እቆያለሁ።

______ 14. እኔ በታማኝነት ስሜት የአክብሮት ሰው ለመሆን እሞክራለሁ።

________ አጠቃላይ ነጥብ

| | |
|---|---|
| እኔ በጣም የአክብሮት ሰው ነኝ | 61–70 |
| አክባሪ ሰው እየሆንኩኝ ነው | 40–60 |
| ለመሻሻል እፈልጋለሁ | 29–39 |
| እርዳታን እፈልጋለሁ! | 0–28 |

# 28 ሴቶችን ማክበር

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | 1. እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ለሴቶች ታላቅ አክብሮት ይኖረዋል |
| **ዝግጅት** | 1. አስፈላጊ መሳሪያዎች፣ ለእያንዳንዱ ወጣት እርሳስ። <br> 2. ለየአንዳንዱ የክፍሉ አባል አንድ አነስተኛ መግለጫ አዘጋጅ። <br> "ለሴቶች ታላቅ አክብሮት አሳያለሁ"። <br> "እኔ ወጣት ሴቶችን አከብራለሁ እታደጋለሁ"። |

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**መግቢያ**

ታሪክ

የሚከተለውን ታሪክ በራስህ ቃል ተናገር ወይም አንብብ።

"ሄይ አይጠመኅጥ!" በማለት ጂም እየሳቀ ጮኸ። ካቲ ፊቷን አዙራ ተመልሳ ሄደች። ጂሚ ካቲን እንባ ሲተናነቃት አላወቀም ነበር። እርሱ ጉዳት የማያስከትልን አነስተኛ ቀልድ መቀለዱ ነበር። ከጥቂት ሳምንታት በፊት የካቲ ታናሽ ወንድም፣ ዳዊት፣ እርሱ ባወጣለት አይጠሞገጥ በሚል ቅጽል ስም እንደ ቀልድ ሲጠራት ሰምቶ ነበር። ከቤተሰብ ጋር ሆነው ሽርሽር በወጡ ጊዜ እንዴት "አይጠኅጥ" ካቲን ያስደነገጠቸበትን ጊዜ እያሰበ በእርሷ ላይ መሳቀን ዳዊት ይወዳል። ጂም ታሪኩን ሳይሆን ቅጽል ስሟን ነበር የሰማው።

ወዲያውኑ ጂም ካቲን ባያት በማናቸውም ጊዜ አይጠመኅጥ ብሎ ይጠራታል። የእርሱ ጓደኞች ይህንን ቀልድ በመያዝ እሷን ከአይጠኅጥ ጋር ለማወዳደር የሚችሉባቸውን መንገዶች ማሰብ ጀመሩ። በሰንበት ትምህርት ክፍል ውስጥ የሚገኙ ወጣት ወንዶች አስተማሪው በማይመለከትበት ጊዜ፣ በቅጽል ስሟ በመጥራት ያሽሚጥጧታል። ምንም እንኳን ካቲ በአንድ ወቀት በክፍሉ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ የነበረች ቢሆንም፣ ከበስተጀርባ በዝምታ መቀመጥ ጀመረች እናም ከማናቸውም ሰው ጋር በክፍል ውስጥ፣ የምታደርገውን ግንኙነት አቋረጠች። በጥቂት ወራቶች ውስጥ ካቲ ወደ ቤተክርስቲያን ተሳተፎዎች መምጣቷን አቆመች። በትክክል ተቀባይነት በማታገኝበት ሥፍራ በጭራሽ ተመልሳ ላለመሄድ መፈለጓን ለወላጆቿ ነገረች።

- እነዚህ ወጣት ወንዶች ካቲን ከመጉዳት ይልቅ እንዴት አድርገው መርዳት ነበረባቸው?

**ሁሉንም ሴቶች ማክበር ይገባናል**

ውይይት

አንድ የእግዚአብሔርን የክህነት ስልጣን የያዘ ወጣት ወንድ ሁሉንም ሴቶች ማክበር እንዳለበት አስረዳ።

- በህይወትህ ውስጥ የምታፈቅራቸው እና የምትወዳቸው ሴቶች የትኞቹ ናቸው?
- ህይወትህን እንዴት ነበር የባረኩት?
- ለእነርሱ አክብሮትን እንዴት ማሳየት ትችላለህ?

የአማካሪው አቀራረብ

አንድ ወጣት ሊያገኛቸው ከሚችላቸው አነቃቂ እና መልካም ውጤቶች አንዱ ከእናቱ እና ከእህቶቹ ጋር በስምምነት መኖር እንደሆነ ግለጽ። በትክክል ለሰው የሚያስቡ እርስ በርሳቸው የሚፋቀሩ ወንድም እና እህትን ማየት የሚያስደስት ነው። አንድ አባወራ ከሚኖሩት በጣም አስፈላጊ ግንኙነት ውስጥ አንዱ ከሚስቱ ጋር ያለው ግንኙነት እንደሆነ ግለጽ። እህቶቹን እና ሌሎች ወጣት ሴቶችን ማክበር እና ማድነቅን ያወቀ ወጣት ከሚስቱ ጋር ለሚኖራቸው ታላቅ እና አስመስጋኝ ልምድ እራሱን እያዘጋጀ ነው። ወጣት ወንዶች ለእናቶቻቸው እና ለእህቶቻቸው ዘወትር ሩህሩህ—የሚረዱ፣ አብሮ ተከፋይ፣ ተባባሪ፣ እና ለእነሱ ፍቀርን እና አድናቆትን ለማሳየት አጋጣሚ ፈላጊዎች መሆን አለባቸው።

ወጣት ወንዶች ለሁሉም ሴቶች ታላቅ አለኝታነትን እና ከበሬታን ማሳየት እንዳለባቸው በደንብ አስረዳ።

- ልጃገረዶች እንደ ሴቶች ተመሳሳይ ግንዛቤን ከማግኘታቸው በፊት ስንት ዓመት ሊሆናቸው ይገባል?

ወጣት ወንዶች እናቶቻቸው እና እህቶቻቸው መስተናገድ አለባቸው ብለው በሚወዱት ሁኔታ ልጃገረዶችን ማስተናገድ እንዳለባቸው እና የእግዚአብሔርን የክህነት ስልጣን የያዘ ወጣት በማናቸውም ዕድሜ ያሉትን ልጃገረዶች ማክበር እንዳለበት ግለጽ።

ሁኔታዎች እና ውይይት

የሚከተሉትን ሁኔታዎች አዛምድ። በእያንዳንዱ ነጥብ ላይ የክህነት ስልጣን ያዦች ሴቶችን ለማክበር ምን ማድረግ እንዳለባቸው ወጣት ወንዶች እንዲወያዩ ጠይቅ። ለእያንዳንዱ ድርጊት ወጣት ወንዶቹ ተገቢውን ማጠቃለያ እነዲሰጡ አድርግ፣

1. እህት ሀኔስ ወርስ የሰንበት ትምህርት ኮርሶችን እንድታስተምር በጳጳሱ ተጠርታ ነበር። በመጀመሪያ ቀን በደንብ ተዘጋጅታ የመጣች ቢሆንም እንኳ ልምድ ስለሌላት ተደናግጣ እንደነበር ግለጽ ነው። ከአሮናዊ የክህነት ስልጣን ያዦች ውስጥ አንዱ . . .
2. ረፋዱ ላይ ልጆች በቡድን በትምህርት ቤቱ ጅምናዚየም ውስጥ ይጫወቱ ነበር። ጨዋታው ትንሽ ወደ መጥፎ ሁኔታ እያዘነበለ በመሄዱ እና ከቁጥጥር ውጪ በመሆኑ፣ ስራውን በመቆጣጠር ላይ የነበረች፣ ሚሲስ ራውሊንስ፣ ፊሽካዋን በመንፋት በህጉ መጫወት እንዲችሉ ጠየቀች። የቡድኑ አባል . . .
3. ጆኒ፣ የዋርዱ ወጣት ሴት፣ ከትምህርት ቤት ወደ ቤቷ እየሄደች ሳለች መጽሐፎቿን ጣለች። በአጠገቧ የአሥራ ሁለት እና የአስራ ሦስት ዓመት ወጣት ወንዶች ቆመው ነበር። አንደኛው የክህነት ስልጣን ያዥ ነበር። እርሱም . . .

በሚከተሉት በእያንዳንዱ ሁኔታዎች ውስጥ የተለያዩ ወጣቶችን መድብ፣

1. አንተ መጽሐፍቶቿን ለማንሳት የሞከርከው የልጃገረዷ ወንድም ነህ። ሁሉም ጓደኞችህ እህትህ መጽሐፍቶችዋን ስትጥል ሳቁባት እና አንድም ለመርዳት የሞከረ የለም። ምን ታደርጋለህ?
2. በአንተ ፊት ከጓደኞችህ መኻል አንዱ ስለ ልጃገረዷ አስጸያፊ የሆነን ነገር ይናገራል። አንተ ምን ማድረግ አለብህ?
3. አንድ ትንሽ ወንድ ልጅ ከአንድ ትንሽ ሴት ልጅ ጋር በመጨቃጨቅ እየተደባደበ ነው። ምን ማድረግ አለብህ?

---

## ክርስቶስን ከሚመስሉ ሰዎች ምሳሌን መማር እንችላለን

ውይይት

- ለሴቶች አክብሮትን እንዴት መማር እንችላለን?።

ወጣት ወንዶች ከመለሱ በኋላ፣ በጣም ጥሩ ከሆኑት መንገዶች አንዱ የታላላቅ ሰዎችን መንገድ መከተል እንደሆነ ግለጽ።

ታሪክ

ለሴቶች ክብርን ስለ አሳዩት፣ የክርስቶስ ደቀመዝሙር ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል የሚከተለውን ታሪክ ተናገር፣

“በታላቁ የበረዶ ማዕበል ወቀት በችካጐ ከኦሄር አየር ጣቢያ ውስጥ ስለ ነበረች ሴት አንድ ታሪክ አለ። አውሮፕላኖቹ ፕሮግራማቸው ተመሰቃቅሎአል እናም በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ተስተጓጉለው ነበር። የእርሷም ገንዘብ አልቋል፣ የሁለት ዓመት ልጅ ነበራት፣ እናም ህጻኑ የቆሸሸ እና የተራበ ነበር። ሴትየዋም የሁለት ወይንም የሶስት ወር እርጉዝ ነበረች ይህን ህጻን እንዳትሸከም ተነግሮአታል ምክንያቱም፣ በሰውነቷ ላይ አስከፊ ጉዳት የሚያስከትል ችግር ሊደርስባት የሚችል በመሆኑ ነው። ህጻኑም በአየር ማረፊያው ወለል ላይ ነበር። ሴትዩዋም ሚችጋን ለመሄድ ትኬት ለመግዛት ከአንዱ ረድፍ ወደ ሌላው ተሞክር ነበር። መስመሩ ወደፊት ሲንቀሳቀስ፣ እግርዋን ወደ ፊት በማንሳት ልጅዋን በመስመሩ ውስጥ ወደ ፊት ስትገፋው ሰዎቹ ይተቿት ነበር ። ይህም የሆነበት ምክንይቱ እርሷ ልጇን ወደ ላይ ማንሳት ባለመቻሏም ነበር።

“አንድ ሰው በፊቱ ላይ ካለ የደግነት ፈገግታ ጋር ሲቀርባት እርሷ በጭንቀት ውስጥ ነበረች። እሱም እንዲህ አለ፣ ‘ወጣት እመቤት፣ እርዳታ እንደምትሺ ይሰማኛል። የቆሸሸውን ትንሽ የሁለት ዓመት ልጅ አቀፎ አነሳው፣ እናም አፈቀረው፣ ጀርባው ላይም ዳበሰው መስቲካ ሰፋው። —ወደሚችጋን ለመሄድ እንዴት በረራ ማግኘት እንደነበረባት መስመር ወደያዙት ሰዎች ሄዶ፣ ስለ ሴትዩዋ ነገራቸው በእርሱ የመንፈስ ተፅዕኖ ከእነሱ ቀድማ እንድትሄድ ፈቀዱላት። ወደ በረራው ወሰዳት እናም በጉዞ መንገዷ ላይ እንድትሆን አደረጋት አውሮፕላኑን እንደተሳፈረች ‘ምን ዓይነት ድንቅ ሰው ነው፣ ስሙን እንኳን አላወቅም።’ ብላ ለእራሷ አሰበች። ነገር ግን ከጥቂት ቀናት በኋላ፣ የፕሬዚዳንትን ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦልን ፎቶ በጋዜጣ ላይ ካየች በኋላ ሰውየውን አስታወሰች።

“አሁን ያ ቀላል ታሪክ ነው፣ ነገር ግን ስንቶቹ ይህን ያደርጉታል? ኢየሱስ ያደርገዋል፣ እናም በምድር ላይ ኢሱስን የሚወክሉ ይህን አድርገውታል” (Norman Vincent Peale, “Remarks at President Kimball’s Eighty-fifth Birthday Dinner, 28 መጋቢት 1980,” *Ensign,* ግንቦት 1980, ገጽ 109).

የቀዱስ መጽሐፍ ታሪኮች

በታሪክ በጌታ ሥራ ውስጥ ሴቶች ስለነበራቸው ታላቅ አስተዋፅኦ ለመግለጽ ከሚከተሉት የቀዱስ መጽሐፍ ጥቀሶች አንዱን ወይም ከዚያ በላይ ተጠቀም፣

1. ሙሴ 5፥11 (ሔዋን በህይወት የሚኖሩ ፍጡራን ሁሉ እናት ነበረች።)
2. መጽሐፈ መሳፍንት 4 እና 5 (ዲቦራ የእስራኤልን ሰራዊት በከነአናውያን ላይ ወደ ድል መራች።)
3. መጽሐፈ ሩት (ሩት የዳዊት ቀድመ አያት ነበረች።)

4. 1ኛ ሳሙኤል 1 (ሃና የነብዩ የሳሙኤል እናት ነበረች።)

5. ሉቃስ 1 እና 2 (ማሪያም የኢየሱስ እናት ነበረች፣ ኤልሳቤጥ የዮሐንስ መጥምቁ እናት ነበረች።)

---

| | |
|---|---|
| | **ማጠቃለያ** |
| ውይይት | ከቤተሰብህ ሴቶችን ማክበር እንዴት እንደተማርክ አንድ ወይም ሁለት ምሳሌዎችን ተናገር። <br> የክፍል አባላት ከአራሳቸው ቤተሰብ ሴቶችን ማክበርን እንዴት እደተማሩ ምሳሌዎችን እንዲያካፍሉ አድርግ። |
| የሚታደል ጽሑፍ እና ሙከራ | ለእያንዳንዱ ወጣት አንድ እርሳስ እና ትንሽ ያዘጋጀኸውን ጽሑፍ ስጥ (“ዝግጅት” የሚለውን ተመልከት)። ለሴቶች ታላቅ አክብሮትን ለማሳየት ማድረግ የሚገባቸውን ሁለት ወይም ሦስት የተወሰኑ ነገሮችን ከጽሁፋ በስተጀርባ እንዲጽፉ አድርግ። በመጪው ሳምንት ውስጥ ይህን ለመፈጸም አቀድ እንዲያወጡ አድርግ። ኃላፊነታቸውን ዘወትር ሊያስታውሱ በሚችሉበት ቦታ አቀዳቸውን እንዲያኖሩ የክፍሉን አባላት አበረታታ። |

# ዘለዓለማዊ ቤተሰብ


# 29

**ዓላማው**

እያንዳንዱ ወጣት ቤተሰቡ ዘላለማዊ ቤተሰብ እንዲሆን የመርዳትን አስፈላጊነት ይገነዘባል።

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች
   ሀ. ለየአንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. "እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ"። የሚለው መዝሙር (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ ገጽ* 2-3) አንድ ቅጂ።
   ሐ. ለየአንዳንዱ ወጣት ወንድ እርሳስ እና ወረቀት።
   መ. ጥቀሶችን ምልክት ለማድረግ እርሳሶች።
2. ሶስት ሰፋፊ ክብ ወረቀቶችን ቁረጥ እና በየአንዳንዱ ክብ ላይ የሚከተለውን ፃፍ፣




**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

## ከውልደት በፊት ቤተሰባዊ ህይወት

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

"ከውልደት በፊት ቤተሰባዊ ሕይወት" የሚለውን ክብ አንሳ እና ከጥቁር ሰሌዳው አናት በስተግራ በኩል አስቀምጥ።

• ከመወለዳችን በፊት የት እንኖር ነበር?

ወጣት ወንዶቹ መልሱን ለማግኘት ይረዳቸው ዘንድ የሚከተሉትን ጥቀሶች ጮክ ብለው እንዲያነቡት እና እንዲወያዩባቸው አድርግ፣ የሐዋሪያት ሥራ 17፥28–29 ዕብራዊያን 12፥9፣ እና ትምሕርት እና ቃል ኪዳን 76፥24። እያንዳንዱ ወጣት በእነዚህ ጥቀሶች ላይ ምልክትን እንዲያደርግ አሳስብ። እንደማጣቀሻም ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።

• የመንፈሳችን አባት ማን ነው? (እኛ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች፣ እንዲሁም የእርሱ የመንፈስ ልጆች ነን። እርሱ የመንፈሳችን አባት ነው።)

ወጣት ወንዶቹ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ መልሳቸውን "ከውልደት በፊት ቤተሰባዊ ሕይወት" ከሚለው ክብ ሥር በጥቁር ሰሌዳ ላይ ጻፍ። እግዚአብሔር የመንፈሳችን አባት እና የሰማይ አባታችን እንደሆነ አሳስብ። ከመውለዳችን በፊት ከእርሱ ጋር ኖረናል እናም ወደ ምድር ከመምጣታችን በፊት አስተምሮናል።

ጥቀስ እና ውይይት

አንድ ወጣት ወንድ በብርግያምያንግ የተብራራውን ከሰማዩ አባታችን ጋር ስላለን ግንኙነት የሚከተለውን መገለጫ እንዲያነብ አድርግ፣

"እያንዳንዳችሁ ከሰማይ አባታችን ጋር በጽኑ እንደምትተዋወቁ ልነግራችሁ እፈልጋለሁኝ . . .፣ ከእርሱ ጋር በደንብ ለመተዋወቅ እየፈለጋችሁ ቢሆንም ቀሉ፣ ሀቁ፣ እናንተ ቀድሞ የምታውቁትን እንዲያው ከመርሳታችሁ በስተቀር በቤቱ ያልነበረ እና ከዓመት ዓመት ከእርሱ ጋርም ለመቀራረብ የማይፈልግ አንድም ነፍስ በመካከላችሁ የለም።

"ዛሬ ያለው ሁሉ የህያው አምላክ ወንድ ልጅ እና ሴት ልጅ ነው" (*Discourses of Brigham Young* [የብርግሃም ያንግ ንግግሮች] sel. John A. Widtsoe [ሶልት ሌክ ከተማ: Deseret Book Co., 1954], ገጽ 50)።

• ከምድራዊ ወላጆችህ በተለየ፣ አንተ የማን ወንድ ልጅ ነህ? (የሰማዩ አባት።)

የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውን አስፈላጊነት ዘወትር የማስታወስን ጠቀሜታ አሳስብ።

• ከሰማይ አባት ጋር መኖር ምን ይመስል ነበር ብለህ ታስባለህ?

ጥቀስ — እኛ ማን መሆናችንን የሚገልጸውን በፕሬዚዳንት ሀሮልድ ሊ. ቢ የተሰጠውን መግለጫ አንብብ፣

"ሁላችሁም የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ናችሁ። ዓለም ከመፈጠሩ በፊት መንፈሳችሁ በተደራጀ እና በላቀ ሁኔታ ተፈጥሮዋል፣ ኖሯልም። በዚያ ቀድመ ምድራዊ ህይወት ለተወሰኑት ትዕዛዛት ታዛዦች በመሆናችሁ ሥጋዊ ሰውነትን በማግኘት ተባርካችኋል። አሁን ለመጣችሁለት ቤተሰብ እና በዚህም ቤተሰብ ወደ መጣችሁለት ህብረተሰብ ተወልዳችኋል . . .

"ደግማችሁ ደጋግማችሁ ለእራሳችሁ፣ የጀማሪ ክፍል ያስተማራችሁን 'የእግዚአብሔር [ወንድ ልጅ ወይንም ሴት ልጅ] ነኝ' የሚለውን እንድትሉ እና ማን እንደሆናችሁ እራሳችሁን በማወቅ እና ይህን በማድረግ ህይወታችሁን ደስተኛ እና በበለጠ ፍሬያማ ለሚያደርጉ ለነዚያ መርሆዎች ዛሬውኑ ቀርብ ሆናችሁ መኖርን እንድትጀምሩ እጠይቃችኋለሁ")። (በ Conference Report, ጥቅምት 1973, ክገጽ 7,10; ወይም *Ensign*, ጥር 1974, ክገጽ 5–6)።

ተሳትፎ — እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ትንሽ ቁራጭ ወረቀት እና እርሳስ ስጥ። የሚከተለውን እንዲጽፉ አድርግ፣ "የእግዚአብሔር ልጅ መሆኔን በፍጹም አልረሳም" ቅዱሳን መጽሐፍትን በሚያነቡበት ጊዜ እንደ ማስታወሻ እንዲጠቀሙበት ግለጽ።

ውይይት — • እንደ ምድራዊ ወላጆቻችን ለመሆን ማደግ እንችላለን፣ ነገር ግን እንደ ሰማያዊ ወላጆቻችን መሆን ማለት ምን ማለት ነው? (ሰማያዊ ወላጆቻችን እንድንኖር በሚፈልጉበት መሰረት መኖር እና እንደርሱ የሚያደርጉትን ማድረግ ማለት ነው።)

• አንተ የእግዚብሔር ልጅ እንደሆንክ ማወቁ ለምን አስፈላጊ ሆነ? (ይህንን መረዳት እግዚአብሔርን ለመከተል እና እንደ እርሱ ለመሆን የምትፈልጉትን ብርታት ይሰጣችኋል።)

• ይህ እውቀት እኛን በቤተሰቦቻችን ውስጥ እንዴት ሊረዳን ይችላል? ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸውን እንድናስታውስ ሊረዳ ይገባል። ቤተሰቦቻችን ወደ ሰማይ አባታችን እንዲመለሱ ለመርዳት በምንሰራበት ጊዜ እያንዳንዱን የቤተሰብ አባል በተሻለ ሁኔታ እንድንይዘው ሊረዳን ይችላል።)

---

**ምድራዊ የቤተሰብ ሕይወት**

ውይይት — በጥቁር ሰሌዳው መኻል አናት ላይ "ምድራዊ የቤተሰብ ሕይወት" የሚለውን ክብ አስቀምጥ።

• ሰማያዊ አባታችንን ትተን ወደ ምድር ለምን መጣን? (ሥጋዊ አካል ለማግኘት፣ አዳዲስ ነገሮችን ለመማር፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እምነታችንን ለማዳበር፣ እና በእምነታችን አማካኝነት ከሰማይ አባታችን ጋር ተመልሰን እንድንኖር።)

"የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ" የሚለውን የህጻናት መዝሙር አንድ ወጣት ደጋግሞ እንዲያነብ አድርግ። በቃሉ ማንም ሰው ይህ ማለት ካልቻለ አንድ ወጣት እንዲያነባቸው አድርግ።

• የሰማዩ አባታችን በቤተሰብ ያደራጀን ለምን ይመስልሃል? (እንድንማር እና እንድናድግ ለመርዳት።)

ጥቀስ እና ውይይት — የሚከተለውን ጥቀስ አንድ ወጣት ወንድ እንዲያነብ አድርግ፣

"ለቤተክርስቲያኗ ወጣቶች ከአንድ ሐሳብ በስተቀር በልቤ ምንም ሌላ ሀሳብ የለኝም። ያም ደስተኞች እንዲሆኑ ነው። በዚህ ህይወት ከቤት በስተቀር ሌላ እውነተኛ ደስታ የሚገኝበትን ቦታ አላውቅም። ቤትን ትንሽ መንግስተ ሰማይ ማድረግ ይቻላል በርግጥም መንግስተ ሰማይን የተስማሚ ቤትን ዘለዓለማዊ ምስል አድርጌ እወስደዋለሁኝ" (David O. Mckay "Temple Marriage," *Improvement Era*, ጥቅምት 1948, ገጽ 618)።

• ቤታችሁን በበለጠ ፍጹም ተስማሚ ለማድረግ ምን ልታደርጉ ትችላላችሁ? (ወንጌልን መኖር፣ የቤተሰብ አባላት እንዲኖሩት መርዳት፣ ለወንድሞች እና ለእህቶች ደግ መሆን፣ ወላጆችን መታዘዝ ነው።)

ውይይት — • የዘለዓለማዊ ቤተሰብ አካል ለመሆን በምድር ላይ አንተ ምን ማድረግ አለብህ?

"ምድራዊ የቤተሰብ ሕይወት" ከሚለው ክብ ስር በጥቁር ሰሌዳ ላይ መልሳቸውን ዘርዝር። የወጣት ወንዶቹ መልስ—ማጠቃለል አለበት።

1. ዘለዓለማዊ ቤተሰብ መሆን እንደምንችል ማመንን።

2. በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን።

3. ለሁሉም ስህተቶችህ ንስኃ መግባትን።

4. በእውነተኛ ቤተክርስቲያን ውስጥ መጠመቅን።
5. መንፈስ ቅዱስን መቀበልን።
6. የክህነት ስልጣንን መቀበል እና ማክበርን።
7. ከቤተሰቦቻችን ጋር በቤተመቅደስ ውስጥ መታተምን።
8. የጌታን ትዕዛዛት ማክበርን።

የአማካሪው አቀራረብ

በዚህ ምድር ላይ እኛ ከቤተሰቦቻችን ጋር በምንኖርበት ጊዜ፣ እያንዳንዳችን በየዕለቱ ክርስቶስን ለመታዘዝ እና ለማክበር መጣር እንዳለብን ግለጽ። ሌሎች የቤተሰብ አባላትን መርዳት አለብን። ምድራዊ ህይወት ከዘለዓለማዊነት ጋር ሲነጻጸር በጣም አጭር ጊዜ ነው፣ ነገር ግን በዚህ አጭር ጊዜ ወቀት የምናደርገው በዘለዓለማዊ የምናከናውነውን ይወስነዋል።

---

**ቤተሰባዊ ህይወት በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ።**

የቅዱስ መጽሀፍ ጥቀስ እና ውይይት

“በጥቁር ሰሌዳው በቀኝ አናት በኩል “ቤተሰባዊ ሕይወት በሰለስቲያል መንግሥት” የሚለውን ክብ አኑር።

• አንተ ሰለስቲያል መንግሥት ምን ይመስላል ብለህ ታስባለህ?

ዮሴፍ ስሚዝም ይህን እንደጠየቀ እና እግዚብሔርም ራዕይ አደሰጠው ግለጽ። በትምህርት እና ቃል ኪዳን 137፥4–5 ውስጥ ወጣት ወንዶቹ ዮሴፍ ስሚዝ ስለ ሰለስቲያል መንግሥት ያየውን ራዕይ እንዲፈልጉት እና ጥቀሱንም ምልክት እንዲያደርጉበት አድርግ። ከወጣት ወንዶች አንዱ ቁጥር 4 እንዲያነብ አድርግ።

• ከዚህ በፊት አንተ የነበርክበት በጣም ያማረው ሥፍራ የት ነው?

ሰለስቲያል መንግሥት በምድር ከሚገኘ ማናቸውም ሥፍራ የበለጠ ድንቅ እና ውብ እንደሆነ አሳስብ።

ሌላ ወጣት ወንድ ቁጥር 5 እንዲያነብ ድርግ።

• ዮሴፍ ስሚዝ ያየው ማንን ነበር? (ወንድሙ ኦሊቨርን እና ወላጆቹን አይቷል።)

ዮሴፍ ስሚዝ ወላጆቹ እና ወንድሞቹ በሰለስቲያል መንግሥት ውስጥ ሆነው ሲያገኛቸው ምን ያህል ደስተኛ እንደነበር ወጣት ወንዶች እንዲረዱ እርዳቸው። ብቁ ሆነው የኖሩ ከሆነ በሰለስቲያል መንግስት ውስጥ በቤተሰብ ለዘለዓለም መኖር እንደሚችሉ ያውቃል።

እያንዳንዱ ወጣት በሰለስቲያል መንግስት ከሰማይ አባታችን ጋር በቤተሰብ የመኖር እድል እንዳለው ግለጽ።

---

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት

የሰማዩ አባት እንዳለ እና እያንዳንዱን ወጣት እደሚወድ እንዲሁም እያንዳንዳቸው የሰማይ አባት ልጅ መሆናቸውን መስክር። በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ካለን እና እሱን ከተከተልን ወደ ሰማዩ አባታችን ከቤተሰቦቻችን ጋር እንድንመለስ ሊረዳን እንደሚችል አስረዳ። በመጪው ዓለም ከሰማይ አባት ጋር ከፍ ከፍ ካሉ ዘለዓለማዊ ቤተሰቦች ጋር መኖር እንደምንችል መስክር።

ሙከራ

“እኔ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኔን መርሳት የለብኝም” ብለው ለወጣት ወንዶች የጻፉበትን ወረቀት አስታውሳቸው።

እያንዳንዱ ወጣት ዘወትር የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን እንዲያስታውስ እና በሚቀጥለው ሳምንት ውስጥ እርሱ እና ቤተሰቡ ከሰማይ አባት ጋር እንዳይቀራረቡ ሊያግዷቸው የሚችሉትን የተወሰኑ ችግሮች ለማሸነፍ እንዲሰራ አበረታታ።


# 30 የደህንነት አቀድ

**ዓላማው**

የሰማይ አባታችን ከእርሱ ጋር ተመልሰን እንድንኖር የሚረዳን አቀድ እንዳለው እያንዳንዱ ወጣት እንዲገነዘብ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. አስፈላጊ የትምህርት መሳሪያዎች
   ሀ. ለየአንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቀዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. ቀስቶችን ምልክት ማድረጊያ እርሳስ።
   ሐ. የመንገድ ካርታ።
2. በሚከተለው ቀደም ተከተል ለማስቀመጥ ቀስቶችን አዘጋጅ፥




**ለትምህርቱ እድገት የቀረበ ሐሳብ**

**መግቢያ**

ታሪክ

ስለ ጳጳስ ቡርክ ፒተርሰን የተጻፈውን የሚከተለውን ታሪክ አንብብ ወይም ተናገር፥

“ወላጆቼ እና አያቶቼ ተወልደው ያደጉት በዩታ ነው። ይሁን እንጂ፣ እናቴ እና አባቴ የትዳር የጀመሩት በፊኒክስ ኦሪዞና ነው። ያም እኔ እና ሣስት ወንድሞቼ የደያግንበት አካባቢ ነው። በብዛት ብዙውን ጊዜ በበጋ ወቀት አባቴ እና እናቴ ሁላችንንም ከኦሪዞና ሙቀት እንድንወጣ እና ደግሞም ከቀርብ እና ከሌሎች ዘመዶቻችን ጋር እንድንደሰት ወደ ዩታ ይወስዱናል።

“ . . . በመደበኛነት ለመስራት እድሜዬ በደረሰ ጊዜ ከፊኒክስ ወደ ዩታ ብቻዬን ኼጄ በመሥራት እና ገንዘብ በማግኘት የበጋውን ወቀት እዚያ ለማሰለፍ ፍላጐቱ ነበረኝ። ይህም የሚሆነው በበጋ የእረፍት ጊዜ ነበር። በአንድ የጸደይ ወቀት ትምህርት ከመከፈቱ በፊት ለሥራ እና ከዚያም ከቤተሰቦቼ ጋር ለመሆን እንዲሁም እንደገና ትምህርት ለመጀመር እናም በበጋው ወቀት መጨረሻ ወደ ፊኒክስ ለመመለስ ወደ ሶልት ሌክ ሲቲ መሄድ እችል ዘንድ አባቴን ጠየቀሁኝ። ከአሰቡበት በኋላ ወላጆቼ ደህና ነው ብለለው ወሰኑ። በግንቦት ትምህርት ቤት ሲዘጋ፣ አባቴ ወደ ኮንትኔንታል የአውተቢስ መናኸሪያ ወሰደኝ፣ እናም ለእራሴ ገንዘብ ስለሌለኝ፣ ለሶልት ሌክ ከተማ ጉዞ ትኬት ገዛልኝ። የደርሶ መልሱን ትቶ የአንድ ጉዞን ትኬት ሲገዛልኝ ወደ ኋላ ቀርቼ ነበር። በሶልት ሌክ ከተማ መድረሱን ለማረጋገጥ ኃላፊነቱን እንደሚውስድ እና ነገር ግን እዚያ እያለሁኝ ወደ ፊኒክስ ለመመለስ ትኬት መግዛት አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ማድረግ የእኔ ፈንታ እንደሆነ ነግሮኛል። መገመት እንደምትችሉት፣ ከሥራው በኋላ ወደ ቤት ለመመለስ ጉጉት ነበረኝ ምክንያቱም በቤታችን ውስጥ ያሳለፍኳቸው የደስታ ገጠመኞች በውስጤ ይቃጠሉ ስለነበር ነው። ከሶስት ወንድሞቼ መገናኘትን ናፈቀኩኝ እናም ከወላጆቼ ጋር መሆን በጣም ደስ የሚል እና የሚያጽናና ነው።

“ሶልት ሌክ ከተማ በደረስኩኝ ጊዜ ወዲያውኑ ሥራ መፈለግ ጀመርኩኝ። ሥራም አገኘሁኝ እናም ወዲያውኑ የመጀመሪያ የክፍያ ቼክ በተሰጠኝ ጊዜ ያደረኩትን ገምቱ። መጀመሪያ አሥራቴን ከፈለኩኝ፣ እና ከዚያም የተቀረውን ገንዘብ ይዤ ወደ ፊኒክስ መመለሻ ትኬት ለመግዛት በሶልት ሌክ ከተማ ውስጥ ወደሚገኘው አውቶቢስ ተራ አመራሁኝ። የበጋው ወቀት በበቃ ጊዜ ወደ ቤት መመለስን የሚያግደኝ ነገር እንደሌለ

እርግጠኛ ልሆን ፈለኩኝ። ቤቴን በጣም ወደድኩኝ። በቀሪው የበጋ ወቅት በሙሉ እራሴን በመንከባከብ እና ወደ ቤቴ ፊኒክስ ለመመለስ የሚያስፈልገውን ነገር በሙሉ በማመቻቸት በሚገባ አስብ ነበር። ከሁሉም ነገር በላይ ከቤተሰቤ ጋር የመሆንን ልምድ ዳግም ለማግኘት ናፈቅኩኝ” (“Return Trip Ticket Home,” New Era ሚያዚያ 1974,ገጽ 5)።

• ወጣቱ ብሩክ ፒተርሰን ወደ ቤት ለመመለስ ይቻለው ዘንድ እራሱን እንዴት አዘጋጀ? (ጠንክሮ ሰራ እናም የመመለሻ ቲኬት ለመግዛት በቂ ብር አገኘ። እቤቱ ይመለስ ዘንድ እራሱን በጥሩ ሁኔታ አዘጋጀ።)

**የአማካሪው አቀራረብ**

ሁላችንም ወደዚች ምድር ከመምጣታችን በፊት ተመሳሳይ ልምድ እንደነበረን ግለፅ። የሰማይ አባታችን እርሱ ስለአዘጋጀው ምድር ገልጾልናል። ወደዚህ ለመምጣት ከመረጥን ከእኛ የሚጠበቀውን አስተምሮናል። ወደ ምድር ለመምጣት ከፈለግን ምድራው ልደታችንን እንደሚያረጋግጥልን አሳውቀናል። የጳጳስ ፒተርሰን የልጅነት ጊዜን በመሰለ ሁኔታ የሰማዩ አባታችን ለእየአንዳንዳችን የመሄጃ ትኬት ሰጥቶናል። ወደ እርሱ ዳግም ለመመለስ ወይም ላለመመለስ የሚወሰነው እዚህ እያለን በምናደርገው ነገር ነው።

**ካርታ እና ውይይት**

የመንገድ ካርታን አሳይ።

• ይህ ምንድ ነው? (የመንገድ ካርታ።)

• በጉዞ ላይ ሳለን ካርታን ለምን እንጠቀማለን? (ከቤታችን ለመድረስ እና ሳንጠፋ እንድንመለስ ይረዳናል።)

ህይወት ጉዞ መሆኑ ግለጽ። መሄጃን ለማግኘት መሪ እንደሚያስፈልገን የሰማይ አባት ያውቃል። ለእኛ ካለው ታላቅ ፍቅር የተነሳ፣ ከመንገድ ካርታ ጋር ልናወዳድረው የምንችለውን እቅድ ሰጠን። ይህን እቅድ ከተከተልን እና በኢየሱስ ክርስቶስ ካመንን፣ ከእርሱ ጋር ለመኖር ወደ ቤቱ እንመለሳለን።

• ስለ ሰማያዊ አባታ እቅድ መማር የምንችለው የት ነው? (ከነቢያት እና ከቀዱሳን መጽሐፍት።)

ቅዱሳን መጽሐፍትን አሳይ።

• ነቢያት እና ቀዱሳን መጽሐፍት የመንገድ ካርታን እንዴት ይመስላሉ? አቀጣጫን ይሰጣሉ። ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ እንዴት መድረስ እንደምንችል ያሳዩናል።)

---

## ቅድመ ምድራዊ ህይወት (ከልደት በፊት)

**የቀዱስ መጽሐፍ ጥቀስ እና ውይይት**

የ “ቅድመ ምድራዊ ህይወት” ምልክትን አሳይ።

አንድ ወጣት ወጣቱ አብርሐም 3፡22–28 እንዲያነብ እና ሌሎች ከቀዱሳን መጽሐፍቶቻቸው ውስጥ እንዲከታተሉ አድርግ።

• ስለ ቀድመ ምድራዊ ህይወት ይህ ጥቀስ ምንን ይነግረናል?

ወጣት ወንዶቹ መልስ በሚመልሱበት ጊዜ፣ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ተወያይ፤

1. እንደ መንፈስ ልጆቹ ከሰማይ አባት ጋር ኖረናል። ይህም የመጀመሪያ ደረጃችን ይባላል።
2. ስለ ሰማይ አባት እቅድ ተምረናል።
3. ወደ ሁለተኛው ደረጃችን። ወደ ምድር ለመሄድ ፈለግን።
4. ወደ እርሱ ለመመለስ ብቃታችንን ለማረጋገጥ ፈለግን።
5. ከሰይጣን ይልቅ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል መረጥን።

• የሰማይ አባትን እቅድ ባንቀበል ኖሮ ህይወታችን ምን ይመስል ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ?

የሰማይ አባትን እቅድ ባንቀበል ኖሮ የመጀመሪያ ደረጃችንን ለማስከበር እንደማንችል፣ እናም የሰይጣን ተከታዮች እንሆን እንደነበር ወጣት ወንዶች እንዲገነዘቡ እረዳቸው።

ይህን ጥቀስ ወጣት ወንዶቹ ምልክት እንዲያደርጉበት አድርግ።

ክርስቶስን ለመከተል እስከመረጥን ድረስ፣ የሰማይ አባታችንን ቤት ለቀቀን በምድር ላይ ለመኖር እድል እንደተሰጠን ንገራቸው።

“ልደት” በመባል ምልክት የተደረገበትን ቀስት እና “ምድራዊ ህይወት” በሚል የተቀባውን ምልክት ለጥፍ።

---

## ምድራዊ ህይወት (ሟችነት)

**ውይይት**

• ምድራዊ ህይወት ከቀድመ ምድራዊ ህይወት በምን ይለያል?

የሚከተሉትን ነጥቦች አጉልተህ አሳይ፣

1. ከመንፈሳዊ አካላችን በተጨማሪ አሁን ስጋዊ አካል (የሥጋ እና አጥንት አካል) አለን።
2. አሁን ከሰማይ አባት ዘንድ አይደለንም።

• ምድራዊ ህይወት ከቅድመ ምድራዊ ህይወት ጋር በምን ይመሳሰላል? የሚከተሉትን ነጥቦች ዘርዝር፦

1. ለጻኛን ወይም ሰይጣንን ለመከተል የመምረጥ ነጻነት አለን።

2. ትምህርቱን ከተከተልን እና በኢየሱስ ክርስቶስ ካመንን ከሰማይ አባት ጋር ተመልሰን መኖር እንችላለን።

የቅዱስ መጽሐፍ ጥቅስ እና ውይይት

ወጣቶቹ እንደገና አብርሃም 3፥25 እንዲያነቡ አድርግ።

• በዚህ ጥቅስ አባባል፣ ምድራዊ ህይወት ለምን በጣም አስፈላጊ ሆነ? (የጌታን ትዕዛዛት የምናከብር እንደሆነ ለማየት እየተፈተንን ነው።)

• ትዕዛዛትን ከጠበቅን፣ ምን ይከሰታል?

ወደ ሰማዩ አባታችን ቤት የሚመልሰንን ትኬት የምናገኘው በዚህ መልኩ መሆኑን አበክረህ አስረዳ።

---

**የመንፈስ ዓለም (ከሞት በኋላ ህይወት)**

ውይይት

የ“ሞት” ምልክት የተጻፈበትን ቀስት ለጥፍ።

• በሰማዩ አባታችን እቅድ መሰረት፣ በምንሞት ጊዜ ምን ይከሰታል? (መንፈሳችን ሥጋዊ ሰውነታችን ይለያል።)

• በሥጋዊ ሰውነቶቻችን ላይ ምን ይከሰታል (አዚሁ ምድር ላይ ይቀራሉ።)

• በመንፈሳዊ ሰውነቶቻችንስ ላይ ምን ይከሰታል? (ወደ መንፈስ ዓለም ይሄዳሉ።)

የ “መንፈስ ዓለም” የሚለውን ምልክት ለጥፍ።

በምድር ላይ ከመወለዳችን በፊት የነበረንን የመንፈስ ሰውነት ዓይነት አሁን እንዳለን ግለጽ። በዚያን ጊዜ እንደምናደርገው ማሰብ እና መሥራት እንችላለን።

የቅዱስ መጽሐፍ ጥቅስ እና ውይይት

በመንፈስ ዓለም ውስጥ የሚከሰተውን ለማወቅ፣ አንድ ወጣት አልማ 40፥12 እንዲያነብ እና ሌሎች ከቅዱሳን መጻሕፍቶቻቸው እንዲከታተሉት አድርግ።

• አልማ ደስተኛ ይሆናሉ የሚለው እነማንን ነው? (ጻድቃን፣ ወይም የሰማዩ አባትን ትዕዛዛት የጠበቁትን ነው።)

• ጻድቅ የሆኑ መንፈሶች የሚሄዱበት ቦታ ስሙ ምን ይባላል? (ገነት)

ይህን ጥቅስ ወጣት ወንዶች ምልክት እንዲያደርጉበት አድርግ።

እንደ አልማ 40፥3–4 አባባል መሰረት በክፉዎች መንፈስ ምን እንደሚከሰት አንብብ እናም ተወያይ። በመንፈስ ዓለም የሰዎች ደስተኛ ወይም በስቃይ ውስጥ መሆን የሚወሰነው በምድር ላይ በሚያደርጉት ድርጊት እንደሆነ ወጣት ወንዶች እንዲገነዘቡት እርዳቸው።

ይህን ጥቅስ ወጣት ወንዶች ምልክት እንዲያደርጉበት አድርግ።

---

**ቤት ከሰማዩ አባት ጋር**

የቅዱስ መጽሐፍ ጥቅስ እና ውይይት

ትንሳኤ ከመንፈስ አለም በኋላ እንደሚመጣ ግለጽ። መንፈሳዊ ሰውነታችን እና ሥጋዊ ሰውነታችን ፍፁም በማይለያዩበት ሁኔታ ዳግም ይዋሃዳሉ።

አንድ ወጣት 2ኛ ቆሮንጦስ 5፥10 እንዲያነብ አድርግ።

• በትንሳኤ ከተነሳን በኋላ ምን ይከሰታል? (ፍርድን ለመቀበል በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለን።)

“ትንሳኤና ፍርድ” የተጻፈበትን ምልክት ለጥፍ።

ኢየሱስ በፍርድ ጊዜ ወደ ሰማይ አባት ለመመለስ ብቁ መሆናችንን እንደሚነግረን ወጣት ወንዶቹ እንዲገነዘቡ እርዳቸው። ውሳኔው በሁለተኛው ግዛታችን ውስጥ እርሱን በመከተል ምን ያህል ታማኞች በመሆናችን ላይ የተመሰረተ ነው።

ከሰማዩ አባት ጋር ለዘለዓለም መኖር ምን ያህል አስደናቂ እንደሆነ አሁን ማወቅ እንደማንችል ግለጽ።

አንድ ወጣት 1ኛ ቆሮንጦስ 2፥9 ሲያነብ ሌሎች እንዲከተሉት አድርግ። ከሰማዩ አባት ጋር በመኖር የምናገኘው ደስታ በምድር ላይ ከምናውቀው ከማንኛውም ደስታ በላይ እንደሆነ አስረዳ።

ይህን ጥቅስ ወጣት ወንዶች ምልክት እንዲያደርጉበት አድርግ።

“ሰለስቲያል መንግሥት” ተብሎ የተጻፈበትን ምልክት አሳይ።

**ማጠቃለያ**

ጥቅስ

የሰማዩ አባትን እቅድ እና ወደ ሰማያዊ ቤታችን እንዴት መመለስ እንደምንችል የሚያጠቃልለውን በጳጳስ ኤች ቡርክ ፒተርሰን የተሰጠውን የሚከተለውን አባባል አንብብ፣

“እርሱ [የሰማይ አባት] ለመመለሻችን የሚያስፈልገንን ሁሉ እንደምንፈጽም ተስፋው እንደሆነ ነግሮናል። በዚህ ምድር ላይ በተወለድን ጊዜ፣ የቀድሞ ኑሮአችንን ትዝታ የሚጋርድ መጋረጃ የተዘጋብን በመሆኑ፣ ያ የቤተሰብ ተዛምዶ ምን ያህል አስደሳች እንደነበር ማስታወስ አንችልም። ስለዚህ በእምነት እንድንኖር ተመክረናል። ከአስደናቂ የሰማያዊ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን እና ወላጆቻችን ጋር ዳግም በሚያገናኘን ሁኔታ ታዛዦች እንድንሆን እና ትዕዛዛትን ለመጠበቅ የሚያስፈልገውን እምነት ለማጉልበት እየተማርን ነው።”

“ በዚህ የምድራዊ ተሞክሮ ህይወት (ሟች) በምንኖርበት ጊዜ ተገቢ የሆኑትን ነገሮች እንተገብር ዘንድ የሰማይ አባታችን ቤተክርስቲያኑን በምድር ላይ አደራጅቷል። ወደ እሱ ዘንድ ዳግም ለመመለስ ለሚሹት ሁሉ አስፈላጊ የሆኑትን ትምህርቶች እና ሥርዓቶችን ቤተክርስቲያኗ ታቀርባለች። መሪዎቻችንን የምንሰማ እና የጠየቁንን ነገሮች የምናደርግ ከሆነ፣ የዚህ ምድር ተሞክሮ ህይወታችን ሲያልቅ ወደ ሰማያዊ ቤታችን ለመመለስ የሚያስችለንን ቲኬት የመግዛት ኃይል ይኖረናል።” (Return Trip Ticket Home,” ገጽ 5)።

ምስክርነት

እንደ ሰማዩ አባት መሆን እና ከእርሱ ጋር መኖር ትዕዛዛትን ለመታዘዝ ከመጣር በላይ እንደሆነ መኞክር።

# 31

# በፆም እና በፀሎት ትጉ

**ዓላማው** — እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ከትልቁ ዓላማ ጋር መጾም ይፈልጋል፡፡

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቀዱሳን መጽሐፍት፡፡
   ለ. ብሎን እና የብሎን ማፈኛ፡፡
   ሐ. ጥቅሶችን ለማስመር እርሳሶች፡፡

**ለትምህርት ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

## ጾም ጌታ የሠጠን መሣሪያ ነው

በቁሳዊ የተደገፈ ትምሕርት

አንድ ብሎን አሳይ፡፡ ብሎን በራሱ እንዴት እንደሚጠቀም ከወጣቶቹ ጋር ተወያይ፡፡

• ይህን ብሎን ጠቃሚ እንዲያደርገው ምን ያስፋልገዋል? (ብሎን ማፈኛ፡፡)

ብሎን ማፈኛውን አሣይ እና ሁለቱም ነገሮች ጠቃሚ እንዲሆኑ፣ በአንድነት ስራ ላይ መዋል አለባቸው፡፡

ታሪክ

እኛም ደግሞ የሚረዱን መንፈሣዊ መሣሪያዎች እንዳሉን ግለጽ፡፡ ወጣቶቹ የሚከተለውን ታሪክ እንዲያዳምጡ እና በታሪኩ ውስጥ ያሉት ሰዎች የተጠቀሙባቸውን መንፈሣዊ መሣሪያዎች እንዲለዩ ጠይቅ፡፡

“በአንድ ወቅት የስቴክ ሚሲዮን ፕሬዚዳንት ሆኜ በማገለግልበት ጊዜ፣ ሚስዊዮናውያን ከአንድ በጣም ጥሩ የቤተክርስቲያን አባል ካልሆነ ነገር ግን ግሩም ከሆነች የመጨረሻው ቀን ቅዱሳን እህት ጋር የተጋባ ሰው ይገናኙ ነበር። ይህ ጥሩ ወንድም ቤተክርስተያኗን ሊቀላቀል ይፈልጋል ነገር ግን በሲጋራ ሱስ የተጠመደ ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ ሊያቆም ሞክሮ ነገር ግን እንዳልቻለ ይናገራል፣ በጣም ደካማ ነበር፡፡

“ለረጅም ጊዜ ከእርሱ ይገናኙ የነበሩ ስድስት የስቴክ ሚሲዮናዊያን ነበሩ ነገር ግን ማጨስ እንዲያቆም የሚረዳውን ጥንካሬ እንዲያዳብር ሊረዱት አልቻሉም፡፡ በመጨረሻም፣ በመንፈስ ግፊት፣ ይህንን ድካም ማሸነፍ ይችል ዘንድ አብረነው መጾም እንችል እንደሆነ ጠየቅነው፡፡ ባቀረብነው ሐሳብ ተስማማ እና ዕቅዱን ተቀበለ፡፡ ከዚያ ጾሙን *ለሁለት ቀናት* ይጾም እንደሆነ ጠየቅነው፡፡ ተስማማ፣ ስለዚህ ጾሙን ቀጠለ፡፡ ስድስቱ የስቴክ ሚሲዮናውያን፣ አጫሹ ወንድም፣ እና ባለቤቱ ሆነን ጾምን፡፡

“በጾሙ ማብቂያ ላይ፣ ሁላችንም በቤቱ ተገናኘን እና ከእርሱ ጋር በእርሱ ሳሎን ውስጥ ተንበርከክን፣ እያንዳንዳችን በየተራ ፀለይን፡፡ ጾሎቶቹ እንደአስፈላጊነታቸው ተመሳሳይ ነበሩ፤ እነርሱም፣ ጌታ ከዚህ ወንድም የማጨስ ፍላጐቱን እንዲወስድ የሚጠይቁ ነበሩ፡፡ በመጨረሻ የፀለየው እርሱ ነበር እናም በመነሳት፣ “ለማጨስ ፍላጐቱ የለኝም” ብሎ አሣወቀ፡፡ እስከዚህ ቀን ድረስ አላጨሰም፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በዋርዱ የጳጳስ ቢሮ እናም. . . . በስቴክ ውስጥ [በወጣት ወንዶች አመራር] አገለገለ፡፡ እርሱ ዛሬ በዕምነት የጠነከረ፣ የጌታ እውነተኛ አገልጋይ ነው፡፡ ጌታ በፍፁም ከእርሱ ድክመቱን ወስዶለታል እ በምትኩ የጥንካሬ ማማ አደረገው” (Hartman Rector, Jr., በ Conference Report, ሚያዚያ 1970, ከገፅ 140–41; ወይም *Improvement Era*, ሰኔ 1970, ገፅ 103)።

• በዚህ ታሪክ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉት መንፈሳዊ መሣሪያዎች የትኞቹ ናቸው? (ጾም እና ጸሎት፡፡)

ከላይ በተጠቀሰው ታሪክ ውስጥ አንድ አማኝ ሰው እንዳደረገው ሁሉ፣ ጾም የግል ሥነ-ሥርዓትን የሚያዳብር መሣሪያ እንደሆነ ግለፅ። እንዲሁም፣ ጾም ለሌሎች በርከት ላሉ ምክንያቶችም ደግሞ ይጠቀማል፡፡

## ጾምን ልባዊ ፀሎት ሊያጅበው ይገባል

ውይይት

• በጾምና ዝም ብሎ ባለመብላት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

• ከጾም ታላቅ ጥቅሞችን እንዴት ልንቀበል እንችላለን?

ከጾም ታላላቅ ጥቅሞችን ለመቀበል፣ ስንጾም ከልብ መፀለይ እንዳለብን ግለፅ፡፡ ፃዲቅ ሰዎች በእምነት በመጾማቸውና በመጸለያቸው ምክንያት ብዙ ታላላቅ ነገሮች ተፈፅመዋል፡፡

**ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት**

• ስለጾሙና ስለፀለዩ ሰዎች በቅዱሣን መፃሕፍት ውስጥ ምን ዓይነት ምሣሌዎች ይኖሩናል?

ከቅዱሳን መፃሕፍት ውስጥ ስለጾሙና ስለጸለዩ ሰዎች ምሣሌ ወጣቶቹ እንዲወያዩ አድርግ። በአጭሩ የወጣቹን ምላሾች ከተወያያችሁ በኋላ፣ ክፍሉ አልማ ምዕራፍ 17 እንዲያወጣ አድርግ። ትንሹ አልማ በጌዲዮን ምድር ሲጓዝ ሳለ፣ በሚያስገርመው እና በሚያስደንቀው ታላቅ ሁኔታ፣ የሞዛያን ወንድ ልጆች ወደ ዘረሄምላ ምድር ሲጓዙ ተገናኛቸው ግለፅ። አንድ ወጣት አልማ 17፥1–4 እንዲያነብ አድርግ። የዚህን ጥቅስ ክፍል ወጣቶቹ ምልክት ሊያደርጉበት ይችላሉ።

አልማ 17፥4 አመልክት እና የሞዛያ ልጆች ከአልማ ጋር ለመጨረሻ ጊዜ ከተገናኙ በኋላ በአስራ አራት ዓመታት ውስጥ ምን ሲያደርጉ እንደነበር ተወያዩ።

ቀጥለው ባሉት ጥቂት ቁጥሮች ውስጥ የሞዛያ ልጆች ሥራዎቻቸውን ለአልማ ሲዘግቡ አብራሩ ሌላ ወጣት አልማ 17፥9–10 እንዲያነብ አድርግ።

• የተሣካላቸው ሚሲዮናዊያን ለመሆን የሞዛያ ልጆች ምን ዓይነት ዝግጅቶችን አድርገዋል? (በእጅጉ ጾመዋል ጸልየዋል።)

• ለምንድን ነው የጾሙትና የጸለዩት? (መንፈስ ከነርሱ ጋር ይሆን ዘንድ።)

**ታሪክ**

በ1850 ዓ.ም. ሎሬንዞ ስኖው፣ እንደ ሞዛያ ወንድ ልጆች በጣም ተመሣሣይ ተሞክሮ እንደነበራቸው ግለፅ። ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሀገሪቱ ክፍት እንድትሆን፣ በጣሊያን ውስጥ በሚሲዮናዊነት ያገለግሉ ነበር።

"እርሳቸውም ዓይን አፋርና ይሉኝታ የሚያጠቃቸው ቢጤ ነበሩ፣ ነገር ግን በመንፈሣዊነት፣ የገዘፉ ነበሩ። ወዳጃቸው ከነበረ አንድ ቤተሰብ ውስጥ በጠና የታመመ ልጅ ነበር። በእርግጥ፣ ቁስ ስኖው በእውነተኛ ጾም፣ በብርቱ ፀሎት፣ በማይናወጥ እምነት፣ እና በክህነት ሀይል አማካኝነት ብቻ ያ የሦስት ዓመት ልጅ ሊድን እንደሚችል ተገንዝበዋል። በዚህ አነስተኛ የጣሊያን መንደር ውስጥ ላሉ ሰሕዝቦች የዚህ ልጅ ፈውስ ምን ያህል ግምት ሊኖረው እንደሚችል አውቀዋል።

"ልክ ከመንደሯ ከፍ ብሎ ጭር ወደ አለበት የአልፕስ ግርጌ ኮረብታዎች ከሚሲዮናዊው ጓደኛቸው ጋር በመውጣት፣ በጾምና ፀሎት መንፈስ፣ ያንን ሕፃን የመፈወስ መለኮታዊ ኃይል ክብርን ለመጠቀም ለስድስት ረጅም፣ አስጨናቂ ሰዓቶች ወደ ጌታ በቁርጠኝነት ማለዱ እናም ተማፀኑ። በመጨረሻም፣ መልሱ መጣ፣ ምላሹም አዎንታ ነበር፣ የጠየቁትንም መብት ሊሠጣቸው ሆነ።

"እንደ ትሑት የጌታ አገልጋይ፣ በፍፁም እምነት ልታልፍ የነበረች የህፃኑ ሕይወት እንደምትድን በማመን የተራራውን ጠርዝ ቁልቁል ወረዱ። ሕፃኑም በዚያን ጊዜ በሕይወት እንዲኖር በረከትና ተስፋ ተሠጥቶት ነበር። ከጥቂት ሰዓቶች በኋላም ቁስ ስኖው እና ሚሲዮናዊ ጓደኛቸው ወደ ቤት በተመለሱ ጊዜ፣ ልጁ በእጅጉ ተሽሎት እናም ወደ መዳን አዝማሚያ ደርሶ አገኙት። ቁስ ስኖው የሳቸው ጾምና ፀሎት ወደ ቸሩ የሰማይ አባት ዙፋኑ መድረሱን ተገነዘቡ። ለአመስጋኞቹ ወላጆች፣ 'የሰማያት አምላክ ይህንን ለእናንተ አደረገ" ብለው ስተያየት ሰጡ (Eliza R. Snow, *Biography of Lorenzo Snow*, [*የሎሬንዞ ስኖው የሕይወት ታሪክ*] ከገፅ 128–29 ይመልከቱ)" (Henry D. Taylor, በ Conference Report, ጥቅምት 1974, ከገፅ 18–19; ወይም *Ensign,* ህዳር 1974, ገፅ15 )።

**ውይይት**

• ለምንድን ነው የፕሬዚዳንት ስኖው ፀሎት ልባዊ እንደነበር የምናውቀው?

• ጌታ ስንጾም እንድንጸልይ እንደሚመክረን የሚሰማህ ለምንድን ነው?

• ጾም በጸሎት ላይ ምን ዓይነት ጥቀሞችን ይጨምራል?

ወጣቶቹ ለጥያቄዎቹ ምላሾች ሲሰጡ፣ የሚከተሉትን ነጥቦች አንሣ፣

1. ከዓለማዊ ነገሮች ስንለይ፣ በመንፈሣዊ ጉዳዮች ላይ ልናተኩር እንችላለን። ከኑሯችን ላይ ዓለማዊ ነገሮችን ካስወገድን፣ ጾም ትልቀ መንፈሣዊ ውጤት ይኖረዋል።
2. ጾም የበለጠ ትሑት እና በሰማዩ አባታችን ላይ የበለጠ የተመካን መሆናችንን እንዲሠማን ይረዳናል።
3. የሰማዩ አባታችን ልጆቹ በጾምና ጸሎት አማካኝነት እምነታቸውን ሲያሳዩ ይደሰታል።

---

### ጾምና ጸሎት ታላላቅ በረከቶችን ያመጣሉ

**የአማካሪው አቀራረብ**

የሞዛያ ወንድ ልጆች እና ሎሬንዞ ስኖው በጾምና ጸሎት የእርሱን እርዳታ በመፈለጋቸው ምክንያት እግዚአብሔር ታላላቅ ተአምራቶችን እንደሰራ ግለጽ። ጾምና ጸሎት እያንዳንዳችን የእግዚአብሔርን ፍቃድ ለማወቅና ለማድረግ የምንፈልግ ከሆነ ደግሞ ሊረዱን ይችላሉ። እኛም፣ በእነዚህ ምሣሌዎች ውስጥ እንዳሉት ጻድቃን ሰዎች ልዩ ለሆኑ በረከቶች ልንጾም እንችላለን።

**ታሪኮች**

የሚከተሉትን ተሞክሮዎች አዛምድ።

*ታሪክ አንድ*

በዋረንስበርግ፣ ሚዚዩሪ ውስጥ ያለ ትንሽ ዋርድ በኋይትማን አየር ኃይል ቤዝ ውስጥ ባለ የጸሎት ቤት ውስጥ ሲሰበሰብ ብዙ ዓመት ቆየ። ለመሰብሰቢያ የራሳቸው የሆነ የጸሎት ቤት እንዲኖራቸው በመፈለጋቸው ምክንያት፣ ጳጳሱ ለዋርዱ ሕንፃ ግንባታ የዕርዳታ ጥሪ አቀረበ። በሺህዎች የሚቆጠር ዶላር ተሰበሰበ፣ የጳጳስ አመራሩም ጸሎት ቤቱ የሚገነባበትን ሥፍራ ለማግኘት ተንቀሣቀሰ። የሚሄድበት ሥፍራ ሁሉ፣ ቦታው የተያዘ ነው። የጳጳስ አመራሩም ለቦታ ለወራት ያደረገው ፍለጋ ስኬት አልባ ነበር።

ልዩ በረከት እንደሚያስፈልግ በማወቃቸው፣ ጳጳሱ ስምንት ዓመት እና ከዚያም በላይ የሆናቸውን እያንዳንዱ የዋርዱ አባላት በሙሉ በአንድ በተለየ እሁድ እንዲጾሙና እንዲጸልዩ ጠየቁ። በሚቀጥለው ሰኞ ማለዳ፣ የአካባቢው ሐኪም፣ የቤተክርስቲያኒቷ አባል ያልሆነ፣ ከጳጳሱ አመራር አባል የሆነውን ወንድም ሊጉበኘው ወደ ሥራ ቦታ ሄደ። “ጆርጅ፣” አለ ሐኪሙ፣ “ቤተክርስቲያንህ ቦታ እንደምትፈልግ እሰማለሁ።”

ዶክተሩም ለጸሎት ቤት መጠኑና የሥፍራው አቀማመጥ ፍጹም ተስማሚ ወደ ሆነ ትንሽ መሬት እያሽከረከረ ወሰደው። ለአዲሷ ቤተክርስቲያን ተስማሚ የሆነ ቦታ ብቻ አይደለም ያገኘው፣ ለዋርዱ መሬቱን ያለክፍያ ነበር የሰጠው። በእርግጥ ጌታ የዋረንስበርግን ዋርድ ባርኮታል! ለመሬት የተቀጣው መዋጮ አሁን ለግንባታው ወጪ ሊውል ችሏል። ዛሬ ውብ የጸሎት ቤት በቁራጯ መሬት ላይ ቆሟል፣ እናም በጾምና ጸሎት ለተገኙት ታላላቅ በረከቶች ቋሚ ማስታወሻ ነው።

*ታሪክ ሁለት*

በትንሽ ዋርድ ውስጥ የሚኖር ዲያቆን ወደ ክህነት ስብሰባ እራሱ ብቻውን ሲመጣ እጅግ በጣም ርቀ የመጣ ሆኖ ይሰማው ነበር። ቄሶቹም፣ ምንም እንኳን ቁጥር ሁለት ቢሆኑም በቡድኑ ውስጥ ያለው ዲያቆን ብቻውን እንዳይሆን ስለዚህም ወደ ትንሿ ዋርዳቸው ብዙ ዲያቆናኖች ይመጡ ዘንድ ለመጾምና ለመጸለይ ተገናኙ እና ወሰኑ።

ቀጥሎ የነበረውም ክስተት ከዚያ ጥረት የመነጨ ነበር። በጥቅምት፣ ሁለት በዲያቆን ዕድሜ የሚገኙ ወጣት ወንዶች ተጠመቁ፤ በኅዳር፣ ሁለት ተጨማሪ ተጠመቁ፣ እና በታህሣሥ እና ጥር፣ ሁለት ዲያቆናኖች ወደ ዋርዱ ተዛወሩ፣ ቡድኑንም ሰባት አደረሱት። የክህነት ቡድኑም ደግሞ አዲስ አባላት ተቀበለ። በጥር ወር ሁለት በክህነት ዕድሜ የሚገኙ ወጣት ወንዶች ተጠመቁ። አሁን እነዚህ ወጣት ወንዶች በጸሎት የታጀበው ጾም በእርግጥ እንደሚሰራ ምስክርነት አላቸው፣ እናም በኑሯቸው ላይ ይህን የወንጌል ትምህርት በመተግበር አዲስ ፍቅር እና ጥንካሬን አዳብረዋል።

ውይይት

ይህንን ትምህርት በራሳቸው ሕይወት ላይ እንዲያውሉ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመወያየት ወጣት ወንዶቹን እርዳቸው፥

- የትኞቹን ልዩ በረከቶች ለመቀበል ነው የምትጾሙት?
- ችግሮቻችሁን ለመፍታት ጾም እንዴት ይችላል?
- ውሣኔዎች እንድታደርጉ ጾም እንዴት ሊረዳችሁ ይችላል?
- ፈተናዎችን እንድታሸንፍ ጾም ሊረዳችሁ ይችላል?
- የትኞዎቹን ፈተናዎች ለማሸነፍ ነው የምትጾሙት?
- በጾም አማካኝነት የበለጠ ግላዊ ሥነ-ሥርዓት ሊኖራችሁ እንደሚችል ይሰማችኋል? ለምን? ካልሆነስ ለምን?
- በአካላዊ ብቃት የተሻላችሁ ናችሁ እንዲሰማችሁ ጾም ሊረዳችሁ ይችላል?
- ለምንድን ነው ጾም ወደ ሰማዩ አባታችሁ የበለጠ እንድትቀርቡ የሚረዳችሁ?

ጥቀስ

“ይህ የጾም ሕግ የትምህርት ቤት አስተማሪን ዓይነት ሊሆን ይችላል። በብቃት ልንኖረው መማር የምንችል ከሆነ፣ ይህንን አስፈላጊ ህግ በመኖራችንት ምክንያት እንደ ተፈጥሯዊ ውጤት በውስጣችን ኃይልና እምነት በመመንጨቱ ምክንያት እያንዳንዱን ሌላ ሕግ በበለጠ ለመጠበቅ ይረዳናል!” (Sterling W. Sill ,“The Law of the Fast” *Ensign*, ሐምሌ 1974, ገጽ 11).

---

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት

ጾምና ጸሎት በሕይወታችን ሊኖራቸው የሚችለውን ኃይል መስክር። ጌታ እያንዳንዱን ወጣት ወንዶች እንደሚወድ እና በመንግስቱም ውስጥ ለእያንዳንዱ ልዩ ቦታ እንደያዘለት ዕውቀትን አካፍል።

ሙከራ

በሕይወታቸው አንድ ነገር እንዲፈጸም ወይም ሌላ ሰውን ለመርዳት—ለተለየ ምክንያት የሚቀጥለውን የጾም ቀን ወጣት ወንዶች እንዲጾሙ አበረታታቸው።

# አስራት

# 32

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ወንድ አስራቱን በመክፈል ለጌታ ያለውን ፍቅር ማሣየቱን ይገነዘባል እናም እንዲህ በማድረግ እርሱም ይባረካል እንዲሁም የእግዚአብሔርን መንግስት ለመገንባት ይረዳል። |

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሣን መጽሐፍት።
   ለ. ሁለት እርሳሶች እና ሁለት ቁራጭ ወረቀቶች።
   ሐ. ጥቅሶችን ለማስመር እርሳሶች።
2. ይህን ትምህርት ከመስጠትህ ከሣምንት በፊት፣ ወጣት ወንዶቹ ከወላጆቻቸው ጋር ስለ አስራት መክፈል በረከቶች እንዲወያዩ ጠይቅ። እነኚህንም ውይይቶች በክፍል ውስጥ ለማካፈል እንዲዘጋጁባቸው ጠይቅ።

---

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**ሁሉም ነገር የጌታ ነው**

የቡድን ሥራ

ወጣት ወንዶቹን በሁለት ቡድን ክፈላቸው። "ከጌታ ምን በረከቶችን ተቀብያለሁ?" የሚለውን ጥያቄ ለመወያየት ሦስት ደቂቃዎች እንዳላቸው ንገራቸው። ከየቡድኑ ለአንዱ ወጣት እርሳስና ቁራጭ ወረቀት ሥጥና የቡድኑን ሐሳቦች እንዲመዘግብ መድብ።

ጊዜው ሲያበቃ፣ እያንዳንዱ የተመደበው ወጣት የቡድኑን ሐሳቦች በክፍሉ እንዲያቀርብ አድርግ።

• ጌታ ለእኛ ያልሰጠን ነገር ምን አለን? (ምንም የለም።)

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

አንድ ወጣት ወንድ ትምህርት እና ቃል ኪዳን 104፥14–15 ሲያነብ ሌሎቹ ከቀዱሳን መጽሐፍቶቻቸው ላይ እንዲከተተሉ አድርግ። እነኚህን ጥቅሶች ምልክት እንዲያደርጉባቸው ሐሳብ ሥጥ።

• በዚህ ጥቅስ መሠረት፣ የጌታ የሆነው ነገር ምንድነው? (ሁሉም ነገር።)

• ትልቅ ንግድ፣ ትልቅ የከብት ማርቢያ ቦታ፣ እርሻ፣ ወይም ሌላ ትልቅ ሥጦታ ቢሰጥህ፣ ለሰጪው መልሰህ ጥቂቱን ክፍል ለመስጠት ፍቃደኛ ትሆናለህ? ለምን?

• ጌታ ከሰጠን ስጦታዎች ውስጥ ምን ያህሉን ነው ለእርሱ እንደንመልስ ያዘዘን? (አንድ አስረኛውን፣ እርሱም አስራት ነው።)

ውይይት

አስራት ዘለአለማዊ ሕግ መሆኑን ግለጽ። ጌታ ቤተክርስቲያኑን በምድር ላይ በመሠረተ ጊዜ ሁሉ፣ የአስራትን ሕግ አንደኛው ክፍል አድርጎታል። ለአስራት ሕግ መታዘዝ ለመዳናችን እና ከፍ ከፍ ለማለታችን አስፈላጊ መሆኑን አትኩሮት ስጥበት።

• ጌታ ሁል ጊዜ ከቤተክርስቲያኑ አባላት አስራትን የሚጠይቀው ለምን ይመስላችኋል? (ለራሳቸው የግል በረከቶች እና ዕድገት እንዲሁም ለቤተክርስቲያኑ ዕድገት።)

---

**አስራትን በመክፈል የሚመጡ በረከቶች**

ቅዱስ መጽሐፍት እና ውይይት

• አስራት እንዴት ይጠቀመናል?

ይህን ጥያቄ ከተወያያችሁ በኋላ፣ አንድ ወጣት ሚልኪያስ 3፥10–12 እንዲያነብ አድርግ። የክፍሉ አባላት እነዚህን ጥቅሶች ምልክት እንዲያደርጉባቸው ሐሳብ ስጥ።

• ጌታ በዚህ ቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ለአስራት ከፋዮች የሠጠው ተስፋ ምንድን ነው? (የሰማይን መስኮቶች ይከፍትላቸዋል እናም በረከቶችን በላያቸው ላይ ያፈሳል።)

• በፍቃደኛነት ሙሉ አስራትን ለሚከፍሉት ለእነርሱ ምን በረከቶች ይመጡላቸዋል?

ለወጣት ወንዶቹ ምላሽ እንዲሠጡ በቂ ጊዜ ስጣቸው። እውነተኛ አስራትን በመክፈል በውጤቱ ከሚገኙት ታላላቅ ጥቅሞች ውስጥ የሠላም እና የፍቅር ስሜቶች መሆናቸውን ልታመለክት ትችላለህ። እውነተኛ ደስታ የሚመጣው ለሰማዩ አባታችን ፍቅር በማሳየት ነው።

ታሪኮች

አስራት ከፋዮች የሚቀበሏቸውን በረከቶች ወጣት ወንዶቹ ለመገንዘብ እንዲረዳቸው፣ የሚከተለውን ገጠመኝ አዛምድ።

*ታሪክ አንድ*

“ጆን ፌትዘር የተጠመቀው በኮሌጅ ዘመኑ ወጣት በነበረበት ጊዜ ነው። የቤተክርስቲያን አባልነቱ በተረጋገጠ ግዜ፣ የአስራትን ክፍያ ጨምሮ በወንጌል ትምህርቶች መኖር እንዳለበት ተነግሮታል። አስራት ምን ማለት እንደሆነ በተማረ ግዜ ደንግጦ ነበር። ለሚቀጥለው ዓመት ለትምህርት ቤት የሚሆነውን ገንዘብ ለማግኘት ይሰራ ነበር። በቂ ገንዘብ አልነበረውም። ምን ማድረግ ነበረበት? ለለየ እና መረመረ እናም በሚቀጥለው የትምህርት ዓመት ለገንዘብ አጥረት የሚዳርገው ቢሆንም እንኳ፣ በመጨረሻ አስራቱን ለመክፈል ወሰነ። አርክቴክት ለመሆን እያጠና ነበር እና፣ አንድ ቀን የንድፍ ሥራ እንዲሰራ ተመደበ። ይህም የንድፍ ሥራ የገንዘብ ሽልማትን አስገኘ። አቶ ፌትዘር በደስታ ሰክሮ ነበር። ጌታ ምንግዜም አስራትን አስራትን ሲከፍሉት በረከቶች የተናገረውን አስታወሰ። ለእርሱም ምስክርነት ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወዲያውኑ ገቢውን እንደተቀበለ ሁል ግዜ አንድ አስረኛውን ለጌታ ይከፍላል እና ሁልግዜም በእጅጉ እንደተባረከ ነው” (*The Epic of the Latter-day Saints* [Sunday School Course Nine teacher’s manual, 1971], ገጽ 183)።

• ምን ዓይነት ውሣኔ ነበር ወንድም ፌትዘር ማድረግ የነበረበት? (አስራት መክፈል ወይም ገንዘቡን ለትምህርት ቤት ማስቀመጥ።)

• አስራት በመክፈል እንዴት ነበር ሊባረክ የቻለው? (ትምህቱን ለመጨረስ እና ተሰጥዎችን ከሌሎች ጋር ለመካፈል የረዳውን የገንዘብ ሽልማት አገኘ።)

*ታሪክ ሁለት*

የሚከተለውን ታሪክ ፕሬዚዳንት ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ ስለ እናታቸው እንደተናገሩ ግለጽ።

“በልጅነቴ ዘመኔ የተከሰተውን ሁናቴ በጣም ቁልጭ አድርጌ አስታውሳለሁ። እናቴ ልተመግባቸው የሚገባት ብዙ ቤተሰብ ያላት፣ መበለት ነበረች። በአንድ የፀደይ ወራት የድንች ጉድጓዶቻችንን በከፈትን ግዜ፣ ወንዶች ልጆችዋን የተመረጡ ድንቾቻችን እንዲጭኑ አደረገች እና ወደ አስራት መቀበያ ቢሮ ወሰደቻቸው፣ በዚያን ወቀት ድንች ጠፍቶ ነበር። በዚያን ጊዜ ትንሽ ልጅ ነበርኩኝ እናም ቡድኑን አጅቤ ነበር። ወደ አስራት መቀበያው ቢሮ ደጃፍ ነድተን፣ ድንቾቹን ለማራገፍ ዝግጁ በሆንን ጊዜ፣ አንደኛው ፀሐፊ ብቅ ብሎ ለእናቴ እንዲህ አለ፣ ‘መበለት ስሚዝ፣ ለአንቺ አስራት መክፈል አሳፋሪ ነው . . .።’ አስራት በመክፈሏ እናቴን ተቃወማት፣ እናም ጠንካራ ሆነው እና መስራት እየቻሉ ከስራት ቢሮው የሚረዱ ሌሎች ብዙ እንዳሉ ተናገረ፣ እርሷንም ብልህ እና ፅኑ ብሎ ከመጥራት በቀር ሌላ ሊል አልቻለም። እናቴም ወደ እርሱ በመዞር እንዲህ አለችው፣ ‘. . .እራስህ ልታዝን ይገባሃል። በረከት ልታሳጣኝ ትሻለህን። አስራቴን ካልከፈልኩኝ፣ ጌታ በረከቱን ከእኔ እንደሚያርቅ መጠበቅ ይኖርብኛል አስራቴን የምከፍለው፣ የእግዚአብሔር ሕግ ስለሆነ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ይህን በማድረጌ በረከት ስለምጠብቅ ነው። ይህንን እና ሌሎች ሕግጋትን በመጠበቅ፣ ለመበልጸግ እና ቤተሰቤን ለመርዳት እንድችል ተስፋ አደርጋለሁ።’ . . .የእግዚአብሔርን ሕግጋቶች በመታዘዟ ምክንያት በልጽጋለች። ቤተሰቦቿን ለመርዳት የተትረፈረፈ ነበራት። ሌሎች የተቸገሩትን ያህል እኛ በፍጹም አልተቸገርንም. . . .። ያች መበለት የእግዚብሔርን ቤት ልዩ መብቶች ልትታደል በቀታለች። ለእግዚአብሔር ሕጎች ታዛዥ በመሆኗ፣ የትኛውንም የወንጌል ሥርዓት ልትከለከል አልቻለችም” (*Gospel Doctrine*, አምስተኛ ህትመት [ሶልት ሌክ ከተማ፡ Deseret Book Co., 1939], ከገጽ 228–29)።

• እህት ስሚዝ እንዴት ነበር የተባረከችው? (መበለት ብትሆንም እንኳን ቤተሰቧን ለመመገብ ብዙ ነበራት፣ እንዲሁም የቤተመቅደስ በረከቶችን ተቀበለች።)

አብዛኞቹ የምቀበላቸው በረከቶች በየቀኑ የሚመጡ እና በይበልጥ የተለመዱ መሆናቸውን ግለጽ። ምናልባትም ልብ የማንላቸውን ብዙ በረከቶችን እንቀበላለን።

ምስክርነትን ማካፈል

ስለ አስራት ወጣት ወንዶቹ ያደረጉትን ውይይቶች ለቤተሰቦቻቸው እንዲያካፍሉ አድርጋቸው እና ይህንን በማድረጋቸው ስለ ተቀበሉት በረከቶች ተሞክሯቸውን ማካፈል የሚሹትን ማናቸውንም ጋብዝ።

ጥቅስ

በፕሬዚዳንት ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ የተነገረውን የሚከተለውን አባባል አንብብ፣

“በዚህ መሰረት ሀሳብ (አስራት) የዚህች ቤተክርስቲያን ሰዎች ታማኝነታቸው ይፈተናል . . .። ከዚህ መሠረተ ሀሳብ ጋር የተያያዘ እጅግ ብዙ ተፈላጊነት ያለው ነገር አለ፣ በዚህም ታማኝ መሆናችን ወይም አለመሆናችን ይታወቃል። በዚህ ረገድ በእግዚአብሔር እንደማመን፣ እንደ ኃጢዓት ንስኃ፣ . . . ወይም እንደ እጅን በመጫን የመንፈስ ቅዱስ ሥጦታ የሚያስፈልገውን ያህል አሥራት ያስፈልጋል” (*Gospel Doctrine*, አምስተኛ ህትመት [ሶልት ሌክ ከተማ፡ Deseret Book Co., 1939], ገጽ225)።

ከአስራት ሕግ ጋር በማያያዝ ዘወትር ልናስታውሰው የሚገባን አንድ መሠረታዊ ሀሳብ ቢኖር አስራትን የምከፍልበት ምክንያት ጌታን ስለምንወደው እና በእርሱም እምነት ስላለን እንጂ፣ በረከትን ፍላጋ ወይን ገንዘብ ስላለን አለመሆኑን ትኩረት ስጥበት።

**የእግዚአብሔር መንግስት እንዲያድግ መርዳት**

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

ወጣት ወንዶቹ ትምህርት እና ቃል ኪዳን 119፥2–4 እንዲያነቡ አድርግ።

• በዚህ ጥቅስ መሠረት፣ አስራት ለምን ጥቅም ይውላል? (ቤተመቅደሶችን ለመገንባት፣ ለፅዮን ግንባታ፣ ለክህነት ሥራ።)

• የቤተክርስቲያን መሪዎች በአስራት አማካኝነት የጌታን ዓላማ የሚያከናውኑት እንዴት ነው?

ምላሾቻቸው የቤተመቅደስን እና ሌሎች የቤተክርስቲያን ሕንፃዎችን ግንባታ እና አያያዝ፣ የሚሲዮን ሥራ ዕርዳታ፣ እና የቤተክርስቲያን ትምህርት (ሴሚናሪ እና ኢንስቲቲዩት) አቀርቦትን ማጠቃለል ይኖርበታል።

ሁናቴ

ወጣት ወንዶቹ በቅዱስ ቁርባን ስብሰባ ላይ እንዳሉ አድርገው እንዲገምቱ አድርግ፣ እናም ጳጳሱ ቤተክርስቲያኗ አባላት ከዚህ በኋላ አስራት መክፈላቸውን እንደማትፈልግ ያስታውቃል። እነርሱም በመደሰት ከእንግዲህ በትርፉ ገንዘባቸው ምን እንደሚገዙ ዕቅድ ያወጡ ጀምር። ምናልባትም ይህ ነገር የገንዘብ ችግሮቻቸውን በሙሉ እንደሚቀርፍላቸው አስበው ይሆናል።

ይሁንና፣ ወራቶች በላፉ ቁጥር፣ አዲሱ መመሪያ ባልጠበቁት ሁኔታ ጥፋተኛ መሆናቸውን ማሳየት ጀመረ። የዋርዱ ሕዝብ ቁጥር በእጅጉ ጨመረ፣ እናም የመሰብሰቢያ አዳራሹ ከዚህ በኋላ በቂ ሊሆን አልቻለም፤ በተመጨማሪም፣ ሕንፃው እና ዙሪያ ገባው ማርጀት ጀምሯል። ነገር ግን ለማደስ እና አፍርሶ ለመስራት ገንዘብ የለም።

ለዓመታት ወደ ሚሲዮን ለመሄድ ያቀዱ ታላላቅ ወንድሞች እንዳሏቸው አድርገው እንዲያስቡ አድርግ፣ ለሚሲዮን መሄጃው ጊዜ አሁን ቢሆንም፣ ሚሲዮኖቹም ተዘግተዋል። የሚሲዮን ቢሮዎችን ለማንቀሣቀስ ወይም የጸሎት ቤቶችን ለመገንባት ወይም ለመከራየት ገንዘብ የለም።

ከዚህ በላይም ደግሞ ወደፊት ወደ ሴሚናሪ ክፍሎች ለመሄድ የሚጠባበቁ ወንድሞች እና እህቶች ያሏቸው መሆኑን እንዲያስቡ አድርግ፣ ነገር ግን ሴሚናሪ ክፍሎች አሁን ተዘግተዋል፣ እንዲሁንም የኢንስቲቲዩት ክፍሎች እና የቤተክርስቲያኗ ኮሌጆችም ጭምር። ሕንፃዎችን ለመገንባትና ለመንከባከብ ወይም ለአስተማሪዎች ለመክፈል ገንዘብ የለም።

ከቤተሰቦቻቸው አብዛኛዎቹ አባላት ደስተኞች አይሆኑም። የቤተሰቦቻቸውን ታሪክ የዘር ግንድ ጥናት ሥራ ለማከናወን አይችሉም ምክንያቱም የምርምር ማዕከሎቹ ይዘጉ ይሆናል እንዲሁም ቤተመቅደሶች አልፎ አልፎ ብቻ ይከፈታሉ።

እነዚህን ችግሮች ለማስተካከል የቤተክርስቲያኗን ዕቅድ ለማወቅ እንደማይችሉ ግልፅ ምክንያቱም የበላይ ባለስልጣንናት የስቴክ ጉባኤዎችን ከዚህ በኋላ አይጉበኙም። ምናልባትም ለዚህ ዋና ነገር፣ እያደገች ባለችው ቤተክርስቲያን እሷም በምድር ላይ የእግዚአብሔር መንግስት በሆነችው ላይ ምን ሊከሰት እንደሚችል መደነቅ ይጀምሩ ይሆናል።

ውይይት

• ይህ በእውን እንዳይከሰት ምን ያበቃዋል? (አስራታችን መክፈል።)

• አስራታችንን ስንከፍል ማን ነው የሚጠቀመው? (እኛ ነን። ጌታ የገቢያችንን ዘጠኝ አስረኛውን እንዴት እንደምንጠቀመበት ውሣኔውን ለኛ ተቶታል። የቀረው አንድ አስረኛ ለእርሱ እንሰጣለን፣ እና እርሱም፣ በቤተክርስቲያን መሪዎቻችን አማካኝነት፣ ለራሳችን ጥቅም ይገለገልበታል።)

---

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት

አስራትህን በመክፈል ስላገኘሃቸው በረከቶች የራስህን ምስክርነት መስክር።

ቅዱስ መጽሐፍ እና ሙከራ

ወጣት ወንዶች ሚልክያስ 3፥10–12 በድጋሚ እንዲያነቡ አድርግ።

እያንዳንዱን ወጣት ወንድ ሙሉ እና ተፈላጊውን አስራት በመክፈል ለጌታ ፍቀሩን ያሳይ ዘንድ አነሳሳ። አስራት ትዕዛዝ መሆኑን ትኩረት ስጥበት፣ በታማኝነት የጌታን ትዕዛዝ ስንታዘዝም፣ እርሱ ይባርከናል።

# 33 የቅዱስ መጽሐፍ ጥናት

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ወንድ በየቀኑ ቅዱሳን መጽሐፍትን ካጠና ሕይወቱን እንደሚጠቀሙት ይገነዘባል። |

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. የአካባቢው መልክዓ ምድር ካርታ።
2. የሚከተሉትን ዝርዝር በሠንጠረዥ ወይም በሠሌዳ ላይ አዘጋጅ፣
   1. ትዕዛዝ
   2. የምስክርነት ቃል
   3. ምስክር
   4. ደስታ
   5. መልሶች
   6. የሚሲዮን ሥራ

   እነኚህን በእያንዳንዳቸው ላይ የወረቀት ቁራጭ በማጣበቅ ሸፍን።
3. (አማራጭ) ለእያንዳንዱ ወጣት በሚያነብበት ጊዜ ምልክት ያደርግ ዘንድ የቅዱስ መጽሐፍ ሰንጠረዥ አዘጋጅ።

**ለትምህርት ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**ቅዱሳን መጽሐፍት እኛን ለመምራት ይረዳሉ**

ውይይት

ወጣት ወንዶቹ በሚከተለው ሁናቴ ውስጥ እራሳቸውን እንዲያስቡ ጠይቅ። አንተ እና የአንተ ቤተሰብ በተራሮች ላይ ጥቂት ቀናት ለማሳለፍ ሄዳችኋል። አካባቢውም ለአንተ አዲስ ነው፣ ከእራት በፊት ለአጭር ሽርሽር ወጣ ለማለት ወሰንክ። በመሄድ ላይ ሳለህ፣ አንዲት ሽኮኮን ተመለከትክ እና እሷን መከታተል ጀመርክ። ወደ የትኛው አቅጣጫ እየተጓዝክ እንዳለህ አላስተዋልክም እናም ድንገት እንደጠፋህ ተገነዘብክ። ፀሐይም ከተራሮች ጀርባ ጠልቃለች፣ ብዙም ሣይቆይ ቀኑ እየቀዘቀዘ እና እየጨለመ ይሄዳል።

• በእንደዚህ ያለ ሁናቴ ውስጥ ምን ሊረዳህ ይችላል? (ካርታ ወይም አቅጣጫ ጠቋሚ መሣሪያ።)

የመንገድ ካርታ አሣይ እና ሁለት ሥፍራዎችን ምረጥ፣ የመነሻ ነጥብ እና የመድረሻ ነጥብ። አንድ ወጣት በተፈለገው የማረፊያ ቦታ ላይ ለመድረስ መከተል ያለበትን መንገድ እንዲገልጽ አድርግ። ካርታ በተጻፉ አቅጣጫዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መንገዳችንን ለማግኘት እንደሚረዳን ሁሉ፣ ቅዱስ መጽሐፍትም ወደ ሰማዩ አባታችን ለመመለስ ይረዱናል።

• ቅዱስ መጽሐፍ ምንድን ነው? (የመጨረሻው ቀን ቅዱሳን የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት እንደሚገልጸው "*ቅዱስ መጽሐፍ* ማለት፣ በቤተክርስቲያኗ የተቀደሱ እና የእግዚአብሔር መንፈስ አለባቸው ተብለው ተቀባይነት ያላቸውን ጽሁፎች የሚያመለክት ነው።")

ቅዱስ መጽሐፍ፣ ጥቁር ሠሌዳ እና ውይይት

ከአጭር ውይይት በኋላ፣ አንድ ወጣት ወንድ ትምህርት እና ቃል ኪዳን 68፥4 እንዲያነብ አድርግ። ከዚያም በሰሌዳ ላይ የሚከተለውን መግለጫ ፃፍ፣ *ጌታ እንደ አገልጋዮቹ የመረጣቸው እና የሾማቸው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሲናገሩ ወይም ሲጽፉ፣ ቃላቶቻቸው ቅዱስ መጽሐፍ ይሆናሉ።*

• ዛሬ የምንጠቀምባቸው ቅዱስ መጽሐፍት የትኞቹ ናቸው? (መደበኛ ቅዱሣን መፅሐፍት፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ [King James Version]፣ መጽሐፈ ሞርሞን፣ የትምህርት እና ቃል ኪዳን፣ እና ታላቅ ዋጋ ያላት ዋጋ እንቁ።)

መደበኛ ቅዱሣን መፅሐፍት በሰሌዳው ላይ ዘርዝር።

• ከመደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት ሌላ እንደ ቅዱስ መጽሐፍ ልናስበው የሚገባን ነገር አለን?

ደግሞም በህይወት ባሉ ነቢያቶቻችን በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተነገሩት ቃላት ቅዱስ ጽሑፍ እንደሆኑ አትኩሮት ስጥበት። ከመደበኛ ቅዱሣን መጽሐፍት ዝርዝር ቀጥሎ *በህይወት ያሉት ነቢያቶቻችን የተናገሯቸው ቃላቶች* ሠሌዳው ላይ ፃፍ።

**ቅዱሳን መጽሐፍትን ማጥናት ሕይወታችንን በእጅጉ ሊባርከው ይችላል**

ሠንጠረዥ እና ውይይት

• ቅዱሳን መጽሐፍትን ለምን ማጥናት ይገባናል?

ያዘጋጀኸው ዝርዝር ቅዱሳን መጽሐፍትን ለምን ማጥናት አንዳለብን ያካተተ ብዙ ምክንያቶች እንደያዘ ግለጽ ("ዝግጅትን" ተመልከተ)፡፡ እያንዳንዱ ዝርዝር እንደተሸፈነ ሰንጠረዡን አሣይ፡፡ በምትወያዩበት ግዜ እያንዳንዱን ዝርዝር በየተራ አንድ በአንድ ግለጽ፡፡

የሠንጠርዡን የመጀመሪያውን መስመር ግለጽ፣ "1. ትዕዛዝ፡፡"

ቅዱሳን መጽሐፍትን እንድናጠና በነቢይ እንደተመከርን ግለጥ፡፡ በፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል ቅዱሳን መጽሐፍትን ስለማጥናት በተመለከተ የተሰጠውን የሚከተለውን ንግግር አንድ ወጣት ወንድ እንዲያነብ አድርግ፣

"ሁላችንም ወደ ቅዱሳን መጽሐፍት መመለስ እንዳለብን በከፍተኛ ሁኔታ ይሰማኛል . . . እናም እስቲ በውስጣችን በኃይል ይስሩ፣ ጌታን ለማገልገል ወደማይናወጥ ውሣኔ ይገፋፉን . . .፡፡

"ቅዱሳን መጽሐፍትን በጌታ ትዕዛዝ መሠረት ማጥናት አለብን (3 ኔፊ 23፥1–5)፤ እናም የኛን ሕይወት እና የልጆቻችንን ሕይወት ይገዙ ዘንድ መፍቀድ አለብን . . .፡፡

"ስለዚህ እስካሁን ይህንን ካላደረጋችሁት ሁላችሁም መጽሐፍትን በቁም ነገር ማጥናት አሁን እንድትጀምሩ እጠይቃለሁ" ("How Rare a Possession—the Scriptures!" *Ensign*, መስከረም 1976, ገጽ 5)፡፡

የሠንጠረዡን ሁለተኛውን መስመር ግለጥ፣ "2. ምስክርነት፡፡"

ቅዱሳን መጽሐፍት የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ምስክርነት ለማግኘት ሊረዱን እንደሚችሉ ግለጽ፡፡ አንድ ወጣት ቀጥሎ በቁስ ማሪዮን ጂ. ሮምኔይ የተነገረውን ታሪክ እንዲያነብ አድርግ፣

"ከወንድ ልጆቼ አንዱ ልጅ በነበረበት ግዜ [መጽሐፈ ሞርሞንን] አብረን ስናነብ አስታውሳለሁ፡፡ በአንድ አጋጣሚ እኔ ከስረኛው የእንጨት አልጋ ላይ ጋደም ስል እሱ ደግሞ ከላይኛው ላይ ተኛ፡፡ እያንዳንዳችን እነኛን የሁለተኛው ኔፊ የመጨረሻዎቹን ሦስት ድንቅ ምዕራፎች ተያያዥ አንቀጾች በየተራ ጮክ ብለን እናነብ ነበር፡፡ ድምጹ ሲቀራረጥ ሰማሁኝ እና ጉንፋን እንደያዘው ገመትኩ፣ ነገር ግን እስከ ሦስቱ ምዕራፎች ማጠቃለያ ድረስ አነበብን፡፡ እንደ ጨረስን እንደዚህ አለኝ፣ 'አባዬ፣ መጽሐፈ ሞርሞንን በምታነብበት ጊዜ አልቀሰህ ታውቃለህ?'

" 'አዎን ልጄ፣' ብዬ መለስኩለት፡፡ 'አንዳንዴ የጌታ መንፈስ ለነፍሴ መጽሐፈ ሞርሞን እውነት እንደሆነ ሲመሰክርላት ያኔ አለቀሳለሁ፡፡'

" 'ደህና፣' አለ፣ 'ዛሬ ማታ በኔ የተከሠተው ያ ነው' " ("The Book of Mormon," *Improvement Era*, ግንቦት 1949, ገጽ 330)፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ጠንካራ ምስክርነት ጌታን በመከተል ለእራሳችን ቃል እንድንገባ እንደሚረዳን ግለጽ፡፡

የሠንጠረዡን ሦስተኛውን መስመር "3. ምስክር" የሚለውን ግለጥ፡፡

ቅዱስ መጽሐፍት ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንደሚመሰክሩ ግለጽ፡፡ የመጽሐፈ ሞርሞን ዓላማ ለኢሱስ ክርስቶስ ሁለተኛ ምስክር ለመሆን እና ሰዎች ኢየሱስ መሲህ እንደሆነ እንዲያምኑ ለመርዳት ነው፡፡

አንድ ወጣት ወንድ የመጽሐፈ ሞርሞንን የአርዕስት ገጽ ሁለተኛውን አንቀጽ ሲያነብ ሌሎች ከቅዱሳን መጽሐፍቶቻቸው ላይ እንዲከታተሉት አድርግ፡፡

የሠንጠረዡን አራተኛ መስመር "4. ደስታ" የሚለውን ግለጽ፡፡

ቅዱሳን መጽሐፍት የመንፈሳዊ ፍስሀ እና ደስታ ምንጭ መሆናቸውን ግለጽ፡፡ ለምሳሌ፣ ኔፊ ቅዱሳን መጽሐፍትን በማንበብ ትልቅ ደስታ ተሰምቶታል፡፡ አንድ ወጣት ወንድ 2 ኔፊ 4፥15 እንዲያነብ አድርግ፡፡

የሠንጠረዡን አምስተኛ መስመር "5. መልሶች" የሚለውን ግለጽ፡፡

ለተወሰኑ ችግሮች እና ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ቅዱሳን መጽሐፍት ከጸሎት ጋር ተጓዳኝ መሆን እንደሚችሉ ግለጽ፡፡ ዮሴፍ ስሚዝ በእነሱ ዕድሜ በነበረበት ግዜ ምን እንዳደረገ እንዲያስቡ ጠይቅ፡፡

• ዮሴፍ ምን እያደረገ ሳለ ነበር ወደ ጫካ ሄዶ የትኛውን ቤተክርስቲያን መቀላቀል እንዳለበት እንዲጸልይ የተገፋፋው? (ቅዱሳን መጽሐፍትን እያነበበ ነበር፡፡)

• ቅዱሳን መጽሐፍትን በማጥናቱ እና በመጸለዩ ምክንያት ምን መልሶችን ነበር ያገኘው? (እውነተኛው ቤተክርስቲያን በምድር ላይ እንደሌለ ተገነዘበ፡፡ የእግዚአብሔርንም ትክክለኛ ገጽታ ተማረ፡፡)

የሠንጠረዡን ስድስተኛ መስመር፣ "6. የሚሲዮንነት ሥራ" የሚለውን ግለጽ፡፡

ቅዱሳን መጽሐፍት ለሰዎች እውነተኛውን የክርስቶስን ወንጌል ለማስተማር በሚሲዮንነት ሥራ አስፈላጊ መሆናቸውን ግለጽ፡፡


ከወጣት ወንዶች አንዱን ትምህርት እና ቃል ኪዳን 42፥12 ሲያነብ ሌሎች ከቅዱሳን መጽሐፍቶቻቸው ላይ እንዲከታተሉት አድርግ፡፡

---

**የዘወትር የቅዱስ መጽሐፍ ጥናት**

ጥቁር ሠሌዳ እና ውይይት

በጥቁር ሠሌዳው ላይ ልክ እንደ ፓይ በክፍልፋዮች ሊከፋፈል የሚችል ክብ ሣል፡፡ ክፍሉ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ሲሠጥ፣ በፓዩ ክፍልፋዮች ውስጥ ወጣት ወንዶቹ ለመኘታ፣ ለትምህርት ቤት፣ ለመመገብ፣ እና ለሌሎች ተግባሮች የወሰዱትን የጊዜ መጠንን የሚወክለውን ሙላ፡፡ ጥቁር ሰሌዳህ ይህን መምሰል አለበት፤




- በምሽት ለመኘታ ምን ያህል ሰዓቶች ታጠፋለህ?
- በትምህርት ቤት ምን ያህል ሰዓቶች ታጠፋለህ?
- በየቀኑ ለመመገብ ምን ያህል ሰዓቶች ታጠፋለህ?
- በየዕለቱ የተቀሩትን ሰዓቶች እንዴት ታጠፋለህ?

ምናልባትም የሚያቀርቧቸው ነገሮች እንደ የቤት ውስጥ ሥራዎችን መስራት፣ የቤት ሥራን መስራት፣ መጫወት፣ እና ቴሌቪዥን መመልከት ይሆናሉ፡፡

የአማካሪ አቀራረብ እና ማሰላሰያ ጥያቄዎች

- በእያንዳንዱ ቀን ጥቂት ደቂቃዎች ለቅዱስ መፅሐፍ ጥናት ልታገኝ ትችላለህ?

በየዕለቱ አብዛኛውን ጊዜአችንን በትምህርት ቤት፣ ሥራ፣ ጨዋታ እና ሌሎች ሥራዎች እንደምናጠፋ፣ ነገር ግን ወደ ሰማዩ አባታችን ለመመለስ የሚረዱንን የተለዩ ነገሮች ለማከናወን ሁሌም ጥቂት ጊዜን እንደምናጠፋ ግለጽ፡፡

- የጌታን ድምጽ ለመስማት በየቀኑ ጥቂት ደቂቃዎችን ለማጥፋት ፍቃደኛ ትሆናለህ?

ብዙ ሰዎች ጌታ ከነርሱ ጋር ሲነጋገር ለመስማት ምንም ዓይነት ነገር ቢሰጡ ይወዳሉ፣ ሆኖም ጌታ ለእነርሱ ምን እንዳለ ለመማር በየቀኑ ጥቂት ደቂቃዎች መጽሐፍትን በማጥናት እንደማያጠፉ ግለጽ፡፡

ቅዱሳን መጽሐፍት እና ውይይት

ከወጣት ወንዶቹ አንዱን ትምህርት እና ቃል ኪዳን 18፥34–36 እንዲያነብ አድርግ፡፡

- ቅዱሳን መጽሐፍትን ስናነብ የማንን ድምፅ ነው የምንሠማው? (የጌታን ድምፅ፡፡)

ጥቅስ

ፕሬዚዳንት እዝራ ታፍት ቤንሰን፣ “ወጣት ወንዶች፣ መጽሐፈ ሞርሞን ሕይወታችሁን ይለውጣል፡፡ ለዘመናችን ክፋቶች ምሽግ ይሆንላችኋል . . .፡፡ መጽሐፈ ሞርሞንን የሚያውቅና የሚወድ ወጣት ወንድ . . . ስለ እውነተኛነቱ የማይጠፋ ምስክርነት ያለው፣ እና ትምህርቱን ተግባራዊ የሚያደርግ የሰይጣንን ተንኮል ሊቋቋም ይችላል እናም በጌታ እጅ ብርቱ መሣሪያ ይሆናል” ብለዋል። (በ Conference Report, ሚያዚያ 1986, ገጽ 56; or *Ensign*, ግንቦት 1986, ገጽ 43)፡፡

---

**ማጠቃለያ**

የአማካሪ አቀራረብ እና ጥቅስ

ሁላችንም በብዙ ሥራዎች ባተሌ ከመሆናችን የተነሳ፣ ግባችንን ለማሣካት አንዱ መንገድ—እንደ ቅዱሳን መጽሐፍት ጥናት የመሳሰለውን—ለዛ ዓላማ በየዕለቱ የተወሰነ ጊዜን መለየት እንደሆነ አሳስብ፡፡ ከወጣት ወንዶቹ ጋር መጽሐፍትን ለማጥናት ሊያበረቷቷቸው የሚችሉትን ዘዴዎች ተወያይ፡፡ እነዚህም ዘዴዎች ሠንጠረዥን መጠቀም፣ የንባብ ፕሮግራምን መከተል፣ እና ከሌሎች ጋር ውድድርን ማድረግ ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፡፡ ቅዱሣን መጽሐፍትን የማጥናትን መንፈስ እንዳገኙ እውነተኛ ደስታ ወደ ሕይወታቸው እንደሚመጣ አትኩሮት ስጥበት፡፡ በሕይወታቸውም ውስጥ ቅዱሳን መጽሐፍት አስደሳች እና ትርጉም ያላቸው መሆን ይጀምራሉ፡፡ መጽሐፈ ሞርሞንን መጀመሪያ ማንበብ በጀመረ ጊዜ ፓርቢ ፒ. ፕራትሰን ስለ ስሜቱ የገለጸውን ከወጣቶቹ አንዱ እንዲያነብ አድርግ፡፡

"በጉጉት ገለጥኩት፣ እና የአርዕስት ገፁን አነበብኩት። ከዚያም ብዙዋን ምስክሮች ከመገኘቱ እና ከአተረጓገሙ ጋር በተዛማጅነት የሰጡትን የምስክርትነት ቃል አነበብኩ። ከዚህ በኋላ ማውጫውን በረድፍ ጀመርኩ። ቀኑን ሙሉ አነበብኩ፤ መመገብ ከበደኝ፣ ለምግብ ፍላጎቱ አልነበረኝም፤ ምሽቱም በመጣ ጊዜ እንቅልፍ ሸክም ሆኖብኝ ነበር፣ ከእንቅልፍ ይልቅ ማንበቤን መርጬ ነበርና።

"ሳነብ፣ የጌታ መንፈስ በላዩ ላይ ነበር፣ እናም መጽሐፉ እውነት እንደሆነ ተረድቼ ነበር . . .። ደስታዬ በዚህ ጊዜ ሙሉ ነበር . . .። ለመገኘቱ እና ለመተርጐሙ መሣሪያ የሆነውን ወጣት ለማየት ወዲያውኑ መሰንኩ" (*Autobiography of Parley P. Pratt*, ed. Parley P. Pratt, Jr. [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Deseret Book Co., 1975], ገጽ 37)።

ሙከራ እና አማራጭ የሚታደል ጽሁፎች

በሚመጣው ሣምንት ውስጥ በየዕለቱ ለጥቂት ደቂቃዎች ወጣት ወንዶቹ ቀዱሳን መጽሐፍትን እንዲያነቡ አበረታታቸው። በቀዱሳን መጽሐፍት ውስጥ ያለውን ጠቃሚ መልዕክት ለማጥናት ወጣት ወንዶቹ ጊዜ ባጠፉ ቁጥር ቀዱሳን መጽሐፍቱ ለሰማዩ አባታቸው፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ፣ እና ለወንጌል ያላቸውን ፍቅር እንደሚያጠነክሩላቸው መስክር። በሚቀጥለው እሁድ ከመካከላቸው ምን ያህሉን በሳምንቱ ውስጥ በየዕለቱ እንዳነበቡ በማየት ክትትል እንደምታደርግ ተናገር። ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ ሲያነብ ምልክት እንዲያደርግ ሠንጠረዡን ልታድል ትችላለህ።

# 34 ታዛዥነት

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ትዕዛዛትን በመታዘዝ ለሰማዩ አባታችን እና ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ማሣየት እንደሚችል ይረዳል፡፡ |
| **ዝግጅት** | 1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣<br>ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቅዱሣን መጽሐፍት፡፡<br>ለ. ጥቅሶችን ምልክት ማድረጊያ እርሳሶች።<br>ሐ. የመዝሙር መጽሐፍ፣ ወይም በማስታወቂያ ላይ አሊያም በሠሌዳ ላይ "እግዚአብሔር ሆይ፣ ስለነቢዩ፣ እናመስግንሀለን" የሚለውን የቁ. 19 መዝሙር፡፡ |

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**ታዛዥነት የወንጌል መሠረታዊ መመሪያ ነው**

ታሪክ

ወጣት ወንዶቹ አንድ ወጣት ልጅ የታዛዥነት መመሪያ እንዴት እንዳሳየ የሚገልፀውን ታሪክ እንዲያዳምጡ አድርግ፡፡

"አንድ ወጣት ልጅ የእናቱ ድምፅ ጐላ ብሎ ቻርሊ!' ብላ ስትጣራ እና ጥርት ብሎ ሲመጣ እርሱ ከጓደኞቹ ጋር ቤዝ ቦል እየተጫወተ ነበር፣ 'ቻርሊ፣ ከመቀፅበትም ዱላውን ጣለ፣ ጃኬትና ኮፍያውን አነሣ እና ወደ ቤት አመራ፡፡

" 'አትሒድ አንጂ፣ ጨዋታውን ጨርስ!' ብለው ሌሎች ተጫዋቾች ጮኹ፡፡

" 'ልክ በዚህች ደቂቃ መሄድ አለብኝ፡፡ እናቴ ስትጠራኝ እንደምመጣ ነግሬያታለሁ፡' የሚል ነበር የቻርሊ ምላሽ፡፡

" 'እንዳልሠማህ አድርገህ አስመስል፡' አሉ ልጆቹ፡፡

" 'ነገር ግን ሰምቼአለሁ፡' አለ ቻርሊ፡፡

" 'እንደሰማህ እሷ አታውቅም፡፡'

" 'እኔ ግን አውቃለሁ፣ እናም መሄድ አለብኝ፡፡'

"በመጨረሻም ከልጆቹ አንዱ፣ 'ኦ፣ ይሒድ በቃ፡፡ ሐሣቡን ልታስቀይሩት አትችሉም፡፡ ከእናቱ ሸርጥ መቀነት ጋር ታስሯል፡፡ እናቱ በጠራቸው በዚያች ደቂቃ ይሮጣል፣ የሆነ ህፃን ነገር ነው።' አለ፡፡'

"እየሮጠ ሳለ፣ ቻርሊ ወደኋላ ዞሮ እንዲህ አለ፣ 'አንድ ሠው ለእናቱ የገባውን ቃል መጠበቅ ህፃንነት አልለውም፡፡ ጉብዝና ነው የምለው፣ እናም ለእናቱ ቃሉን የማይጠብቅ ልጅ ለሌላ ለማንም በፍፁም ቃልን አይጠብቅም' " (N. Eldon Tanner, በ Conference Reprt ጥቅምት 1977,ገጽ 65; ወይም *Ensign,* ህዳር 1977, ከገጽ 43–44)፡፡

ጥቁር ሠሌዳ እና ውይይት

በጥቁር ሠሌዳው ላይ *ታዛዥነት* ፃፍ፡፡

• *ታዛዥነት* ምን ማለት ነው?

ጥያቄውን ወጣት ወንዶቹ እንዲመልሱ አድርጋቸው፣ አንድ ሰው የተነገረውን ማድረግ ወይም ለህግ ወይም ለሥልጣን መገዛት መታዘዝ መሆኑን እንዲገነዘቡ እርዳቸው፡፡ ታዛዥነት በጣም አስፈላጊ እና መሰረታዊ ከሆኑት ከእግዚአብሔር ሕጐች አንዱ ነው።

ቅዱሳን መጽሐፍት እና ውይይት

ወጣት ወንዶቹ በየተራ የሚከተሉትን ጽሑፎች ሲያነቡ የቀሩት ደግሞ ከቅዱሳን መጽሐፍቶቻቸው ላይ አብረው እየተከታተሉ ምልክት እንዲያደርጉ አድርግ፡፡

እያንዳንዱ ጽሑፍ ከታዛዥነት ጋር ምን ግንኙነት እንዳለው ተወያይ፡፡ እነዚህን ነጥቦች በጥቁር ሠሌዳው ላይ ፍሬ ሐሣቡን አጠር አጠር አድርገህ መፃፍ ትችላለህ፡፡

1. አብርሃም 3፡24–25 (ወደ ምድር የተላክነው ታዛዥ መሆናችንን ለማየት ነው፡፡)

2. ዮሐንስ 14፡15 (ለዳኛችንን የምንወድ ከሆነ፣ ትዕዛዛቶቹን እንጠብቃለን፡፡)

3. 1ኛ ኔፊ 3፥7 (ጌታ ትዕዛዛቱን እንድናከብር ለእኛ መንገድን ያዘጋጅልናል፡፡)

4. ትምህርት እና ቃልኪዳን 82፥10 (የምንታዘዝ ከሆነ ጌታ የእርሱን ድርሻ ያከናውናል፡፡)

5. ትምህርት እና ቃል ኪዳን 130፥20–21 (ሁሉም በረከቶች ለተለዩ ሕጐች በመታዘዝ ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡)

6. ማቴዎስ 7፥21 (ከሰማዩ አባታችን ጋር የሚኖሩት የሚታዘዙ ብቻ ናቸው፡፡)

ሦስተኛውን የእምነት አንቀጽ አንድ ወጣት እንዲጠቀስ አድርግ፣ “እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአት ክፍያ አማካኝነት፣ ለወንጌል ሕጐች እና ሥርዓቶች በመታዘዝ፣ የሰው ዘር በሙሉ ይድናል ብለን እናምናለን፡፡”

ታዛዠነት የወንጌል መሠረታዊ ትምህርት መሆኑን መስክር፡፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እምነት ካለን፣ የእርሱን ትእዛዛት እንጠብቃለን እናም ልክ እንደ እርሱ እንሆናለን፡፡ ታዛዥ በመሆን ብቻ ነው የሰማዩ አባታችን ወዳለበት ልንመለስ የምንችለው፡፡

---

**ታላላቅ ሰዎች ታዛዦች ናቸው**

ጥቅስ

የእግዚአብሔር ሰዎች ሁል ጊዜ በታዛዥነት ላይ ትልቅ አትኩሮት ያስቀምጣሉ፡፡ ከክፍሉ ጋር የሚከተለውን ጥቅስ ተካፈል፡

“ፕሬዚዳንት ኤን. ኤልደን ታነር ከአውሮፓውያን ሚሲዮኖች አመራር በተመለሱ ጊዜ፣ በእርሳቸው አስተሳሰብ፣ ለአንድ የተሳካለት ግለሰብ ወይም ሚሲዮናዊ ትልቁ አስፈላጊ ባህሪ ምን እንደሆነ ተጠይቀው ነበር፡፡ ለእንዲህ ላለው ጥያቄ ትክክለኛውን ፍርድ ካሰላሰሉ፣ ከትንሽ ቆይታ በኋላ፣ አንድ ቃል ተናገሩ፣ ‘ታዛዥነት’ ” (Ted E. Brewerton, በ Conference Report, ሚያዚያ 1981, ገጽ. 92; ወይም *Ensign*, ግንቦት 1981, ገጽ. 68)፡፡

የጥቁር ሠሌዳ ሥራ

በጥቁር ሰሌዳው ላይ ስም ስትፅፍ፣ ወጣት ወንዶቹ ተጠቃሹ ግለሰብ ታዛዥነትን እንዴት እንዳሳየ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ አድርግ፡፡

በጥቁር ሰሌዳው ላይ *አዳም* ብለህ ፃፍ፡፡

አዳም መሰዊያ እንደሠራ እና መስዋዕቶች እንዳቀረበ ግለፅ፡፡ መልአክም ቀርቦ ለምን መስዋዕቶች እያቀረበ እንዳለ ጠየቀው፡፡ “እግዚአብሔር ካዘዘኝ በቀር፣ እኔ አላውቅም”፣ ብሎ መለሰለት፡፡ (ሙሴ 5፥5–6 ተመልት።)

*ሌሂ* ብለህ በጥቁር ሠሌዳው ላይ ፃፍ፡፡

ሌሂ በኢየሩሳሌም ያለውን ቤቱንና ሀብቱን በመጣል ለጌታ ትዕዛዝ በመታዘዝ ትልቅ እምነት እንዳሳየ ግለፅ፡፡ በውጤቱም ሌሂ ብዙ መከራን በፅናት አልፏል፡፡ ለታዛዥነቱ ከኢየሩሳሌም ጥፋት በመዳን እና ወደ ውቧ ተስፋይቱ ምድር በመመራት ተሸልሟል፡፡

በጥቁር ሠሌዳው *ዮሴፍ ስሚዝ* ብለህ ፃፍ፡፡

ዮሴፍ ስሚዝ በእምነት ከጠየቀ፣ እግዚአብሔር እውነቱን እንደሚያስተምረው እንዳነበበ ግለፅ፡፡ ዮሴፍ ከአምላክ ዘንድ ለጥበብ በታዛዥነት ፀለየ፡፡ ነቢይ ለመሆን እና ስለ አምላክ እውነቱን ይማር ዘንድ ተባረከ፡፡

በጥቁር ሠሌዳው ላይ *ኢየሱስ ክርስቶስ* ብለህ ፃፍ፡፡

ኢየሱስ ሠላሣ ዓመት በሆነው ጊዜ፣ በዮርዳኖስ መጥምቁ ዮሐንስን ለማግኘት በገሊላ የሚገኘውን ቤቱን ጥሎ ሔደ፡፡ እርሱንም ባገኘው ጊዜ፣ ኢየሱስ ዮሐንስ እንዲያጠምቀው ጠየቀው ምክንያቱም ዮሐንስ የማጥመቅ ሥልጣን እንደነበረው ያውቅ ስለነበር ነው። አዳኛችን ኃጢአት ያልነበረበት ንስኃ የማያስፈልገው እንደነበር ዮሐንስ ያውቅ ስለነበር እንዲህ አለው፣ “እኔ ባንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል፣ አንተም ወደ እኔ ተመጣለህን?”

አዳኛችን ጥምቀት ለኃጢዓት ማስተሠሪያ እንደሆነ እናም እርሱ ምንም ኃጢዓት እንዳልፈፀመ ያውቅ ነበር፡፡ ነገር ግን ጥምቀት የሰው ልጅ ሁሉ የሚያስፈልገው ሥርዓት እንደሆነ ያውቅ ነበር፡፡ ኢየሱስም፣ “አሁንስ ፍቀድልኝ፣ እንግዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና” አለው፡፡ (ማቴዎስ 3፥13–15 ተመልከት፡)

---

**እኛ ሁላችንም ታዛዥ መሆን እንችላለን**

ውይይት

የቀድሞዎቹ ምሣሌዎች የነቢያት እና የአዳኛችን እንደነበሩ ግለፅ፡፡ ይሁንና፣ ታዛዥ ለመሆን የግድ ነቢያት መሆን እንደሌለብን፣ አትኩሮት አድርግበት፡፡ እኛ ሁላችንም ታዛዥ መሆን እንችላለን እናም ታዛዥ መሆን ይገባናል፡፡ እንደ ነቢዩ ታዛዥ በመሆን ለአዳኛችን ፍቀራችንን እናሣያለን፡፡

- ነቢይ አንድን ነገር እንድናደርግ ቢነግረን፣ እንዴት ምላሽ መስጠት ይገባናል?

ወጣት ወንዶች ይህንን ሲወያዩ፣ የነቢይን ምክር ሁልጊዜ መከተል እንደሚገባን አመልክት፡፡ የቤተክርስቲያናችን መሪዎች ምክር ሲለግሱን፣ አዳኛችን እራሱ እየመከረን እንዳለ ነው፡፡

ጥቅስና ውይይት

"መታዘዝ ማለት አቀጣጫን መቀበል እና መከተል ማለት ነው፡፡ የጊዜያችን ነቢይ 'እርምጃችንን ለማስረዘም፣' እራሳችንን ለማበርታት፣ ወደፊት እንድንገፋ እናም ለመቀዳጀት ተጨማሪ ጥረትን የሚጠይቁ ግቦችን እንድንፈልግ አቀጣጫን ሰጥተውናል፡፡ ለዚህ አቀጣጫ ታዛዥ ከሆንን፣ በፍፁም ሊሆኑ አይችሉም ብለን ያሰብናቸውን ነገሮች ስንቀዳጃቸው እራሳችንን እናገኛለን፡፡ ከሰባዎቹ የመጀመሪያው አማካሪ አንዱ የሆኑት ቄስ ሴ. ቴኦዶር ቱተል፣ አንድን ወጣት ወንድ ወደ ሚሲዮን ለመሔድ እየተዘጋጀ እንደሆነ በጠየቁት ግዜ ባደረጉት ንግግር ይህ ተጠቅሷል፡፡ ወጣቱ ልጅ፣ 'ወደ ሚሲዮን መሔድ አልፈልግም' ብሎ መለሰ፡፡ የቄስ ቱተል ምላሽ፣ 'ያ ምን ለውጥ ያመጣል? ጌታ እንድትሔድ ይሻል' የሚል ነበር፡፡ ይህን ታዛዥነት እንዴት መለማመድ እንደሚገባ ፍጹም ምሣሌ ነው" (Keith Brian Rutledge, በ Conference Report, Melbourne Australia የክልል ጉባዔ 1976,ገጽ 18)፡፡

• ቄስ ቱተል፣ "ያ ምን ለውጥ ያመጣል?" ባሉበት ጊዜ ምን ማለታቸው እንደሆነ ታውቃለህ? (ራሳችን ለመስራት የምንሻው ጌታ ከሚሻው በተለየ ጊዜ ጌታ እንድንሠራ የሚሻውን ማከናወን ይገባናል፡፡)

ታሪክ

የቤተክርስቲያን አባላት ታዛዥ በመሆናቸው ምክንያት እንዴት እንደተባረኩ የሚያሳዩትን የሚከተሉትን ምሣሌዎች ወጣት ወንዶቹ እንዲያዳምጡ አድርግ፡፡

"ብራዚል ውስጥ በሳኦ ፓውሎ ደቡባዊ ሚሲዮን ውስጥ አንድ ማንበብ እና መፃፍ በጣም በብቃት ሣይችል ወደ መስኩ የተሠማራ ቄስ ማልሄይሮስ የሚባል ነበር፡፡ ሕዝብ ባለበት እንኳ ፀሎት ለማድረግ ትንሽ ፈሪ ቢጤ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ወጣት ሰው . . . ትልቅ ሚሲዮናዊ ተብለው ከሚታሰቡት ውስጥ አንዱ ሆነ፡፡ [የእርሱ ሚሲዮን] ፕሬዚዳንት የሚሲዮን ጊዜው ወደ መጠናቀቁ ገደማ እንዴት እንደዚህ አንቀሣቃሽ እና የተሣካለት ሚሲዮናዊ ለመሆን እንደበቃ ጠየቀተ፡፡ (ከሁለት መቶ በላይ ሰዎች እንዲሁም ለአርባ ተከታታይ ሳምንታት በየሳምንቱ አጥምቋል፡፡) በጣም ትሕትና በሞላበት ሁኔታ ቄስ ማልሄሮስ እንዲህ ብሎ መለሰ፣ 'ደህና፣ ፕሬዚዳንት፣ አንተን በፍጹም ተጠራጥሬህ አላውቅም፡፡ አንድ ሰው በየሣምንቱ ሊያጠምቅ ይችላል አልህ፣ ስለዚህ እኔም በየሣምንቱ ማጥመቅ እንደምችል አወቀሁ፡፡ በፍፁም አልተጠራጠርኩም፡፡ ሁል ጊዜም ይህ ቀላል አልነበረም፣ *ነገር ግን ለመታዘዝ ጣርኩ'* " (Ted E. Brewerton, በ Conference Report, ሚያዚያ፣ 1981, ገጽ 93; ወይም *Ensign*, ግንቦት 1981,ገጽ 69)፡፡

• ቄስ ማልሄይሮስ እንዴት ነበር የተባረከው? (ፍርሃቱን አሸነፈው እና ብዙ ሰው አጠመቀ፡፡)

• ቄስ ማልሄይሮስ የሚሲዮኑን ፕሬዚዳንት ባይታዘዝ ኖሮ፣ የእርሱ ሚሲዮን በምን ዓይነት መንገዶች ሊለይ ይችል ነበር?

ታሪክ

"ፍሎሪያኖ ኦሊቬይራ፣ በብራዚል ውስጥ በስቴክ የከፍተኛ መማክርት አባል፣ እንደ ሚሲዮናዊነት በጣም የተሣካለት ለምንድን ነው? ምክንያቱም አፉን ለመክፈት እና ወንጌልን ለማካፈል የጌታን ምክር ስለታዘዘ ነው፡፡ አንድ ቀን በተፋፈገው የሳኦ ፓውሎ ትራፊክ ውስጥ እያሽከረከረ ሳለ ለሰከንድ ዓይኑን ከመንገዱ ዘወር ሲያደረግ ፊት ለፊቱ ካለ መኪና ጋር ተላተመ፡፡ ከተሽከርካሪው ዘሎ በመውረድ፣ ወደ ገጨው መኪና ተንደርድሮ፣ በሩን ከፈተና፣ 'ስለገጨሁህ በጣም አዝናለሁ' አለ፡፡ ጥፋቱ ሁሉ የእኔ ነበር፡፡ ሁሉንም ጥፋተኝነት እቀበላለሁ እናም ጠቀላላ ወጪውንም እከፍላለሁ፡፡ ይህን ለማድረግ ሐሣቡም አልነበረኝም፣ ስለዚህ ይቀር በለኝ፡፡ ባልገጭህ ኖሮ ግን፣ ሕይወትህን ሙሉ ስትጠብቀው የነበረውን ላንተ ያለኝን ይህን መልዕክት አትቀበልም ነበር።' ከዚያም የህክምና ዶክተር ለነበረው፣ እና ከሁለት ሣምንታት በኋላ ቤተክርስቲያኗን ለተቀላቀለው፣ ለዚህ ሰው ስለ ወንጌል ዳግም መመለስ ገለፀለት" (Ted E. Brewerton, በ Conference Report, ሚያዚያ 1981,ገጽ 93; ወይም *Ensign*, ግንቦት 1981,ገጽ 69)፡፡

• ወንድም ኦሊቬይራ በሚሲዮናዊነት በጣም የተሣካለት ለምን ነበር? (ወንጌልን ለማካፈል ጌታ ላቀረበው ጥያቄ ታዛዥ ነበር፡፡)

---

**በታዛዥነት ውስጥ ደስታ**

የአማካሪው አቀራረብ

ታዛዥ በመሆን ደስተኛ ልንሆን እና ጥሩ ስሜት ሊኖረን እንደሚገባ ግለፅ፡፡ ታዛዥ ስለመሆን ትክክለኛ አመለካከት ካለን፣ ፍስሃን እና ደስታን ወደ እኛ ያመጣልናል፡፡

ወጣት ወንዶቹ እንዲያሚሏቸው የተሠጧቸውን ምድብ ሥራዎች፣ እንደ ቅዱስ ቁርባንን ማዘጋጀት፣ ማንኛውንም የሠማዩ አባታችንን ትዕዛዝ መታዘዝ፣ የጥበብ ቃልን መታዘዝ፣ ወይንም የጾም በኩራትን በመሰብሰብ፣ ታዛዥ በሆኑበት ጊዜ ስለ አገኙት ስሜት እንዲያስቡ አድርግ፡፡ ከዚያም ይህንን ስሜት ለአንተ እንዲገልፁ አድርግ፡፡ እነርሱንም ወደ በጐው፣ ከታዛዥነት ወደሚመጣው እርኪ ስሜት አቀጣጫ ለውይይት ምራቸው፡፡

መዝሙር

ወጣት ወንዶቹ "እግዚአብሄር ሆይ፣ ስለነቢዩ እናመሰግንሀለን" የሚለውን የመጀመሪያውን ቁጥር እንዲዘምሩ እድርግ፣ ወይንም ከመካከላቸው አንዱ (*የመዝሙር* ቁ. 19) ቃላቶችን እንዲያነብ አድርግ፡፡ ለመዝሙሩ የመጨረሻው መስመር ልዩ ግንዛቤ እንዲሰጡበት አድርግ፡፡

“እግዚአብሔር ሆይ ስለ ነቢይ እናመሰግንህ
በኋለኛው ቀን ለመሚመራን።
ወንጌልን ስለ ላክልን እናመሰግንህ
አዕምሮአችንን እንዲያበራልን።
ለሁሉም በረከት እናመሰግን
በእጆችህ ሞልተህ ስለሰጠህን፣
አንተን ማገልገል ደስ ይለናል፣
ለአንተ መታዘዝ እንወዳለን፡፡

---

**ማጠቃለያ**

ቅዱስ መጽሐፍ እና ምስክርነት

ወጣት ወንዶቹን ሞዛያ 2፥41 እንዲያነቡ እና ምልክት እንዲያደርጉባቸው አድርግ፡፡

የሰማዩ አባታችንን ትዕዛዛት የመታዘዝ ጥቅሞች ምስክርነትን ስጥ፡፡

ታዛዥ መሆን በሰማዩ አባታችን ላይ መታመናችንን እና ለእርሱ ያለንን ፍቀር እንደሚያሣይ ግለፅ፡፡ በእውነት የምንወደው እና የምናምነው ከሆነ፣ በህይወታችን ሙሉ ለእርሱ ታዛዥ እንሆናለን፡፡

# 35 ቅዱስ ቁርባን

**ዓላማው** እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ቅዱስ ቁርባንን በብቃት ሲወስድ ወደ እርሱ ሊመጡ የሚችሉትን በረከቶች ይገነዘባል፡፡

**ዝግጅት**


1. አስፈላጊ የትምህርት መሳሪያዎች፣ ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት፡፡
2. ሁለት ወጣት ወንዶችን በትምህርቱ ውስጥ ምስክርነቶችን እንዲያነቡ መድብ፡፡
3. "ቅዱስ ቁርባንን የበለጠ ትርጉም ያለው ማድረግ" የሚል ቀጂ ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ እንዲታደል አዘጋጅ፡፡
4. አንድ የቅዱስ ቁርባን መዝሙር ምረጥ እና በትምህርቱ ማጠቃለያ ላይ ወጣት ወንዶቹ እንዲዘምሩት ወይንም እንዲያነቡት ለማድረግ አስፈላጊውን ዝግጅት አከናውን፡፡ ለወጣት ወንዶቹ ተስማሚ እና ምቹ የሚመስልህን መዝሙር ምረጥ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

ቅዱስ መጽሐፍ፣ ጥቁር ሠሌዳ፣ እና ውይይት

**ከጌታ ጋር ከፍተኛ ቃል ኪዳኖችን እናደርጋለን**

የ—H2O፣ $ እና የሙዚቃ ኖታ ምልክቶችን ፃፍ—በጥቁር ሠሌዳ ላይ ወደ ታች ዘርዝራቸው፣ እና የእያንዳንዱን ትርጉም ወጣት ወንዶቹን ጠይቅ፡፡




- እነዚህ ሦስት ቀርጾች ምንድን ናቸው? (እያንዳንዳቸው አንድ የሆነ ነገር የሚወክሉ ምልክቶች ናቸው፡፡)

አንድ ወጣት ዮሐንስ 1፥29 እንዲያነብ አድርግ፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን፣ የጠቦት በኩር ለጌታ እንደ መስዋዕት ይቀርብ ነበር፡፡ ከአዳኛችን የመጨረሻው መስዋዕት በፊት ጠቦቱ የእርሱ ምልክት እንደነበር አመልክት እናም ዛሬ ቅዱስ ቁርባን የእርሱን መስዋዕት ይወክላል እና መስዋዕቱን እንድናስታውስ ይረዳናል፡፡

- በቅዱስ ቁርባን ላይ የምንካፈለው ዳቦ ምንን ይወክላል?
- በቅዱስ ቁርባን ላይ የምንጠጣው ውሃ ምንን ይወክላል?

ወጣት ወንዶቹ ከትምህርት እና ቃልኪዳን 20፥77፥79 ውስጥ የቅዱስ ቁርባንን ፀሎቶች እንዲያነቡ አድርግ፡፡

ወጣት ወንዶቹ የቅዱስ ቁርባንን ፀሎቶች እንዲመለከቱ እና ቅዱስ ቁርባንን ስንካፈል የምንገባውን የተስፋ ቃል እንዲያገኙ ጠይቅ፡፡ እነዚህን የተስፋ ቃሎች ሲያገኙ፣ በጥቁር ሠሌዳው ላይ እንደሚከተለው ዘርዝር፣

ለሰማዩ አባታችን—ቃል እንገባለን

1. የክርስቶስን ስም ለመቀበል።
2. ዘወትር ክርስቶስን ለማስታወስ፡፡
3. የክርስቶስን ትዕዛዛት ለመጠበቅ፡፡

• እነኚህን ነገሮች ካደረግን፣ ጌታ ለእኛ የሚገባልን ተስፋ ምንድን ነው? (ከእኛ ጋር የሚሆነው፣ የክርስቶስ መንፈስ ዘወትር ይኖረናል፣ እሱም መንፈስ ቅዱስ ነው፣)

ውይይት

ህጻን ሲወለድ ወይም ጉዲፈቻ ሲወሰድ፣ የቤተሰቡ ስም ይሠጠዋል። እርሱም ለዚያ ስም ክብር ለማምጣት እና በሥርዓት ለመኖር መጣር ይገባዋል።

• የክርስቶስን ስም በላያችን እንድንወስድ ሲባል ምን ማለት ነው? (እርሱን ለመምሰል ጥረት ለማድረግ ቃል መግባት፣ የእርሱን ምሣሌ እና ትምህርት መከተል።)

• "እርሱን ማስታወስ" ምን ማለት ነው?

• እርሱን ማስታወስ የሚገባን መቼ ነው?

• ለዳኛችንን "ዘወትር" እንዴት ልናስታውሰው እንችላለን?

• በሣምንቱ ውስጥ እርሱን ለማስታወስ እንዲረዳን ምን ማድረግ እንችላለን? (መጸለይ፣ ቅዱሳን መጽሐፍትን ማጥናት፣ ትዕዛዛቱን መታዘዝ፣ ፍቅር ማሣየት።)

ኢየሱስን ማስታወስ ማለት በቀላሉ እርሱ በምድር ይኖር እንደነበር እና እኛን ከኃጢያት እንደዋጀን ከማስታወስ በላይ እንደሆነ አትኩትሮት ስጥበት። ምናልባትም እርሱን ለማስታወስ በጣም አስፈላጊው መንገድ ዘወትር የእርሱን ትምህርት እና ትዕዛዛት ማክበር ነው።

ጥቅሶች

የሚከተለውን ንግግር አንድ ወጣት ወንድ እንዲያነብ አድርግ፣

"ቅዱስ ቁርባንን በተካፈልን ቁጥር፣ በአብ ፊት የእርሱን ልጅ ማስታወሳችንን እናሳያለን፣ እናም በዳቦው እና በውሃው የመካፈል ድርጊት ውስጥ፣ የለዳኛችንን ስም በላያችን ላይ የተከበረ ቃል ኪዳን እንገባለን፣ ያንን በማድረጋችን፣ በተጨማሪ፣ ውል እና ስምምነት በመፈጸም በዚያ ድርጊት ትዕዛዛቱን እንጠብቃለን" (Melvin J. Ballard, *Sermons and Missionary Services of Melvin J. Ballard*, በ Bryant S. Hinckley የተዘጋጀ [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Deseret Book Co., 1949], ገጽ 147)።

• የለዳኛችንን ትዕዛዛት መጠበቅ ማለት ምን ማለት ነው?

ቅዱስ ቁርባንን በምንካፈልበት ጊዜ ስለምንገባቸው ቃል ኪዳኖች በመናገር፣ ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ. ማኬይ ያሉትን ግለጽ፣ "እንደዚህ ያለውን የቃል ኪዳን ኃላፊነት ማን ሊለካው ይችላል? ሊደረስበት የማይችል! ሁሉን ያቀፈ! ከሰው ሕይወት ውስጥ ዓለማዊ ጸባይ፣ ባለጌነት፣ በዘኔነት፣ ቀናተኛነት፣ ጠጪነት፣ ወስላታነት፣ ጥላቻ፣ ራስ ወዳድነት እና ማንኛውንም የክፋት መልክን ለይቶ ያስቀራል። ለጠንካራ ሠራተኛነት፣ ለደግነት፣ በሀገሩ እና በቤተክርስቲያን ውስጥ ለየትኛውም ተግባር ከንዋኔ፣ . . . ቅዱስ ቁርባን ያስገድደዋል። ባልንጀሮቹን ለማክበር፣ ክህነትን ለማክበር፣ አስራትን እና በኩራቱን ለመክፈል እና ለሰብዓዊነት አገልግሎት ሕይወቱን ለመቀደስ እራሱን ያቀራኛል" (*Millenial Star*, ታህሳስ 1923, ገጽ 778)።

ቃል ኪዳኖቻችንን ስንጠብቅ፣ ለዳኛችን በመንፈሱ እንደሚባርከን እና ትክክለኛ ውሣኔዎችን እንድናደርግ እንደሚረዳን እንደገና ትኩረት ስጥበት።

• የጌታ የተስፋ ቃል ለእኛ ይህን ያህል በጣም አስፈላጊ የሆነበት ለምንድን ነው? (መንፈስ ቅዱስ ሊያስተምረን፣ ሊመራን፣ ሊያጽናናን፣ እውነትን ሊመሰክርልን፣ እና በእምነትና ምስክርነት እንድናድግ ሊረዳን ይችላል።)

ያለ መንፈስ ቅዱስ የማንጸት ተጽዕኖ፣ የሰማዩ አባታችን ወዳለበት ለመመለስ እንደማንችል ግለጽ።

---

**ቅዱስ ቁርባንን መካፈል ትርጉም ያለው ሊሆን ይገባዋል**

የማሰላሰያ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን የማሰላሰያ ጥያቄዎች ስታነብ ወጣት ወንዶቹን የመጨረሻውን ቅዱስ ቁርባን የተካፈሉበትን አገልግሎት እንዲያስታውሱ ጠይቅ።

• ዝምተኛ እና ቅዱስ ቁርባንን አክባሪ ነበርክን?

• ስለ ቅዱስ ቁርባኑ መዝሙር ቃላት አስበህ ነበርን?

• የቅዱስ ቁርባኑን ፀሎት በሙሉ ሐሳብ አድምጠህ ነበርን?

• ገብተሀቸው ስለነበሩት ቃል ኪዳኖች አስበህ ነበርን?

• ቅዱስ ቁርባኑ ሲዘዋወር አንተ ምን እያሰብህ ነበር? ዳቦውን እና ውሃውን ስትካፈልስ?

• ቅዱስ ቁርባኑን ስታገለግል፣ ለሌሎች መንፈሣዊ ተሞክሮ እንዲሆንላቸው ለመርዳት ምን ልታደርግ ትችላለህ?

ውይይት እና ዕደላ

• በእያንዳንዱ ሳምንት ቅዱስ ቁርባንን ለመካፈል እራሳችንን እንዴት ማዘጋጀት እንችላለን?

በእያንዳንዱ ሳምንት ከልብ ንስኃ በመግባት እና የጐዳናቸውን ሰዎች ይቅርታ በመጠየቅ ለቅዱስ ቁርባን ልንዘጋጅ እንደምንችል አትኩሮት ስጥበት።

ቅዱስ ቁርባኑን እንዴት የበለጠ ትርጉም ያለው ለማድረግ ጥቆማዎችን የያዘውን የዕደላ ቅጂ ለእያንዳንዱ ወጣት ስጥ፡፡ በሣምንቱ ውስጥ ሊያነቧቸው በሚችሉበት ሥፍራ ላይ የታደሉትን ጥቆማዎቹን እንዲያስቀምጧቸው ሐሳብ አቅርብ፡፡ ዝርዝሮቹን በአጠቃላይ ከክፍሉ ጋር አንብብ፡፡

ምንባቦች

አስቀድመው የተመደቡትን ሁለት ወጣት ወንዶች ስለ ቅዱስ ቁርባን የሚከተሉትን የወጣት ሰዎች ምስክርነት እንዲያነቡ ጠይቅ፡፡

*የመጀመሪያ ምስክርነት*

“በቅዱስ ቁርባኑ ወቀት አክባሪ ሆኜ እና ስለ ክርስቶስ በማስብበት ግዜ፣ ኢየሱስ ለሁላችንም እንዴት እንደተሰቃየ እና ምን ያህል እንደሚወደን አስባለሁ፡፡ በቅዱስ ቁርባኑ ወቀት አክባሪ ካልሆንኩ ለምን “አሜን” እንደምል አልገነዘብም፡፡ ቅዱስ ቁርባኑን የምወስደው ልማድ ስለሆነ ብቻ ነው ምክንያቱም በእርግጥ ምንን እንደሚወክል በመረዳት ስላልሆነ፡፡ ቅዱስ ቁርባኑ ምንን እንደሚወክል በምረሳ ወይንም ግድ በማይኖረኝ ግዜ፣ በእርግጥ ምንም ዓይነት ስሜት አይኖረኝም፡፡ ስለ ክርስቶስ ሳስብ ነው ጥሩ ስሜት የማገኘው—የሚወደን እና ከጠየቅነው ሁል ግዜም የሚረዳን ታላቅ ወንድም አለን፡፡ ለእኛ ለመሞት ፈቃደኛ መሆኑ ለእኔ ታላቅ ነገር ነው።”

*ሁለተኛ ምስክርነት*

“ባለፉት ጊዜያት፣ በቅዱስ ቁርባን ፀሎት ላይ “አሜን” ስል ምን ዐይነት ቃል ኪዳን እየወሰድኩ እንዳለሁ አልገነዘብም ነበር፡፡ ምን ነገር እየተደረገ እንዳለ በእርግጥ አላውቅም ነበር፡፡ በፀሎቱ ውስጥ እየተባለ ካለው ይልቅ ለጓደኞቼ ንግግር አትኩሮት እሰጥ ነበር። ባለፈው እሁድ በእውነት የቅዱስ ቁርባኑን ፀሎት ሰማሁኝ እና፣ ‘የልጅህን ስም ይቀበሉ ዘንድ’ ይላል፡፡ ዳቦው እና ውሃው ክርስቶስን ለማስታወስ እንደሚረዱን ተገነዘብኩ፡፡ ቁጭ አልኩ እና ክርስቶስ ለኔ ምን እንዳደረገልኝ አሰብኩ፡፡ ከክርስቶስ ጋር ያለኝን ቃል ኪዳን ወደፊት በጠንካራ ሁኔታ ለመጠበቅ እጥራለሁ፡፡”

---

**ቅዱስ ቁርባን የመንፈሣዊ ዕድገት ምንጭ ነው**

ጥቅስ

“የተፀፀትንባቸውን እና ይቅር ልንባል የምንሻቸውን ነገሮች እናደርጋለን፣ ወይም አንድ ሰውን መጥፎ አድርገንበታል እናም ጉድተንዋል፡፡ ላደረግነው ነገር እንዳዘንን በልባችን ውስጥ የሚሰማን ስሜት ካለ፣ በነፍሳችን ውስጥ ይቅር እንድንባል የመፈለግ ስሜት ካለ፣ ይቅርታን የማግኚያው መንገድ እንደገና በመጠመቅ አይደለም፤ ለሰውም መናዘዝ አይደለም፣ ነገር ግን ለኃጢአቶቻችን ንስኃ መግባት፣ ኃጢዓት ወይም በደል ወደ ፈፀምንብቸው ሰዎች መሄድ እና ምህረታቸውን ማግኘት እናም ከዚያ ወደ ቅዱስ ቁርባን ጠረጴዛ መሄድ፣ እዚያም ከልባችን ንስኃ ገብተን ከሆነ እና ራሳችንን በትክክለኛው ሁኔታ ካስቀመጥን፣ ይቅር እንባላለን፣ እናም መንፈሣዊ ፈውስ ወደ ነፍሣችን ይመጣል፡፡ በእርግጥ ወደ እኛነታችን ይዘልቃል” (Melvin J. Ballard, *Sermons and Missionary Services of Melvin J. Ballard*, በ Bryant S. Hinckley ተዘጋጀ [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Deseret Book Co., 1949], ገጽ 149)፡፡

የሚጠኑ ጉዳዮች

ወጣት ወንዶቹ በሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ያሉት ግለሰቦች እንዴት ይቅርታን እንደፈለጉ እና ቅዱስ ቁርባንን ለመካፈል እንደተዘጋጁ ጠይቅ፡፡

1. በአትክልት ሥፍራ ሥራ ሠርተህ ጥቂት ትርፍ ገንዘብ ተከፍሎሃል እናም ያንን ገንዘብ አዲስ ብስክሌት ለመግዛት ተጠቅመህበታል፡፡ በቅዱስ ቁርባን ስብሰባ ጊዜ፣ ገንዘብህን ሁሉንም እንዳጠፋህ እና አስራትህን መክፈል እንደረሳህ ተገነዘብክ፡፡ ስለዚህ ነገር ጥሩ አይሰማህም፡፡

   • ምን ልታደርግ ትችላለህ? (በፀጥታ ፀልይ እና ይቅርታን ጠይቅ፤ በሚቀጥለው ከምትቀበለው ገንዘብ የተረሣውን አስራት ለመክፈል ተስፋ እና ቃል ኪዳን አድርግ፣ ሁል ጊዜ አስራትን በቅድሚያ ለመክፈል ቃል ግባ።)

2. የቅርብ ጓደኛህ የግል የሆነ ምስጢር ነግሮሃል፡፡ ለማንም እንደማትናገር ቃል እንደገባህለትም ታውቃለህ፣ ነገር ግን ለአንድ ለሌላ ሰው ብትናገር ምንም እንዳማይጐዳው ወሰንክ፡፡ ስለዚህ ለሌላ ሰው ተናገርክ እና ለማንም ሰው እንዳይናገርም ነገርከው፡፡ በኋላ ትምህርት ቤቱ ሁሉ ምስጢሩን እንዳወቀ ደረስክበት፡፡ የጓደኛህን እምነት ባለመጠበቅህ ሀዘን ተሰማህ፣ እናም እንደጐዳኸው አወቅህ፡፡

   • ይህንን ስህተት ለማረም ምን ልታደርግ ትችላለህ? (ወደ ጓደኛህ በመሄድ እንደተፀፀትክ ንገር፣ እናም ይቅርታውን ጠይቅ፤ ለሰማዩ አባታችንም ፀልይ እና ይቅርታን ጠይቅ፤ ይህንን ስህተት በፍጹም ደግመህ ላለመስራት ቃል ኪዳን ግባ፡፡)

እነዚህን የመሰሉ ሁኔታዎች ሊፀዱ እንደሚገባቸው ግለፅ ስለዚህም እንደዚህ ያደረጉት ቅዱስ ቁርባንን በብቃት መካፈል ይችላሉ፡፡ ቅዱስ ቁርባን ሲካፈሉ፣ ድክመታቸውን ለማሸነፍ እና የጌታን ትዕዛዛት ሁሉ ለመታዘዝ ቃል ኪዳን እየገቡ መሆናቸውን ትኩረት ስጥበት፡፡

| | ማጠቃለያ |
|---|---|
| መዝሙር | አስፈላጊ ከሆነ፣ ወጣት ወንዶቹ የቅዱስ ቁርባን መዝሙር እንዲዘምሩ አድርግ፡፡ ወይም አንድ ወጣት ወንድ የቅዱስ ቁርባን መዝሙር ቃላትን ጮክ ብሎ እንዲያነብ ልታደርግ ትችላለህ፡፡ ወጣት ወንዶቹ ለቃላቱ ትርጉም የተለየ ትኩረት እንዲሰጡ ጠይቅ፡፡ |
| ምስክርነት | ለቅዱስ ቁርባን ያለህን ስሜት በማካፈል አጠቃል፡፡ |

# ቅዱስ ቁርባንን የበለጠ ትርጉም ያለው ማድረግ

1. ቅዱስ ቁርባንን ለመካፈል ድክመታችሁን ተገንዘቡ እናም በንስሃ አማካይነት የተዘጋጃችሁ ሆናችሁ ቀረቡ።
2. የቅዱስ ቁርባኑን መዝሙር ዘምሩ እናም የቃላቱን ትርጉም አሰላስሉ፡፡
3. የቅዱስ ቁርባኑን ትርጉም በአእምሮአችሁ ውስጥ ከልሱ፡፡
4. ክርስቶስ ለእናንተ ያለውን ጥልቀ ፍቅር እና እናንተ ለእርሱ ያለችሁን ፍቅር አሰላስሉ፡፡
5. አመስጋኝ የሆናችሁባቸውን በረከቶች አስቡ፡፡
6. የቅዱስ ቁርባንን ቃል ኪዳኖች መጠበቃችሁን ለመወሰን ያለፈውን ሳምንት እንቅስቃሴዎቻችሁን ገምግሙ፡፡
7. በሚቀጥለው ሣምንት ውስጥ ድክመቶቻችሁን ለማሸነፍ ቃል ግቡ እናም የጌታን እርዳታ ጠይቁ፡፡

# 36 ምስክርነት

**ዓላማው** እያንዳንዱ ወጣት ወንድ በጥንቃቄ በምናጠና፣ በምንፀልይ፣ እና የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በምንታዘዝበት ጊዜ ምስክርነት እንድናገኝ ይረዳል።

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሣሪያዎች፣
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. ፅሑፎችን ምልክት ማድረጊያ እርሳሶች።
   ሐ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ አንድ እርሳስ።
2. የአሮናዊ ክህነት ሥልጣን ያዥ አባት የሆነ፣ አንድ ጠንካራ ምስክርነት ያለው ሰው፣ ምስክርነትን ስለማግኘት ተሞክሮውን እንዲያካፍል እና አሁን በሕይወቱ ውስጥ ይህ ምን ያህል ጠቃሚ ሆኖ እንዳገኘው እንዲገልፅ ጠይቅ። ከአምስት ደቂቃ በላይ እንዳይወስድ ጠይቀው።
3. የ"ምስክርነት መመዘኛ ጥያቄ" የሚል ለእያንዳንዱ የክፍል አባል የሚታደል ቅጂ ስራ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**ምስክርነት ምንድን ነው?**

ተሳትፎ

ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ የ"ምስክርነት መመዘኛ ጥያቄ" ቅጂ እና አንድ እርሳስ ስጥ። ክፍሉን ለእውነት ሐሰት ጥያቄው ከቁጥሮቹ ፊት ለፊት "እ" ወይም "ሐ" በማስቀመጥ ምላሽ እንዲሰጡ ጠይቅ።

*የምስክርነት መመዘኛ ጥያቄ*

_____ 1. ለእያንዳንዱ ሰው ምስክርነት ማግኘት ቀላል ነው። (ሐሰት)

_____ 2. አንድ ሰው እውነተኛ ምስክርነት ለማግኘት ራዕይ ማየት ወይም ድምፅ መስማት አለበት። (ሐሰት)

_____ 3. እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ወንጌል እውነት እንደሆነ የራሱን ምስክርነት ለማግኘት መሻት አለበት። (እውነት)

_____ 4. ዮሴፍ ስሚዝ የእግዚአሔር ነቢይ እንደሆነ በእርሱም አማካኝነት ወንጌል መመለሱን፣ ማወቅ የምስክርነት አስፈላጊው ክፍል ነው። (እውነት)

_____ 5. ሌላው የምስክርነት መሠረታዊ ክፍል የኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻው ቀን ቅዱሳን ቤተክርስቲያን ብቻ ዛሬ እውነተኛዋ ቤተክርስቲያን መሆኗን ማወቅ ነው። (እውነት)

_____ 6. አንዳንድ ሰዎች የወንጌልን ምስክርነት ከሌሎች ፈጥነው ያገኛሉ፣ ይሁንና፣ ይህ ማለት እነርሱ የበለጡ ጻድቃን ናቸው ማለት አይደለም። (እውነት)

_____ 7. ምስክርነት ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እና የዓለም አዳኝ መሆኑን ማወቅን ያጠቃልላል። (እውነት)

_____ 8. እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን ነቢይ የራሱ የሆነ የወንጌል ምስክርነት ማግኘት ነበረበት። (እውነት)

_____ 9. ጌታ በእኛ በኩል ምንም ጥረት ሳናደርግ ምስክርነት ይሠጠናል። (ሐሰት)

_____ 10. ምስክርነት ከመንፈስ ቅዱስ በራዕይ አማካኝነት ይመጣል። (እውነት)

_____ 11. እውነተኛ ምስክርነቶች ሁልጊዜ ቀስ በቀስ ከመምጣት ይልቅ በአንድ ጊዜ ይመጣሉ። (ሐሰት)

_____ 12. ወላጆችህ ምስክርነት ካላቸው፣ አንተም ወዲያውኑ አንድ ምስክርነት ትቀበላለህ። (ሐሰት)

_____ 13. ምስክርነትህን ማካፈል የሚገባህ በጾም እና በምስክርነት ስብሰባዎች ብቻ ነው። (ሐሰት)

_____ 14. በቤተክርስቲያን ውስጥ የተወለደ ሰው ስለምስክርነቱ መጨነቅ የለበትም። (ሐሰት)

_____ 15. አንዴ ምስክርነቱን ካገኘህ፣ እሱን ለማሳደግ ማጥናትህን፣ መፀለይህን እና ብቁ ሆኖ መኖርህን መቀጠል አለብህ። (እውነት)

ገለፃዎችን አንብብ እና ወጣት ወንዶቹ መልሶቻቸውን እንዲመለከቱ አድርግ። ትክክለኛውን መልሶች ስጣቸው እናም እንደ አስፈላጊነቱ አጭር ውይይት ፍቀድ። ትምህርቱ መልሶቹን በበለጠ ስለመገንዘብ እንደሚረዷቸው ግለፅ።

ውይይት

• የወንጌል ምስክርነት ምንድን ነው?

ምስክርነት እግዚአብሔር እንደሚኖር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችን መሆኑን እና የእርሱን ትምህርቶችም እውነት መሆናቸውን የሚገልፅ ግላዊ ዕውቀት መሆኑን እንዲገነዘቡ እየረዳሃቸው፣ ወጣት ወንዶቹ መልስ ይስጡ።

• የምስክርነትህ ክፍል አድርገህ ማወቅ የሚገቡህ እውነቶች የትኞቹ ናቸው?

ጥቅስ

ቄስ ቻርልስ ዲዲየር የሚከተለውን የምስክርነት ፍች ሲሰጡ፣

“[ምስክርነት] በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እግዚአብሔር እንደሚኖር እና ትናንት፣ ዛሬ፣ እና ለዘለዓለም የማይቀየር መሆኑን (ት እና ቃ 20፥12 ተመልከት) እናም ‘እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተ የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘለዓለም ሕይወት ናት’ (ዮሐንስ 17፥3) ማወቅ ነው። ምስክርነት ኢየሱስ መሲሐ መሆኑን መመስከር ብቻ ሣይሆን፣ ነገር ግን ዮሴፍ ስሚዝ አብን እና ወልድን ማየቱን፤ መጽሐፈ ሞርሞን መለኮታዊ ምንጭ እንዳለው እና ሌላኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ኪዳን መሆኑን የሚያሳምን፤ እና የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ ከነወንጌሏ እና ቅዱስ ክህነት ሥልጣኗ፣ በእውነት እና ሐቀ የመመለሷን ዕውቀት የሚወስን ወይም የሚያረጋግጥ ሐቀ ነው” ብለዋል (በ Conference Report, ጥቅምት 1991, ከገጽ 84–85; ወይም *Ensign*, ህዳር 1991, ገጽ 62)።

---

**እኛ እያንዳንዳችን የራሳችን ምስክርነት ያስፈልገናል**

ጥቅስ እና ውይይት

እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ችግሮች እንደሚያጋጥሙት እና እነርሱንም ለማሸነፍ እንዲረዳው የራሱ የሆነ ምስክርነት ሊኖረው እንደሚያስፈልግ ግለጽ። የሚከተለውን የፕሬዚዳንት ሂበር ሲ ኪምቦል ገለጻ አካፍል፣

“የሚመጡትን ችግሮች ለመመቋቋም፣ የዚህ ሥራ የእውነተኛነት ዕውቀት ለራስህ ሊኖርህ ያስፈልገሃል። ችግሮቹም አንድ ወንድ ወይም ሴት ይህ ግላዊ ዕውቀት ወይም ምስክርነት ከሌላቸው የመሰናክልን ፀባይ ይሆናሉ። ምስክርነት ከሌለህ፣ በፅድቀ እየኖርክ ጌታን ተጣራ እና እሥክታገኘውም አታቋርጥ። ካላገኘህ ግን. . . . ልትቀም አትችልም. . . .።

“ . . . ወንድም ሆነ ሴት በተውሶ ብርሃን [በሌላ ሰው ምስክርነት] ለመጽናት የማይችሉበት ጊዜ ይመጣል። እያንዳንዱ በራሱ ውስጥ ባለ ብርሃን መመራት ይኖርበታል። ከሌላችሁ፣ እንዴት ልትቆሙ ትችላላችሁ?” (በ Orson F. Whitney, *Life of Heber C. Kimball* [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Bookcraft, 1945], ገጽ 450)።

• እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ የወንጌል ምስክርነት ያስፈለገው ለምንድን ነው? (የሚያጋጥሙትን ችግሮች ማሸነፍ ይችል ዘንድ።)

• በምን ሁኔታዎች ውስጥ ነው ምናልባት ወንጌል እውነት እንደሆነ ማወቅ የሚያስፈልግህ? (ትእዛዛትን ለመጠበቅ፣ ስለ ወንጌል ከሌሎች ጋር ስትነጋገር፣ ስለ ክርስቶስ ስታስተምር፣ በሚሲዮን ስታገለግል፣ ፈተና ሲያገጥምህ ይረዳህ ዘንድ።)

የማሰላሰያ ጥያቄዎች

• ምስክርነት ኖሮ ግን ሣያቁት የሚቻል ነውን?

ወጣት ወንዶቹን በትምህርቱ መጀመሪያ ላይ ካሉት መመዘኛ ጥያቄዎች አንዱ እያንዳንዱ የቤተክርስቲያኗ ነቢይ የራሱ የሆነ የወንጌል ምስክርነት ማግኘት ነበረበት የሚል እንደነበረ አስታውሳቸው። እያንዳንዱም እንዳገኘ፣ ነገር ግን እያንዳንዱ ልክ ሌላው ማድረግ እንዳለበት ሁሉ ለምስክርነት መሻት እና መስራት ነበረበት።

ታሪክ እና ውይይት

ዮሴፍ ኤፍ ስሚዝ፣ የቤተክርስቲያኗ ስድስተኛው ፕሬዚዳንት የሆኑት፣ የመጀመሪያ ሚሲዮናቸውን ያገለገሉት ገና የአስራ አምስት ዓመት ልጅ ሳሉ ነበር። ፕሬዚዳንት ዮሴፍ ኤፍ ስሚዝ የርሳቸውን ምስክርነት እንዴት እንዳገኙ የሚከተለውን ታሪክ አንድ ወጣት ወንድ እንዲያነብ አድርግ።

“ልጅ ሳለሁ መጀመሪያ አገልግሎት እንደጀመርኩ፣ ምስክርነት አገኝ ዘንድ፣ በተደጋጋሚ ወደ ውጪ በመውጣት ጌታ ድንቀ ነገሮችን እንዲያሳየኝ እጠይቀው ነበር። ነገር ግን ጌታ ተአምራትን ለኔ ከመግለጽ ተቆጠበ እና እውነትን እረድፍ በረድፍ፣ ትዕዛዝ በትዕዛዝ፣ ጥቂት በዚህ ጥቂት በዚያ እያለ እውነትን ከራስ ፀጉሬ እስከ እግር ጥፍሬ እንዳውቀ እስኪያደርገኝ ድረስ፣ እውነትን አሳየኝ. . . .። ይህን ለማድረግ ከሰማያት መልአክ መስደድ አልነበረበትም . . .። በትንሽ የሚያንሾካሹከው የረጋ ድምጽ የሕያው እግዚአብሔር መንፈስ፣ አሁን ያለኝን ምስክርነት ሰጠኝ” (*Gospel Doctrine*, 5ኛ ህትመት [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Deseret Book Co., 1939], ገጽ 7)።

• በመጀመሪያ ዮሴፍ ኤፍ ስሚዝ ምስክርነት ለማግኘት እንዴት ነበር የጠበቁት? (ራዕይን በመቀበል።)

በህይወታቸው ውስጥ ዘግይቶ፣ የቤተክርስቲያኗ ፕሬዚዳንት በሆኑትበት ግዜ ድንቀ መገለጦችን ከጌታ እንደተቀበሉ ግለጽ። ሙታንን ስለ መዋጀት አሁን በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ክፍል 138 ውስጥ የሚገኘው ራዕይ ተሰቷቸዋል።

• የፕሬዚዳንት ስሚዝ ምስክርነት ያደገው እንዴት ነው? (ዝግ ብሎ በዝምታ በሚያንሾካሽከው፣ ትንሽ ድምፅ።)

ጥቀስ

ብዙ ሰዎች በአንድ ጊዜ የሚቀበሉት ምስክርነት ትንሽ መሆኑን ግለጽ። ፕሬዚዳንት ማሪዮን ጂ ሮምኒይ ስለ ምስክርነት የሚከተለውን ገለፃ አድረገዋል፦

አንዳንድ ጊዜ ምስክርነት ወደ አንድ ሰው በቀስታ፣ ረዘም ላለ ግዜ ይመጣል። በድንገት ወደ እኔ የመጣ ምስክርነትን አላስታውስም—። ምስክርነት ያጣሁበትን ግዜ ማስታወስ አልችልም። በእርግጥ፣ ምስክርነቱ፣ በዓመታት ውስጥ ነው የጠነከረው፣ ነገር ግን ያላመንኩበትን ግዜ በፍጹም ማስታወስ አልችልም። ነገር ግን ምስክርነት በድንገት ወይም በየደረጃው ይምጣ፣ ለሰውየው ጥቂት ነገር ይፈይድለታል። አንድ ሰው ምስክርነት ከተቀበለ በኋላ የተለየ ነው” (“How to Gain a Testimony,” *New Era*,ግንቦት 1976,ገጽ 11)።

ታሪክ

ሌላም ነቢይ በተመሳሳይ መንገድ ምስክርነትን እንዳገኘ ግለጽ። ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ ዘወትር ምስክርነት ለመፈለግ ስለነበራቸው ትግል ይናገሩ ነበር። የሚከተለውን ታሪክ አንድ ወጣት ወንድ እንዲያነብ አድርግ።

“በልጅነቴ አንድ ቀን ከብት እየጠበኩ ነበር። ቀጥ ያለ ኮረብታ ከወጣሁ በኋላ፣ ፈረሴ አረፍ እንዲል ቆም አልኩኝ፣ እናም አዚያ፣ እንደገና ስለተመለሰው ወንጌል እውነተኝነት መገለጥን ለመቀበል ከፍተኛ ፍላጐት አደረብኝ። ከፈረሴ ላይ ወረድኩ፣ ልጓሙን ወደ ፈረሴ ጭንቅላት ወረወርኩ፣ እና በቁጥቋጦው ተክል ስር ተንበርክኬ እግዚአብሔርን ለዮሴፍ ስሚዝ የሰጠውን ራዕይ እውነተኝነት እንዲያሳውቀኝ ጸለይኩ። አንድ ወጣት ልጅ ሊኖረው በሚችል እምነት እንዲሁም በስሜት እና ከልብ እንደጸለይኩ እርግጠኛ ነኝ።

“በጸሎቱ ማብቂያ ላይ፣ ከተንበረከኩበት ተነስቼ፣ ልጓሙን በታማኙ ግልገል ፈረሴ ጭንቅላት ላይ ወረወርኩ፣ እና ኮርቻው ላይ ወጣሁ። የመንገዱን ዱካ ይዤ መጓዝ እንደጀመርኩ፣ ለራሴ፣ ‘ምንም መንፈሳዊ መገለጥ ወደ እኔ አልመጣም። ለራሴ ሐቀኛ ከሆንኩ፣ ልክ ከመጸለዬ በፊት እንደነበርኩት “የጥንቱ ልጅጁ መሆኔን መናገር አለብኝ’ ማለቴን አስታውሳለሁ።

“ጌታ በዚያን ወቀት መልስ ሊሰጠኝ ብቃትን አላየም፣ ነገር ግን በ1899፣ የስኮትላንድ ኮንፈረንስ ፕሬዚዳንት ሆኜ ከተሾምኩ በኋላ፣ ልጅ ሳለሁ በአስራዎቹ ዕድሜዬ የጸለይኩበት ተግባሬን ስወጣ እንደ ተፈጥሮአዊ ክስተት መጣ” (Clare Middlemiss, comp., *Cherished Experiences from the Writings of President David O. Mckay* [ሶልት ሌክ ከተማ፦ Deseret Book Co., 1976], ከገጽ 6–7)።

ውይይት

• ፕሬዚዳንት ማኬይ፣ “የጸለይኩበት መንፈሣዊ መገለጥ—ተግባሬን ስወጣ እንደ ተፈጥሮአዊ ክስተት መጣ” ሲሉ ምን ማለታቸው ይመስልሃል?

ወጣት ወንዶቹ የፕሬዚዳንት ማኬይ ጸሎት በመንፈስ አማካኝነት መልስ ያገኘው የክህነት ሥራን ሲሰሩ እንደሆነ ይገነዘቡ ዘንድ እየረዳሃቸው መልስ ይስጡ።

• ፕሬዚዳንት ዮሴፍ ኤፍ ስሚዝ እና ፕሬዚዳንት ኦ ማኬይ ምስክርነት ለማግኘት ያሏቸው ተሞክሮዎች እንዴት ተመሳሳይ ነበሩ? (ከምስክርነቶቹ አንድም በመጀመሪያ ጥያቄ አልመጣም፣ ሁለቱም ሰዎች ለምስክርነት ከፍተኛ ፍላጐት ነበሯቸው፣ ሁለቱም ተዓምራትን ጠብቀው ነበር፣ ሁለቱም ብቃት ያለው ሕይወት ኖሩ እና በቀላል መንገድ ምስክርነቶቻቸውን ተቀበሉ።)

---

**የአሮናዊ ክህነት ሥልጣን ያዥ የራሱን ምስክርነትን በጸሎት እና በሥራ ሊያጠናክር ይችላል**

የቅዱስ መጽሐፍ ጥቀስ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ውይይት

ቅዱሳን መጽሐፍት አንድ ሰው እውነትን እንዴት ማወቅ እንደሚችል ማብራራታቸውን ትኩረት ስጥበት።

የተለያዩ የክፍሉ አባላት የሚከተሉትን ቅዱሳን መጻሕፍት ሲያነቡ ሌሎቹ እንዲከታተሉ አድርግ፣ አልማ 32፡27፣ ሞሮናይ 10፡3–5፣ እና ዮሐንስ 7፡17። እነዚህን ጽሑፎች በጥቁር ሠሌዳው ላይ ፃፍ እና ወጣት ወንዶቹ ምልክት ያደርጉባቸው ዘንድ አሳስብ።

ፅሑፎቹ ሲነበቡ፣ ወጣት ወንዶቹ እውነትን ለማግኘት የሚወስዱትን እርምጃዎች ለይተው እንዲያውቁ አድርግ። እርምጃዎቹን በጥቁር ሠሌዳው ላይ ዘርዝር። የሚሰነዝሩት መልሶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

1. ከልብ መሻት።
2. ማንበብ እና ማጥናት።
3. ማሰብ እና በልብህ ውስጥ ማሰላሰል።
4. ከልብ ጸልይ
    ሀ. የሰማዩ አባትን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ጠይቅ።
    ለ. ለማወቅ በመሻት እና ከእውነተኛ ልብ ጠይቅ።
    ሐ. እውነትን ታውቅ ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ባለ እምነት ጠይቅ።
    መ. መንፈስን ታዳምጥ ዘንድ ከጸሎት በኋላ በልብህ አሰላስል።
5. ትዕዛዛትን ጠብቅ።
6. የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እውነትን ይገልጽልሃል።

ለአንዳንድ የወንጌል መሠረተ ኃሳቦች ምናልባት ወጣት ወንዶቹ አስቀድመው ምስክርነት አግኝተው እንደሆነ እንዲገነዘቡ እርዳቸው።

• አንዳንድ እውነት ሆነው ያገኘሃቸው የወንጌል መሠረተ ሀሳቦች ወይም ትምህርቶች የትኞቹ ናቸው?

መልሶቹ የጥበብ ቃልን፣ አስራትን፣ እና ታማኝ መሆንን ሊያካትቱ ይችላሉ።

አንዱን የተወሰነ ትምህርት እውነት መሆኑን ስናውቅ፣ የአስተሳሰቦቻችን እና የድርጊቶቻችን አንዱ ክፍል እንደምናደርገው ግለጽ። ከዚያም የዚያ ትምህርት ምስክርነት ይኖረናል።

ጥቅስ እና ውይይት

• አንድ ነገር እውነት መሆኑን መንፈስ ቅዱስ እንዴት ይገልጽልናል?

አንድ ወጣት ወንድ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 8፡2–3 እንዲያነብ አድርግ። አንድ ነገር እውነት በሆነ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ የሚሞቅ ወይም የሚያቃጥል ስሜት እንዲሰማን እንደሚያደርግ ግለጽ።

አንድ ወጣት ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 6፡22–23 እንዲያነብ አድርግ።

• ይህ ቅዱስ መጽሐፍ አንዳንድ ግዜ መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር ስለሚገኝበት መንገድ ምን ይነግረናል?

ተጋባዥ ተናጋሪ

ምስክርነቱን እንዴት እንዳገኘ ለወጣት ወንዶቹ የሚያካፍለውን፣ ተጋባዥ ተናጋሪ አስተዋውቅ።

---

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት እና ሙከራ

ስለ አዳኛችን እና ስለ ወንጌል እውነተኝነት ምስክርነትህን ስጥ። እያንዳንዱ የክፍል አባላት በጸሎት እና በጥናት እንዲሁም ለእግዚአብሔር ትዕዛዛት በታዛዥነት በመኖር የራሱ የሆነ ምስክርነት ሊያገኝ እንደሚችል መስክር።

ወጣት ወንዶቹ በትምህርቱ ውስጥ የተዘረዘሩትን እርምጃዎች በመከተል ምስክርነትን እንዲያገኙ ሞክር። ለጸሎቶቻቸው ምናልባት ቀጽበታዊ መልስ እንደማያገኙ አትኩሮት ስጥበት። ይሁንና፣ የክህነት ተግባሮቻቸውን መወጣት ሲቀጥሉ፣ በመጨረሻ በፈለጉት ጠንካራ ምስክርነት ይባረካሉ።

---

# የምስክርነት መመዘኛ ጥያቄ

______ 1. ለእያንዳንዱ ሰው ምስክርነት ማግኘት ቀላል ነው።

______ 2. አንድ ሰው እውነተኛ ምስክርነት ለማግኘት ራዕይ ማየት ወይም ድምፅ መስማት አለበት።

______ 3. እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ወንጌል እውነት እንደሆነ የራሱ የሆነ ምስክርነት ለማግኘት መፈለግ አለበት።

______ 4. ዮሴፍ ስሚዝ፣ የእግዚአብሔር ነቢይ እንደሆነ በእርሱም አማካኝነት ወንጌል መመለሱን ማወቅ የምስክርነት አስፈላጊው ክፍል ነው።

______ 5. ሌላው የምስክርነት መሠረታዊ ክፍል የኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻው ቀን ቅዱሳን ቤተክርስቲያን ብቻ ዛሬ እውነተኛ ቤተክርስቲያን መሆኗን ማወቅ ነው።

______ 6. አንዳንድ ሰዎች የወንጌልን ምስክርነት ከሌሎች ፈጥነው ያገኛሉ፤ ይሁንና፣ ይህ ማለት እነርሱ የበለጡ ፃድቃን ናቸው ማለት አይደለም።

______ 7. ምስክርነት ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እና የዓለም አዳኝ መሆኑን ማወቅን ይጨምራል።

______ 8. እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን ነቢይ የራሱ የሆነ የወንጌል ምስክርነት ማግኘት ነበረበት።

______ 9. ጌታ በእኛ በኩል ምንም ጥረት ሳናደርግ ምስክርነትን ይሰጠናል።

______ 10. ምስክርነት፣ ከመንፈስ ቅዱስ በራዕይ አማካኝነት ይመጣል።

______ 11. እውነተኛ ምስክርነቶች ሁልጊዜ በቀስታ ከመምጣት ይልቅ ሁሉም በአንድ ጊዜ ይመጣሉ።

______ 12. ወላጆችህ ምስክርነት ካላቸው፣ ወዲያውኑ አንተም አንድ ታገኛለህ።

______ 13. ምስክርነትህን ማካፈል የሚገባህ፣ በጾም እና በምስክርነት ስብሰባዎች ብቻ ነው።

______ 14. በቤተክርስቲያን ውስጥ የተወለደ ሰው ስለ ራሱ ምስክርነት መጨነቅ የለበትም።

______ 15. አንዴ ምስክርነቱን ካገኘህ፣ ምስክርነትህን ለማሳደግ ማጥናትህን፣ መጸለይህን፣ በብቃት ሆኖ መኖርህን መቀጠል አለብህ።

# 37 የአሮን ክህነት

**ዓላማው**

እያንዳንዱ ወጣት ወንድ የእሱን ክህነት ስልጣን ምንጭ እና አስፈላጊነት በመማር በተሻለ ሁኔታ ጥሪውን ይገነዘባል፡፡

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቀዱሳን መጽሐፍት፡፡
   ለ. ስዕል 13፣ ሙሴ አሮንን ለአገልግሎት ሲጠራው (62538)፡፡
   ሐ. ጥቀሶችን ምልክት ለማድረጊያ እርሳሶች
2. አንድ ወጣት በዮሴፍ ስሚዝ—ታሪክ መጨረሻ ላይ በግርጌ ማስታወሻ ውስጥ ከአንቀፅ አምስት እስከ ሰባት ያሉትን የኦሊቨር ካውድሪን መግለጫ እንዲያነብ አዘጋጅ፣ እና ስለተሞክሮው ያለውን ስሜት ይግለፅ፡፡
3. አንድ ወጣት ወንድ እና አባቱ በክህነት ኃይል ያገኙትን ልዩ ልምድ ያካፍሉ ዘንድ ጋብዝ፡፡ ያኔ ያ ልምድ ለነርሱ ምን ማለት እንደሆነ እና አሁን በክህነት በሕይወታቸው ውስጥ ምን ማለት እንደሆነ እንዲገልፁ አድርግ፡፡

**ለትምህርት ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**አሮን መጀመሪያ ተጠራ**

ሥዕል እና ውይይት

ሙሴ አሮንን ሲሾመው የሚያሳየውን ሥዕል አሳይ፣ እናም ሙሴ እና አሮን የትኞቹ እንደሆኑ ለወጣት ወንዶቹ ለይተህ አመልክት፡፡

- በሥዕሉ ላይ ምን እየተደረገ ነው? (ሙሴ አሮንን ለክህነት ሲሾመው፡፡)
- ስለ አሮን ምን ታውቃለህ? (የሙሴ ወንድም ነበር እናም ለሙሴ እንዲናገር እና እንዲረዳው ተጠራ፡፡)
- አሮን ለምን ለእኛ አስፈለገ? (አሮናዊ ክህነት የአሮንን ስም ተሰጥቶታል፡፡ እኛ የአሮንን ክህነት ይዘናል፡፡)

ቀዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

አንድ ወጣት ወንድ ዕብራዊያን 5፡4 ሲያነብ ሌሎቹ ከመጽሐፍ ቀዱሶቻቸው ላይ እንዲከታተሉ አድርግ፡፡

- በዚህ ጥቀስ መሠረት፣ ክህነትን እንዴት ነው የምንቀበለው? (እንደ አሮን በእግዚአብሔር ልንጠራ ይገባል፡፡)

ወጣት ወንዶቹ ይህን ጥቀስ ምልክት እንዲያደርጉበት አድርግ፡፡ አሮን እንዴት ለክህነት እንደተጠራ የሚያብራራ ሌላ ጥቀስ ለማግኘት የግርጌ ማስታወሻዎች ወይም ማጣቀሻዎች እንዲጠቀሙ ጠይቃቸው፡፡

ወጣት ወንዶቹ ትክክለኛውን ጥቀስ ለማግኘት ከተቸገሩ፣ ዘፀአት 28፡1 እንዲገልጡ ንገራቸው፡፡ አንድ ወጣት ወንድ ይህን ጥቀስ ሲያነብ ሌሎች አብረው እንዲከታተሉ አድርግ፡፡

- አሮን እንዴት ነበር የተጠራው?

አሮን በሙሴ አማካኝነት ክህነትን ለመቀበል በእግዚአብሔር እንደተጠራ ወጣት ወንዶቹ እንዲገነዘቡ እርዳቸው፡፡ በተጨማሪም አንድ ሰው በእግዚአብሔር ክህነት እንዲቀበል ከተጠራ በኋላ፣ እጆችን በመጫን መሾም እንደሚገባው ግለፅ፡፡

አንድ ወጣት ወንድ ዘኁልቁ 27፡18–20፣ 22–23 እንዲያነብ አድርግ፡፡

ወጣት ወንዶቹ እነርሱም እንደ አሮን፣ እያሱ፣ እና እንደ ሌሎች ክህነትን የተቀበሉ ሰዎች ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ እንደተጠሩ ይገነዘቡ ዘንድ እርዳቸው፡፡ የአሮናዊ ክህነት ያዦች ከእግዚአብሔር በጳጳስ አማካኝነት ይጠራሉ፡፡ ወደ ጉባኤ ይቀርባሉ ከዚያም ስልጣኑ ባላቸው እጅ በመጫን ይሾማሉ፡፡

የአማካሪው አቀራረብ

አሮን የክህነት ጥሪውን ሲቀበል ዕድሚው ሰማንያ ሦስት እንደነበር እና ያካህን መሪ ወይም የአሮናዊ ክህነት ራስ እንደነበረ ግለፅ፡፡ ይህም በግምት ከሶስት ሺህ አምስት መቶ ዓመታት በፊት፣ ወይም ከክርስቶስ ልደት አንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመታት በፊት ነበር፡፡

- ዛሬ አብዛኛዎቹ ወጣት ወንዶች የአሮናዊ ክህነትን የሚቀበሉት ዕድሚያቸው ምን ያህል ሲሆን ነው? (አስራ ሁለት ዓመት፡፡)

አሮን እና ልጆቹ የሚከውኑት የተለየ ሥራ ወይም ሥርዓት ተሰጥቷቸው ነበር። በሙሴ ግዜ፣ የአሮናዊ ክህነት አባላት ዕድሚያቸው ቢያንስ ሠላሳ ዓመት መሆን ነበረበት። የይሁዳ ከባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም መመለስን ተከትሎ፣ ዕድሜው ወደ ሃያ እና ከዛያ በላይ ተቀየረ። (ዘኍልቁ 4፡43፤ እዝራ 3፡8 ተመልከት።)

በጥንት ዘመን፣ የአሮናዊ ክህነትን ለመያዝ አንድ ሰው በቀጥታ ከአሮን ዘር መሆን እንደነበረበት ግለፅ። መጥምቁ ዮሐንስ በረጅም የዘር ሐረግ ከአሮን ወገን ነበር።

---

**መጥምቁ ዮሐንስ**

ቅዱስ መጽሐፍ፣ ጥቅስ፣ እና ውይይት

አንድ ወጣት ወንድ ትምህርት እና ቃል ኪዳን 84፡28 እንዲያነብ አድርግ።

ቁስ ብሩስ አር ማኮንኪ በዚህ ቁጥር ላይ የሚከተለውን አስተያየት እንደሰጡ ግለፅ፡

“ለሕጻናት ስም መስጠት እና ወንዶችን መግረዝ በቤተእስራኤል አባላት የሚደረገው በዚህ [ስምንተኛ] ቀን ነበር። ዮሐንስን በተመለከተ፣ እርሱ ‘በእግዚአብሔር መልአክ የስምንት ቀን ዕድሜ በሆነው ጊዜ ነበር የተሾመው’—ለአሮናዊ ክህነት አይደለም፣ ይኼኛው ቀይቶ ነው የመጣው፣ ከጥምቀቱ እና ከሌላ ዝግጅቶች በኋላ፣ ነገር ግን—‘በዚህ ኃይል፣ የአይሁድን መንግስት ለመጣል፣ በሕዝቡ ፊት የጌታን መንገድ ለማቀናት፣ እና ለጌታ መምጣት እነርሱን ለማዘጋጀት፣ ኃይል ሁሉ በእጁ ተሠጠው።’ (ት እና ቃ 84፡28።) እናም፣ በዚህ የስምንተኛ ቀን ሞገስ ባለው ክብረ በዓል፣ መልዓኩ፣ ምናልባትም ገብርኤል፣ ከዘመናት ሁሉ ታላቀ መንገድ ጠራጊ ሆኖ እንዲያገለግል የጌታን ኤሊያስ መለኮታዊ ተልዕኮ ሰጠው” (Bruce R. McConkie, *Doctrinal New Testament Commentary*, 3 vols. [ሶልት ሌክ ከተማ፡ Bookcraft, 1965], 1፡89)።

ወጣት ወንዶቹ የመጥምቁ ዮሐንስ ተልዕኮ ምን ያህል አስፈላጊ እንደነበር እንዲገነዘቡ እርዳቸው። ይህም ደግሞ አሮናዊ ክህነት እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ ማሳየቱን ግለጽ።

አንድ ወጣት ወንድ የሉቃስ 7፡28 የመጀመሪያ ክፍል እንዲያነብ አድርግ።

• ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ከምታውቀው ውስጥ፣ እንደዚህ ያለ ታላቀ ነቢይ ያደረገው ምንድን ነው? (ኢየሱስን አጥምቋል፣ እና ለኢየሱስ አገልግሎት መንገድ አዘጋጅቷል።)

ጥቅስ

በነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ የተሰጠውን ተከታዩን ገለፃ አንብብ፡

“መጥምቁ ዮሐንስ ከታላላቀ ነቢያት እንደ አንዱ የተቆጠረው እንዴት ነው? . . .

“አንደኛ። በጌታ ፊት መንገድን ያዘጋጅ ዘንድ የመለኮታዊ ተልእኮ አደራ ተሰጥቶት ነበር። ከሱ በፊት ወይም ከሱ ጀምሮ እንዲህ ዓይነቱን መታመን የፈጸመ ማን አለ? ማንም።

“ሁለተኛ። የሰውን ልጅ እንዲያጠምቅ፣ . . . አስፈላጊ የሆነ ተልዕኮ ተሰጥቶት ነበር፣ እናም ከእጆቹ ይፈለግበት ነበር።

“ሦስተኛ። ዮሐንስ፣ በዚያን ጊዜ፣ በወቀቱ በምድር ላይ ለነበረችው መንግስት ጉዳዮች ውስጥ ብቸኛው ህጋዊ አገልጋይ ነበር፣ እናም የሥልጣን ቁልፎችን ይዟል። አይሁዶች ትዕዛዛቱን መታዘዝ ነበረባቸው ወይም፣ በራሳቸው ሕግ መረገም፣ እናም እራሱ ክርስቶስ ለሕግ ታዛዥ በመሆን ጽድቅን ፈጽሟል . . .። ቀብ ቁዱስ እና በመንግስተ ሰማያት ዓዋጅ የዘካሪያስ ልጅ ቁልፎችን፣ መንግስትን፣ ኃይልን፣ ክብርን ከአይሁዶች በኃይል ነጠቀ፣ እና እነዚህ ሦስት ምክንያቶች እርሱን እስከ ዛሬ ከሴት ከተወለዱት ሁሉ ታላቀ ነቢይ ያደርጉታል” (*Teachings of the Prophet Joseph Smith*, comp. Joseph Fielding Smith [ሶልት ሌክ ከተማ፡ Deseret Book Co., 1938], pp. 275– 76)።

የአማካሪው አቀራረብ

ወጣት ወንዶቹ መጥምቁ ዮሐንስ ተግባሩን ለመፈጸም ያሳየውን ድፍረት የመገንዘብ ስሜት እንዲያዳብሩ እርዳቸው። አይሁዶችን ወደ ንስኃ ጠራቸው እንዲሁም ልማዶቻቸውን እንዲያቀሙ ታገለ። ከተቀበሉት እና ከተጠመቁ እናም መንፈስ ቁዱስን ከተቀበሉ ሊያድናቸው ስለሚቻለው፣ መጪው መሲህ መሰከረ።

ሌላው የዮሐንስ ወኔ የሔሮድስን ኃጢያት፣ የወንድሙን ሚስት የሆነችውን፣ ሔሮድያዳን ለገዛ ራሱ ሚስትነት መውሰድ በድፍረት ወንጀል መሆኑን ማውገዝ እንደነበር ግለጽ። በእርግጥ፣ ሄሮድስ እና ሔሮድያዳ በኃጢያት የተጨማለቀው ግንኙነታቸውን ዮሐንስ ማውገዙን አልወደዱትም። ያለጥርጥር፣ ሄሮድስ መጥምቁ ዮሐንስን ሊገድለው ወዶ ነበር፣ ነገር ግን ዮሐንስን እና ብዙ ጓደኞቹን ፈራቸው። ስለዚህ በምትኩ ዮሐንስን ወደ ወህኒ አወረደው።

ከሁለት ዓመት በኋላ፣ በሔሮድስ የልደት በዓል ላይ፣ ሰሎሜ፣ የሄሮድያዳን ሴት ልጅ፣ ለሔሮድስ ዘፍናለት በጣም ስላስደሰተችው የፈለገችውን ሊሰጣት ቃል ገባ። ሰሎሚ እናቷን፣ ሔሮድያዳን፣ ምን እንደምትጠይቀ ጠየቀቻት እና እናቲቱ በወጭት የመጥምቁ ዮሐንስን ጭንቅላት እንዲመጣላት እንድትጠይቀ ነገረቻት። ምንም እንኳን ሄሮዶስ ፍቃደኛ ባይሆንም፣ ቃሉን ፈጸመ እናም ዮሐንስ ጭንቅላቱን ተቀረጠ። (ማቴዎስ 14፡3–11 ተመልከት።)

ውይይት

• እኛ በሕይወታችን ውስጥ ለማዳበር መጣር የሚገባን የመጥምቁ ዮሐንስ አንዳንድ መለያ ባህሪያት የትኞቹ ናቸው?

የሚከተሉትን ነጥቦች ወጣት ወንዶቹ እንዲያነሱ እርዳቸው፣

1. ዮሐንስ ለጌታ እራሱን አሳልፎ ሰጥቷል እናም ጌታን በሚያስፈልገው ሁሉ አገልግሏል። ሌሎች የሚሉትን ወይም የሚያደርጉትን በመተው የታዘዘውን አድርጓል።
2. ዮሐንስ የክህነት ሥልጣኑን በብቃት ተጠቀሞበታል።
3. ዮሐንስ ርኩሰትን በድፍረት ተቃውሞታል።

• ወደ አንድ ወጣት ወንድ ሕይወት ውስጥ ምናልባት ድፍረትንና እና መስዋእትነትን የሚጠይቁ ምን ዓይነት ፈተናዎች ይመጣሉ?

---

### የአሮናዊ የክህነት ሥልጣን መመለስ

**ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት**

ከመጥምቁ ዮሐንስ፣ ከኢየሱስ፣ እና ከኃዋሪያት ሞት በኋላ፣ የክህነት ሥልጣን ከምድር ላይ ጠፍቶ ነበር። አሮናዊ የክህነት ሥልጣን በግምት ከመጥምቁ ዮሐንስ ሞት ከአስራ ስምንት መቶዎች ዓመታት በኋላ መመለስ ከዘመናችን እጅግ በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ክስተቶች አንዱ ነበር።

• በመጨረሻዎቹ ቀናት ወደ ምድር አሮናዊ የክህነት ሥልጣንን የመለሰው ማን ነው? (መጥምቁ ዮሐንስ)።

አንድ ወጣት ወንድ የዮሴፍ ስሚዝ—ታሪክ 1፥68 ሲያነብ፣ ሌሎቹ ከመጽሐፍቶቻቸው ላይ እንዲከታተሉ አድርግ።

• ዮሴፍ ስሚዝ እና ኦሊቨር ካውድሪ አሮናዊ የክህነት ሥልጣንን እንዴት ነበር የተቀበሉት? (ትክክለኛ ስልጣን ባለው አንድ ሰው እጆችን በመጫን።)

ይህንን ክስተት ወጣት ወንዶቹ በተሻለ ሁኔታ ለመገንዘብ እንዲረዳቸው፣ ሌላ ወጣት ወንድ የዮሴፍ ስሚዝ—ታሪክ 1፥69–72 እንዲያነብ አድርግ። እነዚህን ቁጥሮች ወጣት ወንዶቹ ምልክት እንዲያደርጉባቸው አሳስብ።

• መጥምቁ ዮሐንስ ለምንድን ነው የአሮናዊ ክህነት ለመመለስ የተላከው? (የዚህን ክህነት ቁልፎች በመያዙ።)

አሮናዊ የክህነት ሥልጣን መመለስ ለሙሉው ወንጌል የመመለስ የመጀመሪያው እርምጃ መሆኑን ግለጽ።

**የማስታወስ ተሳትፎ**

ወጣት ወንዶቹን የዮሴፍ ስሚዝ—ታሪክ 1፥69 እንዲያስታውሱ እርዳቸው።

ወጣት ወንዶቹ በፀጥታ ከምንባቡ ላይ ሲያነቡ የሚከተሉትን ቁልፍ ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ አስፍር። ከሦስት ወይም አራት ደቂቃዎች በኋላ፣ ወጣት ወንዶቹ መጽሐፍቶቻቸውን እንዲዘጉ እና በቃላቸው ባዶ ቦታዎቹን ለመሙላት እንዲጥሩ አድርግ።

በእናንተ ላይ ____________________ ፣በ ____________________ ስም ____________________

በእሰጣችኋለሁ፣ የሚይዛቸው ቁልፎችም ____________________ ወንጌልን፣ እንዲሁም

____________________ ጥምቀት ነው፣ ይህ ክህነት____________________ ልጆች

____________________ ድረስ ____________________።

ወጣት ወንዶቹ የተለያዩትን ባዶ መስመሮች በቃላቸው እንዳስታውሱ፣ ምንባቡን በቃላቸው ደጋግመው መናገር እስኪችሉ ድረስ የቃላቶቹን ቁልፍ ክፍል አጥፋ።

**ጥቅስ**

ኦሊቨር ካውድሪ አሮናዊ የክህነት ሥልጣንን ሲቀበል እንዴት እንደተሰማው ለማየት፣ በዮሴፍ ስሚዝ—ታሪክ ማብቂያ ላይ ያለውን ታሪክ አስቀድሞ የተመደበው ወጣት ወንድ ሲያነብ ሌሎቹ ከመጽሐፍቶቻቸው ላይ እንዲከታተሉ አድርግ (“ዝግጅት” ተመልከት)። ወጣቱ ወንድ ስለዚህ ተሞክሮ የተሰማውን ስሜት እንዲገልጽ አበረታታው።

• ኦሊቨር ካውድሪ እንዴት ነበር የተሰማው? (ሰላም፣ ደስታ፣ ሙሉ ፍስሃ፣ አድናቆት፣ ይህን የመሰለ በረከት ለማግኘት ታደለ።)

**የአባት እና ልጅ ተሞክሮt**

አስቀድመው የተመደቡት አባት እና ልጅ ስለ ክህነት ሥልጣን ኃይል ያላቸውን ተሞክሮ እንዲያካፍሉ እና የክህነት ሥልጣን ለእነሱ ምን ማለት እንደሆነ እንዲገልጹ አድርግ።

---

### ማጠቃለያ

**ምስክርነት**

ያለህን የአሮናዊ የክህነት ሥልጣን የተቀደሰ ተፈጥሮ ምስክርነት ስጥ። ወጣት ወንዶቹ መጥምቁ ዮሐንስ ለዮሴፍ ስሚዝ የመለሰውን የክህነት ሥልጣን መያዛቸውን ትኩረት ስጥበት።

**ሙከራ**

እያንዳንዱ ወጣት ወንድ አሮናዊ የክህነት ሥልጣንን በመያዙ ስለላው የተቀደሰ ጥሪ በጥልቀ ያስብበት ዘንድ ሞክር። እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ከኛ በፊት ያለፉትን ታላላቅ አርአያዎች እንዲከተል እና በክህነት ሥልጣኑ ውስጥ የተቀደሰ ጥሪውን በይበልጥ በደንብ እንዲያጉላ ሞክር።

# የአሮናዊ ክህነት ያዥ ጥሪን ማጉላት 38

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ወንድ በተሻለ ሁኔታ የክህነት ሥልጣን ኃላፊነቶቹን ለመወጣት ይሻል። |
| **ዝግጅት** | 1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፥ ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት። 2. ለእያንዳንዱ ክፍል አባላት "እኔ አንድ ብቻ ነኝ" የሚለውን የዕደላ ቀጂ አዘጋጅ። |

**ለትምህርት ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**አሮናዊ የክህነት ሥልጣን ያዥ የተቀደሱ ኃላፊነቶች አሉት**

ውይይት

• በአሮናዊ የክህነት ሥልጣን የሚፈጸሙ ተግባሮች በድንገት ቢቆሙ ኖሮ በቤተክርስቲያን ውስጥ ምን ዓይነት ለውጦች ይከሰቱ ነበር?

ይህን ጥያቄ ወጣት ወንዶቹ እንዲወያዩ ፍቀድ። ቅዱስ ቁርባን እና ድሀዎችን ለመርዳት ጳጳሶች እንዲጠቀሙበት የተሰበሰበ ምንም ዓይነት የጾም በኩራት እንደማይኖር ይገነዘቡ ዘንድ እርዳቸው።

• በአሮናዊ የክህነት ሥልጣን የሚከናወነው የክህነት ሥልጣን ሥራ አስፈላጊነቱ እንዴት ነው?

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሳኤው በኋላ ኔፋይቶችን በጎበኘበት ግዜ፣ የቅዱስ ቁርባንን አስፈላጊነት እንዳስተማራቸው ግለጽ።

አንድ ወጣት ወንድ 3ኛኔፊ 18፥1–12 ጮክ ብሎ እንዲያነብ አድርግ። ጥሩ አንባቢ የሆኑትን ንባብ እንዲያግዙ ጠይቀ። በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ያሉትን አስፈላጊ ነጥቦች ተወያይ፣ እንደ—

1. ቅዱስ ቁርባን በጣም የተቀደሰ ሥርዓት ነው።
2. ዘወትር ከቅዱስ ቁርባን እንድንካፈል ታዘናል።
3. ቅዱስ ቁርባን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድናስታውስ ይረዳናል።
4. የኢየሱስ ክርስቶስ ትዕዛዛት ሁሉ ለመታዘዝ ተስፋ እንሰጣለን ወይም ቃል ኪዳን እንገባለን።
5. የኢየሱስ ክርስቶስን ትዕዛዛት ስንታዘዝ፥ ሁልግዜም ከእኛ ጋር መንፈስ ቅዱስ እንደሚኖር ተስፋ ተሰጥቶናል።
6. ተገቢውን የክህነት ሥልጣን የያዙ ብቻ ቅዱስ ቁርባንን ማስተላለፍ ይችላሉ።

የቁርባንን የተቀደሰ ባህርይ ወጣት ወንዶቹ እንዲገነዘቡ እርዳቸው። በአግባቡ እንዲለብሱ እና በጥንቃቄ፣ በብቃት፣ እና በአክብሮት ቅዱስ ቁርባኑን እንዲያገለግሉ አበረታታቸው።

• አንድ የአሮናዊ ክህነት ያዥ አክብሮት ባለው ሁኔታ ቅዱስ ቁርባንን ሲያገለግል ሌሎች የቤተክርስቲያንን አባላት እንዴት ይረዳቸዋል? (አባላትን በጥምቀታቸው ላይ የገቡትን ቃል ኪዳኖች እንዲያድሱ እና ለኃጢዓቶቻቸው ምህረት እንዲያገኙ ዕድሉን ያቀርባላቸዋል። እያንዳንዱ ቅዱስ ቁርባን ምን ያህል የተቀደሰ መሆኑን አዲማር ይረዳል።

ጥቅስ

ጳጳስ ኤች ፒተርሰን እንዲህ እንዳሉ ግለጽ፣ "የቁርባን ክፍል ግዜ በጣም ልዩ ክፍል ግዜ ነው፣ እናም እናንተ አሁን የዚህ አስፈላጊው ክፍል ናችሁ። ከፊተኛው እናንተነታችሁ አሁን የተለያችሁ ናችሁ" (በ Conference Report, ጥቅምት 1981, ገጽ 49; or *Ensign*, ሐዳር 1981, ገጽ 34)።

• አንድ አሮናዊ የክህነት ሥልጣንን የያዘ አሮናዊ የክህነት ሥልጣን ከሌለው በሱ እድሜ ካለ ወጣት ወንድ ሊለይባቸው የሚገቡት አንዳንድ መንገዶች ምንድን ናቸው?

ምስክርነት

የቅዱስ ቁርባንን የተቀደሰ ባህሪይ እና ቅዱስ ቁርባንን ለቤተክርስቲያን አባላት ለማዘጋጀት እና ለማስተላለፍ የአሮናዊ የክህነት ሥልጣን ያዦችን ኃላፊነት መስክር።

አሮናዊ የክህነት ሥልጣንን የያዘ ወጣት ወንድ ሌሎች አሮናዊ የክህነት ሥልጣንን ካልያዙ ልዩ ሊሆን እንደሚገባው ትኩረት ስጥበት።

ጥቅስ እና ውይይት

• አንድ አሮናዊ የክህነት ሥልጣንን የያዘ የጾም በኩራትን የሚቀበላቸውን አባላት እንዴት ይረዳቸዋል?

የጾም በኩራትን በመሰብሰብ፥ አባላቶች ድሀን እና የሚያስፈልጋቸውን በመርዳት ጌታን እንዲያገለግሉ እድል እንደሚሰጣቸው ወጣት ወንዶቹ ይገነዘቡ ዘንድ እርዳቸው።

አንድ ወጣት ወንድ ሞዛያ 4፥26 ጮክ ብሎ እንዲያነብ አድርግ፡፡

የጾም በኩራትን ስንከፍል ለድሀ ካለን ንብረት ማካፈል፣ ወይም በሌላ አነገገር፣ የተራበን ማብላት እና የታረዘን ማልበስ መሆኑን ግለጽ፡፡

• የጾም በኩራቶች ድሃን እና ችግረኛን ለመርዳት እንዴት ይጠቀማሉ?

ወጣት ወንዶቹ የጾም በኩራቶች ድሀን እና ችግረኛን ለመርዳት ብቻ እንደሚጠቀሙ ይገነዘቡ ዘንድ እርዳቸው፡፡ ገንዘቡ በጳጳሱ ለችገረኛው ሰው የመብራት ፍጆታ ወጪን፣ የቤት ኪራይን ለመክፈል፣ ወይም አስፈላጊ መድኃኒት ለመግዣ፣ ወይም የጳጳሱ መጋዘን ቀርብ ካልሆነ የሚያስፈልገውን ምግብ እና ልብስ ለመግዣ ይጠቀማል፡፡ ቀሪው ገንዘብ ወደ ዋናው ቤተክርስቲያን መምሪያ ተልኮ በሌላው ዓለም በችግር ላለ አባል መጠቀሚያ እንዲሆን ያደርጋል።

ጥቀስ

"ጌታ በሕይወትህ ውስጥ ሌሎችን ትረዳ ዘንድ ካለው ኃይል እና ሥልጣን የተወሰነውን ላንተ እንደሚያካፍል ተናግሯል፡፡

"...በችግር ያሉትን ከመርዳት በላይ ምንም የሚያስደስት ተግባር የለም፡፡ የጾም በኩራትን መሰብሰብ ጳጳሱን እና ድሃውን እንደ መርዳት ስትመለከተው ለአንተ በረከት ነው፡፡ አንድ ቀን በሰበሰብከው ጾም በኩራት ጳጳሱ ለአንዲት መበለት አንዳንድ የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦችን ሲወስድላት ወይም የቤት ኪራይዋን ሲከፍልላት በፊቷ ላይ ፈገግታ ወይም ከዓይኖቿ እንባን ለማየት ያጋጥምህ ይሆናል" (H. Burke Peterson, በ Conference Report, ጥቅምት 1981, ገጽ 49; or *Ensign,* ሕዳር 1981, ገጽ 34)፡፡

---

**አሮናዊ ክህነት ያዡች ኃላፊነቶቻቸውን ለመወጣት ትጉ መሆን ይገባቸዋል**

የሚታደል ጽሑፍ እና ውይይት

• እንደ አሮናዊ ክህነት ያዥነትህ በአግባቡ ኃላፊነቶችህን መወጣት ቢያቀትህ ምን ይከሰት ይሆን?

ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ "እኔ አንድ ብቻ ነኝ" የሚለውን የዕደላ ቀጂ ስጥ፡፡ አንድ ወጣት ወንድ ይህን ግጥም ጮክ ብሎ እንዲያነብ አድርግ፡፡ ትርጉሙንም ተወያይ፣ እናም ግጥሙን ለማስታወስ የክፍል ሥራውን አግዝ፡፡

---

**ማጠቃለያ**

የቅዱስ መጽሐፍ ንባብ እና ሙከራ

አንድ ወጣት ወንድ 1ኛ፥ኔፊ 3፥7 እንዲያነብ አድርግ፡፡

ወጣት ወንዶቹ የተቀበሏቸውን ምድብ ሥራዎች የችሎታቸውን ያህል እንዲፈጽሙ እና ኔፊን እንዲመስሉ አበረታታ፡፡

ኃላፊነቶቻቸውን በአክብሮት በመወጣት ለሌሎች ጥሩ ምሣሌ እንዲያሳዩ ሞክር፡፡

---

# እኔ አንድ ብቻ ነኝ

እኔ አንድ ብቻ ነኝ፣
ግን አሁንም አንዱ ነኝ፡፡
ሁሉን ነገር ባልችልም መስራት፣
ግን አሁንም አንድ ነገር እችላለሁ መስራት፣
እና ሁሉን ነገር ለመሥራት ባለመቻሌ ምክንያት
መስራት የምችለውን ጥቂት ነገር እምቢ አልልም ለመሥራት።

(Edward Everett Hale, በ *Bartlett's Familiar Quotations*, በጆን በኖትለት የተጠረዘ John Bartlett, 14th ed. [Boston: Little, Brown, and Company, 1968],ገጽ 717)፡፡

# ሚሲዮናዊ ስራ በአርአያነት

# 39

**ዓላማው**

እያንዳንዱ ወጣት ወንድ አርአያ ባለው ሕይወቱ ወንጌልን ያሰራጫል፡፡

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. ቅዱሳን መጻሕፍት ምልክት ማድረጊያ እርሳሶች፡፡
   ሐ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ እርሳስ፡፡
2. የሚከተሉትን ጥቅሶች የያዘ ፓስተር አዘጋጅ (አማራጭ)፣ “ማንኛውም የመጨረሻው ቀን ቅዱስ ብዙ ነፍሳት እኛ እያንዳንዳችን በምናሳየው ምሳሌ እና ተጽእኖ አማካኝነት እንደሚተርፉ ወይም እንደሚጠፉ ማወቅ ይገባዋል” (John T. Kesler, “Being an Example,” *Ensign*, ጥቅምት 1977, ገጽ 58)፡፡
3. “እኔ ምን ዓይነት ምሳሌ ነኝ?” የሚለውን የሚታደል ጽሑፍ ቅጂ ለእያንዳንዱ ወጣት አዘጋጅ፡፡
4. ሁለት ወይም ሦስት ወጣት ወንዶች ጥሩ ምሣሌ በመሆን ወይም ወንጌልን በበለጠ ለመማር ስላበረታታቸው የሚያውቁት ሰው ልምዳቸውን ተዘጋጅተው እንዲያካፍሉ ጠይቅ፡፡

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**ሌሎችን በምሳሌያችን ወደ ቤተክርስቲያን እንዲሳቡ ማድረግ እንችላለን**

ታሪክ

የሚከተለውን እውነተኛ ታሪክ ከእነርሱ ጋር ስትካፈል ወጣት ወንዶቹ የትምህርቱን ዋና መልእክት ለመወሰን እንዲጥሩ ጠይቅ፣

“ እናት፣ ሚሪ ግርሃም፣ የአስራ አራት ዓመት ልጅ በነበረችበት ግዜ፣ አባቷ **በሞት** አልጋ ላይ ተኝቶ ነበር፡፡ የቤተክርስቲያኗ ቄስ በራሪ ወረቀት ይዞ፣ የወንጌልን መመለስ ሊናገር ወደ በሩ መጣ፡፡ አባቷ በራሪ ወረቀቷን አንብቦ እንዲህ አለ፣ “ሚሪ፣ የእኔ ልጅ፣ እውነት ነው፡፡ ያ ወጣት ሰው እውነተኛ ወንጌልን ይዞ ነበር የመጣው፡፡ ይህን እውነተኛ ወንጌል ፈልጊ . . .እናም ተቀበዪው፡፡”

“ ‘ከአባቷ ሞት በኋላ (እናቷ ከጥቂት ዓመታት በፊት ሞታለች)፣ የሙት ልጅ የሆነችው ሚሪ በባለፀጋው አለን ቤተሰብ ውስጥ አገልጋይ ሆነች፡፡ ሞርሞናዊነትን እየመረመረች መሆኑን ባወቁ ግዜ፣ እነኚህን ስብሰባዎች በመካፈሏ ንግዳቸውን እየጎዳቸው መሆኗን በቁጣ ነገሯት፡፡ ይህን የተጠላ ኃይማኖት የአለን ቤተሰቦች እንደሚደግፉት ሰዎች ማሰብ ጀምረው ነበር።

“ ‘በጨለማው እና ዝናብ በበዛበት ምሽት ሁሉም የአለን ቤተሰቦች ተሰብስበው ሚሪን በፊታቸው አስጠሯት፡፡ አባትየው በመመረር፣ “ሚሪ፣ በሩ ይኸው፡፡ ምርጫሽን አሁኑኑ ምረጪ፡፡ ወይ ሞርሞናዊነትን አቁሚ እና በቤታችን (ውስጥ ቆዩ)፣ አሊያም ከቤታችን ወጥተሽ ወደ ጨለማው (ሂጂ)” አላት፡፡ እሷም አለቀሰች፡፡ በእርግጥ ብትቆይ ደስ ይላታል፣ ነገር ግን ወንጌልን ልትክደው አልተቻላትም፣ እውነት መሆኑን አውቃ ነበርና፡፡ ቤት የለሿ ሚሪ በኪሷ ውስጥ አንድ ሽልንግ ብቻ ይዛ በአስፈሪው እና በቀዝቃዛው ጭለማ ወጥታ ሄደች ያንን ሽልንግ የአባቷ ጓደኛ ለሆነው ሰው፣ በዚሁ ዋጋ እልፍኙን ሚሲዮናዊያኖቹ ለመስበክ ይቻላቸው ዘንድ አከራይቷት ስለነበር ከፈለችው፡፡

“ ‘ጓደኞች ሚሪን አስጠጓት፡፡ ሌላም ሥራ አገኘች፣ አገባች፣ እንዲሁም በስኮትላንድ ውስጥ የተወለዱ፣ አስራ ሦስት ልጆች ያለው ቤተሰብ አገኘች፡፡ በ1872 ወደ ዩታህ መጡ፡፡ (የሚሪ ቤተሰቦች) ሶልት ሌክ ከተማ በደረሱበት ግዜ፣ የአለን ቤተሰብ እንኳን ደህና መጣችሁ ለማለት እዚያ ነበር እናም ለግሩም የእራት ግብዣ ወደ ቤታቸው ወሰዷቸው፡፡ “በቤተክርስቲያን ውስጥ ለመገናኘታችን ምክንያቱ አንቺ ነሽ፣” ሲሉ ገለፁ፡፡

“ ‘እውነተኛውን እምነቷን ከመተው ይልቅ ሚሪ በድፍረት የስኮትላንድ ቤታቸውን ጥላ ስትሔድ፣ የአለን ቤተሰቦች ኃይማኖቷ ለየት ያለ ነገር መሆን አለበት ብለው ደመደሙ፡፡ እነርሱም ከተግባቧቸው ጣፋጭ [እና] ብልጫ ካላቸው . . .ልጃገረዶች ውስጥ አንዷ መሆኗን ያውቃሉ፡፡ አቶ አለን፣ “ያለውድታዬ ስለ ሞርሞናዊነት ከምንገነዘበው በላይ የሆነ ነገር እንዳለ ይሠማኛል፣ ሰው ሰራሽ ኃይማኖት ሊሆን አይችልም” ብሏል፡፡ እሱ እና ቤተሰቡም መረመሩ፣ ቤተክርስቲያኗን ተቀላቀሉ፣ ወደ ዩታህም ተሰደዱ፣ እናም ሚሪ እና ቤተሰቧ በደረሱ ግዜ እንኳን ደህና መጣችሁ ብለው አቀባበል አደረጉላቸው’ ” ( በ Robert D. Young, እንደተነገረው “Genealogical Evenings in the Home,” *Improvement Era*, ጥር 1965, ገጽ 33)፡፡

• ሚሪ በአሰሪዎቿ ላይ ያንን ያህል ተፅእኖ ያሳደረችው ምን ዓይነት ሰው ብትሆን ነው?

**የአማካሪው አቀራረብ**

• እንደ ስፖርታዊ ውድድር ቦታ ላይ ወይም አዳራሽ ወይም በሲኒማ ቤት አንተ እዚያ መኖራቸውን እንኳ ሳታውቅ የሆነ ቦታ ሰዎች እንዳዩህ—ነግሮህ የሚያውቅ ሰው አለ?

• አንተ ሳታውቅ ሌሎች ልብ እያደረጉህ እንደነበር እንድትገነዘብ አደረገህ?

ከተቻለ፣ አንድ ወጣት ወንድ አንተ እንዳስተዋልከው እንደሆነ ሳያውቅ የሆነ ነገር ሲያደርግ ያየህበትን አጋጣሚ ተናገር። ቢያውቁትም ባያውቁትም ድርጊቶቻቸው በሌሎች እንደሚታይ ይገነዘቡ ዘንድ እርዳቸው።

• በማናቸውም ግዜ ጥሩ ምሳሌ ማሳየት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? (ድርጊቶቻችን አንድን ሰው ወደ ወንጌል ይስቡት ይሆናል። ይሁንና፣ ትክክለኛ ያልሆነው ምሳሌ ሌሎችን የበለጠ ወንጌልን ለማወቅ መፈለግን እንዲተውት ሊያደርጋቸው ይችላል።)

**ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት**

• መጥፎ ምሳሌን በሚያሳዩ ሰዎች የሰማዩ አባት ምን የሚሰማው ይመስልኃል?

አንድ ወጣት ወንድ የማርቆስ ወንጌል 9፥42 እንዲያነብ አድርግ እና ይህን ቁጥር በመጥፎ ምሳሌዎቻቸው ሌሎችን ከሚያሰናክሉት ጋር በማዛመድ ተናገር።

**ጥቁር ሠሌዳ ወይም ፖስተር**

ያዘጋጀህውን ፖስተር አሳይ ወይም የሚከተሉትን ጥቅሶች በጥቁር ሠሌዳው ላይ ፃፍ፡ “ማንኛውም የመጨረሻው ቀን ቅዱስ ብዙ ነፍሳት እኛ እያንዳንዳችን በምናሳየው ምሳሌ እና ተጽእኖ አማካኝነት እንደሚተርፉ ወይም እንደሚጠፉ ማወቅ ይገባዋል” (John T. Kesler, “Being an Example,” *Ensign*, ጥቅምት 1977, ገጽ 58)።

• የእኛ ምሳሌ ሌሎች እውነትን እንዲያገኙ እንዴት ይረዳቸዋል?

ብዙ ሰዎች በአባላቱ መልካም ምሳሌ አማካኝነት ቤተክርስቲያኗን እንደተቀላቀሉ አመልክት።

ለሌሎች ወንጌልን ማስተዋወቅ ማለት ዘወትር ከእነርሱ ጋር መቀመጥ እና ስለ ኃይማኖት ማውራት እንዳልሆነ ግለጽ። ሌሎች ሰዎች በይበልጥ ወደ ወንጌል የሚሳቡት ሕይወታችንን በሚለውጥበት መንገድ ወንጌልን ስንኖር መመልከት ሲችሉ ነው። ቀጣዩ ምንም ባልጠበቀው መንገድ ጓደኛውን ስለ መሰጠው አንድ ወጣት እውነተኛ ታሪክ ነው።

**ታሪክ**

“አለን ሐሪስ እና ኤዲ ሆፕስ በ[ውትድርና] አገልግሎት ውስጥ ይተዋወቁ ነበር። ሐሪስ ከሌይተን፣ ዩታህ የመጣ የመጨረሻው ቀን ቅዱሳን ነበር። የሕክምና ቴክኒሻይን ነበር። ሆፕስ ደግሞ ከስፕሪንግፊልድ፣ ኦሀዩ የመጣ የኤክስሬይ ቴክኒሻይን ነበር።

“እነርሱም በጣም ተግባቡ። ማናቸውም ለምሽት ብልጭልጮች ደንታ አልነበራቸውም። ነፃነት በነበራቸው ማንኛውም ግዜ፣ እረጅም የእግር ጉዞ ይኳዙ ነበር። ታሪካዊ የሆኑ ቦታዎችን ጐብኝተዋል።

“ ‘አንድ ጊዜ ሣር ላይ ተኝተን ደመናዎችን እንመለከታለን። ከእርሻ በስተቀር በሰፊው አንዳችን ለአንዳችን አውርተናል ብዬ አላስብም። ሁለታችንም ስለ እርሻ ሁሉንም ነገር እንወድ ነበር። ስለ ኃይማኖት ብዙም ያወራን አይመስለኝም። ሁለታችንም ከጥሩ ኃይማኖታዊ ቤቶች መምጣታችንን ብቻ የምናውቅ እንመስል ነበር፣’’ ሲል አለን ተናግሯል።

“በግልፅ፣ አለን ለብዙ ዓመታት ድርጊቶቹ እና ንፁህ የአኗኗር ልምዱ ከኤዲ ጋር ከተለዋወጧቸው ቃላት ይበልጥ መልዕክታቸውን እንዳስተላለፉ አያውቅም ነበር።

“[ከጃፓን ጋር የነበረው ጦርነት ሲያበቃ፣ ሁለቱም አገልጋይ ሰዎች ወደ የቤታቸው ተመለሱ። ኤዲ ሆፕስ ኮንትራክተር ሆነ እና ቤቶችን በመገንባት ሥራ ውስጥ ተሳተፈ።] ኤዲ ሆፕስ . . . የኖርዝሪጅን መንደር የመገበያያ ማዕከል፣ ትምህርት ቤቶች እና 2200 አዳዲስ የመኖሪያ ቤቶች ለማሳደግ ንድፍ እየሠራ ነበር።

“[አንድ ቀን] ሦስት ባለትዳር ጉጉ ሴቶች ወደ ቢሮው መጡ። እነሱም አዲሱን ቀርንጫፍ የኢየሱስ ክርስቶስ የመጨረሻው ቀን ቅዱሳን ቤተክርስቲያንን እንደሚወክሉ ተናገሩ።

“ ‘ከሞርሞን ቤተክርስቲያን ጋር አንድ ነው?’ በማለት ኤዲ ጠየቀ።

“ ‘ሞርሞኖች በመባል እንታወቃለን፣’ አሉት።

“እነርሱም ሚስተር ሆፕስ ጸሎት ቤት መገንባት ይችሉ ዘንድ ቁራጭ መሬት ይሸጥላቸው እንደሆን ለማየት በቤተክርስቲያን መሪዎች እሱን እንዲያገኙት ተፈቅዶላቸው ነበር።

“ ‘በግዳጅ ላይ የእናንተ ቤተክርስቲያን አባል የነበረ አንድ ጥሩ ጓደኛ ነበረኝ፣’ አላቸው ለሴቶቹ። ‘ይመራው በነበረ ንጽሁ እና ጤናማ ሕይወት እኔ እመሰጥ እና እማረክ ነበር። የማደርገውን እነግራችኋለሁ። ጸሎት ቤት መስራት የፈለጋችሁበትን መሬት እሰጣችኋለሁ። ምንም ገንዘብ አያስወጣችሁም።’

“ኤዲ ሆፕስ ለስፕሪንግፊልድ ቀርንጫፍ ሕንፃ ግንባታ ኮሚቴ 10,000 ዶላር የሚያወጣ ስምንት ሺህ ዘጠና አራት ካሬ ሚርት መሬት አበረከተ። ደግሞም ግንባታውን የሚረዱ ሌሎች ዋጋ ያላቸውን አገልግሎቶች ሠጥቷል። የዚህ ሁሉ ምክንያቱ ኃይማኖቱን በትጋት የሚከታተለውን እና ሌሎችንም በመንፈስ ያበረታታ

የነበረውን ወጣት ሞርሞን በመተዋወቁ ነበር” (Dorothy O. Rea, “. . . When You Least Expect It,” *Church News*, ጥር 21, 1967, ገጽ 11)።

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

አንድ ወጣት ወንድ የማቴዎስ ወንጌል 5፥16 እንዲያነብ ጠይቅ። ወጣት ወንዶቹ ይህንን ቅዱስ መጽሐፍ ምልክት እንዲያደርጉበት አድርግ።

በላይኛው ታሪክ ውስጥ ያሉት ሰዎች ብርሃናቸው በሌሎች ላይ ተጽእኖ ይኖረው ዘንድ እንዴት እንዳበሩ ተወያይ።

ሪፖርቶች

በቤተሰባቸው ውስጥ ጥሩ ምሳሌ አንድ ሌላ ሰውን ስለ ወንጌል በይበልጥ እንዲማር ተፅእኖ ያደረገበትን ማንኛውንም ግላዊ ተሞክሮ እንዲያካፍሉ ለተመደቡት ተማሪዎች አጋጣሚውን ፍቀድላቸው። ከተቀሩትም ወጣት ወንዶች ማናቸውም ስለሚያውቋቸው ተመሳሳይ ተሞክሮዎች ያካፍሉ ዘንድ ፍቀድ።

---

**እኔ እንዴት ምሳሌ መሆን እችላለሁ**

የሚታደሉ ጽሑፎች

ወጣት ወንዶቹ የሚኖሩት ምን ዓይነት ምሣሌ እንደሆነ እንዲያስቡ ለመርዳት፣ “እኔ ምን አይነት ምሳሌ ነኝ?” የሚለውን የሚታደል ጽሑፍ ቅጂ እና እርሳስ ለእያንዳንዱ የክፍል አባል ስጥ። ወጣት ወንዶቹ የማረጋገጫን ዝርዝር ካሟሉ በኋላ፣ ከጥያቄዎቹ በማናቸውም ላይ አስተያየት እንዲሰጡ አበረታታቸው። የማረጋገጫ ዝርዝሮቹን ወደ ቤት እንዲወስዱ እና ምሳሌዎቻቸውን የሚያሻሽሉበትን መንገድ እንዲመለከቱ ሀሳብ አቀርብ።

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

ወጣት ወንዶቹ ትምህርት እና ቃል ኪዳን 123፥12 እንዲያነቡ እዘዛቸው። “የት እንደሚያገኙት ባለማወቃቸው ምክንያት ብቻ ከእውነት ርቀዋል።” የሚለውን ሐረግ የበለጠ አትኩሮት ስጥበት። ከዚያም የሚቀጥለውንም ንግግር አንብብ።

“ወንጌል አኗኗራችንን እንዴት እንደሚለውጠው ጥሩ ምሳሌን እያስቀመጥን ከሆነ፣ ሰዎች ያስተውሉታል— እናም ዘወትር በአኗኗራችን ለውጥን ስላመጣው ለማወቅ ዝንባሌ እየኖራቸው ይመጣሉ . . .።

“አባል ያልሆነ ልብ *መጀመሪያ* የሚከፈተው በቤተክርስቲያን እና አባላቶቿ ጥሩ የአድናቆት ስሜት እና በሚያውቋቸው አባላት ፍቅር እና አሳቢነት ነው” (Jay A. Parry, “Converts Tell . . .What Brought Me In,” *Ensign*, የካቲት 1978, ገጽ 43)።

የወንጌልን ትምህርቶች በመኖር እና ክርስቶስን በሕይወቶቻቸው ውስጥ እንደ ትልቅ ምሳሌ በመከተል እነሱም ለሌሎች ጥሩ ምሳሌ የመሆን ዕድል እንዳላቸው ወጣት ወንዶቹን አስታውስ።

ለዚህ አትኩሮት ለመስጠት፣ ሌሎቹ ቅዱሳን መጽሐፍታቸው ላይ ሲከታተሉ አንድ ወጣት ወንድ 1 ጢሞቴዎስ 4፥12 እንዲያነብ አድርግ።

---

**ማጠቃለያ**

ሙከራ

ወጣት ወንዶቹን ከማረጋገጫው ዝርዝር ላይ ማሻሻል የሚችሉበትን ሁለት ወይም ሦስት ሥፍራዎችን ይምረጡ እና በሚመጣው ሣምንት ውስጥ በእነዚህ ላይ እንዲሰሩ ሞክር።

# እኔ ምን ዓይነት ምሳሌ ነኝ?

*ዘወትር*፣ *አንዳንድ ግዜ*፣ ወይም *ከስንት አንዴ* ከሚለው ስር ያለውን ባዶ ሥፍራ እያንዳንዱን ጥያቄ በይበልጥ በሚመልስልህ ቃል አመሳክር። መልሶችህን ለሌሎች አታሳይ ወይም የአደላ ጽሑፎቻቸውን አትመልከት።

| | ዘወትር | አንዳንድ ግዜ | ከስንት አንዴ |
|---|---|---|---|
| የሌሎችን አስተያየት በአክብሮት እሰማለሁኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| ቀጠሮ ለማክበር ፈጣን ነኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| ስለ ሌሎች ሰዎች ተቃራኒውን እናገራለሁኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| ወላጆቼን፣ ወንድሞቼን እና እህቶቼን በፍቀር እንከባከባቸዋለሁን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| ለጓደኞቼ ወላጆች ትህትናን አሳያለሁን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| በትምህርት ቤት ሥራ ውስጥ ታማኝ ነኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| ጥሩ ስፖርተኛ ነኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| የብልግና ቃላትን መጠቀም አስወግጃለሁኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| መልኬና አለባበሴ ንፁህ እና ደስ የሚል ነውን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| ትምህርቴን በጥሩ ሁኔታ ለመስራት እጥራለሁኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| ትዕዛዛትን እጠብቃለሁኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| ቅዱሳን መጽሐፍትን በቁም ነገር አጠናለሁኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| ለራሴ ውድ ጓደኛ ለመሆን እወዳለሁኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| ሌሎችን ለመርዳት ደስተኛ ነኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| በወላጆቼ የተቀመጡልኝን መመሪያዎች አከብራለሁኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| ግብረገብነት ያልጐደላቸውን የቪዲዮ ፊልሞች እና ቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን እመለከታለሁኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| ከፍተኛ የግብረ ገብነት ደረጃዎች ያሏቸውን መጽሐፍትን እና መጽሔቶችን ብቻ አነባለሁኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| ለችሎታዎቼ እና ለግዚዬ ራስ ወዳድ ያልሆንኩ ነኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| አንድ ጥሩ ነገር ሲያደርጉ ጓደኞቼን ከልብ አመሰግናቸዋለሁን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| ራሴን የቻልኩ ነኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |
| በፈገግታ የተሞላ የፊት ገጽታ አጸኝን? | ☐ | ☐ | ☐ |

# የጌታ ቤት

# 40

**ዓላማው**

እያንዳንዱ ወጣት ወንድ የቤተመቅደሶችን ዓላማ እና ቤተመቅደስ ለመግባት ለምን እራሱን ብቁ አድርጐ መጠበቅ እንደሚገባው ይረዳል።

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. ሥዕል 14፣ ኪርትላንድ መቀደስ (62431)፣ ሥዕል 12፣ ሥልት ሌክ መቀደስ (62433)፣ በአካባቢህ ግልጋሎት የሚሰጠውን ቤተመቅደስ ሥዕል፣ ሥዕል2፣ በቤተመቅደስ ውስጥ የጥምቀት ገንዳ (62031)፣ ሥዕል 15፣ በቤተመቅደስ ውስጥ የሥርዓት ክፍል፣ ሥዕል 16፣ በቤተመቅደስ ውስጥ የሰሌስቲያል ክፍል፣ ክፍል 17፣ በቤተመቅደስ ውስጥ ጥንዶች ሲጋቡ።
2. ከትምህርቱ መጀመሪያ ላይ ስለ ቤተመቅደስ ስድስቱን ጥቀሶች በሌላ ቁራጭ ወረቀት ላይ ፃፍ።
3. ጳጳሱ ከወጣት ወንዶቹ ጋር በቡድኑ ስብሰባ እንዲገኝ ጋብዝ። ጳጳሱ መገኘት ካልቻለ፣ አማካሪው የእርሱን ቦታ እንዲወስድ ይጠይቀው። ጳጳሱ ወይም አማካሪው ትምህርቱን እንዲከልሱትን አድርግ ስለዚህም ወጣት ወንዶቹ ምናልባት ስለ ቤተመቅደስ ዓላማ እና ወደሱም ለመግባት እራሳቸውን በደንብ ለማዘጋጀት ስለሚችሉባቸው መንገዶች የሚጠይቁትን ጥያቄዎች ለመመለስ ዝግጁ ይሆናል። ይህን ትምህርት ለማቀረብ ሁለት ሣምንታት ውሰድ። ሁለት ሣምንታት ለመውሰድ ካሰብክ፣ ጳጳሱን ወይም አማካሪውን በሁለተኛው ሣምንት ላይ እንዲሳተፉ ጋብዝ።
4. በአካባቢህ የሚገኝ ከሆነ *ወደ እኔ ኑ* (53146)፣ ከሚለው የቪድዩ ካሴት ውስጥ “በቀዱስ ቤቱ ውስጥ” የሚለውን አሣይ።

**ለትምህርት አድገት የቀረበ ሐሳብ**

**መግቢያ**

ጥቀሶች

ከዚህ በፊት ስለ ቤተመቅደስ የተዘጋጁትን ጥቀሶች ከወጣት ወንዶቹ ውስጥ ለስድስቱ ስጥ። አንድ ቤተመቅደስ ተገንብቶ ካለቀ እና ከመመረቁ በፊት፣ ሕንጻው ለሕዝብ ክፍት ይሆናል ስለዚህም ስዎች በውስጡ መዘዋወር እና መመልከት ይችላሉ። የሚከተሉት ጥቀሶች ቤተመቅደስ ከመመረቁ በፊት ተጉዘዉ ከጎበኙ እና ስለጉብኝቱ ስሚታቸዉን ከገለጹ አንዳንድ የመጨረሻ ቀን ቀዱሳን ወጣት ወንዶች የመጡ ናቸዉ። ጥቀስ የተሰጣቸው እያንዳንቸው ወጣት ወንዶች ለተቀሩት ወጣት ወንዶች እንዲያነቡ ጠይቀ።

1. “በቤተ መቀደስ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ እንደዚህ ያለ አስደናቂ ስሜት ነበረኝ፣ ለቀቄ መዉጣት አልፈለኩም ነበር።”
2. “የጌታን ቤት ለማየት 600 ማይልስ ከተጓዝኩ በኋላ፣ ከዚያም ተሞክሮን ባገኘሁ ግዜ፣ በዓለም ዙሪያ ቢጓዙለትም ዋጋ የነበረው መሆኑን አስተዋልኩ።”
3. “ቤተ መቀደሱ በሙሉ የሰማያት አንዱን ክፍል ይመስላል።”
4. “እስከዛሬ ተሰምቶኝ ከሚያውቀው የበለጠ ሰላማዊ ስሜት ተሰማኝ።”
5. “እዚያ የነበረው መንፈስ የማይታመን ነው።”
6. “በቤተመቅደስ ውስጥ ለመጋባት በጣም እንደምፈልግ አውቃለሁ።”

(ከላይ ያሉት ጥቀሶች ከ “Inside a House of the Lord,” *New Era*, ሚያዚያ 1972, ገጽ 25 የተወሰዱ ናቸው።)

ከወጣት ወንዶቹ ማናቸውም ቤተመቅደስ ከመመረቁ በፊት ጉብኝተው የነበሩ ካሉ፣ በዚያ አጋጣሚ ላይ ምን እንደተሰማቸው እንዲያካፍሉ ጋብዛቸው።

**የቤተመቅደሶች ዓላማ**

ጥቁር ሠሌዳ እና ውይይት

በጥቁር ሠሌዳው እናት አቀራቢያ ላይ *ቤተመቀደስ . . .ነው* የሚል ፃፍ

በትምህርቱ የመጀመሪያ ክፍል ወቀት ወጣት ወንዶቹ ስለቤተመቀደስ አምስት ነገሮችን እንደሚማሩ ንገራቸው፡፡

በመጀመሪያ የትምህርት ክፍል ማጠቃለያ ላይ፣ ጥቁር ሰሌዳው ከሚከተሉት ጋር ተመሳሳይ መሆን ይገባዋል፣

**ቤተመቀደስ . . .ነው።**

ሀ. የጌታ ቤት።

ለ. የቤተመቀደስ መንፈሳዊ በረከትን የምንቀበልበት እና ቃል ኪዳኖችን የምናደርግበት ቦታ

ሐ. ዘላለማዊ ጋብቻዎች የሚፈፀሙበት ቦታ

መ. ለሙታን ሥርዓቶችን የምናከናውንበት ሥፍራ

ሠ. የራዕይ ቦታ

ሥዕል

የኪርትላንድ ቤተ መቀደስን ሥዕል አሣይ እና ነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ የኪርትላንድን ቤተ መቀደስ በመረቀበት ግዜ፣ በቤተመቀደሱ ውስጥ የጌታ መኖር ያለማቋረጥ እንዲሰማ እና በውስጡም ለሚገቡ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ይሰማቸው ዘንድ እንደ ጸለየ ግለጽ፡፡

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

አንድ ወጣት ወንድ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 109፡12–13 እንዲያነብ አድርግ፣ ይህም የኪርትላንድ ቤተመቀደስ የመመረቂያ ጸሎት አንዱ ክፍል ነው፡፡ በዚህ ጸሎት ውስጥ ቤተ መቀደስ የሚጠራበትን ሌላ ስም እንዲያዳምጡ አድርግ፡፡

- የቤተመቀደስ ሌላው ስም ምንድን ነው? (የጌታ ቤት፡፡)

ጥቁር ሰሌዳ

በጥቁር ሰሌዳው ላይ፣ ሀ. *የጌታ ቤት ብለህ ፃፍ*፡፡ ቀዱስነቱ ያለማቋረጥ እዚያ በመኖሩ ምክንያት ቤተመቀደስ የጌታ ቤት መሆኑን አመልክት፡፡

ሥዕሎች

የሶልት ሌክ ቤተ መቀደስን ወይም በአቀራቢያህ ግልጋሎት የሚሰጠውን ቤተ መቀደስ ስዕል አሣይ፡፡ የምድራዊ ቤተሰብ ዘወትር መሰብሰቢያው ቤት መሆኑን ግለጽ፡፡ እናም የሰማዩ አባት ልጆች ነን፣ እንዲሁም ቤተመቀደስ የእሱ ቤት ነው፡፡ ስለዚህም፣ ቤተመቀደስ፣ እንደ እግዚአብሔር ብቁ የቤተሰብ አባላት፣ መንፈሱ እንዲሰማን እና ስለሱ መማር እንድንችል የምንሔድበት ሥፍራ ነው፡፡

የቤተመቀደስን የውስጥ ክፍል ሥዕሎች አሣይ፡፡ እነዚህ ሥዕሎች የቤተመቀደስን ሌላ ዓላማዎች እንደሚያስታውሱን አስገንዝብ፡፡

- *የቤተመቀደስ መንፈሣዊ በረከት* የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?

ወጣት ወንዶቹ ምላሽ እንዲሰጡ ፍቀድ፣ በዚያውም የቤተመቀደስ መንፈሳዊ በረከት ማለት የማያልቅ ዋጋ እና ታላቅ ስጦታ መሆኑን ግለጽ፡፡ ቄስ ብሩስ አር ማካንኪ ሲጽፉ "ለታማኝ እና ብቁ ቀዱሳን በቤተመቀደሶች ውስጥ የሚሰጡ የተወሰኑ ልዩ መንፈሳዊ በረከቶች *የቤተመቀደስ መንፈሳዊ ቡራኬዎች* ተብለው ይጠራሉ" (*Mormon Doctrine*, 2nd ed. [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Bookcraft, 1966], ገጽ 226)፡፡

ጥቁር ሠሌዳ እና ውይይት

በጥቁር ሠሌዳው ላይ፣ ለ. *የቤተ መቀደስ መንፈሳዊ በረከት የምንቀበልበት እና ቃል ኪዳኖች የምናደርግበተ ቦታ* በማለት አክልበት፡፡ ይህንን የቤተ መቀደስ መንፈሣዊ በረከት በምንቀበልበት ግዜም ደግሞ ቃል ኪዳኖችን እንደምንገባ፣ ወይም ለጌታ ተስፋዎች እንደምንሰጥ አመልክት፡፡

የሚከተለው ዝርዝር በቀዱሱ ቤተ መቀደሶቹ ውስጥ የምንማራቸውን፣ ለጌታ ውብ የሕይወት ዕቀድ አስፈላጊ የሆኑትን አንዳንድ ቃል ኪዳኖች እንደሚያሣይ ግለጽ፡፡

1. ጌታን ማፍቀር እና መታዘዝ፡፡
2. የእግዚአብሔርን መንግስት በምድር ላይ ለመገንባት ጊዚያችንን፣ ችሎታዎቻችንን፣ እና ቁሣዊ በረከታችንን ለማካፈል እና ለመሰዋት ፍቃደኛ መሆን፡፡
3. በምግባር ንፁህ ሆኖ መቀጠል፡፡
4. በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲመሩን የተጠሩትን አባቶችን፣ ጳጳሶችን፣ የስቴክ ፕሬዚዳንቶችን፣ እና ሌሎችን መከተል እና መርዳት ያጠቃልላል፡፡

**የአማካሪው አቀራረብ**

ሌሎችን ሁሉ የሚሸፍነው እና በቤተመቀደስ ብቻ ልንቀበለው የምንችል ሌላ አንድ ከጌታ ጋር እያንዳንዳችን የምንገባው ቃል ኪዳን እንዳለ ግለጽ። ይህ ቃል ኪዳን ዘላለማዊ ጋብቻ ነው፡፡

**ሥዕል እና ጥቁር ሠሌዳ**

በቤተ መቀደስ ውስጥ የተጋቡ የጥንዶች ሥዕል አሣይ፡፡ በጥቁር ሠሌዳው ዝርዝር ላይ፣ ሐ. *ዘላለማዊ ጋብቻ የሚፈፀምበት ቦታ* ብለህ አክልበት፡፡

**ጥቀስ**

ስለ ሥርዓቶች ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል የሰጡትን መግለጫ አንብብ፡

"ከሥርዓቶች ሁሉ የመጠመሪያዎቹ እጅግ በጣም አስፈላጊዎቹ . . .ናቸው፣ የተቀሩት ሌሎቹ ወደ እነዚህኛዎቹ ይመራሉ፡፡ የተባረክን ነን፣ የተጠመቅን ነን፣ አባልነታችንን ያረጋገጥን ነን፣ የተሾምን ነን፣ የቤተ መቀደስ መንፈሣዊ በረከቶችን የለበስን ነን፣ እናም በመጨረሻ የተጣመርን ነን፣ ከነኚህ ውጪ ምንም ነፍስ መቼም ቢሆን ከፍ ከፍ ልትል አትችልም . . .፡፡ እያንዳንዱ ወንድ ልጅ እና ልጃገረድ . . . የማጣመር ሥርዓት ፍፁማዊ መሆኑን ማወቀ ይገባቸዋል" (*The Teachings of Spencer W. Kimball*, ed. Edward L. Kimball [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Book craft, 1982], ገጽ 502)፡፡

**የአማካሪው አቀራረብ**

የቤተመቀደስ ጋብቻ ጌታ በዚህ ሕይወት እና እንዲሁም በሚመጣውም ጭምር ሊያቀርብልን የሚቻላቸውን በረከቶች ሁሉ ወደምንደሰትበት መንገድ ይመራናል፡፡ እርስ በርሳችን እና ከጌታ ጋር የምናደርጋቸውን ቃልኪዳኖች በምናከብርበት ጊዜ እዚህ ምድር ላይ ቤታችን የበለጠ ደስተኛ ይሆናል፡፡ ወደ ቤተ መቀደስ አዘውትረን ስንመላለስ፣ ውሣኔዎቻችንን እና ቃልኪዳኖቻችንን ያስታውሱናል፣ እናም ጋብቻዎቻችን ጠንካራ እየሆኑ ይመጣሉ፡፡

**ታሪክ**

ከዚህ ቀጥሎ በቤተመቀደስ ውስጥ በመጣመሩ ጠንክሮ የነበረ የአንድ ጋብቻ ታሪክ አካፍል፡፡

"ምንም እንኳን በ1949 ብጠመቅም፣ አራት የትዕግስት ዓመታት እስኪያልፉ ድረስ ባለቤቴ ዝግጁነት አልተሰማትም፡፡ በ1955 የስዊዝ ቤተ መቀደስ በተመረቀበት ግዜ፣ የቤተሰባችን ብዛት ሰባት ነበረ፣ እና ጉዞው የቤተሰባችን በጀት ሊሸፍነው ከሚችለው በላይ ይመስል ነበር፡፡ ማውድ እና እኔ ጌታ መንገድ እንዲከፍትልን ተንበርክከን ጠየቅነው፣ እናም ከአንድ ወር በኋላ፣ ቀጣሪዬ በስራዬ እንዴት እንደተደሰተ እና ብዙ የደመወዝ ጭማሪ እንዳደረገልኝ ሊነግረኝ አስጠራኝ፡፡ በዚያም የበጋ ወራት ለመጀመሪያ ግዜ ወደ ጌታ ቤት ሔድን፡፡

"ከዚያ የመጀመሪያው የቤተ መቀደስ ጉብኝቴ በኋላ ነፍሴን የሞላት ደስታ እና ፍስሃ እንዲሁም ወንጌልን የመኖር ውሣኔዬ በፍፁም አልረሳውም፡፡ ከዚህ በፊት ጨርሶ አልሜ የማላውቀው ከዘላለማዊው መድረሻዬ ጋር የተያዘ ዕውቀት እና ማስተዋል አገኘሁ፡፡ ቤተሰባችን ባንድ ላይ ለግዜው እና ለዘላለሙ ሁሉ በተጣመረበት ግዜ ሥርዓቱ አንፀባራቂ ነበር፡፡

"በመሰዊያው ላይ አሻግሬ ወደ ባለቤቴ አይኖች ውስጥ ተመለከትኩ እና የደስታ እንባዎች በጉንጮቿ ላይ ወደ ታች ሲንከባለሉ አየሁ፡፡ በፊትም አፍቅሪያታለሁ፣ ነገር ግን እንደ ከዛች አፍታ አንስቶ በፍጹም አይሆንም፡፡ እሷ፣ የአምላክ ሴት ልጅ፣ የልጆቼ እናት ነበረች! እስከዚያን ግዜ ድረስ በፍጹም እንዳልተረዳሁት ዓይነት ነገር ነበር የሚመስለው፡፡ በኋላም ጸሎቶቻችን የበለጠ ትርጉም ያላቸው ነበሩ፣ ከምንግዜውም በላይ ጌታን አፈቀርን፣ እና እርሱን ማገልገል ወደድን፡፡

"ወደ ቤተ መቀደስ መመላለስ ቀጥለናል ምክንያቱም እዚያ ያለውን ሥራ እና መንፈስ እንወደዋለን፡፡ ምንግዜም በተመለስን ቁጥር የገባናቸውን ቃል ኪዳኖች ያስታውሱናል፣ እናም ይህ የወንጌልን የሕይወት መንገድ ያለማቋረጥ እንድንኖር ለእኛ ጠንካራው አነሳሳሽ ምክንያት ነው" (Bo G. Wennerlund, "I Had Loved Her Before . . .," *Ensign*, ነሐሴ 1974, ገጽ 62)፡፡

**የአማካሪው አቀራረብ**

በሚች ሕይወታችን ወቀት ልንቀበላቸው ከምንችለው በረከቶች ጉን፣ በዘላለማዊነት ውስጥ የሚቀጥሉ ሌሎች እንዳሉ ግለፅ፡፡ እንደ ጌታ ዕቅድ በመጣመር፣ በሰሌስቲያል መንግስት ውስጥ ከፍተኛውን ደረጃ ልናገኝ እንችላለን፡፡ ከፍ ከፍ ልንል እና ሙሉ ደስታን ልንቀበል እንችላለን፡፡ የራሳችንን ልጆች በዘላለማዊነት ውስጥ ሊኖሩን ይችላሉ፡፡ መንፈሳዊ ልጆች በማግኘት የቤተሰባችንን ቁጥር እንደምንጨምር ተስፋ አለን፡፡

**ሥዕል፣ ቅዱስ መጽሐፍ፣ እና ውይይት**

የቤተ መቀደስ የጥምቀት ገንዳን ሥዕል አመልክት፡፡ ይህ ሥዕል በጌታ ቤት ውስጥ የሚፈጸመውን ሌላ ሥርዓት እንደሚወክል ግለፅ፡፡

አንድ ወጣት ወንድ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 127፥5–6 እንዲያነብ አድርግ፣ እናም ወጣት ወንዶቹ ይህ ሥርዓት ምን እንደሆነ ለይተው እንዲያውቁ አድርግ፡፡

**ጥቁር ሰሌዳ**

በጥቁር ሰሌዳው ዝርዝር ላይ መ. *ለሙታን ሥርዓትን የምንፈጽምበት ቦታ* ብለህ አክልበት፡፡

ብዙ ሰዎች ወንጌልን የመስማት ዕድል ሣያገኙ እንደሞቱ ግለፅ፡፡ በክህነት ሥልጣን የተጠመቁ አይደሉም፣ የቤተ መቀደስ መንፈሳዊ ቡራኬዎቻቸውን በቤተ መቀደስ አልተቀበሉም፣ እንዲሁም በጌታ ቤት ውስጥ ከተጕዳኟቸው ሰዎች ጋር አልተጣመሩም፡፡

- የሰማዩ አባታችን እነዚህን አስፈላጊ ሥርዓቶችን ሣይቀበሉ ለሞቱት ዕድሉን ያዘጋጀላቸው እንዴት ነው?

ወጣት ወንዶቹ የጶተክርስቲያኗ ብቀ አባላት ወደ ቤተ መቀደስ ገብተው ጥምቀቶችን፣ የቤተ መቀደስ መንፈሣዊ ቡራኬዎችን እና መጣምሮችን በሞቱት ሰዎች ፋንታ ማከናወን መቻላቸውን እንዲያመለክቱ እና ምላሽ እንዲሰጡ ፍቀድ፡፡

ብቁ አባላት አዘውትረው ወደ ቤተ መቅደስ ለሙታን ሥራዎችን ለመስራት ሲመላለሱ፣ በርካታ ልዩ በረከቶችን ሊቀበሉ ይችላሉ። ከነዚህ በረከቶች ውስጥ አንዱ በቤተ መቅደስ ውስጥ ሊያገኙት የሚችሉት ሠላም እና አክብሮት ነው። በቤተ መቅደስ ውስጥ ያለማቋረጥ የጌታ መኖር በመሰማቱ ምክንያት፣ ቤተ መቅደስ የራዕይ ቦታ ነው።

**ጥቁር ሰሌዳ እና ጥቀስ**

በጥቁር ሠሌዳው ዝርዝር ላይ ሠ. *የራዕይ ቦታ* ብለህ አክልበት።

የሚከተለውን ገለፃ ስታነብ፣ ወጣት ወንዶቹ ይህ ሰው በቤተ መቅደስ በመገኘቱ የተሰማውን ልዩ ጥንካሬ እንዲያዳምጡ አድርግ።

"ወደ ቤተ መቅደስ በምሄድበት በእያንዳንዱ ግዜ የየዕለቱን ችግሮች ለመጋፈጥ ተጨማሪ ጥንካሬን እቀበላለሁ። በተጨማሪም፣ ቤተ መቅደስ የአክብሮትን፣ የመቀደስን፣ የታዛዥነትን፣ የሥነ ሥርዓትን፣ የሥልጣን ሐረግ አክብሮትን፣ እና የወንድማማችነት ፍቅርን ከፍተኛ ትርጉም የምለማመድበት ሥፍራ ነው . . .።

"በጽዮን ተራራ ላይ አዳኞች መሆን ለኔ ልዩ ትርጉም አለው። ለሙታን በቤተ መቅደስ ውስጥ መስራት ላስብ ከምችለው በላይ ንፁህ ፍቀር እና መስዋዕትነት ነው" (Christiane Lebon, "I Came to Understand . . .," *Ensign*, ነሐሴ 1974, ገጽ 67)።

**ውይይት**

- በቤተ መቅደስ በመገኘት ልንቀበላቸው የምንችላቸው አንዳንድ ልዩ በረከቶች የትኞቹ ናቸው? (ችግሮችን የመጋፈጥ ጥንካሬ፣ የአክብሮት፣ የሥነ ሥርዓት፣ የፍቅር ስሜቶች፣ ስለ ወንጌል እና ጌታ ያጎለበተ ዕውቀት እና መረዳት።)
- የራስህን የቤተ መቅደስ መንፈሣዊ ቡራኬ እና ለዘላለም መጋባትን ለመቀበል ወደ ቤተ ቀደስ መግባትን መናፈቅ ያለብህ ለምንድን ነው?

ትምህርቱን ለሁለት ሳምንታት እያስተማርክ ከሆነ፣ የመጀመሪያውን ሣምንት እዚህ ላይ አጠቃል። ከዚያም በሁለተኛ ሣምንት ላይ በአጭሩ የቤተ መቅደሶችን ዓላማ ከልስ።

---

### ለቤተ መቅደስ መዘጋጀት

**ታሪክ**

ብዙ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አባላት ወደ ቤተ መቅደስ ለመሄድ መስዋዕትነትን መክፈል እንዳለባቸው ግለጽ። የሚከተለውን ታሪክ ስትናገር፣ ወጣት ወንዶቹ የካሚንግስ ቤተሰብ በቤተ መቅደስ መገኘት ይችሉ ዘንድ ስላደረጓቸው መስዋዕትነቶች እና ዝግጅቶች እንዲያዳምጡ አድርግ።

"የሚሲዮን ፕሬዚዳንቱ የአውስትራሊያን ቀዱሳንን በኒውዝላንድ ቤተ መቅደስ ምርቃት ላይ እንዲገኙ፣ ልክ ከአራት ወራት በፊት ጠይቃቸው ነበር . . .።

"የሚሲዮን ፕሬዚዳንቱ ጥያቄ [ቤተመቅደሱ ከቆመበት ቦታ 4,000 ማይልስ ርቀት ላይ፣ በአውስትራሊያ፣ ፐርዝ ውስጥ የአውራጃው ፕሬዝዳንት በሆነው፣ በዶናልድ ደብሊው ካሚንግስ ጆሮዎች ውስጥ] መደወሉን ይዞ ነበር። 'ጻድቅ የሆነ ዓላማ ካላችሁ እና ከጸላያችሁበት፣ ታገኙት ዘንድ ጌታ ይረዳችኋል።' ፕሬዚዳንት ካሚንግ የገንዘቡን ሒሳብ ከለሰ። እያደገ ለመጣው ቤተሰቡ ቤት ለመግዛት እየታገለ ነበር፣ መጠነኛ የሆነ ደሞዝ ብቻ ነበር የሚከፈለው፣ በባንክ ውስጥ ምንም ገንዘብ አልነበረውም፣ አሮጌ መኪናም ነበር የሚያሽከረክረው። ወደ ኒውዝላንድ ለመጓዝ ዋጋው 600 ፓውንድ ($1,200 የአሜሪካ ዶላር) ነበር . . .።

"በዚህ ጊዜ ፕሬዚዳንት ካሚንግስ ዕድሜው 26 ዓመት፣ ወደ ቤተክርስቲያኗ ከተመለሰ 10 ዓመቱ እና አንድ ሚሊዮን ስኩዌር ማይልስ ገደማ መላውን የአውስትራሊያ ክልል በሚሸፍን አውራጃ ላይ ለስምንት ወር ያህል ፕሬዚዳንት የነበረ ሰው ነበር።

"ለቤተ መቅደስ ጉዞአቸው ዝግጅቶችን ጀምሮአል። በካምፓኒው ተቀባይነት ባለው በመጨረሻው ዓይነት ብድር፣ በቤት ዕቃዎቹ ገንዘብ ተበደረ። መኪናውን ሸጠ እና በእግሩ መጓዝ፣ በአውቶብስ መሳፈር እንዲያውም ተሽከርካሪ መለመን ጀመረ። እናም፣ በተካታዮቹ 18 ወራት ውስጥ፣ ወደ የትኛውም ቀርንጫፍ ጉብኝቱን በፍጹም አላቋረጥም። 'አዎ፣ ይህንን ማሳመን አስቸጋሪ ነበር፣ ነገር ግን ይህ እኔ እና ባለቤቴ በሕይወታችን ውስጥ ከተደሰትንባቸው ጊዜያቶች አንደ አንዱ እናስታውሰዋለን። ለጌታ የሚሰውትን የመስዋዕትነት ደስታዎች አግኝተናል። ከሁሉ በላይ በእግር ጉዞው ተደስተናል . . .።'

"በጣም ርቀው እና ብዙ የሕዝብ ብዛት በማይኖርባቸው የአውስትራሊያን አካባቢዎች ስፋት ላይ በሚያቋርጠው የባቡር የአራት ቀን ከግማሽ ጉዞ፣ የ8,000 ማይል ደርሶ መልስ ጉዞ በ2,000 ማይል ተጀመረ። በሲድኒ ውስጥ ደግሞ፣ ቤተሰቡ ደግሞ ወደ ኦክላንድ ለማለፍ የጀልባ ጉዞ አዘጋጅተው በመጠባበቅ ላይ ከነበሩት ሌላ ቅዱሳን ጋር በደስታ ተገናኙ።

"ሀዘናቸው ዱብ ዕዳ እስኪሆንባቸው ድረስ፣ ጀልባዪቱ ከወደቡ መድረክ ጋር በመጋጨት ተበላሸች፣ ነገር ግን የሚያስደንቅ ሁኔታ፣ ያለምንም ተጨማሪ ወጪ አውሮፕላን መከራየት ችለው ነበር። ወደ ምረቃው ሁሉም በረሩ እናም ፕሬዝዳንት ዴቪድ ኦ ሚኬይ ይህንን የተቀደሰ ሥራ ሲመሩ እና ሲጸልዩ ምስክር ሆኑ። ፕሬዝዳንት ካሚንግስ ለቤተ መቅደሱ አጐራባች በሆነው የአድማጮች መቀመጫ በሚገኝበት ሰፊው የቤተክርስቲያኒቷ ኮሌጅ ሕንጻ ውስጥ ንግግር አደረገ። ቤተሰቡ የመጀመሪያውን ቀን የቤተ መቅደስ መንፈሣዊ ቡራኬዎች በመካፈል ተባርኮ ነበር፣ ለሙታን ሥራ ለመስራት ደግሞ የመጀመሪያው ቡድን አባሎች ነበሩ" (Richard J. Marshall, "Saga of Sacrifice," *Ensign*, ነሐሴ 1974, p. 66)።

• ይህ ቤተሰብ ወደ ቤተመቅደስ ለመሄድ እጅግ ብዙ መስዋዕትነት ለመሰዋት ፍቃደኛ የነበረው ለምንድን ነው?

የአማካሪው አቀራረብ

ልክ ይህ ቤተሰብ በቤተ መቅደስ ለመገኘት ብዙ መስዋዕትነቶች እና ዝግጅቶችን እንዳደረገው፣ እኛም እንዲሁ ወደ ጌታ ቤት ለመግባት ልዩ ዝግጅቶች ማድረግ እንዳለብን ግለጽ። የቤተ መቅደስ መግቢያ ፍቃዳችን ልናደርጋቸው ለሚገቡን የተወሰኑ ዝግጅቶች ማረጋገጫ ነው። በቤተ መቅደስ ለመገኘት የተፈቀደላቸው እንደ ታማኝነት፣ የጥበብ ቃል ለሥራት እና የንጽህና ህግ ጨምሮ የወንጌልን ትምህተቶች፣ ለመኖር ፍቃደኝነታቸውን ላሣዩ የቤተክርስቲያን አባላቶች ነው። ለዚህ ለተለየ እና ለተቀደሰ ተሞክሮ ለመዘጋጀት ጊዜ እንደሚወስድ አትኩሮት ስጥበት፣ ታማኝነትን እና ንስኃን ይጠይቃል።

---

**ማጠቃለያ**

የጳጳሱ ውይይት

ጊዜው እንደሚፈቀደው፣ ጳጳሱ ለቤተ መቅደስ ስለ መዘጋጀት እና መገኘት አስፈላጊነት የእሱን ስሜቶች እንዲያካፍል አድርግ። እንዲሁም ወጣት ወንዶቹ ስለ ቤተ መቅደስ ለሚኖራቸው ጥያቄዎች መልስ ይስጥ።

---

**የተጠቀሱ እንቅስቃሴዎች**

1. በማጠቃለያው ላይ ያሉትን ሐሳቦች በሙሉ ለማጉልበት ጳጳሱ በቂ ጊዜ ያልነበረው ከሆነ፣ እሱን ወይም ሌላ ተገቢ እንግዳ በወጣቶች የእሳት ዙሪያ ወይም ተመሳሳይ ጊዜ እነዚህን ሐሳቦች ለማጉልበት እና ለመወያየት ለመጋበዝ ትፈልግ ይሆናል።
2. በአካባቢህ የሚገኝ ከሆነ *ወደ እኔ ኑ* ከሚለው የቪዲዮ ካሴት ውስጥ፣ “በቀዱስ ቤቱ ውስጥ” የሚለውን አቾይ።

# 41 የፈቃደ ስጋ ንጽህና

**ዓላማው**

እያንዳንዱ ወጣት ወንድ እንደ ክህነት አባልነቱ በፈቃደ ስጋዊ ንጽህና እራሱን የመጠበቅን አስፈላጊነት ይረዳል፡፡

**ዝግጅት**

1. አስፈላጊ የትምህርት መሣሪያዎች፣ ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት፡፡
2. በዚህ ስብሰባ የወጣት ወንዶቹ አባቶች እንዲገኙ ጋብዝ ስለዚህም ምን ዓይነት ቁሳቁስ እንደቀረቡ ያውቃሉ፡፡ ይህ ትምህርት በአባቶች እና ወንድ ልጆቻቸው መካከል የሚኖረውን ውይይት ያሳምረዋል፡፡
3. ከአባቶች አንደኛውን በቤተ መቅደስ ውስጥ ከቤተሰቡ ጋር ለመጣመር ብቁ የመሆንን በረከቶች እንዲመሰክር ጋብዝ፡፡
4. ስለ ፈቃደ ስጋ ንጽህና *ለወጣትነት ማጠንከሪያ* በሚለው መጽሐፍ ገጽ 15 ላይ ያለውን ምክር ከልስ፡፡

**ለትምህርት ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**የጌታ የመፍጠር ኃይል**

የአማካሪው አቀራረብ

ኢየሱስ አስራ ሁለት አመት በነበረበት ጊዜ፣ በበዓል ላይ ለመገኘት ከወላጆቹ ጋር አብሮ እንደተጓዘ ግለጽ፡፡ ወላጆቹ ወደ ቤት ሲመለሱ፣ ኢየሱስን ሊያገኙት አልቻሉም፡፡ እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ እና በመቅደስ ውስጥ ከመምህራን ጋር ሲነጋገር አገኙት፡፡ ኢየሱስ እየበሰለ እና ወደ አካለ መጠን እየገባ እንደነበር ከሚያመለክቱት የቅዱሳን መጻሕፍት ማጣቀሻዎች ውስጥ ይህ የመጀመሪያው እንደሆነ ግለጽ፡፡ (ሉቃስ 2፥41–42 ተመልከት፡፡)

• ትልቅ ሰው መሆን በአንድ የተወሰነ ግዜ ወይም እድሜ ይከሰታልን? (አይደለም፣ ወጣት ወንዶቹ በተለያዩ ጊዜያት ያድጋሉ፡፡)

ብዙ አካላዊ ለውጦች በወጣት ልጅ ላይ መከሰት የሚጀምሩት በአስራ ሁለት እና አስራ ሶሶት ዓመቶቹ ውስጥ እንደሆኑ ግለጽ፡፡ እሱም ለረዥም ግዜ ሲጠብቀው ወደ ነበረው የአቀመ አዳምነት ለውጥ ጉዞ ይጀምራል፣ ድምጹን ይለውጣል ጥንካሬው ይጨምራል፣ እናም ይረዝማል እንዲሁም ይተልቃል። በሳል መሆን ይጀምራል። አካላዊ የውስጥ ፍላጐቱ ዕድገት እና ለወጣት ሴቶች ያለው ፍላጎት እየጨመረ ይመጣል፡፡

• ወንድ እና ሴትን በምድር ላይ ያኖረው ማን ነው? (እግዚአብሔር ነው፡፡)

አንድ ወጣት ወንድ ዘፍጥረት 1፥27–28 ሲያነብ ሌሎቹ ከቅዱስ መጽሐፍቶቻቸው ላይ እንዲከታተሉ አድርግ፡፡

• እግዚአብሔር ለአዳም እና ሔዋን የሰጣቸው ትእዛዝ ምንድን ነበር? (እንዲባዙ እና ምድርን እንዲሞሏት ነበር።)

• መባዛት እና ምድርን መሙላት ምን ማለት ነው? (ልጆችን እንዲኖራቸው፡፡)

ጌታ የመንፈስ ልጆቹ ወደ ምድር እንዲመጡ እና ሟች አካሎችን እንዲቀበሉ ያቀደው በዚሁ መንገድ መሆኑን ይገነዘቡ ዘንድ ወጣት ወንዶችን እርዷቸው፡፡

ይህን ጥቅስ ምልክት እንዲያደርጉበት ለወጣት ወንዶቹ አሳስብ፡፡

ጥቅሶች እና ውይይት

ቄስ ቦይድ ኬ ፓከር ስለ መፍጠር ኃይል የሚከተለውን ንጽጽር እንዳደረጉ ግለፅ፡-

“በአካሎቻችን ውስጥ ተዘጋጅቷል—እናም ይህ የተቀደሰ—የመፍጠር ኃይል፣ ብርሃን ነው፣ ሌሎችን ብርሃኖች ለመለኮስ ኃይል ያለው ነው ሊባል ይችላል፡፡ ይህ ስጦታ ሊጠቀሙበት የሚገባው በተቀደሰ የጋብቻ ግንኙነት ውስጥ ብቻ ነበር፡፡ በዚህ የመፍጠር ኃይል ልምምድ አማካኝነት፣ አካል ይፀነሳል፣ መንፈስም በውስጡ ይገባ እና፣ አዲስ ነፍስ ወደዚህ ምድራዊ ህይወት ይወለዳል” (በ Conference Report; ነሐሴ 1972, ገጽ 136; ወይም *Ensign*, ሐምሌ 1972, ገጽ, 111)፡፡

• የመፍጠር ኃይል እንዲኖረን ለእኛ አስፈላጊ የሆነው ለምን ይመስልሃል?

በዚህ ኃይል አማካኝነት ቤተሰብን መፍጠር እንደምንችል ግለፅ፡፡ ቤተሰቦችን በመፍጠር ሂደት ውስጥ፣ ከሰማዩ አባት ጋር አብረን ፈጣሪዎች እንሆናለን፡፡

እያደጉ ሲሄዱ፣ ይህ ኃይል ሥጋዊ ፍላጐትን ሲፈጥር እንደሚያገኙት ግለፅ፡፡ ወጣት ሴቶች አዲስ እና ልዩ በሆነ መንገድ የሚስቡ ይሆናሉ፡፡ በመጨረሻም ይህ ኃይል እጅግ ጠንካራ ይሆናል፡፡

ከፕሬዚዳንት እዝራ ታፍት ቤንሰን ገለፃ የሚከተለውን አንብብ፣

"የወንዶች እና ሴቶች አንድ ላይ የመሆን ተፈጥሮአዊ ፍላጐት ከእግዚአብሔር ነው፡፡ ነገር ግን እንደዚህ ያለው ማህበር በእሱ ሕጐች የታጠረ ነው፡፡ እነዚያ ነገሮች በአግባቡ ለጋብቻ አስቀድመው ተቀምጠዋል፣ በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ ሲወሰዱ፣ በአምላክ ፊት ትክክለኛ እና አስደሳች ናቸው እንዲሁም ብዙ ተባዙ እና ምድርን ሙሏት የሚለውን ትዕዛዝ ይፈፅማሉ፡፡ ነገር ግን እነዚያ ነገሮች ከጋብቻ ግንኙነት ውጭ በተወሰዱ ግዜ እርግማን ናቸው፡፡ (*The Teachings of Ezra Taft Benson* [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Bookcraft, 1988], p. 279)፡፡

• በፕሬዚዳንት ቤንሰን መሠረት፣ በጋብቻ ውስጥ የፋቃደ ሥጋዊ ወዳጅነት ፍላጐት የሰጠን ማን ነው? (ሕይወትን የመፍጠር ኃይል ይኖረን ዘንድ ስለዚህ የሰማዩ አባታችን ይህንን ፍላጐት ሰጠን፡፡)

• ይህ የመፍጠር ጥሩ ኃይል ኃይል ነውን? (አዎ፣ የተቀደሰ ኃይል ነው፡፡) የእግዚአብሔር ሥጦታ ነው፡፡)

አንድ ወጣት ከፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል ገለፃ የሚከተለውን እንዲያነብ አድርግ፣

"ወሲብ መዋለጃ እና ፍቀርን መግለጫ ነው፡፡ ወንዶች እና ሴቶች ዘላለማዊ የቤተሰብ ክፍል ለማበጀት ባንድ ላይ የሚገናኙበት ነው፡፡ ሕጋዊ ጋብቻ በሚለው የቃል አገባብ፣ ትርጉም የግብረ ሥጋ ወዳጅነት ግንኙነት ትክክለኛ እና መለኮታዊ ማረጋገጫ ያለው ነው፡፡ ወሲባዊ ባህሪይ በራሱ ቀድስናን የሚያረክስበት ወይም ዝቅ የሚያደርግበት ምንም ነገር የለም፣ በዚያ አማካኝነት ወንዶች እና ሴቶች በመፍጠር ሂደት እና ፍቀርን በመግለጫ ውስጥ የሚገናኙበት ነውና" (*The Teachings of Spencer W. Kimball* [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Bookcraft, 1982], ገጽ 311)፡፡

• ጌታ ይህን የመፍጠር ኃይል መጠቀምን በተመለከተ ጌታ ያዘዘን ምንድን ነው? (በጋብቻ ግንኙነት ውስጥ ብቻ መጠቀም ነው፡፡)

ጥቀስ እና ውይይት

የሚከተለውን የፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦልን ገለፃ አንብብ፣

"ሕዝቦቻችንን ከልጅነት እንስቶ እስከ እርጅና ሰውነትን በአግባቡ ካለመጠቀም ከሚመጡት የባርነት ሰንሰለቶች፣ ሥቃይ፣ እና ጸጸት ይጠበቁ ዘንድ በጣም እናስጠነቀቃለን፡፡

"የሰው አካል ለእግዚአብሔር የመንፈስ ልጅ የተቀደሰ ቤት ነው፣ እናም ያልተፈቀደ ጣልቃ ገብነት ወይም ይህን የተቀደሰ ማደሪያ ማቆሸሽ ጸጸት እና ሀዘንን ብቻ ሊያመጣ ይችላል . . .።

"—የራስ ወይም የሌሎች ሰዎችን፣ አካላቶች በፍቀር መዳበስ፣ እና ወሲብ በሰዎች መካከል አግባብ ባለው የጋብቻ ግንኑነቶች ካልሆነ በቀር አይቻልም፡፡ ይህም በፈጣሪያችን በሁሉም ቦታዎች፣ በሁሉም ጊዜዎች፣ በትክክል የተከለከለ ነው፣ እኛም እንደገና እናረጋግጠዋለን" (በ Conference Report, ሚያዚያ 1974, pp. 8–9; ወይም *Ensig*n, ግንቦት 1974, ገጽ 7)፡፡

• ይህን የመፍጠር ኃይልን ያለአግባብ እንዳንጠቀምበት እግዚአብሔር እንዲህ በጣም የሚሰማው ለምን ይመስልሃል?

የሰማዩ አባታችን የመንፈስ ልጆቹ ከተዘጋጁ እናት እና አባት ጠንካራ ቤተሰቦች ውስጥ እንዲወለዱ እንደሚፈልግ ወጣት ወንዶቹ ይገነዘቡ ዘንድ እርዳቸው፡፡ ይህን የመፍጠር ኃይል ያለአግባብ መጠቀም የሚያስከትለውን ሀዘን እና ጸጸት እንደተነገረን፣ ግን ደግሞም ይህን ኃይል በፅድቀ ከመጠቀም የሚመጡ ዘላለማዊ በረከቶች እንዳሉ ግለፅ፡፡ እነዚህን በረከቶች ወጣት ወንዶቹ እስቲ ይወያዩበት፡፡

ጥቀስ

የሚከተለውን የቁስ ማርክ ኢ. ፒተርሰን ገለፃ አንብብ፡፡

"ወሲብ በጣም የተቀደሰ፣ በጣም መለኮታዊ በመሆኑ፣ አግባብ ባለው መንገድ ከተጠቀሙበት፣ እነዚያ ተሣታፊዎች ከእግዚአብሔር ጋር ጣምራ ፈጣሪዎች ይሆናሉ፡፡ ሕይወትን በመፍጠር ታላቅ ድርጊት እና ተግባር ውስጥ ሁሉን ቻይ ከሆነው ጋር ጓደኞች ይሆናሉ" (*Our Moral Challenge* [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Deseret Book Co., 1965], ገጽ 13)፡፡

ውይይት

"እናንተ የእግዚአብሔር ዕቃ የምትሸከሙ ሆይ፣ ንፁሐን ሁኑ" ብሏል ጌታ (ኢሳይያስ 52፣11)።

• ይህ ንግግር ምን ማለት ነው?

ገለፃውን እንዲወያዩበት ለወጣት ወንዶቹ ጊዜ ፍቀድላቸው፡፡ ይህ እኛ እያንዳንዳችን የክህነት ኃላፊነቶቻችንን ስንፈጽም እንደሚያመለክት ይገነዘቡ ዘንድ እርዳቸው፡፡ እራሳችንን ንፁህ አድርገን ለመጠበቅ ከፈቃደ ሥጋዊ ኃጢያት መራቅ ይገባናል፡፡

*ለወጣነት ማጠንከሪያ* የሚለውን መጽሐፍ ገጽ 15 በመከለስ ለግብረ ሥጋዊ ኃጢያት አስተዋፅኦ የሚያደርጉትን መግለፅ ትፈልግ ይሆናል፡፡ ለግብረ ሥጋዊ ኃጢያዓቶች ከልብ ንስኃ የሚገቡ ሰዎች ምሕረትን ሊያገኙ ይችላሉ፣ ነገር ግን የንስኃው መንገድ ሁሌም ረጅም እና አስቸጋሪ እንደሆነ ትኩረት ስጥበት፡፡ ግብረ ሥጋዊ ኃጢያቶችን የፈፀሙ ወጣቶች የጳጳሳቸውን እርዳታ መፈለግ ይገባቸዋል፡፡

• ምን ዓይነት የግብረ ሥጋዊ ኃጢያቶችን ነው ጌታ የከለከለው? (“ከጋብቻ በፊት ያሉ ወሲባዊ ግንኙነቶችን ሁሉ፣ መተሻሸት፣ ያፈነገጠ ወሲብ [እንደግብረ ሰዶማዊነት፣ አስገድዖ መድፈር፣ ከቅርብ ዘመድ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት]፣ ሴጋ፣ ወይም በወሲባዊ አስተሳሰብ፣ ንግግር፣ እና ድርጊቶች መጠመድ።”)

• እንደ ክህነት ያዥነታችን፣ ይህን ያህል ንፁህ መሆን የሚያስፈልገን ለምንድን ነው? (ንጹህ ሕይወትን የማንኖር ከሆነ የጌታ መንፈስ ሊኖረን አይችልም።)

• የጌታን የንጽሕና ሕግ መተላለፍ በምድር ላይ ዕድገታችንን እንዴት ሊገታው ይችላል?

በረከቶች እና ዕድሎች ብቁ ወደ ሆኑት ብቻ እንደሚመጡ ግለፅ። ብቁ ያልሆነ ግለሰብ እንደ ወንጌላዊ አገልግሎት እና የቤተ መቅደስ ጋብቻ ዕድሎችን ሊያስተላልፍ ወይም ሊተው ይገባዋል።

• የንፅሕና ሕግ የተላለፉ ይቅርታን ሊያገኙ ይችላሉ?

ከልብ ንስኃ የሚገባውን አምላክ ይቅር እንደሚለው፣ ነገር ግን ከእንደዚህ ያሉ ኃጢአቶች ለመንጻት ያ ቀላል ሥራ እንዳልሆነ አትኩሮት ስጥበት። በመጀመሪያ ደረጃ ንፁህ ሆኖ መቆየት እና ትዕዛዝን አለመተላለፍ በጣም የተሻለ ነው።

**ጥቁር ሠሌዳ እና ውይይት**

• በፈቃደ ሥጋዊ የበለጠ ንፁህ ሆነን ለመቆየት እንዴት እንችላለን?

ይህንን ጥያቄ ወጣት ወንዶቹ ሲወያዩበት፣ መልሳቸውን በጥቁር ሠሌዳው ላይ ዘርዝር። መልሶቻቸው ማጨትን፣ ጥሩ እና መንፈስ የሚያነቃቁ መጽሐፎች ማንበብን፣ ንፁህ አስተሳሰቦች መጠበቅን፣ ቅዱሳን መጽሐፍት ማንበብን፣ እና ቆሻሻ አስተሳሰቦችን የሚቀሰቅሱ ሲኒማዎች እና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ማስወገድን በተመለከተ የነቢይ ምክሮችን መከተል ይጨምሩ ይሆናል።

በግብረ ሥጋ ግንኙነት ንጹህ መሆን የሚገባቸው መቼ እንደሆነ ለመወሰን ጊዜው አሁን መሆኑን ስለዚህም በሚፈተኑበት ጊዜ፣ ምላሽ እንዴት እንደሚሰጡ አስቀድመው የወሰኑ ስለ መሆናቸው ለወጣት ወንዶቹ አጉላ።

**የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ**

በጲጥፋራ ቤት ውስጥ ለፈተና እንዴት ምላሽ እንደሰጠ የዮሴፍን ታሪክ ንገራቸው (ዘፍጥረት 39፥7–12 ተመልከት)። ዮሴፍ አስቀድሞ እንዴት መኖር እንደሚሻ ማወቁን አመልክት፣ አቋሞቹን ለማቻቻል አሊያም ላለማቻቻል መወሰን አልነበረበትም።

**ጥቅስ**

የሚከተለውን የፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል ሙከራ እና ምክር አንብብ፣

“እያንዳንዱ ወጣት እራሱን ለአደጋ ከሚያገልጡ አቀራረቦች ይጠብቅ እና ከዚያም ከሚያዋርዱ እና ሕይወትን ከሚጐዱ ቆሻሻ ወሲባዊ ተሞክሮዎች በታላቅ መቆጣጠር እራሱን ያድን። ያልዘገየ፣ እና የመጨረሻ እንዲሁም የማያቋርጥ ንስኃ ሊኖር ይገባል. . . .።

“ምድር ያለ ጋብቻ እና ቤተሰብ ሕይወቷን ልትቀጥልም ሆነ ልታረጋግጥ አትችልም። ወሲብ ያለጋብቻ፣ ለሰዎች ሁሉ፣ ወጣት ሆነ ሽማግሌ፣ ለጌታ ርኩሰት ነው፤ እናም በጣም የሚያሳዝነው ለነዚህ ታላቅ እውነቶች ብዙ ሰዎች ዓይኖቻቸውን ማሳወራቸው ነው” (በ Conference Report, ጥቅምት 1974, ከገጽ 8–9; ወይም *Ensign,* ኅዳር 1974, ከገጽ 7–8)።

---

**ማጠቃለያ**

**ሙከራ**

በግብረ ስጋ ግንኙነት እራሳቸውን ንፁህ አድርገው በመጠበቅ የሚያገኙትን በረከቶች ወጣት ወንዶቹ ዘወትር ያስታውሱ ዘንድ አሳስቧቸው። አንድ ቀን በቤተመቅደስ ውስጥ በመሰዊያ ላይ ተንበርክከው ለጊዜው እና ለዘላለም ከሚስቶቻቸው ጋር ሲጣመሩ ምን እንደሚመስል እንዲያስቡ አድርግ።

**ምስክርነት**

ከአባቶች አንዱን (አስቀድሞ የተመደበውን) የሚፈቀር የጋብቻ ግንኑነት በማግኘቱ እና ከቤተሰቡ ጋር በዘለዓማዊነት በመጣመሩ ያመጣለትን ደስታ ምስክርነት እንዲሰጥ አድርግ።

# ታማኝነት

# 42

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ከጌታ እና፣ ከሌሎች ጋር፣ ከራሱ ጋር ታማኝ እና ቀጥተኛ ለመሆን በጣም ይጥራል፡፡ |

**ዝግጅት**

1. አስፈላጊ የትምህርት መሣሪያዎች፣ ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት፡፡
2. መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ፣ ምዕራፍ 5 አጥና፣ እናም የለምጻሙን ንዕማንና ታማኝ ያልሆነውን ሎሌ ታሪክ ለመናገር ተዘጋጅ፡፡
3. *ለወጣቶች ጥንካሬ* በሚለው መጽሐፍ ላይ ስለታማኝነት በገፅ 9 እና 10 ያለውን ምክር ክልስ፡፡

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**መግቢያ**

ታሪክ

ወጣት ወንዶቹ “የአፄው አዲስ ልብሶች፣” የሚለውን ዮሐንስ ክርስቲያን አንደርሰን ወግ የሚያውቁ ከሆነ፣ ለትረካው አንተን ያግዙህ ዘንድ ጋብዛቸው፡፡

ታሪኩ አፄውን ከልብስ ሁሉ በጣም ያማረውን የመፍተል ኃይል እንዳላቸው ስላሳመኑት ሁለት አታላዮች በተመለከተ እንደሆነ ግለፅ፡፡ ልብሱም ልብሱ ቀንጆ ብቻም አልነበረም፣ እንዲሁም አስማተኛ እንደሆነ ጭምር ነገሩት፡፡ ልብሱም ለሹመቱ ብቁ ላልሆነ ወይም ኃጢአተኛ ለሆን ለማንም ሰው የማይታይ እንደነበር ይናገሩ ነበር፡፡ ከዚያም ንጉሱ በታላላቅ ሥርዓት ጉዞዎች ላይ የሚለብሰውን ልብስ የሚፈትሉ እና መጎናጸፊያውን የሚሰሩ አስመሰሉ፡፡ አፄው እና ጭፍራዎቹ ሁሉ ምንም ሊያዩ አልቻሉም፣ ምንም የሚታይ ነገር አልነበረምና፣ ነገር ግን እያንዳንዳቸው ሀቁን መናገር ፈርተው ነበር፡፡ አፄው በሠልፉ አጠገብ ሲያልፍ፣ ስለ አፄው አዲስ ልብሶች መስማማት፣ ቀለም እና ዓይነት አደነቁ፣ በእርግጥ፣ ግን፣ ቀድሞም ምንም አልነበረም፡፡ በመጨረሻም፣ አንድ ሕፃን ልጅ፣ “ለምን አፄው ምንም የለበሰው ነገር የለም”፣ ሲል በድንገት ጮኸ፡፡”

- የልጁን ድርጊቶች ምን ቃል ይገልጸዋል? (ታማኝነት፡፡)
- *ታማኝነት* ማለት ምን ነው?

ታማኝነታችን በየቀኑ እንደሚፈተን አጥብቀህ አሳስብ። ወጣቶች በግንኙነታቸው ሁሉ በእውነት ታማኝ እንደሆኑ ወይም እንዳልሆኑ እንዲያስቡ አድርጋቸው፡፡

---

**ታማኝ በመሆን እናምናለን**

ጥቀስ

- የኋለኛው ቀን ቅዱሳን እንደመሆናችን በተለይ ታማኝ መሆን ለምን አስፈለገን?

ወጣት ወንዶቹ ምላሽ እንዲሰጡ ፍቀድላቸው፡፡ ከዚያም የሚከተለውን የፕሬዚዳንት ሒበር ጄ ገለፃ አንድ ወጣት ወንድ እንዲያነብ አድርግ፣

“ለኋለኛው ቀን ቅዱስ መሠረታዊ ነገር ቢኖር ታማኝነት ነው፡፡ ለኋለኛው ቀን ቅዱስ መሠረታዊ ነገር ቢኖር ልክ እንደተዋዋለው ውል ለቃሉ በታማኝነታ ዋጋ መስጠት፣ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የሰጠውን ተስፋ ለመፈፀም፣ ምንም አስቸጋሪ ቢሆንም፣ በጌታ እርዳታ እና ከጌታ እርዳታ ጋር፣ ሕይወቱን እና ያለውን ኃይል አሳልፎ ለመስጠት አዕምሮውን ማሳመን ነው” (*Gospel Standards* [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Improvement Era, 1943], ገጽ 30)፡፡

የተለያዩ የታማኝነት ገፅታዎች እንዳሉ ግለጽ፡፡

---

**ለጌታ ታማኝ መሆን ይገባናል**

ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት

በጥቁር ሰሌዳ ላይ፣ *ታማኝነት* ለ—ብለህ ፃፍ፡፡ ከእነዚያ ቃላት ሥር፣ 1. ጌታብለህ ፃፍ፡፡

ወጣት ወንዶቹን ለእግዚአብሔር ታማኝ የምንሆንባቸውን አንዳንድ መንገዶች እንዲጠቁሙ አድርግ፡፡ ውይይቱን ለማገዝ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተጠቀም፣

- አስራትን ወይም ሌላ በኩራቶችን በመክፈል እንዴት ታማኝ መሆን እንችላለን?
- ቅዱስ ቁርባንን በምንካፈልበት ጊዜ እንዴት ታማኝ መሆን እንችላለን?

• የቤተክርስቲያን ምድብ ሥራዎችን ለማከናወን እንዴት ታማኝ መሆን እንችላለን?

• ለጌታ ጋር የገባነውን ተስፋ ለመጠበቅ እንዴት ታማኝ መሆን እንችላለን?

---

**ከሌሎች ጋር ታማኝ መሆን ይገባናል**

ታሪክ

በጥቁር ሠሌዳው ላይ ይብንን አክል፣ 2. ሌሎች። እና በቄስ ኬይት ደብሊው ዊልኮክስ የተነገረውን ተከታዩን ታሪክ አንብብ፣

"በሁለተኛው የኮሌጅ ዓመቴ ወቀት በታህሳስ 7፣ 1941፣ ዩናይትድ ስቴትስ ፐርል ሀርበር ላይ ተጠቃች . . .። እኔም የባህር ኃይል መኮንን በመሆን ዓላማ ባህር ኃይልን ለመቀላቀል ወሰንኩ። በባህር ኃይሉ ማሠልጠኛ ቢሮ ውስጥ ተቀባይነት ለማግኘት ቀጾችን በመሙላት አንድ ሙሉ ቀን አጠፋሁ—።

"ከባህር ኃይሉ የአካል ብቃት መመዘኛ ጥያቄዎች ውስጥ የመጨረሻው . . . 'አስም' ይዞኝ ያውቅ እንደሆነ ይጠይቃል። በዚህ ጥያቄ ላይ ለረዥም ጊዜ ማፍጠጤን አስታውሳለሁ . . .። መልሴ ለእጩ መኮንነት ተቀባይነት ማግኘት ወይም ማጣቴን ሊያውክ እንደሚችል እርግጥ ነበር።

"ሐቁ ግን አስም ሕይወቴን ሙሉ ሲያስቃየኝ የነበረ እና አሁንም አሁንም የሚያስነጥሰኝ መሆኑ ነበር። ይህ ጥያቄ ምናልባት ተመልሶ ስለማይመጣ የለብኝም ብሎ ማጥቀሩ ቀላል ነበር። ይሁንና፣ የለብኝም ብሎ መመለሱ ታማኝ አለመሆን ነው። ትንሽ ነገር ነበር፣ ግን እውነታው አጣብቂኝ ውስጥ ነበር። ሳልፈልግ ዝግ ብዬ፣ አለብኝ የሚለውን ቦታ አጥቁሬ ወረቀቱን መለስኩ።

"የሕክምና መኮንኑ፣ መልሴን በመመልከት፣ ቀና ብሎ 'የባህር ኃይል መኮንኖች አስም ሊኖራቸው እንደማይችል አታውቅም? ልዩ የአለርጂ ምርመራ መውሰድ ይገባሃል።' ሲል በመደነቅ ጮኸ።

"ምርመራው በርከት ባሉ አለርጂዎች እንደተሰቃየሁ አመለከተ። [መኮንኑ] የማመልከቻ ቀጾቼን ወስዶ፣ በዝምታ ቦጫጨቃቸውና፣ ወደ ቀርጫት ውስጥ ወረወራቸው። እኔም . . .፣ 'አሁን ምን ማድረግ ይገባኛል?' ስል ጠየቅኩ። መኮንኑ ረጋ ብሎ 'ግዳጁ' እንደሚጠነቀቀልኝ እና መጨነቅ እንደሌለብኝ መልስ ሰጠኝ።

"በልቤ እያዘንኩ፣ ወደ ዩታህ ዩኒቨርስቲ በመዛወር፣ ወደ ትምህርት ቤት ተመለስኩ . . .። ፐርል ሀርበርን ተከትሎ ከሁለት ዓመት በኋላ፣ በታህሳስ 1943፣ በሚካኒካል ኢንጂነሪንግ ሣይንስ በባችለር ዲግሪ ተመረቅሁ።

"በምርቃቴ ቀን ማግስት፣ በጥሪት ወደሚገኘው ባህር ኃይል ቢሮ እራሴን አቀረብኩ . . . እናም [በ] ሚካኒካል ኢንጅነሪንግ መመረቄንም አመለከትኩ . . .እንዲሁም ዲግሪዬን አሳየሁ። የባህር ኃይል መኮንን ለመሆን መፈለጌን በተረዱ ጊዜ፣ 'ቀይ ምንጣፍ' የተባለውን ምርመራ ወሰድኩ . . .። ያን ቀን በባህር ኃይል ውስጥ በባለ ዝቅተኛ የመኮንን ማዕረግተኝነት የማዘዣ ወረቀት ተሠጠኝ . . .።

"ለመኮንኑ እንዲህ ብዬ ነገርኩት . . .፣ 'ጌታዬ፣ በኃይለኛ አስም እሰቃያለሁ። ስለዚያ ጉዳይ ምን ያስባሉ?' መኮንኑ ሣቀ። ባንድ ወቀት መመዘኛ እንደነበረ፣ ነገር ግን አሁን እንደቀረ ተናገረ።

"በኋላ የተመደብኩባት መርከብ . . . USS LSM 558 ነበረች። እንደተረዳነው ይህች መርከብ የተወሰነችው ለጃፓን ወረራ ነበር . . .። በምትኩ ግን፣ በአትላንቲክ ባህር ጠረፍ ከቦስተን እስከ ፍሎሪዳ እንድናስስ ትዕዛዞች ተሰጡን . . .።

"በነሐሴ 1985፣ [እህት ዊልኮስስ እና እኔ] . . . በማኒላ ውስጥ ወደሚገኘው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቀት ከሀገራችን ህይወታቸውን አሳልፈው ለሰጡት ወታደሮች ወደ ተመረቀው የታላቁ ጦርነት መታሰቢያ . . .ተጓዝን። የማኒላው ጦርነት መታሰቢያ ተሞክሮአችን ያስታወሰን ነገር ቢኖር የጦርነቱን የመጀመሪያ ዓመት አገልግሎቶችን የተቀላቀሉ ብዙ የግል ጓደኞቻችን ሁሉ እንደወጡ መቅረታቸውን ነበር። እነዚያን ቀደምት እንቅስቃሴዎች ተቀላቀዬ ቢሆን ኖር፣ ሕይወቴን የማጣቱ ዕድል በጣም ከፍተኛ ይሆን ነበር። አስሚን በተመለከተ ሐሰት ለመናገር ፍቃደኛ ሆኜ ቢሆን ኖሮ፣ አብዛኛዎቹ ሕይወታቸውን ወዳጡበት የመጀመሪያው መራራ ጦርነት በአፋጣኝ የተላኩ በሆንኩ ነበር።

"ወደዚያ ታሪካዊ ቀን ተመልሼ በመመልከት፣ ስለ አስሜ እውነቱን በመናገር በሕይወቴ ውስጥ ከፈተናዎች ሁሉ ታላቁን እንዳለፍኩ ተገነዘብኩ . . .። 'ትንሽዬ ውሸት' በመናገር ትልቅ ፈተና እዚያ ነበር፣ ነገር ግን አባቴ የሰጠኝ ምክር . . .በደንብ አገለገለኝ። ይህን በትሕትና አካፍላችኋለሁ፣ *ሁሌም ታማኝ ሁኑ"* ("The Best Policy," *New Era*, ታህሳስ 1986, ከገጽ 6–7)።

ውይይት

• ቄስ ዊልኮክስ ለመዋሸት ያልፈለገው ለምንድን ነው? ("እውነታው አጣብቂኝ ውስጥ ስለነበር።")

• ባህር ኃይሉ ባልተቀበለው ጊዜ እንዴት ነበር የተሰማው?

• ታማኝ በመሆኑ እንዴት ነበር የተባረከው?

• አንዳንድ ጊዜ ታማኝ መሆን የሚያስቸግረን ለምንድን ነው?

• ታማኝ በመሆናችን ዘወትር በፍጥነት በረከቶችን እንቀበላለንን?

እንደ ቄስ ዊልኮክስ ሁሉ፣ ታማኝነት ዘወትር በአፋጣኝ በረከቶችን እንደማያመጣልን እንደምንረዳ ግለጽ። እንዲያውም አንዳንዴ በታማኝነታችን የተነሳ አንሰቃይ ይሆናል። ስለዚህ በጌታ ልንታመን ይገባናል፣ እናም ታማኝ በመሆናችን እሱ ይባርከናል።

የቅዱስ መጽሐፍ ታሪክ

በራስህ ቃላት የንዕማንና ታማኝ ያልሆነውን ሎሌ ታሪክ ተናገር (መጽሐፈ ነገሥታት ካልዕ ምዕራፍ 5 ተመልከት)። ኤልሳዕ ታማኝ ላልሆነው ሎሌው ሁለተኛ ዕድል እንዳልሰጠው አትኩሮት አድርግበት። ምንም ዓይነት የኪስ ገንዘቦች፣ ገለፃዎች፣ ወይም ምክንያቶችን መደርደር ተቀባይነት አልነበራቸውም። ሎሌው ታማኝ አልሆነም እናም ታማኝ ላለመሆኑ ተሰቃየ። አጭበርባሪነት ሁሉ፣ ትንሽ ወይም ዋጋ የሌለው ዓይነት ቢሆን፣ ሌሎችን እንደሚያውክ ትኩረት ስጥበት።

---

**ለራሳችን ታማኝ ልንሆን ይገባናል**

ምሳሌያዊ ጥናቶች

በጥቁር ሠሌዳው ላይ፣ 3. *እራስህን* ብለህ አክልበት።

• በምን መንገዶች ነው ከራሳችን ጋር ያማንታመነው? (ለድርጊቶቻችን፣ መነሾ እና ለሚያስከትሉት ውጤቶች ምክንያት እንደረድራለን።)

እያንዳንዱ ሰው ከራሱ ጋር እንዴት ታማኝ እንደማይሆን ለማየት የሚከተሉትን ምሣሌዎች ተወያዩበት። ምሳሌዎቹን ከራስህ አካባቢ ሁኔታዎች ጋር ልታዛምደው ትፈልግ ይሆናል።

1. ጳውሎስ በሩን አንድ ሰው ሲያንኳኳ ሰማና ከታችኛው ሰፈር ያ ምናምን ብሬይን መሆን አለበት ሲል አወቀ። ከእሱ ጋር ማውራት አልፈለገም። እናተየው ‘አቤት’ ማለት ስትጀምር፣ ጳውሎስ እቤት የለም እንድትል ነገራት።
2. ጀሰን የመደበሩን ጠባብ የመተላለፊያ መንገዶች ገልመጥ ገልመጥ ብሎ ተመለከተ። ማንም የሚያየው አልነበረም። በፍጥነት አንድ የማስቲካ እሽግ አንስቶ ወደ ኪሱ ጨመረው። “በጣም ትልቅ ሱቅ ነው፤ አይጐዳቸውም፣” ሲል አሰበ።

• ለራሳችን ታማኝ መሆን የሚያስፈልገን ለምንድን ነው? (ታማኝነታችንን እና የራሳችንን ብቃት ለመጠበቅ። እራሳችንን ማፍቀራችን በጣም አስፈላጊ ነው።)

• ሰዎች ለምን አምነተ ቢስ ይሆናሉ?

• በሁሉም ጊዚያት ታማኝ መሆን ያስፈለገን ለምንድን ነው?

ታሪክ

ብዙ ጊዜ ሳናውቀ በታማኝነታችን ሌሎችን እንደምንነካ ግለፅ። በፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል የተነገረውን ተከታዩን ታሪክ አንብብ፣

“ከኒው ዮርክ ወደ ባልቲሞር በባቡር ላይ ከአንድ ነጋዴ በተቃረራኒው ሶፋ ላይ ቁጭ ብለናል እናም ‘በሶልት ሌክ ከተማ አንዳንዴ እንዲህ ይዘንባል፣’ ስል ሐሳብ ሰነዘርኩ።

“ወዲያውኑ ጭውውቱ ወደ ተለመደው ወርቃማው ጥያቄ፣ ‘ስለ ቤተክርስቲያን ምን ያህል ታውቃለህ?’ ወደሚለው መራን።

“ ‘ስለ ቤተክርስቲያኗ ምንም አላውቀም’፣ ‘ነገር ግን ከሕዝቦቿ አንዱን አውቃለሁ’ አለ። በኒው ዮርክ ውስጥ ንኡስ ክፍሎችን እያሳደገ ነበር። ‘ኮንትራቶቼን ተቀብሎ የሚያከናውንልኝ አንድ ረዳት የኮንትራት ሠራተኛ አለኝ፣’ ሲል ቀጠለ። ‘በጣም ታማኝ እና በቀንነት የተሞላ በመሆኑ፣ በፍጹም ሥራ አዝዤው አላውቅም። የክብር መግለጫ ነው። የሞርሞን ሰዎች ልክ እንደዚህ ሰው ከሆኑ፣ እንደዚህ ያሉ የተከበሩ ሰዎችን ስለምታፈልቀው ቤተክርስቲያን ማወቅ እፈልጋለሁ።’ ጹሑፎችን ተውንለት እንዲሁም እንዲያስተምሩት ወንጌላዊያንን ላክንለት” (*Faith Precedes the Miracle* [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Deseret Book Co., 1972], ከገጽ 240–41)።

• የታማኝነት ምሳሌያችን ሌሎችን ሊነካ የሚችለው እንዴት ነው?

በታሪኩ ውስጥ ያለው ሰውዬ ከሰራተኞቹ አንዱ እንዴት ታማኝ እንደነበር በማወቁ ምክንያት ቤተክርስቲያኗን ለመመርመር ፍላጐት እንደነበረው ግለፅ። ብዙ ጊዜ ታማኝ የሆነ ድርጊቶቻችን በሌሎች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። ዘወትር ታማኝነትን መተግበር ቀላል ነው፣ ነገር ግን አንዳንዴ ታማኝ አለመሆን የበለጠ ቀላል እንደሆነ እናስብ ይሆናል። ቢሆንም ቅሉ፣ ታማኝነት ዘወትር በረከቶችን ያስገኝልናል።

---

**ታማኝነት የኅሊና ሰላምን ያስገኝልናል**

ታሪክ

ታማኝነት የኅሊና ሰላም የሚያስገኝበትን አስቸጋሪ መንገድ ስለተረዳ አንድ ወጣት ተከታዩን ታሪክ አካፍል።

“ወንድም እና እህት ፖልም፣ ሁለት ያረጁ ስዊድናዊ ጥንዶች፣ በከተማችን ውስጥ በሚገኘው የኅብረት መደብር ውስጥ በጫማ መሸጫ ሱቅ ውስጥ ሠርተዋል። ወንድም ፖልም ጫማ በሚጠግኑበት ጊዜ እጃቸውን ማየት የሚያጓጓ ነበር። ጂሚ እና እኔ ድርቅ ብለው የተገተሩት ጣቶቻቸው ሲሰሩ ለመመልከት እና በመዳፉ መሐል አቁርጦ የሚያልፍውን ቀዳዳ ለማየት ወደ ሱቁ እንሄዳለን . . .።

“አንድ ቀን እኔ እና ጂሚ እዚያ በነበርንበት ጊዜ ከሚስማር መያዣ ስኒዎቹ በአንዱ ውስጥ አስር ሣንቲም አየን፣ እናም ሁለታችንም ያ አስር ሣንቲም ምን ሊገዛ እንደሚችል ል ማሰብ ጀመርን።

“ ‘ወንድም ፖልም አስር ሣንቲም በፍፁም አያጣም፣’ ስል ለጂሚ አንሾካሾኩ።

“ ‘እኔ ወንድም ፖልም ከሱቁ ጀርባ የሆነ ነገር እንዲያሣዩ ሳደርግ በዚያው ቀጽበት አንተ ገንዘቡን አንሣ እና አሩጥ’ ሲል ጂም ሀሣብ አቀረበልኝ፡፡

“ ‘ዕቅዱ በትክክል ሠራ፣ እናም ከጆ ኮስሌት ኖሽልቲ መደብር እያንዳንዳችን አንዳንድ ጠርሙስ ለስላሳ ገዛን፡፡

“ ‘ስለዚያ አስር ሣንቲም የነበረብኝን የጥፋተኝነት ስሜት ለማሸነፍ፣ ረጅም ጊዜ ወሰደብኝ፡፡ ወንድም ፖልምን ባገኘሁአቸው ቁጥር፣ ከእርሳቸው መስረቄን አስታውስ ነበር፡፡ በእያንዳንዱ ክረምት ዋርዱ ቀዳሚ ቀዳሚ ልጆችን እንጨት ለመበልቶች፣ ላረጁ፣ እና ለአካለ ስንኩላን እንዲፈልጡ ይልካቸዋል፡፡ ከሌላ ቦታ ይልቅ በነፖልም ቤት በጣም ጠንክሬ በመስራት ያቺን አስር ሣንቲም ካህሊናዬ ለመፋቅ ጥረት አደርግ ነበር፡፡

“ ‘ካደኩኝ በኋላ ወንድም ፖልምን በጣም አልፎ አልፎ አያቸው ነበር፡፡ ነገር ግን፣ ካገኘሁዋቸው፣ ሽባ እጃቸውን በእጄ ውስጥ ያስገባሉ፣ እና ከዚያም ያቺ ከእርሳቸው ሚስማር ስኒ ውስጥ የወሰድኳትን አስር ሣንቲም አስታውሳለሁ፡፡ ስለጉዳዩ ልንገራቸው እና አንድ ዶላር ሰጥቼያቸው ህሊናዬን ዝም ላሰኝ እፈልግ ነበር፣ ነገር ግን አለመታመኔን ለመናዘዝ ወኔ አጣሁ፡፡

“በኋላ፣ ወንድም ፖልም ህይወታቸውን ሙሉ በሰሩበት በጥንቱ ኅብረት መደብር ውስጥ በሻጭነት ተቀጠርኩ፡፡ ከእኔ ጋር ሲገበያዩ፣ ከማስከፍላቸው ውጭ አስር ሣንቲም የሚያወጣ ተጨማሪ ዕቃ በከረጢታቸው ውስጥ አስቀምጣለሁ፡፡ ከዚያም ሲሄዱ፣ ከራሴ ሣንቲሞች ውስጥ አንዱን አስር ሣንቲም በገንዘብ ሣጥኑ ውስጥ እጨምርና በመደብሩ መዝገብ ላይ ‘ተከፍሏል’ ብዬ ምልክት አደርጋለሁ፡፡

“ወዲያውኑ ሽማግሌ ገንዘባቸው ከእኔ ዘንድ ብዙ እንደሚገዛላቸው ተረዱና ከሌላ ማንም ሻጭ ጋር አይገበያዩም ነበር፡፡ አንድ ሰው ሊያስተናግዳቸው ሲቀርብ፣ ‘አመሰግናለሁ፡፡ ወንድም ፖልመርን እጠብቃለሁ’ በማለት ይመልሳሉ፡፡

“ከትንሽ ጊዜ በኋላ ከረጅም ጊዜ በፊት የተፈጸመውን ስርቆት ከኅሊናዬ እንዳላወጣሁት ተገነዘብኩ፡፡ በጥፋተኝነት ስለዚያች የተሰረቀች አስር ሣንቲም መጨነቅን ለማቆም ለኔ ብቸኛው መንገድ ያደረኩትን መናዘዝ እና ይቅርታቸውን መጠየቅ ነበር፡፡

“በሚቀጥለው ጊዜ ወንድም ፖልም ለመገበያየት መጡ፣ እንደተለመደው ያዘዙኝን ሰጠኋቸውና ለትንሽ ጨዋታ ወደ ቢሮ እንዲመጡ ጠየኳቸው—፡፡

“ከዚያም ከረጅም ጊዜ በፊት ከሱቃቸው ስለ ሰረቅሁት አስር ሣንቲም እና እንዴት ሁልግዜ በእጃቸው ላይ ያለውን ቀዳዳ ስመለከት ይህ ትዝ እንደሚለኝ ነገርኳቸው፡፡ ይህን ያህል ጊዜ ሁሉ ከሚከፍሉት ውጭ አስር ሣንቲም የሚያወጡ ተጨማሪ ዕቃዎች ወደ ከረጢታቸው በመጨመር እዳዬን በእጥፍ ለመክፈል ስሞክር እንደነበር ገለጽኩላቸው፡፡ ‘ቀሪውን የገንዘብ መጠን እየከፈልኩ እናም በመዝገቡ ላይ ምልክት አደርጋለሁ፣’ ስል ቀጠልኩ፡፡

“ወደ ቁጥሮቹ ዝርዝር እያመለከትኩ እንዲህ አልኩ፣ ‘ወንድም ፖልም፣ እዳዬን ብዙ ጊዜ በተደጋጋሚ ከፍያለሁ፣ ነገር ግን በዚያ መንገድ የህሊና ወቀሳዬን ማንጻት እንዳልቻልኩ ተገነዘብኩ፣ ስለዚህም ነው ጠቀላላ ታሪኩን የምነግርዎት እና ይቅርታዎን የምጠይቀው፡፡’

“ሽማግሌው ፈገግ አሉና እንዲህ አሉ፣ ‘ኦ፣ ወንድም ፖልመር፣ ይቅር ብያለሁ፡፡ ያዘንኩት ቶሎ ብለህ ሳላልነገርከኝ ብቻ ነው፡፡’

“ከዚያም ብድግ አሉ እና እንድጨብጣቸው እጃቸውን ዘረጉልኝ፡፡ ጣቴ ወደ መዳፋቸው ቀዳዳ ተንሸራተተ እናም የጥፋተኝነት ስሜት ለቀቀኝ” (William R. Palmer, as told to Kathryn H. Ipson, “An Expensive Lesson,” *Friend*, ነሐሴ 1975, ከገጽ 34–35)፡፡

---

**ማጠቃለያ**

ጥቀስ

ከፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል የሚከተለውን አስተያየቶች አካፍል፡፡

“ከሐቀኝነት እና ታማኝነት በይበልጥ በፍፁምነት ከፍተኛ ጥረት ልናደርግላቸው የሚያስፈልጉ መልካም ባህሪያት የሉም፡፡ እስቲ እንግዲህ ያንን ለሌሎች ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠውን የነፍስ ጥራት በኛ ውስጥ ለማሳደግ የተሟላን፣ የማናጥፍ፣ ንፁህ፣ እና እውነተኛ እንሁን” (*Faith Precedes the Miracle* [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Deseret Book Co., 1972], ገጽ 248)፡፡

ሙከራ

*ለወጣትነት ማጠንከሪያ* ምክር ላይ ገጽ 9 እና 10 ላይ ያለውን የታማኝነት ክልስ፡፡ ከእግዚአብሔር እና ከሌሎች ከራሳችን ጋር የሚኖረን ታማኝነት ለተሳካ እና ደስተኛ ሕይወት በጣም አስፈላጊ መሆኑን አመልክት፡፡ ወጣት ወንዶቹ በግንኙነቶቻቸው እና በእንቅስቃሴዎቻቸው ሁሉ ታማኝ እንዲሆኑ ምክር፡፡

# ቅዱሳን መጽሐፍትን መመርመሪያ መሳሪያዎች

# 43

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | በኋለኛው ቀን ቅዱስ መጽሐፍት እትሞች ውስጥ የሚገኙትን መርጃዎች ለመጠቀም እያንዳንዱ የአሮናዊ ክህነት ያዥ ለመማር ይነሣሣል። |

**ዝግጅት**

1. እያንዳንዱን ወጣት ቅዱሳን መጽሐቶቹን ወደ ክፍል እንዲያመጣ አበረታታ።
2. ቤትን ለመገንባት የሚጠቀሙ የተለያዩ መሣሪያዎች ለትዕይንት ስብስብ (አማራጭ)።
3. የሚከተሉትን ተለጣፊ የቃላት ስብጥር አዘጋጅ (ወይም በጥቁር ሠሌዳው ላይ ለመፃፍ ተዘጋጅ)፣
   ሀ. አርዕስቶች
   ለ. ተያያዥ አርዕስቶች
   ሐ. የምዕራፍ እና ክፍል አርዕስቶች
   መ. የግርጌ ማስታወሻ
   ሠ. እርስ በርስ ማጣቀሻዎች
   ረ. **GR, HEB, IE, JST, TG, BD, OR**
   ሰ. ተጨማሪ መግለጫ

ለአስተማሪው ማስታወሻ — ይህን ትምህርት ለማስተማር ሁለት ወይም ሦስት ክፍለ ጊዜዎች ያስፈልጉኃል።

**ለትምህርት ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**መግቢያ**

በቁሳዊ ነገሮች ላይ የተደገፈ ትምህርት

ለቤት ግንባታ የምንጠቀምባቸውን የተለያዩ መሣሪያዎች እንደ መዶሻ፣ መጋዝ እና የቀለም ብሩሽ የመሳሰሉትን አሣይ ወይም ወጣት ወንዶች እንዲገልፁ አድርግ። እነዚህ እያንዳንዳቸው መሣሪያዎች ለምን ለምን እንደሚያገለግል ወጣት ወንዶቹ እንዲናገሩ ጠይቅ (መጋዙ እንጨት ወይም ብረት ለመቁረጥ፣ መዶሻው በተለያዩ ዕቃዎች ላይ ሚስማር ለመምታት፣ ብሩሹ ቀለም ለመቀባት)። እያንዳንዱ መሣሪያ የተለየ ጥቅም እንዳለው እና ቤትን ለመገንባት እንደሚጠቀምም ገለጽ፣ ነገር ግን አንዳቸው ከአንዳቸው ሊቀያዩሩ እንደማይችሉ አመልክት። መቀቢያ ብሩሽ እንጨት ለመቁረጫ ሊጠቀም እንደማይችል ሁሉ፣ እንዲሁም መጋዝ ቤት ለመቀባት ሊጠቀም አይችልም። አንዳንድ ጠቃሚ መሣሪያዎች በመገልገል ቅዱሳን መጽሐፍትን የመጠቀም ችሎታዎቻችንና የቅዱሳን መጽሐፍትን ዕውቀታቸውን ሊጨምሩላቸው የሚችሉትን አንዳንድ ጠቃሚ መሣሪያዎችን ሊለማመዱ እንደሆነ ግለፅ።

---

**የኋለኛው ቀን ቅዱስ ቅዱሳን እትሞች ወንጌልን እንድንገነዘብ ይረዱናል**

ጥቀስ እና ውይይት

በሚከተለው ጥቅስ ውስጥ ያለውን መረጃ ግለፅ።

"ከብዙ ምዕተ ዓመታት በፊት አንድ የጥንት ነቢይ የሁለት መዝገቦችን ለቤተ እስራኤላውያን መምጣት ተነበየ (ትንቢተ ሕዝቅኤል 37፥16–19 ተመልከት።) አንዱ መዝገብ ከ 'ይሁዳ'፣ እና ሌላኛው ከ'ኤፍሬም' እንደሚሆን ነው። ምናልባት በሕዝቅኤል ጊዜ ተለምደው እንደነበሩት የ'እንጨት መፃፊያ ሠሌዳዎች'፣ የእንጨት 'በትር' ሲል ገልጿቸዋል . . .። 'አንድ በትርም እንዲሆኑ፣ በእጅህም ውስጥ አንድ ይሁኑ' ተብሎ በእግዚአብሔር እነዚህን መዝገቦች ባንድነት እንዲያጋጥማቸው መታዘዙን ይናገራል። (ሕዝቅኤል 37፥17።)

"ከዚህ ዘመን መጀመሪያ ጀምሮ፣ ይህ ጥቅስ ለመጽሐፍ ቅዱስ እና መጽሐፈ ሞርሞን የቀረበ ነው ተብሎ ተተርጉሟል . . .። (2ኛኔፊ 3፥12 [ተመልከት]፣ ደግሞም ዘፍጥረት 50፥31 ተመልከት።)

"እነዚህ የቅዱሳዊ መጽሐፍት መዝገቦች፣ አንዱ ከይሁዳ ዘር እና አንዱ ከዮሴፍ ዘር 'ባንድ ላይ ማደግ'፣ የእግዚኤሔር ቃል ኪዳኖችን ዕውቀት ለማስፋት፣ ሰላምን ለመመስረት፣ ጭቅጭቅን ለማጥፋት፣ እና ሐሰተኛ ትምህርቶችን ለማስወገድ ይጠቀሙ ዘንድ በዚህ በመመለስ አካባቢ እንዲኖሩ የታቀዱትን የቅዱሳን መጽሐፍትን ታላላቅ ጥንካሬዎች ያመለክታል . . .። አንባቢዎችን የቅዱስ መጽሐፍቶቻቸውን ጥናት ለማገዝ፣ የመጀመሪያው አመራር አዲስ የመጽሀፍ ቅዱስ እና የሦስቱ ኅብር እትም፣ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ የትምህርት ሊቀነትን ለማሻሻል ይዘጋጁ ዘንድ አዟል . . .።

"እነዚህ . . .እትሞች የዓመታት ምርምር እና የመንፈስ ምሪት ውጤቶች ናቸው። በእያንዳንዳቸው ውስጥ ባሉት የተቀናጁ የጥናት መርጃዎች እና የእርስ በርስ ማጣቀሻዎች፣ እነዚህ ሥራዎች በእውነት አሁን በተጠቃሚው እጆች ውስጥ 'አንድ' ናቸው" (Edward J. Brandt, "Using the New LDS Editions of Scripture—As One Book," *Ensign*, ጥቅምት 1982, ከገጽ 42–43)።

• የእነዚህ ቅዱሳን መጽሐፍት ዝግጅት ያዘዘው ማን ነው?

• እነሱን እንዴት መጠቀም እንዳለብን መማር ያስፈልገን ለምንድን ነው?

ይህ ትምህርት በኋለኛው ቀን ቅዱስ የመጽሐፍት እትሞች ውስጥ ያሉትን የተለያዩ የጥናት መርጃዎች አጠቃቀም ለመለማመድ መልካም ዕድል እንደሆነ ግለፅ።

---

**የኋለኛው ቀን ቅዱስ የመጽሐፍት እትሞች እኛን ለመርዳት የተሟሉ መሣሪያዎች ይዘዋል**

የአማካሪው አቀራረብ እና የቅዱስ መጽሐፍ ፍለጋ

ወጣት ወንዶቹን የኋለኛው ቀን ቅዱስ መጽሐፍ እትም የሆኑትን የመጽሐፈ ሞርሞን፣ ትምህርተር እና ቃል ኪዳን፣ እና ታላቅ ዋጋ ዕንቁ እንዲከፍቱ ጠይቅ። ይህ መጽሐፍ ሦስት መጽሐፍት በመያዙ ምክንያት ሦስቱ ኅብር እንደሚባል ግለጽ። በሦስቱ መጽሐፍቶች መካከል ወደሚገኙት የመሃል ክፍሎች እንዲገልጡ አድርግ። እያንዳንዳቸው ገፅ 1 በማለት እንደሚጀምሩ አመልክት። በሦስቱ ኅብር መጨረሻ ላይ ወደሚገኘው የቃላት ማውጫ እንዲገልፁ አድርግ፣ እናም ለሦስቱ መጽሐፎች አንድ የቃላት ማውጫ እንዳለ ግለፅ።

ቀጥሎም በመጽሐፍ ቅዱስ “የብሉይ እና አዲስ ኪዳን መጽሐፍት ስሞች እና ቀደም ተከተል” ተብሎ ወደ ተፃፈበት የመጀመሪያ ገጽ እንዲገልጡ ወጣቶችን ወንዶችን ጠይቅ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሦስት ክፍሎች እንዳሉ አመልክት፣ የብሉይ ኪዳን፣ የአዲስ ኪዳን፣ እና ተጨማሪ ማውጫ። ብሉይ ኪዳን እና አዲስ ኪዳን በተከታታይ ቁጥር እንደተሰየመላቸው አስተውል። የአዲስ ኪዳን የመጀመሪያው ገጽ 1187 ነው፣ ይኸውም በወንጌል ማቴዎስ የሚጀምር ነው። ከዚያም በተጨማሪ መግለጫ ውስጥ ያሉትን አምስት ክፍሎች የሚጀምሩት እንደገና ከገጽ 1 ይሆንና እስከ ካርታው ክፍል የመጀመሪያ ገጽ እንደሚዘልቁ አስተውል።

ተለጣፊ የቃል ዝርዝር ወይም ጥቁር ሰሌዳ እና ውይይት

*አርዕስቶች*። ‘አርዕስቶች’ ተብሎ በተለጣፊ የቃላት ዝርዝር ወረቀት ላይ የጽፃፈውን ቃል ለጥፍ ወይም በጥቁር ሠላውዳው ላይ ጻፍ። በእነዚህ ቅዱሳን መጽሐፍት ውስጥ ሁለት ዓይነት እርዕስቶች እንዳሉ ለወጣት ወንዶቹ ንገራቸው—ተያያዥ አርዕስቶች እና ምዕራፍ አርዕስቶች። መጽሐፍ ቅዱሶቻቸው ወደ ገጽ 2–3 እንዲከፍቱ ጠይቃቸው። ከዚያም “ተያያዥ አርዕስቶች” እና “የምዕራፍ እና ክፍል አርዕስቶች” የሚሉትን የቃላት ዝርዝሮች ለጥፍ፣ ወይም በጥቁር ሠሌዳው ላይ ጻፍ።

1. *ተያያዥ አርዕስቶች*። በእያንዳንዱ ገፅ አናት ላይ ያሉት ተያያዥ አርዕስቶች በገጹ ላይ የተጠቀሱትን የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ቁጥሮች ለይተው እንደሚያሳዩ ግለፅ። የአንድ የተለየን ገጽ ይዘት ባንዴ ለመመልከት ትችላለህ እናም የምታነበውን ምዕራፍ አይመታብህም። ወጣት ወንዶቹ ገጽ 2 ይመልከቱ እና ተያያዥ አርዕስስቱን ለይተው እንዲያሳዩ አድርግ (ዘፍጥረት 1፥15–30)፣ እና ከዚያም ገጽ 3 ይመልከቱና ተያያዥ አርዕስቱን ለይተው እንዲያሳዩ አድርግ (ዘፍጥረት 1፥31–2፥11)። በእያንዳንዱ ገጽ ላይ የመጀመሪያውን እና የመጨረሻውን ቁጥር በምዕራፍ እና ቁጥር ለይተው እንዲያሳዩ አድርግ። የአንድ የተለየን ጥቅስ ቁጥር እነዚህ አርዕስቶች እንዴት ለማመልከት እንደረዱህ አሳይ።
2. *የምዕራፍ እና ክፍል አርዕስቶች*። የምዕራፍ አርዕስቶች የምዕራፉን ፍሬ ነገሮች አጠር አጠር አድረገው ያቀርባሉ (ወይም የትምህርት እና ቃል ኪዳን ክፍል)። ለኋለኛው ቀን ቅዱሳን ደግሞ ለየት ያለው ትርጉም ላላቸው ወሬዎች አትኩሮት ይስባሉ። አንድ ወጣት ኦሪት ዘፍጥረት የምዕራፍ 2 ርዕስ እንዲያመለክት እና እንዲያነብ አድርግ።

• ተያያዥ አርዕስቶች ጥቅሶችን ለመፈለግ እንዴት ይረዱሃል? ስለ ምዕራፎች ያለህን መረዳት ለመጨመር የምዕራፍ አርእስቶች እንዴት ይረዱሃል?

*የግርጌ ማስታወሻ*፣ “የግርጌ ማስታወሻዎች” የሚለውን ተለጣፊ የቃል ዝርዝር ለጥፍ። በቅዱሳን መጽሐፍት ውስጥ፣ በሌሎች መጽሐፎች ውስጥ እንዳሉት ሁሉ፣ የግርጌ ማስታወሻ በተመሣሣይ መንገድ ከገጹ ስር እንዲተኮርበት ወደተሠጠው ቁጥር የሚያመለክቱ ወጣ ተብለው የሚጻፉ ትናንሽ ፊደላት ወይም ትናንሽ ቁጥሮች ናቸው። እነዚህ የግርጌ ማስታወሻ በምዕራፉ ውስጥ ስለ አለው ጠቃሚ ነገር ተጨማሪ መረጃ ይሰጣሉ።

እንደሌሎቹ ቅዱሳን መጽሐፍት እትሞች ሁሉ፣ የኋለኛው ቀን ቅዱስ እትሞች የግርጌ ማስታወሻዎችን ወጣ ተብለው በሚጻፉ ልዩ ጽሑፍ (ዘንበል ተደረገው በሚጻፉ) ፊደሎች ለይተው እንደሚያሳዩ ግለፅ። ለምሣሌ፣ ወጣት ወንዶቹን የማቴዎስ ወንጌል ገልጠው መዕራፍ 1 ቁጥር 1 እንዲመለከቱ አድርግ። ትንሽዬ ወጣ ተብላ የተጻፈች ሀ የምትል ፊደል *ዳቪድ* ከሚለው ቃል በፊት ታገኛለህ። ከገፁ ሥር ጐላ ተደርጐ የተፃፈውን 1 ታገኛለህ፣ ይህም የምዕራፍ 1 የግርጌ ማስታወሻዎችን መነሻ ለይቶ ያመለክታል። የመጀመሪያው ህዳግ *1ሀ* ነው፣ ይህ ደግሞ ህዳግ ሀ የግርጌ ማስታወሻዎችን በቁጥር 1 ማለት ነው።

እያንዳንዱ ገጽ ማስታወሻዎች ከዚያ ገጽ ሥር ታትመዋል። እነርሱም ጐላ ተደርገው በመጻፍ በታተሙ የምዕራፍ ቁጥሮች አማካኝነት ተደርድረዋል፣ ከዚያም የጥቀሱ ቁጥር እና በመጨረሻም በጥቅሱ ውስጥ ወጣ ተብሎ የተጻፈው ፊደል ተዘርዝረዋል። ቁጥሩን እና ፊደሉን ተከትሎ የሚመጣው መረጃ ስለዚያ ልዩ የጥቅስ ክፍል የበለጠ ይነግርሃል።

የሚከተሉት ቃላት እና ምህፃረ ቃላት፣ በጥቁር ሠሌዳው ላይ ፃፍ፣ ወይም ተለጣፊ የቃላት ዝርዝርን ለጥፍ፣ “እርስ በርስ ማጣቀሻ፣” **“GR, HEB, IE, JST, TG, BD, OR።”** ውይይቱን እየቀጠሉ ሲሄዱ፣ እነኚህን እያንዳንዳቸው ምን ማለት እንደሆኑ ወጣት ወንዶቹ እንደሚማሩ ንገራቸው። ምናልባትም የምህፃረ ቃሉ ቁልፍ የታተመበትን ለመመልከት [ዘፍጥረት 1፥1 ወደሚያሣየው] ገጽ ወጣት ወንዶቹ እንዲገልጡ ተፈልገ ይሆናል።

የኋለኛው ቀን አማኝ ቅዱስ መጽሐፍት እትሞች ዘጠኝ የተለያዩ የግርጌ ማስታወሻዎችን እንደሚጠቀሙ ግለፅ። ቀጥሎ ያሉትን ምሣሌዎች ስትወያዩ፣ ወጣት ወንዶቹ ካንተ ጋር የጽሑፎቹን ገጾች እንዲገልጡ ጊዜ የፈቀደውን ያህል እንዲወያዩ አድርግ።

1. *እርስ በርስ ማጣቀሻዎች*፣ እነዚህ በመደበኛ ቅዱሳን መጽሀፍት ውስጥ ያሉትን ከዚህ ጥቅስ ጋር ተዛማጅነት መረጃ ያላቸውን ጥቀሶች በሙሉ ለይተው ያመለክታሉ። በጣም አስፈላጊ የሆኑ ብዙ ሐሣቦችን እንድናገኝ ሊመሩን ይችላሉ። ለምሣሌ ያህል፣ ወጣቶቹ ወደ ማቴዎስ ወንጌል 2፡2፣ የግርጌ ማስታወሻ 2ለ እንዲገልጡ አድርግ።

   • በማቴዎስ ወንጌል 2፡2 የተሰጡት የርስ በርስ ማጣቀሻዎች የትኞቹ ናቸው? (ኢሣያስ 6፡5፣ ኤርሚያስ 23፡5፣ 2ኛኔፊ 10፡14፣ አልማ 5፡50፣ ት እና ቃ 128፡22 [22–23]፣ ሙሴ 7፡53።)

   ይህ የተለየ ጽሑፍ ከእያንዳንዳቸው መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት ጋር እርስ በርሱ እንደተጣቀሰ አስተውል። የእርስ በርስ ማጠቀስን ዋጋ እንዲያገኙ እያንዳንዱ ወጣት ከብሉይ ኪዳን፣ ከመጽሐፈ ሞርሞን፣ ከትምህርት እና ቃልኪዳኖች፣ እና ከታላቀ ዋጋ ዕንቁ ከተሰጡት ማጣቀሻዎች ውስጥ አንድ አንዱን እንዲያመለክቱ እና በጸጥታ እንዲያነቡ አድርግ።

2. *GR* የምንባቡን ተፈራራቂ ትርጉም ከግሪኩ ያሣያል። ለምሳሌ ያህል ወጣት ወንዶቹ ማቴዎስ 2፡16፣ የግርጌ ማስታወሻዎች 16ሀ እና 16መ እንዲያወጡ አድርግ። አንድ ወጣት ተፈራራቂ ትርጉሙን እንዲያነብ አድርግ። የተለያዩ ትርጉሞች እያንዳንዱን ምንባብ በተሻለ ግልጽ እንደሚያደርጉ አስተውል።

3. *HEB* የምንባቡን ተፈራራቂ ትርጉም ከዕብራይስጡ ያሣያል። ወጣቶቹ ማቴዎስ 5፡5፣ 5ሀ የግርጌ ማስታወሻ እንዲያነቡ አድርግ። ይህ የግርጌ ማስታወሻ የጽሑፉን ትርጉም በተሻለ በመገንዘብ ይረዳን ዘንድ ሁለቱንም ማለት የግሪኩን እና የዕብራይስጡን ይጠቀማል። አንድ ወጣት ወንድ ሁለቱንም ትርጉሞች እንዲያነብ አድርግ።

4. *IE* የፈሊጣዊ አነጋገሮች (የሕዝብ ወይም ማኅበረሰብ የተለየ ቋንቋ፣ እንደ ንጉሥ ያዕቀብ ጊዜ እንደሚጠቀሙበት ዓይነት) እና የአስቸጋሪ ትርጉሞች ማብራሪያ ምህፃረ ቃል ነው። ለምሣሌ ያህል፣ ወጣቶቹ ማቴዎስ 5፡3፣ የግርጌ ማስታወሻ 3ለ፣ እንዲያወጡ እና ማብራሪያውን እንዲያነቡ አድርግ።

5. *JST* የዮሴፍ ስሚዝ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ምህፃረ ቃል ነው። ወጣቶቹ በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ "የዮሴፍ ስሚዝ ትርጉም" የሚለውን እንዲፈልጉ አድርግ፣ እናም ከእነርሱ ጋር ከልሰው። ከ **JST** ውስጥ ስድስት መስመሮች የሚረዝም ምንባብ በግርጌ ማስታወሻዎቹ ውስጥ ተጠቅሷል።። በተጨማሪ መግለጫ ካለው ማጣቀሻ ጋር የግርጌ ማስታወሻዎቹ በተጠቀሰበት ሥፍራ ውስጥ በርከት ያሉ ረዣዥም ምንባቦች ይስተዋላሉ። ከንጉስ ያዕቀብ ጋር ያሉ ለውጦች በልዩ ጽሑፍ ተጠቀሰዋል። ወጣቶቹን ወደ ማቴዎስ 4 እንዲገልጡ አድርግና እዚያ የሚገኙትን የግርጌ ማስታወሻዎች ይመልከቱ። በልዩ ጽሑፍ አፃፃፍ ዘይቤ የተቀመጡት የዮሴፍ ስሚዝ ትርጉም ቃላት የአዳኛችንን ፈተናዎች ትረካ እንዴት ግልፅ እንዳረጉት አስተውል። በግርጌ ማስታወሻዎች ውስጥ ለማተም በጣም ረዥም ስለሆኑ ጠቃሚ ነገር ምሣሌ ይሆኑ ዘንድ፣ ወጣቶቹ ወደ ዮሐንስ 1፡1 የግርጌ ማስታወሻዎች 1ሀ እንዲገልጹ አድርግ። ከዚያም ተጨማሪ መግለጫ ውስጥ ወዳሉት ወደ ዮሴፍ ስሚዝ ትርጉም ጭማሪዎች ግለጽ።

6. *TG* የርዕስ መምሪያ ምህፃረ ቃል ነው—"ርዕስ መምሪያ ከተመረጡ ጠቃሚ የቃላት ቀደም ተከተል እና ቃላት ማውጫ ጋር"—ተጨማሪ መግለጫ ውስጥ ይገኛል። ይህ ክፍል 3,514 የተመዘገቡ ምርጥ ቃላትን ይዟል። ከእነዚህ ውስጥ ስድስት መቶ ስምንቱ የወንጌል አርዕስቶች ሲሆኑ በሁሉም መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት ውስጥ እጅግ በጣም ታላላቀ ምንባቦች በመባል ተዘርዝረዋል። የተቀሩት ሁሉ የቃላት ዝርዝሮች ከሁሉም መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት የተመረጡ ጠቃሚ የማጣቀሻ ቀደም ተከተሎች ናቸው። ወጣቶቹ የማቴዎስ ወንጌል 1፡19 የግርጌ ማስታወሻ 19ሀ፣ እሱም ስለ "ምሳሌ" መረጃ የያዘውን ከርዕስ መምሪያው ማጣቀሻ ላይ እንዲፈልጉ አድርግ። ርዕስ መምሪያ ማጣቀሻዎች የያዘው ለመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሣይሆን ለሌሎቹም መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት መሆኑን አመልክት።

   ወጣቶቹ ከመጽሐፈ ሞርሞን ውስጥ 1ኛ ኔፊ 7፡8 እንዲያወጡ ጠይቀ። የግርጌ ማስታወሻ 8ሐ እንዲፈልጉ አድርጋቸው እናም ማጣቀሻው እንደገና *"ምሳሌ"* በሚል አርዕስት ወደ ርዕስ መምሪያው መሆኑን አስተውል። ይህን በአዕምሮ ውስጥ እያሰላሰላችሁ፣ ቀጥሎ በሦስቱ ህብር መጨረሻ ላይ ከሚገኘው የቃላት ማውጫ ውስጥ ምሣሌ የሚለውን ቃል እንዲያወጡ አድርጋቸው። የቃላት ማውጫው የሚያጣቀሰው ከሦስቱ ህብር ጽሑፎች ጋር ብቻ መሆኑን፣ ነገር ግን በርዕስ መምሪያ ውስጥ ያለው ማጣቀሻ የበለጠ የተሟላ መሆኑን አመልክት።

7. **BD** የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ምህፃረ ቃል ነው፣ የሚገኘውም በመጽሐፍ ቅዱስ ተጨማሪ መግለጫ ክፍል ውስጥ ነው። መዝገበ ቃላቱ በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ላይ የተመሠረተ ነው፣ ነገር ግን ጌታ በዘመናችን የገለጠልንን ተጨማሪ ብርሃን እና ዕውቀትን የሚያንፀባርቁ ብዙ ጭማሪዎች እና ለውጦች ይዟል። የመዝገበ ቃላቱ መግቢያ እንደሚነግረን በመዝገበ ቃላቱ ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ዝርዝሮች በዓለም ከሚገኘው ምርጥ የጥናት ዕውቀት የተወሰዱ ቢሆንም ቀሉ፣ በአዲስ ምርምር ወይም አዲስ ራዕይ ላይ ለተመረኮዘ ዳግም ግምገማ የተደረጉ ናቸው (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት መግቢያ ተመልከት)። መዝገበ ቃላቱ መጽሐፍ ጥናትን ለመርዳት የሚያበረታታ ማስተዋል ሊያቀርብ ይችላል። ወጣቶቹ ማቴዎስ 13፡25 እንዲያነቡ አድርግ። ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ

ቃላት ላይ *እንክርዳድ* የሚለውን ቃል እንዲፈልጉ፣ እና የጥቀሱን ግንዛቤ የሚጨምረውን ገለፃ እንዲያነቡ ጠይቃቸው፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ማጣቀሻዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ውስጥ አይገኙም፣ ነገር ግን በሌሎች መደበኛ ቅዳሳን መጽሐፍት ውስጥ ጭምር እንጂ፡፡ ለምሣሌ ያህል፣ ወጣቶቹን 1ኛ ኔፊ 19፥10፣ የግርጌ ማስታወሻ *10ሰ*፣ እንዲፈልጉ አድርግ፡፡ የግርጌ ማስታወሻ መዘርዝር በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ "የጠፉት መጽሐፎች" ወደሚለው መዘርዝር እንደሚያጣቀስ አስተውል፡፡ ያንን መዘርዝር ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ እንዲፈልጉ አድርጋቸው፡፡

8. *OR* በቀዱሳን መጽሐፍት ውስጥ የሚያገለግሉ የጥንት ወይም ጊዜ ያለፈባቸውን የእንግሊዥኛ አገላለጾች ወይም ቃላቶች የሚያብራሩ ተፈራራቂ ቃላቶችን ያስተዋውቃል፡፡ ለምሣሌ ያህል፣ ወጣት ወንዶቹን ማርቆስ 5፥39–40፣ የግርጌ ማስታወሻ *39ሀ* እና *40ሀ* እንዲያወጡ አድርግ፡፡
9. አንዳንድ የግርጌ ማስታወሻ እንደ **GR** ወይም **HEB** በመሳሰሉት ምህፃረ ቃሎች አይከፈቱም፣ ነገር ግን የመጽሐፍ ጥናቱን ለመርዳት የአዘጋጁን ማብራሪያዎች ያቀርባሉ፡፡ ለምሣሌ ያህል፣ ወጣት ወንዶቹን ማቴዎስ 1፥16፣ የግርጌ ማስታወሻ 16ሠ እንዲያወጡ አድርግ፡፡

*ተጨማሪ መግለጫ*፡፡ ተጨማሪ መግለጫ የሚለውን የቃላት ዝርዝር ለጥፍ ወይም በጥቁር ሠሌዳው ላይ ፃፍ፡፡ ቀሪዎቹ የኋለኛው ቀን ቅዱስ የንጉስ ያዕቆብ መጽሐፍ ቅዱስ እትም መርጃዎች በተጨማሪ መግለጫ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ተጨማሪ መግለጫ የሚከተሉትን ይዟል፡

1. *ርዕስ መምሪያ*፡ በዚህ ትምህርት "የግርጌ ማስታወሻ" ክፍል ውስጥ የተጠቀሱት ምሣሌዎች ይህንን ክፍል በምሣሌ ያብራራሉ፡፡

   ወጣቶቹን የጠቃሚ ቃላት ቀደም ተከተል ዓይነትን በምሣሌ ለማስረዳት "*ማደሪያ ሥፍራ*" የሚለውን መዘርዝር እንዲያወጡ አድርግ፡፡ ይህ መዘርዝር እንደ "በእንግዶችም ማደሪያ ሥፍራ ስላልነበራቸው" (ሉቃስ 2፥7) ወደሚለው ዓይነት ምንባብ ይመራቸዋል፡፡ ወጣት ወንዶቹ "*ማደሪያ ሥፍራ*" በሚለው መዘርዝር ውስጥ ከተጠቀሱት ጥቀሶች አንዱን እንዲፈልጉ አድርግ፡፡

2. *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት*፣ ትምህርት "የግርጌ ማስታወሻ" ክፍል ውስጥ *BD* በሚለው ስር ያሉትን ምሳሌዎች ተመልከት፡፡
3. *የዮሴፍ ስሚዝ ትርጉም*፣ በዚህ ትምህርት "የግርጌ ማስታወሻ" ክፍል ውስጥ የ **JST** ምሣሌዎችን ተመልከት፡፡
4. *የቦታ ስም እና ካርታዎች*፣ የቦታ ስም በካርታ ላይ ለተመለከቱት የቦታ ስሞች በፊደልና በቀጥሮች ማጣቀሻዎችን ይዘረዝራል፡፡ ይህ ክፍል ከርሱ ቀጥሎ ካለው ከካርታ ክፍል ላይ የተመለከቱትን ቦታዎች ለማመልከት አጋዥ ነው፡፡ ወጣት ወንዶቹ "የቦታ ስም" የሚለውን እንዲያወጡ አድርግ፡፡ የካርታዎቹን አጠቃቀም መግለጫ አንብብ፡፡ በማቴዎስ 11፥23 የተመለከተውን ቦታ እንዲፈልጉ አድርግ (ቀፍርናሆም)፡፡

   የቦታ ስም የሚለውን አውጣና ቀፍርናሆምን አመልክት፡፡ ይህን ቃል ተከትሎ "D3 14,15" ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ቀፍርናሆም የሚገኘው በካርታ 14 እና 15 ላይ በD3 ሥፍራ ውስጥ ነው፡፡ ካርታዎቹ በሙሉ እያንዳንዳቸው ከገጹ አናት መሐሉ ላይ ቁጥር እንደተሰጣቸው አስተውል፡፡

---

**የጥናት መርጃዎች ቅዱስ ፅሑፋዊ አስተውሎት እንድናገኝ ሊረዱን ይችላሉ**

አንድ ወጣት ወንድ ሞሮናይ 7፥48 እንዲያነብ አድርግ፡፡ የግርጌ ማስታወሻ 48ሐ እንዲመለከት አድርግ፡፡ ይህ ወደ 1ኛ ዮሐንስ 3፥1–3 ይመራል፡፡ ሌላ ወጣት ወንድ ይህን ምንባብ እንዲያነብ አድርግ፡፡ (መፅሐፍቶቻችሁ የግርጌ ማስታወሻ ከሌሏቸው፣ ለአንድ ወጣት ወንድ 1ኛ ዮሐንስ 3፥1–3 እንዲፈልግ ንገር፡

• ጌታ በእነዚህ ሁለት ፅሑፎች ውስጥ ተመሳሳይ ቃላቶች መጠቀሙ ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?

ጌታ ከትውልድ ትውልድ ትዕዛዛቶቹን እንደማይቀይር ግለፅ፡፡ የእርሱ መልዕክት ለኛ የማይቀየር ነው፡፡ ዘወትር፣ በጣም ተመሣሣይ ቃላቶች ይጠቀማል፡፡

የጥቀስ ፍለጋ

ጊዜ እስከፈቀደው፣ ወጣት ወንዶቹ የሚከተሉትን የፅሑፎች ስብስብ እንዲፈልጉ አድርግ፡፡ በተለያዩ ጽሑፎች ውስጥ ጌታ በተደጋጋሚ ጊዚያት ተመሣሣይ ቃላቶች የሚሰጥባቸውን ብዙ ምሣሌዎች ያገኛሉ፡፡ እንደነዚህ ዓይነት በመተዎች የሚቀጥሩ ተመሣሣይ የትዕዛዞች ስብስብ እንዳሉ ግለጽ፡፡ እነዚህን ትዕዛዛት ወጣት ወንዶቹ ሊያገኟቸው የሚችሉት መጽሐፍትን በመመርመር ብቻ ነው፡፡

ትንቢተ ኢሣይያስ 52፥11

3ኛ ኔፊ 20፥41

ትምህርት እና ቃል ኪዳን 38፥42

ትምህርት እና ቃል ኪዳን 133፥5

("እናንተ የእግዚአብሔር ዕቃ የምትሸከሙ ሆይ፣ ንፁሐን ሁኑ፡፡")

• እነዚህ ምንባቦች በእኛ ላይ እንደ ክህነት ያዥነታችን እንዴት ይተገበራሉ?

ለክህነት ያዦች ንፁህ የመሆን ትዕዛዝ በሁሉም ትውልዶች ተመሣሣይ መሆኑ የወጣት ወንዶቹን ስሜት እንዲማርክ አድርግ።

ዮሐንስ 4፥35

አልማ 26፥5

ትምህርት እና ቃል ኪዳን 4፥4

ትምህርት እና ቃል ኪዳን 6፥3

ትምህርት እና ቃል ኪዳን 33፥3፥7

("አሁን አርሻው ለምርት ደርሷል")

• በትምህርት እና ቃል ኪዳን ውስጥ ያሉት ጽሑፎች ግንዛቤያችንን እንዴት ይጨምሩልናል?

• አዝመራውን መሰብሰብ እንዴት ልናግዝ እንችላለን?

ትንቢተ ኢሣይያስ 52፥7

ሮሜ 10፥15

1ኛ ኔፊ 13፥37

ሞዛያ 15፥15–18

ትምህርት እና ቃል ኪዳን 128፥19

("የመልካምንም ወሬ የምስራች የሚናገሩ እግሮች እንዴት ያማሩ ናቸው።")

• በቋሚነት ወንጌላዊነት መሄድ ለአንተ እንዴት አስፈላጊ ነው?

• ጌታ በወንጌላዊነት ስለሚያገለግሉት ሰዎች እንዴት ይሰማዋል?

---

**ቅዱሳን መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቃሎች ናቸው**

ጥቀስ

በጥቁር ሠሌዳው ላይ፣ ቅዱሳን ፅሑፎች *የእግዚአብሔር ቃላት* ናቸው ብለህ ፃፍ።

የሚከተለውን የነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝን ነገሮች አንብብ፣

"በሰማያት ላይ ተቀርፆ ያለውን፣ ሁሉን ማድረግ የሚችለውን ኃይል ልብ ማለት የቻለ፣ በተቀደሱ ጥራዞች ውስጥ ያለውን የእግዚብሔርን የእጅ ፅሑፍ ደግሞ ማየት ይችላል፣ እና እርሱን ዘወትር የሚያነበው በጣም ይወደዋል፣ እንዲሁም ከእርሱ ጋር የተላመደ፣ እጁን የትም ሊያየው ቢችል ያውቀዋል" (*Teachings of the Prophet Joseph Smith*, sel. Joseph Fielding Smith [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Deseret Book Co., 1976],ገጽ 56)።

ቅዱሳን መፅሐፍትን የማናጠና ከሆነ ጌታ ለእኛ ያለውን መመሪያዎች ማወቅ እንደማንችል ግለፅ። ይሁንና፣ ዮሴፍ ስሚዝ እንዳለው፣ ዘወትር ቅዱሳን መፅሀፍትን የምናጠና ከሆነ ጌታ ለእኛ ያለውን መመሪያዎች እንገነዘባለን እንዲሁም በህይወት ውስጥ መያዝ የሚገባንን ፈለግ እንማራለን።

---

**ነቢያት የእግዚአብሄርን ቃላቶች ይናገራሉ**

ቅዱስ መጽሐፍት እና ውይይት

ወጣቶቹ የሚከተሉትን ምንባቦች እንዲያነቡ አድርግ፣ ኢሣይያስ 51፥16 እና ኤርሚያስ 1፥9።

• ጌታ ቃላቶቹን በነቢያት አፎች ላይ አደረገ ሲል ምን ማለቱ የመስልሃል?

ለሙሴ እንዲህ ብሎታል፣ "እኔም ከአፍህ ጋር እሆናለሁ፣ የምትናገረውንም አስተምርሃለሁ" (ዘፍጥረት 4፥12)።

• ሙሴ ለሕዝቡ ምን እንደሚናገር ያስተማረው ማን ነው?

የኔፊ የመጨረሻው ምስክርነት እንዲህ ይላል፣ "እነዚህ ቃላት . . . የክርስቶስ ቃላት ናቸው፣ እናም እሱ ለእኔ ሰጠኝ" (2ኛ ኔፊ 33፥10)።

• ኔፊ የተናገራቸውን ቃላት የሰጠው ማን ነው?

በመጨረሻም፣ አንድ ወጣት ትምህርት እና ቃል ኪዳን 18፥34–36 እንዲያነብ አድርግ።

• በትምህርት እና ቃልኪዳን ውስጥ ያሉት ቃላቶች የማን ናቸው (የጌታ።)

• የጌታን ድምፅ ዛሬ እኛ የምንሰማው እንዴት ነው? (የቅዱሣን መጽሐፍትን እና የህያው ነቢያትን ቃላቶች በማጥናት)።

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት

ስለ ቀዱሳን መጽሐፍት እና እነርሱን ስለ ማጥናት አስፈላጊነት ያለህን ስሜት ለወጣቶቹ መስክር። የኋ.ቀ.ቀ. ቀዱስ መጽሐፍት አትሞች ወጣቶቹ በአግባቡ እስከተጠቀሚቸው ድረስ የጌታ ትምህርቶች በደንብ በተሻለ እንዲገነዘቡ እንደሚረዷቸው ግለጽ።

ሙከራ

ለወጣቶቹ የኋ.ቀ.ቀ ቀዱስ መጽሐፍት አትሞች በትምህርቶቻቸው ውስጥ እንደሚያገለግሉ ግለጽላቸው። ቀዱሳን መጽሐፍቶቻቸውን በየሳምንቱ ይዘዋቸው እንዲመጡ ምከራቸው።

ወጣት ወንዶቹ በኋለኛው ቀን ቀዱሳን መጽሐፍት አትሞች ውስጥ የቀረቡትን መሣሪያዎች በቤተክርስቲያን ክፍሎች ውስጥ ብቻ ሳይሆን በግላዊ የመጽሐፍት ጥናታቸውም ደግሞ ይጠቀሙባቸው ዘንድ አደፋፍራቸው። ከቀዱሳን መጽሐፍት ወጣት ወንዶቹ በየቀኑ እንዲያነቡ ምከር።

# የተሻለ የቤት አስተማሪ መሆን

# 44

**ዓላማው**

በዝግጅት እና በፍቀር አማካኝነት፣ እያንዳንዱ ወጣት ወንድ የቤት አስተማሪ ለሆነበት ቤተሰብ በረከት ይሆናል፡፡

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት፡፡
   ለ. ጥቅሶች ምልክት ማድረጊያ እርሳሶች፡፡
2. “አስርቱ ትዕዛዛት ለቤት አስተማሪዎች” የሚል የተዘጋጀ ጽሑፍ ቅጂዎች ለእያንዳንዱ ወጣት እና በክህነት ስብሰባ ላይ ለሚገኙ ለበላይ የቤት አስተማሪዎች ሥራ፡፡
3. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ “አራት ቤተሰቦች” የሚል የተዘጋጀ ጽሑፍ ቅጂ ሥራ፡፡

ለአስተማሪው ማስታወሻ

ዘወትር ወጣቶችን በጥሪ ኃላፊነት ስሚቶቻችውን እንማርካለን ነገር ግን ጥሪያቸውን ይፈጽሙ እና ያጉሉ ዘንድ የዚያን ጊዜ ጥቂት ድጋፍ እንሰጣቸዋለን፡፡ ይህ ትምህርት ወጣት ወንዶቹ እንደ ቤት አስተማሪነታቸው አሁን ብቻ ሳይሆን በቀሪ ሕይወታቸው ደግሞ፣ ጥሪዎቻቸውን ያጉሉ ዘንድ እንድተረዳቸው ያግዛቸዋል፡፡

የወጣት ወንዶቹ የበላይ የቤት አስተማሪ ጓደኞቻቸው በዚህ በተለየ አንድ የክህነት ስብሰባ ላይ ቢገናኟቸው ይህ ትምህርት ብዙ የተሻለ ውጤት የሚያስገኝ እና በወጣት ወንዶቹ ላይ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ግፊት የሚሰጥ ይሆናል። ጳጳስህ ካጸደቀው፣ አስፈላጊውን ዝግጅቶች እና ግብዣዎች ከውን፡፡

**ለትምህርት እድገት የቀረበ ሐሳብ**

**መግቢያ**

ጥቁር ሠሌዳ እና ውይይት

በጥቁር ሠሌዳው ላይ የሚከተለውን የሚመስል መለኪያ አስቀምጥ፣

| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ውጤት የማያስገኝ | | | | | | | | | በጣም ውጤታማ |

• በቤት ለቤት አስተማሪነትህ ምን ያህል ውጤታማ ነኝ ብለህ ታስባለህ? (እያንዳንዱ ወጣት በጥቁር ሠሌዳ ላይ ባስቀመጥከው መለኪያ የትኛው ላይ እራሱን እንደሚያስቀምጥ ያመለክት ዘንድ ፍቀድ፡፡ የእያንዳንዱ ወጣት የመነሻዎች ሥፍራ እርሱም እራሱን የሚያስቀምጥበትን ሥፍራ የሆነውን መፃፍ ትችላለህ።

የቤት ለቤት አስተማሪዎች ለቤት ትምህርት በሚሄዱበት ጊዜ ጌታን፣ ጳጳሱን፣ እና የቡድኑን ፕሬዚዳንት እንደሚወክሉ ግለጽ፡፡

• ጌታ፣ ጳጳሱ፣ እና የቡድኑ ፕሬዚዳንት ከመለኪያው በየትኛው ላይ እንድትሆን የሚፈልጉ ይመስልሃል? መልሶቻቸውን ተወያዩበት፣ ከመለኪያው ላይ በጋራ የተስማማችሁበትን ምልክት አድርግበት፡፡

ለወጣት ወንዶቹ የተቀረውን የትምህርቱን ጊዜ የተሻሉ ውጤታማ የቤት ለቤት አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ እነርሱን በመርዳት እንደምታጠፋ ንገሯቸው፡፡

### ውጤታማ የቤት ለቤት አስተማሪ ቤተሰቦቹን ይጠነቀቃል እንዲሁም ያገለግላቸዋል

**መጀመሪያ የተዘጋጀ ጽሑፍ እና ውይይት**

ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ እና ለጉብኚ የቤት ለቤት አስተማሪ “አስርቱ ትዕዛዛት ለቤት አስተማሪዎች” የሚለውን የተዘጋጀ ጽሑፍ ቅጂ ስጥ። እያንዳንዱን “ትዕዛዝ” በአጭሩ በመወያየት ወጣት ወንዶቹ ይህ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ መገንዘባቸውን አረጋግጥ። ከትዕዛዛቶቹ እያንዳንዱን መጠበቅ እነርሱ እንዴት ለተመደቡበት ቤት ለእያንዳንዱ ቤተሰብ አባላት እንክብካቤ ማድረጋቸውን ሊያመለክት እንደሚችል ትኩረት ስጥበት። ለምሣሌ፣

- ከአንድ ቤተሰብ ጋር ቀጠሮ ማድረግ ለእነርሱ በእርግጥ እንደምትንከባከባቸው እንዴት ያሣያል? (ለግል ጉዳያቸው እና ለጊዜው አጠቃቀማቸው ያለህን አክብሮትህን ታሳያለህ።)

ከሁለተኛው ትዕዛዝ አንስተህ አስሩንም ሁሉ በአጭሩ እስክትወያይ ድረስ ቀጥል።

**ሁለተኛ የተዘጋጀ ጽሑፍ እና ውይይት**

ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ “አራት ቤተሰቦች” የሚለውን የተዘጋጀ ጽሑፍ ቅጂ ስጥ።

እያንዳንዱ አጭር የሐይወት ታሪክ ባንድ ላይ አንብብ። ከአራቱ ቤተሰቦች ጋር ምናልባት የሚዛመዱ ቢሆኑም ከአስርቱ ትዕዛዛት እያንዳንዱን ለመወያየት ጊዜ አይኖርም፣ ስለዚህ አንድ ጥሩ የቤት ለቤት አስተማሪ ምን እንደሚያደርግ እንደ ምሣሌ ያገለግሉህ ዘንድ ከትዕዛዛቱ ሦስት ወይም አራት እንድትወስድ ተመክራለህ። ቁጥር2፣ 3፣ 8፣ እና 9 ለመመርመር ትሻ ይሆናል።

እንደሚከተለው ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቅ፥

- እንደ ቤት ለቤት አስተማሪነታችሁ ለጉብኝት ወደ ስከሚድት ቤተሰብ? መርዱክ ቤተሰብ? ጆንሰን ቤተሰብ? ሲስተር ሎፔዛ ስትሄዱ ጸሎቶቻችሁን የተሻለ ትርጉም ያለው ለማድረግ እንዴት ትችላላችሁ?

ከአስርቱ ትዕዛዛት ውስጥ ሦስት ወይም አራቱን ትዕዛዛት እስከትወያዩ ድረስ እንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች መጠየቅ ቀጥል እናም ለአራቱ ቤተሰቦች እነዚህንም ጥያቄዎች ተገልገልባቸው። እያንዳንዱን ቤተሰብ እና እያንዳንዱን የቤተሰሳብ አባል ግለሰብ በመንከባከብ እና በማፍቀር አስፈላጊነት ላይ በማነጣጠር መቀየትህን እርግጠኛ ሁን።

---

### የተሻለ የቤት ለቤት አስተማሪ እንዴት መሆን እችላለሁ

**ታሪክ**

ለወጣት ወንዶቹ ልክ እንደነርሱ ወጣት ሆኖ ጥሩ የቤት ለቤት አስተማሪ ስለነበረ አንድ ወጣት እውነተኛ ታሪክ ልትነግራቸው እንደሆነ ንገራቸው። ታሪኩን አንተ ስታነብ እነርሱ ይህ ወጣት ስለጠበቃቸው የቤት ለቤት ትምህርት ትዕዛዛት እንዲያዳምጡ ጠይቃቸው።

“በቅርቡ . . . አንድ ሰው እና ለአስተማሪነት ዕድሜው የደረሰ ወንድ ልጁ ለቤተሰባችን እንደ ቤት ለቤት አስተማሪ ሆነው ተመድበው ነበር። የአባትየውን ለወንጌል እራሱን አሳልፎ መስጠት እናውቃለን ነገር ግን የወጣት ልጅየው ገጽታ እና ጠባይ ተመሣሣይ እራሱን አሳልፎ መስጠት ቢያንጸባርቅም። ከልጁ ምን እንደሚጠበቅ አናውቅም ነበር፣ ምንም እንኳን ከእኛ ጋር በመጀመሪያ ጉብኝታቸው ወቀት፣ በዚህ ወጣት ልጅ ላይ አይኖቼን ተክዬ ነበር። በተገቢው ፀጥ ያለ ቢሆንም፣ የተናገራቸው ወይም ያደረጋቸው ማናቸውም ነገሮች ለተሸከመው ክህነት ክብርን አስገኝቷል። ብዙም ሳይቆዩ ወጣት ልጃችን ከአንድ ዓመት በፊት መሞቱን እና እኛም ሌላ ሕፃን እየጠበቅን እንደነበረ ይረዳሉ። ከዚያች ቀፅበት አንስቶ ለእኛ ሲጸልዩ እና ሲያበረታቱን የሐይወታችን የተለየ ክፍል ነበሩ። በዚያ የመጀመሪያ ጉብኝት ማብቂያ ላይ ወጣቱን ልጅ ጸሎት እንዲያደርግልን ጠየኩት። በጸሎቱ ውስጥ ጌታ ስለሞተው ልጃችን እንዲያበረታታን እና በቅርቡ የሚወለደውን ልጅ እንዲባርከው ጠየቀ። በተለየ ሁኔታ ባለቤቴ በሕፃኑ አወላለድ በኩል ምንም ችግር እንዳይኖርባት ጸለየ። ባለቤቴ እና እኔ በዚህ ወጣት አስተማሪ እውነተኝነት እና ንቁ ስሜት ተማረክን። በተከታዮቹ ቀናት እና ሣምንታት ወቀት እነዚህ ወንድሞች በመደበኛነት ስለ እኛ ይጠይቁ ነበር (በወር ውስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ)። የሕፃኑን ልደት ተከትሎ፣ ወጣቱ ልጅ፣ ከአባቱ ጋር፣ ሥጦታ አመጡ። በጸሎት ሁላችንም ተንበርክከን ሳለ አስተማሪው በሕፃኑ ደህና መወለድ ምስጋናውን ለጌታ ገለፀ” (በኤች ብሩክ ፒተርሰን በድጋሚ እንደተነገረው፣ H. Burke Peterson, በ “The Role of the Teacher,” *New Era*, ግንቦት 1974, ከገጽ 10–11)።

**ውይይት**

- ከቤት ለቤት ትምህርት ትዕዛዛት ነው የትኛው በተለይ ደህና አድርጐ ይህን ወጣት እንዲታዘዝ ያደረገው? (ቁጥር 5፣ 7፣ 8፣ 9፣ እና 10።)

**ታሪክ**

ስለ አንድ የቤት አስተማሪ ጠቃሚነት የሚከተለውን ታሪክ አንብብ።

“ልጅ ሆኜ ዘወትር የዋርድ አስተማሪዎች ጉብኝቶችን (አሁን የቤት ለቤት አስተማሪዎች የተባሉትን) እናፍቃለሁ። ከሁሉም በጣም ወደ ቤታችን የሚመጣውን ትንሽየውን ጓደኛ፣ ወንድም ላቤልን አስታውሳለሁ። ወንድም ላቤል እኛን መጀመሪያ መጐብኘት ሲጀምር የአስራ አምስት ዓመት ገደማ ወጣት ልጅ ነበር—። ጥሩ አትሌት እና በትምህርት ቤታችን በጣም ተስፋ ከሚጣልባቸው እግር ኳስ ተጫዋቾች አንዱ ነበር። ነገር ግን ከሁሉም በላይ ጥሩ የኋለኛው ቀን ቅዱስ ነበር እናም እኔ የእግዚአብሔርን ክህነት እንዴት ጥሩ አድርጐ እንደያዘው አደንቅ ነበር።

“ለኔ ቤተሰብ በሙሉ ትሁት እና ደስተኛ ነበር፡፡ ብዙ አይናገርም፣ ነገር ግን አንዴ የተናገረው ዘወትር መልካም ደውል ሆኖ ይደውልልን ነበር፡፡ ወንድም ላቤል በከተማ አካባቢ፣ በትምህርት ቤት፣ እና ሌሎች ቦታዎች አይቼዋለሁ እናም በእውነት የእሱን ምሣሌ አድንቄያለሁ፡፡ በሚያገኘኝ ጊዜ፣ ስሜን ያውቀዋል እናም ጮክ ብሎ ሰላም ይለኛል፡፡ እርሱን በቤታችን ጠርቶ ማግኘት ለኔ (ለ10 ዓመት ገደማ ልጅ) ምን ዓይነት ክብር ነበር፡፡ በግልፅ፣ የዚያን ክህነት ቡድን የበላይ ጓደኛ ማስታወስ አልችልም፡፡ እርግጠኛ ነኝ ጥሩ ሰው ነበር፣ እና እንዲሁም እናደንቀው ነበር፡፡ ነገር ግን ስለ ትንሹ አምስተኛ ክፍል ልጅ፣ ያ የአስራ አምስት ዕድሜ ያለው አስተማሪ፣ ወንድም ላቤል፣ በእርግጥ ሌላ ሰው ነው፡፡ ጳጳሱ ወደ እኔ ቤት የተሻለ ጥሩ አስተማሪ ሊልክ አይችልም፡፡ በዛ የአስራ አምስት ዓመት ዕድሜ ባለው አስተማሪ ተፅዕኖ ምክንያት ከሠላሣ ሦስት ዓመት በፊት የነበሩት ክስተቶች እስካሁን በጆሮዬ ጐላ ብለው ያቃጭላሉ (እንደተናገረው *Priesthood Study Course, Teachers Quorum*, Series B [1971], ገጽ T–10)፡፡

• ወንድም ላቤል ለዚህ ወጣት አስፈላጊ የቤት ለቤት አስተማሪ ያደረጉት አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ተሳትፎ

እያንዳንዱ ወጣት እና የበላይ ጓደኛውን ከትዕዛዛት ውስጥ እስካሁን በደንብ የሚታዘዟቸውን ከ“አስርቱ ትዕዛዛት የቤት ለቤት አስተማሪዎች” ቀጂ ፊት ለፊት የማረጋገጫ ሠረዝ ምልክት እያደረጉ እንዲያጠቁሩ አድርግ፡፡ ባንድ ላይ ሆነው በማሰብ ይህን ነገር እንዲያደርጉ ጊዜ ፍቀድ፡፡ ከዚያም ወረቀቶቻቸውን እንዲመልሱ አድርግ እና ልክ ቀጥሎ እንዳለው ቀላል ባለ ሁለት ዓምድ ቻርት ሥራ፡፡ በወር ዓምዱ ሥር የሚቀጥሉትን አራት የዓመቱን ወሮች እና ከአስርቱ ትዕዛዛት ማሻሻል የሚፈልጉትን በዚያን ወር በቀኙ ዓምድ ውስጥ እንዲዘረዝሩ አድርግ፡፡ ቻርታቸው ይህን መምሰል ይችላል፣

| **ወር** | **የሚሠራበት ትዕዛዝ** |
|---|---|
| ግንቦት | ከቤተሰቦች ጋር መጸለይ |
| ሰኔ | ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ጋር ቀጠሮዎችን አድርግ |
| ሐምሌ | ልደቶችን በአጭር ጉብኝት መለየት |
| ነሐሴ | ለድንገተኛ ሁኔታዎች በጣም ንቁ መሆን |

---

**ማጠቃለያ**

ጥቅስ

የሚከተለውን የፕሬዚዳንት እዝራ ታፍት ቤንሰን ገለፃ ጮክ ብለህ አንብብ፣

“እያንዳንዱን [የቤት ለቤት አስተማሪ] ሊጠየቅ የሚገባው ጥቂት ጥያቄዎች እነሆ . . .“ማድረግ እንደሚገባህ በቤተሰቦችህ ላይ ክትትል ታደርጋለህን?

“ፍላጎቶቻቸውን ታገለግላለህ?

“ፍላጐቶቻቸው ሆነው ላገኘሃቸው የቤተሰቦችህ ደህንነት፣ ላስታወስካቸው ልደቶችና ልዩ ክስተቶች፣ በደንብ ትንከባከባለህ? እናስ ለነርሱ ያለማቋረጥ ትፀልያለህ?

“ቤተሰቡ እርዳታን በሚሻበት ጊዜ ለቤቱ የመጀመሪያ ደራሽ ነህን?

“የቤተሰቡ አባወራ መጀመሪያ አንተን ይጠራልን?

“ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባላት ፍላጐት ተከታታይ ነህን?

“ከተመደብክበት ቤተሰብ አንዱ ሲዛወር፣ ወዴት እንደተዛወሩ ታውቃለህ? አዲሱ አድራሻቸውን ለማግኘት ጥረት ታደርጋለህ? ከጐረቤቶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው እና ከዘመዶቻቸው አረጋግጠሃል?” (in Conference Report, ሚያዚያ 1983, ገጽ 62–63; ወይም *Ensign*, ግንቦት 1983,ገጽ 45)፡፡

ሙከራ

እያንዳንዱን ወጣት፣ ከጓደኛው ጋር፣ ባንድ ላይ የበለጠ ውጤታማ እና ተፈቃሪ የቤት ለቤት አስተማሪዎች እንዲሆኑ ስምምነቱን ከውጤት ለማድረስ እንዲሰሩ አበረታታ፡፡

# አስርቱ ትዕዛዛት ቤት ለቤት አስተማሪዎች

1. የቤት ለቤት አስተማሪ ለሆናችሁባቸው ለእያንዳንዱ ቤተሰብ የጉብኝት *ቀጠሮ አድርጉ*፡፡
2. ወደ ቤተሰቦቻችሁ የቤት ለቤት ትምህርት ከመውጣታችሁ በፊት *በህብረት ጸልዩ*፡፡
3. ለእያንዳንዱ ቤተሰብ ተስማሚ *መልዕክት አዘጋጁ*፡፡
4. ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ጋር ላላችሁ ቀጠሮ ትክክለኛውን ሰዓት *አክባሪ ሁኑ*፡፡
5. በእያንዳንዱ ጉብኝት ወቀት ቤተሰቦቻችሁ መናገር ስለሚኖሩባቸው ነገሮች ፍላጐት ያላችሁ እና *ተግባቢ* ሁኑ፡፡
6. *ጉብኝቶቻችሁን አጭር* አድርጉ፡፡
7. ከእያንዳንዱ *ቤተሰብ* ጋር ከመለያየታችሁ በፊት *ፀልዩ* (የቤቱ ራስ እንዲህ እንድታደርጉ የሚሻ ከሆነ)፡፡
8. ሌሎች ግንኙነቶችን ወይም ጉብኝቶች አስፈላጊ መሆናቸውን *ካወቀህ ክትትል*አድርግ፡፡
9. *ከቤተሰቡ አባላት የግለሰብን* ልደት እና የተለያዩ በዓላትን *ለማወቀህ* የስልክ ጥሪ አድርግ ወይም የሠላምታ ካርዶች ላክ፡፡
10. ቤተሰቦችህን ልትረዳበት የምትችልባቸውን ድንገተኛ ክስተቶች ወይም ሁኔታዎች በንቃት *ጠብቀ*፡፡

# አራቱ ቤተሰቦች

የ **ስከሚድት** ወላጆች ወጣቶች እና ሦስት ትንንሽ ልጆች ያሏቸው ናቸው፡፡ ወደ ቤተክርስቲያኗ የተመለሱ እና ለተጠየቁት ነገር ሁሉ በጣም ታማኝ የሆኑ ናቸው፡፡ ከልጆቻቸው አንዱ ዘወትር ታማሚ ነው፣ ነገር ግን ስለችግሩ ደስተኞች ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ልጃቸው ዕድሜ ስምንት ዓመት ገደማ ነው፡፡ ስከሚድቶች በደንብ የተማሩ እና በሙዚቃ፣ በግጥም፣ እና በጥሩ የመድረክ ጨዋታዎች ደስተኞች ናቸው፡፡

**የመርዶክ** ቤተሰብ ዕድሚዋ በአስራዎቹ ውስጥ ከሆነች በቤት ከምትኖር ሴት ልጃቸው ጋር ያሉ አረጋዊ ጥንዶች ናቸው፡፡ ሌሎች ልጆቻቸው ሁሉም ያገቡ እና የራሳቸው ትዳር የሏቸው ናቸው፡፡ በአስራዎቹ ውስጥ ያለችው ሴት ልጃቸው ለቤተክርስቲያኗ ፍላጐት ያላት እና በቤተክርስቲያን ስብሰባዎች ላይ መገኘትን ያቋረጠች ነች፡፡ በጣም መጥፎ ከሆኑ ሰዎች የገጠመች እና ለወላጆቿ ትልቀ ጭንቀት ነች፡፡ ትልቁ ፍላጐቷ ለሲኒማ ፊልሞች እና የክብሪት ሣጥኖችን ለመሰብሰብ ነው፡፡

**ጆንሰኖች** ጥሩ ሰዎች ናቸው፣ ነገር ግን ንቁ ተሣታፊ አይደሉም፡፡ የቤት ለቤት አስተማሪዎች ወደ እነርሱ ቤት እንዲመጡ ይፈቅዳሉ፣ ነገር ግን በማናቸውም የቤተክርስቲያኗ ሥራዎች አይሳተፉም፡፡ በቤታቸው ውስጥ በአስራዎቹ የሚገኙ እንዲሁም ደግሞ ከዚህ በጣም የሚያናንሱ ልጆች አሏቸው፡፡ ከነርሱ ማናቸውም ወደ ቤተክርስቲያን አይሄዱም፡፡ በአስራዎቹ ውስጥ ያሉት ልጆች ውጭ ውጭውን በፅኑ የሚመኙ እና በምድረ በዳው ውስጥ ጊዜን ማጥፋት የሚያፈቀሩ ናቸው፡፡

እህት **ሎፔዛ** መልካም፣ የቤተክርስቲያኑ የቀየች አባል ነች፡፡ በየእሁዱ በቤተክርሲያን ለመሄድ በጣም ጠንክራ የምትጥር ነች፣ ነገር ግን ይህ ለርሷ አስቸጋሪ ነው፡፡ እህት ሎፔዛ "አረንጓዴ አውራ ጣት" እና (የአትክልት ሞያተኝነት) ሲኖራት በቤቷ ውስጥ ብዙ የሚያድጉ አትክልቶችና ከቤቷ ውጭ የሚያምር የአትክልት መናፈሻ አላት፡፡ ብቸኛ ነች እናም ሊጐበኟት የሚመጡ የቤት ለቤት አስተማሪዎች እንዲኖሯት ትወዳለች፡፡

# የተቀደሰ የመዋለድ ኃይል

# 45

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ለአካሉ እና ለአምላካዊው የመዋለድ ኃይል ያለውን አድናቆት ያጎለብታል። |

**ዝግጅት**

1. አስፈላጊ የትምህርት መሳሪያዎች፣
   ሀ. አማራጭ፡ ሥዕል 18፣ ቦይድ ኬ ፓከር (64332)፤ ሥዕል 19፣ አንድ ወጣት ወንድ፤ ሥዕል 20፣ ወጣት ጥንድ ከቤተሰብ ጋር፤ ሥዕል 21፣ አካለ መጠን ያልደረሱ የወጣቶች ቡድን፤ ሥዕል 22፣ ወጣት ጥንድ ከበሰተጀርባው ቤተመቀደስ ጋር
   ለ. በአካባቢህ የሚገኝ ከሆነ፣ *ብቸኛው ቁልፍ* የሚባለውን፣ ጥቅልል ፊልም እና የቴፕ ክር።
   ሐ. ጥቅልል ፊልም ማሣያ ፕሮጀክተር፣ የፊልም ማሳያ ነጭ የግድግዳ ልብስ፣ እና የቴፕ ክር ማጫወቻ።
2. ጥቅልል ፊልሙን (ወይም ድርሰቱን) በሚገባ ለመተዋወቅ በሥዕላዊ ሀሳብ አስቀድመህ ተመልከት።
3. ጥቅል ፊልሙ የማይገኝ ከሆነ፣ በትምህርት ውስጥ የሚገኘውን ድርሰት ያነብ ዘንድ በአንተ ዕድሚ ላለው ቡድን ኃላፊ የሆነውን የጳጳስ አማካሪ ጋብዝ። ድርሰቱን ስዕላዊ ለማድረግ የተጠቀሱትን ፊደሎችን ተጠቀም።
4. *ለወጣትነት ማጠንከሪያ* በሚለው መጽሀፍ ገጽ 15 ላይ የሚገኘውን የግብረ ሥጋዊ ንጽህና ምክር ከልስ።

**ለትምህርት ዕድገት የቀረበ ሐሳብ** — **የመዋለድን ኃይል በእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት ተጠቀም**

ጥቅስ

ከፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል ገለፃ የሚከተለውን አንብብ፣

“ምድር ያለ ጋብቻ እና ቤተሰብ ሕይወት ልትቀጥልም ሆነ ልታረጋግጥ አትችልም። ወሲብ ያለጋብቻ፣ ለሰዎች ሁሉ፣ ወጣት ሆነ ሽማግሌ፣ ለጌታ ርኩሰት ነው፣ እናም በጣም የሚያሣዝነው ለነዚህ ታላላቅ እውነቶች ብዙ ሰዎች አይኖቻቸውን ማሳወራቸው ነው” (በ Conference Report, ጥቅምት 1974, ገጽ 9፤ ወይም *Ensign*, ኅዳር 1974, ገጽ 8)።

ማሰላሰያ ጥያቄዎች

- *ንጽሕና* ማለት ለአንተ ምን ማለት ነው?
- ንጽሕና ለምንድን ነው ይህን ያህል አስፈላጊ የሆነው?

ጥቅል ፊልም

*ብቸኛው ቁልፍ* የሚለውን ጥቅል ፊልም አሣይ። ሥራውን የሚያቀላጥፉ መሣሪያዎች የማይገኙ ከሆነ፣ ከጳጳሱ ቢሮ አንድ አባል ድርሰቱን እንዲያነብ በክፍሉ ውስጥ ይገኝ ዘንድ መጋበዙ ይመረጣል። ድርሰቱን ሲያነብ፣ በመምሪያው ጀርባ ላይ የሚገኙትን ሥዕሎች በድርሰቱ ውስጥ በሚጠቀሱ ጊዜ አሳይ።

የጥቅል ፊልም ድርሰት ከሥዕሎች ጋር

“[ቁስ ፓከርን ሥዕል አሣይ።] መልዕክቴ ለእናንተ ጠለቀ ያለ አስፈላጊነት ያለው ነው። የወደፊት ደስታችሁን የሚመለከት ነው። ዓላማው ለእናንተ ታላቅ አስፈላጊነት ሊኖረው ይገባል— በግብረ ገብ ለምን ንጹህ ሆኖ መቆየት አስፈለገን? ትምህርቱን ጥልቀ በሆነ አክብሮት አቀርበዋለሁ።

“በመጀመሪያ፣ ከሟች ሕይወት ቀደም ብሎ፣ ከሰማዩ አብታችን ጋር ተኖሩ ነበር። አምላክ እውን ነው። ሕያው ነው፣ እና ለዚህም ምስክርነቴን እሰጣለሁ።

“እዚያ ያውቃችሁ ነበር። ስለሚወዳችሁ ለደስታችሁ እና ለዘላለማዊው ዕድገታችሁ ጉጉ ነበር። በነፃ መምረጥ እንዲቻላችሁ እና በትክክለኛ ምርጫ ኃይል ውስጥ እንድታድጉ ይፈልግ ነበር፣ ስለዚህም በብዙ ነገር ልክ እንደእርሱ ትሆናላችሁ። ይህንን ለማግኘት ለኛ ከሱ ፊት መልቀቀ አስፈላጊ ነበር። ልክ ወደ ትምህርት ቤት እንደመሄድ ያህል ማለት ነው። እቅዱ ቀርቦ ነበር እናም እያንዳንዳችን የሚችነትን ሕይወት እንድንለማመድ ከሰማዩ አባታችን ፊት ለመልቀቀ ተስማማን።

“ወደ ዓለም ስንመጣ ሁለት ታላላቅ ነገሮች ለኛ በጉተራ ውስጥ ተቀምጠውልን ነበር። አንዱ፣ በእግዚአብሄር አምሣያ የተፈጠረውን፣ ሟች አካል መቀበልን ነው። [የአንድን ወጣት ሥዕል አሣይ።] በዚህ አማካኝነት፣ በተገቢ ቁጥጥር፣ ዘላለማዊ ሕይወት እና ደስታ እናገኛለን። በዚህ ዓይነት መንገድ ሞክረን እና ተፈትነን በጥንካሬ እና በመንፈሣዊ ኃይል ልናድግ እንችላለን።

“ተቀባይነት ባገኘው ዕቀድ መሰረተ፣ የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን በመሆን አዳም እና ሔዋን ወደ ምድር ተላኩ። ለመጀመሪያዎቹ መንፈሶች ከዚህ ሕይወት ጋር እንዲተዋወቁ ሥጋዊ አካላቶች ሊያዘጋጁ ችለዋል።

“በአካሎቻችን ውስጥ ዝግጅት አለ—ይህም የተቀደሰ ነው— የመፍጠር ኃይል፣ ብርሃን፣ እና ለማለት ቢቻል ሌሎች ብርሃኖችን ለማቀጣጠል ኃይል አለው። የተቀደሰ እና አቢይ ኃይል ነው። ይህ ኃይል ጥሩ ነው።

“እናንተ ለአካለመጠን ያልደረሳችሁ ልጆች፣ እንደ ሌሎቹ እያንዳንዱ የአዳም እና ሔዋን ወንድ ልጆች እና ሴት (ልጆች)፣ በውስጣችሁ ይህን ኃይል ይኖራችኋል።

“የመፍጠር ኃይል፣ ወይም የመዋለድ እንበለው፣ ልክ በዕቀዱ ክፍል ውስጥ ያለ የማይረባ ክፍል አይደለም—ለዕቀዱ በጣም አስፈላጊ ነው። ከዚህ ውጪ ዕቀዱ ሊቀጥል አልቻለም። ይህን ያለቦታው መጠቀም ዕቀዱን ያበላሽዋል።

“በዚህ ሕይወት ወደ እናንተ የሚመጡት አብዛኞቹ ደስታዎች በዚህ የተቀደሰ የመፍጠር ኃይል አጠቃቀማችሁ ላይ ይወስናሉ። እናንተ ወጣት ወንዶች አባት መሆን እና እናንተ ወጣት ሴቶች እናት መሆን የመቻላችሁ ሐቀ ለእናንተ አስፈላጊነት ካላቸው ሁሉ አብላጫ ያለው ነው። [ከቤተሰብ ጋር የወጣት ጥንድ ሥዕል አሣይ።] ይህ ኃይል በውስጥህ ማደግ ሲጀምር ጓደኛ ለመፈለግ ያነሣሣሣል እናም [አሁን] ታፈቅራት እና ትይዛት ዘንድ ኃይል ይሰጥሃል።

“እደግመዋለው፣ ሕይወትን በመፍጠር ላይ የሚወለው ይህ ኃይል የተቀደሰ ነው። አንድ ቀን የራሳችሁን የሆነ ቤተሰብ ሊኖራችሁ ይችላል። በዚህ ኃይል ልምድ አማካኝነት ልጆች ከአንተ ጋር አብረውህ እንዲኖሩ ልትጋብዝ ትችላለህ—የራስህ ብቻ የሚሆኑ ትናንሽዬ ወንዶች ልጆች እና ትናንሽዬ ልጃገረዶች—በራስህ አምሣይ፣ የሚፈጠሩትን ማለት ነው። የኃይል እና ተፅዕኖ እንዲሁም የምቹ ጊዜ ሥልጣን እንዲኖርህ፣ ቤት ልትመሰርት ትችላለህ። ይህም ከራሱ ጋር ታላቅ ኃላፊነትን ያመጣል። ይህ የመፍጠር ኃይል ከራሱ ጋር ጠንካራ ፍላጎቶችን እና ግፊቶችን ይዞ ይመጣል። እነሱን ቀድሞውኑ በፍላጎታችሁ እና አስተሳሰባችሁ ለውጦች አማካኝነት ተሰምተውላችኋል።

“[ለአካለ መጠን ያልደረሱትን የወጣት ቡድን ሥዕል አሣይ።] ወደ አስራዎቹ ዕድሜ ስትገፉ፣ የድንገት ያህል አንድ ወንድ ልጅ ወይም ልጃገረድ የሆነች አዲስ ነገር በመሆን በኃይል የሚማርኩ ይሆናሉ። በራስህ እና በሌሎች ሰዎች አካላት ላይ የቀርጽ እና ገፅታ ለውጦችን ትገነዘባለህ። የሥጋ ፍላጐት የመጀመሪያ ሹክሹክታን ትለማመዳለህ።

“ይህ የመፍጠር ኃይል ቢያንስ ሁለት ወርድ እና ስፋት ይኖሩት ዘንድ ያስፈልግ ነበር። አንድ፣ ጠንካራ መሆን፣ እና ሁለት፣ ከሞላ ጎደል ቋሚ መሆን አለበት።

“ይህ ኃይል ጠንካራ መሆን አለበት። ለእነዚህ ስሜቶች አሳማን ከሆነው እምነት በስተቀር፣ ወንዶች ቤትን እና ቤተሰብ የማስተዳደር ኃላፊነት ለመቀበል የዘገዩ ይሁኑ። በቤተሰብ ሕይወት ውስጥ የማጣመሪያ ገመድ ስለሆነ፣ እንዲሁም፣ ይህ ኃይል እንዲሁም ቋሚ መሆን ይገባዋል።

“እንደማስበው፣ በእንስሳት መንግስት ውስጥ እራሳችሁን ለመቃኘት፣ ዕድሚያችሁ ብቁ ነው። ይህ ኃይል ቀፂባዊ ነገር ቢሆን፣ ወቅቱን ጠብቆ ራሱን ቢገልፅ፣ የቤተሰብ ሕይወት እንደማይኖር በቀርቡ ትገነዘባላችሁ።

“በዚህ ኃይል አማካኝነት ነው ሕይወት የሚቀጥለው። በችግር እና ፍርፍሃት እንዲሁም ሀዘን የተሞላችው፣ ዓለም፣ ወደ ደስታ እና ፍስሃ እንዲሁም ተስፋ ልትለወጥ ትችላለች። ልጅ በሚወለድበት በእያንዳንዱ ጊዜ፣ ዓለም በተወሰነ መጠን በየዋህነት ትታደሳለች።

“በድጋሚ ይህ በውስጣችሁ ያለው ኃይል መልካም መሆኑን ልነግራችሁ እወዳለሁ። ከአባታችን እግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነው። በሌላ በምንም ነገር ውስጥ ሳይሆን በዚህ ፃዲቃዊ ተሞክሮ፣ ወደ እርሱ እንጠጋለን።

“የሰማዩ አባታችን እኛን ልጆቹን ሲገዛን፣ እሱ ካለው ከብዙው፣ በትንሽ መንገድ፣ እኛም ሊኖረን ይችላል። የበለጠ ትምህርት ቤት ወይም መፈተኛ ቦታ ሊታሰብ አይችልም።

“[ከበስተጀርባው ቤተመቀደስ ያለበትን የጥንድን ሥዕል አሣይ።] በቤተክርስቲያን ውስጥ እንግዲያስ ከጋብቻ ሌላ በጣም የተቀደሰ እና በጣም አስፈላጊ ድንቅ ነገር ይኖራልን? እነዚህን የመፍጠር ኃይሎች ለራሳችሁ ጥቀም የሚያጐናጽፏችሁ፣ ጋብቻዎቻችሁ ለምን፣ በጣም በጥንቃቄ መታቀድ፣ እና በሕይወታችሁ ውስጥ በጣም በአክብሮት የሚታሰብ እርምጃ መሆን እንደሚገባቸው ልትረዱ ቻላችሁን? ጌታ በቤተመቀደሶች ለጋብቻ ሥነ ሥርዓቶች መፈጸሚያ ዓላማ እንዲገነዘቡ ማዘዙ ያልተለመደ ነው ብለን ማሰብ አለብን?

“አሁን ሌሎች ነገሮች እንደ ማስጠንቀቂያ የምነግራችሁ አሉ። በመጀመሪያ በሰማዩ አባታችን ዕቀድ ላይ ያመጸ አንድ ሰው ከመካከላችን ነበር። ዕቀዱን ለማጥፋት እና ለማበላሸት ተሳለ።

“የሚችነት አካል ከማግኘት ታግዶ ከሰማይም ጣለ— ለዘላለም የራሱን የሆነ መንግስት ከመመስረት ታቀቧል። ሰይጣናዊ ቀናተኛ ሆነ። ይህ የመፍጠር ኃይል ለዕቀዱ አጋጣሚ አለመሆኑን ብቻም ሳይሆን፣ ነገር ግን የዕቀዱ ቁልፍ መሆኑንም ጭምር ያውቃል።

“ይህን ኃይል ያለ እድሜው፣ በጣም ቀደም አድርጋችሁ፣ ወይም በማንኛውም መንገድ ያለ አግባቡ ብትጠቀሙበት በሥነ-ሥርዓት ዘላለማዊ ዕድገታችሁን እንደምታጡ ያውቀዋል።

“ከማይታየው ዓለም የሆነ ገዛዳዊ ፍጥረት ነው። ታላቅ ኃይል አለው። የተቀደሰውን የመፍጠር ኃይል ለምታደግ የተቀመጡትን እነዚያን ሕጐች እንድትተላለፉ አንተን እናንተን ለማሳመን ይህን ኃይል ይጠቀምበታል።

“በቀድሞዎቹ ጊዚያት አንድን ሰው ምግባረ ብልሹ እንዲሆን በገዛድ ግብዣ ፊት ለፊት ለመግጠም ሠይጣን አጅግ ጮሌ ነበር። ይልቅ ግን፣ በማድባትና በፀጥታ ወጣቶችን እና በተመሣሣይ አዋቂዎችን እነዚህን የተቀደሱ የመፍጠር ኃይሎችን አዛብተው እንዲያስቡ ይፈትናል። የተቀደሰ እና ውብ የሆነውን ወደ ልቅ ወይም የተለመደ ደረጃ ዝቅ ለማድረግ ነው።

“ብልሃቶቹ አሁን ተቀይረዋል። እሱ ይህን እንደሚጠገብ የምግብ ፍላጐት ብቻ እየገለጸው ነው። ለዚህ ኃይል አጠቃቀም ሌሎች አጋር ኃላፊነቶች የሉበትም ብሎ ያስተምራል። ደስታ፣ ብቸኛው ዓላማው፣ ነው ብሎ ይነግራችኋል።

“ዲያቢሎሳዊው ግብዣዎቹ በአዳዲስ የቀልድ ቃላቶች እየተፈለሰፉ እና በዘፈን ግጥሞች እየተፃፉ ናቸው። በቴሌቪዥን እና ቲአትሮች ላይ በተውኔት ይቀርባሉ። ከተለያዩ መጽሔቶች በአሁን ጊዜ እናንተ ላይ አፍጥጠዋል።

“እፊታችሁ ላይ በነዚህ የተቀደሱ ኃይሎች ውስጥ ለመዶል ቋሚ ግብዣ ባለበት ማኀበረሰብ ውስጥ አድጋችኋል።

“ለመክራችሁ እወዳለሁ እንዲሁም እነዚህን ቃላት እንድታስታውሱ እፈልጋለሁ። ማንንም ሰው ባጠቃላይ እንዲነካችሁ ወይም አካላታችሁን እንዲይዝ ለማንም! አትፍቀዱ፣ ከዚህ ውጭ የሚነግራችሁን ጥፋቶቻቸውን እንድትካፈሉ እየሰበኳችሁ ነው። ንጽሕናችሁን እንድትንከባከቡት እናስተምራችኋለን።

“በነዚህ ሕይወት ሰጪ በሆኑ ኃይሎች ሙከራ እንድትሰሩ ከሚያሳምናችሁ ራቁ።

“የዚህ የተቀደሰ ኃይል ፃዲቃዊ አጠቃቀም በጋብቻ ቃል ኪዳን ውስጥ ብቻ ነው።

“እነዚህን የተቀደሱ ኃይሎች በፍፁም ያለ አግባብ አትጠቀሙ።

“አሁን፣ ኮስተር ብዬ እና በቁም ነገር አምላክ ግድፈት በሌለው ቋንቋ መከራ እና ሀዘን በንጽህና ሕጐች ላይ ማመጽን እንደሚከተሉ ማስታወቁን ለእናንተ መናገር አለብኝ። ‘ክፋት በፍጹም ደስታ አልነበረም’ (አልማ 41፡10)። እነዚህ ሕጐች አምላክ በእነዚህ ስጦታዎች አጠቃቀም ላይ ልጆቹን ለመምራት ያስቀመጣቸው ነበሩ።

“የሥነ ምግባር ሕጐቹን መስበር ተከትሎ ለሚመጣ ቀጣት እግዚአብሔር በጥላቻ የተሞላ ወይም ተበቃይ ሊባል አይገባውም። ህጐቹ የተመሰረቱት ለእነርሱ ለራሳቸው ነውና።

“በብቁነት የምትኖር ከሆነ የክብር ዘውድ ሽልማት ይጠብቅሃል። የዘውዱን ማጣት ብቻ በቂ ቀጣት ይሆናል። ዘወትር፣ በጣም ሁሌም፣ እራሳችን በፈፀምናቸው ኃጢአቶች ልክ፣ እንቀጣለን።

“ምናልባትም ምራቂ ሣትደርቅ በመተላለፍ ውስጥ ቀድሞውኑ የወደቀ አንዱ ይኖር ይሆናል። ጥቂቶች፣ ከማንኛውም አቀድ ለአብዛኛው ንፁህ የሆኑ፣ ነገር ግን በማባበሎች እና ፈተናዎች ያመኑ፣ ቀድሞውኑ ይህን ኃይል ያለ አግባብ ተጠቀመው ይሆናል። እንግዲያው ታላቅ የመንርደሪያ ኃይል እንዳለ እውቁ። እናም ንፁህ ልትሆኑ እንደምትችሉ እወቁ።

“ከቤተክርስቲያን ውጭ ከሆናችሁ የጥምቀት ቃል ኪዳን እርሱ፣ ከሌሎች ነገሮች ጎን፣ ማጠቢያን እና መንጪያን ይወክላል።

“እናንተ በቤተክርስቲያን ውስጥ ላላችሁት መንገድ አለ፣ ሙሉ በሙሉ ሕመም አልባ ባይሆንም፣ ነገር ግን በእርግጥ የሚቻል ነው። በአምላክ ፊት ንጹህ እና ጉድፍ አልባ ሆናችሁ ልትቆሙ ትችላላችሁ። ጥፋተኝነት ይሄዳል እና እናንተም ሠላም ልትሆኑ ትችላላችሁ። ወደ ጳጳሳችሁ ሂዱ። የዚህን የማንጪያ ኃይል ቁልፎች ይዟል።

“ከዚያም አንድ ቀን የእነዚህን ኃይሎች ሙሉን ፃዲቃዊ መልኮች እና በጻድቃን ቤተሰብ ሕይወት ውስጥ አጋር ደስታዎችንና ፍስሃዎችን ለማወቅ ትችላላችሁ። በጊዜው፣ ለነዚያ የተቀደሱ የፍቀር መግለጫዎች በእነርሱም ፍጻሚ የትውልድ ሕይወት እሱ እራሱ ላለባቸው በጋብቻ ቃል ኪዳን ማሰሪያዎች ውስጥ እራሳችሁን አሳልፋችሁ ልትሰጡ ትችላላችሁ።

“[የቤተሰብ ሥዕልን አሣይ።] አንድ ቀን በክንዶችህ ውስጥ ወንድ ህጻን ልጅ ወይም ሴት ህጻን ልጅ ትታቀፍ እና ከባለቤትህ ጋር ሁለታችሁ ከሰማዩ አባታችን ጋር በሕይወት ፍጥረት በአጋርነት መስራታችሁን ታውቃለህ። ልጁ ያንተ በመሆኑ ምክንያት፣ እራስህን ከምታፈቅረው በላይ ሌላ ሰው ወደ ማፍቀር ተመጣለህ።

“እስካሁን እኔ እስከማውቀው፣ ይህ ተሞክሮ ሊመጣ የሚችለው፣ የራስህ የሆኑ ልጆች በማግኘትህ አማካኝነት ብቻ ወይም ምናልባት ከሌላ የተወለዱ ልጆችን በማደጎ በማሳደግ እና በቤተሰብ ቃል ኪዳን ውስጥ የተጎዳኙ ከሆነ ነው።

“ከእናንተ አንዳንዶቻችሁ የጋብቻ በረከት አሳያችሁ ይሆናል። በምንም ዓይነት ይሁን እነዚህን የተቀደሱ የመፍጠር ኃይሎች ጠብቁ፣ በደንብ የሚጨመርላችሁ ታላቅ የካሳ ኃይል አለላችሁና።

“በዚህም ሌላ ሰውን ከራሳችሁ በላይ በመወደድ እውነተኛ ክርስቲያን ተሆናላችሁ። ከዚያም ጥቂቶች እንደሚያውቁት፣ ከዚያም በቀዱሳን ጽሑፎች ውስጥ አባት የሚለው ቃል ሲነገር ምን ማለት እንደሆነ እናንተም ታውቃላችሁ። የዚያን ጊዜ እሱ ለኛ ስላለው ፍቀር እና አሳቢነት የሆነ ነገር ይሰማችኋል።

“ለእግዚአብሔር ለራሱ፣ ከሁሉም በላይ ከፍተኛው ለሆነው፣ ለእርሱ ሊሰጠው ከተቻለው የአክብሮት እና እንዲሁም የአድናቆት ማዕረጎች ሁሉ፣ በቀላሉ ለባትተብሎ እንዲጠራ የመረጠው ይህ ቃል ትልቅ ትርጉም ሊኖረው ይገባል።

“ሥጦታቸሁን ጠብቁት እናም ተንከባከቡት። እርግጠኛው ደስታቸሁ ለፋፍ ላይ ነው። የዘላለማዊው ቤተሰብ ሕይወት፣ አሁን በተስፋቸሁ እና ሕልሞቻቸሁ ውስጥ ያለው፣ ሊደረስበት ይቻላል ምክንያቱም የሰማዩ አባታችን ከምርጦች ሁሉ ታላቁን ስጦታ በላያቸሁ ላይ አድርጓል—ይህንን የመፍጠር ኃይል። ለደስታ ብቸኛው ቁልፍ ነው። ይህን ስጦታ እንደ ንፁህ እና የተቀደሰ ነገር ያዙት። ጌታ እንደሚያዘው ብቻ ተጠቀሙበት።

“የእግዚአብሔር በረከቶች በእናንተ ላይ እንዲሆኑ እጸልያለሁ። ወደ እርሱ ተቀርቡ ዘንድ በነዚህ የተቀደሱ ስጦታዎች አገላለጽ ላይ ይደግፋቸሁ እናም የሰማዩ አባታችን ይጠብቃቸሁ። እርሱ ሕያው ነው። አባታችን ነው። ይህን ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እመሰክራለሁ። አሜን” (Boyd K. Packer, በ Conference Report, ሚያዚያ 1972, ከገጽ 136–39; ወይም *Ensign*, ሐምሌ 1972, ከገጽ 111–13)።

ውይይት

• ወደዚህ ዓለም ከሚቸ አካሎች ጋር የመምጣታችን ታላቅ ዓላማ ምን ነበር? (ለመፈተን፣ የሰማዩ አባታችን ያዘዘንን ሁሉ እንደምናደርግ ለማሳየት።)

• የተቀደሰውን የመፍጠር ኃይል አምላክ እንዴት እንድንጠቀም ነው ያዘዘን? (በጋብቻ ውስጥ ፍቅርን እንድንገልፅበት እና ልጆች እንዲኖሩን ነው።)

• ይህ የመፍጠር ኃይል ለምንድን ነው ጠንካራ እና ቋሚ መሆን ያለበት? (ወንዶች የቤትና ቤተሰብ የማስተዳደር ኃላፊነቶች ይቀበሉ ዘንድ ነው።)

• ልጃገረዶችን በምታጅብበት ጊዜ ምን ኃላፊነት አለብህ?

• እራስህን በሥጋ ንፅህና መጠበቅ የሚገባህ ለምንድን ነው?

• ወደ ፍትወት ሥጋ ንፅህና መቆሸሽ አንድ ሰው መግባት የሚጀምረው መቼ ነው?

• የመፍጠርን ኃይል አንድ ሰው ያለ አግባብ ቢጠቀምበት እንዴት ሊነጻ ይችላል? (ለጳጳሱ መናዘዝ እና ንስኃ መግባት።)

በቤተመቅደስ የመጣመሪያ ድጋፍ (ፈቃድ) ለማግኘት፣ አንድ ወጣት በጳጳሱ ወይም ቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ እና ከስቴክ አመራር በአንዱ አባል ለሚጠቀመው በርካታ ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት ብቁነቱን ማረጋገጥ እንዳለበት ግለፅ። ከነዚህ ጥያቄዎች አንዱ በተለየ ሁኔታ በንፅህና ላይ ያተኩራል እናም እንደሚከተለው ይነበባል፣ “አግባብ ባላቸው የክህነት ባለሥልጣናት ባልተፈታ ከንፅሕና ሕግ ጋር በተያያዘ መተላለፍ እስከዛሬ ተሳትፈህ ታውቃለህን?”

---

**እራሱን የሚያከብር እሱ ራሱንና ቤተሰቡን የሚባርክ የእግዚብሔር ልጅ ነው።**

ውይይት

• ንፁህ በመሆን እራሱን ለሚያከብር ወጣት ወንድ ምን በረከቶች ይመጡለታል?

• የጌታን የንጽሕና ሕግ አንተ በመኖርህ ቤተሰቦቸህ እንዴት ይባረካሉ?

ወደ ፊት አንድ ቀን፣ ከወጣት ወንዶቹ እያንዳንዱ ሚስት የመምረጥ እና የራሱን ቤተሰብ የመጀመር ዕድል እንዳለው ግለፅ። እያንዳንዱ የወደፊት ልጁ እና የልጅ ልጁ ከእርሱ ሙሉ አካል፣ ንፁህ አዕምሮ፣ እና ያካበተ መንፈሳዊ ውርስ ሊወርሱ መብት አላቸው። ልጆቹ፣ “እኔ ንጹህ ነኝ ምክንያቱም ጌታ እንደዚህ እንድሆን አዞኛልና ደግሞም እናት እና አባቴ በዚያ መንገድ ኖረዋልና። አካሌ ቤተ መቀደስ ነው፣ ይህን ቤተ መቀደስ በንጽሕና እጠብቀዋለሁ” ማለት መቻል ይኖርባቸዋል። እንደዚህ ያለውን ቤተሰብ ባህል በመመስረቱ፣ ጠንካራ እምነቶቹን ለዘር ዘሩ ያስተላልፋል።

የንፅህና ሕግ፣ እንደ እግዚአብሄር ሌሎች ሕጐች፣ ደስታን ለማምጣት መሰጠቱን እንደገና አረጋግጥ። ወሲብ በዚያ መንገድ በተገቢው ጋብቻ በተጠበቀ ጊዜ የተቀደሰ እና ውብ ነው።

---

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት እና ሙከራ

የንፅሕና ጥቀም እና በረከት አስመልክተህ በምስክርነትህ አጠቃል። ለወጣቶች ጥንካሬ በሚለው መጽሐፍ ከገጽ 11 እስከ 16 ያለውን የግብረ ሥጋዊ ንፅሕና ምክር ከልስ። በሁሉም ጊዜ የንጽህናን ሕግ ወጣት ወንዶቹ እንዲታዘዙ ምከር።

# ውሳኔ ማድረግ

# 46

**ዓላማው**

እያንዳንዱ ወጣት ትክክለኛውን ለመማር ጥረት በማድረግ፣ ብቃቱ ካላቸው ከሌሎች ሰዎች ምክርን በመሻት፣ እና የውሣኔውን ትክክለኛነት ማረጋገጫ ጌታን በመጠየቅ ትክክለኛ ውሣኔዎችን ማድረግ እንደሚችል ይገነዘባል።

ዝግጅት

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ ወረቀት እና እርሳስ።
2. ሁለት የተለያዩ መጠን ያላቸውን ጥቅሎችን ጠቅልል። አንዱን በጥንቃቄ እና ሌላኛውን ያለጥንቃቄ ጠቅልል። ትንሽ አሻንጉሊት ወይም ከረሜላ በእያንዳንዱ ውስጥ አስቀምጥ።

ለአስተማሪው ማስታወሻ

በየዕለቱ ለህይወታችን ውሳኔዎችን እናደርጋለን። አንዳንድ ውሣኔዎች ባለትንሽ ውጤት ሲሆኑ፣ አብዛኛዎቹ ግን የሕይወታችንን አቀጣጫ እና የደስታችንን ደረጃ ይወስናሉ።

ውሳኔዎችን በተለያዩ መንገዶች እንወስናለን። ይህ ትምህርት ትክክለኛ ውሣኔዎችን ለመወሰን አንዳንድ መሠረታዊ መመሪያዎችን ይሰጣል። ወጣት ወንዶቹ ውሣኔ እንዴት እንደሚሰጡ እና ሲያደርጉትም ጌታን እንዲያሳትፉ መማር አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋቸዋል።

**ለትምሕርቱ እድገት የቀረበ ሐሳብ**

**መግቢያ**

በቁሳዊ ነገሮች ላይ የተደገፈ ትምሕርት

ለወጣት ወንዶቹ ቀደም ሲል የጠቀለልከውን ሁለት ጥቅሎች አሣያቸው። ከወጣት ወንዶቹ አንደኛውን ወደ ክፍሉ ፊት ለፊት እንዲመጣ አድርግ። ከሁለት ጥቅሎች በሚመረጠው ውስጥ ያለው ዕቃ የእርሱ እንደሚሆን ንገረው። አንድ ጊዜ ምርጫውን ሲመርጥ፣ የምርጫውን ምክንያቶች ከእርሱ ጋር ተወያይ።

ውሳኔ መወሰን በየእለቱ ቀድሚያ ልንሰጠው የሚገባ ነገር መሆኑን አመልክት። ውሳኔን መወሰን እና እንዴት በትክክለኛው እንደሚደረግ መማር አስፈላጊ ነው።

የማሳላሰያ ጥያቄዎች

ወጣት ወንዶቹ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዲመረምሩ ጠይቅ፣

- መወሰን ውሣኔ የመወሰን ያህል የማይሆነው ለምንድን ነው?
- አንድ ሰው ውሣኔዎችን ለመወሰን እርዳታን ከየት ሊያገኝ ይችላል?
- አንድ ሰው አንድ ውሣኔ ትክክል መሆኑን አስቀድሞ እንዴት ሊያውቅ ይችላል?

**ውሣኔ መወሰን ግላዊ ጥረትን ይጠይቃል**

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

በመጽሐፈ ሞርሞን ትርጉም ወቅት፣ ኦሊቨር ካውድሪ ለመተርጎም ፈልጎ ሞክሮ እንዳልተሳካለት ግለጽ።

- ኦሊቨር ካውድሪ ለመተርጎም ያልቻለው ለምንድን ነው?

ለመልሶቹ ወጣት ወንዶቹ ትምህርት እና ቃል ኪዳን 9፥7–9 እንዲያነቡ አድርግ።

- በግልፅ፣ ከጌታ እርዳታ ለማግኘት፣ ኦሊቨር ካውድሪ ምን አደረገ? (በቁጥር 7 መሠረት፣ ጌታን ብቻ ነው የጠየቀው።)
- ኦሊቨር ማድረግ የነበረበትን ጌታ ምን ብሎ ይናገራል? (የሚተረጉመውን በአዕምሮ ውስጥ ማጥናት፣ እና ከዚያም ትርጉሙ ትክክል እንደነበር መጠየቅ ይገባው እንደ ነበር ነው።)
- ከዚህ ተሞክሮ ውሣኔዎችን ስለመወሰን ምን ልንማር እንችላለን? (አማራጭ ውሣኔዎችን ማጥናት፣ ውሣኔ መወሰን፣ እንዲሁም ውሣኔውን ልክ መሆኑን መጸለይ እና መጠየቅ።)
- ውሣኔዎችን ለመወሰን እርሱን ብቻ ከመጠየቅ ይልቅ የሚቻለንን እንድናደርግ ጌታ የሚፈልገው ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ? (የሰማዩ አባታችን ማሰብ እንድንማር እና ለራሳችን እንድናውቅ ይፈልጋል።)

ጥቁር ሠሌዳ

በጥቁር ሠሌዳው ላይ የሚከተሉትን ፃፍ፣

ውሳኔ ማድረግ
የግል ጥረት ያስፈልገዋል፡፡
የያሬድ ወንድም ውሣኔ ይወስናል።

**የቅዱስ መጽሐፍ ታሪክ**

ጌታ ለያሬድ ወንድም ሕዝቦቹን በውቅያኖስ ላይ ለማጓጓዝ ስምንት ታንኳ እንዴት እንደሚሠራ ነገረው፣ ነገር ግን ለታንኳዎ ውስጠኛ ክፍሎች እንዴት ብርሃን እንደሚያበጅላቸው እንዳላብራራላቸው ግለፅ፡፡ አንድ ወጣት ኢተር 2፡22 እንዲያነብ አድርግ፡፡

• ጌታ ምላሽ የሠጠው እንዴት ነው?

ኢተር 2፡23 አንብብ፡፡

ወጣቶቹን የጌታን ምላሽ በራሳቸው ቃላት እንዲገልፁ ጠይቅ፡፡ ለታንኳዎቹ ብርሃን ለማበጀት እንዲወስን ጌታ በቀጥታ ኃላፊነቱን በያሬድ ወንድም ላይ ማስቀመጡን ይገነዘቡ ዘንድ እርዳቸው፡፡ በራሱ ሊሆኑ በሚችሉ መፍትሄዎች ጋር ብቀ እንዲል ጌታ ፈልጓዋል፡፡

የያሬድ ወንድም ምን እንዳደረገ ለማወቀ፣ አንድ ወጣት ኢተር 3፡1–4 እንዲያነብ አድርግ፡፡

አንድ ወይም ሁለት ወጣት ወንዶች የያሬድ ወንድም ምን እንዳደረገ በራሳቸው ቃላት እንዲናገሩ አድርግ፡፡

**ምሳሌያዊ ጥናት**

ለእያንዳንዱ ወጣት ቁራጭ ወረቀት ሥጥ፡፡ እያንዳንዱ ወጣት ወረቀቱን እኩል ቦታ ከመኃሉ ተነስቶ ቁልቁል መስመር በማስመር እንዲከፍል አድርግ፣ ከዚያም *አዎንታዊ* የሚለውን ቃል ከአናቱ ላይ በቀኝ በኩል፣ እና *አሉታዊ* የሚለውን ቃል ከአናቱ ላይ በግራ በኩል እንዲጽፍ አድርግ፡፡ በማንኛውም ውሣኔ *"አዎንታዊ"* ብለን የምናስባቸው— አንድን ነገር የማድረግ ምክንያቶች— እና *"የአሉታዊ"*— የአንድን ነገር ለማድረግ የሚሰጡ *ተቃራኒ* ምክንያቶች መሆኑን ግለፅ፡፡

የሚከተለውን ምሳሌያዊ ጥናት መርምር፡፡

ሻውን የአስራ አምስት ዓመት ልጅ እና በትምህርቱም ጎበዝ ነው። በስፖርት፣ ማለትም በተመልካችነት እና በተሳታፊነት፣ ፍላጎት ያደረበት ነው። ለሁለቱ የተለያየ የትርፍ ጊዜ ስራዎች እድል አለው። ከእነርሱ አንዱን ብቻ መምረጥ ይቻላል። የመጀመሪያው ሥራ በየዕለቱ ከትምህርት በኋላ ከሁለት እስከ ሶስት ሰዓት እንዲሰራ ይጠይቀዋል። ሊላኛው ሥራ አርብ እና ቀዳሚ ከአስራ ሁለት ሰአት እስከ እኩል ሌሊት እንዲሰራ ይጠይቀዋል። ሻውንን ብተሆኑ ኖሮ፣ ለእያንዳንዱ ሥራ የመወሰኛ ቁራጭ ወረቀትን በመጠቀም እናም ልታስቡአቸው የምትችሉትን ድጋፎች እና ተቃውሞዎች ሁሉ መጻፍ ትችሉ ነበር። ክፍሉን በሁለት ክፈል። ከወጣት ወንዶች ግማሹን የመጀመሪያውን ሥራ እንዲመረምሩ ድጋፎች እና ተቃውሞዎች እንዲጽፉ አድርግ። ሌላውን የክፍሉን ግማሽ ሌላኛውን ሥራ ከድጋፎች እና ተቃውሞዎች ጋር እንዲመረምሩ አድርግ። ለዚህ መልመጃ በግምት አምስት ደቂቃ ፍቀድ፣ ከዚያም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያይ፣

• አንድ ሰው በተሳካ ሁኔታ ለሌላ ሰው የውሣኔ ወረቀቱን ሊሠራለት ይችላል? ለምን?

• ከትምህርት በኋላ ላለው ሥራ ሻውን ሊያስብበት የሚፈልጋቸው አንዳንድ "አዎንታዊ" እና "አጹታዊ" ምክንያቶች የተኞቹ ናቸው?

• በሣምንቶች ማብቂያ ላይ ላለው ሥራ ሻውን ሊያስብበት የሚፈልጋቸው አንዳንድ "አዎንታ" እና "አሉታ" የተኞቹ ናቸው?

• ሻውን እሁድ ዕለት የመስራት ዕድል ቢኖረው እና የውሣኔ ወረቀቱን የሚሰራ ቢሆን ኖሮ፣ ውሣኔ ለማድረግ ምን ዓይነት ምክንያት ሊጤን ይገባዋል? (የሰንበት ቀንን በቅድስና መጠበቅ፡፡)

• የውሳኔው ወረቀት እንዴት ሊረዳችሁ ይችላል? ("አዎንታ" እና "አሉታ" ፊት ለፊታችሁ ማየት ትችላላችሁ፡፡)

---

### ብቃቱ ካላቸው ምክር መፈለግ ብልህነት ነው

**ምሳሌያዊ ጥናት**

የሚከተለውን ምሳሌያዊ ጥናት ለወጣት ወንዶቹ አቀርብ፣

ትንሽዬ ልጅ ሳለ ጀምሮ፣ ቶም ለወንጌላዊነት እንዲሄድ ሲበረታታ ነበር። አሁን ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመርቋል እናም ጥሩ ደሞዝ ያገኛል ለወንጌላዊነት ለመሄድ መፈለጉ ግን በደንብ እርግጠኛ አልነበረም። በወንጌላዊነት ማገልገል ረጅም ጊዜ መስሎ ታየው። ቤተሰቡን እና ጓደኞቹን ሊለይ ሆነ። ጳጳሱ እንዲሄድ ሲጠይቀው፣ ውሣኔ ለማድረግ ቶም ጥቂት ቀናትን ጠየቀ። ወደ ቤቱ ሄደና በችግሩ ላይ አሰበበት። ከሴት ጓደኛው እና ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር ተነጋገረ። የሴት ጓደኛው እሱ ከሄደ ተመልሶ ሲመጣ ለመጠበቅ ዋስትና እንደማትሰጠው ተናገረችው። ጓደኞቹም ገንዘብ ከማጠራቀም ይልቅ ያን ያህል ገንዘብ ማጥፋት አብድ ቢሆን ሲሉ አሰቡ። አለቃውም ለቶም በሚመለስበት ጊዜ ለሥራው ዋስትና ለመስጠት እንደማይችል ነገረው። በሚቀጥለው ቀን ቶም ለጳጳሱ ለወንጌላዊነት ላለመሄድ መወሰኑን ነገረው።

• ውሳኔውን ለመወሰን ቶም እርዳታ የጠየቃቸው ሰዎች ምን ያህል ብቁ ናቸው? (ለእነርሱ የቶም ውሣኔ በግል ምን ማለት እንደሆነ— ምናልባት ራስ ወዳድ በሆነ መንገድ አይተውት ነበር።)

• ቶም ምክር መጠየቅ ይገባው የነበሩ ሌሎች ሰዎች የትኞቹ ናቸው? (ወላጆቹን፣ ጳጳሱን፣ እምነት የሚጣልባቸው ዘመዶቹን፣ ሰማያዊ አባቱን።)

አሁን ታሪኩን አጠቃል።

ለበርካታ ወራት ሥራውን ከሠራ በኋላ፣ ቶም አለመረጋጋት እና ሀዘን ተሰማው። በአንዳንድ አዲስ ጓደኞች ግብዣ አማካኝነት፣ በቋሚነት የበለጠ ቤተክርስቲያን ውስጥ መሳተፍ ጀመረ። ከጳጳሱ ጋር ባደረጋቸው በርካታ ጭውውቶች ተደሰተ እናም በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ መደበኛነት የመጽሐፈ ሞርሞን ንባብ ጀመረ። ከበፊቱ ይልቅ ጠንክሮ ጸለየ። በርካታ ምሽቶችን ከወላጆቹ ጋር ስለወንጌላዊ ሥራ በመነጋገር አጠፋ። ቀስ በቀስ በወንጌላዊነት ለማገልገል ፍላጐት ተሞላ። አንድ ቀን ጳጳሱን ጠራውና "ለወንጌላዊነት ለመሔድ በጣም ዘግይቶብኛልን ሲል ጠየቀው?"

• ቶም ውሳኔውን ለመወሰን ምን ጥሩ ነገሮችን አደረገ? (ቅዱሳን መጽሀፍትን አነበበና ከጳጳሱ፣ ከወላጆቹ፣ እና ከጌታ ጋር ተነጋገረ።)

በጥቁር ሰሌዳ ላይ *ብቃት ያላቸውን ሌሎች ሰዎች አማክር* ብለህ ፃፍ፣

---

**ውሳኔዎችን ስንወስን ጌታን እናሳትፍ**

**የጥቁር ሰሌዳ ክለሳ**

የሚከተለውን በጥቁር ሰሌዳው ላይ አክልበት፣ *ውሣኔዎችን ስትወስን ጌታን አሣትፍ።*

**ቅዱሳን መጽሐፍት እና ውይይት**

ጌታ በተለየ ሁኔታ ምን ማድረግ እንዳለብን የሚነግረን ጊዜያቶች እንዳሉ ግለፅ።

ወጣት ወንዶቹ ሊተር 2፡19–20 እንዲያነቡ እና እንዲወያዩ አድርግ።

በትምህርቱ ውስጥ ቀደም ብለን እንደተወያየንበት፣ ጌታ ውሣኔዎቻችንን በራሳችን እንድንጨርስ የሚጠብቅበት ሌሎች ጊዜያቶች እንዳሉ ወጣት ወንዶቹን አስታውሳቸው (ት እና ቃ 58፡26–27 ደግሞ ተመልከት)።

• አንዴ ችግሩን ካጠናነው እና የበለጠ መስሎ የተሰማንን ከወሰንን፣ ጌታን በውሣኔ አሠጣጣችን ውስጥ እንዴት እናሳትፈዋለን? (ምርጫ ካደረግን በኋላ፣ ውሣኔያችን ትክክል ለመሆኑ ጌታን በጸሎት እንቀርበውና እንጠይቀዋለን። ውሣኔው ትክክል ከሆነ፣ መንፈስ ቅዱስ ሰላምን በመስጠት፣ ውሣኔያችንን ትክክል ስለመሆኑ የማረጋገጫ ስሚትን ለእኛ በመስጠት ውሣኔውን ያረጋግጥልናል።)

ትምህርት እና ቃል ኪዳን 6፡22–23 እና ትምህርት እና ቃል ኪዳን 9፡8 አንብብ።

በተወሰኑ ምክንያቶች በትክክል ካልመረጥን፣ ጌታ ስሚታችንን በመረበሽ እና ኃይለኛ ጥርጣሬ ውስጥ በመተው ውሣኔያችን ስህተት መሆኑን እንደሚገልጽልን ተስፋ እንደሰጠን ግለጽ። ቅዱሳን መጽሐፍት ይህን እንደ "አስተሳሰብ መሳት" ይገልፀዋል። ይህ በተከሰተ ጊዜ፣ ውሳኔ የመወሰኑን ሂደት እንደገና መጀመር ይገባናል።

ትምህርት እና ቃል ኪዳን 9፡9 አንብብ።

**ጥቅስ እና ውይይት**

• ትክክለኛ ውሣኔ ለመወሰን የሚፈለጉብንን ነገሮች ካደረግን እና በአንድ መንገድ ወይም በሌላ ቁርጥ ያለ የስሚት ምልክት ካልተቀበልን ምን ማድረግ ይኖርብናል?

ፕሬዚዳንት ማርዮን ጂ ሮምኒይ እንዳሉት፣ "መፍትሂ ላገኝላቸው የማልችል የሚመስሉ ችግሮች ነበሩኝ፣ እና መፍትሔ እስካላገኘሁላቸው ወደ ፊት ፈቀቅ ለማለት የማልችል እስከመሰለኝ ጊዜ ድረስ ችግሮቹን ፊት ለፊት ለመግጠም ተቸገርኩ። ከጸሎት እና በብዙ አጋጣሚዎች ላይ ለረጅም ጊዜ በእያንዳንዱ ሣምንት አንድ ሙሉ ቀን በመጾም፣ ለአዕምሮዬ የተገለፁ መልሶች ሊኖሩኝ ቻሉ" (*Look to God and Live: Discourses of Marion G. Romney,* comp. George J. Romney [ሶልት ሌክ ከተማ፡ Deseret Book Co., 1971], ገጽ 45)።

• ፕሬዚዳንት ሮምኒይ እንዳመለከቱት ሁሉንም ብናደርግ እና አሁንም ምንም ማረጋገጫ ባይሰማንስ?

“ከባድ ችግሮችን ለመፍታት በወቀቱ መጾም እንዲሁም ማጥናት እና መጸለይ ይገባናል፡፡ አልፎ አልፎ፣ ብናጠናም ብንጸልይም ብንፆም፣ ብንወስንም፣ በውሣኔው መሰረትም ስንሰራ፣ አሁንም ማረጋገጫ ማግኘት አንችልም ይሆናል፡፡ እንደዚያን ባለ ወቀት፣ በቀላሉ ብልጫ ያለውን የራሳችንን ፍርድ መከተል፣ አንድ ቀን ማረጋገጫው እንደሚመጣ በትዕግስት እምነትን መለማመድ አለብን፡፡ እግዚአብሔር በራሱ በፍርድ፣ መልስ እኛ እንድናገኝ መልካም በሆነልን ጊዜ፣ ጸሎቶቻችንን እንደሚመልስልን ዘወትር ማስታወስ ይገባናል (Duties and Blessings of the Priesthood, Part B, (የክህነት ሥልጣን ተግባር እና ቡራኬዎች ክፍል ለገጽ 190)፡፡

---

**ማጠቃለያ**

አቀራረብ

እኛ የሰማዩ አባታችን ልጆች እንደሆንን፣ እና እርሱ ወደ ምድር የላከን እንድናድግ እና እንድንሻሻል መሆኑን አስረዳ። ጥሩ ውሣኔዎችን ለመወሰን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እምነት ሊኖረን እና የመንፈስ ቅዱስ ጓደኛነትን ለማግኘት በብቁነት መኖር አለብን፡፡ ውሣኔዎቻችንን ተግባራዊ እናደርግ ዘንድ በራሳችንም ላይ እምነት ሊኖረን ይገባል፡፡ ይህ ጥንካሬ እና ቁርጠኛ ውሣኔ ይፈልጋል፡፡

ገለፃዎቹን በአጭሩ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከልስ፡፡

ውሳኔን ስትወስን ጌታ በረዳህ ጊዜ የነበረህን ተሞክሮ ልታካፍላቸው ትፈልግ ይሆናል፡፡

ሙከራ

በሚመጣው ሳምንት ውስጥ ውሳኔ ሊያደርጉበት የሚገባ ቢያንስ አንድ ውሣኔ እንዲመርጡ እና በትምህርት ውስጥ የተማሯቸውን ሐሳቦች እንዲተገብሩ ወጣት ወንዶቹን ምከር፡፡ በሚያጤኑበት ጊዜ የውሣኔ ወረቀት እንዲጠቀሙ፣ የግል ጥረት እንዲያደርጉ፣ ብቃት ያላቸውን ሰዎች እንዲያማክሩ፣ እና ጌታን ለእርዳታ እና ማረጋገጫ እንዲጠይቁ አበረታታቸው፡፡

# መለየት እና መስዋእትነት

# 47

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ወንድ የመስዋዕትነት እና መቀደስ ሕጐች በመጠበቅ የሚመጣውን መንፈሣዊ እድገት ይሻል። |
| **ዝግጅት** | 1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች፣<br>ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።<br>ለ. ጥቅሶችን ምልክት ማድረጊያ እርሳሶች።<br>2. (አማራጭ) ለእያንዳዱ ወጣት በላዩ ላይ "ሁለንተናችሁ እና ያላችሁን ሁሉ ለእርሱ መልሳችሁ ለመክፈል እናንተ ለሰማዩ አባታችሁ በዘለዓማዊነት ውለታው ያለባችሁ ናችሁ፣" ብለህ የፃፍክበትን ማራኪ ካርድ አዘጋጅ።" (ሞዛያ 2፥34)።<br>3. 3ኛኔፊ 9፥19–20 እና ሙሴ 5፥6–8 በጸሎት አጥና። |

**ለትምህርት እድገት የቀረበ ሐሳብ**

**መስዋእትነት እና መለየት ሠለስቲያዊ ሕጐች ናቸው**

ውይይት

በጥቁር ሰሌዳው ላይ *መስዋዕትነት* የሚለውን ቃል ፃፍ።

- *መስዋዕትነት* ምን ማለት ነው?
- መስዋዕትነትን መማር ለምን አስፈለገ?
- መቀደስ ምን ማለት ይመስላችኋል? (መቀደስ፣ መሰዋት ወይም አሳልፎ መስጠት።)

የመቀደስ እና መስዋዕትነት ሕጐች ዘላለማዊ እንደሆኑ እና ምድር ከመፈጠሯ በፊት ከጌታ ለሰው መስጠታቸውን አስረዳ።

ጥቅስ

ስለ እነዚህ ሕጐች የቁስ ብሩስ አር ማካንኪን መግለጫ አንብብ፣

"መስዋዕትነት እና መቀደስ ሣይነጣጠሉ የተሳሰሩ ናቸው። የመቀደስ ሕግ፣ የጌታን ፈቃድ በምድር ላይ ለማስፋፋት በሚያስፈልጉት ያህል መጠን እንዲገኙ ጊዜያችንን፣ ችሎታዎቻችንን፣ እንዲሁም ገንዘባችንን እና ንብረታችንን ለጌታ የምንቀድሰው ነው።

"የመስዋዕትነት ሕግ ለእውነት ስንል ሁሉንም ጸባያችንን እና ዝናችን፣ ክብራችን ሙገሳችን ፣ በሰዎች መካከል መልካም ስማችን፣ ቤቶቻችን፣ መሬቶቻችን፣ እና ቤተሰቦቻችን፣ ሁሉን ነገሮች፣ አስፈላጊም ከሆነ ብቸኛ ነፍሣችን እንኳ ብትሆን ለመሰዋት ፈቃደኛ መሆናችን ነው" (በ Conference Report, ሚያዝያ 1975, ገጽ 74; ወይም *Ensign*, ግንቦት 1975, ገጽ 50)።

የሰማዩ አባታችንን መንግስተ በምድር ለመገንባት ፍላጐቶቻችን፣ ኃይላችንን፣ ጊዜአችንን፣ ወይም ቁሳዊ ዕቃዎችን ለመስዋት ፈቃደኛ መሆን እንዳለብን አስረዳ። በጊዜው እነዚህን ህጐች መጠበቅ አስቸጋሪ ይመስላል። ይሁንና፣ ግንዛቤያችን እና እምነታችን በጨመረ ቁጥር፣ ከታዛዥነት የሚገኙትን አስደናቂ በረከቶችን መገንዘብ እንጀምራለን።

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

- የመስዋእትነት ሕግ መጀመሪያ የተሠጠው ለማን ነበር?

እነዚህ ሕጐች ለአዳም በአንድ መላእክ እንደተገለጸለት አስረዳ። አዳምና ሔዋን ከኤደን ገነት ከተባረሩ በኋላ፣ ከመንጋዎቻቸው ውስጥ በኲሩን ለእሱ መስዋዕት ማድረግ እንደሚገባቸው ጌታ አዟቸዋል። አዳም ይህን ህግ ጠብቋል።

አንድ ሰው ሙሴ 5፥6–8 እንዲያነብ አድርግ።

ከኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለት እና ትንሣኤ በኋላ፣ የሙሴ ህግ ስለተፈጸመ ሰዎች የእንስሣት መስዋዕቶች ማቅረብን ተው።

አንድ ወጣት 3ኛኔፊ 9፥19–20 ጮክ ብሎ እንዲያነብ አድርግ። ወጣቶች ቁልፍ ቃላቶችን እንዲያሰምሩባቸው ሐሳብ አቀርብ።

- ምን ዓይነት መስዋእት ነው ማቅረብ የሚገባንን? (የተሰበረ ልብ እና በጸጸት የተሞላ መንፈስ።)

• ለጌታ “የተሰበረ ልብ እና በጸጸት የተሞላ መንፈስ” ማቅረብ ማለት ምን ማለት ነው? (የ“ተሰበረ ልብ” ማለት ጌታ ለኛ ብሎ በተሰቃየልን ሥቃይ ላይ እና በስህተት ሥራዎቻችን ላይ ልባችን በሐዘን ተሰብሮ ንስኃን እስክንሻ ሀዘን ሲሰማን ነው። “በጸጸት የተሞላ መንፈስ” የተፀፀተች መንፈስ፣ ንስኃ ለመግባት የሚፈልግ ሰው ማለት ነው።

• እንደነዚህ ዓይነት ስሜቶች ኖረዋችሁ ያውቃልን?

**ጥቀስ እና ውይይት**

ነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ ሲያስተምር፣ “የሁሉንም ነገር መስዋዕትነት የማተጠይቀ ኃይማኖት ወደ ሕይወት እና ደህንነት [ለመምራት] የሚያስፈልገውን እምነት የሚያመነጨውን በቂ ኃይል በፍፁም አይኖራትም። በዚህ መስዋዕትነት አማካኝነት፣ እናም በዚህ ብቻ፣ እግዚአብሔር ሰዎች በዘላለም ሕይወት ለመደሰት ይገባቸው ዘንድ አዟል” (*Lectures on Faith* 6፥7)

የመስዋእትነት እና የመቀደስ ሕጐች የሰማያዊ ሕጐች መሆናቸውን አስረዳ። ሰማያዊ ክብርን የምንፈልግ ከሆነ፣ እነዚህን ሕጐች መጠበቅ አለብን።

• እነዚህን ሕጐች ለመጠበቅ የምንችልባቸው አንዳንድ መንገዶች የትኞቹ ናቸው? (መንግስቱን ለመገንባት ጊዜያችንን፣ ፍቀራችንን፣ ችሎታዎቻችንን፣ እና ዓለማዊ ሐብቶቻችንን በመስጠት ነው።)

---

**መስዋዕትነት እና መቀደስ ፍስሃ እና በረከት ያመጡልናል**

**ታሪክ እና ውይይት**

በፕሮቮ፣ ዩታህ ውስጥ የቀድሞ የወንጌላዊያን ማሰልጠኛ ማዕከል ፕሬዚዳንት በነበሩበት የተነገረውንየሚከተለውን ታሪክ አንብብ፣

“አንድ ወጣት በጃፓን ውስጥ ለማገልገል—በወንጌላዊያን ማሠልጠኛ ማዕከሉ ውስጥ እየተዘጋጀ ነበር። በመጨረሻው የሀገር ቤት እግር ኳስ ጨዋታ ላይ ወንጌላዊያኑ ሁሉ እንዲገኙ ከቢ. ዋይ. ዩ. ቲኬት ቢሮ ጋር ቀደም ብለን ተዘጋጀን። በሰሚን መጨረሻ ቀጠና ውስጥ ለኛ የተዘጋጁ ሁሉም ትኬቶች ነበሯቸው . . .እና እኛም ወንጌላዊያኑ ሁሉ በሚቀጥለው ቀትር በኋላ ወደ እግር ኳስ ጨዋታው ለመሔድ እንደተፈቀደላቸው አስታወቅን። ይህ ወጣት ልጅ ሊያነጋግረኝ ገባና፣ “ፕሬዝዳንት ፓይንግ፣ ነገ ወደ እግር ኳስ ጨዋታው መሄድ ይኖርብናልን? ሲል ጠየቀኝ?”

“ታሚል ብዬ አሰብኩ። ‘ይህን ኳስ ጨዋታ ማየት አልፈለክምን?’ አልኩት።

“ኦ፣ ይህን ጨዋታ ክፉኛ ማየት መፈለጌን ብቻ እንዴት ባወክልኝ! ለሁለት ዓመታት የኮሌጅ እግር ኳስ ተጫውቻለሁ። ነገር ግን ወደ ወንጌላዊያን ማሰልጠኛ ማዕከል ስመጣ ለራሴ እና ለጌታ ስምንቱንም የሚሲዮናዊ ውይይት በጃፓንኛ ለመማር ቃል ገብቼያለሁ። ነገ ወደ ኳስ ጨዋታው ከሔድኩ፣ ግቤን አልቀዳጅም’ አለ።

“አዎ፣ በእርግጥ፣ ለእርሱ እዚያው እንዲቀይ እና እንዲያጠና ፍቃድ ተሠጠው።

“ከጥቂት ሣምንታት በኋላ አየሁት። በትክክል፣ ወደ መስክ ከመሔዱ ከአምስት ቀናት በፊት ነበር። በካፍቴሪያው ውስጥ ወደ ነበርኩበት መጣና፣ ‘ፕሬዝዳንት ፓይንገር፣ አስታወስከኝ? እኔ ውይይቶቹን ለማጥናት በመፈለጊ ምክንያት ወደ ኳስ ጨዋታው ያልሄድኩት ቄስ ነኝ። ዛሬ ስምንቱንም ውይይቶች አጠናቀቀሁ’ አለ። እንዲህ ሲል ቀጠለ፣ ‘ወደ ኳስ ጨዋታው ባልሄኩበትና እዚህ በቀየሁበት ግዜ በኔ ላይ ምን እንደተከሰተ መስማት አለብህ። እስከዚያን ጊዜ ድረስ በቀን በጃፓንኛ በቃሌ መያዝ የቻልኩት ዛያ መስመሮች ብቻ ነበር፤ ያን ቀን፣ መስዋዕትን የሰዋሁበትን ቀን— እና መስዋዕት እንደሆነ የሚሰማኝ ዕለት—120 መስመሮችን በቃሌ ሸመደድኩኝ። ከዚያን ጊዜ አንስቶ፣ ወደ ፊት መንቀሳቀሴን ቀጠልኩኝ እና ዛሬ ስምንቱንም ውይይቶቼን ልጨርስ ነው’ ” (Max L. Pinegar, “Serious About the Things to Be Done,” 1978 *Devotional Speeches of the Year* [ፕሮቮ፣ ብሪንግሀም ያንግ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ 1979], ከገጽ 55–56)።

• የዚህ ወጣት መስዋዕት ወደ ሕይወቱ ፍስሃ እና በረከት እንዴት አመጣለት?

**ጥቀስ**

ቄስ ጎርደን ቢ. ሒንክሊይ ሲሉ በየዕለቱ ባህሪይ ላይ ከዋለ የመስዋዕትን አስፈላጊነት እንዲህ ገልጸውታል።

“መስዋዕትነት የኃይማኖት ዋናው መሠረተ ነው፣ የደስተኛ ቤት ሕይወት፣ የእውነተኛ ጓደኝነት መሠረት፣ የሰላማዊ ማኅበረሰብ ኑሮ መሠረት ነው፣ በሕዝቦች እና መንግስታት መካከል የጤናማ ግንኙነት ማሰሪያ ድንጋይ ነው።

“ያለ መስዋዕትነት እውነተኛ የእግዚአብሔር አምልኮ የለም። በየዕለቱ እምነቴ እየጨመረ መጥቼያለሁ። ‘አብ ልጁን ሰጠ፣ እና ወልድ ሕይወቱን ሰጠ’ እና እኛም— ንብረቶቻችንን፣ ጊዜያችንን፤ ጥንካሬያችንን፣ ተሰጥዎቻችንን፣ እምነታችንን፣ ምስክርነታችንን እስካልሰጠን ድረስ አላመለክንም” (*Without Sacrifice There Is No True Worship*, Brigham Young University Speeches of the Year [ፕሮቮ, ጥቅምት 17 1962], ገጽ 4)።

**ውይይት**

• መስዋእቶችን ሣናደርግ በእውነት እግዘኢብሔርን ለምን ማምለክ አንችልም?

• ለምንድን ነው መስዋእትነት የደስተኛ ቤት ሕይወት እና ለእውነተኛ ጓደኝነት ቁልፍ ድንጋይ የሆነው?

• በሕይወቶቻችን ውስጥ ምን ዓይነት መስዋዕቶችን ማድረግ እንችላለን?

የግል ፍላጐቶችን መስዋዕት ወደ ቤታችን፣ ሥራችን፣ እና ትምህርት ቤታችን እንዴት ስምምነት ሊያመጣልን እንደሚችል ተወያይ። ወንጌላዊያን አገልግሎት የጊዜ እና ገንዘብ መስዋዕት እንዴት አቢይ የአምልኮ ዓይነት እንደሆነ አመልክት።

የጥናት መረጃዎች እና ውይይት

ከሚከተሉት ተረካዎች፣ ለክፍልህ ተስማሚ የሆኑትን ምረጥ፣ ወይም በክፍልህ ውስጥ ካሉት ወጣቶችጋር የሚዛመድ የራስህን ሁኔቴዎች ተጠቀም። እያንዳንዱን ጮክ ተብሎ ከተነበበ በኋላ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዲወያዩ ወጣቶቹን ጠይቀ፥

• ወጣቱ በዚህ ሁናቴ ውስጥ እንዴት ይሰማው ይሆን?

• ምን ያደርግ ይሆን?

• እንዴት መስዋዕትን ይሰዋ ይሆን?

• የእሱ መስዋዕት እሱን እና ሌሎችን እንዴት ይነካ ይሆን?

1. ጂም በጓደኛው ቤት ውስጥ ወደሚደረግ ፓርቲ ለመሄድ አቀዶ ነበር፣ ነገር ግን አባቱ የጎረቤቶቻቸውን መበለት ጓሮ ለጽዳት እንዲረዳ ጠየቀው።
2. ሁለቱም ዕድሚያቸው አስራ ሰባት በነበረ ጊዜ፣ ማይክ እና ጀኒፈር መተጫጨት ጀመሩ። ሁለቱም ማይክ በወንጌላዊነት እንዲያገለግል በመፈለጋቸው ምክንያት አንዳቸው ለአንዳቸው ስላላቸው ስሜቶች አሳሰባቸው።
3. ከኮሌጅ ከተመረቀ በኋላ፣ ዊሊያም ወደ ውጭ ሀገር ለመጓዝ በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ዕድል አገኘ። ነገር ግን የዊሊያም ጳጳስ ለወንጌላዊነት እንዲሄድ ጠራው።
4. ቢል የእግር ኳስመጫወት ይወዳል፣ ነገር ግን ከሞላ ጎደል በየቀኑ ይዘንብ ነበር። አንድ እሁድ ጠዋት፣ ጓደኛው ዮሐንስ ስልክ ደወለ እና የእግር ኳስ ጥሎ ማለፍ ግጥሚያ እንዲጫወት ጋበዘው ምክንያቱም ቀኑ ፀሐያማ ነበርና።
5. ወይዘሮ ማህለር ብቸኛ፣ አረጋዊ ሴት ነበረች። አድማጭ ለማግኘት ከቻለች ለአንድ ሰዓት ያለማቋረጥ ታወራለች። ፍራንክን በጐዳና ላይ አገኘችውና በዛምቡርግ ስለሚገኘው የወንድሟ ልጅ ማውራት ጀመረች። ነገር ግን ፍራንክ ለእራት ቤት መግባት ፈልጓል።
6. ጃወሪ ከጳጳሷ ጋር 1፡10 ላይ ቀጠሮ ነበራት እናም ቀደም ብላ 1፡00 ላይ ደረሰች። ጳጳሱ ለሌላ ሰው ቃለ መጠየቀ እያደረገ ነበረ። 2፡00 ላይ ጀሪ አሁንም እሱን ለማግኘት እየጠበቀች ነበር።
7. ማርክ አዲስ ብስክሌት ለመግዛት ገንዘብ እያጠራቀመ ነበር። ጳጳሱ በቀዱስ ቁርባን ስብሰባ ላይ ከዋርዱ ለአንድ ወንጌላዊ ድጐማ እንዲደረግለት ዘንድ ተጨማሪ የመዋጮ ልመና አቀረበ።
8. ዶሬ ሰባት ሰዓታት በትምህርት ቤት እና አራት ሰዓታት በሥራ አጥፍቷል። እቤት በደረሰ ጊዜ፣ እራት በላ፣ ሳህኖቹን ማጠብ አገዘ፣ ለሁለት ሰዓታት አጠና፣ እና ለጥቂት ደቂቃዎች በሙቀ ውሃ ባኞ ውስጥ ተዝናና። ለመኝታው ሲዘጋጅ፣ ጠረጴዛው ላይ ቀዱሳን መጽሐፍቶቹ ተዘርግተው አተኮረባቸው ሊያጠናቸው ፈልጓል፣ ነገር ግን ደግሞም ደክሞት ነበርና መኝታው ውስጥ ሊወድቀ ፈለገ።
9. የሣም ታናሽ ወንድም በመታመሙ ምክንያት ሌላ ጊዜ ቴኒስ እንጫወታለን ካለው ከሣም የስልክ ጥሪ ተቀበለ። ሣም ቤተሰቦቹ ወደ ቤተመቀደስ ስለሄዱ ከወንድሙ ጋር መቆየት ነበረበት።

---

**ማጠቃለያ**

ቀዱስ መጽሐፍ እና ጥቀስ

ንጉስ ቢንጃሚን ስለመስዋዕትነት እና መቀደስ በዝርዝር እንደተወያየ አስረዳ። እነዚህን ሕጐች በአንድ ዓረፍተ ነገር አስሮአቸዋል፣ ‘ሁለንተናችሁን እና ያላችሁትን ሁሉ ለእርሱ መልሳችሁ ለፈክፈል እናንተ ለሰማዩ አባታችሁ በዘለዓለማዊነት ውለታው ያለባችሁ ናችሁ፣” (ሞዛያ 2፡34)።

ፕሬዚዳንት ብሪግሃም ያንግ የጌታ ውለታ ተስምቷቸው አንዴ እንዲህ ብለው ነበር፣ “ልቤ ለዚህ ሥራ [መንግስቱን በመገንባት] ሙሉ በሙሉ ካልተሰጠች፣ ጊዜዬን፣ ችሎታዎቼን፣ እጆቼን፣ እና ንብረቶቼን እሰጣለሁ፣ ልቤ ለመገዛት እስክትፈቀድ ድረስ፣ ልቤ ለእሷ በታዛዥነት እጅ እስክትነሣ ድረስ እግዚአብሔርን በተመለከተ እጆቼ እንዲተገ አደርጋለሁ” (በ *Journal of Discourses*፡ 1፡202)።

የሚታደል ጽሁፍ

ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ ሞዛያ 2፡34 ጥቀስ የያዘውን ካርድ ስጣቸው። የመስዋዕትነትን እና የመቀደስን ሕጐች ለመጠበቀ ዘተር እንዲያስታውሰው በግድግዳው ላይ እንዲለጥፍ ሐሳብ አቀርብ።

# የማጥመቅ ኃይል

# 48

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | እያንዳንዱ ወጣት ወንድ በተሻለ የጥምቀትን ሥርዓት ይገነዘባል። |
| **ዝግጅት** | 1. የሚያስፈልጉ ትምህርት መሳሪያዎች፣<br>ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።<br>ለ. ሥዕል 23፣ የኢየሱስ የቀብር ሥነ ስርዓት (62180)፤ ሥዕል 24፣ ማርያም እና የተነሣው ጌታ (62186)።<br>ሐ. ጽሑፎች ምልክት ማድረጊያ እርሳሶች።<br>2. በጸሎት ሮሜ 6፡3–5፤ ሞዛያ 18፡7–10፤ እና ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 20፡73–74 አጥና። |

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሣብ**

**የጥምቀት ቃል ኪዳን**

ታሪክ እና ውይይት

የሚከተለውን ታሪክ ተናገር፣

ጳውሎስ እና ጂም ሁለቱም የአንድ ክህነት ቡድን አባሎች ነበሩና በአንድ የስቴክ ጥምቀት አገልግሎት ላይ ይረዱ ዘንድ ተጠይቀው ነበር። ያን አርብ ከሰዓት በኋላ በትምህርት ቤቱ አውቶብስ ውስጥ ሲገቡ፣ በጥምቀት አገልግሎት ላይ የእነርሱን ክንዋኔ በተመለከተ ያደረጉት ውይይት አባል ያልሆነው ሮበርት በተባለው ጓደኛቸው አልፎ ተሰማ። በአውቶብሱ ውስጥ ተቀምጠው ሳለ፣ ሮበርት ምንም ዝግጅት ያላደረጉባቸውን አንዳንድ ጥያቄዎች ጠየቀ ተደብቄ በመስማቴ ይቀርታ፣ ነገር ግን አንድ ነገር ማወቅ እፈልጋለሁ። እውን እናንተ ሰዎችን የማጥማመቅ መብት አለን ብላችሁ ታምናላችሁ? እናንተ ካህን አይደላችሁም፣ ናችሁ እንዴ? በተጨማሪ፣ በማንኛውም መንገድ ስለ ጥምቀት ምን የተለየ ነገር አለ?"

• ጳውሎስን ወይም ጂምን ብትሆኑ ኖሮ፣ የጥምቀት ቃል ኪዳን አስፈላጊ መሆኑን እና በአሮናዊ ክህነት ውስጥ ካህን የሆነ ጥምቀቶችን ለማከናወን ሥልጣን እንዳለው እንዴት ትገልጹ ነበር?

ጥቅስ እና ውይይት

ባለፈው ውይይት ወጣት ወንዶቹ ለቃል ኪዳን መግለጫ ካልሰጡ፣ ገለፃ እንዲሰጡ ጠይቃቸው። የሚከተለው ቁስ ብሩስ አር ማካንኪ ገለፃ ይህንን ነጥብ ለማብራራት ይጠቀማል፣

"በወንጌል ስሜት፣ *ቃል ኪዳን* የተቀደሰ እና የሚያስገድድ ሥምምነት፣ ውል፣ ኮንትራት፣ ወይም በእግዚአብሔር እና በአንድ ነጠላ ሰው ወይም በተመረጡ የሰዎች ቡድን መካከል የሚደረግ የጋራ ቃል ነው" (*Mormon Doctrine*, 2nd ed. [ሶልት ሌክ ከተማ፣ Bookcraft, 1966], ገጽ 166)።

ሰዎች የጥምቀትን ቃል ኪዳኖችን በሚያደርጉበት ጊዜ የሰማዩ አባታችንን ለመምሰሉ ሂደት የመጀመሪያውን ሥርዓት እያደረጉ እንደሆነ አስረዳ። በዚህም ምክንያት፣ የማጥመቅ ኃይል የተቀደሰ ልዩ መብት ነው። ጌታ ይህንን ልዩ መብት ለብቁ ቀሳውስት ሰጥቷል።

ቅዱስ መጽሐፍ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ውይይት

አንድ ወጣት ሞዛያ 18፡7–10 እንዲያነብ አድርግ።

• በጥምቀት ላይ እርግጠኛውን ቃል ኪዳን የሚገልጸው የትኛው ቁጥር ነው፣ እናስ ምንድን ነው ቃል ኪዳን የምንገባው? (ቁጥር 10። እርሱን ለማገልገል እና ትዕዛዛቱን ለመጠበቅ ተስፋ እንሠጣለን ወይም ቃል ኪዳን እንገባለን።)

• በቁጥር 7–9 ምን ይገልፃሉ? (አንድ ቃል ኪዳንን የፈጸመ ሰው የሚያሳየው ባህሪይ እና በልቡ ውስጥ ምን አስተሳሰቦች ሊኖሩት እንደሚገቡ።)

• የጥምቀት እውነተኛ ቃል ኪዳን ምንድን ነው?

ወጣቶቹ የሚከተሉትን ነጥቦች እንዲያነሱ አርዳቸው፣ እና በጥቁር ሠሌዳው ላይ ዘርዝራቸው፡፡

| | |
|---|---|
| የጥምቀት ቃል ኪዳን | |
| የእኛ ድርሻ፡ | የጌታ ድርሻ፡ |
| 1. ወደ እግዚአብሔር መንጋ መምጣት፡፡ | 1. መንፈሱን በላያችን ላይ ሊያፈስ፡፡ |
| 2. የኢየሱስ ክርስቶስን ሥም በላያችን ላይ መልበስ፡፡ | 2. ሊዋጀን፡፡ |
| 3. የሌሎችን ሸክሞች መሸከም፡፡ | 3. በመጀመሪያው ትንሣዔ ካላቸው ጋር ሊቆጥረን፡፡ |
| 4. ከአዘኑ ካዘኑት ጋር ማዘን | 4. ዘላለማዊ ሕይወት ሊሠጠን፡፡ |
| 5. መጽናናት የሚፈልጉትን ማጽናናት፡፡ | |
| 6. በሁሉም ግዜያት እንደ እግዚአብሔር ምስክር መቆም፡፡ | |
| 7. እግዚአብሔርን ለማገልገል እና ትዕዛዛቱን ለመጠበቅ መስማማት፡፡ | |

**የጥምቀት ምልክታዊነት**

የአማካሪው አቀራረብ እና ውይይት

ለወጣቶቹ አንድ ሥርዓት ምሳሌያዊ መሆኑን አስታውሳቸው፡፡ የኢየሱስን ሥርዓተ ቀብር ሥዕል አሳይ፣ ከዚያም ከትንሣኤው በኋላ የኢየሱስን ሥዕል አሳያቸው፡፡ አንድን ወጣት ሮሜ 6፡3–5 እንዲያነብ ጠይቅ፡፡ በጳውሎስ የተገለጸውን ምሳሌያዊነት ወጣቱ እንዲፈልግ ምራው፡፡

• በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት እና ትንሣኤ እንዲሁም የጥምቀት ሥርዓት መካከል ምንም ማነፃፀሪያ ተሠጥቷል?

ውይይቱ— ጥምቀት—ወደ ውሃ ውስጥ መግባት እና ከውሃ ውስጥ መውጣት—የኢየሱስን ወደ መቃብር፣ ወይም ሞት መውረድን እና ከሱም የትንሳኤ አካል ይዞ መነሳቱን በመወከል ላይ መመስረት አለበት። እንዲሁም በዚያ አሮጌው የኃጢያት ሰውነታችን ተቀብረን እና በክርስቶስ በአዲሱ ሰውነታችን በመነሳት፣ እርሱን ለመከተል እና ንፁህ ሆኖ መቆየትን በመሻት፣ ዳግም መወለዳችንን ይወክላል፡፡

**በአሮናዊ ክህነት ውስጥ የሚገኝ ቄስ ለማጥመቅ መለኮታዊ ሥልጣን ተሰጥታል**

ሁናቴ እና ውይይት

የሚከተለውን አንብብ፡

ዮሐንስ ንቁ እና ብቁ እንዲሁም በወንጌላዊነት ለመሄድ የሚጠባበቅ ቄስ ነው፡፡ ታናሽ እህቱ፣ ሱ፣ ስምንት ዓመቷን ልክ ስትሞላ ወንድሟ ጥምቀቷን እንዲያከናውንላት ጠየቀችው፡፡ እሱ በጣም ጽኑ ፍላጐት አደረበት ምክንያቱም ይህ ለርሱ ሲያጠምቅ የመጀመሪያው በመሆኑ ነው፡፡ አንድ ቀን ምሽት ከቤተሰብ የቤት ምሽት በኋላ፣ ሱ ጥምቀቷን ስለማከናወኑ ጉዳይ ጠየቀችው፡፡ ጳውሎስ፣ ታላቅ ወንድሟ፣ በጣሊያን አገር ወንጌላዊነት የተያገለግል እና ስለሚያጠምቃቸው ጥምቀቶቹ የሚጽፍልኝ፣ ነገር ግን ዮሐንስ እድሚው አስራ ስድስት የሆነው እና በሚሲዮን ላይ ያልሆነ የሚል ሐሳብ መጣባት፡፡ "ወንጌላዊ ካልሆንክ እንዴት ጥምቀቴን ልታከናውንልኝ ትችላለህ?" ስትል ተጠይቃለች፡፡

ለወጣት ወንዶቹ የቃላት ማውጫውን ከመጽሐፈ ሞርሞን፣ ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች፣ እንዲሁም የታላቁ የእንቁ ዋጋ ጋር በመጠቀም ዮሐንስ ለእህቱ የሚሰጣትን መልስ እንዲያበጁ አድርግ፡፡

ወጣት ወንዶቹ በጣም የተሻለ መልስ በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 20፡46 ላይ ያገኛሉ፡፡ ቡድኑ መልሱን ከሰጠ በኋላ፣ ወጣት ወንዶቹ ትምህርት እና ቃል ኪዳን 20፡46 ምልክት እንዲያደርጉበት አድርግ፡፡

ሁሉም ጥምቀቶች በጳጳሱ አመራር ወይም በሌሎች የመልከጸዲቀ ክህነት ኃላፊ አመራር ሥር መፈፀም እንዳለባቸው እና ቄሱ እያንዳንዱን ጥምቀት ለመፈፀም ከአመራር ኃላፊዎቹ ፍቃድ ሊኖራው እንደሚገባ አስረዳ።

**የጥምቀት አፈፃፀም መንገድ ተገልጿል**

ቅዱስ መጽሐፍ እና ውይይት

• በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች ውስጥ የጥምቀት ጸሎት የሚገኘው በምን ምዕራፍ ውስጥ ነው? (ትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 20፡73፡፡)

በጥምቀት ሥርዓት ውስጥ ትክክለኛ የመሆን አስፈላጊነት ለማጉላት፣ ወጣት ወንዶቹ ትምህርት እና ቃልኪዳኖች 20፡73 እንዲያወጡ እና በኢየሱስ ክርስቶስ የተመለከተውን ግልጽ ዘዴ እንዲያነቡ አድርግ፡፡

ይህን ጥቀስ ወጣት ወንዶቹ እንዲጠቀሙ እና ምልክት እንዲያደርጉበት ጊዜ ስጣቸው፡፡ በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች እንደተቀመጠው የትክክለኛ ቃላት አጠቃቀም አስፈላጊነት እና ጠቃሚነት አጉላ፡፡ ከዚያም ለወጣት ወንዶቹ ፀሎቱን በልባቸው እንዲይዙ አንድ ደቂቃ ስጣቸው፡፡ ጥቂት ወጣት ወንዶች ከትውስታቸው እንዲደግሙት ጥራቸው፡፡

የጥምቀት ጸሎት በቤተክርስቲያን ውስጥ ከተዘጋጁ ጥቂት ጸሎቶች ውስጥ አንዱ መሆኑን አጉላ፡፡ አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሣ ዘወትር በትክክል መባል አለበት፡፡

የጥምቀት ስርዓት ለመፈፀም ቄስ እንደ እግዚአብሔር ወኪል ሆኖ እንደሚሠራ ግለፅ፡፡ ይህ በጥምቀቱ ጸሎት ላይ "በኢየሱስ ክርስቶስ በመሾሚ" የሚለውን ሀረግ ትርጉም ይገልፃል፡፡

• በትምህርት እና ቃል ኪዳኖች 20፥74፣ ከጥምቀት ጸሎት ቀጥሎ፣ ስለ አጠማመቁ ዘዴ ምን ይላል? (ውሃ ውስጥ በማጥለቅ መፈፀም አለበት፡፡)

• ዛሬ ካነበብነው ውስጥ በመጥለቅ የመጠመቅን አስፈላጊነት አፅንኦት የሰጠ ሌላ ጥቅስ የትኛው ነው? (ሮሚ 6፥3–5፡፡)

በመጥለቅ የመጠመቅ አስፈላጊነት ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ካሉት ኃይለኛ ጽሑፎች አንዱ ይህ በሮሚ ላይ ያለው ምንባብ መሆኑን አጉላ፡፡ ይህ ወጣት ወንዶቹ ወንጌላዊ ሲሆኑ የሚጠቀሙበት አስፈላጊ ጽሑፍ ይሆናል፡፡ እነዚህን ቁጥሮች ምልክት እንዲያደርጉባቸው ሐሣብ አቀርብ፡፡

የገፀ ባህሪ ክወና (ለቄሶች ብቻ)

ከቄሶች ጥቂቶቹ (ይህ ትምህርት ለቄሶች የሚሰጥ ከሆነ) ጥምቀትን ያከናወኑ ቢሆኑም ሌሎቹ እንደዚህ አላከናወኑም ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ ቄስ ከአፈፃፀሙ መንገድ ጋር መተዋወቁን ለማረጋገጥ ይህ ተስማሚ ጊዜ ይሆናል፡፡

ቄሶች ጥንድ እየሆኑ ለጥምቀት እጬዎች አያያዝ በተገለፀው መንገድ ለመለማመድ ተራ ይያዙ፡፡ አጥማቂው በግራ እጁ የሚጠመቀውን ሰው ቀኝ እጅ አንጓ ዙሪያ ይያዝ፡፡ የሚጠመቀው ሰው የሌላኛውን ግራ እጅ አንጓ ዙሪያ በግራ እጁ ይያዝ፡፡ የእጅ አንጓዎቹ በሚጠልቀበት ጊዜ እንዲረዱ ጥብቅ ተደርገው መያዝ ይገባቸዋል፡፡ የዕጬው ቀኝ እጅ በሚጠልቀበት ጊዜ አፍንጫውን እንዲይዝ ነፃ ሆኖ ይቀራል፡፡ ጥምቀቱን የሚፈፅመው ሰው ቀኝ እጅ በጸሎቱ ወቀት በአራት ማዕዘን ቀርፅ ወደ ላይ ያነሳና በመጥለቁ ወቀት ዕጬውን ለመርዳት ጀርባው ላይ ተመልሶ ይቀመጣል፡፡ እጬው በሚጠልቀበት ጊዜ እግሮቹ ከውሃ ውስጥ እንዳይወጡ ለመከላከል ጉልበቶቹን እጠፍ ያደርጋል፡፡

በቄሶቹ ቀድስና እና ጥምቀቶቹን ይፈፅሙ ዘንድ በጥሪያቸው አስፈላጊነት ላይ ጥቅል ስሚትን አሳድር። ጥምቀት ለእግዚአብሔር መንግስት አባልነት አስፈላጊ ነው፣ እናም ሥልጣን ባላቸው ሰዎች ብቻ መፈፀም አለበት፡፡

ከተቻለ፣ እያንዳንዱ ቄስ እውነተኛውን የጥምቀት ክንዋኔ ልምድ እንዲኖረው ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ከጳጳሱ ጋር ሥራ፡፡

---

**ማጠቃለያ**

አቀራረብ

ይህን አስፈላጊ ሥርዓት በሚፈጸምበት ጊዜ ቄሱ ትክክለኛ፣ ብቁ እና አክባሪ የመሆን አስፈላጊነትን በድጋሚ አጉላ፡፡ ጥምቀት የሚያከናውኑት ሰዎች ዕውቀት ያላቸው እና በራስ መተማመን ካከናወኑት በሚጠመቁት ሰዎች ሕይወት ውስጥ የበለጠ ትርጉም ያለው ይሆናል፡፡

# ጊዜን በብልሃት መጠቀም

# 49

**ዓላማው**

እያንዳንዱ ወጣት ወንድ ጊዜን በብልሃት የመጠቀምን አስፈላጊነት እና ጥቅሞች በመገንዘብ እንዲሁም ጊዜውን በውጤታማነት ለመጠቀም እንዴት እንደሚያቀናጅ ይማራል።

**ዝግጅት**

1. የሚያስፈልጉ የትምህርት መሣሪያዎች፡
   ሀ. ለእያንዳንዱ ወጣት መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. ለእያንዳንዱ ወጣት ቁራጭ ወረቀት እና አንድ እርሳስ።
   ሐ. ጥቅሶችን ምልክት ማድረጊያ እርሳሶች።
2. በፖስተር ላይ የግድግዳ ሰዓት ገጽታ አዘጋጅ። ከፊት ለፊቱ *ጊዜ ሕይወት ነው፣ ለታባክነው ብለህ ለትም።*
3. በጥቁር ሠሌዳው ላይ ለምስቱን የውጤታማነት ኤክስፖርቱን ምክራዊ ጥቀማዎች ዘርዝር ወይም ፖስተር ሥራ (በትምህርቱ ውስጥ ያለውን ናሙና ተመልከት)።
4. ትምህርት ምሣሌውን ባዶ ጠርሙስ ወይም ብልቃጥ፣ ትናንሽ ጠጠሮች፣ እና አሸዋ በመጠቀም ብትለማመድ ወደ ክፍሉ ትክክለኛውን የድንጋይ እና አሸዋ መጠን ይዘህ ለመሄድ ትችላለህ።
5. በተሚላ ጸሎት መክብብ 3፡1–8 እና አልማ 34፡32 አጥና።

**ለትምህርት ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

**በምድር ላይ ያለው ጊዜአችን አስፈላጊነት**

*ፖስተር፣ ጥቅስ እና ውይይት*

የግድግዳ ሰዓት ገጽታ ያለበትን ፖስተር አሳይ።

በዚህች ምድር ላይ ስላለን ጊዜ አልማ በጣም አስፈላጊ ነው ሲል እንደሚነግረን ግለፅ። ወጣት ወንዶቹ በፀጥታ አልማ 34፡32 እንዲያጠኑ እና ምልክት እንዲያደርጉበት ጠይቅ።

• በዚህች ምድር ላይ የጊዜያችን ዋና ዓላማ ምንድን ነው? (እግዚአብሔርን ለመገናኘት እንድዘጋጅ ነው።)

ስለሚያውቋቸው ሰዎች እንዲያስቡ ወጣት ወንዶቹን ጠይቅ።

• እነዚህ ሰዎች በሰዓታቸው ከሚያደርጓቸው ነገሮች የተነሳ፣ ይህን ቅዱስ መጽሐፍ እነርሱ የሚያምኑበት እና በእውን እግዚአብሔርን ለመገናኘት የሚጥሩ ይመስላልን?

• ሌሎች ሰዎች አንተን በመመልከት እግዚአብሔርን ለመገናኘት እየተዘጋጀህ መሆንህን ይገነዘባሉን?

• እግዚአብሔርን በቁም ነገር ለመገናኘት የሚዘጋጅ ሰው ሁሉንም ዓይነት ደስታ እና መዝናናት ከሕይወቱ ያስወግዳልን?

---

**ለሁሉ ነገር ወቅት አለው**

*የአማካሪው አቀራረብ*

የምድራችን ሕይወት የተነደፈው ለእኛ ዕድገት እና መደራጀት እንደሆነ አስረዳ። የሰው ልጅ የበለጠ የሚያድገው ለተለያዩ ተሞክሮዎች ሲጋለጥ ነው። የሚያድገውን ልጅ ፍልጉቶች በበለጠ ሁኔታ ያገለግሉ ዘንድ እነዚህ ተሞክሮዎች በሆነ መንገድ በቀደም ተከተል መቀመጥ ይኖርባቸዋል። በተመሣሣይ ጌታ ለእኛ የተለያዩ ተሞክሮዎች በትክክለኛ ጊዜያቸው እና ቀደም ተከተላቸው እንዲኖሩን አስቦልናል።

*ቅዱስ መጽሐፍ፣ ጥቁር ሠሌዳ፣ እና ውይይት*

በመጽሐፈ መክብብ ሦስተኛው ምዕራፍ ላይ አንድ ግጥማዊ ምንባብ እግዚአብሔር ለኛ ስላዘጋጀው ቀደም ተከተል ያስረዳል። አንድ ወጣት ወንድ መክብብ 3፡1–8 እንዲያነብ ጠይቅ።

• ከእነዚህ ቁጥሮች ጊዜያችንን በብልሃት ስለመጠቀም ምን መማር እንችላለን?

• ስለ እነዚህ ነገሮች ቀደም ተከተል ጌታ ምን ብሏል? (የሁኔታዎች ተገቢ ወቀት እንደሚደርስ እርሱ አሳስቧል። ለምሣሌ ያህል ለመፈቃቀር እና ለመተቃቀፍ ጊዜ አለው እንዲሁም ከመተቃቀፍም ለመራቅ ጊዜ አለው። በወንጌላዊነት አስክናገለግል እና የጋብቻ ኃላፊነቶችን ለመቀበል እስክንዘጋጅ ድረስ ጋብቻን እንድናቆይ በዘመናችን መሪ ተምረናል።)

• ለመኖር የሣምንት ጊዜ እንደቀረህ ተነግሮሃል እንበል። በዚያ ውድ ጊዜ የምታደርጋቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ወጣት ወንዶቹ ምላሽ እንዲሰጡ ጥቂት ጊዜ ስጣቸው፡፡ በጥቁር ሠሌዳው ላይ ምላሾቻቸውን ዘርዝር፡፡ ምናልባት ምላሾቻቸውን እንደ አስፈላጊነታቸው በቀደም ተከተል ለመዘርዘር ትሻ ይሆናል፡፡

---

**ጊዜን በጥበብ መጠቀም ዕቅድ ይጠይቃል**

ትምህርተ ምሣሌ

ባዶውን ጠርሙስ አሳይ፡፡ በቀን ሃያ አራት ሰዓት እንደሚወክል አስረዳ።

በቀኑ ውስጥ በእርግጥ ሲሰሯቸው የሚደሰቱባቸውን እንቅስቃሴዎች ስም እንዲሠጡ ጠይቀ፡፡ እነዚህን እንቅስቃሴዎች ምናልባት መዝናኛን ወይም ሌሎች እንቅስቃሴዎችን ያካትቱ ይሆናል፡፡ እነርሱ በርካታ ነገሮችን ሲጠቁሙ፣ አሸዋውን ማሰሮ ውስጥ ጨምር፡፡

ከዚያም በአዘቦቱ ቀን ውስጥ ወጣቶቹ ሊያደርጓቸው የሚገባቸውን አንዳንድ ነገሮች እንዲዘረዝሩ ጠይቀ፡፡ እነዚህ ምናልባት የትምህርት ቤት ሥራ፣ በቤት አካባቢ ትናንሽ ሥራዎች፣ እና የቀዱሳን መጽሐፍት ጥናትን ያካትቱ ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ሲጠቀም፣ (ማሰሮው) እስኪሞላ ድረስ ጠጠሮቹን ጨምር፡፡

አሁንም ሊጨምሩ የሚችሉ በርካታ ጠጠሮች ቢኖሩም፣ ጠርሙሱ፣ ወይም ቀኑ፣ ሙሉ እንደሆነ ግለፅ፡፡ ጠጠሮቹን አውጣ እና፣ አሸዋውን ወደ ቀድሞው መያዣ መልሰህ ጨምር፡፡

እጅግ በጣም አስፈላጊውን ነገር መጀመሪያ ማድረግ እንዳለብን ግለፅ፡፡ ትምህርተ ምሣሌውን በድጋሚ ጀምር፣ በዚህ ጊዜ አንድ ጠጠሩን መጀመሪያ ጨምር፡፡ በጠርሙሱ ውስጥ እያንዳንዱን ጠጠር ስታስቀምጥ፣ በየዕለቱ ከሚያስፈልጉ ነገሮች ማለትም እንደ ቀዱሳን መጽሐፍ ጥናት፣ ጸሎቶች፣ የትምህርት ቤት ሥራ እና የቤት ውስጥ ትናንሽ ሥራዎች ውስጥ፣ ሕይወታችንን ሥርዓት በማስያዝ አሁንም በደስታ እና በመዝናኛ እንቅስቃሴዎችን ለመሣተፍ ጊዜ ማግኘት እንደምንችል ግለፅ፡፡ እነዚህን እንቅስቃሴዎች በመወከል አሸዋ በማሰሮው ውስጥ ጨምር፡፡

ጥቁር ሰሌዳ፣ ታሪክ፣ እና ውይይት

የሚከተለውን ታሪክ ተናገር፣

“በአንድ ወቀት አንድ የውጤታማነት ባለሙያ የአንድ ትልቀ የብረት ኮርፖሬሽን ፕሬዝዳንትን ቀርቦት ዋና ዋናውን የመፍትሄ አገልግሎት ገለፀለት፡፡ “እርባና ቢስ ነው፣” ሲል ፕሬዚዳንቱ መለሰ። “እንዴት እንደማስተዳድር አውቃለሁ፣ አሁን ግን በሚገባ እያስተዋልኩ አይደለም፡፡ ብዙ ተግባር እንጂ ብዙ ማወቀ አያስፈልገንም፡፡ እንድናደርገው ማወቀ የሚገባንን ነገር ለኛ ካገኘህልን፣ የጠየከኝን ማንኛውንም ነገር እከፍልሃለሁ፡፡”

“መልካም፣” ሲል መለሰ አማካሪው፡፡ “በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ተግባርህን በ50 በመቶ የሚያሣድግ አንድ ነገር ልሰጥህ እችላለሁ፡፡ በመጀመሪያ፣ በባዶ ወረቀት ላይ ነገ ልትሠራቸው የሚገቡህን ስድስት እጅግ በጣም አስፈላጊ ሥራዎች ፃፍ፡፡ ሁለተኛ፣ እንደ አስፈላጊነታቸው በቀደም ተከተል አስቀምጣቸው፡፡ ሦስተኛ፣ በመጀመሪያ ነገር ነገ ጠዋት ወረቀቱን አውጣ እና በመጀመሪያው ዝርዝር ላይ መስራት ጀምር፡፡ አራተኛ፣ ስትጨርስ፣ ሁለተኛውን ዝርዝር ሥራ፣ ከዚያም ሦስተኛውን ዝርዝር ሥራ፡፡ ይህንኑ ጊዜው እስኪበቃ ድረስ ሥራ፡፡ ሁለቱን ወይም ሦስቱን ብትጨርስም ወይንም አንዱን ብቻ እንኳ ብትጨርስም አትጨነቀ፡፡ እጅግ በጣም አስፈላጊዎቹ ላይ መጀመሪያ ትሠራለህ፡፡ አምስተኛ፣ የሚቀጥለው ቀን ሥራዎች አዲስ ዝርዝር ለማውጣት የእያንዳንዱን የሥራ ቀን የመጨረሻዎቹን አምስት ደቂቃዎች ውሰድ፡፡”

በጥቁር ሠሌዳው ላይ ወዳለው የሙያ ቀልጥፍና ዝርዝር አመልክት ወይም ፖስተሩን አሳይ፣

> የአማካሪው አቀራረብ
>
> 1. ሊሠሩ የሚገባቸውን ስድስቱን እጅግ በጣም አስፈላጊ ሥራዎች ፃፍ፡፡
> 2. እነዚህን ዝርዝሮች እንደ አስፈላጊነታቸው በቀደም ተከተል አስቀምጥ፡፡
> 3. ጠዋት በቁጥር አንድ ላይ መስራት ጀምር፡፡
> 4. ቁጥር አንድ ሲጠናቀቀ፣ ወደ ቁጥር ሁለት ሒድ፣ እናም ሌላውን ቀጥል።
> 5. በሚቀጥለው ቀን ለመገልገል በእያንዳንዱ ምሽት አዲስ ዝርዝር ሥራ፡፡

- በእቀዳችን ውስጥ የሰማዩ አባታችን እንዴት ልናሳትፈው እንችላለን? (ጊዜያችንን በመልካም ሁኔታ ለመጠቀም እና ቀዳሚዎቹን ለመወሰን ይረዳን ዘንድ መጸለይ እና መጠየቀ፡፡)

የጸሑፍ ተሳትፎ

ለእያንዳንዱ ወጣት ወንድ አንድ እርሳስ እና ቁራጭ ወረቀት ስጥ፡፡ ወረቀቶቻቸውን በሦስት አምዶች እንዲከፍሉ አድርግ፣ የመጀመሪያውን አምድ “መደረግ አለበት፣” ሁለተኛውን “መደረግ ይገባዋል፣” እና ሦስተኛውን “መደረግ ይፈልጋል” በማለት ይሰይሙ፡፡ “መደረግ አለበት” በሚለው ርዕስ ሥር ነገ

ሊያደርጓቸው የሚገቧቸውን ነገሮች፣ “መደረግ ይገባዋል” በሚለው ርዕስ ሥር መደረግ የሚገባቸውን መድረግ ይፈልጋል በሚለው ርዕስ ሥር ሲያደርጓቸው የሚደሰቱባቸውን ነገሮች እንዲጽፉ እዘዝ። እነዚህ በትምህርተ ምሣሌው ላይ ከተመለከቱት ነገሮች ጋር ተመሣሣይ መሆናቸውን ግለፅ። እነዚህን እንቅስቃሴዎች ሊቆጣጠሯቸው የሚችሏቸው ከመሆናቸው የተነሳ፣ በመጨረሻዎቹ ሁለት አምዶች ውስጥ ያሉትን ዝርዝሮች እንደ አስፈልጊነታቸው መሠረት ቁጥር እንዲሠጧቸው ወጣቶቹን ጠይቀ።

ውይይት

• በሰዓታችን በጣም ብዙ ለመስራት በማቀድ ምን ዓይነት የጤና ለውጦች ይከሰታሉ? (የሰውነት ዝለት፣ መሳቀቅ፣ ድካም፣ እና ሥጋት፣ በጥቂት ነገሮች ጥሩ ሥራ ከመስራት ይልቅ በብዙ ነገሮች መጥፎ ሥራ መስራት ናቸው።)

የሚፈልጉትን እና የሚወዱትን ሥራ መፈጸም ይቻላቸው ዘንድ ለወጣት ወንዶቹ ጊዜያቸውን በብልሃት የማቀድን አስፈላጊነት አጉላ።

---

**ውጤታማ የጊዜ አጠቃቀም መንፈሣዊ እና ሥጋዊ በረከቶችን ያመጣል**

ታሪክ

ሊኖሩን ከሚችሉት ታላላቀ በረከቶች አንዳንዶቹ የሚመጡት ሌሎችን በማገልገል መሆኑን ግለጽ። ለአንድ የኢግል ስካውት አለቃ፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ቤተሰቦች ንቁ ተሳታፊ ካልነበሩ፣ ከቀደምቶቹ የሱ ኢግል ስካውቶች መካከል በአንዱ፣ የተፃፈውን ተከታዩን ደብዳቤ አንብብ። ከቤተክርስቲያን አገልግሎት ሊመጡ የሚችሉትን በረከቶች ያትታል።

ውድ ሮን፣

ከፈጠርካቸው ከብዙዎቹ ኢግል ስካውቶች መካከል አንደኛው ነኝ— በደንብ አስብና ማን እንደሆንኩ አስታውስ። የኢየሱስ ክርስቶስን የወንጌል ምስክርነት እንዴት እንዳገኘሁ በሚያጠናው ፍሬ ሐሳብ ዙሪያ የግል ታሪኬን ለመጻፍ ጀምሬ ነበር።

ከበርካታ ወራት በፊት ለመጻፍ ስነሳ፣ ለወንጌል ውሣኔዬ የረዱኝን ሰዎች ማሰላሰል ጀመርኩ። ያንተ ሥም ወደ አዕምሮዬ ከመጡት ውስጥ የመጀመሪያው ነበር። በእነዚያ በሕይወቴ አስፈላጊ በሆኑት ዓመታት ውስጥ ስላሳየኸኝ ፍቅር የሰማዩ አባታችንን በርካታ ጊዜያት አመሰግኜዋለሁ።

የአንተን ኢግል ስካውቶች ከልብ ወደሃቸዋል እናም እንዴት ሰው እንደምንሆን ስታበረታታን እና ስታስተምረን ጊዜህን አጥፍተሃል። አንዴ ገመድ በማሰር እና ወይም በማጥበቀ ምናልባት ጥሩ እንደምሆን ኃሳብ መጣልህ፣ ስለዚህ በካምፑ ውስጥ ብልጫ ያለኝ እንድሆን አበረታታኸኝ። ጠንክሬ ሞከርኩኝ እና ያን ግብ ተቀዳጀሁ።

በጠንካራ ጎኖቼ ላይ እንድሠራ ለማበረታታት ያደረክልኝን የስልክ ጥሪዎችን ደግሞ አስታውሳለሁ። ከዚያም በመጨረሻ የኢግል ስካውት መሆን እንደቻልኩ ኃሳብ አደረብኝ። ከዩታህ ወደ ካሊፎርኒያ ከሄድኩ ከጥቂት ሣምንት በኋላ የኢግል ስካውትነትን ሽልማት ተቀበልኩ።

የእኔ የቤተክርስቲያን ውስጥ እንቅስቃሴ በአብዛኛው በአንተ ግፊት ነበር።

በወንጌላዊነት ሚሲዮን አገልግያለሁ፣ እናም በብርግሃም ዩኒቨርስቲ ውስጥ አሁን ሲቪል ኢንጅነሪንግ፣ እያጠናሁ ነኝ። በአሁኑ ሰዓት በወንጌላዊያን ማሠልጠኛ ማዕከል የስፓኒሽ አስተማሪዎች አስተባባሪ ሆኜ ተቀጥሬአለሁ። ሥራዬን፣ ትምህርት ቤቴን እና አንድ ቀን እንድተተዋወቃት የምፈልጋትን ልጃገረድ አፈቅራለሁ። ሮን አመሰግናለሁ።

ከልብ፣

ስታን

ውይይት

የኢግል ስካውት አለቃ በነበረበት ጊዜ፣ ሮን ሚስት፣ ቤተሰብ፣ እና የሙሉ ጊዜ ሥራ እንደነበረው አስረዳ።

• ሮን ለሥራው ከስካውት ፕሮግራም ጋር እንዴት ጊዜ ያገኘለት ይመስልሃል? (ጊዜውን በብልሀት ማቀናጀት ነበረበት።)

• ከስካውቶቹ ጋር መስራት ጊዜውን ለመጠቀሙ ለምን እንደዚያ የጐላ መንገድ ሆነለት? (ካለው የጊዜ አጠቃቀም የበለጠ በሆነው በእርሱ፣ የእግዚአብሔርን ልጆች እየረዳ ነበር።)

• አንድ የአሮናዊ ክህነት ያለው ጊዜውን የእግዚአብሔርን ልጆች በመርዳት ሊጠቀምባቸው ከሚችልባቸው አንዳንድ መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

• ወጣት እና በተመሣሣይ ትላልቆች ጊዜያቸውን የሚያጠፉባቸው አንዳንድ መንገዶች የትኞቹ ናቸው? (ከልክ በላይ ቴሌቪዥን መመልከት፣ በቀልድ አስቀድሞ መጠመድ፣ ወይም ብዙ መተኛት።)

| | **ማጠቃለያ** |
|---|---|
| አቀራረብ | ቀልጣፋ አገልግሎት ይሠጡ ዘንድ ለመዘጋጀት ጊዜያቸውን በሥነ-ሥርዓት እንዴት እንደሚያደራጁ በመማር አሁን ለእነርሱ መዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን ለወጣት ወንዶቹ በአንዳንድ ነገሮች ላይ የቀድሚያዎች ለውጥ በየቀኑ እንደሚደረግ እና የረጅም ጊዜ ግቦች በየወቀቱ እንደገና መገምገም እንደሚገባቸው ጥቀስ። በመንፈስ ምሪት የምንኖር ከሆነ፣ እነዚህን ማስተካከያዎች መቼ ማድረግ እንዳለብን እናውቃለን። |
| ሙከራ | በቀን ውስጥ ብዙ ማከናወን ይችሉ እንደሆነ ለማየት የውጤታማነት ባለሞያውን ምክሮች ለሁለት ሣምንታት እንዲመክሯቸው ወጣት ወንዶቹን አለማምድ። የየቀኑ ግባቸውን ከምሽቱ በፊት ወይም በእያንዳንዱ ጠዋት ሲተልሙ ግቦቻቸውን ለመተለም እና ለመፈጸም የርእሱን እርዳታ ማግኘት ይቻላቸው ዘንድ ወደ ሰማዩ አባታችን እንዲጸልዩ አበረታታቸው። ከዚያም ውጤቶቻቸውን ለእርሱ ማታ ላይ ሪፖርት ማድረግ ይገባቸዋል። |

# ለቡድኑ አማካሪ፥ ከአጠቃላይ ጉባዔ ንግግሮች ላይ ትምህርቶችን ማቀናበር

# 50

**ዝግጅት**

ከመምሪያው ውስጥ የነበሩት ትምህርቶች ስትከተል እንደነበረው እነዚህን ትምህርቶች ለማዘጋጀት እና ለማቀረብ ተመሳሳይ የአሰራር መንገድ ተከተል። በተጨማሪ፣ የሚከተሉት የመዘጋጃ እርማጃዎች የሚያግዙ ይሆናሉ፣

1. በተመረጡት ንግግሮች ውስጥ ሙሉ በሙሉ የትኛው የወንጌል ትምህርት ወይም ዋና ሐሳብ ለትምህርት እንደቀረበ ወስን። ዋናውን ሐሳብ የሚያጠናክሩ ወይም ሦስት ዋና ዋና ደጋፊ ሐሳቦች ግለፅ።
2. በትምህርቱ ውጤት አማካኝነት ክፍፃሚ ለማድረስ ምን እንደምትሻ ወስን። ለምሣሌ፣ ወጣት ወንዶቹ አንድን ትምህርት እንዲረዱ፣ በእምነት እንዲያድጉ፣ ሐሳባቸውን እንዲያዳብሩ፣ ወይም ባህሪያቸውን ለመቀየር እንዲነሳሱ ልትረዳቸው ትፈልጋለህን?
3. የትምህርቱን ቁሣቁሶች አቀናጅ። ተጨማሪ የቀዱሣን መጽሐፍ ጥቀሶችን አመልክት። ለተስማሚ የዕይታ ቁሣቁሶች የመሰብሰቢያ አዳራሹን ቤተ መፅሐፍት ሠራተኛ ጠይቅ።
4. በንግግሩ ውስጥ ስላሉት የተመረጡ ጥቀሶች እና ጽሑፎች ጥያቄዎችን አዘጋጅ። ጥቀሶች እና ቀዱሳን መጽሐፍት ምን ማለት ናቸው? ከወጣት ወንዶቹ ጋር አዛምድ (1ኛ ኔፊ 19፥23 ተመልከት)። *Teaching—No greater Call*
5. የክፍሉን አባላቶች የሚያሣትፍ የማስተማር መንገድ ምረጥና፣ የክፍል አባላቶች እንዲሳተፉ መድብ። ለማስተማሪያ ዘዴዎች ገለፃ ከማስተማር—የበለጠ ጥሪ የለም (33043) ከሚለው ጋር አመሣክር።

**ለአስተማሪው ማስታወሻ**

ለተጨማሪ ትምህርቶች የሕያው ነቢያት ቃላቶች እጅግ በጣም ጥሩ ምንጮች ናቸው። *በሊያሆና* እና ዓለም አቀፋዊ መጽሔቶች ላይ ከታተሙት ወቀታዊ የጉባዔ ንግግሮች ምረጥ። ለተለዩ የቡድን አባላት ፍላጎቶች ንግግር ለማድረግ እነዚህን ትምህርቶች ስታዘጋጅ እና ስታቀርብ በመንፈስ የመመራትን ዕድሎች ይሰጡሃል። ወጣት ወንዶች የትኛውን ንግግር እንደሚማሩ አስቀድሞ ሊነገራቸው ይገባል ስለዚህም እነርሱ ለውይይት የተዘጋጁ ይሆናሉ። እነዚህን ትምህርቶች በማጉልበቱ ጊዜ፣ የበላይ ባለሥልጣናትን ትምህርቶች፣ የጉባዔ ንግግሮችን እና ቀዱሣን መጽሐፍትን ተጠቀም።

**የትምህርት አስተዋፅኦ**

1. የሚቀጥለው ሠንጠረዥ ምናልባት ከንግግር ላይ ትምህርቱን በማዘጋጀት ጊዜ ይረዳ ይሆናል።

የንግግሩ ርዕስ፥____________________

የወንጌል መሠረት ወይም ዋና ኃሳብ፥____________________

የሚደገፉ ኃሳቦች፥____________________

| | |
|---|---|
| 1. የወንጌሉን መሠረት እና አጋዥ ኀሳቦች አስተዋውቅ። | • የወንጌሉን ትምህርት እና አጋዥ ኀሳቦችን በጥቁር ሠሌዳው ላይ ፃፍ። ትምህርቱን ለማስተዋወቅ ትምህርተ ምሣሌ፣ ታሪክ፣ ሥዕል፣ ወይም ኀሳብ አነሣሣሽ ጥያቄዎችን ተጠቀም። |
| 2. የትምህርቱን አካል አቀርብ<br>• ስለወንጌል መሰረት ጌታ ምን ብሏል?<br>• ዛሬ ነቢያቶችስ ስለእርሱ ምን ብለዋል? | • በንግግር ውስጥ እና የወንጌሉን ትምህርት ለማብራራት በማንኛውም ቅዱስ መጽሐፍ ላይ ጣልቃ ጥቀሶችን አመልክት እና ተወያይ።<br>• በንግግሩ ውስጥ ስላሉት ጥቀሶች ጥያቄዎችን ጠይቅ። የወንጌሉን ትምህርት በምሳሌ ለማሣየት ከንግግሩ ውስጥ ታሪኮችን ምሣሌዎችን ተርክ። |
| • በዕለታዊ ሕይወታችን ውስጥ የወንጌልን መሰረት እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንችላለን? በዚህ መሰረት መኖር እንዴት እምነታችንን ሊጨምርልን እና የጽድቅ ውሣኔዎችን እንድናደርግ ሊረዳን እንዲሁም ችግሮቻችንን ሊፈታ ይችላል? | • ወጣት ወንዶቹን የንጌሉ ትምህርት በሕይወታቸው ይተገብሩት ዘንድ የሚያግዟቸውን ጥያቄዎች እና ቀጥተኛ ውይይቶች ጠይቅ።<br>• ስለምተወያየው ርዕስ ልምዶችን፣ ስሜቶችን፣ እና ምስክርነቶችን ያካፍሉ ዘንድ የቡድን አባላትን ጋብዝ። |
| 3. እስካሁን በትምህርት ላይ የቀየውን መሰረት ሐሳብ አጠር አጠር አድርገህ በመግለፅ አጠቃል። | • ስለምታስተምረው የወንጌል ትምህርት የእውነት ሙላት እና በሕይወትህ ውስጥ ስላለው ዋጋ መስክር። |

## ማስታወሻዎች

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን

የኢየሱስ ክርስቶስ

ቤተክርስቲያን

AMHARIC

4 02348 20506 0

34820 506